www.abyssinialaw.com

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



## ቅፅ19

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

www.abyssinialaw.com

# የፌደራል ጠቅላይ

# ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

**ቅጽ-19**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ነሃሴ 19, 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

www.abyssinialaw.com



<u>**የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት**</u>

በተሻሻለው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሠበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ መደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሠበር ችሎቱ የሰጠውን የህግ ትርጉም ተከትለው በመስራት ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ለማስቻል ነው፡፡

በሀገሪቱ ያሉ ፍርድ ቤቶች ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ ውሳኔዎችን መስጠት መቻላቸው የዳኝነት አገልግሎቱ ተገማች እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ ባለጉዳዮችን ካልተገባ ወጭና ከእንግልት ሊያድናቸው እንደሚችልም ይታመናል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ በተቻለ መጠን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በአግባቡ ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለተለያዩ አካላት እንዲሁም ለህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በጥራዝ መልኩ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚካሄዱ የህግ ተመራማሪዎች፤ ለህግ ባለሙያዎች ለጠበቆች፣ ለምሁራንና በጠቅላላው ለህብረተሰቡ ውሳኔዎችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑም ስለ ታመነበት ጭምር ነው፡፡

**ዳኜ መላኩ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት**

www.abyssinialaw.com

www.abyssinialaw.com

## የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 19/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አሠሪና ሠራተኛ 1** | | | | | |
| 1. | አንድ ሠራተኛ ከአንድ ዓመት በታች አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ተመጣጣኝ የሆነ የረፍት ጊዜ በአገልግሎት ጊዜው ልክ (proportion to the length of his service) የሚሰጠው ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 77(6) | 112583 | የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጅማ ቅርንጫፍ እና አቶ ብሩክ አበራ | ጥቅምት 5 ቀን 2008ዓ.ም | 2 |
| 2. | በውጭ ሃገር ስለሚኖር የስራ ውል የግል አገልግሎት(በውጭ ሃገር ለተሰጠው አገልግሎት) ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ህግ ስለስራና ሰራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ 632/2001 ስለመሆኑ<br>በዚህ አይነት የውል ግንኙነት ውስጥ የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ በአስር አመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 1677(1) እና 1845 | 101675 | ወ/ሮ መስከረም ሞጋ እና ወ/ሮ ትግስት አረጋ | ጥቅምት 24 ቀን 2008ዓ.ም | 6 |
| 3. | አንድ ሠራተኛ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ መታሰሩ እና ከስራ ገበታው መቅረቱ ከ30 ቀናት የሚበልጥ እስራት እንደተወሰነበት ተቆጥሮ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ ተገቢ ስላለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/በ/ | 114669 | የኢትዮጲያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን እና አቶ አስማረ ፈጠነ | ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 12 |
| 4. | አሠሪው ሠራተኛው በሚፈጽመው የሥራ ጥፋት ማስጠንቀቂያ በሰጠው ጊዜ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚችለው በ30 ቀናት ውስጥ | 118263 | ወ/ሮ ሙሪዳ ኑረዲን እና | ጥር 18 ቀን 2008 ዓ.ም | 16 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሲሆን ይህ ቀን ካለፈ በኂላ የሚያደርገው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ማቋረጥ የሥራ ውል የሚቋረጥባቸውን ሕጋዊ ሥርዓቶች ያላገናዘበ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(3)<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሀ/3/፣43/2/ | | አቡል ኬስ ሀ/የተ/የግ/ማህበር | | |
| 5. | አንድ ሠራተኛ ከስራ ከተሰናበተ በኂላ የአገልግሎት ክፍያ ከሚያገኝባቸው ሕጋዊ ምክንያቶች አንዱ በድርጅቱ ከ5 ዓመት በላይ አገልግሎ በገዛ ፈቃዱ ስራ መልቀቁ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ | 112956 | ሙስጠፋ ኑር ትዕም<br>እና<br>የኦሮሚያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኢንተርኘራይዝ | ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ.ም | 21 |
| 6. | ውዝፍ ያልተከፈለ ደሞዝ ከስራ ስለተሰናበተ ሠራተኛ የሚከፈል ሳይሆን ወደ ስራ እንዲመለስ ለተወሰነበት ሰራተኛ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43(5) | 116002 | የአንቦ ገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩኒየን<br>እና<br>አቶ ጨመዳ መገርሳ | ህዳር 6 ቀን 2008ዓ.ም | 25 |
| 7. | አንድ ሠራተኛ የሥራ መሪ ሆኖ የሚቆጠረው እንደ ድርጊቱ የሥራ ፀባይ ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንጻር መታየት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 3/2/ሐ/ | 117076 | የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ እና<br>አቶ ዮሐንስ ብዙነህ | ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም | 29 |
| 8. | አሰሪው በሰራተኛው ህይወት ላይ አደጋ ሊያደርስ በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ህገ ወጥ ተግባር ሲሆን ይህም ሰራተኛው የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለመቋረጥ በቂ ምክንያት ነው ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ ሠራተኛው በአዋጅ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን የማግኘት መብት ያለው | 117517 | ሬድ ፎክስ ኢትዮ.ኃ/የተ/የግ/ማህ<br>እና<br>ወ/ት ጻለኔ ጌታቸው | ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም | 34 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 14 (1) (ሠ)፣32(1)(ለ) | | | | |
| 9. | የአንድ ድርጅት ከሌላ ጋር መቀላቀል ወይም መከፋፈል ወይም የባለቤትነት መብት ወደ ሌላ መተላለፍ የስራ ውልን የማቋረጥ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/1996 አንቀፅ 23(2) | 119734 | ይርጋ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህ<br>እና<br>እነ አቶ በዛብህ መኮንን (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም | 38 |
| **የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት**<br>**41** | | | | | |
| 10. | በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን ወገን የሚጎዳ ውሳኔ የተላለፈው ጉዳዩን በተዋረድ ባየው የሰበር ችሎት በሚሆንበት ጊዜ ይህ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነው ወገን አለኝ የሚለውን መብት ለማስከበር ይችል ዘንድ መብቴን ተጋፍቷል በሚለው ሰው ላይ በስሙ ቀጥታ ክስ በመመስረት መብቱን ከማስከበር ውጪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት ተቃውሞውን ለሰበር ችሎቱ ሊያቀርብ የሚችል ስላለመሆኑ | 102056 | አቶ ሳምሶን ካሳዬ<br>እና<br>ወ/ሮ መሰረት ግርማ (አራት ሰዎች) | ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም | 42 |
| 11. | አንድ ተከሳሽ በከሳሽ በመጀመሪያ ክስ ሲቀርብበት መጥሪያ ደርሶት በተከራከረበት እና ከሳሽ ክስ ያሻሽል ተብሎ በተዘጋ መዝገብ ላይ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ከተከፈተ በኂላ ለተከሳሽ በተገቢው መንገድ መጥሪያ ሳይደርስ የሚሰጥ ውሳኔ ስነ- ስርዓታዊ ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 94-110 | 107838 | እነ አቶ ታከለ አርአያ<br>እና<br>አቶ ደጀን ገ/እግዚአብሔር | ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም | 46 |
| 12. | በክስ ማሻሻል ሥርዓትና ዓላማ ቀድሞ ዳኝነት ከተጠየቀበት ጉዳይ ፈጽሞ የተለየ ጥያቄ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 | 100475 | አቶ ሳምሶን አበራ<br>እና<br>ወ/ሮ ፀሐይ አበራ | ታህሳስ 20 ቀን 2008 ዓ.ም | 50 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 342 | | | | |
| 13. | ፍ/ቤቱ የግዛት ስልጣን የለውም በማለት ለሚቀርብለት መቃወሚያ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ሥ/ሥ/ቁ. 10(2) | 109383 | ሳሊሆም ከፍተኛ ክሊኒክ<br>እና<br>ዶ/ር ዘመኑ ዮኃንስ | የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም | 54 |
| 14. | ተከሳሽ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ በእምነቱ መሰረት ይገባኛል የሚለው ማናቸውም ዳኝነት እንዲሰጠው አመልካች(ከሳሽ) ሊጠይቅ የሚችል ስለመሆኑ | 109206 | አቶ ፍስሃ እርቅ<br>እና<br>አቶ ኪሮስ ስዩም | የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም | 59 |
| 15. | ፍ/ቤት በተዋዋዮች መሃል የተደረገን ውል (የእርቅ ስምምነት) ህጋዊነታቸውን ሳይረጋገጥ ሊያፀድቅበት የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ.1731<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.277 | 109497 | አቶ አግማስ ኡመር (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ኡመር አሳዮ | የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም | 63 |
| 16. | ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ለሚደርሰው ኪሳራ ዋስ እንዲያሲዝ የሚጠየቀው ከሳሽ በክሱ ምክንያት በተከሳሽ ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመክፈል የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚያጠራጥር ሲሆንና ኪሳራውንም ለመክፈል የሚያስችል ሃብት ወይም ገንዘብ የሌለው በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 200 | 110150 | አቶ ገ/መድህን ወ/ሚካኤል<br>እና<br>እነ አቶ ግርማይ ፍትዊ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም | 66 |
| 17. | ከሳሽና ተከሳሽ ያልተካካዱበትና ከሳሽ በክሱ ገልፆ ተከሳሽ ባመነው ነጥብ ላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ማስረጃ በመመዘን ሳይሆን ተከሳሹ በሰጠው የእምነት ቃል ወይም መልስ መሰረት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 | 112927 | የማር ዘነብ እቁብ ዳኛ<br>እና<br>እነ አቶ ዋለልኝ ተመስገን | የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም | 70 |
| 18. | የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለሚሉ ስለሚገባቸው ጥብቅ | 104028 | ወ/ሮ ብዙአየሁ ያለው | የካቲት 17 ቀን | 74 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መስፈርቶች;-<br>አንድ ክስ በይርጋ መዘጋቱ ዳግም ዳኝነት ጥያቄውን ለማስተናገድ እንደበቂ ምክንያት/እንደመመዘኛ/ የማይወሰድ ስለመሆኑ:-<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 | | እና<br>አቶ ሲሳይ ካሴ | 2008ዓ.ም | |
| 19. | በጊዜያዊ ትእዛዝ ላይ በሚሰጥ ብይን ቅር የተሰኘ አካል የስረ ነገሩ ክርክር የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ እስካልተገኘ ድረስ ይግባኝ (የሰበር) አቤቱታ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320(3) | 116209 | የኢ.ት/መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ ምፅላል አብርሃ | የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ.ም | 79 |
| **ቤተሰብ**<br>82 | | | | | |
| 20. | በገጠር መሬት ላይ የሚኖረው መብት የመጠቀም መብት ሲሆን ይህንን መብት ለ3ኛ ወገን /ለሌላ/ ሰው ለረጅም ጊዜ ሰጥቶ ተጠቃሚነቱ የተቋረጠበት ባለመብት መልሶ መጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የኦሮሚያ ክልለ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1997 አንቀፅ 9(5) | 113973 | ወ/ሮ ጠጅቱ ኩርጋ<br>እና<br>አቶ ገመዳ ሆባ | ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም | 83 |
| 21. | አንድ ጋብቻ ሲፈርስ ንብረት ክፍፍልን በሚመለከት በእርቅ ውል ስምምነት በሽማግሌ የተደረገው እርቅ በፍ/ቤት ተመዝግቦ ከተዘጋ በኋላ እንደገና እንደ ባልና ሚስት አብረን እየኖርን ስለነበር በድጋሚ የንብረት ክፍፍል ይደረግ የሚል ጥያቄ አግባብነት ያለው ስላለመሆኑ፣ | 105054 | ወ/ሮ ጌጤ እጅጉ<br>እና<br>አቶ ብርሃኑ ተሠማ | ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም | 87 |
| 22. | ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ሊባልባቸው ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎች<br>ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ ከሚታሰብበት ጊዜ አንስቶ<br>በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ካልቀረበ በይርጋ | 102662 | ወ/ሮ አልማዝ ለሼ<br>እና<br>አቶ በቀለ በላቸው | የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም | 90 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚታገድ ስለመሆኑ | | | | |
| 23. | አንድ ሰው በወላጅ አባቴ ስም መጠራቴ ቀርቶ በአሳዳጊዬ ስም እንድጠራ ብሎ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በሕጉ ስለስም ለውጥ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች የማያሟላ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ.32(1)፣36(1) | 116977 | ወ/ት ሃና ታምራት<br>እና<br>የለም | የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 94 |
| 24. | በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የቤተሰብ ህግ መሰረት ባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸውን እኩል የማስተዳደር መብት ያላቸውና የጋራ ስምምነት ሳይኖር ንብረትን ለሌላ 3ኛ ወገን በአንደኛው ተጋቢ ፍቃድ ብቻ የተላለፈ ከሆነና ይህንን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በህጉ በተፈቀደለት ጊዜ ገደብ ውስጥ የይፍረስልኝ ጥያቄውን ካላቀረበ የተፈፀመው ተግባር እንደፀና የሚቆይ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.213/92 አንቀፅ 68፣69 | 103721 | ወ/ሮ ሰሚራ ጀማል<br>እና<br>እነ አቶ ጀማል እንድሪስ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 29 ቀን 2008 ዓ.ም | 97 |
| **ውርስ** | | | | | |
| 25. | ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ፈጽሞ ሲገኝ ሊወሰዱ ስለሚገቡ ዝርዝር ሁኔታዎች<br>የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች፤ ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.213/1992 አንቀጽ 306፣277 የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2207/1 | 103151 | አቶ ግርማ ብሩ<br>እና<br>አቶ መርዕድ ብስራት | መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 108 |
| 26. | የወራሾች ድርሻ በክፍያ ጊዜ ሊገመትበት ስለሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083 | 103049 | ወ/ሮ ሊዕማ ሓዲሽ<br>እና<br>አቶ አንዋር ሓዲሽ | መስከረም 28 ቀን2008 ዓ/ም | 114 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 27. | እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው ወራሾች ወይም ባለገንዘቦች ይህ ሰው የፈጸመው ውል ጉድለት የሌለበት ፈቃድ አልሰጠበትምና ውሉ ሊፈርስ ይገባል ሲሉ እብደቱን ምክንያት በማድረግ የውሉን መፍረስ መጠየቅ የማይችሉ ስለመሆኑ፡-<br>የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውልን ዋጋ ተጎዳሁ በሚል ምክንያት ሊፈርስ የማይችል ስለመሆኑ፡-<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁ. 348፣347/1//2/፣349፣350፣341፣342<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2887 | 100931 | አቶ ጥላሁን አለሙ<br>እና<br>አቶ ደረጀ ማሞ | ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም | 117 |
| 28. | የሟች ወራሾች ተመላሽ የሚያደርጉት ንብረት ስለሚመለስበት ሥርዓት<br>የፍ/ሕ/ቁ. 1074 እና 1076 | 106856 | ወ/ሮ እየሩሳሌም ገመቹ<br>እና<br>ወ/ሮ ሮማን ገመቹ | ጥር 16 ቀን 2008ዓ.ም | 125 |
| 29. | የሟች ንብረት (የውርስ ሃብት) ወደ ወራሾች የሚተላለፈው በመጀመሪያ የሟች እዳ ከተከፈለ ብቻ ስለመሆኑ፤-<br>ሟች ከሞተ በኂላ ለቀብር ማስፈፀሚያ የሚወጡ ወጪዎች ከውርሱ ክፍፍል በፊት መከፈል ያለባቸው ስለመሆኑ፡-<br>የፍ/ሕ/ቁ.1014 | 111216 | ወ/ሮ ኤልሳቤት አህመድ<br>እና<br>ወ/ሮ ማፈኛ አባዬ | የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም | 130 |
| 30. | ተተኪ ወራሽ ለመሆን ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች<br>የፍ/ሕ/ቁ. 842(3) | 110040 | እነ ወ/ሮ እሴተማርያም አክሎግ (ሦስት ሰዎች)<br>እና<br>የለም | የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 133 |
| ውል<br>136 | | | | | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 31. | የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ የካሳ ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩ በየትኛው የህግ ማዕቀፍ እንደሚገዛ መለየት የይርጋውንም ሆነ የካሳ ስሌቱን በአግባቡ ለመዳኘት የሚያስችል ስለመሆኑ<br><br>የን/ሕ/ቁጥር 587፣595 ፣597፣599 እና 603<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143፣ 2090 | 95922 | እነ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ሃምሳ አለቃ ለገሰ ክፍለይ(ሁለት ሰዎች) | መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ/ም | 137 |
| 32. | ተወካይ የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ከሶስተኛ ወገን ጋር የሚያደርገው ውል ከወካይ ጋር የጥቅም ግጭት ተፈጠሯል ብሎ ወካይ ካወቀ ይህንን ለመቃወም /ለመስፈረስ/የሚችለው ወካይ ይህንን ሁኔታ መፈጠሩን ካወቀበት እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ድረስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 2187(1)(2) | 98961 | አቶ ኡመር መሃመድ<br>እና<br>ሻ/ባሻ ከድር ሼህ አብድላሂ | መስከረም 24 ቀን 2008ዓ.ም | 144 |
| 33. | አንድ የዋስትና ውል ዋሱ ግዴታ የገባበትን ኃላፊነት መጠን ወይም ልኩ ምንያህል እንደሆነ በዋስትና ውሉ ላይ በገንዘብ ካልተገለፀ በስተቀር ዋስትናው ፈራሽ ስለመሆኑ<br>ከፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) | 104061 | አቶ ፍቅሬ ግርማ<br>እና<br>አቶ ደስታ ጫምሶ | መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 148 |
| 34. | የአንድን የውል ሰነድ እርግጠኛ ቀን የሚባለው ሰነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው እንደ ሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ፅ/ቤትን የመሰለ የመንግስት መስሪያ ቤት ሲሆን የፃፈበት ወይም የተቀበለበት ቀን ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ.2015(ሀ) | 98583 | እነ ወ/ሮ ኤደን ሲሳይ(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ሰይፉ አለሙ | መስከረም 27ቀን 2008ዓ.ም | 151 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 35. | የተዋዋዮች የውል ግንኙነት መሰረት ያደረገው ፕርፎርማን ሳይሆን ፕሮፎርማን ተከትሎ በፅሑፍ የተደረገን ውል በሆነ ጊዜ በፕሮፎርማው ላይ ተጠቅሶ ነገር ግን ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል አድርገው ያልተሰማሙበት ጉዳይ በፕሮፎርማ ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ ብቻ እንደውሉ አካል ተቆጥሮ በተዋዋዮቹ (ከተዋዋዮቹ) በአንዱ ላይ አስገዳጅነት እንዳለው አድርጎ መውሰድ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2287-2300 ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በተሸጠው እቃ ላይ የተገኘው ጉድለት መኖሩ በገዥው የታወቀው ከርክክቡ በኋላ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ | 99667 | ቻኩ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን | መስከረም 27 ቀን 2008ዓ.ም | 155 |
| 36. | አንድ የሽያጭ ውል የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ነው ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ<br><br>የፍ/ብ/ሕ/ አንቀጽ 2278(1) | 97797 | ናሽናል ስሚንቶ አ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ብርሃኑ ግደይ | መስከረም 28 ቀን 2008 ዓ/ም | 162 |
| 37. | አንድ ውልን ለመተረጎም አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የውሉ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት በውሉ አስገዳጅ የሆነው ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ ሳይሆን በውሉ ተገዳጅ ለሆነው ሰው ምቹ በሚሆንበት አኳኋን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738(1) | 103910 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ<br>እና<br>አቶ ሀብታሙ ተመስገን | መስከረም 28ቀን 2008 ዓ/ም | 165 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 38. | የኮንዶሚኒየም ቤት የደረሰው ሰው ሌላ የኮንዶሚኒየም ቤት ከደረሰው ሰው ጋር እጣው ከደረሰው አምስት ዓመት ባይሞላውም በልውውጥ(በስምምነት ሊቀያየሩ የሚችሉ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀፅ 14(2) | 105919 | ወ/ሮ መኪያ አብደላ<br>እና<br>አቶ ጣሰው ሽምሱ | ጥቅምት 4 ቀን 2008 ዓ.ም | 169 |
| 39. | ለመልካም ሥራ አፈጻጸም ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ ውሉ እንደውሉ ሳይፈጸም ሲቀር ዋስትና አስያዡ የተያዘውን ገንዘብ በውል ለተጎዳው ወገን መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ<br>ለመልካም ስራ አፈፃፀም የሚሰጥ ዋስትና ዓይነተኛ ዓላማው በተሰራው ነገር ጉዳት የደረሰበት ተዋዋይ ወገን በገንዘቡ ረገድ ለመካስ ስለመሆኑ<br>ፍ/ሕ/ቁ. 1815 | 98348 | እነ አቶ ዘርይሁን የኔነህ /አመስት ሰዎች/<br>እና<br>ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ | ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም | 173 |
| 40. | በአከራይና ተከራይ መካከል በሚደረግ የኪራይ ስምምነት መሠረት አከራዩ ለተከራዩ ባከራየው ቤት ላይ ስለተደረገው ጥገና /ማሻሻያ/ አከራይ የሰጠው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አከራዩ ለተከራዩ አወጣሁ ያለውን ወጪ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6/3/<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ አንቀጽ 2917፣2973/1/፣2912 | 101053 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እነ<br>አቶ የምሩ ነጋ | ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም | 180 |
| 41. | የዋስትና ውል በግልፅ መደረግና ዋሱ ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘብ ልክ በዋስትናው ውል መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ ለዋስትናው መሠረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊና ግራ ቀኙን የተስማሙበትና የሚታወቅ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፡-<br>ፍ/ሕ/ቁ 1928፣1922<br>አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ | 111778 | ወ/ት ገንዘብ ስጦታ<br>እና<br>የሲ.ያ ቆቦ ወረዳ ፍ/ቤት ዐ/ህግ | ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም | 186 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 42. | በጽሑፍ የተደረገ ውል ውስጥ እማኞች በመሆን የፈረሙ ምስክሮች ስለ ውሉ መኖር አለመኖር እንዳያስረዱ ክልከላ ማድረግ ተገቢ ስላለመሆኑ<br><br>የፍ/ሕ/ቁ.2005 | 106535 | አቶ ረዲ ተፈራ<br>እና<br>እነ አቶ ረዲ ተፈራ/ሁለት ሰዎች/ | ጥር 17ቀን 2008 ዓ/ም | 191 |
| 43. | አንድን ንብረት የሸጠ ሰው የሸጠውን ንብረት ባለሃብትነት ለገዥው የማዛወር ግዴታ ያለበትና ይህንን ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራቶችን የማከናወን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ሕ/ቁ.2273፣2281፣1771(1)፣1757 | 112328 | ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ<br>እና<br>አቶ ኤፍሬም እሸቱ | የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም | 195 |
| 44. | ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው በባለእዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የሚያስችል ክስተት ሲፈጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 1792<br>በየብስ የእቃ ማጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁ. 547/1999 | 112168 | የሺ ትራንስፖርት የጭነት ማመላለሻ ባለንብረቶች ማህበር<br>እና<br>አቶ አስክንድር ዘርፉ | የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 200 |
| 45. | በማጓጓዝ ውል ግንኙነት በደረሰ የሕይወት ሕልፈት የሚከፈል ካሣ በንግድ ህጉ መሰረት ስለመሆኑ | 99447 | አቶ ተፈራ ጣሰው<br>እና<br>ወ/ሮ ፋንታዬ በንቲ | ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም | 206 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 46. | ተዋዋዮች የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ሲተላለፍ በህጉ በተደነገገው መሰረት ውል ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርቦ የማስመዝገብ ግዴታን ስምምነታቸው ላይ ካካተቱና ነገር ግን ይህንን ተፈፃሚ ማድረግ ካልተቻለ የተዘጋጀው ስምምነት ረቂቅ እንጂ ከጅምሩ ውል ነው ተብሎ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚገባቸውን ጉዳዮች ማንሳት ሰህተት ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ.1723፣1810፣1885(1) | 99124 | ወ/ሮ ሰብለ ማሞ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የ ׀ አለቃ ተስፋዮ በዛብህ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 28 ቀን 2008ዓ.ም | 211 |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት**<br>215 | | | | | |
| 47. | አንድ ሰው በህግ ወይም የሚፀና ውል የሚሰጠው አንዳች መብት እንደሌለ እያወቀ የሌላ ሰው የሆነን ንብረት በእጁ ባደረገ ጊዜ ንብረቱ ሊያፈራ የሚችለውን የገንዘብ ግምት እንዲመልስ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2178 | 100651 | ወ/ሮ መንበረ ሰፈርህ<br>እና<br>ወ/ሮ ብርሃኔ ጌቱ (ሦስት ሰዎች) | መስከረም ቀን 2008 ዓ/ም | 216 |
| 48. | በወሊድ ወቅት በህክምና ተቋሙና በሙያው ባለቤት ዘርፉ የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ሳይደረግ በሚወለደው ህፃን ላይ የአካል ጉዳት ከደረሰ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1790፣2028፣2031፣2647 /2/ እና 2651 | 96548 | ሐያት ሆስፒታል<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን | መስከረም 24 ቀን2008 ዓ.ም. | 220 |
| 49. | በውል የተገባ አንድ ግዴታ መፈጸም ያለመፈጸሙን ለማጣራት የግራ ቀኙ ተዋዋይ ወገኖች የገቡት ግዴታ እና ያላቸው መብት የሚገልጽ የሰነድና የሰው ማስረጃ እንዲሁም የግዴታ ልዩ ባህርይ መሰረት በማድረግ ልምድን መዳሰስ የሚጠይቅ ስለመሆኑ<br>ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ 246፣247፣248 እና 249 | 96041 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>ወ/ሮ አልማዝ ግዛው | ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም | 231 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 50. | የካሳን መጠን በርትዕ ለመወሰን የሚያስገድድ ሁኔታ በገጠመ ጊዜ መጠኑን ለመወሰን የጉዳት ካሳው መጠን ከጉዳቱ ተመጣጣኝ ይሆን ዘንድ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ የሚገባቸው መለኪያዎች ሊኖሩ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ሕ/ቁ.2102 እና 2153 | 108251 | የኢትዮጵያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን<br>እነ<br>አቶ አመከክ ከሊፋ | ጥር 5 ቀን 2008 ዓ.ም | 235 |
| **ወንጀል** | | | | | |
| 51. | በወ/መ/ህ//አ/ቁ. 676(1) የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው የዋስትና መሰጠት (መፈቀድ) ጥያቄ የሚሰጠው በጉዳዩ ላይ በአግባቡ ተመርምሮ እንጂ ከወዲሁ ስላለመሆኑ<br>አዲሱ የፀረ ሙስና ህግ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀፅ 31 | 117383 | አቶ አዲስ ዋለልኝ በላይ<br>እና<br>የፌ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ህግ | መስከረም 6 ቀን 2008ዓ.ም | 240 |
| 52. | በወንጀለኛ ህግ ቁጥር 627(2) መሰረት በክብረ ንህፅና ላይ የሚደረግ ድፍረት የተበዳይ ክብረ ንፅህና በጥቃቱ መገርሰስ ወይም አለመገርሰስ እንደ መስፈርት ሊቆጠር የሚገባው ስላለመሆኑ | 107166 | መኳንንት ግርማ<br>እና<br>የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ | ጥቅምት 4 ቀን 2008 ዓ.ም | 244 |
| 53. | አቃቤ ህግ በዋስትና መለቀቅ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>ፍርድ ቤት የዋስትና መብትን የሚከለከልበቻው ምክንያቶች ከተለየዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዝናቸው የሚገባቸው ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር67፣75 | 112725 | አቶ ሀሰን አብዳል<br>እና<br>የፌዴራል ማዕከል ዐቃቤ ህግ | ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ/ም | 246 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 54. | የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃ የአስረጅነት ብቃት ያለው ተአማኒነት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንዲወሰድ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ ስለሚገባቸው ነገሮች | 109441 | ፈይሳ ማም ማሩ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ጥር 17 ቀን 2008 ዓ/ም | 250 |
| 55. | በወንጀል ጉዳይ ከአንድ በላይ ሰዎች የተከሰሱ እንደሆነ የእያንዳንዱ ተከሳሽ ሚና እና ተሳትፎ ደረጃው በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በከሳሽ ወገን በኩል በሚቀርበው ማስረጃ ነጥሮ ሊወጣ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 32፣40<br>የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141<br><br>ተያያዥነት የሌላቸው ፍሬ ነገሮችን መሰረት ተደርጎና የአንድን ነገር መኖር ያለመኖር ሣይረጋገጥ ለአካባቢ ማስረጃ ክብደት መስጠት የማስረጃው አይነት የምዘና መርህን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.173(1) | 113464 | እነ እናት ሁናቸው(አራት ሰዎች)<br>እና<br>የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዓቃቤ ህግ | ህዳር 22 ቀን 2008 ዓ.ም | 258 |
| 56. | በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188/5/ መሰረት አንድ ፍርድ በተከሳሽ ላይ ከተሰጠ ተከሳሹ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብሎ ሲቀርብ የበታች ፍርድ ቤትን ውሳኔ የበላይ ፍርድ ቤቱ ማገድ የሚችልበትን አግባብ የሚያሳይ ድንጋጌ ከመሆኑ ውጪ ከሳሽ ወገን በተከሳሽ ነፃ መለቀቅ ላይ ይግባኝ ብሎ ሲሄድ ፍርዱ እንዳይፈፀም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመስጠት መነሻ የሚያደርገው ስላለመሆኑ | 118252 | ሀብታሙ አያሌው<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ጥር 24 ቀን 2008 ዓ/ም | 268 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 57. | በወንጀል ክርክር ሂደት ፍ/ቤት በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሂደቶች ውስጥ ሊኖረው(ሊያደርገው) ስለሚችለው ሚና<br><br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136(4)፣137፣138፣143(1)፣145፣194 | 111498 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ ሃብታሙ ካርሎ | የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 275 |
| 58. | በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ጠበቃ ብቻውን ሊቀርብ አይችልም የሚለው ጉዳይ ተፈፃሚ የሚሆነው ለተፈጥሮ ሰዎች እንጂ የህግ ሰውነት ላላቸው ሰዎች ስላለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.127 | 120762 | የፌድራል ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>እነ አቶ ዱባይ አውቶ ጋለሪ(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 279 |
| 59. | ህጉ በሚጠይቀው አግባብ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጸና ፈቃድ ሳይኖረው ከቴሌኮሚኒኬሽን እውቅናና ፈቃድ ወጭ ሶፍትዌሮችን በመገልገል በኢንተርኔት ስልኮች ማስደወል ሊያስከትለው ስለሚችለው ኃላፊነት<br>የቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 | 103940 | ወ/ሮ አመለወርቅ ጌታነህ<br>እና<br>የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | ጥር 24 ቀን 2008 ዓ/ም | 285 |
| 60. | አንድ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ከኃላፊዎች አንዱ ወይም ከሠራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም አነሳሽነት ወይም አባሪነት ወንጀል ሲፈጸም ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ሕግ አንቀጽ 23 እና አንቀጽ 34/1/<br>ጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 93/1ሀ/ እና 93/2/ | 94913 | የኢ/ገ/ጉ/ባ/ቅ /ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ጀሳቢን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>/ሁለት ሰዎች/ | ህዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 290 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 61. | አንድ ሰው በሀሰት የተዘጋጀን ወይም የተለወጠን ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት ካልሆነ በቀር የወንጀል ኃላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ፣<br><br>የወ/ሕ/ቁ 378 | 101618 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ፀረ ሙስና ኮሚሽን<br>እነ<br>መስከረም ፋንታዬ | ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም | 295 |
| **ጉምሩክ /ታክስ** | | | | | |
| 62. | የቲ.ኦቲ /ተርን ኦቨር ታክስ/ ተመዝጋቢ የሆነ ሰው በህግ ፊት እንደ መረጃ /ማስረጃ / ሊያቀርብባቸው የሚገቡ ደረሰኞች ከቫት በተቀበለው የቲ.ኦ.ቲ ደረሰኝ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>/ታክስ የቲ.ኦቲ አዋጅ ቁጥር 285/194 አንቀጽ 21/ | 95941 | ሔስትራብል ሀ/የተ/የግ/ማህበር እና<br>እነ የኢ.ት/ገ/ጉ/ባለስልጣን | ታህሳስ 7 ቀን 2008 ዓ.ም | 300 |
| 63. | በተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ መሰረት የጉምሩክ ቁጥጥርን አሰናክለሃል ተብሎ ሊጠየቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ መፈፀሙን አቃቢ ህግ በበቂ ሁኔታ ሲያስረዳ ስለመሆኑ<br>የጉሙሩክ አዋጅ ቁ. 859/2006 አንቀፅ 166 | 114043 | የኢ.ት.ገ/ጉ/ባለስልጣን ዓ.ህግ<br>እና<br>አብዲ ሞገስ | የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም | 304 |
| 64. | በቀድሞ ህግ እንደ ወንጀል የሚቆጠር ድርጊት በአዲሱ ህግ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ቀሪ ከሆነ ጉዳዩ በወንጀል የሚታይበት አግባብ ስላለመኖሩ በአዲሱ የገቢ.ዎችና ጉምሩክ አዋጅ መሰረት ከቀረጥ በነፃ በገባ እቃ አላግባብ መገልገል የወንጀል ተጠያቂነት ሳይሆን አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ብቻ የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ..ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 5(3)<br>አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀፅ 98(1)(ሀ)(ለ)<br>የጉሙሩክ አዋጅ ቁ.859/2006 አንቀፅ 163(1)(ሀ)(ለ) | 111086 | የኢ.ትዮ.ገቢ.ዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>አሚኮ/ሸማቾች የህ/ስራ ማህበር | የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 308 |
| 65. | ማንኛውም እቃ ወይም መጓጓዣ ሊወረስ በሚችል ወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ተጨማሪ ትእዛዝ መስጠት ሳያስፈልግ እቃው ወይም መጓጓዣው እንዲወረስ የሚደረግ ስለመሆኑ | 117065 | የኢ.ት/ገ/ጉ/ባለስልጣን ዓ.ህግ እና<br>አቶ ሚፍታህ ከማል | የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም | 311 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀፅ 104(1) | | | | |
| **አእምሮዊ ንብረት**<br>315 | | | | | |
| 66. | በቅጂና ተዛማጅ መብቶች መጣስ /ለሚደርስ ለጉዳት ካሳ/ ወይም የሞራል ካሳ ዋጋው በተዋዋዮች ወገን ካልተቆረጠ የወቅቱን ዋጋ አጣርቶ መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የሞራል ካሳ አከፋፈል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ ውጪ መወሰን የሌለበት ስለመሆኑ<br>የቅጂና ተዛማጅ መብቶች አዋጅ ቁ 410/96 አንቀጽ 7፣8፣37<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2102 | 99082 | ወ/ሮ ፍሬሕይወት ደመቀ<br>እና<br>ቤሩት ዳዊት | ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም | 316 |
| **የዳኝነት ሥልጣን**<br>324 | | | | | |
| 67. | የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች አስቀድመው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በቀረበ አቤቱታ ላይ ባሳለፉት ውሳኔ የሚነሳን ተቃውሞ አቤቱታ ተቀብለው ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ/361/1995 አንቀጽ41/ሸ/ አዋጅ 408/96 አንቀጽ 2/ንኡስ ቁ፣1 | 105211 | እነ አቶ እንዳለ ደንቦባ (አራት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አልማዝ ደንቦባ<br>(አራት ሰዎች) | ጥቅምት 1 ቀን 2008ዓ.ም | 325 |
| 68. | ካሳ አነሰኝ ወይም ተከለከልሁ ካልሆነ በቀር በኢንቨስትመንት የሚቀርቡ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ይግባኞች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 138 አንቀጽ 6/5/ | 92991 | አቶ ተፈራ ተሰማ<br>እና<br>የአርሲ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት | ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም | 329 |
| 69. | ከመንግስት ገቺና አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ስልጣኑ የማየት መብት ያለው የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ እንጂ የመደበኛ ፍ/ቤት ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 75(1) | 107805 | ጄዳው አርክቴክቶችና መሃንዲሶች<br>እና<br>የፌድራል ስፖርት | ጥቅምት 04 ቀን 2008ዓ.ም | 332 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው መመሪያ አንቀፅ 49(1) | | ኮሚሽን | | |
| 70. | በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ጋር የሚመሰረቱት የሥራ ግንኙነት ስምምነት ያለ እንደሆነ ጉዳዩ የሚዳኘው በዓለም አቀፍ ስምምነቱ መሠረት ስለመሆኑ፡- | 117390 | አቶ አለማየሁ መኮንን እና የምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት | ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም | 337 |
| 71. | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በምትክ ቦታ ይሰጠኝ ጥያቄ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ የሠበር አቤቱታ ለከተማው ፍ/ቤት ሳይቀርብ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የከተማው ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43(5)፣ አንቀጽ 42(2)<br>አንቀጽ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(6) | 104858 | አቶ ታደሰ ካሣ እና ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር/ሁለት ሰዎች/ | ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም | 340 |
| 72. | አዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የጉዲፈቻ ስምምነትን ማስረጃን ተመልክቶ የወራሽነት ማስረጃን የመስጠት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/1995 አንቀፅ 41(ሸ) | 112575 | አቶ አፈወርቅ መኩሪያ እና ወ/ሮ ማደሊና ፍራንሲኔት | የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም | 343 |
| **ንብረት** | | | | | |
| 73. | በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ይዞታን የመጠቀም መብት የሚተላለፈው በውርስ ሕግ መሰረት በይዞታው የመጠቀም መብት ላለው የቤተሰብ አባል ሲሆን በዚሁ አግባብ ቅድሚያ የውርስ መብት የሚሰጠው ከመሬቱ በሚያገኙት ገቢ ለሚተዳደሩ(ሌላ መተዳደሪያ)ገቢ ለሌላቸው ወራሾች ሥለመሆኑ<br>የኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 130/1999 አንቀፅ 9(1)(2)<br>አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 10(1) | 108335 | እነ አቶ አለሙ ስሜ(ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ብዙነሽ ስሜ (ስድስት ሰዎች) | የካቲት 4 ቀን 2008ዓ.ም | 347 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 74. | በትግራይ ክልል ገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ባለይዞታ አርሶ አደር ይዞታውን የመሸጥ መብት የሌለውና የሸው ተፈፅሞ ሲገኝ ይህ ውል እንዳይረጋ በማንኛውም ጊዜ ተቃውሞ ሊነሳና ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤትም ውሉ ከጅምሩ ህገወጥ መሆኑን አውቆ ውሉ ህጋዊና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የትግራይ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 55/1994፣<br>አዲሱ አዋጅ ቁ. 236/2006<br>የፍ/ሕ/ቁ. 1678፣1716፣1718፣1195 እና 1196 | 110549 | ወ/ሮ ደመቀች ንርኢ<br>እና<br>አቶ ጋስመ ረብሶ | የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም | 352 |
| 75. | አንድ አርሶ አደር የሚጠቀምበት ይዞታ (መሬት) በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው መሆኑን እስካላረጋገጠ ድረስ የመንግስትና የህዝብ መሬትን ለረዥም ዓመት ይዤዋለሁኝ ስለዚህ ይርጋ አይመለከተኝም ብሎ የሚያነሳው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 112906 | ማንአህሎህ አንተነህ<br>እና<br>የማቻካል ወረዳ አከባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ፅ/ቤት | የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም | 357 |
| **የንግድ ህግ**<br>360 | | | | | |
| 76. | በውል መሰረት ከተቋቋመ የሽርክና ማህበር ውስጥ አንድ የማህበር አባል ከማህበሩ ሊወጣበት ስለሚችልበት አግባብ<br><br>የንግድ ህግ 227 እና ተከታዮቹ | 99900 | አቶ ኃይሉ መንግስቱ<br>እና<br>አቶ ሬገን መሐመድ (ሁለት ሰዎች) | መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 361 |
| 77. | በአጓዥ ጥፋት በደረሰ አደጋ ምክንያት በተጓዥ(መንገደኛው) ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ለመወሰን ልንከተላቸው ስለሚገቡ የካሳ አከፋፈል መርሆች<br>የን/ሕ/ቁ. 599፣<br>የፍ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 | 97760 | ወ/ሮ ንግስቲ አትክልቲ<br>እና<br>አቶ አበባው ሽፈራው | ታህሳሥ 19 ቀን 2008 ዓ.ም | 365 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 78. | የህንጻ ኪራይ ውል ካለቀ በኂላ የታጣ ገቢ የኪራይ ዋጋ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣኖች በወሰኑት ታሪፍ መሠረት ወይም ታሪፍ የሌለ እንደሆነ የቦታዎች ልማድ በመከተል መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ሕ/ቁ. 2950/2/ | 105628 | ዩኒቨርሳል ሜታልስና ሚኒራልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በስፋት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 372 |
| **አፈፃፀም** 378 | | | | | |
| 79. | አንድ ፍርድ የማይፈፀምበት ምክንያት ያለመኖሩ ሲረጋገጥ ለአፈፃፀም ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርድ እንዲፈፀም ትእዛዝ መስጠት የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392(1) | 101631 | የባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ፅ/ቤት እና አቶ በየነ አሸናፊ | ጥቅምት 2 ቀን 2008ዓ.ም | 379 |
| 80. | የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርድ እንዲፈጸም ትዕዛዝ የሚሰጠው የፍርድ ባለዕዳውን ጠርቶ ከመረመረው በኃላ እንደፍርዱ የማይፈጸምበት ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ በኃላ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 207 እና 320(2) መሰረት በተሰጠው ትእዛዝ ላይ ቅሬታ አቅርቦ ነገር ግን ቅሬታው ተቀባይነት ቢያጣ የይግባኝ መብቱን (የይግባኝ ጊዜ ሊሰላበት) ስለሚችልበት አግባብ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 392 (1) | 95537 | ክራውን ቴክስታይል ዊቪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚድሮክ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ.ም. | 382 |
| 81. | በአፈጻጸም ወቅት አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ተሸጦ ከእዳ መክፈያ /ከግራ ቀኙ/ ይካፈሉ በተባለበት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ የፍ/ባለመብትን ጥቅም ላይ በቀጥታ ጉዳት እስካላደረሰ ወይም የሚያደርስ | 110681 | ወ/ሮ ሃዋ ጆሬ ተወካይ ታጆጂሆ እና አቶ አብዲ ቀንጨራ | ታህሳስ 8 ቀን 2008 ዓ.ም | 388 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያው ተገቢ ለሆነ ቀን በአየር ላይ አልዋለም ወይም በጨረታው ለሚሳተፉ ሰዎች በቂ ጊዜ አልተሰጠም የሚባልበት ሁኔታ አለመኖሩ፣<br>የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. አንቀጽ 445 | | | | |
| 82. | በፍርድ ባለመብት አማካኝነት የተፈረደን ፍርድ ለማስፈጸም የቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ ይፈጸም የተባለውን ፍርድ ብቻ መሰረት ሊያደርግ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | 103787 | የኢት/ገ/ጉ/ባለስልጣን ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት<br>እና<br>ፉአድ ደኑር ሀሰን | ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም | 392 |
| **ልዩ ልዩ**<br>396 | | | | | |
| 83. | የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሚተላለፍ ቅጣትን ለአፈፃፀሙ ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል ስላለመሆኑ<br>*የትራፊክ ፍሰትን ለመቆጣጠር የወጣው ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 85* | 103826 | አንዋር አህመድ<br>እና<br>የቤ/ጉ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ | መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም | 397 |
| 84. | የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 የተፈፃሚነት ወሰን | 103458 | አቶ ጋረድ ለበሰ<br>እና<br>የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | መስከረም 27ቀን2008 ዓ.ም | 400 |
| 85. | የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 300/95 አንቀጽ 4/1/ | 104512 | አቶ አባስ ኢብራሂም<br>እና<br>ሐረር ቢራ አ/ማህበር | መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ/ም | 403 |

www.abyssinialaw.com

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 86. | የድለላ አበል ክፍያ መጠን ከተሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>በድለላ አበል መጠን ላይ በሚደረገው ክርክር እንደ ጉዳዩ ዓይነት እና የተሰጠው አገልግሎት እየተገናዘበ የሚወሰን ስለመሆኑ<br>የን/ሕ/ቁ. 59(3) | 109535 | ሳልቫቶሪ ዴቤታ ኮምፕሌክስ<br>እና<br>ሃብታሙ አባዲ | የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም | 406 |

www.abyssinialaw.com

# አሠሪና ሠራተኛ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112583

ጥቅምት 5 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መለሰ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጅማ ቅ/የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ብሩክ አበራ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረባቸውን ጉዳይ የሥራ ውል መቋረጥ ተከትሎ ሊከፈል የሚገባ ልዩ ልዩ ክፍያ ክርክር የሚመመለከት ነው፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረው የሥራ ውል ማቋረጥ ተከትሎ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን የጠየቀ ሲሆን የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ተጠሪ የሠራበት የእሁድ ቀን ክፍያ የ2006 ዓ.ም የአመት ዕረፍት እና የጥር ወር 2006 ዓ.ም ሙሉ ደመወዝ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡

ይግባኙ ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም

አመልካች ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ ችሎቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የጥር ወር 2006 ዓ.ም ደመወዝ ለተጠሪ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ፕሮፊደንት ክፍያ ጉዳይ እንዲጣራ ለሥር ፍርድ ቤት በነጥብ እንዲመለስ ሌላው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት ፍርድ ሰጥቷል ፡፡

www.abyssinialaw.com

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች የቅሬታ ነጥብ የእሁድ ቀን ሥራ ተጠሪ ሳይሰራ እንዲከፈለው መወሰኑ እና የ2006 ዓ.ም ተጠሪ አገልግሎት (የሥራ ውል) የተቋረጠው ጥር ወር 2006ዓ.ም አገልግሎት እንደሰጠ ተቆጥሮ የዓመት እረፍት ሙሉ ታስቦ እንዲከፈል መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አቤቱታውን ከመረመረ በኃላ የእሁድ ቀን ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑን እና የ2006ዓ.ም ሙሉ የዓመት እረፍት ተብሎ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ በሕግ አግባብ የተወሰነ ነው በማለት ተከራክሯል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

የአመልካች አንደኛው የቅሬታ ነጥብ እሁድ ቀን ተጠሪ ይሰራበት የነበረው ፋርማሲ ዝግ ስለነበር ተጠሪ እሁድ ቀን መሥራቱን ሳያረጋግጥ የሥር ፍርድ ቤት እሁድ ቀን ለሰራበት ይክፈሉ ማለቱ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት ላይ እንደተገነዘብነው የአመልካች ነ/ፈጅ በወረዳ ፍርድ ቤት በቃል ክርክርና ሲያደርግ ተጠሪ ለስራው ተከፍሎታል በማለት ስለመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገቡ አስፍሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም ተጠሪ እሁድ ቀን መሥራቱን የአመልካች ነ/ፈጅ ሳይክድ ነገር ግን ተከፍሎታል እያለ ስለተከራከረ የክፍያ ፔሮል አስቀርቦ መርምሮ በፔሮል የተከፈለው ወርሃዊ የደመወዝ እንጂ የትርፍ ቀን ክፍያ ስለመክፈሉ አላስረዳም በሚል በእሁድ ቀን ለሰራበት እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ቅሬታ የፍሬ ነገር ክርክር ከመሆኑም ባሻገር ተጠሪ እሁድ ቀን አልሰራም በማለት በሥር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ደረጃ አጉልቶ ማቅረቡ ሲታይ ለዚህ ሰበር ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት ከተሰጠ የሰበር ሥልጣን እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ ውጪ ከመሆኑም ባሻገር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ 329/1/ መሠረትም በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳም የክርክር ነጥብ በየትኛውም ደረጃ ባለው የበላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ስለሌለው ቅሬታው የሕግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው ነጥብ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረው የሥራ ውል ጥር ወር 2006 ዓ.ም መቋረጡ ተረጋግጦ እያለ በ2006ዓ.ም በጀት ዓመት ሙሉ አገልግሎት እንደሰጠ ታስቦ የዓመት እረፍት በገንዘብ ተሰልቶ እንዲከፈል መደረጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 77 (1)(ሀ) ላይ እንደተመለከተው ለአንድ ዓመት አገልግሎት የ14 የሥራ ቀናት በቃድ ይሰጣል፡፡አንድ ሰራተኛ ከአንድ አመት በታች አገልግሎት የሰጠ እንደሆነም በዚሁ ልክ ተመጣጣኝ የሆነ የእረፍት ጊዜ እንደሚሰጠው አንቀጽ 77(6) ላይ ተደንግጓል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በ2006 ዓ.ም የበጀት ዓመት በአመልካች መ/ቤት ያገለገለው እስከ ጥር ወር 2006ዓ.ም ሲሆን የአገልግሎት ጊዜው በበጀት ዓመቱ ሲሰላ 7 ወራት ብቻ ያገለገለ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም አገልግሎት በሰጠበት ጊዜ ልክ ያልተጠቀመበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው የሚገባው በ2006 ዓ.ም የበጀት ዓመት ሙሉ እንዳገለገለ ሳይሆን በአዋጅ አንቀጽ 77(6) በተደነገገው አግባብ በአገልግሎት ጊዜው ልክ (proportion to the length of his service) የሚለውን መርህ ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ በአግባቡ ሳይመለከቱ የአንድ ዓመት ሙሉ አገልግሎት እንደሰጠ  በመቁጠር የሙሉ ዓመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈል መወሰናቸው የሕጉን ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ በ1/2006ዓ.ም በአመልካች መ/ቤት የሰጠው አገልግሎት 7 ወራት ብቻ በመሆኑ ይኸው አገልግሎቱ የሚያሰጠው የዓመት ፈቃድ 8 ቀናት ብቻ ሲሆን ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው ተጨማሪ የሁለት ዓመት አገልግሎት ስላለው ሁለት ቀናት ሲደመርለት ሊያገኝ የሚገባው የዓመት ፈቃድ አሥር ቀናት (10) ይሆናል ፡፡

በዚሁ መሠረት ስዓቱ ሲሰራ (2576*30) X10 = 858.66 ያልተጠቀመው የዓመት እረፍት ክፍያ ሆኖ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው ይገባል ብለናል ፡፡

በዚሁ መሠረት ተከታዩ ተወስኗል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 1202 153በ07/07/07ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል ፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የዓመት እረፍት ክፍያ ብር 1,373.86 ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ፍርድ ክፍል ብቻ ተሻሽሎ ብር 858.66( ስምንት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከ66/100) ነው ተብሎ ተወስኗል ፡፡
3. ሌላው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፍል ፀንቷል ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ ብለናል ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 101675

ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ መስከረም ሞጋ ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ትዕግስት አረጋ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

የስራ ውል መነሻ ያደረገ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኗ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሰረቱት ክስ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍ/ቤቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረባቸው አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡ በአሁኗ ተጠሪ የቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡- በፈረንሳይ ሀገር በአመልካች መኖሪያ ቤት ውስጥ በየወሩ 1200 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ዩሮ/ ደመወዝ እየተከፈላቸው በሞግዚትነት እንዲሰሩ በ19/02/2001 ዓ.ም በተዓፈ ውል በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 በሚገኘው በአመልካች ወላጆች ቤት ውስጥ ተፈራርመው ከመጋቢት 02/2001 ዓ.ም እስከ መጋቢት 08/2002 ዓ.ም ድረስ ለአንድ አመት ሲሰሩ እንደቆዩ፣ የስራ ውሉም አመልካች ፈረንሳይ አገርን ለሁል ጊዜ ሲለቁ የሚቋረጥ ስለመሆኑ፣ አመልካች የተጠሪ ደመወዝ ሳይከፈሉ እንዳሰናበቷቸው የዓመት ረፍት ጊዜም አምስት ሳምንት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በውሉ የተመለከተ ቢሆንም እንዳልተሰጣቸው፣ አመልካች ደመወዛቸውን እንዲከፍሉዋቸው በውጭ ጉዳይ ሚኒስተር በኩል፣ በሽምግልና ጥረት ቢያደርጉም ሊከፈላቸው እንዳልቻለ፣ 1200 ዩሮ ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ ሲመነዘር 20.80 /ሀያ ሺህ ከሰማንያ ሳንቲም/ በመሆኑ፣ ደመወዝ 299,520.00 የአምስት ሳምነት የእረፍት ጊዜ 29,120.00 በድምሩ 328,640.00 /ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ

www.abyssinialaw.com

አርባ ብር/ እና ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 9% ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው፣ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች የበኩላቸውን መልስ ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ነገሩ በሰጡት መልስ ክሱ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቀርቦ የተዘጋ ስለመሆኑ፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው፣ የተጠሪ የደመወዝ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በፍሬ ጉዳዩም ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝ አለመኖሩን፤ ደመወዝ ካልተከፈላቸው ውሉ ለመዘገበዉ የፈረንሳይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀረቡ እንደነበር፣ በመግለፅ መከራከራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ በ18/06/2006 ዓ.ም ብይን የሰጠ ሲሆን ጉዳዩን ተመልክቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን እንዳለው በመጥቀስ የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት ቃል ከመረመረ በኋላ በግራ ቀኙ የተፈረመው የስራ ቅጥር ውል መኖሩን ተቀብሎ የተጠሪ የወር ደመወዝ 1200 ዩሮ እንደነበር በአመልካች ከቀረበው ማስረጃ ፍ/ቤት የተቀበለው የክፍያ መጠን በድምሩ 6,408 ብር ብቻ እንደሆነ፤ ተጠሪ የሚገባቸው ቀሪ ክፍያ ብር 293,112.00 መሆኑን፤ የአምስት ሳምንት የእረፍት ክፍያ በድምር ብር 29,120.00 እንደሆነ በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ብር 322,232.00 /ሶስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር/ እንዲከፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር አድርጓአል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የተጠሪ የክፍያ ጥያቄ በፍ/ሕ/ቁ.2601 እና 2023/ሀ/ መሰረት በይርጋ የሚታገድ ነው፤ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚዳኝ አይደለም፤ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች መቅረብ ከነበረበትም በሥራ ክርክር ችሎት መቅረብ ነበረበት የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ክሱን በወቅቱ ማቅረባቸው እና በይርጋ የሚታገድበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታውን የሚደግፍ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር

www.abyssinialaw.com

በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ነጥቦች፡-

1. ግራ ቀኙ በሚከራከሩበት ጉዳይ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ የትኛው ነው?
2. የደመወዝ ክፍያ ግምት በተመለከተ የተነሳው የይርጋ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በአጣሪ ችሎቱ የተጠቀሰው የፍ/ሕ/ቁ.2023/ሀ/ ነው ወይስ አይደለም?
3. አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ የሥራ ውል ግንኙነት እንደነበራቸው፣ ውሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈርሞ በፈረንሳይ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደተመዘገበ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት እንደነበራቸው ሳይክዱ ሁሉም ክፍያዎች በወቅቱ እንደተከፈሉ፣ አልተከፈለም የሚባል ገንዘብ ካለም በይርጋ እንደሚታገድ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች ቤት በሞግዚትነት ለአንድ አመት ማገልገላቸው እና የጠየቁት ክፍያ እንዳልተፈፀመላቸው እንዲሁም ክሱን በወቅቱ ስለማቅረባቸው በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሰረታዊ ጭብጥ እንደሚከተለው መርመሮታል፡፡

<u>**የመጀመሪያው ጭብጥ በተመለከተ**</u>፡- አመልካች የተጠሪ የስራ ቅጥር ውል ከፍ/ሕ/ቁ. 2601 አንፃር እንዲታይ በሰበር አቤቱታቸው አመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት በቤተሰብ አስተዳደር ውስጥ ስለሚኖር አሽከር የስራ ውል፣ ሰራተኛውን የሚኖሩት መብትና ግዴታዎች የሚመለከት ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ያለው የተፈፃሚነት ወሰን ሲታይ በአገር ውስጥ በሚቀጠሩ ሰራተኞች ስለመሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፅሞ በፈረንሳይ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፀድቆ አመልካች እና ተጠሪም በፈረንሳይ አገር ሲኖሩ እንደነበር ባለተካደበት ሁኔታ ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ስለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የወጣው አዋጅ ቁጥር 377/96 እና የዚህ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓላማና ግብ በሀገር ውስጥ ስለሚኖረው የስራ ስምሪት የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ፣ ሊሟሉ የሚገባቸው አነስተኛ መመዘኛዎች ማለትም የስራ ሰዓት፣ የእረፍት ጊዜ፣ የሕመም ፈቃድ ወዘተ ያካተቱ ሕግ እንጂ በውጭ አገር ተቀጠረው ስራ ሲሰሩ የነበሩ ሰዎች የሚያነሱት የመብት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች እና ተጠሪ በሚከራከሩበት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ /Governing Law/ በሀገር ውስጥ ባለው የስራ ስምሪት የግራ ቀኙ አንፃራዊ መብትና ግዴታ

www.abyssinialaw.com

የሚደነግጉ የፍ/ሕ/ቁ.2601 እና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የሚመለከት አዋጅ 377/96 አለመሆኑን ተረድተናል፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ስለስራና ሰራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ነው፡፡ የዚህ አዋጅ መግቢያ፣ የተፈፃሚነት ወሰን የሚመለከት አንቀፅ 3/2/ "የግል አገልግሎት ስራ ላይ ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄዱ ኢትዮጵያ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል" በማለት ደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል የግል አገልግሎት /personal service/ ስራ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ አዋጅ ቁጥር 632/2001 ነው ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተ</u>፡- ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሰረታዊ ነጥብ አንዱ ይርጋን የተመለከተ ነው፡፡ አመልካች የተጠሪ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በ6 ወር የሚታገድ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ችሎት እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥም የይርጋ ጥያቄው ከፍ/ሕ/ቁ.2023/ሀ/ አንፃር እንዲታይ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ሕ/ቁ.2601 በማጣመር ስንመለከተው በሀገር ውስጥ በቤት አገልጋይነት የተቀጠሩ አሽከሮች በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ ካልተጠየቁ እንደተከፈለ የሕግ ግምት ይወሰዳል የሚል ይዘት ያለው ስለመሆኑ ተመልክተናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የፍ/ሕ/ቁ. 2601 ይሁን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሀገር ውስጥ የስራ ስምሪት ላይ በሚነሱ ክርክሮች እንደነገሩ ሁኔታ ተፈፃሚ ከሚሆኑ በስተቀር በውጭ አገር ለተሰጠው አገልግሎት እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የክፍያ ክርክር አግባብነት ያላቸው የሕግ ማዕቀፎች ባለመሆናቸው አመልካች የተጠሪ የመብት ጥያቄ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የሚታገድ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

አዋጅ ቁጥር 632/2001 አንቀፅ 3/1/ የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን አንቀፅ 20 ስለ ሰራተኛው መብት፣ አንቀፅ 24 ስለ አነስተኛ ደመወዝ መጠን የሚመለከቱ መሰረታዊ ድንጋጌዎች ያካተተ ቢሆንም በአሰሪና ሰራተኛው የሚነሳው የክፍያ ጥያቄ በተለይም የመብት ጥያቄ ለማቅረብ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው የይርጋ ጉዳይ መታየት ያለበት ከአጠቃላይ የውል ድንጋጌዎች አንፃር ስለመሆኑ ተቀባይነት ያለው የሕግ አተረጓጎም ስርዓት ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ. 1677/1/ "ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀፅ ደንቦች ይፈፀሙባቸዋል" በማለት የደነገገ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ተዛማጅ የሆነው የእንግሊዘኛው ትርጉም" 1677/1/ the relevant provisions of this title shall apply to obligations not withstanding that they do not arise out of a contract" በማለት የተደነገገ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው የክፍያ ጥያቄ ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ከፍ/ሕ/ቁ. 1677/1/ እና 1845 አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ የአመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል ግንኙት

www.abyssinialaw.com

መሰረት በማድረግ የሚነሳው ክርክር በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው የውል ግንኙነት የተቋረጠው መጋቢት 2002 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ እስከቀረበበት መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም ያለው ጊዜ ሲታይ በፍ/ሕ/ቁ. 1845 የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ሳይጠናቀቅ ክስ መቅረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የማያነሱት የይርጋ ጥያቄ ተፈፃሚነት ካለው የይርጋ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡

<u>**የመጨረሻው ጭብጥ በተመለከተ**</u>፡- የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በወር 1200 ዩሮ እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበር አረጋግጧል፡፡ አመልካች ክፍያ መፈፀማቸው ቢከራከሩም የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተደገፈ ነው በማለት የተቀበለው ክፍያ 6,408 ብር ብቻ መሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ መረዳት ተችሏል፡፡ ተጠሪ ያልተከፈላቸው አጠቃላይ ደመወዝና የዓምስት ሳምንት የእረፍት ጊዜ ክፍያ ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ ሲመነዘር /6,408 ተቀንሶ/ 322,232.00 መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተመልክቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መዝኖ አመልካች ለተጠሪ ብር 322,232.00 ይክፈሉ በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍልም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ከፍተኛ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በውጤት ፈርጀ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው መሆኑ የሚያሳይ ነገር ያልተገኘ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 99933 በ12/07/2006 የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 99977 ግንቦት 6/2006 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት የይርጋ ጊዜ የሚገዛው በፍ/ሕ/ቁ 1677/1/ እና 1845 ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሰረት የተጠሪ የመብት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ብር 322,232.00 /ሶስት መቶ ሀያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት/ ከ13/07/2003 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

4. በዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያወጡት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- በዚህ ፍ/ቤት ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

*መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

www.abyssinialaw.com

መ/ቁ.114669

ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** የኢትዮጲያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን የደብረ ማርቆስ መንገዶች ጥገና ዲስትሪክት ነገረ ፈጅ መሰረት አበራ

**ተጠሪ፡-** አቶ አስማረ ፈጠነ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ውል ማቋረጥ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአ.ብ.ክ.መ.የደብረማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ከሚያዚያ 21 ቀን 1984 ዓ/ም ጀምሮ በጠቅላላ 22 ዓመት ሲያገለግሉ እንደቆዩ፣ መስሪያ ቤቱም በየጊዜው እድገት ይሰጣቸው እንደነበር፣ በሹፍርና ሙያ የስራ መደብ እስከ መጋቢት 10 ቀን 2006 ዓ/ም ድረስ ስራቸውን በተገቢው መንገድ እየፈጸሙ በነበሩበት ሁኔታ አመልካች ከመጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ክስ እስካቀረቡት ድረስ ከስራ ያገዳቸው በመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ነው ተብሎ ወደ ስራ ገብታችሁ እንዲመለሱ፣ ይህ የማይወሰን ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተፈቀዱትን የስራ ስንብት ክፍያ የ6 ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ደመወዝ በወቅቱ ባለመክፈሉ በድምር 60,601.70 /ስልሳ ሺህ ስድስት መቶ አንድ ብር ከሰባ ሳንቲም ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፈል እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁኑ አመልካች ባቀረበው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ከ30 ቀን በላይ የቀሩ በመሆኑ ስንብቱ በህጉ አግባብ የተከናወ ነው ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም የህግ መስረት የለውም፡፡ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉአቸው ያቀረቡት ጥያቄም በአግባቡ አይደለም፡፡ የአመት እረፍት በተመለከተ የቀረበ የክፍያ ጥያቄም ተገቢነት የለውም፡፡ የስራ ልምድ የተሰጣቸው በመሆኑ ድጋሜ ሊጠይቁ አይገባም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ ተገቢ ነው ያለው ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገቡ ከመረመረ በኃላ የአሁን ተጠሪ ከባህር ዳር ወደ ደብረ ማርቆስ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነው ሌላ አሽከርካሪ ከእንጅባራ ወደ ደብረማርቆስ በሚነዱበት ጊዜ የመኪና ግጭት ተከስቶ የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ እስከሚጣራ በጊዜ ቀጠሮ ለ4 ወር ከ11 ቀን መታሰሩን ዓቃቤ ህግ ጉዳዩን ካጣራ በኃላ በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ አያስከስስም በማለት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/42/1/ሀ/ መሰረት የዘጋው ሲሆን ተጠሪ ማረሚያ ቤት የገቡት ፍ/ቤት ጥፋተኛ ተብሎው ተፈርዶባቸው ሳይሆን በጊዜ ቀጠሮ እስከ ሆነ ድረስ በተባለው ጉዳትም ተጠያቂ የሆነው ሌላ መኪና ሲነዳ የነበረ ሹፌር በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ እንዲመለስላቸው ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም አቤቱታው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/በ/ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ለሚታሰሩ ሰራኞች የሚመለከት አይደለም፡፡ ተጠሪ በጊዜ ቀጠሮ መታሰራቸው ፍርዱ ወይም ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው የሚያስብል አለመሆኑን ገልጾ የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ይከፈላቸው የሚለውን የውሳኔ ክፍል በማሻሻል ወደ ስራ እንዲመለሱ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ በድምጽ ብልጫ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ሰበር ችሎቱ በፍርድ ወይም በውሳኔ ከ30 ቀን በላይ ያልታሰረው ሰራተኛ ስራ ሲሰራ በተፈጠረ አደጋ በምርመራ ላይ በእስር የቆየ ለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የስራ ውል መቋረጥ ከህግ ውጭ ነው ወደ ስራ ይመለስ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርጓል /ተለዋውጧል/፡፡ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት፡- ተጠሪ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ታስረው ከስሩ የቀሩ መሆኑን ተረጋግጦ ስንብት መከናወኑ በአግባቡ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/37256 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ያላገናዘበ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች የስራ

ውሉ ያቋረጠው ከህግ ውጭ ነው፡፡ የሰበር ውሳኔው በጭብጥ ከተያዘው ጉዳይ ግንኙነት እንደሌለው፤ በጊዜ ቀጠሮ ታስረው እንደተለቀቁ ጉዳዩም አያስከስስም ተብሎ በዓ/ህግ መወሰኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም አቤቱታውን የሚያጠናክር ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ፡- ተጠሪ ፈጸሙት በተባለው ወንጀል ተጠርጥረው በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ታስረው ከተፈቱ በኃላ ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/በ/ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከባህር ዳር ወደ ደብረማርቆስ በሚያሽከርክሩበት ጊዜ ከሌላ መኪና ጋር ግጭት በመፍጠሩ ጉዳዩ ለማጣራት በጊዜ ቀጠሮ 4 ወር ከ11 ቀን ከታሰሩ በኃላ የዓቃቤ ህግ ጉዳዩን በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/42/1/ሀ/ አያስከስስም በማለት የዘጋው በመሆኑ ከእስር እንደተለቀቁ እና በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን መታሰር የሰራተኛው የስራ ውል ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም ተብሎ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋኛ መሆን አለመሆናቸው ሳይሆን ከ30 ቀን በላይ ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት ከስራ ለማሰናበት በቂ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ጉዳይ ተጠሪ በጊዜ ቀጠሮ ከ30 ቀን በላይ ከመታሰራቸው ውጭ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ጥፋተኛ አልተባሉም፡፡

አንድ አሰሪ ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሚያሰናብትባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰራኛው ከ30 ቀን በላይ የእስራት ፍርድ ተወስኖበት ከስራ መቅረቱን ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/በ/ ተመልክቷል ፡፡ የድንጋጌው ሙሉ ይዘት "በሰራተኛው ላይ 30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የእስራት ፍርድ ተወስኖበት ከስራ ሲቀረ" የሚል ሲሆን የእንግሊዘኛው ቅጂ ደግሞ "absence from work due to sentence of imprisonment passed against the worker for more than 3 days" በማለት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የተቻለው አንድ ሰራተኛ ከ30 ቀናት የሚበልጥ እስራት ተወስኖበት ከስራ መቅረቱን ሲረጋገጥ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ እንደሚሰናበት የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከስራ መቅረታቸው ሳይካድ የቀሩበት ምክንያት ግን በወንጀል ተጠርጥረው በጊዜ ቀጠሮ ታስረው ስለነበር ነው፡፡ ስልጣን ያለው የዐቃቤ ህግም የወንጀል ክስ ለመቀጠል የሚያስችል ነገር የሌለው በመሆኑ ጉዳይ አያስከስስም በማለት ስለ መዝጋቱ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው

www.abyssinialaw.com

ጥፋተኛ ተብለው አልታሰሩም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከ30 ቀን በለይ ከስራ መቅረቱን ተረጋግጦ ያልተወሰነበት ሰራተኛ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ማሰናበት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 /1/በ/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች በተሰጣቸው ኃላፊነት ሙያዊ ግዴታቸው ሲወጡ በተከሰተው የመኪና ግጭት ተጠርጥረው በመታሰራቸው ምክንያት ብቻ ፍ/ቤት ጥፋተኝነታቸው ሳያረጋግጥ አመልካች በራስ አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችለው የህግ መሰረት የለውም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/37256 ህዳር 4 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪ የስራ ውል ከህግ ውጭ ማቋረጡን በማረጋገጥ ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰናቸው በአግባቡ መሆኑ ከሚያሳይ በቀር የፈጸሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው አይደሉም ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአብክመ የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0119921 በ27/04/2007 ዓ/ም የደብረማርቆስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/10694 በ20/20/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ፍርድ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/44956 በ26/09/2007 ዓ/ም በድምጽ ብላጫ የሰጠው ፍርድ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ወደ ስራ እንዲመልሰው መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ችሎት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- ሰኔ 30/2007 ዓ/ም በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 118263

ቀን ጥር 18/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሪዳ ኑረዲን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቡልኬስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ በሰበር እንዲታይ የቀረበው መሰረታዊ የክርክር ነጥብ የአሁኑ ተጠሪ የወሰደው ከስራ የማሰናበት እርምጃ በሕጉ አግባብ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኗ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ በመ.ቁ. 39053 ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ በየደረጃው የተመለከቱት የስር ፍ/ቤቶች በአሁኑ ተጠሪ የተወሰደው ከስራ የማሰናበት ተግባር በሕጉ መሰረት ነው በማለታቸው በሰበር እንዲታረም ያቀረበው አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች በስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- በተጠሪ ድርጅት በመጋዘን ሃላፊነት ከታህሳስ 06 ቀን 2004ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው እስከተቋረጠበት ግንቦት 21ቀን 2006ዓ.ም ድረስ በወር 3386.32 (ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ስድስት ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም) እየተከፈላቸው ስራቸውን ሲሰሩ እንደነበር፤ የአሁኑ ተጠሪ የስራ ውላቸው ከሕግ ውጪ ያቋረጠው በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ የስራ ስንብት ካሳ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የግንቦት ወር የ21ቀን ደመወዝ፣ የ4ቀን የዓመት ረፍት ክፍያ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ የመከላከያ መልስ ያቀረበ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ፡- አመልካች እቃ እያለ የለም እያሉ፤ ከድርጅቱ ሰራተኞች ባለመግባባት እና በተደጋጋሚ ከስራ በማርፈድ ጥፋት ፈጽመው ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም አላሻሻሉም፡፡ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ አይገባቸውም የ4ቀን እረፍት ወስደውታል፤ የግንቦት የ21ቀን ደመወዝ በሂሳብ ቁጥራቸው ገቢ ሆነዋል፡፡ ስንብቱ በሕግ አግባብ የተከናወነ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የተጠሪ ምስክሮች አድምጧል፡፡ የሰነድ ማስረጃም ተመልክተዋል፡፡ በተጠሪ የቀረቡ ምስክሮች አመልካች የድርጅቱ የስራ መግቢያ ሰዓት አያከብሩም፡፡ ከ2፡00 — 2፡30 ሰዓት ድረስ የስራ መግቢያ መሆኑን እየታወቀ ከ3፡00 - 3፡30 ይገባሉ፡፡ ከጥበቃና ሌሎች ሰራተኞች ይጋጫሉ፡፡ ፈጸሙት ለተባለው ጥፋት በ03/03/2005ዓ.ም ፣ በ12/03/2005ዓ.ም እና በ29/02/2006ዓ.ም ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው በ12/03/2005ዓ.ም የሁለት ቀን ደመወዝ ተቀጥቷል፡፡ አመልካች የተጠሪ ማስረጃ አላስተባበሉም፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1(ሀ) እና (ረ) መሰረት ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው በተደጋጋሚ ከስራ የቀሩ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ የስራ ስንብት ካሳ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ አይገባቸውም፡፡ የእረፍት ጊዜ በተመለከተ መውሰዳቸው የተረጋገጠ ሲሆን የግንቦት ወር 21ቀን ደመወዝ ፈርመው መውሰዳቸው አልተረጋገጠም ብር 2370.59 ይክፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ግራቀኙ በማከራከር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓአል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ለስንብቱ ምክንያት የተባለው ነገር በስንብት ደብዳቤ እንዳልተገለጸ፤ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት መፈጸማቸው ሳይረጋገጥ የስራ ውል መቋረጡ ሕገወጥ ነው ሊታረም ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በስንብት ደብዳቤው ላይ ምክንያት አለመገለጹ ስንብቱ ሕገወጥ አያደርገውም ውሳኔው ሊነቀፍ አይገባም የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከለይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚጠይቀው ጭብጥ የአሁኑ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካች የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ በሆነ አግባብ ነው በማለት አጥብቀው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በፈጸሙት ጥፋት ነው የሚል መልስ

www.abyssinialaw.com

ማቅረቡን መዝገቡን ያሳያል፡፡ በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋገጠ የተባለው አመልካች እቃ የለም እንደሚሉ፤ ከስራ ባደረቦቻቸው እንደማይግባቡ እና በ03/05/2005 ፣ በ12/03/2005 ፣ እና በ29/02/2006 ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው የሚገልጽ ነው፡፡ ከዚህ መዝገብ ጋር የተያያዘው እና በተጠሪ ተጻፈ በተባለው ደብዳቤ የአመልካች የስራ ውል ከ21/09/2006ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው እንደሚቋረጥ የሚገልጽ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በስንብት ደብዳቤው ምክንያት ሳይገልጽ ፍሬ ነገሩ በማስረዳት የስራ ውል ማቋረጥ እንደሚችል ግልጽ ቢሆንም ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጥፋት መቼ እንደተፈጸመ ማጣራትና ግልጽ ማድረግ ግን የአሰሪው ግዴታ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የተከራከረ ቢሆንም እስከ ጥቅምት 29ቀን 2006ዓ.ም ተፈጸሙ የተባሉ ጥፋቶች መሰረት በማድረግ ቅጣት ወስኖ እንደነበር የስር ፍ/ቤት መዝገብ የሚያሳይ ቢሆንም ለመጨረሻ ጥፋት ቅጣት ከተወሰነ በኋላ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት ስለመፈጸማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ አንድ አሰሪ ሰራተኛው ያለበቂ ምክንያት ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው በመደጋገም የስራ ሰዓት የማያከብር ሰራተኛ የስራ ወሉ ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ እንደሚችል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሀ) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተያያዘ እንደጥፋቱ ክብደት በስራ ቦታ አምባጓሮ መፍጠር ወይም ጠብ አጫሪነት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ እንደሚያሰናብት ከላይ በተመለከተው ሕግ አንቀጽ 27(1(ረ) ስር ተደንጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት አመልካች በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው አርፍደዋል ከተቋሙ ሰራተኞች አይግባቡም ያለ ቢሆንም ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ጊዜ በኋላ ስለመሆኑ አላረጋገጠም፡፡ አንድ አሰሪ በሰራተኛው ተፈጸመ ያለው ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ድርጊት የስራ ውሉ ለማቋረጥ ያለው መብት ድርጊቱ መከሰቱ ከታወቀበት ከ30ቀናት በኋላ በይርጋ እንደሚታገድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27(3) ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ተፈጸመ ያለው በተደጋጋሚ ማርፈድ፤ ከድርጅቱ ሰራተኞች ያለመግባባት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ከጥቅምት 2006ዓ.ም በኋላ የተፈጸሙ እና ድርጊቱ መከሰቱ በታወቀ በ30ቀናት ውስጥ ህጋዊ እርምጃ ስለመወሰዱ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ያቋረጠው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሀ)፣ (ረ) እና (3) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ሳይከተል ነው ብለናል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም በተጠሪ የተወሰደው የስራ ውል ማቋረጥ ተግባር በሕጉ አግባብ ነው ማለታቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የተደነገጉትን የስራ ውል የሚቋረጥባቸው ሕጋዊ ስርዓቶች ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በሕጉ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ነው ከተባለ የሕገወጥ ሥራ ውል ማቋረጥ ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ የስራውሉ በሕገወጥ መንገድ ሲቋረጥ በሕጉ የተቀመጠው መፍትሔ በሕጉ የተፈቀደው ውዙፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራ መመለስ ወይም ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተፈጽመውለት ከስራ ማሰናበት ናቸው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(1) እንደተመለከተው የስራ ውሉ ከሕግ ውጭ የተቋረጠበት ሰራተኛ ወደ ስራ የመመለስ መብት አሰሪው ደግሞ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ ሰራተኛው ወደስራ የመመለስ ካልፈለገ/ች ካሳ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤት አንድ ሰራተኛ ወደስራ ሊመለስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው አንኳር ነጥብ ሲወሰን የስራው ባህሪ የግራቀኙ ግንኙነት እና የኢንዱስትሪ ሰላም ታሳቢ መደረግ አለባቸው፡፡ ፍ/ቤቱ ሰራተኛው ወደስራ ቢመለስ ከአሰሪው ጋር ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ብሎ ካመነ ሰራተኛው በሕጉ አግባብ ካሳ ተከፍሎት ከስራ እንዲሰናበት ሊወሰን እንደሚችል ከላይ በተመለከተው አዋጅ አንቀጽ 43(2) ስር ተመልክቷል፡፤ በተያዘው ጉዳይ የአሁኗ አመልካች በድርጅቱ ሲኒየር እስቶር ኪፐር /የመጋዘን ኃላፊ/ የነበሩ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የመጋዘን ሃላፊ የሚሆነው ሰራተኛ ከፍተኛ የሆነ እምነት የሚጣልበት ስራ ከመሆኑ አንጻር ከአሰሪው ጋር ጥሩ የስራ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ አሁን ያላቸው ግንኙነት ከፍተኛ እምነት በሚጠይቀው የስራ መደብ አመልካች በነበሩት የስራ መደብ እንዲቀጥሉ ማድረግ በኢንዱስትሪ ሰላም እና የድርጅቱ ውጤታማነት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጠር እንደሚች ግምት ወስደናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወደ ስራ ከሚመለሱ ይልቅ በሕጉ የተፈቀዱላቸው ክፍያዎች ተከፍሏቸው ከስራ ቢሰናበቱ ለሁለቱም ተከራካሪዎች ጠቃሚ ነው ብለናል፡፡

የአመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጭ በመቋረጡ ምክንያት በሕጉ የተፈቀዱ ክፍያዎች የስራ ስንብት ክፍያ፣ የካሳ ክፍያ እና የማስጠንቀቂያ ክፍያ ስለመሆናቸው ከላይ በተመለከተው አዋጅ አንቀጽ 39፣40፣43 እና 44 ተመልክቷል፡፡ የአመልካች የወር ደመወዝ 3386.38 መሆኑ በቀረቡት ክስ የተጠቀሰ ሲሆን ተጠሪም የደመወዝ መጠኑ በመካድ ያቀረበው ክርክር የሌለ በመሆኑ ለሚወሰነው ካሳ መነሻው ይህንን የደመወዝ መጠን ይዘናል፡፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ከታህሳስ 06 ቀን 2004 እስከ ግንቦት 21ቀን 2006ዓ.ም የሰሩ መሆናቸውም አላከራከረም፡፡ የአመልካች የአገልግሎት ዘመን 3 አመት ከ 7 ወር ከ 16 ቀን ነው፡፡ በመሆኑም የስራ ስንብት ክፍያ በአንቀጽ 40(1) እና (2) መሰረት ብር 6,349.44፤ የካሳ ክፍያ በአንቀጽ 43(4)(ሀ) መሰረት 20,318.28 ብር፤ ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ በማቋረጡ በአንቀጽ 35(1)(ለ) መሰረት የሁለት ወር ደመወዝ ለመክፈል የሚገደድ ይሆናል፡፡ ይሁንና የአሁኑ ተጠሪ የሁለት ወር ደመወዝ እንዲወስዱ በደብዳቤ የገለጸ በመሆኑ ይህንን በደብዳቤው የገለጸውን መጠን ገንዘብ

www.abyssinialaw.com

ካልከፈለ ይክፈል ብለናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤቶች በተጠሪ የተወሰደው የማሰናበት እርምጃ በሕጉ አግባብ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 39053 በ14/04/2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 156383 በ4/12/2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ያቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ የአመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጭ በማቋረጡ የስራ ስንብት ክፍያ፣ ብር 6,349.44፤ የካሳ ክፍያ ብር 20,318.28 እና የማስጠንቀቂያ የሁለት ወር ደመወዝ ያልተከፈለ ከሆነ እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡ በድምር ብር 26,667.72 (ሃያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ሰባት ከሰባ ሁለት ሳንቲም) እንዲሁም በስንብት ደብዳቤ የተገለጸው የሁለት ወር ደመወዝ ስራ ማፈላለጊያ የተባለው የ2ወር የማስጠንቀቂያ ደመወዝ የሚተካ ነው ብለናል፡፡ ገንዘቡ ያልተከፈለ ከሆነ ተጠሪ አሁን ከተወሰነው ገንዘብ ደምሮ መክፈል አለበት ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112956

ጥቅምት 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ሙስጠፋ ኑር ትዕም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኢንተርኘራይዝ ነ/ፈጅ ጋሻው ቡልቶ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ቅጥር ውል ማቋረጥን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በተመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ ወደ ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ተለውጦ፣ ይህም ድርጅት ወደ ኢንተርኘራይዝ ተቀይሮ ብር 3666.00 በማግኘት ለ28 አመታት የሰራ ቢሆንም ከስራ ሳይቀር፣ ከስራ ለቀረበት ቀንም የሃኪም ማስረጃ አቀርቦ ሳለ ደመወዝም እየተከፈለው በነበረበት ሁኔታ በ18/12/2004 በፅሁፍ ከስራ መሰናበቱ እንደተገለፀለት፤ የተጠሪ ድርጊት ሕገ ወጥ በመሆኑ ወደ ስራ እንዲመለስ እንዲወሰንለት ዘርዝሮ በአጠቃላይ 89,328.20 ከወጪና ኪሳራ ከጠበቃ አበል ጭምር እንዲከፈለው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ከስራ የተሰናበተው ከ20/9/2004 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ለአምስት የስራ ቀናት ከስራ የጠፋ ስለሆነ ምክንያቱና ማስረጃውን በወቅቱ ባለማቅረቡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ለ/ የስራ ውል ማቋረጥ ሕጋዊ ነው፡፡ የስራ ስንብት ክፍያ አይመለከተውም በአዲሱ ድርጅትም 5 አመት አላገለገለም፡፡ የማስጠንቀቂያ ክፍያም አይገባውም

www.abyssinialaw.com

የቀረ ደመወዝ የለውም፣ በአንፃሩ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከስራ በመቅረቱ የአንድ ወር ደመወዝ በካሳ መልክ እንዲከፍል እንዲወሰን በማለት አቅርበዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ከስራ የቀረበት በቂ ምክንያት የማቅረብ ሕጋዊ ግዴታ እንዳለበት የሕክምና ማስረጃ ለተጠሪ አስተዳደር የስራ ክፍል መስጠቱን፤ ከታመመ በኋላ ተመልሶ ስራ መጀመሩን የተከራከረ ቢሆንም አላረጋገጠም፤ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው፡፡ ክፍያ በተመለከተ ከ5 አመት በላይ በማገልገሉ እንዲሁም ክፍያው በወቅቱ ባለመፈፀሙ የአገልግሎት ክፍያ 36,660 እና ቅጣት 10,998 በድምር 47,658.00፣ የጠበቃ አበል 10% ወጪና ኪሳራ 500.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም የይግባኝ ቅሬታው ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ካከራከረ በኋላ አመልካች በራሱ ፍላጎት 5 አመት ካገለገለ በኋላ መልቀቁን ያልተረጋገጠ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች ሽሮ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ ይሁን ክፍያ ለዘገየበት ተብሎ የሚከፈለው ነገር የለም ብሎዋል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጧል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ነጥብ፡- በተጠሪ ድርጅት ለረጅም ዓመታት አገልግሎት የአገልግሎት ክፍያ አይገባውም መባሉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ ያላገናዘበነው የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ለ5 ቀናት ከስራ በመቅረቱ ምክንያት ከስራ በመሰናበቱ የአገልግሎት ይሁን ክፍያ ዘገየበት ለተባለው ጊዜ የሚከፈለው ነገር የለም ተብሎ መወሰኑ የአዋጁን መንፈስ የተከተለ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ በአመልካች የቀረበው የመልስ መልስም አቤቱታውን የሚደግፍ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር፤ ለሰበር ችሎት መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እንዲሁም ጉዳዩ በሰበር ይመርመር ተብሎ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

www.abyssinialaw.com

እንደመረመርነውም አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው መሰረታዊ ጭብጥ የሰራተኛውን በተከታታይ ለ5 ቀናት ከስራ መቅረት ተከትሎ የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በአመልካች የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡ አመልካች በሕመም ምክንያት ከስራ የቀረ ቢሆንም ከሕመሙ አገግሞ ወደ ስራ እንደተመለሰ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ያለ በቂ ምክንያት ለተከታታይ 5 የስራ ቀናት ከስራ በመቅረቱ በሕጉ አግባብ ከስራ ተሰናብቷል የሚል መልስ አቅርበዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ አመልካች ለተከታታይ 5 የስራ ቀናት ከስራ የቀረበት በቂ ምክንያት ስለመኖሩ አላስረዳም የሚል ነው፡፡ አመልካች ከስራ የቀረበት ምክንያት በጤና እክል ስለመሆኑ በቅሬታ ከመግለፅ ውጪ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር መጣራትና ማስረጃ ምዘና እና ድምዳሜ ተገቢ አለመሆኑን ስልጣን ባለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማስቀረብ የሻረ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር እና ማስረጃ ምዘና ስርዓት እና ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሚመረመር ባለመሆኑ እንዳለ የምንቀበለው ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ጉዳዮችም መርምሮ ማረም ስለመሆኑ ከሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 መሰረታዊ ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳነው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ያለበቂ ምክንያት ተከታታይ 5 የስራ ቀናት ከስራ መቅረቱን በማረጋገጥ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ እንዲሰናበት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1//ለ/ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

የአመልካች የስራ ስንብት በሕጉ አግባብ የተደረገ መሆኑ ከተረጋገጠ ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለተሰናበተ ሰራተኛ የአገልግሎት ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት በቅጣት መልክ የ3 ወር ደመወዝ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው አመልካች ለተከታታይ 5 የስራ ቀናት በስራ ገበታው ባለመገኘቱ ያለማስጠንቀቂያ ነው፡፡ አመልካች ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ቢሰናበትም የአገልግሎት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው አጥብቆ እየተከራከረ ነው፡፡ አንድ ሰራተኛ ከስራ ከተሰናበተ በኋላ የአገልግሎት ክፍያ ከሚያገኝባቸው ሕጋዊ ምክንያቶች አንዱ በድርጅቱ ከ5 አመት በላይ አገልግሎት በገዛ ፈቃዱ ስራ መልቀቁን ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ "ቢያንስ አምስት አመት በአሰሪው ዘንድ የስራ አገልግሎት ኖሮት በሕመም ወይም በሞት የስራ ውሉ ሲቋረጥ ወይም ስራው ከስልጠና ጋር የተያያዘ ለአሰሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ስራው በገዛ ፈቃዱ" የለቀቀ የአገልግሎት ክፍያ እንደሚያገኝ ደንግጎአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከስራ የለቀቀው በገዛ ፈቃዱ /on his own initiative/ ሳይሆን አሰሪው ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ስለአሰናበተው ነው፡፡ አመልካች ከስራው በገዛ ፈቃዱ የለቀቀ መሆኑ ካልተረጋገጠ ደግሞ የስንብት ክፍያ የሚያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ በተያያዘ ጉዳይ

www.abyssinialaw.com

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ 25511 እና ሌሎች መዝገቦች አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የስር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች ስራውን በገዛ ፈቃዱ አለመልቀቁን በማረጋገጥ የስራ ስንብት ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሻሩ ሕጉን በአግባቡ ተርጉሟል ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የፈፀሙት ስህተት ማረሙ በአግባቡ በመሆኑ ጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ለማለት የሚችል ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 181962 በ2/06/2007 ዓ.ም የስር የአዳማ ልዩን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 18244 በ08/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በመሻር፤ የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 73239 በ30/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በመሻር የሰጠው ፍርድ በድምፅ ብልጫ ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው ያለማስጠንቀቂያ መሆኑ በመረጋገጡ በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀፅ 2/ሸ/ የተመለከተው ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት አይመለከተውም ተብሎ መወሰኑ በሕጉ አግባብነት ነው ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 116002

ቀን 6/3/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የአንቦ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩንየን አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ጫመዳ መገርሳ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር የአሁኑን አመልካች የአንቦ የገበሬዎች የህብረት ሥራ ዩንየን በቀን 13-11-2007 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የኤሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 202963 በቀን 29-10-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታውም የስር ፍ/ቤት የ12 ወር ውዝፍ ደሞዝ ለከሳሽ /ለአሁን ተጠሪ/ሊከፍለው ይገባል ብሎ ቢወስን ምንም ነገር ማሳመኛ ምክንያት ሳይጠቅስ ነው፡፡ ከሳሽ / የአሁን ተጠሪ/የአሁን አመልካች ንብረት መጥፋቱን ባልካደበትና የአሁን አመልካች ተጠሪ ወደ ስራ እንዳይመለስ ተከራክሮ እያለ አመልካች የተጠሪን ወደ ስራ መመለስ አልቃወምም ብሏል በማለት ወደ ስራ እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፡፡፡ ውዝፍ የዓመት ዕረፍት ለተቋረጠ የስራ ውል የሚከፈል እንጂ በህጉ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 77/5/ መሠረት ወደ ስራ እንድመለስ ለተወሰነ ሠራተኛ አይደለምና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የወሰደው የስንብት እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያ ተከፍሏቸው ወደ ስራ

www.abyssinialaw.com

ይመለሱ የመባሉን አግባብነት ከሰበር ውሳኔ መ.ቁ.106371 አንፃር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስ ተሰጥቶበታል፡፡

የአሁን ተጠሪ በቀን 14 12 2007 በተፃፈ መልስ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ቅሬታና ሙሉ ሃሳብ እንዲሁም የተያዘው ጭብጥ በዚህ ችሎት የሚታይ ስህተት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 183802 በቀን 22-3-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እና ወደ ስር ፍ/ቤት በተመለሰው ላይ የአሁን አመልካች በወቅቱ ይግባኝ ያላለበት በመሆኑ አሁን እንደ ቅሬታ ልያነሳ አይችልም፡፡ አመልካች የአሁን ተጠሪን የዓመት ፋቃድ 76 ቀን መሆኑንን አልካደም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይሁንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካችም በቀን 29/12/2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የቀረበውን አቤቱታ በማጠንከር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 183802 ወደ ስር ፍ/ቤት በውሳኔ የመለሰው የይርጋን ጉዳይ ጭብጥ ይዞ በመሆኑ ይርጋን በበተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ አይደለምና አሁን ቢነሳ ስህተት አይደለም፡፡ ተጠሪ ጥፋት መፈፀሙ እየታወቀ ወደ ስራ እንዲመለስ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ልታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በዚሁ መሠረት መዝገቡን እንደመረመርነው ክርክሩ የጀመረው ከኦሮሚያ ክ/መ/የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ አቶ ጨመዳ መገርሳ ያቀረበው ክስ በተከሳሽ የአምቦ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ዩኒየን ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳለ ያለምንም ጥፋት በሕግ ወጥ መንገድ ከሥራ ስላሰናበተኝ ወደ ኪራዩ እንዲመልሰኝ ካልሆነ ከሕግ ውጭ ከስራዬ ያሰናበተኝ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈለኝ የሚገባ ክፍያዎች እንዲከፍለን በማለት አቅርቧል፡፡ ተከሳሽም/ የአሁን አመልካች/ በሰጠው መልስ ከሳሽ የሥራ ድርሻውን የጥበቃ ስራ ባግባቡ ባለመወጣቱ በ29-11-2005 ዓ.ም የተሽከርካሪ ሞተርም ስለተወሰደና በተከሳሽ መ/ቤት ላይ ጉዳቱ ስላደረሰ ከስራ ተሰናብቶአልና የስራ ውሉ የተቋረጠው ህጋዊ ነውና ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከራክሏል፡፡

የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤትም በመ.ቁ. 35655 አከራክሮ በቀን 7-5-2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ይርጋን በተመለከተ ጥፋት መፈፀሙ ከታወቀበት ከቀን 29-11-2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሉ መቋረጡን ደብዳቤ እስከተፃፈበት ቀን 8-1-2006 ዓ.ም ድረስ ሲቆጠር 31 የስራ ቀናት /ሆኗል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሠረት በይርጋ የታገደ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ጥፋት ተፈፅሞ ከሥራ ማሰናበት ከሚገባበት ጊዜ ካለፈ በኃላ ተከሳሽ ከሳሽን ከሥራ ያለማስጠንቀቂያ ያሰናበተው በመሆኑ ህገ ወጥ ነው ብሎ ከሳሽ ወደ ስራ እንዲመለስና የደሞዝ መክፈያ ከተቋረጠበት ጊዜ ደምሮ ውዝፍ እንዲከፈለው በማለት ወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

የምዕ/ሸዋ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 02963 በቀን 4-6 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 183802 በቀን 22-8-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት አጣርቶ እንዲወሰን በውሳኔ የመለሰለት መሆኑን ገልፃ የሰጠው ፍርድ ግራና ቀኝ ተከራካሪዎች ይግባኝ ባይ /ከሳሽ/ ወደ ስራ ይመለስ በሚለው ውሳኔ ላይ ክርክር ወይም ተቋውሞ የላቸውም ሊከፍለው የሚገባ ውዝፍ ደሞዝና የአመት እረፍት ክፍያን በተመለከተ ውዝፍ ደሞዝ በማስላት የ12 ወራት ብር 22,080 የ76 ቀን የዓመት ዕረፍት ብር 4657.50 በአጠቃላይ ብር 26737.50 ለከሳሽ ይከፈለው ከሳሽ ወደ ሥራ ይመለስ ብሎ ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች አቤቱታ አቅርቦ በመ.ቁጥር 202963 አከራክሮ በቀን 29-10-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ አመልካች ለክርክሩ ተጠሪ የዓመት ዕረፍት እንደሌለው አልተከራከረም፡፡ በመሆኑም የዓመት ዕረፍትን በተመለከተ ሕጉ አዋጅ 377/96 የዓመት ዕረፍት ከሁለት ቀጣይ ዓመታት በላይ ማስተላለፍ አይችልም ይላል ይህ ማለት ተጠሪ ከ2006 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም የዓመት ዕረፍት ተደምሮ ሊከፈለው ይገባል በመሆኑም የተጠሪ 76 የዓመት እረፍት ቀናት ከህጉ ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡ ውዝፍ ደሞዝ በተመለከተ ወደ ስራ ይመለስ የተባለ ሠራተኛ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተከራክሮ ከተወሰነ የ12 ወር ውዝፍ ደሞዝ ስለሚከፈለው የስር የምዕ/ሸዋ/ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ፀንቷል፡፡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር ምክንያት የሆነው የክርክር ጭብጥ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 183802 በቀን 22-3-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመከራከሪያ ጭብጥ በመያዝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ የመለሰውና እንዲጣራ ጭብጥ ተይዞ የተመለሰውም የአሁን ተጠሪ ወደ ሥራ ይመለስ ወይስ አይመለስ በሚለውና አይመለስ ከተባለ ስለሚከፈለው ክፍያ በተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ከሥራ ማሰናበት ሕጋዊነት ወይም ሕገወጥነት እና የይርጋ ጉዳይ የጭብጡ አካል አይደሉም፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍርድ የታለፈን ጉዳይና ለከፍተኛው ፍ/ቤት ጭብጥ ያልሆነውን የይርጋ ጉዳይ አሁን በአቤቱታ ሊያንሱ የሚችሉበት የህግ መሠረት የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ ወደ ስራ ይመለስ ወይስ አይመለስ የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የተጠሪን ወደ ሥራ መመለስ የተስማማ መሆኑን አረጋግጦ የወሰነ መሆኑን ከተሰጠው ፍርድ ላየ መገንዘብ የሚቻል ነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎችን ከህግ ወጪ ከስራ የተሰናበተ ሠራተኛ ወደ ስራ ሲመለስ ሊከፍሉት የሚገቡ ክፍያዎች የዓመት እረፍትና ያልተከፈለ ውዝፍ ደሞዝን በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ እና አንቀጽ 79/5/ መሠረት ተሰልቶ የተወሰነው ክፍያ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ የሚደነግገው የአሁን አመልካች እንደሚከራከረው ውዝፍ ያልተከፈለ ደሞዝ ከሥራ ስለተሰናበተ ሰራተኛ የሚከፈል ሳይሆን ወደ ሥራ እንዲመለስ ለተወሰነበት ሰራተኛ ነው፡፡ ውሳኔውም ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ወደ ስራው ይመለስ ውሳኔ ከፀና እስከ አንድ አመት ውዝፍ ደሞዝ እንደሚከፈል ይገልፃል፡፡ የአመት ፍቃድ ክፍያንም በተመለከተ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንድ 79/5/ የዓመት እረፍት ከሁለት ቀጣይ ዓመት በላይ እንጅ እስከ ቀጣይ ሁለት ዓመት ማስተላፍን የሚከለከል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከህግ ወጪ ከስራ የተሰናበተ መሆኑን አረጋግጦና የተጠሪ"ን ወደ ሥራ መመለስ የአሁን አመልካች የተስማማበት መሆኑን በማየት መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ እና 79/5/ መሠረት ወደ ሥራ ለሚመለስ ሠራተኛ የሚከፈለውን ያልተከፈለ ውዝፍ ደሞዝና የዓመት ዕረፍት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35655 በቀን 7-5 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 02963 በቀን 4-6-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 202963 በቀን 29-10-2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ውጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.117076

ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ተብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች**፡- በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ነ/ፍጅ ብሩክ ታፈነ ቀረቡ ወክልና አያያዝ

**ተጠሪ**፡- አቶ ዮሐንስ ብዙነህ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብት ክፍያ ጥያቄን አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ከሳሽ በ14/02/2007 ዓ.ም. ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ17/08/2005 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ብር 4,699 እየተከፈላቸው በሳይት መሀንዲስነት በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት የስራ ውላቸውን ከሕግ አግባብ ውጪ ያቋጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸው እና ተዛማጅ ክፍያዎች አግባብነት ባላቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች መሰረት በድምሩ ብር 77,219 (ሰባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺህ) እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ08/03/2007 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሽ የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካስቀደመ በኃላ በፍሬ ጉዳዩ ረገድም የስራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እና በየሶስት ወሩ የሚታደስ መሆኑን፣እያንዳንዱ ወገን የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል በውሉ የተመለከተ መሆኑን፣ውሉ የተቋረጠውም ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሱ በርካታ ጥፋቶችን መፈጸማቸውን ተከሳሽ ገምጋሚ ቡድን ወደ ቦታው በመላክ በማረጋገጡ መሆኑን በመግለጽ ክሱ

www.abyssinialaw.com

ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የመቃወሚያ ነጥቡን በብይን አልፎ እና በፍሬ ጉዳዩ ላይ ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የስራ ውሉ የኮንትራት ውል መሆኑን፣የስራው ባህርይም የሚያልቅ መሆኑን እና ከሳሽ ስራቸውን በአግባቡ እንደማያከናውኑ የተከሳሽ ምስክሮች ያስረዱ መሆኑን ገልጾ የስራ ውሉ በሕግ አግባብ የተቋረጠ በመሆኑ ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሽ የሚከፍለው ክፍያ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ ያሰናበተው ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ከሳሽ የስራ መሪ ስለመሆናቸው ተከሳሽ ድርጅት በማስረጃነት ያቀረበው የስራ መዘርዝርም ሆነ የስራ ውል የሚያረጋግጡ ባለመሆኑ በተከሳሽ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በስር ፍርድ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ መሆኑን፣የስራ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ስለመሆኑ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 10 (1) ድንጋጌ መሰረት ያላስረዳ መሆኑን እና በከሳሽ ተፈጽመዋል የተባሉት ጥፋቶቸ በአዋጁ አንቀጽ 28 (1) ስር የሚሸፈኑ ካለመሆኑም በላይ ተከሳሽ ድርጅት ለእነዚህ ጥፋቶች እርምጃ ሲወስድ የነበረ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር አለመኖሩን ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት የወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ በስር ከሳሽ የተጠየቀውን የክፍያ ዓይነት እና መጠን አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመመለስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው የስራ መሪ ናቸው በማለት አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የማጣቱን አግባብነት ከተጠሪው የስራ መዘርዝር አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት የተስተናገደው አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው እና ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ተጠሪው ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት ሊስተናገድ የሚገባው አይደለም በሚል አመልካች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም?

www.abyssinialaw.com

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት የተስተናገደው አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው እና ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ተከራክረዋል፡፡በመሰረቱ አመልካቹ ይህንን የክርክር ነጥብ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊያቀርብ የቻለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጭብጥነት ይዞ ውሳኔ ያሳረፈው በዚህ የክርክር ነጥብ ላይ ጭምር በመሆኑ ነው፡፡ተጠሪው የስራ መሪ አይደሉም ተብሎ በወረዳ ፍርድ ቤት በተሰጠው ብይን ላይ አመልካች በወቅቱ ያቀረበው ይግባኝ ሳይኖር ተጠሪው ባቀረቡት አቤቱታ ሳቢያ አመልካች ይህንን የክርክር ነጥብ በክልል ሰበር ደረጃ ማንሳቱ ስነ ስርዓታዊ አይደለም የሚሉ ከሆነ ተጠሪው የዚህ ዓይነት መከራከሪያ ማቅረብ የነበረባቸው በክልሉ ሰበር ችሎት እንጂ በዚህ የሰበር ደረጃ አይደለም፡፡የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ አቅርቦ የተከራከረ አንድ ተከሳሽ ወገን መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎበት ነገር ግን ክርክሩን በሚሰማው ፍርድ ቤት በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ተጠቃሚ ከሆነ አቅርቦት የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ብቻ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚቸልበት አግባብ ካለመኖሩም በተጨማሪ ከሳሽ ወገን ለበላይ ፍርድ ቤት በሚያቀርበው ይግባኝ እና አቤቱታ ላይ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገበትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተጨማሪ መከራከሪያነት ከማቅረብ የሚከለክለው ነገር ባለመኖሩ ተጠሪው የስራ መሪ ናቸው የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ አንስቶ ሊከራከር የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ተጠሪው ያቀረቡት መከራከሪያ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጁ አንቀጽ 2 ስር የተመለከቱትን ሳይጨምር በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ላይ ስለመሆኑ በአንቀጽ 3 (1) ስር የተደነገገ ሲሆን የአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚደረጉበት የስራ ውል ተቋቁሟ የሚባለውም ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት በተስማማ ጊዜ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2 (3) እና 4 (1) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡

በሌላ በኩል የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈጻሚ ከማይሆንባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የስራ መሪን አስመልክቶ በሚደረግ የስራ ውል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 (በአዋጅ ቁጥር

www.abyssinialaw.com

494/1998 እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 3 (2 ) (ሐ) ስር የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ በተሰጠው ትርጉም መሰረትም የስራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሰሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሰረት የስራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣት እና የማስፈጸም ከነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሰራተኛን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣የማሰናበት፣የመመደብ ወይም የስነ ስርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውን እና የሚወስን ግለሰብን የሚመለከት እና እንዲሁም እነዚህን የስራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሰሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሰሪው ሊወስድ ስለሚገባው እርምጃ በራሱ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የሕግ አገልግሎት ኃላፊንም የሚጨምር ነው፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ተጠሪው የስራ መሪ ስለሆኑ ጉዳያቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና በስራ ክርክር ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት አመልክች ያቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ ያልገለጸ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ችሎት ግን በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ሳይቀበል የቀረው የተጠሪው የስራ መዘርዝር እና የግራ ቀኙ የስራ ውል ይዘት ተጠሪው የስራ መሪ ናቸው የሚያሰኝ የስራ ኃላፊነት የተሰጣቸው መሆኑን አያመለክትም በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በመሰረቱት ክስ ላይ የስራ መደባቸው ሳይት መሀንዲስ እንደሆነ አድርገው የገለጹ ቢሆንም በቀጣይ የክርክር ሂደት ሳይት መሀንዲስ ሳይሆኑ አመልካች ድርጅት በሆሳዕና ከተማ የሚያከናውናቸውን አራት ፕረጀክቶች በበላይነት የመምራት የስራ ኃላፊነት ያላቸው የፕሮጀክት መሀንዲስ መሆናቸው ተረጋግጦአል፡፡ተጠሪነታቸውም ለአመልካች ድርጅት የኮንስትራክሽን መምሪያ መሆኑን የስራ መዘርዝራቸው ያመለክታል፡፡ የተጠሪው የስራ መዘርዝር በስሪ መሪ የሚከናወኑ ተግባራትን የማከናወን የስራ ኃላፊነት  እንዳላቸው የሚያመለክት አይደለም የሚባል ካለመሆኑም በተጨማሪ በድርጅቱ የስራ መመሪያ መሰረት ተጠሪው የፕሮጀክቶቹ ማኔጅመንት ኮሚቴ የበላይ ኃላፊ በመሆን የሰው ኃይል፣የፋይናንስ፣የንብረት ግዢ እና አስተዳደር ጉዳዮችን በበላይነት የማስተዳደር እና የመምራት፣የባንክ ሂሳብ የማንቀሳቀስ፣ ለፕሮጀክቶቹ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል የመቅጠር፣ማገድ እና የማሰናበት ስራዎችን ጨምሮ በስራ መሪ የሚከናወኑ ናቸው የተባሉትን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት የነበራቸው ስለመሆኑ አመልካች በሰበር አቤቱታው ላይ በዝርዝር ላቀረበው ክርክር ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት ግልጽ የማስተባበያ ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡አንድ ሰራተኛ የስራ መሪ ሆኖ የሚቆጠረውም የሚያከናውናቸው ተግባራት እንደየድርጅቱ የስራ ፀባይ  እየታየ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 (በአዋጅ ቁጥር 494/1998 እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 3 (2 ) (ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በማከናወን ተጠሪነታቸው ለአመልካች ድርጅት የኮንስትራክሽን መምሪያ ሆኖ ድርጅቱ በሆሳዕና ከተማ የሚያከናውናቸውን አራት ፕሮጀክቶች

www.abyssinialaw.com

በበላይነት የሚመሩ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ደግሞ ተጠሪው ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት የስራ መሪ ናቸው ሊባሉ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡የስራ መሪ ከሆኑ ደግሞ ተጠሪው ያቀረቡት ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት ሊስተናገድ የሚገባው አይሆንም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርገው ተጠሪው ያቀረቡትን ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት በማስተናገድ በስር ፍርድ ቤቶች በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29077 በ02/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ፣በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17538 በ30/07/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 65144 በ01/12/2007 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በሙሉ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪው የስራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት እና በስራ ክርክር ችሎት የተስተናገደው በአግባቡ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117517

ቀን ጥር 30/2008ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ሬድ ፎክስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወ/ት ጀላኔ ጌታቸው - ከጠበቃ መስታውት አሸናፊ ጋር - ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ሲጀመር ከሳሽ የነበረችው ተጠሪ ናት፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው የስራ ውል ከሕግ ውጪ አቋርጠዋል በማለትነው፡፡ በዚህ መሰረትም ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፈላት ጠይቃለች፡፡

በአመልካች ድርጅት ተመድቤ የምሰራበት ሥራ ከኬሚካል ንኪኪ ያለው በመሆኑ ለሰራተኛው በየጊዜው ምርመራ ይደረጋል፡፡ በመጀመሪያ የተወሰደው የደም ናሙና ውጤቱ የደም ጥራት መጠን በታች በመሆኑ ለሶስት ወር ከኬሚካል ጋር ግንኙነት በሌለበት ሥራ እንዲያዛውር በባለሙያ የተሰጠው አስተያየት ከአንድ ወር በላይ በመደበቅ ውጤቱ አውቄ ራሴን እንዲጠናቀቅ አልቻልኩም፡፡ ወደ ሌላ ስራ አላዘወረኝም፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የደም ናሙና ተወስዶ ውጤቱ እንዲያሰውቀኝ ብጠይቅም ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 32/1/ለ/ መሰረት ከመስከረም 5 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ስራዬን ለማቋረጥ ተገድጃሎህ፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕገ ወጥ ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እና ማስረጃዎች እንዲሰጣት እንዲወሰንላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የአሁኑ አመልካች መከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በገዛ ፍቃድዋ ሥራውን ያቋረጠች እንጂ በአመልካች ምክንያት ወይም በህገ ወጥ መንገድ አይደለም፡፡ የመጀመሪያ

www.abyssinialaw.com

ምርመራ ውጤት መሰረት ወደ ሌላ ስራ ተዛውራ እንድትሰራ ተደርገዋል፡፡ በሁለተኛ የደም ናሙና ውጤቱ ወደ ኖርማል የተመለሰ በመሆኑ ወደ ቀድምዋ ስራ ተመልሳለች፡፡ ከተሰናበተች በኋላ የ3ኛው የደም ናሙና ምርመራ ውጤት ከጤነኛ ደም ሬንጅ ውስጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የ30 ቀን ማስጠንቀቅያ ሳትሰጥ የለቀቀች ስለሆነ የ30 ቀን ደመወዝ በመቀነስ እንድትሰናበት የተደረገው፡፡ ስለሆነም የቀረበው ክስ የህግ መሰረት የለውም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መልሳቸውን አቅረበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኋላ የስራ ወሉ የተቋረጠው ከሕጉ ውጭ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 59,103 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት ስላላገኘ ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ነሀሴ 21 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፈው ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟአል የሚልበትን ምክንያት በመግለፅ አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡ አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪ እንዲቀርብ በማድረግ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርቧል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስሕተት ነው የሚልበት የስራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ እንጂ በአመልካች አይደለም፡፡ በመጀመሪያው በተደረገው ምርመራ ውጤት ዝቅተኛ የነበረ ቢሆንም ከዚያ በኋላ የተደረጉት ምርመራ ውጤት ጤነኛ መሆኑን በመረጋገጡ አመልካች ለተጠሪ አደጋ የሚጥል ሁኔታ እንዲትሰራ አላደረገም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 12 ግዴታው አልተወጣም የሚያሰኝ ሁኔታ ሳይኖር ሕገ ወጥ መባሉ አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡ በተጠሪ በኩል ደግሞ ስራውን ለመቋረጥ የተገደድኩት ለጤነንቴ ስል ነው፡፡ የምርመራ ውጤት ከአንድ ወር በላይ በመደበቅ፤ ከኬሚካል ነፃ የሆነ ስራ ለሶስት ወር እንድሰራ በባለሙያ የተገለፀው ባለመፈፀሙ፤ ሁለተኛው ምርመራ ውጤት በፅሑፍ ብጠይቅም ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ ይህ ደግሞ አመልካች ግዴታውን አልተወጣም በማለት የተሰጠ ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

በአመልካችና ተጠሪ የተደረገው የስራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት መብትና ግዴታ ያቋቁማል፡፡ በሕጉ አንቀጽ 12 የአሰሪው ግዴታ በአንቀጽ 13 ደግሞ የሰራተኛው በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሕገ ወጥ ድርጊት የተባሉት የአሰሪና ሰራተኛ በቅደም ተከተል በአንቀጽ 14 /1/ እና 14/2/ በዝርዝር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ የአሰሪው ግዴታ ከተገለፁት 12/4/ ከስራው ጋር

www.abyssinialaw.com

በተያያዘ ሰራተኛውን ደኅንነትና ጤንነት ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ሁሉ የመውሰድና እነዚሁንም እርምጃዎችን በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎችን መመሪያዎች የመከተል በአሰሪው ግዴታ ላይ የጣለ ነው፡፡ በሌላ በኩል አሰሪውና ሰራተኛው ሕገ ወጥ ድርጊት ተብለው ከተገለፁት ውስጥ በሕጉ አንቀጽ 14/1/ሠ/ በአሰሪው ሰራተኛውን በሕይወቱ ላይ አደጋ ሊያደርስበት በሚችል አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ ሕገወጥ ድርጊት መሆኑን የተመለከተ ነው፡፡አሰሪው ግዴታውን ካልፈፀመና ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀሙ ከተረጋገጠ ሰራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉ ማቋረጥ በቂ ምክንያት ይሆናል በማለት በአንቀጽ 32/1/ለ ይደንግጋል፡፡ ይህን ከተረጋገጠ ደግሞ ሰራተኛው በአዋጁ መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን ከአሰሪው የማግኘት መብት አለው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ክርክር በአንቀጽ 32/1/ለ የተመለከቱትን ሳይሟላ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ ሊሻር ይገባል ሲል፤ በተጠሪ ደግሞ በማስረጃ የተረጋገጠና በአግባቡ የተወሰነ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ እንደሚያመለክተው አመልካች ለሰራተኞቹ በየሶስት ወር ምርመራ እንደሚያደርግ ግልፅ ነው፡፡ እዚህ ላይ አከራካሪ የሆነው ውጤቱ ከሚመለከተው አካል በወቅቱ ማምጣት፤ እንደመጣም በጊዜ መግለፅ እና በውጤቱ መሰረት ተገቢውን እርምጃ መውስድ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በፍሬ ጉዳይ የማጣራትና የየመመዘን ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የተጠሪ የምርመራ ውጤት እንድታውቅ የተደረገው ዘግይቶ መሆኑ፤ ከኬሚካል ንኪኪ ነፃ በሆነ ስራ ለሶስት ወር እንዲሰሩ አለማድረጉ እና ውጤት በወቅቱ ሂዶ አለማምጣት የተደጋገመ ድርጊት መሆኑን የአመልካች ክሊኒክ ሓላፊ የሰጡት የምስክርነት ቃል ውጤት ሂዶ በወቅቱ የማይመጣው ትራንስፖርት የለም እየተባሉ እንደሆነ፤ የተጠሪ የምርመራ ውጤት መሰረት በሌላ ስራ እንዲመደቡ የሰጡት ምክር ተቀባይነት እንደለገኘ፤ የነርቭ ችግር እንደሚያስከትል፡፡ የተጠሪ የደም ናሙና ሶስት ተወስዶ ዝቅተኛ ስለሆነ ወደ ጤነኛ ተመልሰዋል ለማለት የሚቻለው ሶስት ጊዜ ምርመራ ከተደረገ በኂላ የሚረጋገጥ እንጂ በአንድ በሁለት የተደረገ ምርመራ ውጤት ጤነኛ ነው ለማለት እንደማይቻል ሙያዊ ምስክርነታቸው ሰጥተዋል፡፡

አመልካች ምርመራ እንዲደረግ ማድረጉ ብቻ በቂ ነው ግዴታውን ወጥቷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ከምርመራ በኂላ በተገኘው ውጤት መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ከመውሰድ ላይ ነው፡፡ በትራንስፖርት ምክንያት በወቅቱ አለማምጣት፤ ከመጣም በኂላ በባለሙያ የተሰጠ ምክር ተግባራዊ አለማድረጉ ግዴታው አለመወጣቱና ለጉዳዩ ትኩረት ያለሰጠው መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት ያለበት ሆኖ ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 15958 በቀን 11/09/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠ ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 168399 በቀን 29/11/2007 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ከዚህ በፊት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስተዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 119734

የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ተብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች፡-** ይርጋ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፡-**

1. አቶ ብዙነህ መኮንን
2. አቶ ሻምበል አሰፋ
3. አቶ ረድኤት መሐመድ

} ጠበቃ እስጢፋኖስ ተስፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብት እርምጃን በመቃወም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በአዳማ ልዩ ዞን በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾቹ በ16/10/2007 ዓ.ም. ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከሳሾቹ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከተለያየ ጊዜ ጀምሮ በተለያየ የስራ መደብ የተለያየ መጠን ያለው ደመወዝ እየተከፈላቸው በመስራት ላይ እያሉ የድርጅቱ ባለቤት ተከሳሽ ድርጅትን ሸጠው ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሾቹ ሌላ ስራ ሳይሰጥ ወይም ተገቢ ክፍያዎችን ሳይከፍል አላግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የስንብት እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ሕገወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸው እና ተያያዥ ክፍያዎች በአዋጁ መሰረት ተሰልቶ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ02/11/2007 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሾቹ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ድርጅቱ በመሸጡ እና የሚመደቡበት ሌላ የስራ ቦታ ባለመገኘቱ መሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ከሳሾቹ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ድርጅቱ በመሸጡ ምክንያት ቢሆንም ተከሳሽ ደርጅት ይህንኑ በመግለጽ ለከሳሾቹ አስቀደሞ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ከዛሬ ጀምሮ ስራ የለም በማለት ከሳሾቹን በቀጥታ ማሰናበቱ ሕገወጥ መሆኑን ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት ለእያንዳንዱ ከሳሽ በውሳኔው ላይ ተለይቶ በተገለጸው መጠን ሕገ ወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸው እና ተያያዥ ክፍያዎችን ከአስር በመቶ የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በትዕዛዝ በማጽናታቸው የሶስቱም ስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ድርጅት ተሸጦ ንብረትነቱ ለዘለቄታው ወደ ሌላ ሰው መተላፉ እና ተጠሪዎቹን ወደ ሌላ ስፍራ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪዎቹ የማስጠንቀቂያ እና የስንብት ክፍያ የሚያገኙ ከሚሆን በቀር ለተሸጠ ድርጅት ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ የካሳ ክፍያ እንዲከፈላቸው የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ ጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቹ ከስር ጀምሮ የሚከራከረው ተጠሪዎቹ ይሰሩበት የነበረው ድርጅት የተሸጠ እና ለሶስተኛ ወገን የተላለፈ በመሆኑ ምክንያት የስራ መደባቸው የተሰረዘ በመሆኑ ተጠሪዎቹ የተሰናበቱት በሕግ አግባብ መሰረት ነው በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በመሰረቱ ተከሳሽ ድርጅት "ይርጋ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" በሚል የሚታወቅ ሲሆን የተሸጠውም ይኸው ማህበር በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ንብረቶች መካከል አንዱ የሆነው እና ተጠሪዎቹ ሲሰሩበት የነበረው በአዳማ ከተማ የሚገኝ መጋዘን ነው፡፡

በመሆኑም የተሸጠው ተከሳሽ ድርጅት በአጠቃላይ ወይም በሙሉ አይደለም፡፡በመሰረቱ የስራ ውል የሚቋረጠው በአሰሪው ወይም በሰራተኛው አነሳሽነት ወይም በሕግ በተደነገገው መሰረት ወይም በሕብረት ስምምነት ወይም በተዋዋይ ወገኖች በሚደረግ ስምምነት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 23 (1) ስር የተደነገገ ሲሆን የአንድ ድርጅት ከሌላ ጋር መቀላቀል ወይም መከፋፈል ወይም የባለቤትነት መብት ወደ ሌላ መተላፍ የስራ ውልን የማቋረጥ ውጤት

www.abyssinialaw.com

የማይኖረው ስለመሆኑም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር (2) ስር ተመልክቷል፡፡አመልካች የድርጅቱ አካል የሆነውን መጋዘን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ በሚያስተላልፍበት ጊዜ የሰራተኞቹ የቅጥር ውል ከገዥው አካል ጋር የሚቀጥልበትን አግባብ ማመቻቸት ወይም ለሰራተኞቹ በሕጉ የተመለከተውን ተገቢ ክፍያዎች ከፍሎ ማሰናበት ሲገባው ድርጅቱ የተሸጠ በመሆኑ ምክንያት የስራ መደባቸው ተሰርዞአል የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪዎቹን ማሰናበቱ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡የመጋዘኑን መሸጥም ከስራ መደብ ስረዛ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡ከመሰረቱ የመጋዘኑ በሽያጭ መተላለፍ የስራ ውሉን በማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ባለመሆኑ የመጋዘኑ መሸጥ ሰራተኞቹን በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት እንደሚያስችል አድርጎ አመልካች ያቀረበው ክርክርም ሆነ በዚህ ረገድ በሰበር አጣሪ ችሎት ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረጉ ናቸው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡አመልካቹ የወሰደው የስንብት እርምጃ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 23 (2) ድንጋጌን በቀጥታ የሚቃረን ከሆነ ደግሞ የስንብት እርምጃው ሕገ ወጥ የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቹ የተወሰደውን የስራ ስንብት እርምጃ ሕገ ወጥነት በማረጋገጥ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪዎቹ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ስሕተት ተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90108 በ27/01/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 21815 በ23/02/2008 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 231434 በ02/03/2008 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
3. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91780 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዙህ መዝገብ በ09/03/2007 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

# ፍትሐ ብሔር

# ሥነ - ሥርዓት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 102056

ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን ካሳዬ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰረት ግርማ - ተወካይ ኃይሉ ቦሰት ቀረቡ

2. አቶ ሳሙኤል ካሳዬ
3. አቶ ኢሳያስ ካሳዬ
4. ወ/ሮ ሜላት ካሳዬ

} ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይለቀቅልኝ ጋር ተያይዞ የተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበውን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ በ17/04/2006 ዓ/ም የተፃፈ ሁኖ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፣ የአሁኑ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረው በመ/ቁጥር 24515 በ16/10/2002 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ከእናቴ ከወ/ሮ ፀሐይ ገብሬ በውርስ ሊተላለፍልኝ በሚገባ ንብረት ላይ የተሰጠና መብቴን የነካ ነው በሚል ምክንያት ውሳኔ ተነስቶ የክርክሩ ተካፋይ ልሆን ይገባል የሚል ሲሆን የአሁኑ ሥር ፍርድ ቤትም ለፍርዱ መሰረት የሆነው ንብረት ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ ነው በሚል ድምዳሜ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በመዝገቡ ሊስተናገድ እንደማይችል፣ ሆኖም አመልካች መብታቸውን ቀጥታ ክስ አቅርበው ማስጠበቅ የሚችሉ መሆኑን ጠቅሶ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 ያሉት ተጠሪዎች በአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ላይ የውርስ ንብረት ይለቀቅልን ክስ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳው ይዞታና ንብረት ለከሳሾች እንዲለቀቅላቸው መወሰኑን፣ ይህ ውሳኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቶ የነበረ ቢሆንም የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በመ/ቁጥር 11115 በ03/03/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት

www.abyssinialaw.com

ያለበት ነው በሚል ምክንያት ሙሉ በሙሉ በመሻር ክርክር የተነሳበት ይዞታና ንብረት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን፣ ይህ ውሳኔ በመሰጠቱ ምክንያትም 1ኛ ተጠሪ የተወሰደባቸው ንብረት እንዲመለስላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ባሉት ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ቤት ፈርሶ ስለነበር በአሁኗ 2ኛ ተጠሪ ስም ያለው ቤት ተሸጦ ለ1ኛ ተጠሪ ግምቱ እንዲከፈል ጨረታ እንዲወጣ አድርጎ በሂደት እንደሚገኝ፣ የወረዳው ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ አፈጻጸሙን እየመራ ያለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የሰጠውን ውሳኔ መነሻ አድርጎ ስለመሆኑና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚገባው ደግሞ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት መሆኑን ጠቅሶ የአሁኑ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት ስርዓቱን የተከተለ አይደለም በሚል ድምዳሜ የሥር ፍርድ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን ተገቢ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የወረዳው ፍርድ ቤት እያስፈጸመ ያለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የሰጠውን ውሳኔ ሁኖ እያለና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ክርክሩ መኖሩን አመልካች ባላወቁበት ሁኔታ እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪ አፈጻጸም ሂደት ላይ ስለመኖሩ ክርክሩ እያሳየ ፍርዱ ተፈጽሟል ተብሎ የፍርድ መቃወሚያው በወረዳው ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉም ሆነ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ በወረዳ ፍርድ ቤት የፍርድ መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም በማለት መወሰኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ አላማ ውጪ የሆነ እና የአመልካችን የውርስ መብት የጎዳ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና የአሁኑ ተጠሪ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 የተጠቀሱት ተጠሪዎች የወ/ሮ ጸሐይ ገብሬ ወራሽ መሆናቸውን፣ የአሁኑ አመልካች ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከወ/ሮ ጸሐይ ገብሬ በውርስ የሚተላለፍልን ቤትና ይዞታ በ1ኛ ተጠሪ ከሕግ ውጪ ተይዞ ይገኛል በሚል በተጠሪዋ ላይ ክስ መስርተው በወረዳው ፍርድ ቤት ንብረቱ እንዲለቀቅላቸው ተወስኖላቸው በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፀንቶ የነበረ ቢሆንም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አከራካሪው ቤትና ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ነው ተብሎ መወሰኑን፣ በዚህ ሂደት ግን የስር ከሳሾች በ1ኛ

www.abyssinialaw.com

ተጠሪ ቤት ላይ ጉዳት አድርሰው/አፍርሰው/ ስለነበር ተጠሪዋ የፈረሰው ቤታቸው ግምቱ እንዲከፍላቸው አፈጻጸሙን በወረዳው ፍርድ ቤት ቀጥለው ባሉበት ሁኔታ የአሁኑ አመልካች በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ የውርስ መብቴን የነካ ነው በሚል የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡና ተቀባይነት ያጡ መሆኑን ነው፡፡

የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልፅ የሚያሳየው አመልካች የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡበት ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የተሰጠና ፍርዱ ከተፈፀመ በኃላ የቀረበ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች መቃወሚያው የቀረበበት ፍርድ አልተፈፀመም፣ በሂደት ላይ ያለ ነው የሚሉት 1ኛ ተጠሪ ቤታቸው በሌሎች ተጠሪዎች የፈረሰባቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት የቤቱን ግምት ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ አድርጎ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ አቤቱታ ለማስፈፀም በ28/04/2006 ዓ/ም የሰጠውን ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከወረዳው ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ተመልክተናል፡፡

በእግርጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ የሚስተናገደው ለመቃወሚያው መነሻ የሆነውን ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት ነው፡፡ አቤቱታው የሚጣራው ወይም የሚስተናገደው ማንኛውም ክስ በሚስተናገድበት ሥርዓት በመሆኑ እና ይህም ማስረጃ መስማትንና ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ መስጠትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም ታህሳስ 17 ቀን 2006 ዓ/ም ለወረዳው ፍርድ ቤት የቀረበው የተቃዋሚ ማመልከቻ ወይም ክርክር በማስረጃ ተጣርቶ የሚወሰን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የፍርድ መቃወሚያ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡ የሰበር ችሎቱ ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ የማጣራትም ሆነ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን የለውም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ፍሬ ነገርን የሚያጣራበት ወይም የማስረጃ ምዘናን ክርክርና ቅሬታ የሚመለከትበት ሥልጣን የሌለው መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ))፣ ከክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64 (2(ሐ)) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 31 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም በሕግ አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመውን ስህተት ለማረም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ)) ከክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64(2(ሐ)) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 31 ድንጋጌዎች መሰረት ስልጣን በተሰጠው በክልሉ ሰበር ችሎት የሚታይ አይሆንም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ክርክሩ የተጀመረው በወረዳው ፍርድ ቤት እንደሆነ መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ለዚሁ ፍ/ቤት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የተሻረው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡፡ በመሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍርድ መቃወሚያ መነሻ አይቶ እንዲሽር ማድረግ ከፍርድ ቤቶች የስልጣን ተዋረድ አንጻር ሲታይ ያልተፈለገ ውጤትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍርድ መቃወሚያውን እንዲመለከትና ዳኝነት እንዲሰጥ ማድረግ የሚመረጥ አይሆንም፡፡ በሌላ

www.abyssinialaw.com

በኩል ግን ተቃዋሚው መብታቸውን የሚያስከብሩበትን መድረክ ሊያገኙ የሚገባ መሆኑ ሲታይም ይኸው ሊታይላቸው የሚገባው በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አይደለም፡፡ የክርክሩ ሂደት እንደሚያሳየው ከወረዳው ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተቃዋሚ የክርክሩ ተካፋይ አልነበሩም፡፡ ከዚህ የተነሳም በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተቃዋሚውን የሚያስገድድ አይሆንም፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተቃዋሚ አለኝ የሚሉትን መብት ለማስከበር ይችሉ ዘንድ መብቴን የሚነካ ውሳኔ ሰጥቷል በሚሉት ፍርድ ቤት አቤቱታቸውን ከሚያቀርቡ ወይም መብቴን ተጋፍቶአል በሚለው ሰው ላይ በስሙ ቀጥታ ክስ መመስረት መብታቸውን ከሚያስከብሩ በስተቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ለወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ስርዓቱን የጠበቀ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በሌሎች ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349(1) መሰረት ያቀረቡት አፈጻጸም በሂደት ላይ መሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካችን የፍርድ መቃወሚያ እንዲያስተናገድ የሚያስችለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በዋናው ክርክር ላይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11115 የተሠጠው ውሳኔ የ1ኛ ተጠሪን በይዞታውና በቤቱ ላይ ሙሉ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ እስከሆነ ድረስ ይሄው መብታቸው የሚለወጥ መሆኑን አመልካች በቅድሚያ በቀጥታ ክስ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ከክርክሩ ሂደት እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር የሚነቀፍ ሁኖ ስላልተገኘ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በአደአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 24515 በ10/04/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.036604 በ19/09/2006 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 185034 በ4/10/2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች አለኝ የሚሉትን መብት በሌላ አግባብ ከማስከበር ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>**ት ዕ ዛ ዝ**</u>

በ24/10/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡ **መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 107838

ቀን 19/4/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- 1. አቶ ታከለ አርአያ - አልቀረቡም

2. አቶ አብርሃ ተክሉ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ደጀን ገ/እግዚአብሔር - ቀርበዋል

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች 1.አቶ ታከለ አረአያ 2.አቶ አብረሃ ተክሉ በቀን 23/3/2007 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 05504 አከራክሮ በቀን 11/2/2007 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታቸውም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት መጀመሪያ የቀረበው ክስ መጥሪያ ደርሶን ከቀረብን በኃላ በፍ/ቤቱ ክሱ እንዲሻሻል ታዞ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ሲንቀሳቀስ ግን የአሁን ተጠሪ (ከሳሽ) አድራሻችንን እያወቀ የሁመራ ቤት ሲታገድ መጥሪያ ሊሰጠን ሲችል በቤታችን ላይ መለጠፍ ሲቻል ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ መጥሪያውን በመለጠፍና በጋዜጣ ጥሪ ማስደረጉ ሆን ብሎና ተገቢ አለመሆኑን መገንዘብ ሲቻል የስር ፍ/ቤት በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልን ብለን ያቀረብነውን ማመልከቻ ውድቅ ማድረጉ ስህተት በመሆኑ ይታረምል የሚል ነው፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካቾች መጀመሪያ ክስ ሲቀርብባቸው ቀርበው መልስ የሰጡ ሲሆን በሌሉበት ይታይ የሚል ትዕዛዝ የተሰጠው ተጠሪ ክስ አሻሽሉ ተብለው መዝገቡ ከተዘጋባቸው በኃላ ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ ጊዜ አመልካቾች ከአካባቢው አልተገኙም ተብለው በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ እና በጋዜጣ ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ክርክሩ

www.abyssinialaw.com

በሌሉበት ተካሂዶ ውሳኔ የተሰጠውና አመልካቾች ይህንኑ ገልፀው ሲያመለክቱ ማመልከቻቸውን ውድቅ ማድረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን. 94-110 ጋር ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/7/2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች በአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.37304 የተወሰነልኝን ውሳኔ በመ.ቁ.08505 የአፈፃፀም መዝገብ ከፍቼ መጥሪያ ላለመቀበል ከተሰወሩ በኃላ ንብረታቸው ከታገደ ከ2 ወር በኃላ ቀርበው ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርጉ ሲጠየቁ በሌለንበት የተወሰነ ውሳኔ ነው በማለት በአፈፃፀም መዝገብ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን. 78 መሠረት አመልክተዋል እኔም ይህንኑ አንስቼ ተከራክሬያለሁ፡፡ መጀመሪያ መዝገቡ ክስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ አዞ መዝገቡን ዘጋው ይበሉ እንጅ የተዘጋ መዝገብ የለም፡፡ አመልካቾች በሚኖሩበት ሁሉ ፈልጌ በማጣቴ ለፍ/ቤቱ አመልክቼ መጥሪያው ተለጥፏል በጋዜጣም ጥሪ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ አቤቱታቸው ውድቅ ይሁንልን ብለው ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 16/8/2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሠረት መዝገቡን እንደመረመርነው ክርክሩ የጀመረው ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች (የከፍ/ፍ/ቤት ተከሣሾች) ለአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከሳሽ አቶ ደጀን ገ/እግዛብሄር በተከሳሾች (የአሁን አመልካቾች) ላይ በቀን 7/3/2005 ዓ.ም በተፃፈ ክስ አቅርቦብን እኛም ቀርበን ክርክር ከተጀመረ በኃላ ፍ/ቤቱ ከሳሽ ክስህን አሻሽል ተብሎ መዝገቡ ተዘጋ ከዚህ በኃላ መዝገቡ ሲንቀሳቀስ እኛ ያልሰማንና ከሳሽ የኛን አድራሻ እያወቀ ሆን ብሎ ላገኛቸው አልቻልኩም በማለት በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በመለጠፍና በጋዜጣ ጥሪ በማስደረግ ሲሆን ባለመስማታችን በሌለንበት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በሌለንበት መወሰኑን የሰማነው በቀን 6/8/2006 ዓ.ም በመሆኑና እንደሰማንም ቀርበን ያመለከትን ስለሆነ በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ እንድነሣልን በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪም (የከፍ/ፍ/ቤት ከሳሽ) የሰጠው መልስ የተከሳሾች ማመልከቻ የቀረበው ለፍርድ ቤቱ በመሆኑ እኔ መልስ እንድሰጥ አይጠበቅብኝም፡፡ ፍ/ቤቱ ከሳሽ ክሱን ያሻሽል ብሎ መዝገቡን ቢዘጋም በተለዋጭ ቀጠሮ ክሱ ተሻሽሎ የሚቀርብ እንጂ መዝገብ እንድዘጋ የሚያዝ ሥነ ሥርዓትም የለም፡፡ ተከሳሾቹ መጥሪያ እንዳይደርሳቸው ሆን ብለው ከአካባቢው በመሰወራቸው ተፈልገው በአድራሻቸው ስላልተገኙ መጥሪያውን ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ተለጥፏል ስለዚህ ማመልከቻቸው ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 08505 በቀን 21/9/2006 ዓ.ም በቀረበው ማመልከቻ ላይ የሰጠው ብይን ተከሳሾች ያቀረቡት ማመልከቻ ክርክሩ ተጀምሮ ክሱ እንዲሻሻል ከተደረገ በኃላ ከአካባቢው ቢሰወሩም ይኖራሉ በሚባልበት ቦታና ህዝብ

www.abyssinialaw.com

በሚሰበስብበት ቦታ ሁሉ በፍ/ቤት አጥር ግቢ እና በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው አልቀረቡም ተከሣሾች (አመልካቾች) ክሱ እንዲሻሻል የታዘዘ ቢሆንም በቀጣዩ የሚቀጥል ጉዳይ መሆኑን አያውቅም ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህ ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም በማለት ማመልከታቸውን አልተቀበልነውም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 05445 በቀን 10/10/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን. 337 መሠረት የሚያስቀርብ ሆኖ አልተገኘም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ. 05504 አከራክሮ በቀን 11/2/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ አመልካቾች የተሻሻለው ክስ ከመጥሪያ ጋር እንዲደርሳቸው በተደጋጋሚ ጊዜ ታዞ ከአካባቢው በመሰወራቸው ሌሎች የመጥሪያ አደራረስ ምርጫዎችን በመጠቀም አመልካቾች ሊመለከቱት ይችላሉ በተባሉ ግልፅ ቦታዎች እና በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ በመለጠፍና በጋዜጣ ቢጠሩም ስላልቀረቡ በሌሉበት መወሰኑ እና የስር ፍ/ቤት ማመልከቻቸውን በዚህ ሁኔታ ውድቅ ማድረጉ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ትዕዛዝና ብይን በማፅናት ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡

በዚህ ሰበር ችሎት የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች በመጀመሪያ ክስ ሲቀርብባቸው መጥሪያ ደርሷቸው ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክስ ያሻሽል ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ከተከፈተ በኃላ አመልካቾች በአካባቢው አልተገኙም በማለት መጥሪያ በፍ/ቤት ግቢ በመለጠፍና በጋዜጣ ጥሪ በማድረግ አልቀረቡም በማለት በሌሉበት የተወሰነው ተጠሪና አመልካቾች ጎን ለጎን በእርሻ እንቨስትመንት የተሠማሩ መሆኑ እየታወቀ በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ መለጠፉና በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው እየታወቀ በፍ/ቤት ቅጥር ግቢ መለጠፉና በጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አን 94-110 ካለው የመጥሪያ አሰጣጥ ድንጋጌና ከመጥሪያ አሠጣጥ አላማ ጋር ለመመርመር ነው፡፡ በተያዘው ጭብጥ መሠረት አመልካቾች መጀመሪያ በአሁን ተጠሪ ክስ ሲቀርብባቸው መጥሪያ አድርሷቸው ቀርበዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ (የሥር ፍ/ቤት ከሣሽ) ክሱን ያሻሽል ብሎ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ክሱ ተሻሽሎ መዝገቡ ሲከፈት ለአመልካቾች መጥሪያ ሊደርሣቸው ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾች አቤቱታ መጥሪያ ሣይደርሰን በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሣልን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት አመልካቾች መጥሪያ እንዳይደርሳቸው ተሸሽገዋል በሚልና መዝገቡ ተዘግቶ በሚቀጥለው ቀጠሮ ክርክሩ እንዲቀጥል ማወቅ ይችላሉ ሲል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተከሣሾች (የአሁን አመልካቾች) በሚቀጥለው ቀጠሮ ክርክሩ ይቀጥላል ለማለት የሚችሉት መዝገቡ ባይዘጋና ቀጠሮ ቢሰጥ እንጂ መዝገቡ ተዘግቶ ቀጠሮ ባልተሰጠበት የሚቀጥለውን ቀጠሮ ሊያውቁ የሚችሉበት መንገድ የለም፡፡ አመልካቾች መጀመሪያ መጥሪያ ደርሷቸው ቀርበው እያለ መጥሪያ እንዳይደርሳቸው የተሸሸጉ

www.abyssinialaw.com

ወይም መሰናክል ያደረገ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ተረድቻለሁ የሚለው ተጠሪ ከገለፁላቸው ውጪ በሌላ መንገድ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የተገለፀው ነገር የለም፡፡ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ጎን ለጎን የእርሻ ኢንቨስትመንት ሥራ ይሰራሉ በዚህ የሥራ ቦታቸው መጥሪያ እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑ ወይም የተለጠፈ መሆኑ የተገለፀ ነገር የለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ.አንቀጽ 100 ይገልፃል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 105 በተደነገገው መሠረት በመኖሪያ ቤታቸው ወይም በመጨረሻ ጊዜ ይኖሩበት በነበረ ሥፍራ መጥሪያ የተለጠፈ መሆኑ የተገለፀ የለም፡፡ ይህ በቅድሚያ የሚወሰድ የመጥሪያ አደራረስ ዘዴ እያለ የሥር ፍ/ቤት የመጨረሻ አማራጭ በጋዜጣ ጥሪ መጥሪያ ማድረግ ዘዴ ተጠቅሞ እና ተከሳሾች (የአሁን አመልካቾች) መጥሪያ ሣይደርሰን ሳንሰማ በሌለንበት የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልታየንም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ተዘግቶ የነበረው መዝገብ ተከፍቶ ክርክር የጀመረ መሆኑን ባልሰሙበት የሥር ፍ/ቤት የመጥሪያ አስፈላጊነት ተከራካሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ ያላቸውን ህጋዊ መብት ለማክበር ፍ/ቤቱም እውነቱን እንዲደርስበት ለማስቻል በመሆኑ መጥሪያ ለአመልካቾች ሲያደርሳቸው በቅድሚያ ሊጠቀም የሚገባውን የመጥሪያ አደራረስ መንገድ በመተው የመጨረሻ አማራጭ በጋዜጣ ጥሪ በመጠቀሙና አመልካቾች ይህንኑ ገልፀው መጥሪያውን ያልሰሙና በሌለንበት የተሰጠው ውሳኔ ይንሣልን ብለው ሲያመለክቱ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአሳሳ ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08505 ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የቤ/ጉ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05454 ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የቤ/ጉ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 05504 ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካቾች ክስ እንዲሻሻል ተብሎ የተዘጋ መ.ቁጥር 07304 ተከፍቶ ክርክር የጀመሩ መሆኑን ሳያውቁ መጥሪያ በአግባቡ ሳይደርሳቸው የተሰጠ ውሳኔ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/አንቀጽ 78(2) መሠረት ውሳኔውን ለማንሳት በቂ በመሆኑ በመ.ቁጥር 07304 የተሰጠው ውሳኔ ተነስቷል የቤ/ጉ/ክ/መ/የአሶሳ ከፍ/ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ለአመልካቾች አድርሶ ካከራከረ በኃላ ውሳኔ እንዲሰጥበት መልሰናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሣራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
4. በ17/6/2007 ዓ.ም የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 100475

ታህሳስ 20 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን አበራ ጠበቃ ክፍሌ አማረ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ አበራ ጠበቃ አሸናፊ ወጂ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን እንደቅደም ተከተላቸው አመልካች እና ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩም ፍቺን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው መሠረታዊ ጭብጥም የአሁኑ አመልካች የንብረት ክፍፍል በጠየቀበት ጊዜ ለአሁን ክርክር መነሻ የሆነችውን የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 መኪና በተመለከተ መኪናው የተፈራችው በጋብቻ ውስጥ ሳይሆን እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የተፈራች ስለመሆኑ ለማሳየት አመልካች የክስ ማሻሻያ ጥያቄ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ፈቅዶ ክሱ ከተሻሻለ በኃላ ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት ከጥቅምት 1998 እስከ ህዳር 2001 ዓ.ም አብሮው ይኖሩ እንደነበር ግምት ተወስዶ መኪናው የጋራ ንብረት ነች ተብሎ ተወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91 አቤቱታ የሚሻሻልበት ሥርዓትና ዓላማው ዳኝነት ከተጠየቀበት ጉዳይ ፈፅሞ የተለየ ጥያቄ ለማቅረብ እንደማይፈቀድ፤ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረን ኖረን ነበር በዚህ ጊዜ የተፈሩ ንብረቶች እንዲከፈል በሚል ማስረጃዎች ጭምር በመጥቀስ የቀረበው ጥያቄ

www.abyssinialaw.com

የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.256 ድንጋጌን ያላገናዘበ ስለመሆኑ፤ የፍቺ ውጤት በተጠየቀበት መዝገብ እንደባልና ሚስት አብረው ኑረዋል ወይስ አልኖሩም? የሚለው ጥያቄ በክስ ማሻሻል ምክንያት ተቀብሎ መታየቱ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡ እንደባልና ሚስት አብረው ሳያቋርጡ ኖረዋል ወይስ አልነበረም? የሚለው ነጥብም ማየት ባያስፈልገውም እንደተመለከተው ከጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም እስከ ነሃሴ 19 /1998 ዓ.ም ድረስ አብረው ቆይተው ከዛ በኃላ ግንኙነታቸው እንደተቋረጠ እንደገና አብረው መኖር የጀመሩት ጋብቻ ከተመሰረተበት ህዳር 2001 ዓ.ም ጀምሮ ስለመሆኑ የአሁን ተጠሪ ምስክሮች የአመልካች ምስክሮች ከሰጡት ቃለ ሚዛን በሚደፋ አግባብ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 የሆነውን መኪና የግለ ንብረት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ባንክ ላይ ነበር በተባለው ገንዘብ በተመለከተ ግን የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በማየት እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 /1/ መልሶታል፡፡የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ ቢያቀርቡም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የአመልካች ቅሬታ መሠረታዊ ይዘትም ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖሩ እንደነበር የፍቺ ጥያቄ የቀረበበት መዝግቦ ለመግለጽ እንደማይገደዱ፤ በአመለካች የቀረቡ ምስክሮችም በተጠሪ ከቀረቡ ምስክሮች በተሻለ አግባብ ያስረዱ በመሆኑ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው ይኖሩ እንደነበር የሕግ ግምት እንዲወሰድላቸው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ከ1998 እስከ ተጋቡበት 2001 ዓ.ም ያልተቋረጠ ግንኙነት መኖሩን አመልካች አላስረዱም፡፡ በግል የተፈራ ንብረት የግል ነው መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉይዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከሥር የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ቤት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-15556 የሆነውን መኪና የአመልካች እና ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በመሻር መኪናው የተጠሪ የግል ሀብት ነው በማለት ወስነዋል፡፡ አመልካች ከሥር ፍ/ቤት አንስቶ አጥብቆ የሚከራከረው የፍቺ ጥያቄ በቀረበበት መዝገብ ላይ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር የሚል ክርክር የማቅረብ ግዴታ እንደሌላቸው ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ

www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤት የክስ ማሻሻል ጥያቄው የተለየ ውጤት የሚያመጣ መሆን የለበትም እንዲሁም አመልካችና እና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ስለመኖራቸው አላስረዱም በማለት ውሳኔ መስጠቱ መዝገቡ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አቤቱታ የሚሻሻልበት ዓላማና ማሻሻያው የሚቀርብበት ስርዓት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 ሥራ ተመልክቷል፡፡ የክስ ማሻሻያ ጥያቄ መሠረታዊ ዓላማም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የሚረዳ መሆኑ በፍርድ ቤቱ የታመነ ከሆነ ነው፡፡ አመልካች የፍቺ ጥያቄ በቀረበበት መዝገብ ላየ እንደባልና ሚስት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ሲኖሩ ቆይተው በ2001 ዓ.ም ስለመጋባታቸው ያቀረቡት ክርክር የነበረ ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት እንኖር ነበር የሚለው አከራካሪ ጥያቄ የተነሳው የጋራና የግል ንብረት ለመለየት የተደረገው ክርክር ስለመሆኑ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በሥር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፍቺን ተከትሎ የቀረበው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የቀረበው በአመልካች ነው፡፡ አመልካች የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲያነሱ ለክርክሩ መሠረት የሆኑ መሠረታዊ ጉዳዮች በዝርዝር መገለጽ ያለባቸው ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222/1/ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የምንረዳው የጋራ ንብረት የተፈጠረበት /የተገኘበት/ አግባብ እና ሁኔታ በቀረበው ክስ በግልጽ ማመላከት ይጠበቅ ነበር፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-15556 በክስ ማሻሻያ እንደገለጹት እንደባልና ሚስት ሲኖሩ በነበሩበት ጊዜ ከሆነ መጀመሪያ ክስ ሲያቀርቡ ዳኝነት ያልጠየቁበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ አንድ የመብት ጥያቄ የሚያቀርብ ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ መነሻ የሆነ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 222(1)(2) በሚያዘው አግባብ "ምክንያት የሆኑ ነገሮች እና የተፈጠሩበት ሁኔታ" በግልጽ ዳኝነተ መጠየቅ እየተገባው የፍቺ ውጤት ክርክር ሲደረግ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብረን ኖረናል የሚለው አዲስ የተለየ ክርክር ማቅረብ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 ያላገናዘበ ነው የሚለው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድምዳሜ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአቤቱታ ማሻሻያ ጥያቄ የቀረበበት አግባብ ብቻ ሲሆን በእርግጥም በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ከ1998 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም ያልተቋረጠ ግንኙነት ነበር ወይስ አልነበረም የሚለውን ጭብጥ መርምሮ በፍሬ ነገር ደረጃ ግንኙነት አልነበረም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዎል፡፡ አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገቡ ላይ በሰፈረው ማስረጃ መሠረት ተገቢ ሁኖ ሲያገኘው ጭብጥን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ተገቢ የመሰለውን የመጨረሻ ፍርድ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 ሥር ተደንግጓል፡፡ የተያዘው ጉዳይ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመረመረው አቤቱታው የተሻሻለበት አግባብ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም አመልካች እና ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረው ኖረዋል ወይስ አልኖሩም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ

www.abyssinialaw.com

ቀኙ ማስረጃ መርምሮ ግንኙነት አልነበረም፡፡ መኪናው የግል ሀብት ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘናና ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚለወጥበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም ያለመፈፀሙን በማረጋገጥ ፍርድ መስጡት ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በነዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰሌዳ ቁጥሩ 3-15556 በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ በመሻር መኪናው የተጠሪ የግል ንብረት ነው ማለቱና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ በጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ስለማያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 135453 በ21/04/2006 ዓ.ም የሰጠው፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 89470 በ15/08/2005 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 በተመለከተ የሰጠው ፍርድ መሻሩ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 97972 በ30/07/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. የሰሌዳ ቁጥር 3-15556 የተጠሪ የግል ሀብት ነው መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ችሎት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡

መዝገብ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 109383

የካቲት 2 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች** - ሳሊሆም ከፍተኛ ክሊኒክ - ተሾመ ጉታ ቀረቡ

**ተጠሪ** - ዶ/ር ዘመኑ ዮሃንስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ሲሆን አላግባብ ከስራ መሰናበታቸው ህገወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ድርጅቱ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ ቀበሌ 02 በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና በፍሬ ገዳዩም ስንብቱ ህጋዊ ነው እንዲባል የበኩላቸውን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራቀኙ ተከራካሪዎች በተለያየ ክልል ነዋሪዎች ስለሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው በማለት መቃወሚያውን በብይን አልፎ በፍሬ ጉዳዩ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የስራ ዉሉ በአመልካች የተቋረጠው ከህጉ ውጭ ነው፤ ስለሆነም ለተጠሪ የካሳ፤ የስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በድምሩ ብር 104,730.00 (አንድ መቶ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ) እንዲሁም በክርክሩ ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰው ወጪ እና መጉላላት በቁርጥ ብር 500.00 (አምስት መቶ) እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም አመልካች በይግባኝ ተጠሪ ደግሞ በመስቀለኛ ይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክርክራቸውን ሰምቶ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ ማለቱና ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ በአግባቡ መሆኑን፤ ወጭና ኪሳራን በተመለከተ ተጠሪ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2007 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ተጠሪ በስር ክሳቸው በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር ገልፀው ክስ ማቅረባቸው ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ግራቀኙ በተለያየ ክልል ነዋሪዎች ስለሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው? አይደለም? የሚለው ነጥብ እንዲጣራ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ክርክሩን ቅሬታ ካስነሳው ውሳኔ እና ተገቢነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል ፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ተጠሪ ተቀጥረዉ ሲሰሩ የነበረበት ድርጅት የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ ቀበሌ 02 በመሆኑ፤ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138(1) እና በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 22(1) መሰረት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ድርጅቱ በሚገኝበት ቦታ ያለው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት (ሰበታ ሀዋስ ወረዳ ፍርድ ቤት) በመሆኑ፤ በአዲስ አበባ እና ድሬድዋ ያሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክርን ለማየት ስልጣኑ የተሰጣቸው ቢሆንም በሁለት ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ተከራካሪዎች በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(2) መሰረት ጉዳዩን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የማየት ስልጣን አላቸው ተብሎ የክስ መቃወሚያው ውድቅ መደረጉ የስራ ክርክርን አስመልክቶ የተከራካሪ ወገን ማንነት ወይም የሚኖርበት ክልል ከግምት ውስጥ ሳይገባ የክልል ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንዲኖራቸው ታስቦ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በግልፅ የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ምድብ የስራ ክርክር ችሎት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም ተብሎ ውሳኔው እንዲሻር ፤ እንዲሁም በፍሬ ነገሩ የስራ ውሉ እንዲቋረጥ የተደረገው የአመልካች የስራ እንቅስቃሴ እየቀዘቀዘና ትርፉም እየቀነሰ በመሄዱ ምክንያት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ ለጠሪ የሚከፈል ክፍያ የለም ተብሎ በነፃ እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ክሊኒኩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑና ክሱም የቀረበው ስራ አስኪያጅ እና ባለቤት አቶ ተሾመ ጉታ ተብሎ በመሆኑ፤ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(2) መሰረት ከሳሽና ተከሳሽ መደበኛ መኖሪያቸን በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ መሆኑ መነሻ ተደርጎ ክሱ መቅረብ ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ብይን መስጠቱ የሚነቀፍ ባለመሆኑ፤ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል እና የክልል በማለት ለይቶ ያላስቀመጠ በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 20 እና 23 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክሮችንም እንደሚመለከቱ ስለሚደነግግ የተሰጠው ብይን የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

እንደመረመር ነው በክርክሩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን (የግዛት ክልል) የለውም ተብሎ በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) መቅረቡ ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? በፍሬ ጉዳዩ ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ወይስ የለም? የሚሉት ናቸው በዚሁ ቅደም ተከተል መሰረት መርምረናል፡፡

ቀዳሚውን ጭብጥ በተመለከተ ከክርክሩ እንደተረዳነው አመልካች ያቀረቡት የስልጣን መቃወሚያ ስረ ነገርን የተመለከተ ሳይሆን የግዛት ክልል ስልጣንን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ግራ ቀኙ እንደገለፁት በአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ያሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክርን ለማየት የስረ ነገር ስልጣኑ በህግ ተሰጥቷቸዋል፡፡ አመልካች እየተከራከሩበት ያለው የግዛት የዳኝነት ስልጣን በዋነኛነት መሰረት የሚያደርገው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረበትን ቦታ፤ለተከራካሪ ወገኖች የሚኖረውን አመቺነት እና መሰል ሁኔታዎችን ሲሆን የስረ ነገር ስልጣን መሰረት የሚያደርገው ግን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ይዘት፣የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ጥቅም ክብደት እናመጠን፤የጉዳዩን የውስብስበነት ደረጃ እና መሰል ነጥቦችን በመሆኑ በጉዳዮች አመራር ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ለስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ነው፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9 እና 10 ድንጋጌዎች ተገናዝበው ሲታዩም ሕጉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ከግዛት ስልጣን ይልቅ ለስረ ነገር ስልጣን መሆኑን መገንዘብ የሚያስችሉናቸው፡፡ በተለይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 10(2) ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ የግዛት ክልል ስልጣን የለውም በማለት ለሚቀርብለት መቃወሚያ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ይግባኝ ሊቀርብበት እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች ቅሬታ በስር ፍርድ ቤት የተላለፈው ውሳኔ ፍትህን የሚያጓድል ነው በማለት የቀረበ አይደለም፡፡ ፍትህን የሚያጓድል ውሳኔ ስለመተላለፉ የቀረበ ክርክር በሌለበት ደግሞ የስር ፍርድ ቤት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ተብሎ በቀረበው መቃወሚያ ላይ ባሳለፈው ብይን ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ መቅረቡ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሳ ክርክርን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑበአዋጁ 25/1988 አንቀጽ 5(2) ስርመደንገጉ የግዛት ክልል ስልጣንን ሳይሆን የስረነገር ስልጣንን የሚመለከት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህን ምክንያት በመጥቀስ የስልጣን ክርክሩን መወሰናቸው ተገቢ ሆኖ ባናገኘውም በግዛት ክልል ስልጣን ረገድ በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) መቅረቡ የስነ ስርአት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ክርክርና ማስረጃውን ተመልክተው የስራ ውሉን ለማቋረጥ አመልካች እንደሚሉት ባጋጠማቸው የገቢ ማሽቆልቆል የተነሳ ሰራተኛን ለመቀነስ

www.abyssinialaw.com

የሚያስችል አስገዳጅ ሁኔታ ስለመፈጠሩ ያላረጋገጡ በመሆኑ፣ ቅነሳውም በህጉ የተዘረጋውን ስርዓት የተከተለ ስለመሆኑ የቀረበ መከራከሪያና ማስረጃ አለመኖሩን በማረጋገጥ የስራ ስንብቱ ህገወጥ ነው በማለት መወሰኑ እና በሕጉ የተመለከቱ ክፍያዎች ይከፈሉ ማለታቸው የሚነቀፍ አይደለም ፡፡ በዚህ ረገድ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ብለናል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 32414 ታህሳስ 11/2006 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 139491 ህዳር 25/2007 ዓ.ም የተሻሻለው ውሳኔ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል ፡፡
2. በስር ፍርድ ቤት የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ይፃፍ
3. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ እልባት ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሐሳብ

በዚህ መዝገብ ለክርክር በቀረበው ጉዳይ ተጠሪው ሲሰሩበት የነበረው ተቋም የሚገኝ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን በሰበታ ሃዋስ ወረዳ ውስጥ መሆኑ፣ የስራ ውሉ የተደረገውም ሆነ ሲፈጸም የነበረው በዚያው ወረዳ ውስጥ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በክልል ውስጥ የሚነሳ የግል የስራ ክርክር ጉዳይን አይቶ የመወሰን ስልጣን ደግሞ በአዋጅ ቁ. 377/1996 አንቀጽ 138(1) ስር የተሰጠው ለክልል ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ የግዛት ስልጣን የሌለው አንድ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፍትሕን የሚያጓድል ካልሆነ በቀር ተቀባይነት እንደማያጣ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀጽ 10(2) ስር የተመለከተ ቢሆንም በመሰረቱ ቀደም ሲል አሃዳዊ የመንግስት አወቃቀርን መሰረት አድርገው የወጡት እና አሁን ድረስ በስራ ላይ ያሉት ሕጎች መተርጎም እና ተግባራዊ መደረግ የሚገባቸው በአሁኑ ጊዜ ያለው ፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ስርዓት ካስከተላቸው ለውጦች ጋር ተጣጥመው ነው፡፡ በአሁኑ የመንግስት አወቃቀር ስርዓት መሰረት የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ለመወሰን እንደመስፈርት ከሚወሰዱት ነጥቦች አንዱ ደግሞ ጉዳዩ የተነሳበት ስፍራ ወይም ግዛት በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ክሱ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተስተናግዶ ውሳኔ ማግኘቱ የሚያስነሳው የስረ ነገርን ሳይሆን በስነ ስርዓት ሕጉ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌ መሰረት የግዛት

www.abyssinialaw.com

ስልጣን ጥያቄን ብቻ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ የስነ ስርዓት ሕጉ አንቀጽ 10(2) ድንጋጌን በዚህ አግባብ መተርጎም በአንድ ክልል ወረዳ ፍ/ቤት ቀርቦ መታየት ያለበት ጉዳይ ትይዩ ስልጣን ባለው በማንኛውም የሌላ ክልል ወረዳ ፍ/ቤት ታይቶ ቢወሰን ጉዳዩ የሚያስነሳው የስረ ነገር ሳይሆን የግዛት ስልጣን ጉዳይን ነው እንደማለት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የፍርድ ቤቶች ስልጣን በአሁኑ ጊዜ በፌዴራል እና በተለያዩ ክልሎች በተደለደለበት ሁኔታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ጉዳዩ የሚያስነሳው የስረ ነገር ሳይሆን የግዛት ስልጣንን ጥያቄ ነው ሊባል ይችል የነበረው ክሱ ተስተናግዶ ውሳኔ ያገኘው በዚያው ክልል በሚገኝ ሌላ ወረዳ ፍ/ቤት ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ በክልል ወረዳ ፍ/ቤት ቀርበው መስተናገድ የሚገባቸውን የግል የስራ ክርክር ጉዳዮች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁ. 100950 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን የስራ ክርክር ጉዳዮችን አስመልክቶ በመዝገብ ቁ. 113339 እና 113675 የተሰጡ ገዥ ውኔዎችም ቢሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣንን አስመልክቶ በተከሳሽ ወገን የቀረበለት መቃወሚያ ባይኖር ኖሮ እንኳ የቀረበለትን ጉዳይ አስተናግዶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረነገር ስልጣን ያለው መሆኑን በቅድሚያ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ሲሆን ስልጣን የሌለው በሆነ ጊዜም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁ. 9(1) እና 231 (1) (ለ) መሰረት ጉዳዩን ዘግቶ ማሰናበት ይጠበቅበታል፡፡

በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በስልጣን ምክንያት ሊሻር ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁ. ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሃሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 109206

የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች - አቶ ፍስሃ እርቅ ይሁን

ተጠሪ - አቶ ኪሮስ ስዩም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በጋምቤላ ክልል ማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው ፡፡ የክሱ ይዘት ግራቀኙ በነበረን የንግድ ግንኙነት ጀንፈል ቡና በጋራ ገዝተን አስበጥረን ለማእከላዊ ገበያ አቅርበን በመሸጥ ትርፉን ለመከፋፈል ባደረግነው ስምምነት መሰረት ለጀንፈል ቡና መግዣ ብር 122,000.00 (መቶ ሃያ ሁለት ሺ.ህ) ሰጥቸው ቡናው ተገዝቶ አስበጥረን እና በከሳሽ ፈቃድ ማእከላዊ ገበያ ተልኮ በከሳሽ የቡና ሽያጭ ወኪል በአቶ ዘላለም ጥላሁን አማካኝነት ተሸጦ ገንዘቡ በንግድ ባንክ በኩል የተላከልኝ ሲሆን ይህን ገንዘብ አውጥቼ ትርፉን ተሳስበን እስክንከፋፈል ድረስ ሙሉ ገንዘቡን ለተከሳሽ የሰጠሁት ቢሆንም ሂሳብ ተሳስበን ገንዘባችንን ሳንካፈል በመካከላችን አለመግባባት ስለተፈጠረ በ 10/07/2006 ዓ.ም በሽማግሌ ዋና ገንዘቤንና ትርፉን እንዲሰጠኝ አስጠይቄው ቡና መግዣ ብር 122,000.00 (መቶ ሃያ ሁለት ሺ.ህ) እንደሰጠሁት አምኖ ከዚህ ገንዘብ ብር 41,000.00 (አርባ አንድ ሺ.ህ) የሰጠኝ ሲሆን ቀሪውን ብር 81,000.00 (ሰማንያ አንድ ሺ.ህ) ዛሬ ነገ በማለት ሊሰጠኝ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ዋና ገንዘቤንና ትርፉ ታስቦ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማና የሰነድ ማስረጃዉን ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ በምስክሮች ለመክፈል ተስማምቷል የተባለውን ቀሪ ገንዘብ ብር 81,000.00 (ሰማንያ አንድ ሺ.ህ) ለከሳሽ እንዲከፍለው ወስኗል፡፡ ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የይግባኝ ክርክሩን ሰምቶ የባንኩ ሰነድ ገንዘቡ

የተላከ ለከሳሽ ስለመሆኑ ከሚያስረዳ በቀር ለተከሳሽ ስለመላኩ ስለማያስረዳ፤ ከሳሽ ገንዘቡን ከባንክ አውጥቶ ለተከሳሽ ስለመስጠቱ የሚያስረዳ አንዳች የሰነድ ማስረጃ ስላልቀረበ፤ የተሰሙት ምስክሮችም ገንዘቡን ሲሰጥ አይተናል በማለት ስላልመሰከሩ፤ እንዲሁም ተከሳሹ ገንዘቡ ያለበት መሆኑን በሽማግሌዎች ፊት ተስማምቷል ለተባለውም ስለመስማማቱ የቀረበ የስምምነት ሰነድ ስለሌለ ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም ገንዘቡንም ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ጉዳዩን ለክልሉ ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ቅሬታቸው ተቀባይት ሳያገኝ አያስቀርብም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ 4/አራት/ ገፅ የሰበር ማመልከቻ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ውሣኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱን በዝርዝር ክደው መልስ ያልሰጡ በመሆኑ በመሸሽ ክሱን እንዳመኑ የሚያስገምት በመሆኑ፤ ገንዘቡ በብድር የተሰጠ ባለመሆኑ በሰው ምስክር ማስረዳት እየተቻለ የሰነድ ማስረጃ አላገኘንም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ፤ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የተጠየቀበትን ከቡና ሽያጭ የተገኘን ትርፍ ሂሳቡ እንዲጣራ አስደርጎ አለመወሰኑ እና የወለድ ጥያቄውን ማለፉ የህግ ስህተት በመሆኑ እንዲታረም መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግንቦት 25 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ 4 /አራት/ ገፅ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ከብር 500.00 (አምስት መቶ) በላይ በሆነ የገንዘብ ክርክር በፅሁፍ ማረጋገጫ ካልተደገፈ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መዝገቡ እንዲዘጋ፤ በሽማግሌዎች ፊት ተጠሪ ገንዘብ ስለመውሰዱ አምኖልኛል የሚለው መከራከሪያም ከእውነት የራቀ ከመሆኑም በላይ የተቆጠሩት ምስክሮች የሰጡት ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭና ገንዘቡን ሰጥቶኛል ብሎ ነግሮናል የሚል አመሰካከር በመሆኑና ገንዘቡን አመልካች ለተጠሪ ሲሰጥ አይተናል የሚል ባለመሆኑ የፍታብሄር ስነ ስርዓት ህጉን አንቀፅ 242 እና 128 ድንጋጌዎች አፈጻጸም ያልተከተለ ምስክርነት አሰጣጥ በመሆኑ፤ ያለሰነድ ተሰጠ ለተባለው ገንዘብ ተጠሪ ኃላፊነትም ተጠያቂነትም የለበትም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ስለሆነም ሊጸና ይገባል የሚል ነው ፡፡ አመልካችም ሰኔ 26 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፈት 2/ሁለት/ ገፅ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ዴንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነው ተጠሪ በሽማግሌዎች ፊት አምነው ለመክፈል ስለመስማማታቸው የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም በማለት ገንዘቡን መክፈል ኃላፊነት

www.abyssinialaw.com

የለባቸውም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሃብሔር ግዴታ ከውል ወይም ከህግ ከሚመነጭ ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ሲሆን ክስ አቅራቢው ወገን የግዴታውን ምንጭ በመግለጽ የሚጠይቀውን ዳኝነት በዝርዝር የማቅረብ ግዴታ አበለት፡፡ ተከሳሹም በክሱ የተጠቀሰን ግንኙነት አስመልክቶ ዝርዝር በልሱን እንዲያቀርብ ይጠበቃል፡፡ በዚህ መልኩ ግንኙነቱ ተለይቶ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የህጉን ድንጋጌዎች በመመልከት ግንኙነቱን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችለው ማስረጃ አይነት እና የማስረዳት ሸክሙ ስለሚያርፍበት ወገን በህጉ አግባብ ሊወሰን የሚገባ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተፈጠረው የንግድ ግንኙነት ጀንፈል ቡና በጋራ ገዝተው አስበጥረው ለማእከላዊ ገበያ በማቅረብ ትርፉን ለመከፋፈል ስለመሆኑና የሚጠይቁትን ዳኝነት ገልፀው አመልካች ክስ ያቀረቡ ሲሆን በማስረጃነትም ጉዳዩን በሽምግልና አይተዋል የተባሉ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ የተጠቀሰው ግንኙነት መኖሩን ሳይክዱ ከሳሽ ራሱ የቡና ሽያጭ ገንዘቡን ከባንክ የተቀበለ መሆኑን በክሱ ስላመነ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ፤ እንዲሁም ከብር 500.00 በላይ ያለሰነድ ማስረጃ መክሰስ አይችልም የሚሉ መቃወሚያወች እና በአማረጭም ከሳሽ ባቀረበው ሰነድ መሰረት ከባንክ ከተረከበው የድርሻቸውን ገንዘብ እንዲከፍል የሚጠይቅ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከተደረገው ክርክር የግራቀኙ ግንኙነት በፅሁፍ ያልተረጋገጠ የሽርክና የንግድ ግንኙነት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በእንዲህ አይነቱ ግንኙነት ተቃራኒ ስምምነት ከሌላቸው በቀር ግራ ቀኙ ገቢ ላደረጉት መዋጮ ባለሀብትነቱን እንደያዙ ይቆያሉ፡፡ ተጠሪ በመከላከያ መልሱም ባይሆን በሌላ በማናቸውም መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ በእምነቱ መሰረት ይገባኛል የሚለው ማናቸውም ዳኝነት እንዲሰጠው አመልካቹ ሊጠይቅ እንደሚችል፤ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ የታመነውን ለማስረዳት የጽሁፍ የስምምነት ሰነድ ሊያቀርቡ ይገባል በሌላ አይነት ማስረጃ ሊያስረዱ አይችሉም የሚባልበት የህግ ምክንያት እንደሌለ ክርክሩ ከሚመራበት የስነ ስርዓት ህግ ድናጋጌዎች እና ከማስረጃ ፅንሰ ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ክሱን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ተቀባይነት የላቸዉም የሚባልበት የህግ ምክንት ባለመኖሩ፤ ይልቁንም ባቀረቡዋቸው ማስረጃዎች ተጠሪ ገንዘቡ እንዳለበቸውና ለመክፈል መስማማታቸውን ማስረዳታቸውን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ በአንጻሩ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም ተብሎ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም ገንዘቡንም ሊከፍል አይገባም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔውን መሻሩ እና የሰበር ችሎቱም ይህን ሳያርም ማለፉ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘንውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ

www.abyssinialaw.com

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የሳለፉት ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በቅሬታቸው የስር ፍርድ ቤት ዳኝነት የተጠየቀበትን ከቡና ሽያጭ የተገኘን ትርፍ ሂሳቡ እንዲጣራ አስደርጎ አለመወሰኑ እና የወለድ ጥያቄውን ማለፉ የህግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረም የጠየቁ ቢሆንም በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የበኩላቸውን ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው በየደረጃው ውሳኔ የተሰጠበት ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የጋምቤላ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 01686/07 ጥቅምት 21 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በፍ/ሰ/መ/ቁ 00396/07 ህዳር 8 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ/ 01978/06 ጳጉሜ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡

3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ፊት ስለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 109497

የካቲት 3 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ አግማስ ኡመር እና ወ/ሮ ሰብረና ጌታቸው

ጠበቃ ይትባረክ መኮንን ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ኡመር አሳዬ እና ወ/ሮ አሰገድ ሃሰን -ጠበቃ መስፍን እሼቱ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካቾች አቶ አግማስ ኡመር እና ወ/ሮ ስብርና ጌታቸው ጥር 26ቀን 2007ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌ.ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 156998 ታህሳስ 20 ቀን 2007ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታቸውም የውል ስምምነት በተዋዋዮች መሀከል ሕግ መሆኑ ተደንግጎ እያለ የውል ስምምነት የህግና የሞራል ጥሰት እንዲሁም ሌሎች ህጋዊ ምክንያቶች የተጓደሉበት ሁታዎች የተካተቱበት ሲሆን እና እነዚህ ምክንያቶች ከተዋዋዩ በአንዱ ወገን ላይ የመብት ሆነ የግዴታ ተጽእኖ የበለጠ የሚያበዛበት ሆኖ የተገኘ ከሆነ ተቀባይነት የለውም ሊባል ካልተቻለ በቀር የስር ፍ/ቤት ካለበቂ ምክንያት ስምምነታችንን ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ባለመሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የተደረገው ክርክር በአፈጻጸም የፍ/ባለመብቶች (የአሁን አመልካቾች) በፍ/ባለእዳ (የአሁን ተጠሪዎች) ላይ ብር 480,000 እንዲከፍሉን ተወስኖልናል ሲሉ የአፈጻጸም መዝገብ በፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት ይከፍታሉ፡፡ ፍ/ቤቱም የአ.ፍ/ባለእዳዎች በውሳኔው መሰረት እንዲፈጽሙ

www.abyssinialaw.com

ያዛል፡፡ የፍርድ ባለመብቶች (የአሁን አመልካቾች) ከፍ/ባለእዳዎች ጋር ሰኔ 13 ቀን2006ዓ.ም በአፈጻጸም ስምምነት አድርገናል፡፡

በዚሁ ስምምነት መሰረት ፍርዱ እንዲፈጸም ስምምነቱን ፍ/ቤቱ አጽድቆ የፍ/ቤት ማህተም አርፎበት እንዲሰጠን ሲሉ ያመለክታሉ፡፡ የፍ/ባለእዳዎችም ተስማምተዋል፡፡

የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 215541 አከራክሮ ሐምሌ 11ቀን 2006ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ የቀረበው አቤቱታ በተመለከተ ፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ ያስፈጽማል፡፡ የተሰጠው ውሳኔ ብር 480,000 እንዲከፍል ነው የቀረበው ስምምነት ደግሞ ቤት ለማስረከብ የተዋዋሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲፈጸም ከቀረበው ፍርድ የተለየ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 396(1) መሰረት ተስማምተው ፈጽመው ከቀረቡ ተቀብሎ ትእዛዝ ይሰጣል ይሁንና እንደዋና ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 መሰረት ውል ተመዝግቦ ውሳኔ መስጠት ግን የሚቻል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም ሲል አዟል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለፌ.ከፍ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 156998 ታህሳስ 20ቀን 2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ስህተት የተገኘበት አይደለም ሲል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ግራቀኙ ስለፍርዱ አፈጻጸም ከፍርድ ውጪም ቢሆን የተስማሙበትን ውል በተመለከተ ተቀብሎ አልመዘግብም ያለበትን አግባብ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 እና 396 እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731 ድንጋጌዎች አንጻር ተገቢነቱን ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ሰኔ 5 ቀን 2007ዓ.ም በተጻፈ መልስ የፍ/ባለእዳዎች ከፍ/ባለመብቶች ጋር ተስማምተን ስምምነቱን ለፍ/ቤት አቅርበን እያለ በተጠሪነት መጠራታችን ተገቢ ባመሆኑ በነጻ እንሰናበት ሲል ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾችም ሐምሌ 3 ቀን 2007ዓ.ም በተጻፈ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች ግንቦት 26 ቀን 2006ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ያቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ብር 480,000 እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 መሰረት ተዋዋዮቹ በእርቅ መጨረሳቸውን ገልጸው እንዲጸድቅላቸውና ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ በእርቁ መሰረት እንዲፈጸም ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው የጠየቁት ፍርዱ የባለእዳ (የአሁን ተጠሪ) ቤት ላይ እንዲፈጸም ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277(1) ተከራካሪዎቹ ነገሩን በእርቅ ለመጨረስ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርቡ የእርቁ ስምምነት ሕግንና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን ፍ/ቤቱ ስረዳው እርቁን ተቀብሎ በማጽደቅ ከመዝገቡ ጋር ማያያዝ እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡ የአሁን አመልካችና የተጠሪ የእርቅ ስምምነት በገንዘብ እንዲከፈል የተወሰነን ውሳኔ የአሁን ተጠሪን ቤት ለአመልካች ለማስተላለፍ (ለመፈጸም)

www.abyssinialaw.com

የተደረገ ስምምነት ነው፡፡ ለአሁን አመልካች የሚፈጸም ቤት የእርቅ ስምነነቱ ህጋዊነት የማረጋገጥ ጉዳይ በተመለከተ ሊነሳበት የሚችል ክርክር ጋር በተያያዘ እራሱን የቻለ ማጣራት የሚፈልግና ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ በመሆኑ ፍ/ቤት በተዋዋዮች መሃል የተደረገ ውል በፍ/ብ/ሕ/አንቀጽ 1731 እንደሚደነግገው ውሎች ባቋቋማቸው ሰዎች ላይ ሕግ በመሆናቸው ብቻ ህጋዊነታቸው ሳይረጋገጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277 በሚደነግገው አንጻር የእርቅ ስምምነቱን ተቀብሎ በአፈጻጸም መዝገብ ላይ የሚያጸድቅበት አግባብ የለም፡፡ ለአፈጻጸም ተብሎ የተደነገገው ስርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 396 በሚደነግገው መሰረት አመልካችና ተጠሪዎች ከፍ/ቤት ውጭ በተደረገ ስምምነት በውሳኔው መሰረት ለፍ/ባለመብቱ የተከፈለ መሆኑን ለፍ/ቤቱ ካሳወቁት ፍ/ቤቱ ስምምነቱን ተቀብሎ ትእዛዝ የሚሰጥበት አካሄድ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ይህንኑ በማተት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ.ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 156998 ታህሳስ 20ቀን 2007ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ፣ የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 215541 ሐምሌ 8 ቀን 2006ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር 110150

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ገ/መድህን ወ/ሚካኤል - ጠበቃ አብይ ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ግርማይ ፍትዊ - ጠበቃ ወርቅነሽ መንግስቱ ቀረቡ

2. የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ፅ/ቤት - ነ/ፈጅ ሙሴ ዳዊት ቀረቡ

3. የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

- ዐቃቤ ሕግ ታደሰ አንዳርጌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ተከራክረው በለቱ አንደኛ ተጠሪ ለሚደርስባቸው ኪሳራ ዋስትና የሚሆን ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ እንዲያስይዙ የተሰጠውን ትዕዛዝ አልፈፀመም በሚል የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተከሳሾች ላይ ያቀረበውን ክስና መዝገብ መዝጋቱ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘትም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ኤርትራዊያን ከአገር ሲወጡ፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 13 የሚገኘውን ቁጥሩ 3018 የሆነ ቤት ለአንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ/ አከራይቸው ነበር ሁለተኛ ተከሳሽ ይህንን ቤት በአንደኛ ተከሳሽ

www.abyssinialaw.com

ሸጦለታል፡፡ የከሳሽ ዕዳ ነው በሚል ከቤቱ ዋጋ በመቀነስ ለሶስተኛ ተከሳሽ ከከፈለ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ በኩል ሲሳብ በስሜ አስቀምጧል፡፡ ከሳሽ ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በመንግስት ፈቃድ ከተመለስኩ በኋላ ለሶስተኛ ተከሳሽ በድጋሜ ክፍያ ፈፅሜለሁ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ከመንግስት መመሪያ ውጭ አከራይቸው ለሄድኩት አንደኛ ተከሳሽ ቤቴን ለመሸጥ ሁለተኛ ተከሳሽ ያደረገው ውል ፈራሽ እንዲሆንልኝ፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ከቤቱ ዋጋ አላግባብ ያስቀነሰው ገንዘብና ለሶስተኛ ተከሳሽ በድጋሜ የከፈልኩት ገንዘብ እንዲመለስልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2. አንደኛ ተጠሪ /አንደኛ ተከሳሽ/ አመልካች በዚህ አገር ዜጋና ኗሪ ባለመሆኑ በክርክሩ ለሚደርስብኝ ኪሳራ ዋስትና ያስብልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ በአንደኛ ተከሳሽ ላይ ለሚያደርሰው ኪሳራ ብር 5,500 /አምስት መቶ ሺ አምስት መቶ ብር/ ዋስትና እንዲያስይዝ፣ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በዋስትና እንዲያሲዙ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠበትን የዋስትና ገንዘብ ያላስያዙና በሁለተኛ ተከሳሽና በሶስተኛው ተከሳሽ ላይ የቀረበው ክስ በአንደኛ ተከሳሽ ጋር ከቀረበው ክስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልፆና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 201 ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች አንደኛ ተጠሪ ከጠየቀው የዋስትና ገንዘብ በላይ በብሔራዊ ባንክ በስሜ በግል አካውንት የተቀመጠ ገንዘብ እንዳለ በክስ ማመልከቻየ ገልጪ እያለ፣ ከዚህ ገንዘብ ለኪሳራ የሚሆን ገንዘብ እንደታገደ በማድረግ ክርክሩን መቀጠል ስችል የስር ፍርድ ቤት የዋሰትና ገንዘብ እስዲያስይዝ የሰጠው ትዕዛዝና ትዕዛዙን አልፈፀምክም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት የካቲት 17 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች በተናጥል አመልካች የስር ፍርድ ቤት በሕግ በተደነገገው መሰረት እንዲያስይዝ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የዋስትና መዝገብ ያላስያዘው በመሆኑ አመልካች ትዕዛዙን እስኪፈፀም ድረስ የስር ፍርድ ቤት መዝገቡን መዝጋቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 201 መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ክስ ያቀረበው ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተከሳሽ በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል በነበረው ጦርነት ምክንያት እኔ ከአገር ስወጣ፣ ከመመሪያ ውጭ የፈፀመው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ይደረግልኝ፡፡

www.abyssinialaw.com

የሽያጭ ውሉ አይፈረስም ከተባለ፣ በብሔራዊ ባንክ በከሳሽ ስም በግል አካውንት የተቀመጠ ገንዘብ፣ ከቤቱ ሽያጭ አንደኛ ተከሳሽ ከሳሽ የግብር እዳ ያለብኝ መሆኑን ሣያረጋግጥ ቀንሶ ለሶስተኛ ተከሳሽ የከፈው ክፍያ እና ከሳሽ ለሶስተኛ ተከሳሽ ከቤቱ ዋጋ ተቀንሶ ለሶስተኛ ተከሳሽ የተከፈለ መሆኑን ሣላውቅ በድጋሜ የከፈልኩት ገንዘብ እንዲመለስ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት እንደሆነ ግራ ቀኝ ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡

5. የከሳሽ ክስ በመሰረታዊ ባህሪውን ይዘቱ ከሳሽ በክርክሩ ረች ወይም ተረች ቢሆን አንደኛ ተጠሪ በክርክሩ ምክንያት የሚያደርስበትን ኪሣራ ለመሸፈን የሚያስችል ገንዘብ የሚያሳጣ አይደለም፡፡ ከሳሽ በአንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ መካከል የአመልካች ቤት ለመሻሻጥ የተዋዋሉት ውል ፈራሽ ነው ቢባል፣ አመልካች ለተጠሪዎች ኪሳራ መክፈል እንደማይገደዱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ 463 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ውድቅ ቢሆንበትና አመልካች በክርክሩ ተረቶ ቢሆን፣ በክርክሩ ምክንያት በተጠሪዎች ላይ ያደተሰውን ኪሳራ ለመክፈል የሚችል ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን በአንደኛ ተጠሪ ሽጦ በአመልካች ስም በብሔራዊ ባንክ በግል አካውንት ያስቀመጠው ጥሬ ገንዘብ ያለ መሆኑን አመልካች ካቀረበው ክስ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አንደኛ ተጠሪ አመልካች በክርክሩ ለሚያደርስበት ኪሳራ የዋስትና ገንዘብ እንዲያሲዝ ያቀረበውን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት በብሔሪዊ ባንክ ከሚገኘውና በአመልካች ስም በዝግ አካውንት ከተቀመጠው ገንዘብ፣ በአንደኛ ተጠሪ በክርክር ምክንያት ለሚደረስበት ኪሳራ መከፈያ እንዲሆን ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ብሔራዊ ባንክ አግዶ እንዲያቆይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 155 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ትዕዛዝ መስጠት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና አከራክሮ ውሳኔ ለመስጠት እየቻለ፣ አመልካች የኪሳራ ገንዘብ እንዲያስይዝ የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 200 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መስፈርት የሚያሟላ አይደለም፡፡

6. በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 200 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ለሚደርሰው ኪሳራ ዋስ እንዲያስይዝ የሚጠየቀው፣ ከሳሽ በክሱ ምክንያት በተከሳሽ ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመክፈል የሚችሉ ሁኔታ የሚያጠራጥር ሲሆንና ኪሳራውንም ለመክፈል የሚያስችል ሀብት ወይም ገንዘብ የሌለው በሆነ ጊዜ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 200 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 ተደግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ በክርክሩ ለሚደርስበት ኪስራ አመልካች ዋስትና እንደሰጠው ያቀረበውን ጥያቄ፣ በአመልካች ስም በዝግ አካውነት በብሔራዊ ባንክ ከተቀመጠው ገንዘብ በአንደኛ ተጠሪ ላይ ሊደረስ ይችላል ተብሎ የገመተውን ኪሳራ ማለትም ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ባንኩ ይዞ እንዲቆይ በማዘዝ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ ፍትሕ

www.abyssinialaw.com

የማግኘት መብት በማያጣብብ ሁኔታ ለማስፈፀም እየቻለ፣ አመልካች የዋስትና ገንዘብ እንዲያስጥ የሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 200 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 እና የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

7. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሕግ አግባብ ውጭ የዋስትና ገንዘብ እንዲያስይዝ የሰጠውን ትዕዛዝ እንዳልፈፀመ ገለፆ መዝገቡን መዝጋቱ ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች፣ የሚጥስ መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻር ሲገባው፣ የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 212488 ሰኔ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 157449 ታህሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብሔራዊ ባንክ በአመልካች ስም በዝግ አካውንት ከተቀመጠው ገንዘብ ብር 5,500 /አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ወጭ እንዳይሆን የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠትና የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 212488 በማንቀሳቀስ የአመልካችን እና የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112927

ቀን የካቲት 16/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የማርዘነብ ዕቁብ ዳኛ አቶ ባዬ አጥናፉ - ጠበቃ አለጌታ መርሻ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ዋለልኝ ተመስገን - ቀረቡ

2. አቶ አዲሱ ጥሩነህ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ ላልተከፈለ የዕቁብ ገንዘብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ የሚመለከት ነው፡፡ የአመልካች ዕቁብ አባል የሆነ ወርቁ ሚናስ የተባለና የሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነ ሰው የዕቁብ እጣ ደርሶት ብር 465,000 /አራት መቶ ስልሣ አምስት ሺ ብር/ ተቀብሎ ሲወስድ ቀሪውን የዕቁብ እጣ በየጊዜው የሚከፍል ስለመሆኑ፣ አቶ ወርቁ ሚናስ የዕቁብ ገንዘብ መጣሉን ቢያቋርጥ፤ ተጠሪዎች ገንዘቡን የሚከፍሉ ስለመሆኑ ተጠሪዎች የዋስትና ግዴታ ገብተው ፈርመዋል፡፡ አቶ ወርቁ ሚናስ መክፈል የነበረበትን ብር 222,000 /ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ብር/ ሣይከፍል የዕቁብ ገንዘቡን መጣሉን በማቋረጡ አመልካች አንደኛ ተከሳሽ ወርቁ ሚናስና እሱ የዕቁብ ገንዘቡን ሲወስድ ዋስ የሆኑት ተጠሪዎች ገንዘቡን እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ለምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡
2. ተጠሪዎች የዕቁብ አባላትና የዕቁብ ገንዘብ በእጣ ደርሶት የወሰደው አቶ ወርቁ ሚናስ ዋስ እንደሆነ ገልፆም በዕቁብ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የዚህ አይነት የዕቁብ ገንዘብ ለዕቁብተኛ ሲሰጥ የዕቁቡ ኃላፊዎች አራት ዋሶችን አስጠርተው ገንዘቡን መስጠት ነበረባቸው፡፡ የዕቁብ ኃላፊዎች ሁለት ዋሶችን አስጠረተው ገንዘብ መስጠታቸው የዕቁቡን መተዳደሪያ ደንብ ያልተከተለ መሆኑን ስለማያሳይ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሳሾች እያንዳንዳችን ክስ የቀረበበትን

www.abyssinialaw.com

ገንዘብ አንድ አራተኛውን ብቻ ነው የመክፈል ኃላፊነት ያለብን በማለት መልስ የሰጡ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሮታል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት ዕቁብ የደረሰው ሰው የደረሰውን የዕቁብ ገንዘብ ከመውሰዱ በፊት የዕቁብ አባላት የሆኑ ስንት ዋሶችን የመጥራት ኃላፊነት እንዳለበት በጭብጥነት ይዞ ለማጣራት የዕቁቡን መተዳደሪያ ደንብና የምስክሮችን ቃል ከሰማ በኃላ የዕቁቡ ኃላፊዎች የዕቁቡን ገንዘብ የወሰደውን አቶ ወርቁ ሚናስ አራት ዋሶችን የማስጠራት ኃላፊነት የለባቸውም ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ ወርቁ ሚናስ ያልከፈለውን የዕቁብ ገንዘብ ይክፈል፡፡ የዕቁቡን ገንዘብ አንደኛ ተከሳሽ ካልከፈለ፣ ሁለተኛ ተከሳሽና ሶስተኛ ተከሳሾች ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
4. ተጠሪዎች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የተጠሪዎችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ ተጠሪዎች የፈረሙት የዋስትና ውል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1725 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 የተደነገገውን መሰረት የሚያሟላ ባለመሆኑ ዋስትናው ህጋዊ ውጤት የለውም፡፡ ተጠሪዎች አንደኛ ተከሳሽ የዕቁብ ገንዘብ ሲወስድ በሰጡት ዋስትና አይገደዱም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
5. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የዕቁብ ገንዘብ ደርሶት ቢወስድ ዋስ መሆናቸውን በግልፅ ክደው አልተከራከሩም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪዎች ዋስ እንደነበሩ አምነው ክስ ከቀረበበት ገንዘብ አንድ አራተኛውን ብቻ እንደሆነ ገልፀው ተከራክረው እያለ የዋስትና ውሉ የህጉን ፎርማት አያሟላም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት የዋስትና ውሉን በመቃወምና በመካድ የተከራከርን በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የዋስትና ውሉ ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በመመርመር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡
6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪዎች የፈረሙት የዋስትና ውል የህጉን ፎርም አያሟላም በማለት ተጠሪዎች ክስ ያቀረበበትን የዕቁብ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ ተጠሪዎች በሥር

አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አቶ ወርቁ ሚናስ ለደረሰው የዕቁብ ገንዘብ ዋስ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤት አከራካሪ ጭብጥ ሆኗል ወይስ አልሆነም? የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

7. ተጠሪዎች ለሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ የአመልካች የዕቁብ አባላት መሆናቸውንና እነርሡም በስማቸው የዕቁብ ገንዘብ የሚጥሉ መሆኑን፣ አቶ ወርቁ ሚናስ የተባለ ዕቁብተኛ የዕቁብ ገንዘብ ሲደርሰው ዋስ ሆነው ያፈረሙ መሆኑን በማመን ለሥር ፍርድ ቤት መልስ የሰጡ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው በግልፅ አስፍሯል። ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት አቶ ወርቁ ሚናስ ለወሰደው የዕቁብ ገንዘብ የዋስትና ግዴታ የገቡ መሆኑን ሣይክዱ፣ አከራካሪ ነጥብ አድርገው ያቀረቡት በገቡት የዋስትና ግዴታ መሠረት ሊከፍሉ የሚገባውን የገንዘብ መጠን እንደሆነና ተጠሪዎች የቁብ ኃላፊዎች በአቶ ወርቁ ሚናስ የዕቁብ ገንዘቡን ከመስጠታቸው በፊት አቶ ወርቁ ሚናስ አራት ዋስ እንዲጠራ ማድረግ ሲገባቸው በእኛ ዋስትና ብቻ የዕቁቡን ገንዘብ የከፈሉት ከዕቁቡ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ስለሆነ እኛ የምንገደደው እያንዳንዳችን አቶ ወርቁ ሚናስ የወሰደውንና ሣይከፍል የቀረውን የዕቁብ ገንዘብ 1/4ኛ ብቻ ነው በማለት እንደሆነ የሥር ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል።

8. የአንድ ጉዳይ አከራካሪ ጭብጥ ከሳሽ በክስ የገለፀውንና ተከሳሽ በመልሱ ክዶ የተከራከረበት ነጥብ እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 ንዑስ አንቀጽ ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ ተከራካሪዎች ክርክራቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚገደዱትና ፍርድ ቤቱን በተከራካሪዎች ያቀረበውን ማስረጃ ተዓማኒት ክብደት የሚመዝነው ግራ ቀኙ ተካክደው በሚከራከሩበት ጭብጥ ላይ ብቻ እንደሆነና ከሳሽና ተከሳሽ ያልተካካዱበትና ከሳሽ በክሱ ገልፆ ተከሳሽ ባመነው ነጥብ ላይ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ማስረጃ በመመዘን ሣይሆን በተከሳሹ በሰጠው የዕምነት ቃል ወይም መልስ መሠረት መወሰን እንዳለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 242 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ በመመርመር ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር ተጠሪዎች አቶ ወርቁ ሚናስ የዕቁብ እጣ ወጥቶለት በቁብ ያደረሰውን ገንዘብ ከዕቁቡ የሥራ ኃላፊዎች ሲወስድ እነርሱ የዋስትና ግዴታ የገቡ መሆኑ ያልተካደና አከራካሪ ጭብጥ ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች የታመነውን ወርቁ ሚናስ ላልተከፈለው የዕቁብ ገንዘብ የገቡት የዋስትና ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት አመልካች ያቀረበው የውል ሰነድ የህጉን ፎርም አያሟላም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 (1) የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 242 ድንጋጌዎችና አመልካቾች ያለበት የማስረዳት ግዴታ እስከምን ድረስ እንደሆነ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

9. የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች የዕቁብ ኃላፊዎች ተጠሪዎችን በሰጡት ዋስትና ብቻ የዕቁቡን ገንዘብ በዕቁቡ ባለዕድል /ባለ እጣ/ አቶ ወርቁ ሚናስ መክፈላቸው ተገቢ ነው ወይስ

www.abyssinialaw.com

አይደለም? ተጠሪዎች በዋስትናው መክፈል የሚገባቸው ወርቁ ሚናስ የወሰደውን የዕቁብ ገንዘብ ሙሉውን ነው ወይስ እያንዳንዳቸው አንድ አራተኛ (ግማሹን ገንዘብ) የሚለውን አመልካችና ተጠሪዎች የተካከደበትን ጭብጥ በመያዝ የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች ወርቁ ሚናስ የወሰደውን ሣይከፍል ያቀረበውን የዕቁብ ገንዘብ እያንዳንዳቸው 1/2ኛውን (ሙሉ ገንዘቡን) የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ፀንቷል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት አከራካሪ የፍሬ ጉዳይ ጭብጥ ያልሆነ ተከራካሪዎች ያልተካካደበት ነጥብ ጭብጥ አድርጎ በመያዝ የዋስትና ውሉ የህጉን ፎርም ስለማያሟላ ተጠሪዎች የዕቁብ ዋስ በመሆን ለገቡት ግዴታ ተጠያቂ አይደሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 44853 መጋቢት 24 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 7630 ጥቅምት 19 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39054 ታህሣሥ 23 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰበር መዝገብ ቁጥር 104028

የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-1.አልማው ወሌ

2.ዓሊ መሐመድ

3.ተኽሊት ይመስል

4. እንዳሻው አዳነ

5.ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ብዙአየሁ ያለው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-**አቶ ሲሳይ ካሴ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት መብት መሰረት አድርጎ የቀረበውን ይዞታ ይለቀቀልኝ ጥያቄን የሚመለከት የቀረበውን ክርክር በግራ ቀኙ ማስረጃና ከሚመለከተው አካል በቀረበው ማረጋገጫ መሰረት ይዞታው የተጠሪ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ለውሳኔው መሰረት የሆነውና ከሚመለከመተው አስተዳደር አካል የተሰጠው የሰነድ ማስረጃ ሐሰተኛነቱ ከውሳኔው በኋላ ማስረጃውን በላከው አካል ተረጋግጧል በሚል የቀረበውን የዳግም ዳኝነት ይታይልን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በላይ ጋይነት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 02162 ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ ሲጀመር የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካችና አመልካች እና አቴ ብርሃን ደመቀ ደግሞ ተከሰሽ ነበሩ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘትም፡- ቁበላይ ገይንት 01 ቀበሌ አስተዳደር መኮቢያ ገብሬኤል ገብር ውሥት ጥሩ 498/ለ እና 501 የሆኑ ቤቶች ግማሹ የሚች አባታችን የአቶ ገብሬ ድንቅነህ ሲሆኑ ወረሾች ነን፣ ግማሹን ደግሞ ሚች ወ/ሮ ብዙነሽ አደራ በኑዛዜ ሰጥተውናል በማለት ቤቱን ተጠሪዎች ያላግባብ መያዛቸውን ዘርዝረው ቤቱ እንዲለቀቀ ይወሰን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎችም ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከማቅረባቸውም በተጨማሪ በፍሬ ነገሩም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን መሰረት

www.abyssinialaw.com

አድርጎ ጉዳዩን በመመርመር የአመልካቾች ክስ ከሰላሳ ሶስት አመት በኋላ የቀረበ ነው በማለት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ሲል በመ/ቁጥር 75780 የተከፈተውን መዝገብ ዘግቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካቾች የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ብዙነሽ አደራ ወራሽነትን በመጠየቅ የሟቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 147267 የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ተቃውመው ፍርድ ቤቱን ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪው የሟቿ ልጅ ሳይሆኑ የወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸውን አመልካቾች አረጋግጠዋል ተብሎ የቀደመው የወራሽነት ማስረጃ እንዲረዝ ታህሳስ 09 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶአል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልቾች የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75780 የተሰጠውን ብይን በሕገ ወጥ መንገድ በተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ምስክር ወረቀት ያሰጡት ብይን ነው በማለት በድጋሚ እንዲታይ ዳኝነት ጠይቀው ፍርድ ቤቱም በይርጋ የተዘጋ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሰረት በድጋሚ የሚታይበት አግባብ የለም በማለት ሳይቀባላቸው ቀርቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-3ኛ ተጠሪ ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ሐሰተኛ ነው ከተባለ ተጠሪዎች ይህንኑ የሚያስተባብል ማስረጃ ባላቀረበቡት ሁኔታ የውርስ ንብረቱን አይለቁም ተብሎ የተሠጠው ብይን በዳግም ዳኝነት የሚታይ አይደለም ተብሎ የአመልካቾች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካቾች የቀደመው ክስ በይርጋ የታገደ ን በሚል ምክንያት የዳግም ዳኝነት ጥያቄው ሳይታይ የመታለፉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን 1ኛ፣2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ሊቀርቡ ስላልቻሉ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎአል፡፡ 3ኛ ተጠሪ ግን ቀርበው በሠጡት መልስ፡-የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ስርዓቱን ያልጠበቀ መሆኑን፣ የአመልካቾች የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በይርጋ ውድቅ የሆነበት መ/ቁጥር 75780 እና የተጠሪን የወራሽነት ማስረጃ ያሰረዙበት መዝገብ ቁጥር 147267 ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ የዳግም ዳኝነት ጥያቄው የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የተሰጠው ተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ተፈፅሞና ተገቢው ጭብጥ ተይዞ፣ በሕጉ አግባብ

www.abyssinialaw.com

መጣራት ተደርጎ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ድንጋጌዎች ይዘት መመልከቱ ተገቢ ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኑ አመልካቾች ለወረዳው ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሰረት ዳግም ዳኝነት እንዲታይላቸው በመጠየቅ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም አቤቱታውን በጉዳዩ ላይ ቀድሞ ፍርድ ቤት ከተሠጠበት መዝገብ ቁጥር 02162 ውጭ በመቀበል ተጠሪዎችን ያቀረቡት አቤቱታ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 6 መሰረት ሊስተናገድ እንደማይችል በማመን የአመልካቾች የቀድሞ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን የተሰጠበት በመሆኑ በዳግም ዳኝነት ስርዓት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት አቤቱታው ውድቅ አድርጎታል፡፡

ይህ ችሎት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ይዘቱንና መንፈሱን ከሌሎች የፍተሓብሔር ሥነ ስርአት ውስጥ ከተመለከቱት የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች እና የፍርድ መቃወሚያ ስርዓቶች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የድንጋጌው ዓላማ በእውነት ላይ የተመሰረተ ዳኝነት እንዲሠጥ ማድረግ ከመሆኑ አኳያ በመመርመር ለተጠቀሰው ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ መሰረት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም በመ/ቁጥር 43821 እና በመ/ቁጥር 32269 ሠጥቶበታል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 43821 ላይ በቀረበው ጉዳይም ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 16624 የያዘውን አቋም ማለትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 መሰረት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ መቅረብ ያለበት ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት እንጂ በይግባኝ ቀርቦ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ አይደለም በማለት የሠጠው የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት ተለውጧል፡፡ በዚህም መሰረት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ውሳኔ ከተገኘ በሁዋላም ቢሆን በቁጥር 6 ስር የተመለከቱት መመዘኛዎች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ መቅረብ እንደሚችል ተግለጸ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው የሕግ ነጥብ /ጉዳይ/ የአመልካቾች ጥያቄ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6(2) ስር የሚወድቅ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ስለሆነ ይህን ድንጋጌ ማየቱ ለጉዳዩ አወሳሰን ይጠቅማል፡ ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ከተሰጠ በኂላ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ የተሰጠው በሃሰት ተዘጋጅቶ በቀረበ ሰነድን ሃሰተኛ የምስክርነት ቃልን፣ ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቅሶ የሆነ ተግባርን መሰረት አድርጎ መሆኑን አቤት ባዩ ሲረዳው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ውሳኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ ዳኝነቱን በድጋሚ እንዲያይ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጠው ነው፡፡ የድንጋጌው ሙሉ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው የመጨረሻው ፍርድ ከተሰጠ በሁዋላ ሀሰተኛ ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ወይም መደለያ እንደተደረገና አቤት ባዮም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ ያለመቻሉን በሚገባ ለማስረዳት የሚችል የሆነ እነደሆነ፣እነዚህ ጉዳዮች መኖራቸው ወይም መፈጸማቸው ታውቆና ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለፍርድ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችል እንደነበር ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣ የተሰጠ ፍርድ ሊያስለውጥ የሚችል አዲስ ማስረጃ ማግኘቱ ብቻ ፍርድ

www.abyssinialaw.com

እንደገና እንዲታይ የማያደርግ መሆኑን፣ ማስረጃው ፍርዱን በማሳሳት ውጤቱን ያበለሸና ተገቢ ያልሆነ ድርጊትን የሚያሳይ መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ማስረጃውም በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድን፣ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ ተግባርን መሰረት ያደረገ መሆንና ማስረጃው ፍርዱ በሚሰጥበት ጊዜ ፍርዱ እንደገና ይታይልኝ የሚለው ተከራካሪ ወገን ማስረጃው መኖሩን ያውቀው የነበረ ያለመሆኑ፣ ይግባኝ ቀርቦበት ከሆነ አዲስ ማስረጃው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ይግባኙ ለቀረበለት ፍርድ ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑ፣ የተገኘው አዲስ ማስረጃ የሀሰት ሰነድን፣ ሀሰተኛ ምስክርነትን፣ መደለያንና የመሳሰሉትን የሚመለከት ለመሆኑ ማረጋገጫ መኖሩን በሚጠቅስ ቃለመሐላ የተደገፈና ማስረጃው አስፈላጊው ትጋት የተደረገበት ቢሆንም ፍርዱ በተሰጠ ጊዜ በአመልካቹ ያልታወቀ መሆኑን የሚገልፅ መሆን ያለበት መሆኑ በቅድመ ሁኔታነት ሊሟሉ የሚገባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ድንጋጌው ያስገነዝባል፡፡ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ጥብቅ መለኪያዎች ያሉት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ሲሆን የድንጋጌው ጥብቅ የመሆን አይነተኛ አላማም የተሰጡ ውሳኔዎችን አጣራጣሪነት ለማስወገድ መሆኑ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት የሆነው ሰነድ ወይም ማስረጃ ሐሰተኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በሕጉ የተመለከቱት ሁሉም መመዘዎችን አቤቱታ አቅራቢው ማሟላቱን በቅድሚ ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የሚከራከሩት 3ኛ ተጠሪ አለኝ የሚሉት የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰረዝ ተደርጎአል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት ይህ የሰነድ ማስረጃ ሐሰተኛ ነው ከተባለ 3ኛ ተጠሪ በመ/ቁጥር 75780 በነበረው ክርክር የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ይችል ነበር ወይስ አልነበረም?፣ በአመልካቾች ላይ የይርጋ መቃወሚያውን ሊያነሳ የሚችልበት ሕጋዊ መብትና ጥቅም አለው ወይስ የለውም?፣ ይርጋ ለማንሳት የሚችል ከሆነስ ለግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ ምን ያህል ነው፣ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ከተለየ በኋላስ የአመልካች የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትንና ይህ ሁሉ የሚታለፈ እና ወደ ፍሬ ነገሩ የሚገባ ከሆነ ደግሞ አከራካሪ ቤቶች የውርስ ንብረት መሆን ያለመሆናቸውንና ለአመልካቾች የሚለቀቁበት አግባብ መኖር ያለመኖሩ በጭብጥነት ተይዞ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢው ዳኝነት የሚሠጠበት ይሆናል፡፡ ስለሆነም አንድ ክስ በይርጋ መዘጋቱ የዳግም ዳኝነት ጥያቄውን ላለማስተናገድ እንደበቂ ምክንያት የማይወሰድና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ድንጋጌም በመመዘኛነት ያልተቀመጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት ያስቀመጠውን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካቾች የዳግም ዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ስር የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎችን ያማሏ መሆን ያለመሆኑ በቅድሚያ ከታዬ በኋላና ጥያቄያቸው በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟላ ነው የሚባል ከሆነም በመልካቾች እና

www.abyssinialaw.com

በተጠሪዎች መካከል ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ ተለይቶ ክሱ አግባብነት ባለው የይርጋ ጊዜ ቀሪ የማይሆን ከሆነም ግራ ቀኙ በፍሬ ነገሩ ክርክር አድርገውበትና በተገቢው መንገድ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነትም በተጨማሪ ማስረጃዎች አጣርቶ እንዲሁም ወደ ክርክሩ ሊገባ የሚገባው አስፈላጊ አካል ካለም ወደ ክርክሩ እንዲገባ አድርጎ ክርክሩን ከመራው በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊወሰንበት የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 75780 ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡
2. የአመልካቾች የዳግም ዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 6 ስር የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎችን ያሟላ መሆን ያለመሆኑ ሳይጣራ ክሱ በይርጋ ውድቅ የሆነ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ተቀባይነት የሚያጣበት አግባብ የለም፣ አቤቱታቸው በሕጉ የተመለከተውን መመዘኛ ያሟላል ከተባለም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ተለይቶና በስነ ስርዓት ሕጉ አግባብ ክርክሩ ተመርቶ ተገቢው ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል ብለናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 75780 ቀጥሎ በፍርድ ሐተታው ላይ ስለዳግም ዳኝነት አቀራረብ ስርዓትና መመዘኛዎች እንዲሁም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለውን ይርጋ ጊዜ በመለየት እና የአመልካቾችን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም የተጠሪዎችን ክርክርና ማስረጃ በመመርመርና እውነታውን ለማወቅ የሚረዱ የሰነድ ማስረጃዎችን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 145(1) መሠረት በማስቀረብ፣ የክርክሩ አስፈላጊ ወገን ካለም ወደ ክርክሩ በማስገባት አከራካሪውን ቤት የማን ነው? በሚለው ላይ ተገቢውን ሁሉ በማጣራት ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 116209

የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች - የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - አልቀረቡም

ተጠሪ - ወ/ሮ ምፅላል አብርሃ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው በግራ ቀኙ መካካል ባለው የንብረት ካሳ ክርክር በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማዕከላዊ ዞን ማዕከላዊ ፍርድ ቤት የአብይ አዲ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 02634 ግንቦት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈውን ብይን በመቃወም ነው ፡፡ አመልካች ይግባኝ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ብር 791,225.00 (ሰባት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አምስት) በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመወሰን ስልጣን የለዉም፤ እንዲሁም በስር በተደረገ ክርክር ተካፋይ አልነበርኩም የሚሉ መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም መቃወሚያዎችን ከመረመረ በኂላ ባሳለፈው ብይን ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 11(4) እንዲሁም የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(4) ስር እንደተደነገገው ካሳን በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ለሚመለከተው የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሌለበት ለሚመለከተው መደበኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችል ከሚደነግጉ በቀር የተጠቀሱት አዋጆች በካሳዉ ግምት መጠን ወደተለያየ ፍርድ ቤት ይግባኝ እንደሚቀርብ የሚደነግጉ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ብሏል፡፡ ሁለተኛውን መቃወሚያ በተመለከተም የአሁን አመልካች እየተሰራ ያለው መንገድ ባለቤት በመሆኑ ለመንገድ ስራ ስለተወሰደው መሬት እና በመሬቱ ላይ ስለነበረው ንብረት ካሳ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት

www.abyssinialaw.com

በአዋጁ በግልፅ ስለተደነገገ፤ በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ፊት ተከራካሪ አልነበርኩም የሚል ክርክር ቢያቀርብም በስር የተወሰነውን ካሳ ከፋይ ከሆነ በካሳው መጠን ላይ ለቀረበው ይግባኝ መልስ እንዲሰጥ እና እንዲከራከር መደረጉ በአግባቡ ነው በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህን ተከትሎም የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት ቀጠሮ ለውጧል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ የቀረበው አመልካች ያነሳቸውን መቃወሚያወች ውድቅ በማድረግ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመቃወም ነው ፡፡ አመልካች ሀምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም ያቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ መቃወሚያዎቹ ውድቅ ተደርገው ወደ ክርክሩ ለመግባት የተሰጠውን ብይን ስነስርዓታዊነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል ፡፡ በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ ተለዋዉጠዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን በመጀመሪያ በሰበር የተያዘውን ጭብጥ ከመወሰናችን በፊት ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትና በሰበር መታየት የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የሰበር አቤቱታ የቀረበው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቶ ክርክር ለመስማት ቀጠሮ መያዙን በመቃወም ነው ፡፡ ነገር ግን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዳኝነት አይቶ ውሣኔ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንኡስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል ፡፡ ከዚህም ሌላ ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በመጀመሪያ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን ሲሰጥ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) ሊቀርብ እንደማይችል ፤ ስለሆነም ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመቃወሚያው ላይ በተሰጠው ብይን ያለውን ቅሬታ ጨምሮ ከስረ ነገሩ ጋር ይግባኝ (የሰበር አቤቱታ) ለማቅረብ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 320(3) ስር ተደንግጓል

ቅሬታ የቀረበበት ብይን ይዘትና ተገቢነት ያላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ከላይ የተመለከተው በመሆኑ አመልካች በተሰጠው ብይን ላይ ቅሬታ ካለውም በስረ-ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይህንን ቅሬታም ጨምሮ በአንድ ላይ በማጠቃለል ያቀርባል እንጂ ክርክሩ እንዲቀጥል በተደረገበት ሁኔታ በብይኑ ላይ የሰበር አቤቱታ ማቅረቡ ህጉን መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1. አመልካች ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ ሳያገኝ ለሰበር ችሎት ያቀረበውን አቤቱታ ለማስተናገድ የሚቻልበት የህግ መሠረት የሌለ በመሆኑ አቤቱታውን አልተቀበልነውም፡፡

2. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማዕከላዊ ዞን ማዕከላዊ ፍርድ ቤት የአብይ አዲ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 02634 ግንቦት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ባሳለፈው ብይን ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት የሰበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚቻል አይደለም ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ በ05/01/2008 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም ዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡

4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

# ቤተሰብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 113973

ቀን 21/04/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጠጅቱ ኡርጋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገመዳ ሬባ - አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ሜታ ሮቢ ወ/ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች በዚህ ወረዳ ፍ/ቤት ባለቤታቸው በነበሩት አቶ አሰፋ ገመዳ ላይ ክስ የመሰረቱት ኤጴ ከተባለ አከባቢ የሚገኝ ሁለት የበሬ መዋያ መሬት እና ሰምንተኛ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ግማሽ የበሬ መዋያ ይዞታ መሬታችንን እኩል እንደንካፈል ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው የተጠቀሰው ይዞታ መሬት የጋራ ይዞታችን አይደለም ሊካፈል አይገባም ብለዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ግራ ቀኙ የሚከረከሩበት መሬት የግል ይዞታዬ ነው በስሜ ተለክቶ የሚገኝ እና በስሜ የምግብርበት ነው ከሳሽና ተከሳሽ በዚህ መሬት ላይ አንዳችም መብት የላቸውም ብለው ተከራካረዋል፡፡

ከሳሽ (የአሁኑ አመልካች) በበኩላቸው ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት በ1994 ዓ/ም ከተከሳሽ ጋር ስንጋባ የተከሳሽ አባት የሆኑት ጣልቃ ገብ ሰጥተውን በጋብቻ ውላችን ላይም ተጠቅሶ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ በይዞታችን ስር ሆኖ ስንጠቀምበት ቆይተናል፡፡ ሰሞንኛ ተብሎ ከሚታወቀው አካባቢ ባለን ይዞታ ላይ ቤት ያለን ሲሆን በመ/ቁ. 15710 እና 14792 በሆኑ መዝገቦች በዚህ ቤት ውስጥ ሆኜ ልጆችን እንደሳደግ ፍ/ቤት አዞልኛል የጣልቃ ገብ አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ ብለው ተከራከረዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙ ምስክሮችን ሰምቶ ክርክራቸው ከቀረበው ማስረጃ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት በጋብቻ ውሉ ላይ የተመዘገበ እና ከሳሽና ተከሳሽ ይዘውት ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ ጣልቃ ገብ የመሬቱ ይዞታ በስማቸው የሚገኝና ግብር በስማቸው የሚገብርብት ቢሆንም ከሳሽና ተከሳሽ ይዘው የሚጠቀሙበትን መሬት ጣልቃ ገብ መጠየቅ አይችሉም ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት ከሳሽና ተከሳሽ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ጣልቃ ገብ (የአሁኑ ተጠሪ) በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት የስር ከሳሽና ተከሳሽ ሲጋቡ ይ/ባይ (የስር ጣልቃ ገብ) የሰጠው መሆኑን የስር ከሳሽ ምስክሮች ያስረዱ ቢሆንም መሬት የሚሰጠው በቃል ሳይሆን በጽሁፍ ማስረጃ ሆኖ ስልጣን ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበት ከገጠር መሬት አዋጅና ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መረዳት ይቻላል፡፡ መሬቱ የጣልቃ ገብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለይግባኝ መልስ ሰጭ ከባለቤታቸው ጋር በህጋዊ መንገድ የተሰጠ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የጋብቻ ውሉም ለወደፊቱ ከአባታችን ላይ የምናገኛው መሬት የሚል በመሆኑ እና ከዚያ ወዲህም የተደረገ ስጦታ የሌለ በመሆኑ ክርክር ያስነሳው መሬት የይግባኝ ባይ (የስር ጣልቃ ገብ) ይዞታ ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ ክርክር ያስነሳውን መሬት ይ/ባይ ከስር ተከሳሽ ጋር በሚጋቡበት ጊዜ በጋብቻ ውላቸው ላይ የተገለጸ እና ከዚያ ወዲህ ይ/ባይ ከባለቤታቸው ጋር እየተጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ ተመስክሯል የቀበሌው አስተዳደር ለወረዳ ፍ/ቤት በጻፈው ሪፖርት ላይም መሬቱን ተጋቢዎቹ በጋራ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን ገልጿል፡፡ የመሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ለወ/ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ መሬቱ በመልስ ሰጭ (በስር ጣልቃ ገብ) ስም የተለካ መሆኑን ነገር ግን እየተጠቀሙበት ያሉት ተጋቢዎቹ መሆናቸውን ገልጿል፡፡ መሬቱ በጋብቻ ውል ላይ የተጠቀሰ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱም ከዚያ ወዲህም ተጋቢዎቹ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ መ/ሰጭ በስሙ በመመዝገቡ ብቻ እስካሁን ያልተጠቀሙበትን መሬት በስሜ ተለክቷል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ቤት የሰሩበትን መሬት ይ/ባይ ቀደም ሲል እንደኖርበት በፍ/ቤት ተውስኖልኛል ብለው ያቀረቡትን መከራካሪያ መ/ሰጭ አላስተባበሉም ክርክር ያስናሳውን መሬት ይ/ባይ ከባለቤታቸው ጋር ሊካፈሉ ይገባል በማለት የከፍ/ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለማስረም ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማገናዘብ መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ተጠሪዋ ከባለቤቷ አባት (ከአመልካች) ያገኙትና ለ9 ዓመት ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ የገጠር መሬት አጠቃቀም ደንብ እና

www.abyssinialaw.com

ፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 መሰረት የገጠር መሬት ስጦታ በጽሁፍ መሆንና መመዝገብ አለበት ተጠሪ መሬቱን በጋብቻ ወቅት በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ አግባብነት ያለው ማስረጃ አቅርበው ያላረጋገጡ በመሆኑ ክርክር ያስነሳው መሬት የአመልካች (የስር ጣ/ገብ) ይዞታ ነው በማለት ወረዳ እና የጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት ውሳኔን በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ በመዘርዘር እንዲታረምላቸውን አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን 2 ጥማድ እርሻ መሬት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ከስር ተከሳሽ ጋር እስከተፋቱበት ጊዜ 2003 ዓ/ም ድረስ በጋራ ሲጠቀሙ መቆየታቸው ተረጋግጦ እያለ መሬቱን ልትካፈል አይገባም ተብሎ ጥያቄዋ በክልሉ ሰበር ችሎት ተቀባይነት የማጣቱን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው እንዲመረመር ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ክርክር ያስነሳውን መሬት አመልካች የስር ተከሳሽ ከነበሩበት ባለቤታቸው ጋር በ1994 ዓ/ም ሲጋቡ የባለቤታቸው አባት የሆኑት ተጠሪ ሰጥተዋቸው በጋብቻ ውላቸው ላይም ተጠቅሶ ጋብቻ ከመሰረቱበት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ጋብቻው በፍቺ እስከፈረሰበት 2003 ዓ/ም ድረስ ተጋቢዎቹ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተረጋግጧል፡፡ ክርክር ያስነሳው መሬት ተመዝግቦ የሚገኘው እና ግብር የሚከፈልበት በተጠሪው ስም ቢሆንም ይህን መሬት ለአመልካቹ እና ለባለቤታቸው ሰጡ ከተባለበት ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ/ም ድረስ ተጠሪ ተጠቅመውበት የማያውቁ መሆኑና ሲጠቀሙበት የቆዩት አመልካች ከባለቤታቸው (የስር ተከሳሽ) ጋር መሆኑ በስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ማንኛውም አርሶአደር በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብቱን በዚያ መሬት ገቢ ለሚተዳደሩ ወይም ሌላ ገቢ ለሌላቸው የቤተሰብ አባላት ወይም መሬት ለሌላቸው ልጆቹ በስጦታ ማስተላለፍ እንደሚችል በኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1997 አንቀጽ 9(5) ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በጽሁፍ የተደረገ የስጦታ ውል ባይኖርም ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ያለ መሆኑን ነገር ግን እየተጠቀሙበት ያሉት አመልካች እና ባለቤታቸው መሆኑን ገልጻ ለሜታ ሮቢ ወ/ፍ/ቤት መልስ የሰጠ ሲሆን የቀበሌው አስተዳደርም ለስር ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን ገልጿል፡፡ ስር ፍ/ቤት ቀርበው የተሰሙ የአመልካች ምስክሮችም

www.abyssinialaw.com

መሬቱን ተጠሪ ሰጥተዋቸው አመልካችና ባለቤታቸው ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ተጠሪ ለክርክር ምክንያት በሆነው መሬት ላይ የነበራቸውን የመጠቀም መብት ልጃቸው የሆነው የአመልካች ባለቤት ከአመልካች ጋር ጋብቻ ሲፈጽሙ በዚህ መሬት እንዲተዳደሩ በአባትነታቸው አስልፈው ሰጥተው ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች ከባለቤታቸው ጋር በፍቺ ውሳኔ እስከተለያዩበት 2003 ዓ/ም ድረስ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ በመሬቱ የነበራቸውን የተጠቃሚነት መብት ካስተላለፉ በኋላ መሬቱ ተመዝግቦ የሚገኘው እና ግብርም የሚከፈለው በተጠሪው ስም ብቻ በመሆኑ መሬቱ ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት እንደቤተሰብ በእኔ ስር ሆነው አመልካች ባለቤቷ ተጠቀሙ እንጂ በግላቸው ስር ሆኖ አንድም ቀን አልተጠቀሙበትም በማለት ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት መልስ የተጠቀሱ ቢሆንም ይህን ስር ፍ/ቤት በነበረው ክርከራቸው አላስረዳም፡፡ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተረጋገጠው መሬቱን ተጠሪ ለአመልካች ከሰጡ በኃላ ሲጠቀሙበት የቆዩት አመልካች እና ባለቤታቸው መሆናቸውን ነው፡፡ በገጠር መሬት ላይ የሚኖረው መብት የመጠቀም መብት ሲሆን ተጠሪ ይህን መብታቸውን ለአመልካችና ባለቤታቸው አሳልፈው ሰጥተው ለረጅም ጊዜ በዚህ መሬት ላይ ተጠቃሚነታቸው በተቋረጠበት ሁኔታ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በጽሁፍ የተደረገ ስጦታ ውል አለመኖሩን ብቻ መሰረት በማድረግ በክርክሩ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆነ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 55478 በቀን 3/03/2006 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.186326 በቀን 26/08/2007 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ሜታ ሮቢ ወ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.15357 በቀን 10/01/2006 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 170790 በቀን 8/11/2006 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት የአመልካች እና ባለቤታቸው የነበሩት የስር ተከሳሽ የጋራ ይዞታ ነው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ላደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡** የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 105054

ታህሳስ 22 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጌጤ እጅጉ -ቀርበዋል

ተጠሪ፡-አቶ ብርሃኑ ተሰማ -ቀርቧል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ የአቤቱታውን ይዘትም ባጭሩ በመ/ቁ.343/96 በቀን 21/8/1996 ዓ/ም የነበረው ጋብቻ ሲፈርስ ንብረት ክፍፍል በሚመለከት በእርቅ ውል ስምምነት በሽማግሌ የተደረገው እርቅ በፍርድ ቤት ተመዝግቦ ተዘግተዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም አንድ ወፍጮ ቤት፤ አንድ የዘይት መጭመቂያ ቤት እና አንድ ፒፒሻ ሸጉጥ የተጠሪው እንደሆነ ፍርድ ቤት በውሳኔው አረጋግጠዋል፡፡ ከውሳኔ በኃላ ታርቀን በባልና ሚስት ሆነን ስንኖር የዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት መ/ቁ.19963 በቀን 9/8/ 2005ዓ/ም እና የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.6054 በቀን 19/10/05ዓ/ም በመ/ቁ. 343/96 በሆነው መዝገብ ላይ የተሰጠ የንብረት ክፍፍል እንዳይነካ ሲል ተወስነዋል፡፡ ስለዚህ የወፍጮ ቤት የነበረው አሁን የእንጨት መሰንጠቂያ የሆነው እና የዘይት መጭመቂያ ቤት ስም ይዛወርልኝ ፒፒሻ ሽጉጥ ታስረክበኝ ወይም ግምቱ 26,000 ብር እንዲከፈለኝ ሲሉ አፈፃፀም መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በሰጡት መልስ በ1996 ዓ/ም ባልና ሚስት መሆናችን የማይካድ እውነት ነው፡፡ ትዳር ሲፈርስ ለኔ የተሰጠኝ የያዝኩት እንጂ የተጠሪ አይደለም፡፡ ያልተወሰነበት የሚፈፅምበት ነገር የለም፡፡ በእጄ የሌለውን ነገር ለመፈፀም አልገደድም፡፡ ጋብቻ ከፈረሰ የሰራሁት በስሜ ካርታ አውጥቼ የሚሰራበት ነው በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ማስረጃ በመመዘን በውሳቸው መሰረት መፈፀም አለበት በማለት የዘይት መጨመቂያና የወፍጮ ቤት የነበረ ወደ እንጨት መሰንጠቂያ የተቀየረው ወደ ተጠሪ ስም እንዲዛወር እና ሽጉጥ እንዲያስረክቡ ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡

በዚሁ ትእዛዝ ላይ ከአሁኑ አመልካች ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በሽጉጥ የተሰጠው ትእዛዝ በማሻሻል በሌሎቹ ንብረቶች ላይ የስር ፍርድ ቤት በማፅናት ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ በመቀጠል ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ በአመልካች በመቅረቡ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ የዘይት መጭመቂያ በተመለከተ የተሰጠው ትእዛዝ በማፅናት፤ ወፍጮ ቤት የነበረው ወደ እንጨት መሰንጠቂያ ቤቱ የተጠሪ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ እንጨት ድርጅት ሲቀየር ማሽኖቹና መሳሪያዎቹ የተገዙት እንደ ባልና ሚስት በአንድ ቤት በሚኖርበት ጊዜ ስለሆነ ማሽኖቹና ዕቃዎቹ በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ወይም በጨረታ በመሸጥ እኩል እንዲካፈሉ በማለት በመሻሻል ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለበትም ሲል አቤቱታው ሳይቀበለው በትእዛዝ ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ የእንጨት ድርጅት የተቋቋመው ወፍጮ ቤት የነበረው በ1996ዓ/ም በስምምነት ከተካፈሉ በኃላ እንደገና እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ መሆኑ ባልተካደበት በተደረገው የንብረት ክፍፍል ስምምነት መሰረት ቤቱ የተጠሪ ነው ተብሏል በሚል መነሻ አመልካች በአፈፃፀም መዝገብ ላይ ለተጠሪ እንድትለቅ የተሰጠው ትእዛዝ ህጋዊ የክርክር አካሄድና አመራርን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባ ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን በዚህ መሰረትም በጭብጥነት በተያዘው ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክስ ስለሆነ በዋናው ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈፀም መደረግ አለበት፡፡ በግራ ቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ በመሐከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺ ሲፈርስ የንብረት ክፍፍል በስምምነት በማድረግ በፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ነው፡፡ ከፍቺ በኃላም እንደባልና ሚስት አብረው እየኖሩ እንደነበር በስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ በ2005ዓ/ም የአሁኑ ተጠሪ የፍቺ ክስ ለፍርድ ቤት አቅርበው ነገር ግን ጋብቻ የለም ግንኙታቸው

www.abyssinialaw.com

እንደ ባልና ሚስት አብረው እንደሚኖሩ ሰዎች የሚባል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አብረው ያፈሩት ንብረት የጋራ እንዲሆንና በ1996 ዓ/ም የተደረገው ክፍፍል የተጠበቀ መሆኑን ውሳኔ ተሰጥተዋል፡፡

ውሳኔው ይህ ከሆነ አፈፃፀሙን የዘይት መጭመቂያና የወፍጮ ቤት ለተጠሪ የደረሰው መሆኑን አመልካችም የራስዋ ድርሻ እንደያዘች ከስር መዝገብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከፍቺ በኃላ አብረው መኖር ከጀመሩ ያፈሩት ንብረት መኖር አለመኖሩን ለማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ወፍጮ ቤት የነበረው ወደ የእንጨት ድርጅት ሲቀየር የተለያዩ ማሽኖችና ዕቃዎች አብረው ያፈሯቸው እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም አብረው ያፈሩት ማሽኖችና እቃዎች እኩል እንዲካፈሉ፤ ቤቱ ደግሞ ለተጠሪ እንዲሆን በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠ/ ፍ/ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.181913 በቀን 12/10/2006 ዓ/ም የስር

ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማሻሻል ሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.185727 በቀን 22/11/2006ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት አጽንተናል፡፡

2. በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነሰተዋል ለሚመለከተው አካል ይተላለፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.102662

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ለሼ- ጠበቃ ኤርሚያስ ደስታ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ በቀለ በላቸው- ወኪል ትርፍነሽ በቀለ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻ ፈርሷል ሊባል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደብረብርሃን ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ክሱን ያቀረቡት የአሁኑ አመልካች ናቸው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በአገር ባህል የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት ጋብቻ ፈጽመው ለአርባ አመታት ያህል አብረው መኖራቸውን፣ ይሁን እንጂ ከመስከረም 2006 ዓ/ም ጀምሮ ሊስማሙ ባለመቻላቸው በመካከላቸው ሰላም እንደሌለ ገልፀው ጋብቻው ፈርሶ የጋራ ንብረት እንዲካፈሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ከአመልካች ጋር ባልና ሚስት የነበሩ መሆኑን ሳይክዱ አመልካች ከአስራ ዘጠኝ አመታት በፊት ቤቱን ጥለው መሄዳቸውንና ተለያይተው የሚኖሩ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያስቀደሙ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ከአመልካች ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የሥር ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ከአስር አመታት በፊት ፈርሷል የሚል ድምዳሜ ደርሶ የአመልካች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል፡፡እንዲሁም የወረዳው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲመጣ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በተጠሪና በአመልካች መካከል ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ተገቢነት አለውን? የሚለውነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ በአመልካችናበተጠሪ መካከልየነበረውጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር አልተቀበለውም፡፡ ፍርድ ቤቱ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነታቸው ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ ተቋርጦ ግራ ቀኙ ለየብቻ መኖር መጀመራቸው ተረጋግጧል በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡ ይህ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ባለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት አጥብቀው የሚከራከሩት ግራ ቀኙ ሌላ ትዳር መስርተው የራሳቸውን ሕይወት የማይኖሩ መሆኑን፣ አልፎ አልፎ በጤና ምክንያት አመልካች ለፀበል ወደ ሌላ ቦታ ከመሄዳቸው ውጪ አመልካችና ተጠሪ ያልተለያዩና እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ አንድ ላይ የሚኖሩ መሆኑን ዘርዝረው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው አስገዳጅ ውሳኔ ተጠቅሶ መወሰኑ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14290፣ 20983፣ 31891፣ 67924 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገውና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 31891 ሌሎች ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት በሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች በባልና ሚስት መካከል ያለ ጋብቻ በፍ/ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሷል ባይባልም የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረጅም ጊዜ መኖር፣ በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መሥርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተቋርጧል ሊያስብል ይችላል በማለት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም ውሳኔ ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የጋብቻ መፍረስ በተጋቢዎች የረዥም ጊዜ መለያየት ሊከናወን የሚችል መሆኑና ፍርድ ቤቱም በዚህ አግባብ የፈረሰውን ጋብቻ እንደገና እንዲፈርስ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 67924 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ አግባብ የመተጋገዝና የመተባበር ግዴታቸውን

www.abyssinialaw.com

ሲወጡና የነበሩና ያልተለያዩ መሆኑ ከተረጋገጠ ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ለማለት የማይቻል መሆኑን በመዝገቡ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች በመነሳት የተወሰነ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካችና ተጠሪ በሕጉ አግባብ ጋብቻ መሰርተው ልጆችን ከወለዱ በኋላ በ1987 ዓ/ም ጀምሮ በአካል ተለያይተው ለአስራ ዘጠኝ አመታት ያህል ሳይገናኙ የኖሩ መሆኑን ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል የተረጋገጠ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ደምድመዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀረበው የወረዳው ፍርድ ቤት ዋና መዝገብም የግራ ቀኙ ምስክሮች የመሰከሩት የፍሬ ነገር ነጥብ በይዘቱ የበታች ፍርድ ቤቶች ከደመደሙት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ተገንዝቦአል፡፡ በመሆኑም አመልካች ከተጠሪ ጋር እስከ መስከረም 2006 ዓ/ም ድረስ አልተለያየንም በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ በስር ፍርደ ቤት ዋና መዝገብ ውስጥ በምስክሮች ከተነገረው የምስክርነት ቃል ይዘትና ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ከደረሱበት ድምዳሜ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች አግባብ የተሰጠውን ስልጣንም ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል የመተጋገዝ፣ የመከባበርና መደጋገፍ እንዲሁም አብሮ የመኖር ግዴታን የሚጥል መሆኑን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 60 እና 61 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚሁ አኳያ በተጠሪና በአመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ ይህ ሰበር ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ተቋርጧል? ወይንስ አልተቋረጠም? የሚለውን ለመወሰን ከፍ ብሎ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በጋብቻ ውስጥ በግራ ቀኙ የሚጠበቁ ግዴታዎች ባግባቡ ሲተገበሩ ያልነበሩና እነዚህን ግዴታዎችን ለመወጣት ደግሞ በአመልካች በኩል ያጋጠመው ሁኔታ በሕጉ የተጣሉባቸውን ግዴታቸውን ለመወጣት የማያስችል የነበረ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪ ጋር አልተለያየንም፣ በጤና ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ ለፀበል ሌላ ቦታ እሄድ ነበር በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በክርክሩ ሂደት በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን መሰረት አድርጎ ያልቀረበ ሁኖ አግንተነዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተያዘው መዝገብና ይህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው መዛግብት የያዟቸው መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ከዚህ መዝገብ ከተረጋገጡት እውነታዎች ሙሉ በሙሉ የተመሳሳይነት ያላቸው ሁኖ እያለ አመልካችም ሆነ ተጠሪ ሌላ ትዳር መስርተው ሕይወታቸውን በመምራት ላይ አይገኙም በማለት በሰ/መ/ቁጥር 31891 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመተውና ግንኙነቱ ያልተቋረጠ ተጋቢዎችን መሰረት ተደርጎ በመ/ቁጥር 67924 የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች መከራከራቸው ከአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (1) አተገባበር ጋር የሚጋጭ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በሁኔታ የፈረሰ

www.abyssinialaw.com

በመሆኑ እና ለጉዳዩ አግባብነት በላቸው ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት በተሰጠው ትርጉም መሰረት የጋራ ንብረት ጥያቄም በአስር አመት ያልቀረበ በመሆኑ የተጠሪ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ብይን መሰጠቱ የሚነቀፍበትን የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሁኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0108191/06 በ22/08/2006 ተሠጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0114418 በ30/08/2006 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 030-5041 ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአገር ባህል የጋብቻ አፈፃጸም ስርዓት ተመስርቶ የነበረው ጋብቻ ለረዥም ጊዜ ተለያይቶ በመኖር ምክንያት ፈርሷል በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

ከደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርደ ቤት የመጣ መዝገብ ቁጥር 0108191/06 በመጣበት አኳሀን ይመለስ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 116977

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች** ፡- ወ/ሪት ሃና ታምራት ጠበቃ አሰፋ ካሳ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የለም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረጉና በየደረጃው ያሉ የከተማው አስተዳደር የበላይ ፍርድ ቤቶችም የመ/ደ/ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናታቸው ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 08 ቀን 2007 ዓ/ም ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ቃሉ፡- ቀድም ሲል ጸሐይ ብርሃኔ እና ሀና ታምራት እየተባልኩ በሁለት ስም ስለምጠራ ጸሐይ ብርሃኔ መባሌ ቀርቶ ሃና ታምራት ብቻ እየተባልኩ እንድጠራ ውሳኔ ይሰጠኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም አመልካች የአቶ ታምራት አመዴ ልጅ ለመሆናቸው ከሚመለከተው ፍርድ ቤት የልጅነት ውሳኔ ይዘው ሲቀርቡ መዝገቡ ይቅረብ በማለት መዝገቡን የዘጋው ሲሆን በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ይግባኛቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸው ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ የአመልካቸ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ሁለት ስም የነበረኝ በመሆኑ የግል ስሜና የወላጅ አባቴ ስም ተቀይሮ በአንዱ የግል ስም እና በአሳዳጊዬ የቤተዘመድ ስም እንድጠራ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ከሕግ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች በወላጅ አባቴ ስም እንዲጠራ ይወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመርህ ደረጃ አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም( family name)፣አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች( first names) እና የአባት ስም( patronymic ) እንደሚኖረው በፍ/ህ/ቁ/32(1) የተደነገገ ሲሆን ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው ደግሞ የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በቁጥር 36 ተመልክቷል፡፡

በመሰረቱ እያንዳንዱ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው፣እንዲሁም ለልጁ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም እንደሆነ በፍ.ሕ.ቁ.32(1) እና 36(1) ድንጋጌዎች ተመልክቶአል፡፡አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች በአባቱ ብቻ ሳይሆን በአሳዳጊው ስም ጭምር ሊጠራ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን እንዲህ ዓይነቱ ሰው ተገቢ ሆኖ ባገኘው ጊዜ በአሳዳጊው ስም ጭምር መጠራቱ ቀሪ ሆኖ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ  መሰረት በአባቱ ስም ብቻ እንዲጠራ የመወሰን መብት ያለው በመሆኑ ይህንኑ መብቱን በፍርድ ለማረጋገጥ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካች ክሱን ያቀረቡት ከሚጠሩበት ሁለት የግልና የቤተዘመድ ስሞች መካከል ባንዱ እንዲጠሩ ሲጠሩበት ከነበረው የቤተዘበመድ ስሞች መካከል ደግሞ አሁን ለመጠራት የፈለጉት ወላጅ አባቴ በሚሉት ሰው ስም ሳይሆን የአሳዳጊያቸው ስም በመምረጥ መሆኑን ከዳኝነት ጥያቄአቸው ይዘት ለመንገዘብ ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በአሳዳጊያቸው ስም እንዲጠሩ በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚያገኙበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ከግል ሰሞቻቸው መካከል ደግሞ ሃና ተብዬ ልጠራ፣ ፀሐይ መባሌ ይቅርልኝ ብለው በአማራጭ የጠየቁት የሰበር የዳኝነት ጥያቄ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወላጅ አባቴ ናቸው በማይሏቸው ሰው የቤተዘመድ ስም ልጠራ ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በሕጉ ስለስም ለውጥ ጥያቄ ማቅረብ ስለሚቻልባቸውና የዳኝነት አካሉም ለመቀበል መሟላት ከሚገባቸው ሕጋዊ መስፈርቶች ይዘትና ሕጋዊ ውጤት ጋር አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 87420 የተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የቤተዘመድ ስሙ አሳዳጊ በሆኑ ሰው ሲጠሩ የነበሩት አመልካች በትክክለኛ ስጋ ወላጆቻቸው ስም ለመጠራት ባቀረቡት ጥያቄ የተሰጠ ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 95995 የቀረበው ጉዳይም አመልካች ክሱን ያቀረቡት በሚጠሩበት የአሳዳጊያቸው ስም የተሰጡ ሰነዶችን ወደሚጠሩበት አባታቸው ስም በሕግ አግባብ ለማስቀየር እና እነዚሁ ሰነዶች በሚሰጡት መብት ለመገልገል ጭምር ስለመሆኑ ታይቶ ዳኝነት የተሰጠበት በመሆኑ ከአሁኑ ጉዳይ ጋር በመሰረታዊ የፍሬ ነገርና የሕግ ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይነተ የሌለው

www.abyssinialaw.com

በመሆኑ ይህ ችሎት በእነዚህ መዛግብት የተሠጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ክርክርና የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 117/08 በቀን 13/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/23938 በቀን 17/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የከተማው አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/24066 በቀን 6/12/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ወላጅ አባታቸው ባልሁኑት አቶ ታምራት አመዴ ስም እንዲጠሩ የጠየቁት የዳኝነት ጥያቄ ስለልጅነታቸው ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ሲያቀርቡ የሚታይ ነው ተብሎ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

**መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 103721

የካቲት 03 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሰሚራ ጀማል ከጠበቃ ሰለሞን ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1ኛ. አቶ ጀማል እንዲሪስ ከጠበቃ መሰረት ስዩም ጋር ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ሉላ አረፈ አልቀረቡም

3ኛ.አቶ ሀጎስ አብዱራህማን በመዝገብ ቤት በኩል እንዲሰሙ ተናግሯል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት ለየካቲት 01 ቀን 2008 ዓ/ም ቀጠሮ የያዘ ሲሆን በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን በአዳሪ በዚሁ እለት የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በአሁን አመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ መሰረት መፍረሱን ተከትሉ በአሁን አመልካች የጋራ ንብረት ድርሻ ጥያቄ መነሻ የስር ፍ/ቤቶች የጋብቻ ውጤት በሆነው የንብረት ክርክር ላይ የሰጡትን ዳኝነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ካስነሳው የውሳኔ ክፍል አንፃር ተመልክቶ የውሳኔውን አግባብነት ከግራ ቀኙና ክርክሩ የሚመለከተው ሆኖ የተገኘው 3ኛ ተጠሪም ካቀረቡት ክርክር ጋር በማገናዘብ አስፈላጊውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው በአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል ሚያዚያ 21 ቀን 1987 ዓ/ም ተደርጎ የነበረው ጋብቻ ግንቦት 24 ቀን 2003 ዓ/ም በፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተክትሎ የአሁን ተጠሪ ሀምሌ 27 ቀን 2003 ዓ/ም ተሻሽሎ ባቀረቡ ማመልከቻ የጋራ ንብረት ናቸው ያሏቸውን ናቸው የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቶች በመዘርዘር ድርሻቸው ተለይቶ ይወሰንላቸው ዘንድ ተገቢ የነበሩትን የአሁን 1ኛ ተጠሪን እና የ1ኛ ተጠሪ ሌላ ሚስት የሆነችን የአሁን 2ኛ ተጠሪን በተከሳሽነት ላይ ደመወዝ በዚሁ የጋብቻ ውጤት በሆነው የንብረት ድርሻ ጥያቄ ላይ፣ እንደዚህም 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረትን ሲያስተዳድር የደረሰው፣ ጉዳት ሲታወቅ በኃላ ተገቢውን የካሳ ለአመልካች እንዳይከፍል ይወሰንልኝ በማለት

www.abyssinialaw.com

ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ እንደክርክራቸው ያስረዳልናል ያሏቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃም አያይዘው አቀርበናል፡፡

የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የጋራ ንብረት ናቸው በሚል በአሁን አመልካች የክስ ማመልከቻ ላይ ከተዘረዘሩት ንብረቶች የጋራ ንብረት የሆኑትን በማመን፣ በጋራ ሀብትነት የማይታወቁትን፤ የሚያገኙትን ደግሞ በመካድ በአመልካች ክስ በተዘረዘረው የንብረት ዝርዝር አንፃር መልስ የሰጡ ሲሆን፤ በንብረት አስተዳደር ረገድ ያደረስኩት ጉዳት የሌላ በመሆኑ የሰጠው ጥያቄ አይመለከተኝም በማለት ክርክራቸውን አቅርቧዋል፡፡ ለክርክሩም ድጋፍ ያላቸውን ማስረጃዎች አያይዘው አቅርበዋል፡፡

የአሁን 3ኛ ተጠሪም የጋራ ንብረት ነው በሚል በአሁን አመልካች ከተጠቀሱት ንብረቶችና መካከል በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍል ከተማ ወረዳ 3 ክልል በቤት ቁጥር 2545 የሚታወቀውን ቤት በውል አዋዋዩ ክፍል ዘንድ ጂ. ኤስ. ኤ.ጄኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከተባለው ድርጅት የገዙት ስለሆነ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ይወሰንልኝ በማለት በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብተውም ተከራክረዋል፡፡ ለዚህም ክርክራቸው ለማስረጃነት ሰነዶችን እንዳቀረበም የመዝገቡ መልሰን ያስረዳል፡፡

እኚሁ ጣልቃ ገብ ያቀረቡትን ክርክር አስመልክቶ የአሁን አመልካች ጣልቃገብ ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ በሰጠበት ንብረት ላይ ግዥ የፈጸሙ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ከጅምሩ ፈራሽ ስለሆነ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይህንኑ በቁጥር 2545 ተመዝግቦ የሚታወቀውን ቤት አስመልክቶ ንብረቱ በማናቸውም ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ የጋራ ንብረት ባለመሆኑ እንጂ የጋራ ንብረት ተቆጥሮ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካች ባቀረቡት ክስ ቀጥተኛ መልስ የሰጡ ከመሆኑም በላይ በጣልቃ ገብ በኩል የቀረበው ክርክር አስመልክቶ ደግሞ ተቃውሞ የሌለባቸው መሆኑን ገልጸናል፡፡

ሁሉም ወገኖች ከላይ ባጭሩ ለይዞታ ደረጃ የተገለጸውን የጹሁፍ ክርክር ካደረጉ በኋላ ለጉዳዩም ላይ የቃል ክርክር እንዳደረጉ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

የስር ፍ/ቤትም ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በአከራካሪነታቸው በጭብጥነት ተይዘው ከማስረጃ አንፃር ለማየት ዳኝነት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በማለት ከሙግት ደረጃ ደርሶ ለማስረጃ ሰምቶ ዳኝነት ካሳረፈባቸው ንብረቶች መካከል በአከራካሪያቸው ከዚህ ሰበር ደረጃ ዘልቀው ከደረሱት መካከል አንዱ በቤት ቁጥር 2545 የተመዘገበውን ቤት አስመልክቶ

www.abyssinialaw.com

የአሁን አመልካች በጋብቻ ዘንድ የተፈራውን ይህንኑ ንብረት ከእኔ ለማሸሽ ሲል ያለ እኔ ፈቃድ ጂ. ኤስ.ኤ አጄኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ወደ ተባለው ድርጅት በመዋጨነት አስገምቶ አሸሽቶ የሰጠ በመሆኑ፤ እንዲሁም ይህን ንብረት የአሁን 3ኛ ተጠሪ ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ ከተሰጠበት በኋላ እንዲገዙት የተደረገ ስለሆነ ንብረቱ የጋራ ሀብት መሆኑ ታውቆ በድርሻዬ ልከፍል ይገባል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም በኢፌድሪ የፍትህ ሚንስተር የሰነዶች ማረጋገጫና ከዘገባ ጽ/ቤት በቀን 10/3/2002 ዓ/ም በተፈረመ የጂ ኤስ ኤ ጄነራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር የመመስረቻ ጽሁፍ ይዘው በቤት ቁጥር 2545 ተመዝግቦ የሚታወቀው በ1ኛ ተጠሪ አማካኝነት በመጭነት የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ሚያዚያ 16 ቀን 2002 ዓ/ም በተካሄደ የጂ ኤስ ኤ.ኤጄኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለሂሳብ 1ኛ ተጠሪ በማህበሩ የየራሳቸውን አክስዮን በብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ሽጠው የተሰራበት መሆኑ በኢፌደሪ የፍትህ ሚኒስቴር ማስረጃ ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት ማህተም በተረጋጠ ሰነድ ተረጋግጧል ጂ. ኤስ ጄኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/ የግል ማህበር ግንቦት 17 ቀን 2003 ዓ/ም በተፃፈና በሰነዶች ማረጋገጫና መዝገብ ጽ/ቤት በተመዘገበ የሽያጭ ውል ይህንኑ የቤት ቁጥር 2545 የሆነው በብር 240,000.00 /ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ለጣልቃ ገብ ለአሁን 3ኛ ተጠሪ አብዱራህማን አህመድ የተሸጠ ስለመሆኑም በጣልቃ ገብ አማካኝነት በቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧ በመሆኑም ይኸው ቤት ከ1ኛ ተጠሪ እጅ ሙሉ በሙሉ ወጥቶ በጂ ኤስ. ኤ.ተራ ደንብ ኃ/የተ/የግል ማህበር ተጠቃሎ ተላልፏል የተስፋፋውም የአመልካችና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ እንዳይፈርስ የፍቺ ጥያቄ ለመቅረቡ በፊት እና ለፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ በፊት ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

የጋራ የሆነውን ንብረት ያለ ሁለተኛው ተጋቢ ፈቃድ በአንደኛው ተጋቢ አማካኝነት ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 68/ሀ/ እና 69 እንደተደነገገው ፈቅደን ባልሰጠው ተጋቢ ጥያቄ መሰረት ንብረቱ የተላለፈበት ግዴታ እንዲፈርስ ካልተደረገ በቀር በተፈጸፀመው የንብረት ማስተላለፍ ስምምነት ውስጥ ተጋቢዎች እንደታሰበው ግምት እንደሚሰጡ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች በዚህ በመ/ቁ 2545 የተደረገውን የሽያጭ ስምምነት በመቃወም በፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው ያስወሰኑት የለም፡፡ ስለሆነም ንብረቱን ከእኔ ለማሸሽ ሲል ለኢኤስኤ ትሬድንግ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር በመውጫ ሰጥቷል የፍ/ቤቱን ዕግድ በመጣስ ሸጦታል በማለት ያቀረቡት ክርክር ራሱ ችሎ መቅረብ የነበረበት ክርክር እንጅ በዚህ አሁን በቀረበው ክርክር ሊታይ የማይችል ከመሆኑም በላይ ንብረቱ ወደ ማህበሩ የተዛወረው በአመልካች በኩል የፍቺ ጥያቄ ለመቅረብና የዕግድ ትዕዛዝ ከመተላለፉ በፊት ስለሆነ የመ/ቁጥር 2545 የሚታወቀው ቤት የአመልካችና የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ሳይሆን ጣልቃ ገብ በግዥ ያገኙት ንብረት ነው በማለት ወስኗል፡፡ እንዲሁም በዘምዘም ባንክ አ/ማህበር በተጠሪዎች ስም የአክሲዮን

www.abyssinialaw.com

ድርሻ የለም፣ በባንክ ስማችን የተቀመጠ ገንዘብ የለም በማለት ተጠሪዎች ቢከራከሩም ፍ/ቤቱ ስላቀረበው ማስረጃ ጭምር የተረጋገጠ ሆኖ ተገኝቷል በማለት ተረጋግጧል ባለው የገንዘብ መጠን መሰረት የአሁን አመልካች ድርሻ እንዳላቸው ገልፆ ዳኝነት ሰጥቶበታል በሌላ በኩል ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ወቅት ንብረት በማስተዳደር በኩል የፈፀሙት ጉድለት ያለመሆኑ ያለ መሆኑ ተጣርቶ ከተረጋገጠ በኋላ ለማ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል። ይሁን እንጅ ተጋቢዎች በጋብቻቸው ዘመን የጋራ ንብረታቸውን በጋራ እንዲያስተዳድሩ በሕጉ ግምት የሚወስድ ሲሆን ይህን ግምት ማፍረስ የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ የሌለውን መብት የሚጎዳ ተግባር ፈፅሞ ስለመገኘቱ የማረጋገጥ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ በሕጉ አንቀፅ 87 ተደንግጓል 1ኛ ተጠሪ ንብረት ሲያስተዳድሩ ፈፀሙ በሚል በማስረጃ የተረጋገጠና ተለይቶ የታወቀ ጉድለት ያልተገኘ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን አልተቀበለውም የሚለውን ውሳኔ ሰጥቶበታል።ፍ/ቤቱ ለሰጠው ዳኝነት በምክንያትነት ያሰፈረውን ሐተታ እና የሰጠውን የዳኝነት ዓይነት ከዚህ በላይ ባሰፈረው አኳኋን በሰጠው የፍርድ ክፍል ላይ ከገለፀው በኋላ በፍርድ መሰረት የተረጋገጠውንና ሊረጋገጥ ያልቻለውን ምስክር አስመልክቶ የፍርድ ተከታይ በሆነው የውሳኔ ክፍል ላይ

በቂርቆስ ክ/ከተማ በቀሌ 02/03 ክልል በቤት ቁጥር 297 ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ የሚገኘውን ቤት አመልካችና ተጠሪዎች በጋራ ያፈሩት ንብረቶች ስለሆነ የክፍፍሉንም መንገድና ስልት ከመጥቀስ ጋር ሶስቱም እኩል እንዲከፈሉ በን/ስ/ላፍ/ክፍለ ከተማ በመ/ቁጥር 2545 የግልግል ሀብት ነው፤

1ኛ ተጠሪ በቴክኖሎጅ ሲስተም ኃ/የተ/የግ/ማህበር ያላቸውን ሽር፣ በፒስ ደልለን ኃ/የተ/የማህበር ውስጥ ያለው ሽር 2ኛ ተጠሪ በዘምዘም ባንክ አ/ማህበር ያላቸው በሁለተኛ ተጠሪ ስም በዳሽን ባንክ ስለ አካባቢ ቅርንጫፍ በ1ኛ ተጠሪ ስም በወጋገን ባንክ ተ/ኃይማኖት ቅርንጫፍ በ1ኛ ተጠሪ ስም በዳሽን ባንክ ስለ አካባቢ ያስቀመጠውን ገንዘብ ከእነ መጠኑ በመግለፅ ሶስቱም እኩል እንዲካፈሉ በማለት በኮ/መ/ቁ 61875 በቀን 13/10/2004 ዓ.ም ወስኖ ግራ ቀኙን አሰናብቷል።

በዚህ ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 125893 ሁሉንም ወገኖች ከክርክር በኋላ

የቤት ቁጥር 2545 አስመልክቶ የቀረበውን ጉዳይ በሚመለከት በዚሁ ቤት ላይ የስር ፍ/ቤት የካቲት 16/2003 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ቤቱ በ1ኛ አማካኝነት በመውጫነት ወደ ጅ.ኤስ.ኤ ጀኔራል ትሬድግግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ገብቶ የነበረ እና 1ኛ ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ የነበራቸውን 4127/4/ለ/2002 በቀን 12/9/2002 መተላለፋን የሰነዶች ማረጋገጫ ፅ/ቤት ለስር ፍ/ቤት በቀን 20/4/2004 ዓ.ም ከላከው ማስረጃ አረጋግጧል። እንዲሁም የዚሁ ቤት ስመ-

www.abyssinialaw.com

ሀብትነት ወደ ጅኤስኤ ጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቀን 04/8/2002 በቁጥር ን/ስ/ቀ/05/83/3805/02 የተላለፈ ስለመሆኑ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት አስተዳደርና ግንባታ ፅ/ቤት የካቲት 14 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈና ለስር ፍ/ቤት ከላከው ሰነድ ተረጋግጧል፡፡

ቤቱ ወደ ሶስተኛ ወገን በተላለፈበት ጊዜ ግንቦት 1/2002 ዓ.ም ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ የነበሩ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው የፍቺ ውሳኔ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ይኸው ንብረት በጋብቻ ጊዜ ወደ ሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ መተላለፉን አላወቀም ነበር የሚሉ ሲሆን አሁን ለዚህ ችሎት ውሉ እንዲፈርስ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው እየተከራከሩ እንደሚገኙ በገለፁት መልኩ ይኸው ውል በማስፈረስ መብታቸውን ከሚያስከብሩ በቀር በጠየቁት ዳኝነት አኳኋን ሊስተናገድ የሚችል አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲያፀናው በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ ስም የሚገኘውን የሼር ሀብት መጠንን በሚመለከት ማህበሮቹ ለስራ ተሰማርተው ያገኙትን ትርፍ ሁሉ አጠቃሎ መወሰን ሲገባው ማህበሮች በተቋቋሙበት ጊዜ በተደረገው መነሻ ይካተታል መጠን ላይ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን እንዲሁም በልዩ ልዩ በባንኮች በእነዚሁ ተጠሪዎች ስም አንፃር ይገኛል የተባለውን ሀብት መጠን አስመልክቶ ፍ/ቤቱ ገንዘብ ስለመኖሩ በጠየቀበት ጊዜ በባንኮች ተቀምጦ ተገኝቷል የተባለውን የገንዘብ መጠን ሳይሆን በትዳር በነበሩበት ጊዜ አንደኛዉ ወገን ብቻ በማውጣት ለግል ጥቅም ተጠቅሞበታል ከሚያሰኝ በቀር ለጋራ ጥቅም እንደዋለ አያስቀጥርም በማለት መነሻ ሊሆን ከሚችለው ጊዜ ጋር በማስተያየት በባንኮች ካላቸው ሂሳብ እንቅስቃሴ በመነሳት መሠረት የሚገባዉ መሆኑን ጠቅሰን በዚሁ መሠረት እራሱ ይግባኝ በከካሽ ፍርድ ቤት ጉዳዮን ተመልክተ የገንዘቡን መጠን በፍርዱ የውሣኔ ክፍፍል በተገለፀው አኳኋን ከፍ አድርጎ በሚሻሻል መወሰን ፤

በሸር ድርሻ ላይ የተወሰነውን የድርሻ መጠንን ከላይ በተመለከተው መሠረት ከውሳነ በኃላ የክፍፍል ማስረጃን በሚመለከት 1ኛ መልስ ሰጭ በሀብቱም ማህበሮች የተወሰነላቸውን የአክስዮን ድርሻ ለተቻለ እና ተጠሪዎች የሚስማሙ ከሆነ በአባልነት እንዲቀጥሉ ይህ ካልተቻለ ተሸጦ የሽያጩን ድርሻ ይከፈላቸው የአከስዮኖች አሻሻጭም በንግድ ህግ አንቀጽ 523 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች እንደዚሁም የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.57288 በሰጠው የህግ ትርጉም መሠረት ሆኖ ድርሻቸው እንዲሰጣቸውና እንዲሁም በቤት ቁጥር 2545 ውስጥ/ የተሰጠውን ዕቃ በሚመለከት ቀርቧል በተባለው የወንጀል ክስ ምርመራ ውጠት መሠረት የአሁኑ አመልካች ጥያቄ የማቅርብ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን ከዚህ በላይ ከተገለፁት በቀር ሥማቸው በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን ለመግለፅ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የወሰነ መሆኑን ከፍርዱ ግልባጭ ተረድተናል ፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁን አመልካች በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረም ይገባል በማለት ለቅሬታቸው መሠረት ያደረጉት የቤት ቁጥር 2545 የሆነው ቤት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው ወይስ የአሁን 3ኛ ተጠሪ የሚለውን ለይቶ በመወሰን ረገድ፤እንዲሁም በሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የተረጋገጠባቸውን የአክስዮን ድርሻዎ የክፍፍሉን መንገድ በሚመለከት የአክስዮን ድርሻዎች በሚገኙበት ማህበር በአባልነት እንድቀጥል በማድረግ መወሰን ስገባው ማህበሩ ለተስማማ በሚል ተገልፆ የህግ መሠረት የለውም ለሚሉት መወሰኑ ነጥቦች ላይ ፡፡

ተጠሪዎችም በበኩላቸው ክርክር በሚመለከታቸው ክርክር አንፃር በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚሉበትን ምክንያት በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ የጉዳዮ አነሳስ፤የክርክሩ ይዘትና የሥር ፍ/ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ዳኝነት ፤የዚህን ዳኝነት አግባብነት በሚመለከት ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር በይዘት ደረጃ ከላይ ከፍ ሲል ባጭር ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን ፤እኛም ጉዳዮን እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡ ተመልክተናል ፡፡

ጉዳዮን እንደመረመርነውም በቤት ቁጥር 2545 የተመለከተውን ቤት አስመልክቶ የአሁን አመልካች ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት ንብረቱ በሽያጭ ወደ አሁን 3ኛ ተጠሪ የተላለፈው ፍ/ቤቱ በዚሁ ንብረት ላይ ዕግድ ከሰጡበት በኃላ የፍ/ቤቱ ዕግድ ተጥሶ ስለሆነ የሽያጭ ተግባሩ ዋጋ አልባ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል የሚለውን አንደኛው የክርክር ነጥብ ሲሆን የዚህኑ ክርክር አግባብነት ለዚሁ ጉዳዮ በሥር ፍ/ቤቶች በነበረው የክርክር ሂደት በማስረጃ ከተረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ በመነሳት ተመልክተናል ፡፡

የአሁን አመልካች ለዚህ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነውን ክስ ከቀረቡ በኃላ የክርክሩ ውጤት እስክታወቅ በሚል ይኸው ቤት በማናቸውም መንገድ ቢሆን ወደ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትእዛዝ የሰጡት የካቲት 16 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑና ይኸው ቤት በአሁን 1ኛ ተጠሪ አማካኝነት በዓይነት በመወጫነት ወደ ጂ.ኤስ.ኤ ጀኔራል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የገባውና ስመ ሀብትነቱም ወደ ዚሁ ማህበር ስም የተላለፈው ይኸው የወሰነበት የዕግድ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የአንድ ንብረት ባለሀብት ማን ነው የሚለው የሚወሰነው ደግሞ ንብረት ከአንዱ ወደ ሌላው ለማስተላለፍ የሚያስችለው እንደ ሽያጭ ስጦታ ወዘተ የመሳሰሉት ህጋዊ ተግባሮች በህግ ፊት በሚፀና አኳኋን ተፈፅመው እንደሆነ እና በዚሁ አኳኋን በተፈፀመው ህጋዊ ተግባር የተነሣ በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት ያገኘ ሰው ንብረቱን ካስተላለፈዉ ተፈጥሯዊም ሆነ የህግ ሰው ባሻገር ማናቸውንም 3ኛ ወገን ለመመለስ የሚያስችለውን የስመ ሀብት ዝውውር ሥርዓት ሁሉ ታከናውኖ እንደሆነ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር

www.abyssinialaw.com

1678 ፣1731፣1184፣1195 ተደንግጓል፡፡ አሁን የተያዘውን ጉዳይ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንፃር ስነየው ክርክር ያስነሰው ንብረት በ1ኛ ተጠሪ እና ጀ አስ ኤ ጀኔራል ትሬዲንግ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት ይኸው ንብረት በዓይነት በመወሰኑ ወደ ከማህበሩ ገብቶ፤ ማህበሩ በዚሁ ንብነት ላይ መብትና ግዴታ ያቋቋመ ሲሆን ከዚሁ ንብረት ወደ ማህበሩ መግበት የተነሰ ለአስተላለፈውም ግዴታ ፈጥሮለታል ይህ በህግ የተፈቀደ ንብረት ሊተላለፍ የሚችለበት አንዱ ህጋዊ ተግበር ሲሆን ማህበሩ በዚሁ ንብረት ላይ የእኔ በይ በመጣ ለመመለስ ዋስትና የሆነውን የስመ ሀብት ዝውውር ሥርዓት ሁሉ ፈፅሟ፡፡ በዚህም መሠረት የዚሁ ንብረት የበላቤትነት መብት ያለው ይኸው ማህበር እንጂ ሌላ ማናቸውም ወገን ሊሆን አይችልም ይህን በንብረት ላይ ያለን የበለሀብትነት መብት ማህበሩ ያቋቋመው ፍ/ቤቱ በንብረቱ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ነው ከዚህ በንብረቱ ላይ የበለቤትነት መብት ከቋቋመ በኃላ በዚህ በህግ ከቋቋመው ላይ የበለቤትናት መብቱ ተጠብቆም በንብረቱ ላይ የማዘዝ ወደ ሌላ 3ኛ ወገን የመስተልለፍ መብት ያለው ሲሆን ሌላ ማየናቸውም 3ኛ ወገን ይህንኑ ንብረት ለሚመለከት ከመህበሩ ጋር በሚያደረገው ህጋዊ ተግበር ወደ እራሱ ያዛወረው ከሆነ ንብረቱን ለማዘወር መብትና ስልጣን ከለው ወገን ያገኘ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመለየት ማህበር ንብረቱን በሸጠበት ጊዜ በንብረቱ ላይ የተመለከተውን ስመ ሀብትነት ምዝገባ የሚከተል እንጂ 3ኛ ወገን ከማህበሩ ጋር ግብይት የፈፀመበት ጊዜ ሊሆን አይችልም ከዚህ በላይ ንብረት ከንደኛው ወገን ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችልበትን መንገድ በሚመለከት በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተቀመጡት ሁለት ቋሚ መሚያዎች ማናቸውም በንብረት ላይ ሊኖር የሚችለው ግብዓት በህግ ዋስትና ተሰጥቶት በህ/ሰብ ደረጃ ያለስጋት የሠለጠ ኢኮኒሚያዊ ግንኙት ለመፍጠር እንዲያስችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአሁን አመልካች የፍ/ቤቱ የዕግድ ትዕዛዝ ከተለለፈ በኃላ 3ኛው ተጠሪ ከማህበሩ ጋር የሽያጭ ውል ያደረገበትን ጊዜ ተንተርሰው የሚያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

ከዚህም በቀር የማይንቀሳቀስ ንብረት በዓይነት ለመውጫ ወደ አክሲሆን ማህበር ወይም ወደ ኩባንያ ስለመዘወሩ በመመስረቻ ፅሑፍ ሰፍሮና በዚህ መስረጃ መዝገብ ጽ/ቤት ተመዝግቦ በማንቀሰቀስ ንብረት በመዝገብ ውስጥ መመዝገቡ ከተረጋገጠ የ3ኛ ወገኖችን ላይ ለመመለስ የሚያስችለው ሥርዓት መሟለቱን እንደሚያመለክት ይህ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀርቦ ተመሰሰይ በሆነው በሰበር መ/ቁ.. 27869 ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ በመሆኑም ጭምር ከዕግድ ትዕዛዝ ጋር በተያየዘ የአሁን አመልካች የሚያቀርብበት ክርክር በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረተዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን የሚያመለክት ህጋዊ መሰረት የለው ክርክር አይደለም ሌላውና ይህንኑ በቤት ቁጥር 2545 የተመለከተውን ቤት አስመልክቶ የአሁን አመልካች ያቀረቡት ክርክር በዋጅ ቁጥር 2/3/92 ስለጋራ የበልና ሚስት ሀብት አስተዳደርና ጥበቃ በህጉ የተቀመጠውን የተጋቢዎች የጋራ ስምምነትን አስፈላጊነት በመጥቀስ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የጋራ ሃብት የሆነን ንብረት አንደኛው ተጋቢ ያለ ሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ለሌላ ሶስተኛ ወገን በሽያጭ ማስተላለፍ እንደማይችል በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68 የተደነገገ ሲሆን፤ ይህ ድንጋጌ በይዘቱ የጋራ በሆነ ንብረት ላይ ተጋቢዎች እኩል መብት ያላቸው መሆኑን በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 34(1) የተመለከተውን ህገ-መግስታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የተደነገገ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአገር በማህበረሰብ ውስጥ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረገው ግብይት ያለማነቆ በሰለጠ አኳኋን እንዲፈጸም ካልተደረገ በአገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን እንቅፋት በማየት ይህ ከላይ የተመከተው የጋራ ስምምነት አስፈላጊነት በሁኔታ ላይ እንዲመረኮዝ በማስፈለጉ ተከታይ በሆነው አንቀጽ 69 እንደተመለከተው አንደኛው ተጋቢ ያለፈቃዱ ንብረቱ በአንደኛው ተጋቢ ብቻ መሸጡን በተረዳ ጊዜ ይህ የሽያጭ ተግባር በህጉ የተሰጠውን መብት የጣሰ መሆኑን መነሻ አድርጎ በክስ አማካኝነት ማስፈረስ እንደሚቻል፤ ይህንኑ የማስፈረስ ተግባሩን ካልተጠቀመ፤ ወይም በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የማስፈረስ ጥያቄው ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ካልቀረበ ግን አንደኛው ተጋቢ ብቻውን የፈጸመው ህጋዊ ተግባር እንደጸና እንደሚቀር እንጂ የጋራ ስምምነት ባለመኖሩ ምክንያት ብቻ ንብረቱ የተላለፈበትን ግብይት ወይም የሽያጭ ውል በዘፈቀደ በማናቸውም ጊዜ መቃወም እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ዳኝነት የህጉን ትክክለኛ አፈጻጸም የተከተለ እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመ አይደለም፡፡

የአሁን አመልካችም ይህንኑ ተገንዝበው ክርክራቸው በይግባኝ ደረጃ ለደረሰበት ጊዜ በዚሁ ስርዓት መሰረት በንብረት ላይ ያላቸውን መብታቸውን ለማስከበር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ክስ አቅርበው በክርክር ላይ የሚገኙ መሆኑን የገለጹ በመሆኑና ይህ ችሎም ለትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይህንኑ የተባለውን በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበውን የኮ/መ/ቁ. 194776 የሆነውን መዝገብም አስቀርበን እንደተመከትነው ጥያቄውን በዚያው አግባብ ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ ይኸው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ለጊዜው የዘጋው የፌዴራል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 125895 የቀረበለትን የይግባኝ ጉዳይ መርምሮ የመጨረሻ ዳኝነት እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ በማገዱ ምክንያት በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዳኝነት የሰጠበት ጉዳይ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች በፍርዳቸው ላይ እንደገለጹት መብታቸውን ከሚያስከብሩ በቀር በዚህ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጦ የጋራ ሃብትን ለማከፋፈል እንዲቻል በቀረበው መዝገብ ላይ ወደ ሶስተኛ ወገን በሽያጭ አማካኝነት ተላልፎ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት መሆኑ ያልተረጋገጠውን የቤት ቁጥር 2545 እንደጋራ ሃብት ሊቆጠር ይገባል በማለት የሚያቀ ርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለውም አይደለም፡፡

ሌላውና ለዚህ የሰበር ጉዳይ የክርክር ምክንያት የሆነው ለአሁን አመልካች ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛው ፍ/ቤት አሻሽሎ በወሰነላቸው የአክሲዮን ሼር ድርሻ ላይ ያላቸውን ሀብት

www.abyssinialaw.com

የሚያገኙበትን ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚስማማ ከሆነ በአባልነት እንዲቀጥሉ ይህ ካልሆነም ተሽጦ የሽያጭ ድርሻ እንዲያገኙ በማለት በንግድ ህግ ቁጥር 523 እና ተከታዮቹ የተመለከተውን መሠረት በማድረግና በሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ.57288 የተሰጠውን ትዕዛዝ በመከተል የሰጠውን ዳኝነት አግባብነቱን አስመልክቶ ግራ ቀኙ ክርክር ያደረጉበት ጉዳይ ነው፡፡

ይህንንም ጉዳይ እንደተመለከትነው በማናቸውም ምክንያት በፍ/ቤት በሚሰጥ ፍርድ የሚረጋገጠው መብት ከተብ ወይም ከውል የመነጨውን መብት መኖርና አለመኖር አስመልክቶ እንዲህጉ አነጋገር ለማስረዳት የቀረበውን ክርክርና ክርክሩን አነጋገር ለማስረዳት የቀረበውን ክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበውን መብት ወደ ተግባር ይህንኑ ከህግ እንዲያስችል ለመብት ምንጭ የሆነውን ህግ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ከዚህም አንፃር ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

አግባብነት ካላቸው ህጎች አንዱ ይኸው የአክቢዮን ድርሻ ግራ ቀኙ በጋብቻ ዘን በነበሩበት ጊዜ የተፈራ የጋራ ሀብት እንደመሆኑ መጠን በሀብቱ የባለእኩልነት ድርሻቸውን የሚቃረጋግጠው አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 62 አንዱ ሲሆን እንዲሁም ከዚሁ የጋራ ሀብት ነው፡፡ ከተባለው የሀብት ዓይነት አንፃር ሲታይ ደግሞ የዚህ የጋራ ሀብት የክፍፍል ሁኔታ የሀብቱን ጉዳይ ምክንያት በማድረግ በሚደነግገው በንግድ ህጉ አንቀጽ 523 የተመለከተው ድንጋጌ ደግሞ ሌላው ነው፡፡ ስለሆነም የዚህኑ ክፍፍል ሥርዓት የሚደረግበትን መንገድ በሚመለከት የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በንግድ ህጉ አንቀጽ 523 ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት ማድረግ የሚያነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህንኑ ድንጋጌ እንደሙሉ ይዘቱ አይነት ተፈፃሚ በማድረግ ስለሆነም የአሁኑ አመልካች በፍርድ በተረጋገጠላቸው የአክሲዮን ድርሻ ባት መብት ላይ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 523 አንፃር አየቶ መብቱን ለማረጋገጥ መነሻ ለሆኑ ከሚገባቸው የህጉ ክልሎች መካከል በንግድ ህጉ አንቀጽ 523/2/ እንደተመለከተው የአክሲዮን ማህበር መመሥረቻ ፅሑፍ የይዙቱ የአሁን አመልካች በማህበሩ አባልነት ተካተው በአባልነት ይህንኑ ለፍርድ በተረጋገጡባቸው የአክሲዮን ድርሻ ሀብት መገልገል የሚቻሉ መሆኑንና አለመሆኑን አስመልክቶ ምን እንደሚል ከመመስረቻ ፅሑፍ ጋር አገናዝቦ ከታየ በኋላ ሊታይ የሚገባው እንጂ ሆና እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ዳኝነት በዚህ ረገድ የተባለ ሆኖ አላገኘነውም ስለሆነም በዚሁ የነግድ ህግ ቁጥር 523/2/ ድንጋጌ ተትክከለኛ አፈፃፀሙን ተከትሎ ፍርድ በመስጠት ረገድ የታየው ጉድለት ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡

www.abyssinialaw.com

# ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.61875በቀን 13/10/2004 ዓ5ም የሰጠውን ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ12559 ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 325/1/ መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
2. በን/ስ/ላ/ከተማ ወረዳ 03 ክልል ውስጥ በመ/ቁጥር 2545 ተመዝገቦ የሚታወቀው ቤት ላይ የባለቤትነት መብት ያለው የአሁን 3ኛ ተጠሪ አቶ ሐገስ አብዱራህማን ናቸው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለአሁን አመልካች በፍርድ በተረጋገጡላቸው የአክሲዮን ድርሻና መጠን ላይ ባላቸው የሀብት መብት ላይ መገልገል የሚቻልበት ማበህበሩ አባልነት ተካተው በአባልነት ነው ወይስ በአባልነት መገልገሉ የሚቻሉበት ህጋዊ ምክንያት ታይቶ በሐራጁ ተሽጦ ይህንኑ ሀብት እንደያገኙት ነው?የሚባለው ጭብጥ ከማህበሩ መመስረቻ ፅሑፍ ይዘት እና ከንግድ ህጉ አንቀጽ 523/2/ አንፃር ታይቶ ይወሰልን ዘንድ ብቻ መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.343/1/ መሠረት ወደ ሥር ፈ/ቤት መልሰናል፡፡
4. የዚህ ክርክር ውጤት እሰኪታወቅ ድረስ በሚል በዚህ የስር መዝገብ ቁጥር 103721 ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
5. የዚህ የሰበር ክርክር ጉዳይ ስላስከተው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

# ውርስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መቁ.103151

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

**አመልካች፡-** አቶ ግርማ ብሩ አየለ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ መርዕድ ብስራት - ጠበቃ አበበ ማስረሻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የሥር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የወላጅ አባቴ እና የ2ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት የሆነውን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር አዲስ ካረታ ቁ.3329 የሆነውን ቤት 2ኛ ተከሳሽ ከሞግዚትነት ስልጣን ተቃራኒ ሚያዝያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ ሽያጭ ውል ለ1ኛ ተከሳሽ በብር 350,000 የሸጠች ስለሆነ 1ኛ ተከሳሽም /የአሁኑ አመልካች/ የከሳሽና የሌሎች ሰዎች የጋራ ንብረት መሆኑን እያወቀ ለቅን ልቡና ተቃራኒ በሆነ መንገድ ስለገዛ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስልኝ፣ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን እንዲያስረክበኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ ተከሳሾች መልስ እንዲሰጡበት የታዘዘ ሲሆን የሥር 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/መጥሪያ ደርሶት የጽሑፍ መልስ ስላልሰጠ ታልፏል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ በሰጠችው መልስ ባለቤቴ ከሞተ በኂላ ልጆች ለማሳደግ የተቸገርኩ በመሆኑ የቤት ሽያጭ ውል ፈጽሜአለሁ፡፡ 1ኛ ተከሳሽም የቤቱን ሽያጭ ገንዘብ እንደውሉ አልከፈለኝም፤ እኔ ቤቱን የሸጥኩኝ ለከሳሽና ለሁለት ወንድሞቹ ጥቅም እንጂ ለግሌ ጥቅም አይደለም፤ ፍ/ቤቱ የመሰለውን ውሳኔ ቢሰጥ አልቃወምም በማለት ተከራክራለች፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ክርክር በሚሰማበት ቀን ቀርቦ ሲከራከር

www.abyssinialaw.com

ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ ትችላለች፣ እኔ በቤቱ ላይ ሰፊ ለውጥ ያደረኩ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የከሳሽን የሰው ምስክር በመስማት በሰጠው ውሳኔ በተከሳሾች መካከል ሚያዝያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የልጆችን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ስለተፈጸመ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ይመለሱ፣ 2ኛ ተከሳሽ ብር 60,000 ለ1ኛ ተከሳሽ ትመልስ፣ 1ኛ ተከሳሽ በገዙት ይዞታ ሲገለገሉበት በነበረው ቤት ላይ ያወጡት ወጪ ካለ ክስ አቅርቦ መጠየቅ ይችላል በማለት ወስኗል። የሥር 1ኛ ተከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ማመልከቻውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ፣ የቤቱ ሽያጭ ዋጋ በአብዛኛው ስላልተከፈለ 2ኛ ተከሳሽ ለግል ጥቅም አውላለች፣ የልጆች ቅጥም ላይ ጉዳት ድርሷል የሚያስብል ስላልሆነ፣የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ በቂና አሳማኝ ምክንያት ስለሌለ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሥር ውሳኔ በመሻር ወስኗል። የሥር ከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ማመልከቻውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ፣ የቤት ሽያጭ ውሉ የከሳሽን ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ የቀረበ ነው።

የአሁን አመልካች ሐምሌ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የተጠሪ ሞግዚትና አስተዳዳሪ የነበሩት ወ/ሮ ክብካብ አስፋው የቤት ሽያጭ ውሉን ያደረጉት ለተጠሪ እና ለሌሎች ሁለት ወንድሞቻቸው መልካም አስተዳደር ስለሆነ ውሉን የተደረገው ለልጆቹ ቅጥም መዋሉ በተጠሪም ሞግዚት በጽሑፍ እና በምስክሮች በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ውሉ ሊፈረስ ይገባል በማለት የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው። የተጠሪ ሞግዚት ከተቀበለችው የቤት ሽያጭ ውሉ ገንዘብ የተጠሪ ድርሻ ብር 10,000 ብቻ ስለሆነ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም። አመልካች ቤቱን ከገዛሁ በኋላ ሌላ አዲስ ሰርቪስ ቤት ክፍሎች ብር 450,000 በላይ ወጪ በማድረግ በቤቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የይዘት ለውጥ አድረጎበታል። ስለዚህ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሉ ፈርሶ ወደ ነበራችሁበት ተመለሱ በማለት የወሰኑት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎትም መዝገቡን በመመርመር "በአመልካች እና በተጠሪ ሞግዚት መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስ ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከመዝገብ ቁ.46490 አንጻር ለመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ

www.abyssinialaw.com

በታዘዘው መሰረት መስከረም 7 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘትም፡- የተጠሪ ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ አትችልም፡፡ እኔ ከቤቱ ድርሻ እያለኝ ያለ እኔ ፈቃድ ሸጣለች፡፡ የተጠሪ መብት መጣስ እና መጎዳት የሚጀምረው ከዚህ መሰረታዊ ከሆነው የባለቤትነት መብቶች አኳያ ስንነሳ ነው፡፡ እኔ በቤቱ ሽያጭ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰብኝ አስረድቼአለሁ፣ አመልካች ግን ከሽያጩ ጥቅም ያገኘሁት መሆኑን አላስረዳም፡፡ አመልካች ከቤቱ ሽያጭ ገንዘብ የከፈለው ብር 60,000 ብቻ ሲሆን ቤቱን ተረክቦ እያኖረበት ነው፣ ከጉዳት በቀር ጥቅም ሊኖር አይችልም፡፡ ተጠሪው በሽያጩ ጉዳት እንጂ ያገኘሁት ጥቅም ስለሌለ ለሰበር መዝገብ ቁ.46490 ከሰጠው ውሳኔ ጋር የማይቃረን ስለሆነ ውሳኔው እንዲፀናልኝ፣ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልኝ፡፡ አመልካች ከቤቱ ድርሻ የተጠሪ ድርሻ 10,000 ብር ብቻ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር የባለቤትነት መብትን የጣሰ እና ሕጉ ተቃራኒ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካቹ በቤቱ ላይ ግንባታ ስለመካሄዱ ያቀረበው ማስረጃም የለም፣ በቤቱም ላይ የይዘትም ሆነ የቅርጽ ለውጥ አላደረገም፣ የተጠሪ ሞግዚት የቤት ሽያጩን ገንዘብ ማባከናቸውን እንጂ ለልጆች ጥቅም ያወሉት መሆኑን ያረጋገጠ ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀናልኝ፣ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥቅምት 04 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተ ሲሆን፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ባቀረበው ክስ የሽያጭ ውል የተፈጸመበት ቤት ላይ ድረሻ እያለኝ የእኔን ጥቅም በሚጎዳ መልክ ሞግዚት የሆነችው ወ/ሮ ክብካብ ሣህሉ ወልደማርያም በሽጨጭ ውል ለአመልካች የሸጠች ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስልኝ በማለት አልክቷል፡፡ የተጠሪ ሞግዚት /የሥር 2ኛ ተከሳሽ/ በጽሑፍ ባቀረበችው መልስ ቤቱን የሸጥኩት ለተጠሪ እና ለሌሎች ወንድሞቹ ቅጥም ነው በማለት የተከራከረች ቢሆንም እንደምስክር ሆነ በሰጠችው ቃል ደግሞ ከቤቱ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ ብር 60,000 ብቻ የተቀበለች እንደሆነና ለራሷ ትምህርት ክፍያ እንደከፈለችና ቀሪውን ለወንድሟ እንዳበደረች ገልጻለች፡፡ አመልካች በበኩሉ መጥሪያ ደርሶት የፍሑፍ መልስ ባለመስጠቱ የታለፈ ስለሆነ የጽሑፍ መልስ እና ማስረጃ በማቅረብ በማስረዳት መከራከር የነበረበትን ክርክር በተመለከተ መብት አጥቷል፡፡ ስለዚህ አልካች በጽሑፍ መከራከር የነበረበትና ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት የነበረበትን ፍሬ ነገር በተመለከተ አሁን ለማንሳት የሚችልበት የሕግ መሰረት የለውም፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክርክር አመልካች ከተጠሪ ሞግዚት ጋር

የቤት ሽያጭ ውሉን ሲፈጽም በቤቱ ላይ ልጆች ድርሻ ያላቸው መሆኑን ውሉ እያመለከተ ነው ቤቱን የገዛው የሚለውን፣ አመልካች ይህን ፍሬ ነገር ክዶ እየተከራከረ አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው በሞግዚቱ በኩል የተደረገው የቤቱ ሽያጭ ለልጆች ጥቅም ነው እንጂ ጥቅማቸውን የሚጎዳ አይደለም የሚል ነው፡፡ የተጠሪ እናት የሆነችው የሥር 2ኛ ተከሳሽ የተሻሻለው የቤተሰብበ ሕግ አዋጅ ቁ.213/1992 አንቀጽ 220/1/ መሰረት ሕጋዊ የሞግዚትነት ስልጣን እንደተሰጣቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት የሥር 2ኛ ተከሳሽ ተጠሪን በመወከል ሕጋዊ ተግባሮችን ለተጠሪ ጥቅም ለመፈጸም ስልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚሁ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 277 የሞግዚት ስልጣን በተመለከተ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሸጥ ጋር ተያይዞ የሚለው ነገር የለውም፡፡ ነገር ግን ሕጉ ሞግዚት መሸጥ የሚችላቸውን የንብረት ዓይነቶች በመዘርዘር በማስቀመጡ፣ ከዚህ ዝርዝር ወጭ ያሉትን ንብርቶች በተመለከተ ሞግዚት መሸጥ አይችልም ቢባል እንኳን ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ፈጽሞ ከተገኘ ግን ምላሽ ለማግኘት ሌላ ሕግ መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ አንጻር የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.213/1992 አንቀጽ 306 እንደሚደነግገው "የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች፤ ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ" የሚል ነው ፡፡ በዚህ መሰረት ተወካዩ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በመውጣት የሰራውን ስራ በተመለከተ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2207/1/ እንደሚያመለክተው "ተወካዩ ከስልጣኑ ውጭ የሠራው ስራ በቅን ልቡና ሆኖ ሲገኝ ሥራውን ወካዩ እንዲያጸድቅለት ይገደዳል" የሚል ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሞግዚቱ "ቅን ልቡና" መታየት ያለበት የተሰራ ስራ የልጁን ጥቅም የሚጎዳ ነው ወይስ አይደለም? ከሚል አንጻር መሆን እንዳለበት ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁ.46490 መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለልጆች መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሸጠ መሆኑ ከተረጋገጠ የሽያጭ ውል ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ማለት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን በተመለከተ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ጭብጥ መታየት ያለበት ለልጆች ቅጥም መሆን አለመሆኑን በማጣራት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተጠሪ ሞግዚት እና በአልመካች መካከል የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል ለተጠሪ እና ለሌሎች ወንድሞቹ ጥቅም የዋለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ሲታይ ለተጠሪ ጥቅም መዋሉን የሚያመለክት ምንም ነገር የለም፡፡ የተጠሪ ሞግዚት ከቤቱ ሽያጭ አመልካች የከፈላት ገንዘብ ብር 60,000 እንደሆነ ከዚህ ውስጥ ብር 10,000 ለትምህርት እንደከፈለች፣ ቀሪውን ለወንድሟ እንዳበደረች አረጋግጣለች፡፡ ይህ ማለት ከቤት ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ለተጠሪም ሆነ ለሌሎች ልጆች አለመዋሉን ያመለክታል፡፡

www.abyssinialaw.com

እንዲሁም ከቤቱ ሽያጭ የተገኘ ገንዘብ ለልጆቹ ጥቅም መዋሉን የሚያመለክት ማስረጃ መቅረቡን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ አመልካች ራሱ ከቤቱ ሽያጭ ብር 350,000 ውስጥ እስካሁን የከፈለው ብር 60,000 ብቻ ሲሆን ቀሪውን ገንዘብ ያለመክፈሉ ግራ ቀኙ የሚካከዱት ጉዳይ ስላልሆነ፣ የቤቱ ሽያጭ ውል ለተጠሪ እና ለሌሎች ልጆች ጥቅም የዋለ ነው ለማለት የሚያችል አንድም ነገር የለም፡፡ አመልካች ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ አብዛኛውን ሳይከፍል እንዲያውም አነስተኛ ገንዘብ ብቻ ከፍሎ በዚህ ሽያጭ የልጆቹ ጥቅም ተጠብቆላቸዋል፣ የሽያጭ ውሉም ለልጆች ጥቅም  የተደረገ ነው፤ ለተጠሪና ለሌሎች ወንድሞቹ መልካም አስተዳደግ ውሏል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አይታይም፡፡ ስለዚህ የሚያዝያ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተጠሪ ሞግዚትና በመአልካች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ለተጠሪና ለሌሎች ወንድሞቹ ማለትም ለልጆች ጥቅም እና መልካም አስተዳደግ ያልዋለ መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር በየትኛውም የሕግ መመዘኛ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ ከቤቱ ያለው ድርሻ አነስተኛ መሆኑን በመግለጽ ለውሉ መፍረስ መክንያት ሊሆን አይችልም የሚለው ሲታይ ተጠሪ ከቤቱ ድርሻ እስካለው ድረስ የጋራ ንብረቱ ከሱ ፈቃድ ውጭ መሸጥ የሌለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከልጆች መብት አንጻር የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡  በሌላ በኩል አመልካች ቤቱን ከገዘሁ በኋላ በቤቱ ላይ ግንባታ አካሄጃለሁ ያለውን በተመለከተ ተጠሪ ምንም ዓይነት ግንባታ አልተደረገም በማለት ክዶ የተከራከረ ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ የጽሑፍ ክርክር በማቅረብ በማስረጃ ስላላስረዳ፣ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ያላስረዳውን ክርክር ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅሬታ ነጥብ ማቅረቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329/1/ መሰረት ተቀባይነት የለውም፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤቶች የሽያጭ ውሉ የልጆችን ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል፣ አመልካች በቤቱ ላይ ያወጣ ወጪ ካለ ከሶ መጠየቅ ይችላል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተተ የሌለው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.201566 በ07/08/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.137501  ታህሳስ 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለው በመሆኑ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.98101 በ22/09/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ በውሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 103049

ቀን 28/01/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

. ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሊዕማ ሓዲሽ

ተጠሪ፡- አቶ አንዋር ሓዲሽ

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳዩ የውርስ ንብረትን በተመለከተ የተሰጠን ውሳኔ አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ የአፈጻጸም ከሳሽ የተባሉት የአሁን አመልካች በአፈ/ ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ላይ በወረዳው ፍ/ቤት ንብረቱን ለመከፋፈል የአፈጻጸም ክስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመቐለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት አስቀድሞ ሌላ የአፈጻጸም ክስ ተከፍቶ እንደነበር ፤ በቀደመው መዝገብ ንብረቱ በባለሙያ እንዲገመት ተደርጎ ብር 163,349.50 መገመቱን ፤ በዚህ ላይ ከግራ ቀኙ ወገኖች የቀረበ ተቃወሞ አለመኖሩን ፤ ነገር ግን ከወራሾች መካከል አካለ መጠን ያላደረሱ በመኖራቸው እድሜያቸው ደርሶ ቤቱን በጋራ ተስማምተን እንሸጠው መዝገቡ ተዘግቶ ይቆይ የሚል ሃሳብ በማቅረባቸው መዝገቡ ተዘግቶ እንደነበር ፤ ለአፈጻጸሙ ምክንያት የሆነው በፍ/መ/ቁ.03151 ታህሳስ 22/2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ለአፈ/ከሳሽዋ "በድርሻዋ ይሰጣት" የሚል በመሆኑና ከውሳኔው ውጭ ወደ ሽያጭ የሚኬድበት ህጋዊ አግባብ ባለመኖሩ እና ለአንድ ልጅ ሲባል በቤቱ የሚኖሩ አራት ልጆችን በማስወጣት ቤቱ ይሸጥ ማለት ፍትሃዊነት የለውም በማለት የባለሙያው ግምት ለአምስቱ ወራሾች ተካፍሎ የከሳሽ ድርሻ የሆነው ብር 32,669.09 እንዲከፈላቸው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ "አመልካች ያላቸውን ድርሻ በገበያ ዋጋ ሊያገኙ ይገባል ወይስ ባለሙያ በገመተው" በሚለው ነጥብ ላይ

www.abyssinialaw.com

አከራክሮ በመጨረሻ ባሳለፈው ውሳኔ አመልካች ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ወራሾች እንዲከፋፈሉ የሚያቀርቡትን ክርክር በተመለከተ እንዲፈጸም በቀረበው ውሳኔ አመልካች ድርሻቸውን እንዲያገኙ እንጅ ንብረቱ በሃረጅ እንዲሸጥ ስላልተወሰነ ተቀባይነት የለውም ፤ በሰበር ለማጣራት የተያዘውን ጭብጥ በተመለከተም ንብረቱ እንዲሸጥ እስካልታዘዘ ድረስ የገበያ ግምቱ ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ መገመት የሚቻል ባለመሆኑ ባለሙያ ከገመተው ውጭ የገበያ ዋጋው የሚረጋገጥበት ዘዴ የለም በማለት የስር ፍ/ቤቶች ያሳለፉትን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበ ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች በውርስ የጋራ የሆነው ቤትና ቦታ በአይነት መካፈል እስካልተቻለ ድረስ በሓራጅ ተሸጦ እንጅ በመሃንዲስ መነሻ ግምት ብቻ ድርሻ ይሰጥሽ በሚል የተላለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡

አቤቱታቸው ተመርምሮ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ህጉ የውርስ ሃብት የመከፋፈለን አሰራር በተመለከተ ከተደነገገው አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በሰጡት መልስ የአሁን አመልካች ከስር ክሳቸው ጀምሮ ጥያቄያቸው የወላጆች ድርሻ ይሰጠኝ የሚል እንጅ ቤቱ በሃራጀ ተሸጦ ድርሻዬ ይሰጠኝ የሚል ክስ ስላልነበር ፍ/ቤቱ ይህን ታሳቢ በማድረግ ድርሻዋ እንዲሰጣት የወሰነ በመሆኑ ፤ ጉዳዩ በአፈጻጸም ደረጃ ከደረስ በኃላ በሃራጅ ተሸጦ ሊከፈለኝ ይገባል የሚሉት ክርክርም ከውሳኔው ውጭ የቀረበ በመሆኑና የህግ መሰረት ስለሌለው አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎ በቀረበው ግምት መሰረት ሊወስዱ ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቹም ክርክራቸውን በማጠናከር የመ/መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለመግለጽ የሞከረነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ፍርዱን ለማስፈጸም በተሰጠው ትዕዛዝ እና ውሳኔ የተፈጸመ የህግ ስህተት ቢኖር መርምረናል፡፡

ከላይ ለመግልጽ እንደተሞከረው አከራካሪው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የተመለከተ ቢሆንም የተመራው በፍርድ አፈጻጸም ስርዓት ነው፡፡ የፍርድ አፈጻጸም በፍርድ የተገኘ መብት ውጤት እንዲሰጥ እና በፍርድ ባለመብት የተባለው ወገን ፍርዱን እንዲያጣጥም የሚደረግብት ስርዓት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በፍርድ አስፈጻሚው ፍ/ቤት የሚፈጸመው እንደ ፍርዱ ነው፡፡ ነገር ግን ፍርድ አስፈጻሚው ፍ/ቤት በሚያስፈጽምበት ጊዜ ፍርዱ ውጤት እንዲያገኝ አመች የሚሆነውን በህጉ የተፈቀደ ስርዓት ሊከተል ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በአፈጻጸም ወቅት ከፍርዱ ውጭ እንዲየስፈጽም የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ ከፍርዱ ውጭ እንዲፈጸም የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ንብረቱ እንዲሸጥ እስካልታዘዘ ድረስ የገበያ ግምቱ

www.abyssinialaw.com

ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ መገመት የሚቻልበት ስርዓት የለም በመሆኑም ባለሙያ ለገመተው ዋጋ አመልካች የድርሻቸውን እንዲወስዱ የደረስበት መደምደሚያ በህጉ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1083 በግልጽ እንደተደነገገው የወራሾች ድርሻ በክፍያ ጊዜ እንደሚገመት ፤ የንብረቱን ግምት የሚያደርጉት ራሳቸው ወራሾች መሆናቸው ፤ እንዲሁም ወራሾቹ በግምቱ የማይስማሙ ከሆነ ግምቱ እነሱ በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች ፣ በመምረጥ ባይሰማሙ ዳኞች በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች ግምቱ እንዲሚደረግ ተመልክቷል፡፡ አመልካች “የድርሻቸው እንዲሰጣቸው” የተላለፈው የስር ፍርድ በዚህ የህግ ስርዓት መሰረት መፈጸሙ ህጉን መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ ፍርዱ ውጤት እንዲያገኝ የሚያደርግ ነው፡፡

ስለሆነም ይህን የህግ ስርዓት መከተል ሲቻል ንብረቱን እንዲሸጥ እስካልታዘዘ ድረስ የገበያ ግምቱን ማወቅ አይቻልም ባለሙያ ከገመተው ውጭ ዋጋው የሚረጋገጥበት ዘዴ የለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ህጉን መሰረት ያላደረገ እና ፍርዱ በህጉ አግባብ ውጤት እንዲያገኝ የሚያደርግ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩም ተወስኗል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ. የመቐለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የዓደር ምድብ ችሎት በመ/ቁ.04388 ግንቦት 6/2006 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ ፤ የመቐለ ከተማ ማእከላይ (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በመ/ቁ.15262 ግንቦት 18/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 66999 ሰኔ 20/2006 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የወረዳው ፍ/ቤት የአፈጻጸም መዝገቡን በማንቀሳቀስ ንብረቱን ራሳቸው ወራሾች እንዲገምቱ በማድረግ ፣ ወራሾቹ በግምቱ የማይስማሙ ከሆነ ግምቱ እነሱ በመረጧቸው የሽምግልና ዳኞች ፣ በመምረጥ ካልተስማሙ ፍ/ቤቱ በሚመረጣቸው የሽምግልና ዳኞች እንዲገመት በማድረግ ተገቢውን እንዲወሰን ብለናል፡፡

3ኛ. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

4ኛ. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ በየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ.ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 100931

ታህሳስ 18 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ጥላሁን ዓለሙ ጠበቃ አቶ ተስፋሁን ጸጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ደረጀ ማሞ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ወላጅ እናቴ ሚች ወ/ሮ ዘውዱ በየነ የአእምሮ በሽተኛ በነበሩበት ጊዜ የፈጸሙት የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ይደረግልኝ በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የበታች ፍ/ቤቶች ውድቅ ያደረጉት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች በከሳሽነት ቀርቦ ሚች እናቴ ወ/ሮ ዘውዱ በየነ በአእምሮ ህመም ምክንያት በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሲታከሙ ቆይተው፣ ጤናማ አእምሮ ሙሉ ፈቃዳቸውን ለመስጠት በማይችሉበት ሁኔታ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ቁጥሩ 1020 የሆነውንና በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺ ብር/ ለተከሳሽ ሸጠውላቸዋል፡፡ ሚች እናቴ በአእምሮ ህመም ሲሰቃዩ ቆይተው ከዚህ ዓለም በ2003 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፡፡ ስለዚህ እናቴ የአእምሮ ህመምተኛ በሆኑበትና ፈቃዳቸውን ለመስጠት በማይችሉበት ሁኔታ በእርካሽ ዋጋ ቤታቸውን ለተከሳሽ (ተጠሪ) ለመሸጥ የተዋዋሉት ውል እንዲፈርስ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሽ የከሳሽ እናት የአእምሮ ህመም በግልጽ የታወቀ የአእምሮ ህመም አይደለም፡፡ ተከሳሽ ቤቱን ከከሳሽ እናት የገዛሁት እናቱ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ጤናማ አእምሮ እንዳላቸውና ቤታቸውን ለመሸጥ ፈቃደኛ መሆናቸው ተረጋግጦ ነው፡፡ የከሳሽ እናት የሽያጭ ውሉን ከተከሳሽ ጋር በተዋዋሉበት ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም ድብርት ውስጥ አልነበሩም፡፡ ተከሳሽ ቤቱን የገዛሁበት ትክክለኛ ዋጋ ብር 1,350,000 /አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ ብር/ ሲሆን የከሳሽ እናት ይህንን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ተቀብለዋል፡፡ ተከሳሽ ቤቱን ከገዛሁ በኋላ ከፍተኛ ወጭ በማውጣት የተለያዩ የእድሳት ስራዎችን የሰራሁ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮች ወደ ነበርንበት ለመመለስ የማይቻል በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡
3. የስር ፍ/ቤት የከሳሽ /የአመልካች/ እናት ወ/ሮ ዘውዱ በየነ የቤት ሽያጭ ውል ከተጠሪ /ከተከሳሽ/ ጋር ሲዋዋሉ የታወቁ የአእምሮ ህመምተኛ ነበሩ? ወይስ አልነበሩም? የቤት ሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ውሉ ሊፈርስ ይገባል ከተባለ ተዋዋዮች ወደነበሩበት መመለስ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚሉትን ጭብጦች መስርቶ፣ የከሳሽ እናት በድብርት ምክንያት በአማኑኤል ሆስፒታል በየቀጠሮ እየተመላለሱ የህክምና አገልግሎት ሲያገኙ የነበሩ መሆናቸው የህክምና ማስረጃው ያሳያል፡፡ የከሳሽ እናት ተመላላሽ ታካሚ በመሆናቸው በግልጽ የታወቀ የአእምሮ ህመም የነበረባቸው ሴት ነበሩ ብሎ ለመደምደም በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟሉም፤ ተከሳሽ የከሳሽ እናት የአእምሮ ህመም /ችግር/ ያለባቸው መሆኑን እያወቀ ውሉን የተዋዋለ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የከሳሽ እናት በመጨረሻ ጊዜ በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተገኝተው የሕክምና አገልግሎት ያገኙት ጥር 21 ቀን 2001 መሆኑን የቀረበው የሕክምና ማስረጃ ያሳያል፡፡ ይህም ውሉ በተደረገበት ሰኔ 18 ቀን 2001 ህክምናቸውን ጨርሰው በጤናማ የአእምሮ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሽ የከሳሽ እናት በጤናም አእምሮ የቤት ሽያጭ ውል የተዋዋሉ ስለመሆኑ የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ አስረድቷል፡፡ ስለዚህ የቤት ሽያጭ ውሉ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡
4. አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ መስቀለኛ ይግባኝ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ተጠሪ የስር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል፤ አመልካች የመክሰስ መብት

www.abyssinialaw.com

የለውም በማለት ያቀረብኩትን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አላግባብ ውድቅ አድርጎብኛል በማለት ያቀረበውን መስቀለኛ ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

5. አመልካች ግንቦት 12 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ፤ ሟች ወላጅ እናቴ 1996 የአእምሮ ህመም ምክንያት ወደ አማኑኤል ሆስፒታል በመሄድ ስትታከም የቆየች መሆኑንና ህመሙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 256 መሰረት ለማቅረብ ጠይቀው የነበረው ሆስፒታሉ ጥር 3 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠው ማስረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወላጅ እናቴን በሰኔ ወር 2001 ዓ.ም ከሌላ ገዥ ጋር አገናኝቷት የነበረ ደላላ እናቴ እራሷን መቆጣጠር የማትችል እንደነበረች መስክሯል፡፡ እናቴ ቤት ተዘግቶባት የምትኖር ነበረች፡፡ ቤቱንም የሸጠችው በእርካሽ ዋጋ ነው፡፡ እንደዚሁም ውሉ የሟች ጣት አሻራ የሌለው መሆኑ ዋናውን ቅጅ ለማረጋገጥ ፈልጎ ሊያገኘው እንዳልቻለ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ገልጾ እያለ፤ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የአመልካች እናት እብደታቸው በግልጽ የተወቀ ወይም የተዘጋባቸው እብድ አልነበሩም፡፡ የአመልካች እናት እብደታቸው በግልጽ ያልታወቁ ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ወላጅ እናቱ የተዋዋሉትን ውል ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብት በህግ አልተሰጠውም፡፡ ተጠሪ ቤቱን የገዛሁት የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በአዋጅ ቁ. 334/95 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚያጣራቸውን ነገሮች አጣርቶና አረጋግጦ፤ የአመልካች እናትም ውል ለመዋዋል ችሎታ ያላቸው መሆኑንና በነጻ ፈቃዳቸው ውሉን የተፈራረሙ መሆኑ ተረጋግጦ ነው፡፡ አመልካች ውል መዋዋል አይችሉም ነበር በማለት አንድ ሃኪም የሰጠው ማስረጃ የግል አስተያየቱና ከሙያ ስነ ምግባሩ በወጣ ሁኔታ የተሰጠ ነው፡፡ በሆስፒታሉ ህክምና ቦርድ በኩል ተረጋግጦ የቀረበ ማስረጃ አይደለም፡፡ አመልካች እናታቸው የአእምሮ ህመምተኛ መሆናቸውን ካወቁ በህግ በተደነገገው መሰረት እናታቸው ውል እንዳይዋዋሉ በፍርድ ማስከልከል ሲገባቸው ይህንን ሳያደርጉ ውሉ ይፍረስ በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ የአመልካች እናት፤ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተደረገው ውል ከተገለጸው በላይ የሆነ ገንዘብ ከተጠሪ መቀበላቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ እንዲሰናበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2007ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ተጠሪ ከሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ

ጋር አድርጎት የነበረው የቤት ሽያጭ ውል ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

8. መዝገቡን እንደመረመርነው የአመልካች እናት ወ/ሮ ዘውዱ በየነ የፍተሐ ብሔር ህግ ቁ. 341 እና የፍተሐ ብሔር ህግ ቁ. 342 በሚደነግገው መሰረት የነበረባቸው የአእምሮ ጉድለት፤ በግልጽ የሚታወቅ የአእምሮ ጉድለት ስለመሆኑ አመልካች የማስረዳት ግዴታውን /Burdon or proof/ ያልተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች በወላጅ እናቱ ላይ ነበረ የሚለው የአእምሮ ጉድለት በፍተሐ ብሔር ህጉ በግልጽ ያልታወቀ የአእምሮ ጉድለት በሚል መንገድ የሚገልጸው የአእምሮ ጉድለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

9. የእብደቱ ሁኔታ በግልጽ ያልታወቀ ሰው የፈጸማቸው የህግ ስራዎች በዚሁ ሰው የአእምሮ ጉድለት ምክንያት ሊሻሩ የማይችሉ ስለመሆኑ በመርህ ደረጃ የፍተሐ ብሔር ህግ ቁ. 347 ንዑስ አንቀጽ 1 ደንግጓል፡፡ ከዚህ ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የተፈቀደው በፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 347 ንዑስ አንቀጽ 2 እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው ውሉ እንዲፈርስለት የሚጠይቅበት ሁኔታና በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 349 እና በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 350 የተደነገጉት ልዩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ሟች ወ/ሮ ዘውዱ በየነ ቤታቸውን ለተጠሪ የሸጡት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተደረገ ውል ሲሆን፤ አመልካች የሚከራከረው የቤቱ ዋጋ ዝቅተኛ መሆኑ ሟች እናቴ የአእምሮ ህመም ምክንያት ንብረቱን በበቂ ዋጋ ያልሸጠች እና የአእምሮ ህመም ምክንያት ውል የተዋዋለች መሆኑን ያሳያል በማለት ነው፡፡

10. ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በምን ያህል ገንዘብ ነው የገዛው የሚለው ነጥብ፤ በመጀመሪያ ሟች ወ/ሮ ዘውዱ በየነ ከተጠሪ ጋር በውሉና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ያደረጉት ውል ፈራሽ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ ምላሽ ካገኘ በኋላ የሚታይ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ስለቤቱ ዋጋ ያደረጉትን ክርክርና ክርክሩን ለማስረዳት ለበታች ፍ/ቤቶች ያቀረቧቸውን የተለያዩ ማስረጃዎች ይዘት መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ደረጃ አመልካች የቤቱ ዋጋ ማነሱን ለውል ማፍረሻነት ምክንያት አድርገው ያቀረቡት ክርክር የህግ ድጋፍ አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህ አመልካች ያነሳው መከራከሪያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ለማፍረስ በቂ ምክንያትና መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ የማይችል መሆኑ በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 2887 የተደነገገ በመሆኑ፤ አመልካች ቤቱ በዝቅተኛ ዋጋ የተሸጠ መሆኑ፤ ሻጭ የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው

www.abyssinialaw.com

መሆኑን ስለሚያሳይ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

11. በአጠቃላይ ሲታይ የፍተሐ ብሔር ህጉ እብደቱ በግልጽ ያልተወቀ ሰው ወራሾች ወይም ባለገንዘቦች ይህ ሰው የፈጸመው ውል ጉድለት የሌለበት ፈቃድ አልሰጠበትምና ውሉ ሊፈርስ ይገባል ሲሉ እብደቱን ምክንያት በማድረግ የውሉን መፍረስ መጠየቅ እንደማይችሉ በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 348 ተደንግጓል፡፡ ህጉ ይህንን የደነገገው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ባለቤቱ በግልጽ ያልታወቀ የአእምሮ ህመም ምክንያት የእለት በእለት እንቅስቃሴው በራሱ መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስ የህግ ተግባር ሊፈጽም የሚችል መሆኑን በቅርበት የሚያውቁት ይህ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀው ሰው ወራሾች፣ ወይም አበዳሪዎች፣ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው /ሴት/ ህጋዊ ተግባራትን የመፈጸም ችሎታው በፍርድ ክልከላ እንዲደረግበት ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በማመልከትና በፍርድ በማስከልከል መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚችሉበት እድል በትጋት በመጠቀም፣ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀውን ሰው፣ የራሳቸው እና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚከላከል ግዴታ ጥሎባቸዋል፡፡ አመልካች የሚች እናቱ የአእምሮ ህመም በስር ፍ/ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ደረጃ የሚያውቅበት ጊዜ፣ የእናቱ ችሎታ በፍርድ ክልከላ እንዲደረግበት መጠየቅና ማስወሰን ሲገባው ይህንን ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም፡፡

12. ተጠሪ ከወ/ሮ ዘውዴ በየነ ጋር ቤት ገዥ ውል ሲዋዋል፣ ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የአእምሮ ህመም ያለባቸው መሆኑን የማያውቅና በቅን ልቦና የሽያጭ ውሉን የተዋዋለ መሆኑን የበታች ፍ/ቤት አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስለት ያቀረበው ጥያቄ ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ፣ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበውን የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው፣ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት፣ ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75175 ህዳር 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 142657 ሚያዚያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ነሐሴ 5 ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ የእግድ ትእዛዙ የተነሳ መሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

**የልዩነት ሐሳብ**

ስሜ በተራ ቁ. ሶስት የተመዘገብኩት ዳኛ የስራ ባልደረቦቼ በአብላጫ ድምጽ በሰጡት ውሳኔ ላይ ባለመስማማት የልዩነት ሐሳቤ እንደሚከተለው አስፍሬለሁ፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪው ጉዳይ የአመልካች አውራሽ ወ/ሮ ዘውዴ በየነ ከተጠሪ ጋር አደረጉት የተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በሕግ ፊት የሚጸና መሆን ያለመሆን ነው፡፡ አመልካች ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት ወላጅ እናታቸው በከፍተኛ የአእምሮ ህመም እየተሰቃዩ በነበሩበት ጊዜ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በርካሽ ዋጋ ለተጠሪ መሸጣቸውን ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ከአመልካች አውራሽ ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል በውልና ማስረጃ የተደረገ መሆኑን በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የመረመረው የስር ፍ/ቤትም የአመልካች አውራሽ በግልጽ ያልታወቀ የአእምሮ ጉድለት የነበራቸው ስለመሆኑ በመግለጽ የቤት ሽያጭ ውሉ ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አፅንቷል፡፡

በመሰረቱ አንድ ውል በተዋዋይ ወገኖች በሕጉ አግባብ ተደረገ የሚባለው በፍ/ሕ/ቁ. 1678 የተመለከቱት መሰረታዊ መስፈርቶች ሲሟሉ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደመሰረታዊነት ከተመለከቱት ነጥቦች አንዱ ፈቃድ /consent/ የሚሰጥበት አግባብ ነው፡፡ አንድ ተዋዋይ ጉድለት የሌለበት ፈቃድ ሰጥቷል ለማለትም ያከናወነው ሕጋዊ ተግባር /juridical act/ በምክንያታዊ ሰው አእምሮ ተቀባይነት ያለው ድርጊት ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች አውራሽ በህመም ላይ እንደነበሩ ቤቱም የተሸጠው ከገበያ ዋጋ በታች ስለመሆኑ ክርክር መቅረቡን መዝገቡን ያሳያል፡፡ የአመልካች አውራሽ ሃኪም ቤት እየተመላለሱ የድብርት ህመም ህክምና እንደተደረገላቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ በስር ፍ/ቤት መዝገቡ እንደተገለጸው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ለሌላ ሰው ለመሸጥ በተደረገ ጥረት የአእምሮ ችግር የነበራቸው በመሆኑ ቤቱ ሊሸጥ አለመቻሉን በአመልካች የቀረቡ ምስክር አስረድተዋል፡፡

የስር ፍርድ የአመልካች አውራሽ የሕመም ሁኔታ ያልታወቀ የአእምሮ ጉድለት ነው ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ሆስፒታል ውስጥ አልጋ ይዘው እየታከሙ አለመሆኑን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በእርግጥ የታወቀ የአእምሮ ጉደለት ታማሚው የተዘጋበት መሆን እንደመነሻ የተወሰደ ስራ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 341 ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ይህ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት አገሪቷ አሁን ከደረሰችበት የእድገት ደረጃ እና የሆስፒታሎች የማስተናገድ አቅም ተገናዝቦ ነው፡፡ የአእምሮ ህመም ያላቸው ታካሚዎች ለማስተናገድ የሚያስችል በቂ የጤና ተቋም በሌለበት ሁኔታ ሆስፒታል ወይም ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው መኖሪያ ያልተዘጋበት ግለሰብ እንደ የታወቀ የአእምሮ

ጉድለት ያለበት ሰው አይወሰድም የሚለው ክርክር ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበ የሃኪም ማስረጃ ሟች እናታቸው በከፍተኛ የአእምሮ ሕመም ይሰቃዩ እንደነበር ከአማኑኤል ሆስፒታል የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ በተጠሪ ሳይካድ ሙያዊ አስተያየቱ ዋጋ የሌለው ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ሌላ ያቀረቡት ክርክር ተደረገ የተባለው ውል የጣት አሻራ የለውም፤ ውሉ ከውልና ማስረጃ ቀርቦ ይጣራ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በተመለከተም ተጠሪ ውሉ በውልና ማስረጃ የተደረገ ነው ከማለት ውጭ በእርግጥም በስር ፍ/ቤት የቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ በሕጉ አግባብ ስለመስተናገዱ የቀረበ ክርክር የለም፡፡

የአመልካች አውራሽ ሽያጩ ሲፈጸሙ ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም የአእምሮ ጤናቸው ምን ደረጃ ላይ ነበር የሚለው ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ማጣራት የተደረገበት አይደለም፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ ሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የጤና ሁኔታቸው በጥሩ ሁኔታ እንዳልነበረ ለማጣራት መነሻ የሆነውን የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከአማኑኤል ሆስፒታል የተገኘ ማስረጃ ይሁን በአመልካች የቀረበው የሰው ምስክር የሟች የጤና ሁኔታ ሕጋዊ ተግባር ለማከናወን በሚችሉበት ሁኔታ እንዳልነበሩ መነሻ ክርክር ከቀረበ ፍ/ቤቱ እውነት የማፈላለግ (truth finding) ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ግራቀኙ የሚያቀርቡት ማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የሟች የጤና ሁኔታ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ በዚህ ጉዳይ ሙያ ያላቸው (expert opinion) ሳይክትሪስት ትንታኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካች አውራሽ የአእምሮ ሁኔታ በግልጽ ያልታወቀ እብደት ነው ከሚል ድምዳሜ ለመድረስ መሰረት ያደረገው አልተዘጋጀባቸውም በሚል ምክንያት እንጂ የአእምሮ ጉድለቱ ያልታወቀ እብደት ስለመሆኑ ሳይንሳዊ ትንታኔ የተሰጠበት ጉዳይ አይደለም፡፡ የህመሙ ደረጃ በግልጽ አልተለየም፡፡

በአመልካች አውራሽ እና የተጠሪ የተደረገው ሽያጭ ጉድለት የሌለበት ስለመሆኑ ለመለየት ግራቀኙ ያደረጉት የውል ማቅረብ (offer) እና መቀበል (acceptance)፤ እንዴት እንደተገናኙ፤ ቤቱ በምን ያህል ገንዘብ እንደተሸጠ፤ የሽያጭ ገንዘቡ የተከፈለበት አግባብ በዝርዝር መጣራት የነበረበት ጉዳይ ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ የተደረገ ነው ከተባለም የሟች ወ/ሮ ዘውዴ በየነ የጤና ሁኔታ አከራካሪ እስከሆነ ድረስ ሂደቱን ሊመረመር ይገባ ነበር፡፡ ሕጉ ጥበቃ የሚያደርገው የቅን ልቦና ገዥ ነኝ ለሚል ሰው ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው ግለሰቦችም ሕጋዊ መብታቸው እንዳይጣስ የወራሾችም መብትና ጥቅም ጭምር ለማስከበር በፍ/ሕ/ቁ. 339 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም የአመልካች አውራሽ የሽያጭ ውል አደረጉ በተባሉበት ጊዜ የነበራቸው የአእምሮ ሁኔታ እብደቱ በግልጽ የሚታወቅ ነው ወይስ የማይታወቅ ? የሚለው መሰረታዊ ጭብት

www.abyssinialaw.com

በባለሙያ በተደገፈ ሳይንሳዊ ትንታኔ ተደርጎበት በአግባቡ አለመጣራቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊሆን ይገባው ነበር፡፡ የአመልካች አውራሽ እና ተጠሪ የቤት ሽያጭ ግንኙነት እንዴት እንደተመሰረተ? ተከፈለ የተባለው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ እና ገንዘቡ ማን እንደተቀበለው? በመንደር ውል የተጻፈው የገንዘብ መጠን እና በውልና ማስረጃ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ ልዩነት ካለው ለምን ሊሆን እንደቻለ በዝርዝር ቢጣራ በእርግጥም የአመልካች አውራሽ የጤንነት ሁኔታ የሚጠቁም እውነት ላይ ለመድረስ የሚያችል ነገር ይገኝ ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ፍ/ቤቶች የአመልካች አውራሽ እና ተጠሪ አደረጉት የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ከጉድለት የጸዳ ስለመሆኑ ከላይ በተገለጹ ዝርዝር ምክንያቶች ሳይጣሩ የሽያጭ ውሉ በሕግ ፊት የጸና ነው በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ አይደለም፡፡ ጉዳዩ በሕጉ አግባብ ተመርምሮ በእርግጥም በሕግ ፊት የሚጸና የቤት ሽያጭ ውል ነበረ ወይስ አልነበረም? የሚለው አከራካሪ ነጥብ በስር ፍ/ቤት በድጋሚ ከተጣራ በኂላ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በስር ፍ/ቤት የተፈጸሙ ግድፎቶች ሳይጣሩ ውሳኔውን ማጽናቱ ተገቢ አይደለም በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 106856

ጥር 16/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም ገመቹ ወኪል ሀቢብ መሐመድ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሮማን ገመቹ ጠበቃ እንዳርጋቸው ዳኘው ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሀብት ነው የተባለው ንብረት ለይቶ ከመወሰን ጋር የተያያዘ የቀረበ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባቀረቡት የውርስ ሀብት ይጣራልኝ ጥያቄ መሰረት የውርስ አጣሪ ተሾሞ ጉዳዩን አጣርቶ ለፍርድ ቤት ባቀረበው ሪፖርት መነሻነት ነው፡፡ የውርስ አጣሪው በ29/03/2005 እና ግንቦት 08 ቀን 2005 አሻሽሎ ያቀረበው ሪፖርት ላይ የውርስ ሀብት ንብረት የሆኑና ያልሆኑ ለይቷል፡፡ የውርስ ሀብት ንብረት አይደለም ተብሎ የተለየው እና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 3215 የሆነውን መኖሪያ ቤት ሲሆን የአሁኗ ተጠሪ ቤቱ የውርስ ሀብት ነው በማለት ሲከራከሩ፤ አመልካች በበኩላቸው አውራሻቸው (ገመቹ ውለታ) በሕይወት እያሉ ቤቱን ለአመልካች የገዙት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የውርስ አጣሪው ባደረገው ማጣራት ቤቱ በ18/05/1994 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 የኑሮ በህብረት የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ያለው በ160 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈው ጅምር ቤት በብር 27,000.00 /ሀያ ሰባት ሺህ ብር/ ከወ/ሮ ከድጃ ሀሰን በአመልካች ስም መገዛቱን አረጋግጠዋል፡፡ በማጠቃለያ አስተያየቱም ቤቱ በሚች ገንዘብ እንደተገዛ ማስረጃ አልቀረበም በሚል ምክንያት የውርስ ሀብት ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም ሲል ደምድመዋል፡፡

የውርስ አጣሪው ሪፖርት የመረመረው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ አስተያየት ያዳመጠ ሲሆን በሌሎች ጉዳዮች ተስማምተው በዚሁ ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በወረዳ 4 የቤት ቁጥር 3215 የሆነው መኖሪያ ቤት በሟች አቶ ገመቹ ውለታ ገንዘብ በአመልካች ስም የተገዛ በመሆኑ የውርስ ሀብቱ ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል አቤቱታ እና ሟች በአመልካች ስም ወደው የገዙት ቤት በመሆኑ የውርስ ሀብት ሆኖ መመዝገብ የለበትም የሚል ክርክር መቅረቡ ፍ/ቤቱ መዝግበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ አስተያየት ከመረመረ በኃላ ምንም እንኳ ጅምር ቤቱ በተጠሪ ስም የተገዛ ቢሆንም ጅምር ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ ግን በአመልካችና ተጠሪ ወላጅ አባት የሟች አቶ ገመቹ ውለታ መሆኑን አመልካች አልካዱም፡፡ ስለሆነ ጅምር ቤቱ መገኛ ምንጩ የተገዛበትን ገንዘብ የሟች አቶ ገመቹ ውለታ ስለሆነ ተጠሪ እስካልካዱ መኖሪያ ቤቱ የውርስ ሀብት ንብረት ነው በማለት የውርስ አጣሪው ሪፖርት በማሻሻል በማፅደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ቤቱ በአመልካች ስም የተገዛ ቢሆንም ቤቱ የተገዛው በአውራሻቸው ገንዘብ መሆኑ ታምነዋል፡፡ የሽያጭ ውልና የማህበሩ አባልነት መታወቂያ ቢያቀርቡም እንደ ፍ/ሕ/ቁ. 1195 (1) አነጋገር የቀረበ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት ያልቀረበ መሆኑን እና የቤቱ መግዣ ምንጭ ሟች አባታቸው ስለመሆናቸው እየተከራከሩ ቤቱ የውርስ ሀብት ንብረት የማይሆንበት ምክንያት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ቤቱ በስማቸው የተገዛ በመሆኑ የውርስ ሀብት ንብረት ሊሆን አይገባም፤ ባለቤትነት ለማረጋገጥ በፍ/ሕ/ቁ. 1195 (1) የሚቀርበው የይዞታ ማረጋገጫ ብቸኛ ማስረጃ አይደለም፤ በማህበራት የተደራጀ የመኖሪያ ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ በሂደት እንደሚሰጥ እየታወቀ መታለፍ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ቤቱ የተገዛው በአውራሽ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የውርስ ሀብት ንብረት ነው መባሉ በአግባቡ ነው በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ አከራካሪ የሆነውን ቤት ሟች በሕይወት እያሉ በአመልካች ስም የተገዛና በስማቸው የተመዘገበ መሆኑን ባለተካደበት፤ ቤቱ የተገዛው በሟች ገንዘብ ነው በሚል ምክንያት

www.abyssinialaw.com

የውርስ ሀብት ንብረት ነው ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በአመልካች ስም የተገዛና የተመዘገበ ቢሆንም ቤቱ የተገዛው በአውራሽ ገንዘብ ስለመሆኑን ነው፡፡ አመልካች ቤቱ በስማቸው የተገዛው የውርስ ሀብት መሆን እንደማይገባው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩላቸው ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ ምንጩ የአውራሽ በመሆኑ ቤቱ ከውርስ ሀብት ውጭ የሚሆንበት አግባብ እንደሌለ መከራከራቸውን ተረድተናል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በአመልካች ስም የተገዛና የተመዘገበ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ቤቱ ለመግዛት ምንጭ የሆነውን ገንዘብ የአውራሻቸው በመሆኑ ቤቱ የውርስ ሀብት ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ቤቱ የውርስ ሀብት ነው ለማለት መነሻ ያደረጉት ቤቱ በአውራሽ ወይም በሟች ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወራሽ የሟች ውርስ የተቀበለ ከሆነ አስቀድሞ የወሰደው ንብረት ተመላሽ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 1065 ሥር ተደንግጓል፡፡ ይሁንና አውራሽ አስቀድሞ ንብረት የወሰደ ወራሽ ንብረቱ ተመላሽ እንዳይደረግ ነፃ ሊያደርገው እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቤቱን በስማቸው የተገዛና የተመዘገበ ቢሆንም አስቀድሞ የተወሰደው ንብረት ተመላሽ እንዳይደርጉ በሚፈቅድ አግባብ ቤቱ የተሰጣቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ቤቱ በሟች ገንዘብ ስለተገዛ ቤቱ የውርስ ሀብት ነው ያሉ ቢሆንም ቤቱ ለአመልካች ሟች ከመሞታቸው በፊት የተገዛ ከመሆኑ አንፃር ጉዳዩ መታየት የነበረበት የፍ/ሕ/ቁ.1065 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የሟች ወራሾች ተመላሽ የሚያደርጉት ንብረት የሚመለስበት ሥርዓት ከፍ/ሕ/ቁ.1074 እና 1076 አንፃር መታየት አለበት፡፡ የሟች ሀብት ወራሹ ከወሰደውና ከሚደርሰው ገንዘብ በላይ ከሆነ አስቀድሞ የወሰደው የንብረት መጠን /ግምት/ ተቀንሶ በቀሪ የጋራ ወራሾች ሀብት ላይ ድርሻውን ማግኘት ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ሕ/ቁ.1074 (2) እና 1076 (1) ድጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ነው፡፡ በሌላ በኩል ወራሽ አስቀድሞ የወሰደው ንብረት ግምት ወራሾች በጋራ ከሚወርሱት ሀብት የበለጠ ከሆነ ድርሻው ተሰልቶ እስከ ድርሻውን መጠን ታስቦ የውርስ ሀብት እንደሆነ ግምት የሚወሰድ ቢሆንም ከግምት በላይ የተወሰደውን ለመመለስ ግዴታ እንደሌለው በፍ/ሕ/ቁ. 1076(2) ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ቤቱ የተገዛው በብር 27,000.00 /ሀያ ሰባት ሺህ ብር/ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የታመነ ፍሬ ነገር ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ከአውራሻቸው ሀብት አስቀድመው ብር 27,000.00 ግምት ያለው ንብረት መውሰዳቸው የሕግ ግምት ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም የሟች ሀብት አመልካች አስቀድመው ከወሰዱት ግምት በላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ድርሻቸው ይህ የገንዘብ መጠን ከተቀነሰ በኃላ ከቀረው ገንዘብ የሚወሰዱ

www.abyssinialaw.com

ሲሆን የአውራሻቸው ሀብት አመልካች አስቀድመው ከወሰዱት ብር 27,000.00 በታች ከሆነ ግን ይህንን ገንዘብ ለመመለስ የሚገደዱበት የሕግ ሥርዓት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ቤቱ የተገዛው በአመልካች እና ተጠሪ አውራሽ ገንዘብ ነው በሚል መነሻ ቤቱ የውርስ ሀብቱ ንብረት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ከአውራሻቸው ከሚያገኙት ሀብት የብር 27,000.00 ግምት አስቀድመው እንዲወስዱ ከሚቆጠር በስተቀር በአመልካች ስም የተገዛና የተመዘገበ ቤት የውርስ ሀብት አካል ተደርጎ ክፍፍል የሚደረግበት አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች አስቀድሞ በስማቸው የተገዛውና የተመዘገበው ቤት ተመላሽ ለማድረግ የማይገደዱ ሲሆን የአውራሻቸው ሀብት ከዚህ ቤት መግዣ ገንዘብ በላይ ከሆነ፤ ይህ ገንዘብ ተቀንሶ ድርሻቸው እንዲወሰዱ፤ የአውራሽ ሀብት ከወሰዱት ቤት ተመጣጣኝ ከሆነ በዚህ መጠን ተወስነው እንዲቀሩ፤ የአውራሽ ሀብት በክሱ ከተጠቀሰው የቤቱ ዋጋ በታች ከሆነ ግን አመልካች ገንዘቡን ወይም ቤቱን የውርስ ሀብት አካል ለማድረግ የሕግ ግዴታ እንደሌለባቸው ከፍ/ሕ/ቁ. 1074(2) እና 1076(2) ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አንዱ ወራሽ አውራሹ ከመሞቱ በፊት ያገኘው ንብረት ተመላሽ የሚያደርግበት ሥርዓት /Collation by heirs/ በሕጉ አግባብ ሳያገናዝቡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የውርስ ሀብት ነው ማለታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26419 ሐምሌ 4/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 140321 መስከረም 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 3215 በአውራሽ ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ ብቻ የውርስ ሀብት ሊሆን አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከአውራሻቸው የሚያገኙት ንብረት በክሱ ከተጠቀሰው ቤቱ የተገዛበት ብር 27,000.0 በላይ ከሆነ፤ ይህንን ገንዘብ ከድርሻቸው ተቀንሶ ከቀረው ገንዘብ ድርሻቸው እንዲገኙ፤ ከአውራሻቸው የሚያገኙት ገንዘብ እኩል ከሆነ ባሉበት እንዲፀኑ፤ የቤቱ ዋጋ በውርስ ከሚያገኙት ገንዘብ በላይ ከሆነም በፍ/ሕ/ቁ. 1076(2) መሰረት ለመመለስ አይገደዱም ብለናል፡፡
4. የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

www.abyssinialaw.com

5. በዚህ ችሎት ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.111216

ቀን የካቲት 15/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኤልሳቤት አህመድ ተወካይ ፀሃይነሽ አህመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማፈኛ አባዩ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፈርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ አከራከሪ የሆነው ጭብጥ የውርስ እና የሚስት ግማሽ ድርሻ ንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ሟች ከተቀበሩበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ቀን ድረስ ያለውን ውጪ በእኩል ለመካፈል የተደረገው ስምምነት መሠረት ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች የአሁኗ አመልከች የብር 153,040.00 ግማሽ ይክፈሉ በማለት የሰጡት ትእዛዝ በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

አመልካች ውሉን እንዳልተስማሙበት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት የቀረበው ውል ሪፖርት እንደተቀበለ፤ በቀረበው ውል መሠረት ሟቹ ከተቀበሩበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ድረስ ያለው ወጪ ብር 153,540.00 እንደሆነ፤ በፍ/ህ/ቁ. 1014 መሠረት ወጪ ከውርስ ንብረት ክፍፍል በፊት የሚከፈል ስለመሆኑ በደንገጉን የግራ ቀኙ የውል ስምምነትም በዋናው መዝገብ ቁጥር 08093 ላይ ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ ቤቶቹ የሚከፋፈሉት ከማንኛውም እዳ ነፃ ከሆኑ በኃላ ስለ ሚል፤ ወጪውም ሁለቱም ተከራከሪ ወገኖች እንደሚመለከት፤ የአፈፃፀም ከሳሽ (አመልካች) የወጪውን ግማሽ ብር 76,520.00 ከፍለው እንዲሁም እንደውላቸው የሴንተናል ሆቴል ቤት ግምት አንድ መቶ ሺህ ብር ከፍለው የቤት ቁጥር 1345 የሆነውን እንዲራክቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች የዲጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 08412 በ21/08/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በመቃወም ሰምስረቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ከተመረመረ በኃላ በአመልካች በኩል እዳው ከሆቴሉ ገቢ ተከፍሏል የሚል ክርክር እንደቀረበ ይሁንና ለክርክሩ መነሻ የሆነውን እዳ ብር 153,040.00 ከሆቴል ገቢ መከፈሉን እንዳልተረጋገጠ፣ ግራ ቀኙ ባደረጉት የውል ስምምነትም አውራሹ ከሞቱ በኃላ ከሞቱበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ቀናት ድረስ የወጣው ውጪ ሊካፈሉ መስማማታቸው እንደሚያሳይ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡኩት አቤቱታ ውድቅ ተደርጓአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ /ትእዛዝ/ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርመሮ በሰበር እንዲታይ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዕዳ ከሟ የጋራ ሀብት የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ብር 76,520.00 እንዲከፍሉ መወሰናቸው በአግባቡ አይደለም የሚል ክርክር ሲያቀረቡ፤ ተጠሪ በሰጡት መልስ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት የሟች ዕዳዎች ተለይተው አመልካችም በግልጽ የተስማሙበት ስለመሆኑ፣ ወጪ የተደረገውም ለቀብር ብቻ ሳይሆን ሟች በህይወት በነበሩበት ጊዜ የነበረባቸው የብድር ዕዳዎች የሚመለከት በአመልከችም የታመነ ነው የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚነቀፍ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህ ችሎት ዕልበት የሚያስፈለገው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች እና ተጠሪ ሟች ከተቀበሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 80 ቀን ተደረጉ የተባሉትን ወጪዎች እኩል ይክፈሉ በማለት ትዕዛዝ የመስጠታቸው አግባብነት በግራ ቀኙ ያደረጉት ስምምነት መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ከስር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት የተቻለው ሟች ከተቀመሩበት ቀን ጀምሮ እስከ 80 ቀን ድረስ ያለውን ወጪ ብር 153,040 መሆኑን በ15/08/2004 ዓ/ም በተጻፈው ውል ቃለ ጉባኤ እንደተገለጸ፣ የህም ሁለቱን ወገኖች የሚመለከት ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች ዕዳው ለሴንትራል ሆቴል ገቢ የተከፈለ ነው የሚል ክርክር ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በደረገው ማጣራት ዕዳው ከሆቴሉ ገቢ ስለ መከፈሉ የሚያረጋግጥ ነገር አለመቅረቡን በትዕዛዙ አስፍሯል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ሚያዝያ 15 ቀን 2008 ዓ/ም በሽማግሌዎች ፊት የፈረሙት ውል ላይ እንደተመለከተው የሟች ዕዳ ከግብአት ቀብር እስከ 80 ቀን በአጠቃላይ የሚመለከት እንዲሆነ፤ ሟች ከግለሰቦች የወሰዱት ዕዳም እንደሚያከቲት እና አጠቃላይ ወጪው 153,040.00 /አንድ

www.abyssinialaw.com

መቶ ሀምሳ ሦስት ከአርባ ብር/ እደሆነ ተገልጸዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአሁኑ አመልካች እንዲጋሩት የተጠየቁት ዕዳ ለቀብር ስነ ስርዓት ማስፈጸሚያ የወጣውን ወጪ ብቻ ይሆን የሟች ዕዳዎች የሚያጠቃልል ስለመሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው /ትዕዛዙ/ እንደገለጸው በአመልካች እና ተጠሪ የተፈረመው ውል በመዝገብ ቁጥር 08093 ውሳኔ የተሰጠበት ለፍርድ አፈፃፀም መነሻ እንደሆነ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል አለማደረጋቸውን በህግ የተደገፈ ክርክር አላቀረቡም፡፡ ይህ ከሆነ ግራ ቀኙ ባደረጉት ግልጽ ስምምነት የውርስ ሀብት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የሟች ዕዳዎች ቅድሚያ እንደሚከፈሉ የተስማሙ መሆኑን መስራት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ግማሹን ዕዳ እንዲከፍሉ መወሰናቸው በህጉ አግባብ ነው ከሚበል በቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት በፈጸማቸውን አያሰይም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ከአውራሻቸው ያገኙት ሀብት ወደ ስማቸው ሊተላለፍ የሚችለው በቅድሚያ የሟች ዕዳ የሆነውን ግማሹ ማለትም 153,040.00 ሲካፈል ለሁለት 76,520.00 የመክፈል ግዴታቸው ከተወጡ በኃላ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም አመልካች ከተጠሪ ጋሪ በገቡት ውል መሠረት የሟች ዕዳ መሆኑን የተረጋገጠው ግማሹን ይክፈሉ በማለት መወሰናቸው በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የዲጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08412 በ29/08/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 34524 በ10/11/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 186415 በ18/5/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አመልካች የሟች ዕዳ መሆኑን በገቡት ውል መሰረት ያረጋገጡት የብር 153,040.00 ግማሹን 76,520 /ሰባ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሀያ/ እንዲከፍሉ መወሰኑ በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/ 110040

የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

**አመልካች**፡- 1. ወ/ሮ እሴተማርያም አክሎግ
2. ወ/ሪት ወይንሸት አክሎግ
3. አቶ መክብብ አክሎግ
} የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ውርስ ጥያቄ የመመልከት ነው፡፡ አመልካቾች ለአ.አ.ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀ/ሚካኤል ወራሽነት ይረጋገጥልን በማለት አቅርበዋ፡፡ የአባታቸው ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ወራሽነት ያረጋገጡ ሲሆን የወላጅ አባታቸው እናት ወራሽነት ለማረጋጥ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ወላጅ አባታቸው በ1981 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን አያታቸው ወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል የሞቱት ደግሞ በ1978 ዓ/ም ነው፡፡ በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤቱም አያታቹህ ከአባታቹሁ ቀድመው የሞቱ ስለሆነ ተተኪ ወራሽ ልትሆኑ አትችልም በማለት ብይን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ብይን ባለመስማማት አቤቱታቸውን ለአ.አ.ከተማ ይግባኝ ሰሚና ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞውታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች ተወካይ የካቲት 10 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፉት የሰበር

www.abyssinialaw.com

አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ብይን ተእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ወላጅ አባታችን እናቱ ከሞቱ ጀምሮ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ በህመም ላይ እንደነበረ ለስር ፍርድ ቤቶች አስረድተን እያለን የአያታችን ወራሽነት አታረጋግጡም መባሉ ከፍተኛ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ወላጅ አባታችን ለ3 አመት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የእናቱ ወራሽነት ሳያረጋግጥ ቢቀርም አመልካቾች ተተኪ ወራሾች የአያታችን ወራሽነት የሚከለክለን አንዳችም ህግ የሌለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ በመሻር የአያታችን ወራሽነት እንዲረጋገጥላቸው አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተተኪ ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም በማለት የተሰጠ ብይን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 830፣831/3/844 እና 839 አንፃር ለመመርመር በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ሊቀርብ የቻለው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ካቀረበበት ብይን እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የአመልካቾ ጥያቄ ወላጅ አባታቸው ተከተው የአያታቸው ወራሽነት እንዲረጋጥላቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ደግሞ ተተኪ ወራሾች ልትሆኑ አትችሉም በማለት ብይን ተሰጥተዋል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ ስር እንደተመለከተው የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ልጆች ቀድመው ከሞቱና ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ትተው ከሆነ ተወላጆቹ ወላጃቸውን ተተክተው ሚችን እንደሚወርሱ ያመላክታል፡፡ የተተኪ ወራሽነት የተፈፃሚነት ወሰን ወደ ታች የሚቆጥሩ ተወላጆች እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸው፡፡ አመልካቾችም የወላጅ አባታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እንደሆኑ ህጉ ከመገንዘብ ይቻላል፡፡ ተተኪ ወራሽ ለመሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ/ 842/3/ አንፃር ሲታይ የአመልካቾ ጥያቄ የሚያሟላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ወላጅ አባታቸው የእናታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆን የወረሱ ስለሆነ የምትክ ጉዳይ ሊነሳ አይችልም፡፡ በሌላ አነጋገር አመልካቾች አባታቸው ተክተው አያታቸውን መውረስ የሚችሉት አባታቸው ከአያታቸው በፊት የሞቱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች የሚች አባታቸውን ወራሽነት ስለማረጋገጣቸው ከክርክሩ ስለተረዳን አባታቸው የወረሱትን ንብረት ለመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪየ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 1118/07 ጥር 6 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የአ/አ፤ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ/23073 ጥር 21 ቀን 2007 ዓ/ም እና የአ/አ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 23140 የካቲት 2 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 348/1/መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   መዝገብ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሀሳብ

የአመልካቾቹ መሰረታዊ የአቤቱታ ነጥብ ወላጅ አባታችን ሻለቃ አክሎግ አድማሱ ከወላጅ እናታቸው ከወ/ሮ ደብረወርቅ ሀብተ ሚካኤል በኃላ የሞቱ በመሆኑ አባታችን የነበራቸው እናታቸውን የመውረስ መብት ለእኛ ለሻለቃ አክሎግ አድማሱ ልጆች እና ወራሾች የሚተላለፍ መሆኑ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠን የሚል መሆኑን ከስር ጀምሮ ከሚያቀርቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሰረቱ ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኃላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለርሱ ወራሾች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 ተመልክቶአል፡፡ ከአውራሹ አስቀድሞ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 844 (2) እና ከአውራሹ በኃላ የሞተን ወራሽ ተክቶ መውረስ (ቁጥር 833) የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆም ለአቤቱታው አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ ቁጥር 844 (2) ሳይሆን 833 ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በቁጥር 833 ድንጋጌ መሰረት ከአውራሹ በኃላ የሞተ ወራሽ ተተኪ ወራሾች መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ ተሽሮ በአመልካቾቹ አቤቱታ መሰረት ሊወሰን ይገባው ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

መ/ተ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

# ውል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 95922

መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- 1.አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ - ነ/ፈጅ ብሩክ ዘረሁን - ቀረቡ

2. አቶተፈራ ታርቄ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.ሃምሳ አለቃ ለገሰ ክፍለይ } ጠበቃ አወግቸው መኮንን ቀረቡ

2. ወ/ሮ አክበረት አማረ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአንኘ ተንኘ ውልን መሰረት ያደረገን የጉዳት ካሳ ይከፈለን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ 2ኛአመልካች ላይ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ንብረትነቱ የአሁኑ 2ኛአመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 3-10457 ፣ የጎን ቁጥሩ 1320 የሆነ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የተጠሪዎች ልጅ የሆነውን አለም ለገሰ ከአዲስ አበባ ተሳፍሮ ወደ መቸሌ በመንዝ ላይ እያለ ደብረ ብርሃን ከተማ ቀበሌ 09 ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ ሲደርስ መኪናው ተገልብጦ በዚህ ምክንያት የልጃቸው ህይወት ማለፉንና በህይወትእያለም በግብርና ስራ ላይ ተሰማርቶ ይረዳቸው የነበረ መሆኑን ገልጸው በጠቅላላው ብር 484,000.00( አራት መቶ ሰማንያ አራት ሺ ብር) ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ አመልካችም ሟች በመኪናቸው ተሳፍረው ሲሄድ መሞቱን ሳይክዱ ግንኙነቱ የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ክሱ ከውል ውጪ ሊቀርብ እንደማይገባ፣ በአንኘ ግንኙነትም ክሱ መቅረብ የነበረበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁኖ እያለ ከአራት ዓመታት በላይ ቆይቶ መቅረቡ ያላግባብ መሆኑን፣ በተሳፋሪዎች ለሚደርስ ጉዳትም ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ የመድን ውል

www.abyssinialaw.com

የገባ መሆኑን ጠቅሶ ይኼው አካል ወደ ክርክሩ እንዲገባለት ጠይቆአል፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካችም ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ የተጠሪዎች ክስ ከውል ውጪ ሕግን መሰረት አድርጎ መቅረቡ ያላግባብ መሆኑን፣ ክሱም በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የተጠሪዎች የካሳ ስሌት ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግና በእርግጥም ያጡትን ጥቅም ያህል በማስረጃ አስደግፎ ያልቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የይርጋ መቃወሚያውን ያለፈው ሲሆን ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ግንኙነቱ በንግድ ሕጉ የሚገዛ መሆኑንና አደጋው የደረሰውም በንግድ ሕጉ አንቀፅ 599 አግባብ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ደምድሞ ተጠሪዎች ብር 40,000.00 የጉዳት ካሳ፣ ብር 1000.00 የሕሊና ጉዳት ካሳ፣ ለአስክሬን ማጓጓዣ የአወጡት ብር 11,000.00 በድምሩ ብር 52,000.00 (ሃምሳ ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፈላቸው፣ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ የአሁኑ 1ኛ አመልካች በሰጠው የመድን ሽፋን መጠን ብር 10,000.00 (አስር ሺህ)፣የአሁኑ 2ኛ አመልካች ደግሞ ቀሪውን ብር 42,000.00 (አርባ ሁለት ሺህ) ለተጠሪዎች እንዲተኩ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የተጠሪዎች ልጅ በ2ኛ አመልካች ንብረት በሆነው የሕዝብ ተሸከርካሪ ተሳፍረው በመሄድ ላይ በደረሰው የመገልበጥ አደጋ ሕይወቱ ያለፈ ሁኖ እያለ ክሱ ከሁለት አመት በላይ ቆይቶ ቀርቦ የይርጋው መቃወሚያ ታልፎ ለተጠሪዎች ከብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) በላይ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል መወሰኑ በን/ሕ/ቁጥር 587 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በተለይም የን/ሕ/ቁ/ጥር 603 እና 597 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ ተቃውሞ ታልፎ አመልካቾች ለክሱ ኃላፊ የመባላቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክርለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋርበማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. ጉዳዩ መዳኘት ያለበት ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙት ድንጋጌዎች ነው? ወይስ በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ነው? እና
2. ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚሉትን ሁኖ አግኝቷል፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በግብርና እርሻ ስራ ተሰማርቶ ይኖር የነበረው የተጠሪዎች ልጅ የህዝብ ማመላለሻ ሁኖ ለንግድ በሚሰራው ንብረትነቱ

የ2ኛ አመልካች ተሽከርካሪ ላይ ተሳፍሮ ከአዲስ አበባ ወደ መቐሌ ሲሄድ ተሽከርካሪው በመገልበጡ ምክንያት ለሕልፈተ ህይወት የተዳረገ መሆኑን ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎችን የካሳ ጥያቄ በመመልከት ተገቢ ነው ያሉትን ዳኝነት ሲሰጡ የአመልካቾችን ኃላፊነት የወሰኑት የንግድ ሕጉን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑም ከውሳኔው ግልባጭ ተመልክተናል። በ2ኛ አመልካችና በሟች መካከል የንግድ ህግ ቁጥር አንቀጽ 587 በሚደነግገው መሠረት የአጓዥና የመንገደኛ ግንኙነት መኖሩን አመልካቾችና ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ባቀረቡት ክርክር የሚተማመኑበት ጉዳይ ስለመሆኑ ተገንዝበናል። በአመልካቾችና በሟች መካከል ሰው ለማጓጓዝ የተደረገ ውል መኖሩን አመልካቾችና ተጠሪዎች የሚስማሙበት ከሆነ 2ኛ አመልካች ሟች ዋጋ ከፍለው ሲጓጓዙበት የነበረው የትራንስፖርት ተሽከርካሪ ባለሀብት ሲሆኑ 1ኛ አመልካች ደግሞ በመኪናው ተሳፋሪ ለሚደርሰው ጉዳት የመድን ሽፋን የሰጠ ነው። በን/ሕ/ቁጥር 588 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ አጓዡ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ስለ ምቾቱና ስለ ጉዞው በውሉ የተወሰነውን ጊዜ አክብሮ እንደተወሰነው እመድረሻ ስፍራ የማድረስ ግዴታ እንዳለበት በሐይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን። የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የአጓዡን የትራንስፖርት መኪና በኃላፊነት ተረክቦ የመኪናውን ደህንነትና ብቃት አረጋግጦ የትራፊክን ደንብና ሥርዓትን አክብሮ የማሽከርከር ኃላፊነት ያለበት አሽከርካሪ /ሹፌር/ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች መንገደኛውን መልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ምቾት በመጠበቅ በሰላም ወደሚፈለግበት ቦታ የማድረስ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስቻል ሲሆን ይህንኑ በሕግ የተጣላባቸውን ግዴታ ካልተወጡ ደግሞ መንገደኛው በጉዞው ላይ ስለሚደርስበት መዘግየትና በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሣፈርበት ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል ማጉደል ወይም የህይወት ማለፍ አጓዡ ኃላፊ እንደሚሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ስር በግልጽ ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌ አጓዡ መንገደኛው በጉዞ ጊዜ በሚሣፈርበትና በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም ህይወት ማለፍ አጓዡ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በመሠረታዊ መርህነት የሚያስቀምጥ ሲሆን ፣ አጓዡ ከኃላፊነት ነጻ የሚሆንባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የሀላፊነቱን መጠንና አጓዡ በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ በሀላፊነት ሊጠየቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል። በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ከተደነገገው ኃላፊነት አጓዡ ነጻ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የንግድ ህጉ አንቀጽ 596 ሲሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 596 አጓዡ በመንገደኛው ላይ የአካል መጐዳት ወይም የሞት አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሀይል መሆኑን ፣ ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ሰው ጥፋት መሆኑን ወይም በመንገደኛው ጥፋት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አጓዡ ከኃላፊነት ነጻ እንደሚሆን ተደንግጓል። የካሳ መጠኑን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አጉዡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት

www.abyssinialaw.com

በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የኃላፊነት መጠን በተመለከተ ደግሞ ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የኃላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከኃላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነገገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን የ2ኛ አመልካች ንብረት የሆነውን የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ያሽከረክር የነበረው የ2ኛ አመልካች ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር የሆነው ለአደጋው ምክንያት ስለመሆኑ ያለመረጋገጡንና በወንጀልም ክስ ተመስርቶበት በሂደት ላይ ያለ ወይም በሕጉ አግባብ የተቋረጠ ወይም የተቀጣ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ኃላፊነቱን ሊወጡ የሚገባቸውን ወገኖች የመኪና ባለቤት፣ ሹፌር፣ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 "አጓዡ የተፈፀመው ተግባር ወይም ጉድለት" የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 67973 በሆነው መዝገብ ላይ በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የተያዘው ጉዳዩ ሲታይም አደጋው የደረሰው የ2ኛ አመልካች መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ባጠፋው ጥፋት ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የክርክር ሂደት ያልተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የን/ሕ/ቁጥር 599 የሚሆንበት አግባብ የሌለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ 2ኛ አመልካች በተጠሪዎች ልጅ ላይ ለደረሰው የሞት ጉዳት በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አይኖርባቸውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የኃላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንደሌለባቸው የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በን/ሕ/ቁ ህግ ቁጥር 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈለ ኃላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸውም ይህ ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ አሰገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሲታይም ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣ 2091፣ 2092፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ለሚጠየቅ የአንዥ ተንዥ ግንኙነት ተፈፃሚነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌ ስር ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ክሱ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚገዙትን ድንጋጌዎችን መሰረት አድርገው ማቅረባቸውም ሆነ የስር ፍርድ ቤት ይርጋውን በተመለከተ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ መመልከቱ በ2ኛ አመልካችና በሟቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ የካሳውን መጠን በን/ሕ/ቁጥር 597 ድንጋጌ ማስላቱ ተገቢነት የነበረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>አንዥ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሟች የሞቱት ንብረትነቱ በ2ኛ አመልካች በሆነ የሰው መጓጓዣ አገልግሎት ይሰጥ በነበረ የህዝብ ማመላለሻ ላይ በደረሰው የመገልበጥ አደጋ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ሲሆን በመካካላቸው ካለው የትራንስፖርት ውል ግንኙነት አኳያ ሲታይ አመልካቾች ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆኑበት ሁኔታ በንግድ ህጉ ወይም በዚሁ ሕጉ በልዩ ሁኔታ በአንቀፅ 599 በተመለከተው አግባብ ነው፡፡ ስለሆነም በንግድ ሕጉ ስለ ይርጋም ሆነ ለካሳ የተደገጉትን ድንጋጌዎች ወይም በንግድ ህጉ አንቀፅ 599 በተመለተከው ሁኔታ ጉዳዩን ለመዳኘት ይቻል ዘንድ አስቀድሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን መለየት የግድ የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም የመጓጓዣ ውልን መሰረት አድርጎ የሚቀርበው ክስ የሚታገድበት የይርጋ ጊዜና የካሳ መጠኑ የሚሰላበት አግባብ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 599 አግባብ በልዩ ሁኔታ ጉዳዩ ሲታይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊኖረው ከሚገባው የይርጋ ድንጋጌ እና የካሳ አሰላል የተለየ መሆኑን በንግድ ሕጉ አንቀፅ 587፣ 603 እና 597 ድንጋጌዎችን በአንድ በኩል፣ የንግድ ሕጉ አንቀፅ 599 እና ከውል ውጪ ኃላፊነትነት በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143፣ 2090 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተቀመጡትን ሁኔታዎች በሌላ በኩል በመመርመር የምንረዳው ጉዳይ ነውና ስለሆነም የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ የካሳ ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩ በየትኛው የህግ ማዕቀፍ እንደሚገዛ መለየት የይርጋውንም ሆነ የካሳ ስሌቱን በአግባቡ ለመዳኘት የሚያስችል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚገዙ ድንጋጌዎችን ጠቅሰው ሲሆን የአሁኑ አመልካቾች የክሱ አመሰራረት ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት ማድረጉ ያላግባብ መሆኑን በመጥቀስ ግንኙነቱ የመጓጓዣ ውል መሆኑንና በንግድ ሕጉ ሲታይም ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ገልፀው ተከራክረው የስር ፍርድ ቤት የይርጋውን መቃወሚያ በሟች ላይ የደረሰው የሞት አደጋ በወንጀል ተጠቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ጠቅሶና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(2) ድንጋጌን ዋቢ በማድረግ ከአለፈው በኃላ የካሳውን መጠን

www.abyssinialaw.com

ሲወስን ግን አደጋው የደረሰው በጥፋት ስለመሆኑ ያለመረጋገጡንና የን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ ካሳው ሊሰላ የሚችልበት ምክንያት ያለመኖሩን ገልጾ ካሳውን በን/ሕ/ቁጥር 597 አግባብ መወሰኑን የውሳኔው ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለይርጋ ጉዳይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ መሰረት ማድረጉ በካሳው ስሌት ጊዜ ከደረሰበት ምክንያት ጋር የሚጋጭ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ጉዳዩ በን/ህ/ቁጥር 599 አግባብ በተቀመጠው ልዩ ሁኔታ አግባብ ወደ ውል ውጪ ድንጋጌዎች የሚያስኬድ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ ለይርጋ አፈጻጸም ወደ ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌ ለመሄድ የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ተጠሪዎች ጉዳቱ በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ በተቀመጠው ጥፋት የደረሰ ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ከሕግ እና ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ ነው የሚሉ ከሆነም በስርዓቱ መሰረት ያቀረቡት ይግባኝ ወይም የሰበር ክርክር ስለመኖሩ ተጠሪዎች ገልጸው ያለመከራከራቸውን ተገዝበናል፡፡ እንዲሁም የ2ኛ ተጠሪን ተሽከርካሪ ያሽከረክር የነበረው አሽከርካሪ በወንጀል ተከሶ ነበር የሚል ክርክር ተጠሪዎች ከማቅረባቸው ውጪ ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያለማቅረባቸውንና የወንጀል ክርክሩ ተጀምሮ ከነበረም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲያቀርቡ በቂ ጊዜ ተሰጥቶአቸው ማስረጃው ያለመቅረቡ የይርጋው ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143(2) ድንጋጌ አግባብ የሚታይ ነው ለማለት የሚያስችል አግባብ ያለመኖሩን የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡

እንግዲህ በ2ኛ አመልካች በተጠሪዎች ልጅ መካከል የተመሰረተው የመጓጓዣ ውል ነው ከተባለና ግንኙነቱ በንግድ ሕጉ የሚገዛ ነው ከተባለ ይርጋውን አስመልክቶም ይኼው ልዩ ሕግ በአንቀፅ 603 ስር በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት አጓዥ ተጓዥ መሰረት ተደርገው የሚቀርቡት ክሶች በንግድ ሕጉ 603 በተደነገገው አግባብ መሰረት በሁለት ዓመት ጊዜ መቅረብ እንደአለባቸውና በዚህ አግባብ ካልቀረቡ ግን የአጓዥ ተጓዥ ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ማቅረብ እንደማይቻል የድንጋጌው ይዘት ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት ልጃቸው ሰኔ 07 ቀን 2001 ዓ/ም በመኪና መገልበጥ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኂላ ግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ/ም መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ይህ ጊዜ የን/ሕ/ቁጥር 603 መሰረት ተደርጎ ሲታይ ሶስት አመት ከ11 ወራት ከ21 ቀናት በኂላ ክስ መቅረቡን የሚያስገነዝብ በመሆኑና ይርጋውን ሊያቋርጥ የሚያስችል የሕግ ምክንያትም የሌለ ሁኖ ስለአገኘነው የበታች ፍርደ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2143 ድንጋጌን መሰረት አድርገው የይርጋ ክርክሩን ማለፋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሣ ኔ

1. በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0111646 ህዳር 13 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01-14794 ታህሳስ 01 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ካሳ እንዲከፈላቸው የመሰረቱት ክስ የሚገዛው በን/ሕ/ቁጥር 587፣ በን/ሕ/ቁጥር 595 597 እና 603 ድንጋጌዎች አንፃር በመሆኑ ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.98961

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሣለኝ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ኡመር መሐመድ ⎫ ከጠበቃ ገናነው ተሾመ

2. ወ/ሮ ነፍሳ ሲራጅ ⎭ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሻ/ባሻ ከድር ሼህ አብዱላሂ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከውክልና /እንደራሴነት/ ህግ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የቀረበን ክርክር የሚመከለት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ለስር ፍ/ቤት ያቀረበው የክሱ ይዘት ባጭሩ፡- ተጠሪ በጊኒር ከተማ 02 ቀበሌ ውስጥ በስማቸው የተመዘገበ ቤት ያላቸው መሆኑን፣ ይህንኑ ቤትና ቦታ 1ኛ አመልካች በአደራ እንዲጠብቁና እንዲያስተዳድሩ የሚል በ4/9/1985 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተመዘገበ የውክልና ስልጣን ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፣ ሆኖም ግን አንደኛ አመልካች ከተሰጠው ውክልና ስልጣን ውጭ በመውጣት ባለቤታቸው ለሆኑት ለሁለተኛ አመልካች በዝቅተኛ ዋጋ በብር 2500 የሸጡ መሆኑን፣ በዚሁ መነሻነት ለ1ኛ አመልካች ተሰጥቶ የነበረው የውክልና ስልጣን በተጠሪ መሻሩን፣ ይህንኑን ተከትሎም አንደኛ አመልካች ቤቱን ለማስረከብ ፍላጎት ስላልነበረው በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ-05861 በሆነው ላይ ክስ ቀርቦ እንደነበረና ፍ/ቤቱም በበኩሉ አንደኛ አመልካች በቤቱ ላይ የፈፀመው የሽያጭ ውል የተጠሪን መብት የሚጋፋ ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187 መሠረት ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብቱን ጠብቆ ወስኖ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው ይህ በአመልካቾች መካከል የተፈፀመው የሽያጭ ውል አንደኛ

www.abyssinialaw.com

አመልካች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከራሱ ጋር እንደፈፀመ የሚቆጠር በመሆኑና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187 መሠረት የጥቅም ግጭት መፈጠሩን የሚያሳይ ስለሆነ በዚሁ የህግ ድንጋጌ መሠረት ውሉ ፈርሶ አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቡና እንዲሁም ከ5/3/1998 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ያለአግባብ ለተጠቀሙበት የቤቱ ኪራይ ገቢ በወር ብር 500 ታስቦ በድምሩ ብር 33,000 አመልካቾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ጭምር ይወሰንባቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ሲሆን አንደኛ አመልካችም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው የመከላከያ መልስ፡- ይህንኑ ቤት በተመለከተ ከዚህ በፊት ክስ ቀርቦ ውድቀ የተደረገ ስለሆነ ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ-5 መሠረት በድጋሚ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑንና ክሱም በ2 ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመቃወም የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም የውክልና ስልጣኑ ቤቱን እንዲያስተዳድር ብቻ የሚል ሳይሆን ቤቱን የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ጭምር ያካተተ ስለሆነ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በ19/5/1986 ዓ.ም የተደረገው የአንድ ክፍል አሮጌ ቤት ሽያጭ ውል ከወቅቱ የቤቱ ዋጋ ጋርም ተገናዝቦ ሲታይ ህጋዊና የተጠሪን መብት የነካ ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ አመልካችም በበኩሏ ከ1ኛ አመልካች ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መቃወሚያ አቅርበው የተከራከሩ መሆኑን ከስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም የቤቱ ሽያጭ ውል ህጋዊ በመሆኑ ሊሰረዝ የማይገባ መሆኑንና እንዲሁም ሽያጭ ውሉን ተከትሎ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ስማቸው እንዲዞር ከተደረገ በኋላ በ1987 ዓ.ም ቤቱን አፍርሰው በአዲስ መልክ ትልቅ ቤት ገንብተው እየተገለገሉበት ያለ የግል ንብረታቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ይወሰንላቸው ዘንድ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ፡- 1. ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍ/ቤቱ መ.ቁ 05861 ውሳኔ አግኝቷል? ወይስ አላገኘም? 2. አመልካችስ ቤቱን ለመሸጥና ለመለወጥ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን ነበረው? ወይስ አልነበረውም? 3. ነበረው ከተባለስ ተጠሪ ሽያጭ ውሉን መቃወም ይችላል? ወይስ አይችልም? 4. ይችላል ከተባለስ ይሄንን ጥያቄ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ይዞ 1ኛ አመልካች ከተጠሪ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ቤቱን ስለመሸጡና የውክልና ሰነዱም ይሄንን ለማድረግ ለ1ኛ አመልካች ስልጣን የሚሰጠው ስለመሆኑ በመ.ቁ.05861 ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ነጥብ ላይ በድጋሚ ውሳኔ መስጠቱ አላስፈላጊ ነው በማለት አልፏል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በክሱ እንደገለፀው 1ኛ አመልካች በእንደራሴነት ስልጣኑ ቤቱን ባለቤታቸው ለሆኑት ሁለተኛ አመልካች መሸጡን የውክልና ስልጣኑን በ1/3/1998 ዓ.ም በሚያነሳበት ጊዜ ያውቅ የነበረ መሆኑን ስለገለፀና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ያለው ጊዜ ደግሞ ሲቆጠር 5 ዓመት ከ6 ወር በላይ መሆኑን በማስፈር ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187/2/ መሠረት በ2 ዓመት ይርጋ ይታገዳል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢቀርቡም

ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ሆኖም ግን በተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪና አንደኛ አመልካች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ-05861 ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ክርክር ላይ የቆዩ መሆናቸውን ጠቅሶ እና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ-1851 መሠረት የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጥ ሆኖ ሳለ የበታች ፍ/ቤቶች ክሱ በ2 ዓመት ይርጋ ይታገዳል ሲሉ መወሰናቸው ህጋዊ አይደለም በማለት ሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ-341/1/ መሠረት መልሶ ልኮለታል፡፡ አመልካቾችም ይህንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን አቤቱታውም ተመርምሮ በሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲታይ በመታዘዙ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በይርጋ አይታገድም ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪ ክሱን በስር ፍ/ቤት ሲያቀርብ አንደኛ አመልካች ቤቱን ለማስተዳደር እንጅ ለመሸጥና ለመለወጥ የውክልና ስልጣን አልተሰጠውም በማለት ቢከራከሩም ለአንደኛ አመልካች ተሰጥቶ የነበረው የውክልና ስልጣን ቤቱን ለመሸጥና ለመለወጥ የሚያስችላቸው ስልጣንም ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ ከዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ቢሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን መደምደሚያ ሃሳብ በውሳኔው ጠቅሶ አልለወጠውም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ይህ ክርክር የቀረበበት የውክልና ስልጣን አድማሱ ቤቱንም የመሸጥና የመለወጥ ተግባርንም ያካትታል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ የተያዘበት ጉዳይ እኛም ልንቀበለው የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አመልካቾች ባልና ሚስት መሆናቸው አልተካደም፡፡ እንዲሁም 1ኛ አመልካችም የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ቤቱን በ19/5/1986 ዓ.ም በተደረገው ሽያጭ ውል ስምምነት መሠረት የሸጡት ሚስታቸው ለሆኑት ሁለተኛ አመልካች ስለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ ካለመሆኑም በላይ በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ውክልና ስልጣኑን መሰረት ተደርጐ ከተፈጸመው ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187/1/ ስር እንደተመለከተው የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ የሚያከራክር ጉዳይ ባለመሆኑ ተጠሪ የሽያጭ ውሉን በዚሁ በተጠቃሹ ድንጋጌ መሠረት ለማስፈረስ ለመጠየቅ መብት አላቸው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ቤቱ ለ2ኛ አመልካች መሸጡን ተጠሪ የውክልና ስልጣኑን በሻሩበት ጊዜ /በ1/3/1998 ዓ.ም/ ያውቅ የነበረ ስለመሆኑና ይህንኑም በክሱ አቤቱታ ጭምር እራሱ ገልጾ የነበረ

www.abyssinialaw.com

ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ የሚለው ጥያቄ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ-2187/2/ መሠረት በ 2ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ከተጠቀሰው የህጉ ድንጋጌ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ ቀርቶ ተጠሪ በቀድሞው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ.ቁ-05861 በሆነው እራሱ ክሱን ያአቀረበው በ22/9/2000 ዓ.ም ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይህም ከ1/3/1998 ዓ.ም ጀምሮ ጊዜው ሲቆጠር ከ2 ዓመት በኂላ የቀረበ ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መ.ቁ-05861 የቀረበው ጉዳይ ለክርክሩ አግባብነት ያለውንና በፍ/ብ/ህ/ቁ-2187/2/ ስር የተመለከተውን የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ስለሚያቋርጥ ክሱ በይርጋ አይታገድም የሚል የመደምደሚያ ሀሳብ ላይ ደርሶ የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ-1851 እና 2187 ድንጋጌዎች ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያገናዘበ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.158348 በ21/4/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ-348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የባሌ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ-11926 በ19/11/2004 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ-144852 በ9/4/05 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ-348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የተጠሪ ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ-2187/2/ መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል ብለናል፤ በዞኑ ከ/ፍ/ቤት መ.ቁ.05861 በተጠሪ ቀርቦ የነበረው ክስም ተጠሪ ሽያጭ ውሉ መደረጉን ካወቁበት ጊዜ አንስቶ ከ2 ዓመት ጊዜ በኂላ የቀረበ በመሆኑ የይርጋውን ጊዜ አቆጣጠር የሚያቋርጥ አይደለም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ክሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/አ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.104061

መስከረም 25ቀን 2008ዓ.ም

**ዳኞች**:-አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሣለኝ

**አመልካቾች፡** አቶ ፍቅሬ ግርማ ቀረቡ

**ተጠሪ፡** አቶ ደስታ ጫምሶ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከዋስትና ውል ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው ያአሁኑ አመልካች በኦሮሚያ ክልል አርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት የሰበር ክርክሩ ተከፋይ ያልሆነው አቶ አበበ ኤርጊቾ እና ሰበር ተጠሪ ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፦ግምቱ 20,000 ብር የሆነውን የኢጣሊያን ስሪት እህል ሚዛን 1ኛተከሳሽ በ 24/2/2001 ዓም በተደረገ ኪራይ ውል ወስዶ በኋላ ላይ እንዲመልስ ሲጠየቅ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም፣2ኛ ተከሳሽም በበኩሉ ሚዛኑን ለመመለስ ወይም መተካት የዋስትና ግዴታ ገብቷል፣ስለዚህ ተከሳሾቹ ተጠይቀው ሚዛኑን የማይመልሱ ከሆነ በገቡት ግዴታ መሠረት ግምቱን ይክፈሉኝ በሚል ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ክሱ ስነ-ስርዓቱን ጠብቆና ተሟልቶ አልቀረበም በሚል ምክንያት ተከሳሹ በወረዳ ፍ/ቤቱ ከክሱ ወጭ መደረጉን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ ግን ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ የገባው የዋስትና ግዴታ የሌለ መሆኑን፣የዋስትና ውል ነውተብሎ በቀረበው ሰነድ ላይ ያለውም ፊርማ የራሱ ያለመሆኑንና የዋስትና ውሉም ራሱ ለምን ያህል ገንዘብ ግዴታ እንደተገባ ስለማያሳይ በፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) መሠረት ውሉ ፎርማሊቲን አያሟላም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ወረዳ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና በዋስትና ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ምስክሮች ቃል ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የዋስትና ዉሉን መፈረሙ በምስክሮች ቃል መረጋገጡን መገንዘቡን ካሰፈረ በኋላ ተጠሪ በዉሉ የተጠቀሰውን ሚዛን አይነት አዲስ ለአመልካች ይተካ ሲል ወስኗል፡፡ ባአሁኑ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በዋስትና ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ፊርማው በፎረንሲክ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብ የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የዋስትና ውሉ ፎቶ ኮፒ በመሆኑ ምርመራውን በዚህ ምክንያት ማካሄድ አልተቻለም የሚል ምላሽ ከተሰጠው በኋላ ጉዳዩን ባለበት ሁኔታ መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ-348(1) መሠረት መልሶ አፅንቶታል፡፡ ተጠሪ አሁንም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርቦና ችሎቱም በበኩሉ ግራ ቀኙ ቀርበው እንዲከራከሩ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የዋስትና ውሉ ዋሱ (ተጠሪ) ለምን ያህል ገንዘብ ግዴታ እንደገባ የማይገልፅ መሆኑን ጠቅሶና እንዲህ ከሆነ ደግሞ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) ስር የተመለከተውን የህግ መስፈርት ስለማያሟላ በዋሱ ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካችም ይሄንኑ በክልሉ ስበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም ባጭሩ፣ለዋስትና ውሉ መነሻ የሆነው ግዴታ ዓይነትም የእቃ ኪራይ እንጅ ብድር ውልን የሚመለከት ካለመሆኑ በላይ ተጠሪም እራሱ በዋስትና ውሉ መሠረት የገባው ግዴታ በፍ/ብ/ህ/ቁ-2727 እና 2738 ስር እንደተመለከተው ሚዛኑን እራሱን በአይነት ለመተካት ወይም ለመመለስ ከመሆኑ አንፃር በውሉ ላይ የገንዘብ መጠን መጥቀስ የግድ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ሲሆን አቤቱታውም ተመርምሮ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት በመመራቱ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሚዛን ከአመልካች የተከራየሁ ግለሰብ (ዋና ባለእዳ) በውሉ መሠረት መልሶ ለአመልካች አለማስረከቡ ክርክር የቀረበበት ጉዳይ አይደለም፡፡ተጠሪም በበኩሉ በዋስትና ውሉ ላይ ተመሳሳዩን ሚዛን በዓይነት ለመተካት በሚል የዋስትና ግዴታ እንደገባ ተደርጎ በውሉ ላይ መስፈሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ሆኖም ግን የዋስትና ውሉ አፃፃፍ ወይም ይዘት ምንም ይሁን ምን ዋሱ ግዴታ የገባበትን የኀላፊነት መጠን ወይም ልኩ ምን ያህል እንደሆነ በዋስትና ውሉ ላይ በገንዘብ ካልተገለፀ በስተቀር ዋስትናው ፈራሽ እንደሚሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

www.abyssinialaw.com

በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ተመሳሳዩን ሚዛን በዓይነት ለመተካት በሚል የዋስትና ውሉን የፈረመ ቢሆንም የግዴታው መጠን ግን እስከ ምን ያህል እንደሆነ በገንዘብ ተገልፆ በውሉ ላይ አልተመለከተም። ይህ የዋስትና ግዴታ አድማስ ደግሞ ለምን ያህል እንደሆነ በውሉ ላይ በገንዘብ ካልተገለፀ የዋስትና ውሉ ዋጋ ስለማይኖረው ወይም ፈራሽ ስለሚሆን አመልካች የገንዘቡ መጠን መገለፅ የግድ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሠረት ስለሌለው አልተቀበልነውም።

በሌላ በኩል ለዋስትና ግዴታው መሠረት የሆነው ጉዳይ የእቃ ኪራይን የሚመለከት ግዴታ ይሁን ወይም ሌላ ዋናው ቁም ነገር በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የዋናው ግዴታ ውል (የእቃ ኪራይ ውል) እራሱ ሳይሆን የእሱ ተቀፅላ (accessory) የሆነው የዋስትና ውል ነው።አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጉዳይ የዋስትና ውሉ ከሆነ ደግሞ በተለይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የህጉ ክፍል የፍ/ብ/ህ/ቁ- 1920ና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ናቸዉ እንጂ አመልካች በሰበር አቤቱታዉ የጠቀሳቸዉ የፍ/ብ/ህ/ቁ2727 እና 2738 ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም። ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመው የዋስትና ውል ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ህ/ቁ-1922(3) ድንጋጌን መስፈርት ስለማያሟላና ፈራሽ ስለሆነ ተጠሪ ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም በማለት ከኃላፊነት ነፃ በማድረግ መወሰኑ ህጉን በትክክል መሠረት ያደረገነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ሊባል የሚቻል ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመቁ-175321 በ 23/10/2006 ዓም የሰጠዉ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ-348(1) መሠረት ፀንቷል።
2. የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል።
3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.98583

መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካቾች፡- 1ኛ/ ወ/ሮ ኤደን ሲሳይ } ጠበቃ አቶ በላይነህ ማሞ ቀረበ

2ኛ/ ወ/ሮ አስቴር ደምሴ

ተጠሪ፡- አቶ ሰይፈ ዓለሙ - የህፃን ናትናኤል ሰይፉ እና የህፃን ዮናታን ሰይፉ ሞግዚት ጠበቃ አለማየሁ አበበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ወስነናል ፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳዩ የውል ይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው ፡፡ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ፤የአሁን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ከሥር ፍ/ቤቾች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት እንደሚቻለው ከሳሽ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ የሟች ወ/ሮ ፈትለወርቅ ተረፈ በህይወት በነበሩበት ወቅት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ቀበሌ 09/14 የቤት ቁጥር 750 የሆነ የድርጅት ቤት የነበራቸው ሲሆን ይህን ቤት 1ኛ ተከሳሽ ከሟች ውክልና ተሠጥቶኛል በሚል ሟች በከፍተኛ ህመም በነበሩበት ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም ተደረገ በተባለ ውል ለ 2ኛ ተከሳሽ የሸጡ በመሆኑና ውሉንም አደረግን የሚሉት በውል አዋዋይ ፊት ሟች ከሞቱ ከዘጠኝ ቀን በኃላ በመሆኑ ፤ውክልናው በሞት ምክንያት ቀሪ ከተደረገ በኃላ የተደረገ በመሆኑና ፤ቤቱም በሚሊዮን የሚቆጠር ዋጋ የሚያወጣ ሆኖ እያለ ሞግዚት የሆንኩላቸውን ተተኪ ወራሾች ለመጉዳት በብር 250,000.00 ተሸጠ መባሉ ተገቢ ባለመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል ፡፡

www.abyssinialaw.com

ተከሳሾችም በየራሳቸው በሠጡት መልስ ሟች ቤቱን ሚያዝያ 1/2001 ዓ.ም በተደረገ የመንደር ውል የሸጡ መሆኑን፤በዚህ ውል ቤቱን ከዕዳ ነፃ ሲያደርጉ በአዋዋይ ፊት ለመፈረም በተስማሙት መሠረት ይህን ለማክበር ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም የሽያጭ ውል መደረጉን ፤በዕለቱም በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ለመፈራረም ውሉንና ምስክሮች ይዘው በአካል ቀርበው ወደ እገዳ ማጣሪያ ክፍል ተመርቶ ግብሩ ላይ እንዲታረም የተነገራቸው ታርሞ ከተጠናቀቀ በኃላ ውሉ በ 27/2/2002 ዓ.ም የተፈረመ መሆኑንና፤ ህዳር 7/2002 ዓ.ም የግዥ አገልግሎት ክፍያ የተፈፀመበት እንጂ ውሉ የተፈረመበት አለመሆኑን ፤ውሉ ከተፈፀመ በኃላ ሟች ወ/ሮ ፈትለወርቅ ተረፈ ጥቅምት 28/2002 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዮ መሆኑን ነገር ግን በ1/08/2001 ዓ.ም ከሽያጩ ገንዘብ ብር 200,000.00 መከፈሉን በመጥቀስ ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዮን በቅድሚያ የተመለከተዉ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ተመልክቶ በመጨረሻ በሰጠው ውሳኔ ሟች ለ 1ኛ ተከሳሽ ውክልና የሠጡትና በሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በ27/02/2002 ዓ.ም በወኪሉ 1ኛ ተከሳሽ እና በገዥ 2ኛ ተከሳሽ መካከል ውል ሲፈረምና ከሽያጩ የቀረው ገንዘብ ብር 5000.00 ሲከፈል በህይወት የነበሩ በመሆኑ ፤በፍ/ብ/ህ/ቁ.2232/1/ መሠረት ወካዮ ከሞተ የውክልናው ስልጣን ወዲያውኑ ቀሪ የሚሆን ቢሆንም በንዑስ ቁጥር 2 ሥር በእንዲህ አይነት ሁኔታ ተወካይ ሥራውን ቢያቋርጥ በጉዳዩ ላይ አደጋ የሚደርስበት እንደሆነና በዉክልናው ሥልጣን መሠረት ሥራውን ጀምሮ እንደሆነ የዋናው ወካይ ወራሾች ወይም ህጋዊ እንደራሲዎች አስፈላጊውን እስኪያደርጉና ራሳቸውም ሊያስቡበት እስኪችሉ ድረስ ስራውን መቀጠል አለበት በማለት የሚደነግግ በመሆኑ፤በተያዘውም ጉዳዮ 1ኛ ተከሳሽ ተወካዮ መሆናቸው ያልተካደና ውሉም ቀደም ብሎ በመንደር የተደረገውን ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ለማድረግ መሆኑን መገመት የማያዳግት በመሆኑ ፤ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2232/2/ መሠረት ተወካዮ (1ኛ ተከሳሽ )ሥራውን ጀምሮት ስለ ነበር መቀጠል እንዳለበት የተደነገገውን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከሳሽ ውክልናው ቀሪ ከሆነ በኃላ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኃላ ባሳለፈው ውሳኔ ሚያዝያ 1/2001 ዓ.ም ተደረገ ስለተባለው የገንዘብ አከፋፈል በተመለከተ የአሁን 1ኛ አመልካች የሽያጭ ገንዘቡን እኔ እራሴ ቆጥሬ ተቀብያለሁ ሲሉ 2ኛ አመልካች ደግሞ ለሟች ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገንዘቡን ቆጥሬ በእጃቸው ሰጥቻለሁ በማለት የሚቃረን መልስ ማቅረባቸው የሽያጭ ውሉ ሚያዝያ 1/2001 ዓ.ም የተጀመረ ነው በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር አሳማኝ የማያደርገዉ በመሆኑ፤ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ሟች ከመሞታቸው ከ3 ቀናት በፊት መሆኑና በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበው ደግሞ ህዳር 7/2002 ዓ.ም ሟች ከሞቱ ከዘጠኝ ቀን በኃላ

www.abyssinialaw.com

መሆኑ የታመነ ጉዳይ በመሆኑ፣የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2232(2) አግባብነት የሚኖረዉ በወኪሉ ቀድሞ የተጀመረው ሥራ ወራሾችን በሚጠቅም መልኩ እንዲቀጥል የተደረገ እንደሆነ ብቻ ሲሆን በተያዘው ጉዳዮ ግን ወኪሉ ወካያቸው ከሞቱ በኃላ በሟች ንብረት ላይ የሽያጭ ውል መፈራረማቸው ወራሾችን የሚጠቅም ሳይሆን ንብረቱን ለሌላ አሳልፎ በመስጠት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግና በእጅጉ የሚጐዳቸው በመሆኑ፣ የቤት ሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረው ሟች ከሞቱ በኃላ ህዳር 7/2002 ዓ.ም ነው እንጅ እንደ መ/ሰጭዎች /የአሁን አመልካቾች / አባባል ሟች ከመሞታቸው ከ 3 ቀን በፊት ተጀምሮ ነበር ቢባል አንኳን ሟች በጠና ታመው ኮማ ውስጥ ነበሩ በተባለበት ሰዓት ላይ በመሆኑ በጅምር የቤት ሽያጭ ውሉ ላይ የሟች ፈቃድ ነበረበት ለማለት አያስደፍርም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር በአመልካቾች መካከል ጠቅምት 25/2002 ዓ.ም የተጀመረውና ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ.ም የተመዘገበው የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት ወስኗል ፡፡

የአሁን አመልካቾች ይህን ውሣኔ በመቃወም ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ውሳኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙ ተሠርዟል ፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው በዚህ ነው አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ መልስ እንዲሠጡበት ጥሪ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሑፍ አቅርበዋል ፡፡ ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታውን ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አመልካቾች የሽያጭ ውሉ የተደረገው ሟች በህይወት ሳሉ በመሆኑ ወራሾች ሟች በህይወት ሳሉ የፈፀሟቸውን ህጋዊ ተግባራት መቃወም መብት ስለሌላቸው ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት እንዳይኖረው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ውክልናው በወካዮ ሞት ምክንያት ቀሪ ከሆነ በኃላ የተደረገ ውል በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባ ተከራክረዋል ፡፡ ስለሆነም የሽያጭ ውሉ ተደረገ የሚባለው መቼ ነው የሚለውን አግባብ ካለው ህግ ጋር በማያያዝ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

የሽያጭ ውሉ የሚመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረትን በመሆኑ ውሉ በጽሑፍ ከመደረጉ በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723/1/ ሥር ተደንግጓል ፡፡ የቤት ሽያጭ ውሉ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው በዚህ የህግ ስርዓት /ፎርም/ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ የሚያስፈልገው የተዋዋዮችን ማንነት፣ያላቸውን ችሎታና መብት እንዲሁም ነፃ ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ውሉ የተደረገበትን ቀንም ለማረጋገጥ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በተያዘው ጉዳይ እንደ አመልካቾች ክርክር ቤቱን የተመለከተ ዕዳና እገዳ ለማጣራትና ክፍያ ለማስፈፀም የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተወሰኑ ቀናት መውሰዱ የተመለከተ ቢሆንም በውሉ ላይ ማህተሙ የተደረገውና የፕሮቶኮል ቁጥር ተሠጥቶት የተረጋገጠው ህዳር 7/2002 ዓ.ም መሆኑ እና በዚህ ቀን ውክልና ስልጣን ሰጭ በህይወት እንዳልነበሩ አላከራከረም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2015/ሀ/ መሠረት ሠነዱ የተፃፈበት እርግጠኛ ቀን ነው የሚባለው ሠነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው እንደ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤትን በመሠለ የመንግስት መ/ቤት ሲሆን የፃፈበት /የተቀበለበት/ ቀን መሆኑም ተደንግጓል፡፡ ፍሬ ነገሩን ለማጣራት በህጉ ሥልጣን የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች የአመልካቾችን ክርክር ተቀብለው የሽያጭ ረቂቅ ሰነዱን ጽ/ቤቱ የተቀበለበትን ቀን እስካላረጋገጡ ድረስ በሰነዱ ላይ የተፃፈበት ቀን ተደርጐ የሚወሰደው በባለሥልጣኑ የተጻፈው ቀን ነው፡፡

ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገው ህዳር 7/2002 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ጊዜ በሿሚው ሞት ምክንያት ለሻጭ /1ኛ አመልካች/ የተሰጠው ውክልና ቀሪ በሆነበትና ንብረቱን በሽያጭ ማስተላለፍ የሚያስችል ሥልጣን በሌለበት የተደረገ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በመወሠኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበትን ነጥብ በሥር ፍ/ቤቶች ያልተረጋገጠን ፍሬ ነገር የያዘና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2232/2/ መሠረት ያደረገ በመሆኑ መመርመር አላስፈለገንም ፡፡ በመሆኑም ተከታዮ ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.131733 ታህሳስ 10/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.96979 የካቲት 12/2006 ዓ.ም ያሳለፈው ተእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ፡፡
3. የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 99667

መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሊሲ ደሳለኝ

**አመልካች**፡- ቻኩ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -- የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- ናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር -ጠበቃ ነስቡ ሜኮ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሽያጭ ውል አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ በ26/07/2004 ዓ.ም. አዘጋጅቶ ያቀረበው ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከሳሽ እና ተከሳሽ በ06/04/1998 ዓ.ም. ባደረጉት የሽያጭ ውል ከሳሽ ብዛታቸው 13 የሆነ ሬኖ ክራክስ ተሽርካሪዎችን/ሻሲዎችን/ የተጨማሪ እሴት እና የስም ማዛወሪያ ወጪዎችን ጨምሮ እያንዳንዳቸውን በብር 1,051,346 በጠቅላላው ደግሞ በብር 13,667,498 ለመሸጥ በመስማማት ተሽከርካሪዎቹን ከ29/02/2000 ዓ.ም. በፊት ለተከሳሽ ያስረከበ መሆኑን፣ተከሳሽ ከሽያጩ ገንዘብ ውስጥ ብር 9,434,248.80 በባንክ በኩል የከፈለ መሆኑን፣ከቀሪው ብር 4,233,249.80 ውስጥ ከሳሽ ብር 2,183,125 በውሉ አንቀጽ 4.2 መሰረት መክፈል የነበረበት ተሽርካሪዎቹን ከመረከቡ በፊት ቢሆንም ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 545,781.27 ያልከፈለ መሆኑን፣የመጨረሻውን ክፍያ ብር 2,050,124.70 በውሉ አንቀጽ 4.3 መሰረት ተከሳሽ ተሽርካሪዎቹን ከተረከበ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜ ካለፈ በኃላ ባለው 12 ወር ጊዜ ውስጥ ከ9.5% ወለድ ጋር ከፍሎ ለማጠናቀቅ የተስማማ ቢሆንም ክፍያውን ያልፈጸመ መሆኑን፣የሚፈለግበትን ገንዘብ እንዲከፍል ከሳሽ በ23/07/2003 ዓ.ም. ለተከሳሽ ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ የሚፈለግበትን ገንዘብ ብር 2,595,905.97 መክፈል ከነበረበት

www.abyssinialaw.com

ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በውሉ አንቀጽ 5 መሰረት በዚሁ ገንዘብ ላይ ከሚታሰበው 9.5% ወለድ ጋር እንዲከፍል ከሳሽ በክሱ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ በ18/10/2004 ዓ.ም. በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጠው መልስ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1803 መሰረት የገንዘብ ዕዳ ያለበት ሰው ወለድ ለመክፈል የሚገደደው ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ከሳሽ ማስጠንቀቂያ ከሰጠበት ከ10/08/2003 ዓ.ም. በፊት ወለዱ እንዲታሰብ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ይህ የሚታለፍ ከሆነ ከሳሽ ተሽከርካሪዎቹን አስረክቤለሁ ካለበት ከ29/02/2000 ዓ.ም. ጀምሮ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወለዱ መታሰብ መጀመር የሚገባው ተከሳሽ ገንዘቡን አልከፈለም ሊባል ከሚችልበት ከ29/03/2001 ዓ.ም. ጀምሮ በመሆኑ ከሳሽ ከዚህ ቀን በፊት ወለዱ መታሰብ እንዲጀምር ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1757 ድንጋጌን እና በመዝገብ ቁጥር 38568 የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሚቃረን ሁኔታ የበኩሉን ግዴታ ሳይወጣ ክስ ማቅረቡ ተገቢነት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ተከሳሽ የመቻቻል ጥያቄ ያቀረበ በመሆኑ ገንዘቡን በማቻቻል ከሳሽ ተራፊውን ገንዘብ ለተከሳሽ እንዲከፍል እንዲወሰን በመጠየቅ ተከራክሮአል፡፡

ተከሳሽ በ18/10/2004 ዓ.ም. ባቀረበው የመቻቻል ጥያቄ ከሳሽ ለተከሳሽ በሰጠው ፕሮፎርማ ተሽከርካሪዎቹን ለማስረከብ የተስማማው በስምንት ወራት ውስጥ ሆኖ እያለ ያስረከበው ግን ለ15 ወራት አዘግይቶ በመሆኑ እና ለመኪናው የአካል ግንባታ የሚያስፈልገው ሶስት ወር ሲቀነስ ተከሳሽ በ12 ወራት ከተሽከርካሪዎቹ ስምሪት ማግኘት ይችል የነበረውን ገንዘብ ብር 6,240,000 ያጣ በመሆኑ ከዚሁ ገንዘብ እና በዚሁ ገንዘብ ከሚታሰበው ወለድ ላይ ከሳሽ የሚፈልገው ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጎ ቀሪውን ገንዘብ ከሳሽ ከነወለዱ ለተከሳሽ እንዲከፍል እንዲወሰንለት የጠየቀ ሲሆን ከከሳሽ በመቻቻል ጥያቄው ላይ በ12/11/2004 ዓ.ም. በሰጠው መልስ በውሉ አንቀጽ 4.2 መሰረት ተከሳሽ ከርክከቡ በፊት መክፈል ከሚገባው ገንዘብ ብር 2,183,125 ውስጥ ብር 545,781.27 ያልከፈለ እና የውል ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ ምክንያት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1757፣2278 (1) እና በመዝገብ ቁጥር 39568 በተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የበኩሉን የውል ግዴታ ሳይወጣ የኪሳራ ጥያቄ ሊያነሳ የማይችል መሆኑን፣ተከሳሽ የርክክቡን የጊዜ ስምምነት ያስረዳልኛል በማለት በማስረጃነት ያቀረበው ፕሮፎርማ የተሰጠው ለተከሳሽ ሳይሆን ለ3ኛ ወገን በመሆኑ እና ለተከሳሽ ነው ቢባል እንኳ የውሉ አካል ያልተደረገ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ውሉ የተደረገው በተሽከርካሪዎቹ ሞዴል እና የመጫን አቅም እንጂ በሻንሲ ርዝመት ላይ አለመሆኑን፣ይሁን እንጂ ተከሳሽ እና ሌሎች ገዥዎች በጠየቁት መሰረት ከሳሽ የውል ግዴታ ባይኖርበትም ለመልካም ስሙ በማሰብ እና በቅን ልቦና

www.abyssinialaw.com

በርካታ ወጪ በማውጣት እና አስፈላጊ ዕቃዎችን የተሽከርካሪዎቹ የስሪት አገር ከሆነው ከፈረንሳይ አገር አስመጥቶ በመስፍን ኢንጂነሪንግ አማካይነት የማስተካከያ ስራ እንዲከናወን በማድረግ ርክክቡን የፈጸመ በመሆኑ ተከሳሽ በአስረጂነት የጠቀሰው እና የገዙትን ዕቃ ከነጉድለቱ የተረከቡትን ገዥዎች የሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2299 (2) ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ ተሽከርካሪዎቹን ማስረከብ የነበረበት በዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ ነው ቢባል እንኳ ተከሳሽ ተገቢነት የሌለውን የካሳ ጥያቄ በማንሳት ማስተካከያ የሚደረግባቸው ከሆነ የሚረከባቸው መሆኑን ወይም አለመሆኑን በወቅቱ ባለመግለጹ እና በኃላ ላይ ግን በከሳሽ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት የሚረከባቸው መሆኑን የገለጸ ቢሆንም ማስተካከያ ተደርጎባቸው እንዲረከብ በተገለጸለት ጊዜም ባለመረከቡ በአጠቃላይ ርክክቡ ሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀን የዘገየው በተከሳሹ ጥፋት መሆኑን፣ተቋረጠብኝ የሚለው ጥቅምም ተከሳሽ የገለጸውን ያህል አለመሆኑን በመግለጽ የመቻቻል ጥያቄው ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሮአል፡፡

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን በ09/04/2005 ዓ.ም. በብይን በማለፍ በ22/06/2005 ዓ.ም. ክሱን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ከሳሽ ክስ ባቀረበበት የገንዘብ መጠን ላይ ተከሳሽ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር ባለመኖሩ እንደታመነ የሚቆጠር መሆኑን፣ተከሳሽ ወለዱ መቆጠር መጀመር ያለበት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ወይም ከርክክቡ ቀን ጀምሮ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜን ሳይጨምር ገንዘቡ ተከፍሎ መጠናቀቅ ከሚገባው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ አለመሆኑ በውሉ አንቀጽ 5.2 የተመለከተ በመሆኑ እና ተከሳሽ የጠቀሰው የፍተሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1803 ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ወለዱ መታሰብ የሚገባው ከርክክቡ ቀን ጀምሮ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ መሆኑን፣የመቻቻል ጥያቄውን በተመለከተ ፕሮፎርማው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1685 መሰረት የውሉ አካል ነው በማለት ተከሳሽ የተከራከረ ቢሆንም የተጠቀሰው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው አስቀድሞ የውል ግንኙነት ባላቸው ተዋዋዮች መካከል በመሆኑ ምክንያት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን፣በቁጥር 1687 ድንጋጌ መሰረት ፕሮፎርማ የሀሳብ መግለጫ እንጂ ውል ባለመሆኑ የውሉ አካል አለመሆኑን፣በመሆኑም በውሉ መሰረት የርክክቡ አፈጻጸም መሰረት ያደረገው ጊዜን ሳይሆን የክፍያ ሁኔታን መሆኑን፣ከሳሽ ተሽከርካሪዎቹን ማስረከብ ያለበትን ጊዜ ውሉ የማይገልጽ በመሆኑ ምክንያት ሻጭ ማስረከብ የሚገባው በቁጥር 2276 እና 1756 (3) መሰረት ገዥው ሲጠይቀው መሆኑን፣ነገር ግን ተከሳሽ ከርክክቡ በፊት መክፈል ከነበረበት ገንዘብ ውስጥ ብር 545,781.27 ያልከፈለ በመሆኑ እና በባንኩ በኩል የተከፈለው ክፍያም የተከፈለው ከርክክቡ በኃላ ዘግይቶ መሆኑን፣ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1757፣2278 (1) እና በመዝገብ ቁጥር 39568 በተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ተከሳሽ የበኩሉን የውል ግዴታ ሳይወጣ ርክክብ

www.abyssinialaw.com

እንዲፈጸምለት ከሳሽን የመጠየቅ መብት የማይኖረው በመሆኑ ርክክቡ የዘገየው በከሳሽ ምክንያት ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን፣ተከሳሽ በአስረጂነት የጠቀሰው ቁጥር 2299 (2) ደንጋጌ ተፈጸሚነት የሚኖረው የዕቃው ርክክብ የተፈጸመው ጉድለት እንዳለበት ሳይታወቅ በሆነ ጊዜ እንጂ ዕቃው አለበት የተባለው ጉደለት እየታወቀ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎበት ርክክብ በተፈጸመበት ጊዜ ጭምር አለመሆኑን፣ተከሳሽ እንደሚለው ሻሲዎቹ ችግር አለባቸው ቢባል እንኳ ተከሳሽ ውሉን ማፍረስ ወይም የበኩሉን ግዴታ በመፈጸም ርክክብ በመጠየቅ ከተረከበ በኃላ ለደረሰበት ጉዳት ካሳ መጠየቅ የሚችል ሆኖ ሳለ ግዴታውን ሳይወጣ ርክክቡ በመዘግየቱ ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት ከሳሽ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ጥያቄ የውልም ሆነ የሕግ አግባብ የሌለው መሆኑን ገልጾ የመቻቻል ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ የሚፈለግበትን ቀሪ ክፍያ ብር 2,595,905.97 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አምስት ከዘጠና ሰባት) ከ26/04/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9.5% ወለድ ለከሳሽ እንዲከፍል የወጪን ኪሳራ መብት በመጠበቅ ጭምር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ወለዱ መታሰብ የሚጀምርበትን ጊዜ በተመለከተ ብቻ ውሳኔውን በማሻሻል ወለዱ መታሰብ የሚገባው ከሳሽ በክሱ ከጠየቀበት ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው የመቻቻል ጥያቄ ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2299 ድንጋጌ አንጻር መታለፉ አላግባብ ነው የሚለውን እና ርክክብ የተፈጸመው በ29/02/2000 ዓ.ም. በመሆኑ ክፍያው መጠናቀቅ ያለበት ከ29/03/2000 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 29/03/2001 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑ በውሉ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ገንዘቡን ከፍሎ አላጠናቀቀም ተብሎ በዕዳው ላይ ወለድ መታሰብ መጀመር የሚገባው ክፍያው ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን ማለትም ከ29/03/2001 ዓ.ም. ጀምሮ እንጂ መከፈል ከሚጀምርበት ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ መሆን የለበትም የሚለውን የአመልካች የአቤቱታ ነጥቦች ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብም በ09/03/2007 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ቀርቦ ተያይዞአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዙት ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህም መሰረት ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2299 ድንጋጌ አንጻር የአመልካች የመቻቻል ጥያቄ የታለፈው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? በሚል የተያዘውን የክርክር ነጥብ በተመለከለተ አመልካች በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመቻቻል ጥያቄ ያቀረበው በፍትበሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1685 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት ፕሮፎርማው የውሉ አካል መሆኑን በመጥቀስ እና በፕሮፎርማው ላይ የተመለከተውን የርክክብ ጊዜ መሰረት በማድረግ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በፕሮፎርማው ላይ የርክክብ ጊዜ የተመለከተ መሆኑን ሳይክድ ነገር ግን ፕሮፎርማው የውሉ አካል ባለመሆኑ የርክክብ ጊዜውን ለመወሰን መሰረት ሊሆን አይችልም በማለት መከራከሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበውን የክርክር ነጥብ ሳይቀበል የቀረው የፍትበሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1685 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ተዋዋዮቹ አስቀድሞ የተቋቋመ የውል ግንኙነት ሲኖራቸው በመሆኑ እና አስቀድሞ የውል ግንኙነት ያላቸው ስለመሆኑ ደግሞ አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡በመሰረቱ የግራ ቀኙ የውል ግንኙነት የተመሰረተው ፕሮፎርማውን ብቻ በቂ አድርጎ በመቀበል ሳይሆን ፕሮፎርማው ከተሰጠ በኃላ ስለ ሽያጩ ዝርዝር አፈጻጸም ራሱን ችሎ በጽሁፍ በተደረገ የሽያጭ ውል ላይ ነው፡፡በፕሮፎርማው ላይ የተጠቀሱት የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሽያጭ ዋጋ፣የክፍያ ሁኔታ እና የተሽከርካሪው ሞዴል በቀጣይ በጽሁፍ በተደረገው ውል ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የሽያጭ ዋጋ እና የክፍያ ሁኔታ በሽያጭ ውሉ የተካተተው በፕሮፎርማው ከተገለጸው በተለየ መጠን እና ሁኔታ ነው፡፡ በፕሮፎርማው ላይ የተመለከተውን የርክክብ ጊዜ ግን ግራ ቀኙ የውሉ አካል አላደረጉትም፡፡በውሉ ውስጥ የተመለከቱት ዝርዝር የውል አፈጻጸም ሁኔታዎችም በፕሮፎርማው አልተጠቀሱም፡፡ፕሮፎርማ በባህርይው የዚህ ዓይነት ዝርዝር የውል አፈጻጸም ሁኔታዎችን እንዲያካትትም አይጠበቅም፡፡የተዋዋዮች የውል ግንኙነት መሰረት ያደረገው ፕሮፎርማን ሳይሆን ፕሮፎርማውን ተከትሎ በጽሁፍ የተደረገን ውል በሆነ ጊዜ ደግሞ በፕሮፎርማው ላይ ተጠቅሶ ነገር ግን ተዋዋዮቹ የውላቸው አካል አድርገው ያልተስማሙበት ጉዳይ በፕሮፎርማው ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ ብቻ እንደ ውሉ አካል ተቆጥሮ በተዋዋዮቹ ወይም ከተዋዋዮቹ በአንዱ ላይ አስገዳጅነት እንዳለው አድርጎ መውሰዱ የሕግ ጥበቃ ካለው ፈቅዶ የመዋዋል ነጻነት እና መብት አንጻር ሕጋዊ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው አይደለም፡፡ በመሆኑም በፕሮፎርማው ላይ የተመለከተውን የርክክብ ጊዜ በአስረጂነት ጠቅሶ ተጠሪው ርክክቡን ለ12 ወራት ያዘገየው በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከተሽከርካሪዎቹ ስምሪት ማግኘት እችል የነበረውን ገቢ ተጠሪው ሊተካልኝ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍበትን ሕግዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡አመልካች ከርክክቡ በፊት ማጠናቀቅ ከነበረበት ክፍያ ውስጥ የተወሰነውን ያህል እንዳልከፈለ ያልተካደ ከመሆኑም በላይ ሻሲዎቹ ጉድለት ያሉባቸው ናቸው በሚል መነሻ የዋጋ ቅናሽ ካልተደረገለት በስተቀር ለመረከብ ፈቃደኛ አለመሆኑን ለተጠሪው አስታውቆ የነበረ

www.abyssinialaw.com

መሆኑን፣ተጠሪውም ለዚሁ ማስታወቂያ በሰጠው ምላሽ በውሉ ምክንያት የተቀበለውን ቅድመ ክፍያ ከሕጋዊ ወለድ ጋር መልሶ ውሉን ለማስቀረት ፈቃደኛ መሆኑን ለአመልካች የገለጸ መሆኑን እና አመልካች ሀሳቡን በመቀየር ተሽከርካሪዎቹን እንደሚረከብ ሀሳቡን የገለጸው ከዚህ በኃላ መሆኑን ቀርቦ ከተያዘው የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ተገነዝበናል፡፡ይህም ተጠሪው ርክክቡን አዘግይቶአል በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለውሉ አፈጻጸም መዘግየት አመልካቹ ጭምር አስተዋጽኦ እንደነበረው መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ከቁጥር 2287 እስከ 2300 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገለጸው በዕቃው ላይ ተገኘ የተባለው ጉድለት መኖሩ በገዥው የታወቀው ከርክክብ በኃላ በሆነ ጊዜ እንጂ ጉድለቱ ከርክክቡ በፊት ታውቆ በሻጩ እንዲስተካከል ከተደረገ በኃላ ርክክብ በሚደረግበት ጊዜ ጭምር እንዳልሆነ ከድንጋጌዎቹ አነጋገር እና ይዘት በግልጽ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ቁጥር 2299 ድንጋጌን ጠቅሶ አመልካች ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉም ቢሆን የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ለተጠሪው በተወሰነው ገንዘብ ላይ ወለድ መታሰብ የሚጀምርበትን ቀን በተመለከተ ርክክብ መፈጸሙን ተከትሎ የአንድ ወር የችሮታ ጊዜ ካበቃ በኃላ አመልካች ከራሱ የሚከፈለውን የመጨረሻ ክፍያ ብር 2,050,124.70 በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ እንዲያጠናቅቅ ግራ ቀኙ የተስማሙት ዋናውን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ከ9.5% ወለድ ጋር ስለመሆኑ በውላቸው አንቀጽ 4.3 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በዚህ የውል ቃል አነጋገር ትርጉም ረገድ ወይም በውል ቃሉ ሕጋዊነት ረገድ አመልካች ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ አመልካች እንደሚከራከረው ወለዱ የ12 ወራት ጊዜ ካበቃ በኃላ መታሰብ መጀመር ይችል የነበረው በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ ግራ ቀኙ የተስማሙት ወለድ ሳይታሰብበት ዋናው ገንዘብ ብር 2,050,124.70 ብቻ ቢሆን ኖሮ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግን ገንዘቡ በ12 ወራት ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ ግራ ቀኙ የተስማሙት ከነወለዱ ነው፡፡ይህም በገንዘቡ ላይ ወለዱ መታሰብ የሚጀምረው የአንድ ወር የእፎይታ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ገንዘቡን በየወሩ እየከፈለ በ12 ወራት ቢያጠናቅቅም ሆነ በ12ኛው ወር መጨረሻ ላይ ገንዘቡን አጠቃሎ በአንድ ጊዜ ቢከፍል በዋናው ገንዘብ ብር 2,050,124.70 ላይ በግራ ቀኙ ስምምነት መሰረት 9.5% ወለድ የእፎይታ ጊዜው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ መታሰቡ የሚቀጥል በመሆኑ ገንዘቡ በየወሩ መከፈሉ ወይም በዓመቱ መጨረሻ በአንድ ጊዜ ተጠቃሎ መከፈሉ በአመልካቹ የግዴታ አፈጻጸም ረገድ የሚያስከትለው ልዩነት የለም፡፡ ውሳኔ ካረፈበት ገንዘብ ውስጥ ብር 545,781.27 መከፈል የነበረበት ከርክክቡ በፊት በመሆኑ በዚህኛው ገንዘብ ላይ ወለዱ ከ20/05/2000 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲታሰብ መደረጉ አመልካችን ተጎጂ ሳይሆን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117102 በ11/10/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 92783 በ30/05/2006 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኝ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.97797

መስከረም 28/2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስለሴ

ብርሃኑ አመነው

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች፡-** ናሽናል ስሚንቶ አ/ማህበር አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ ብርሃኑ ግደይ ጠበቃ አቶ በላቸው ዘመድኩን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሽያጭ ውል አፈፃፀም የተመለከተ ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ከአመልካች ጋር መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ስምንት ሺህ ኩንታል (8000) ስሚንቶ የአንዱ ኩንታል ብር 255.41 ሂሣብ ቫት እና ታርንኦቨር ታክስ ጨምሮ ነው 2,360,000 (ሁለት ሚሊዮን ሦስት መቶ ስልሣ ሺህ) መክፈሉን እና አመልካች (ሻጭ) 7272 ኩንታል ሲምንቶ ካሰረከበ በኃላ 723 ኩንታል ስሚንቶ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይህንኑ ቀሪ ስሚንቶ ተገዶ እንዲያስረክብ አለያም ዋጋውን ብር 214. 760 እንዲከፍል እንዲወሰን ጠይቋል በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር የዋጋ ለውጥ ሊደረግ እንደሚቻል አስቀድሞ መስማማታቸው በዚሁም መሠረት በየጊዜው የዋጋ ለውጥ ሲደረግ እንደነበርና ተጠሪም ይህንኑ አውቆ ሲረከብ እንደነበረ ገልጾ አጠቃላይ እስከ አሁን የተረከበው በየጊዜው ከነበረው ዋጋ ለውጥ አንፃር ተሰልቶ ቀሪ ብር 120 (አንድ መቶ ሃያ ብር) ብቻ መሆኑን ጠቅሶ ክሱ ውድቅ እንድደረግ ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን ያከራከረው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የስሚንቶ ዋጋ ለውጥ ወይም ጭማሪ መደረጉን የተጠሪ (የከሳሽ) ወኪል ያውቃል እንዲሁም ለተጠሪም አሳውቋል ዋጋ ጭማሪ የተደረገውም በስምምነታቸው መሠረት

www.abyssinialaw.com

ነው በማለት ተጠሪ የተረከበው ሲምንቶ ሲሳላ የተከፈው ዋጋ ጋር ተቻችሏል ቀሪ ብር 120 (አንድ መቶ ሃያ ብቻ) ነው ሲል ክሱ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል የእጅ በእጅ የሽያጭ ውል ነው በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕጉን አንቀጽ 2278(1) በመጥቀስ የዋጋ ጭማሪ የማድረግ መብት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ቀሪውን ስሚንቶ ያስረክብ ወይም ዋጋውን ይመልስ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አለገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ውል ከተደረገበት ንብረት መጠን አኳያ የሽያጭ ውሉ የእጅ በእጅ የሽያጭ ውል ነው ማለት ይቻላል ወይስ አይችልም? የዋጋ ጭማሪ አስመልክቶ ተጠሪ ስምምነት አልሰጠም የሚልውን አግባብነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የለውም በአግባቡ ነው በማለት ተከረክሯል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከህጉ ጋር አገናዝበናል፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተነሳው ክርክር መሠረቱ መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ/ም የተደረገ ውል ነው፡፡ በዚህ የሽያጭ ውል ላይ የ8000 ኩንታል ስሚንቶ ዋጋ ተጠሪ ብር 2,360,000 መክፈሉም ተረጋግጧል፡፡ የስሚንቶ ርክክብ አፈፃፀም በተለያየ መጠን በተለያዩ ጊዜያት የተፈፀመ ሲሆን በጥቅሉ ከ6 ወራት ያላነሰ ጊዜ ወስዷል፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገ ውል ክፍያ የተፈፀመበት ደርሰኝ (ሰነድ) የእጅ በእጅ ሽያጭ የሚል ሲሆን በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 2278(1) በሚደነግገው አግባብ ይህ ውል የእጅ በእጅ ሽያጭ ውል ይሰኛል ወይ የሚለው ነጥብ ምለሽ የሚያሸው ሆኖ አግኝተናል፡፡ ምክንያቱም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው ይህንኑ ድንጋጌ በመሆኑ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ አንቀጽ 2278(1) በውሉ የተነገረ ተቃራኒ ነገር ከሌላ በቀር የተሸጠውን ማስረከብ ከዋጋው መከፈል ጋር በአንድ ጊዜ መሆን አለበት በማለት ይገልፃል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ መረዳት የሚቻለው የዋጋ ክፍያ እና የተሸጠው ነገር ርክክብ በአንድ ጊዜ የተፈፀመ እንደሆነ በእርግጥም የእጅ በእጅ ሽያጭ ተደርጓል ለማለት የሚቻል መሆኑን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የ8000 ኩንታል ሲሚንቶ ዋጋ ውሉ ሲፈፀም የከፈለ ቢሆንም እቃውን የተረከበው ግን በተለያየ መጠን በተለየየ ጊዜና ዋጋ ልክ ስለመሆኑ በስር ፍርድ

www.abyssinialaw.com

ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ እንደ ሕጉ ህሳቤ የእጅ በእጅ ሽያጭ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡

ከዚህም ባሻገር ተጠሪ ሲሚንቶ የተረከበው ውል ከተደረገ በኃላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ በተለየየ ጊዜና መጠን ከመሆኑም በተጨማሪ የዋጋ ለውጥ ሊደረግ እንደሚችል አመልከች አስቀድሞ በሰጠው ፕሮፎርማ ላይ ከማስታወቁም አልፎ ስሚንቶ ርክክብ ሲደረግ በየጊዜው የነበረውን የዋጋ ለውጥ ተጠሪ ለወከለው ተረካቢ ማስታወቁን በዚሁ አግባብም የመረካከቢያ ሰነድ ላይ ይፈርም እንደነበር በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ማስረዳቱን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተው ሽያጩ የእጅ በጅ ሽያጭ ነው በሚል ምክንያት ብቻ አልፎታል፡፡

ስለሆነም በአመልካች እና በተጠሪ መከከል የተደረገው የስሚንቶ ሽያጭ ውል 8000 (ስምንት ሺህ) ኩንታል ስሚንቶ በአንድ ጊዜ ተጠሪ የተረከበው ካለመሆኑም በላይ አመልካች የዋጋ ጭማሪ ሊደረግ እንደሚችል አስቀድሞ አሰውቆ በዚሁ አግባብ መዋዋላቸው አልፎም አመልካች የዋጋ ጭማሪ ስለማድረጉ በመረካከቢያ ሰነድ እያረገገጠ ተጠሪም ይህንን ሳይቃወም ተረክቦ እያለ አሁን የዋጋ ጭማሪ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚልውን ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ የሕጉን ይዘት የግራ ቀኙን ውል እና በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህታት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128323 ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 94351 ታህሳስ 30 ቀን 2006 ዓ/ም በማፅናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል
2. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03910 በ05/03/05 የሰጠው ፍርድ ፀንቷል
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 103910

ቀን 28/01/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ሀብታሙ ተመስገን - ጠበቃ አቶ ሙሉ ገ/ስላሴ

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ለስልጠና የወጣ ወጪ በውሉ መሰረት ይመለሰልኝ በማለት አመልካች በተጠሪ ላይ ላቀረበው ክስ የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በግራ ቀኙ መካከል በቅድሚያ ህዳር 9/2002 ዓ/ም በተደረገ ውል በአመልካች የስልጠና ት/ቤት ውስጥ የሚሰጠውን የቢ 737 አውሮፕላን አካላት ስልጠና ተጠሪ በመውሰድ ለ24 ወራት ለማገልገል ይህን ግዴታውን ባይወጣ ግን የስልጠናውን ወጪ ብር 50,000.00 ለአመልካች ለመክፈል ተስማምቶ ለ 9 ወራት ቀሪ አገልግሎት ሳይሰጥ ስላቋረጠ ብር 16,664.00 እንዲመልስ ፣ በሌላም በኩል ሀምሌ 24 ቀን 2002 ዓ/ም በተደረገ ውል ተጠሪ በአሜሪካን ሀገር ቢሲያትል በሚገኘው የቦይንግ ስልጠና ማዕከል የሚሰጠውን የቢ 777 አውሮፕላን አካላት ስርዓተ ትምህርት ለመውሰድ የሚያስፈልገውን ወጪ ብር 389,059.23 አመልካች ለመሸፈን ተጠሪ ደግሞ ስልጠናውን ወስዶ ለ36 ወራት ለማገልገል ይህን ግዴታውን ባይወጣ ግን የስልጠናውን ወጪ ለመክፈል የተሰማማ ቢሆንም ስራውን ጥሎ ስልጠፋ የሁለተኛውን ውል የስልጠና ወጪ ብር 389,059.23 በአጠቃላይ ብር 407,806.23 ከነወለዱ እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ክሱ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ የሰጡትን መልስ ፤ ውሎቹ የተደረጉበትን ጊዜና የውሎችን ይዘት በመመርመር ተጠሪ በቀደመው ውል መሰረት ግዴታውን በመፈጸም ላይ እያለ ለ2ኛው ስልጠና የተላከ በመሆኑ ፤ ሀምሌ 24 ቀን 2002 ዓ/ም የተፈረመው ውል አንቀጽ 7 ደግሞ ሰልጣኙ የቀድሞ ግዴታውን በመፈጸም ላይ እያለ ለሌላ ስልጠና ቢጠራ (ቢመደብ) ሰልጣኙ ለዚሁ ስልጠና አዲስ ውል እንደሚፈርምና የአገልግሎት ጊዜውም በዚሁ ጊዜ የሁለቱንም ስምምነት ለመሸፈን እንደሚጠቃለል የሚደነግግ በመሆኑ ፤ ይህም በቀደመው ግዴታ መሰረት ሳይፈጽም የቀረውን ጊዜ ቀሪ የሚያደርገው በመሆኑ ከቀደመው ውል ሳይፈጸም ቀርቷል ተብሎ የተጠየቀውን የ9 ወራት የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ፤ በ2ኛው ዙር በተደረገው ስምምነት መሰረት ስልጠናውን ወስዶ በውሉ ለተመለከተው ጊዜ ያላገለገለ በመሆኑ ለስልጠና የወጣውን ወጪ ብር 389,059.23 ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች የሁለቱም ውሎች ግዴታዎች በ2ኛ ውል እንደተጠቃለለ ተደርጎ ውሉ መተርጎሙን በመቃወም ይግባኝ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመጨረሻ ውሉ የተተረጎመበት መንገድ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት የስር ፍ/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች ውሉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲሻርና ህዳር 9/2002 ዓ/ም በተደረገው ውል መሰረት ተጠሪ ላላገለገለበት ጊዜ የሚፈለግበትን ብር 16,664.00 ለአመልካች መክፈል አለበት ተብሎ በዚህ ነጥብ ላይ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሻሽሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታቸው ተመርምሮ ውሉ የተተረጎመበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ተጠሪ ቀርበው መልስ እንደሰጡበት ተደርጓል፡፡

በበኩላችን የተያዘውን ጭብጥ ግራ ቀኝ ወገኖች ካደረጉት ክርክር ፣ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር በማገናዝብ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንዲሚቻለው ለክሱ መነሻ የሆኑት ውሎች ስለመደረጋቸው ፤ ተጠሪም በሁለቱም ውሎች መሰረት ስልጠና መውሰዱ ፤ ሁለተኛው ስልጠና የጀመረው ተጠሪ የቀደመውን ስልጠና አጠናቆ ግዴታውን በመወጣት ላይ እያለ ነገር ግን የቀደመውን ግዴታ ከማጠናቀቁ በፊት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከቀደመው ውል የሚጠበቀው የ9 ወራት የአገልግሎት ቀሪ ዋጋ ብር 16,664.00 ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነው ሁለተኛው የስልጠና እና የአገልግሎት ውል የቀረውን የቀደመ ግዴታ የሚጠቀልል እና ቀሪ

የሚያደርግ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ የተቃወሙት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ውል እና ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም በማለት ነው፡፡

ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረጉትን ውሎችና ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረውን ህግ መሰረት በማደረግ ሲሆን አከራካሪ የሆነውን የውሉን አንቀጽ 7 ይዘት እና ተገቢነተ ያለውን የህጉን ድንጋጌ ተመልክተናል፡፡

አመልካች ክሱን ለማስረዳት ባቀረበው ውል አንቀጽ 7 እንደተመለከተው ሰልጣኙ (ተጠሪ) በቀዳሚው ውል የነበረበትን የአገልግሎት ግዴታ ሳይጨርስ ለሌላ ስልጠና ሊመደብ እንደሚችል ፣ በዚህ ሁኔታ አዲስ ውል እንደሚፈረምና የአገልግሎት ጊዜውም በዚሁ ጊዜ የሁለቱም ስምምነት ለመሸፈን እንደሚጠቃለል ተደንግጓል፡፡

አመልካች ይህ የውሉ አንቀጽ ግልጽ እና ተጠሪ የሁለቱም ውሎች የአገልግሎተ ጊዜ አጠቃሎ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት የሚያመለክት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ሁለተኛው የስልጠና የአገልግሎት ጊዜ የሁለቱም ስምምነቶች የሚሸፍን (የሚያጠቃልል) መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የተጠሪን መከራከሪያ ተቀበሎ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የውሉ ስምምነት በስር ፍ/ቤት የተተረጎመበት መንገድ ስህተት ሆኖ እንዳላገኘው በውሳኔው አመልክቷል፡፡

ከላይ እንዲተመለከተው የውሉ አንቀጽ 7 ተጠሪ የሚኖርበትን የአገልግሎት ጊዜ ግዴታ በተመለከተ አጠራጣሪ ይዘት ያለው ነው፡፡ እንዲህ አይነት አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የውሉ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት በውሉ አስገዳጅ የሆነው ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ ሳይሆን በውሉ ተገዳጅ ለሆነው ሰው ምቹ በሚሆንበት አኳኋን ነው፡፡ ይኸው የትርጉም መርህ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738(1) ስር ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ በቀዳሚው ውል የነበረበትን የአገልግሎት ግዴታ ሳይጨርስ ለሌላ ስልጠና ሲመደብ እና አዲስ ውል ሲያዝ የአገልግሎት ጊዜ ግዴታን በተመለከተ የሚደነገገው የውሉ አንቀጽ 7 መተርጎም ያለበት አመልካችን በሚጠቅም መንገድ ሳይሆን በአንቀጹ ተገዳጅ የሆነውን ተጠሪን በሚጠቅም መንገድ ነው፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ከውል ድንጋጌዎች አተረጓጎም አንጻር አይተው አለመወሰናቸው የሚነቀፍ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ተጠሪ ከቀዳሚው ስምምነት ሳይፈጸም ቀረውን የአገልግሎት ጊዜ ግዴታ በገንዘብ ተሰልቶ የቀረበውን ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1ኛ. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 73094 የካቲት 19/2005 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.135184 ግንቦት 13/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በውጤቱ ጸንቷል፡፡

2ኛ. የሰበር ክርክሩ ስላስከተለው ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

3ኛ. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 105919

ቀን ጥቅምት 4/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ መኪያ አብደላ -ጠበቃ ቶማስ ወ/ሰንበት ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጣሰው ሽምሱ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ ውል መሰረት ያደረገ ክርክር ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን ክሱም ከአመልካች ጋር ባደረግነው የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ ውል መሰረት ቤቱን ታስረክበኝ የሚል ሲሆን አመልካች ክሱ ከደረሳቸው በኋላ ውሉ በተንኮልና በማሳሳት የተደረገ ነው በሚል እንዲፈርስ እንዲወሰን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያከራከረው የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም አመልካች በዚህ የልውውጥ ውል መነሻም ተጨማሪ ብር 9000 (ዘጠኝ ሺ) መቀበላቸው ስለተረጋገጠ በውሉ መሰረት ይፈጸም በማለት ወሰነ፡፡

አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የሰበር ችሎቱም ኮንኮሚኒየም ቤት የደረሰው ሰው እስከ አምስት አመት ድረስ ቤቱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል ወይ? የሚለውን ጭብጥ ከአዋጅ ቁጥር 19/1997 አንቀጽ 14(2) አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

www.abyssinialaw.com

ተጠሪም በግራቀኙ መካከል የተደረገው የቤት ልውውጥ ውል ያልተሻረ እና ጸንቶ ያለ ስለሆነ ሊፈጸም ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው መጋቢት 14ቀን 2001ዓ.ም በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የኮንዶሚኒየም ቤት ቅይይር ውል በአመልካች ስም በጀሞ 1ሳይት ብሎክ ቁጥር 1 የሕንጻ ቁጥር 93 የወለል ቁጥር 1 የቤት ቁጥር JG - B 93/9 የሆነው ቤት በተጠሪ ስም ያለው ጀሞ 1ሳይት ቁጥር - 163 ወለል ቁጥር 1 የቤት ቁጥር JC - B — 163/11 በሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት በመለዋወጥ መስማማታቸውን ይገልጻል፡፡ የቤቶቹ ይዘት በተመለከተ በተጠሪ ስም ያለው ስቱዲዮ ሲሆን በአመልካች ስም ባለ አንድ መኝታ በመሆኑ ይህንኑ በገንዘብ ለማስተካከል ተስማምተው ብር 9000 (ዘጠኝ ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች ለመጨመር መስማማታቸውም ተገልጿል፡፡በክርክሩ ሂደትም አመልካች ብር 9000 መቀበላቸው ተረጋግጧል፡፡

እንግዲህ ይህ የኮንኮሚኒየም ቤት ልውውጥ በአዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 14/2/ መሰረት የተከለከለ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 14(2) ገዢው ጠቅላላው ዋጋውን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም ቤቱን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ 5(አምስት) አመት ሲሞላው ብቻ ይሆናል በማለት ደንግጓል፡፡

ድንጋጌው በግልጽ ቃል የጠቀሰው ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የከለከለ መሆኑን ሲሆን አመልካች በማንኛውም መልክ ማስተላፍን ይከለክላል በሚል ህሳቤ ይከራከራሉ፡፡ የተያዘው ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ እንጂ በሽያጭ ወይም በስጦታማስተላለፍ የተመለከተ ባለመሆኑ ሕግ አውጭው ይህንንም ለመከልከል ፈልጎ ቢሆን ኖሮ "በማናቸውም አኳኋን" ማስተላለፍ አይቻልም የሚል አጠቃላይ የሆነ ቋንቋ መጠቀም ይችል እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሰረቱ እዚህ መነሳት ያለበት መሰረታዊ ጥያቄ በአንድ በኩል አንድ ዜጋ ባፈራው ንብረት የመጠቀም ሙሉ መብት ያለው መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ በተያዘው የኮንዶሚንየም ቤት አጠቃቀም መብት ላይ በጊዜ ገደብ በተወሰነ ሁኔታ ገደብ ማድረጉን አስፈላጊነትና አላማ በማመዛዘን የሕጉን አላማ በሚያሳካ መልኩ ማስተግበር መቻሉን ማረጋገጥ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ስለሆነም በእጣ የደረሰው ሰው ቤቱን በሽያጭም ሆነ በስጦታ ለሶስተኛ ወገን እስከአምስት አመት ጊዜ ድረስ ማስተላለፍ አይችልም ተብሎ በሕገ መብቱ ሲገደብ ታሳቢ የተደረገው ጥቅም የራሱ የመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ባለእጣ መሆኑን ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም የአዋጅ መግቢያ እንደሚያመላክተው በከተማ ውስጥ ያለውን አነስተኛ የመጠለያ ችግር መቅረፍ እና በሂደትም ነዋሪው የቤት ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ የደረሰው የከተማው ነዋሪ በተለያዩ ጊዜያዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ተገፋፍቶ ቤቱን በሽያጭ ወይም በስጦታ የሚያስተላልፍ ከሆነ ነዋሪው የቤት ባለቤት እንዲሆን በሕጉ ታስቦ የተሰራው ስራ መክኖ ይቀራል የሚል ህሳቤ በመያዝ ምናልባት ችግሮች እንኳን ቢኖሩበት ወይም ሌላ ማህበራዊ ምክንያቶች ቢያስገድዱት በ5አመት ቆይታ ጊዜ ስለጥቅምና ጉዳት የማሰላሰያ ጊዜ አግኝቶ አመዛዝኖ ከውሳኔ ይደርሳል ተብሎ ተገምቶ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ውል የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ እስከሆነ ድረስ አንዳቸውም ያለቤት ቀርቷል የሚያሰኝ ባለመሆኑ የህጉን ሃሳብና አላማ ይጥሳል ወይም ሕገ-ወጥ ውል ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

ይህ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 65140 አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 14(2) ጠቅሶ ውሉ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው ፍርድ ለተያዘውም ክርክር ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል በማለት በአመልካች በኩል የቀረበውን ክርክር መሰረት አድርገን በመ/ቁጥር 65140 የተሰጠውን ፍርድ ይዘት ስንመረምር ተጠቃሹ መዝገብ ላይ የቀረበው ክርክር የኮንዶሚኒየም ቤት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ውል የሚመለከት ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም በዚህ መዝገብ ከተያዘው ኮንዶሚኒየም ቤት በልውውጥ ማስተላለፍ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤት ልውውጥ አዋጅ ቁጥር 19/97 አንቀጽ 14(2) ድንጋጌ የተላለፈ ሕገ-ወጥ ውል ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በስር ፍ/ቤት ለቀረበባቸው መልስ ሲሰጡ ልውውጥ ከተደረገ በኋላ የቤቱን ማጠናቀቂያ ስራዎች ለመስራት ብር 12,000 (አስራ ሁለት ሺህ) ወጪ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ለዚህም ማስረጃ አለኝ ሲሉ ዘርዝረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ

www.abyssinialaw.com

ሲያቀርቡ ተጠሪ ይህንን ገንዘብ እንዲተካላቸው በተለዋዋጭ (በአማራጭ) ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ይዘት አያመለክትም፡፡

ስለሆነም ውሉ የጸና ነው የሚለው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በዚህ ሰበር ችሎት የሚሻርበት ህጋዊ ምክንያት ባለመገኘቱ አመልካች ከውሉ በኂላ አወጣሁ ያሉት ብር 12,000 አስመልክቶ ወደፊት የሚጠይቁት ዳኝነት ካለ ይህ ፍርድ አያግዳቸውም ብለናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 60424 በ22/5/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 132260 በ4/02/2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ
3. በዚህ መዝገብ ታህሳስ 15 ቀን 2007ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/98348

ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች:አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካቾች:.1ኛ አቶ ዘሪሁን የኔነህ ቀረቡ

2ኛ የአቶ የኔነህ ጨርቆሴ ህጋዊ ወረሾች

1. አቶ ታረቀኝ የኔነህ

2. ,, የኃላሸት የኔነህ አልቀረቡም

3. ,, ዘሪሁን የኔነህ

ተጠሪ:- ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ ነገረ ፈጅ እንግዳወርቅ ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልከቾች ባሁኑ ተጠሪ እና በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተከፋይ ባልሆኑ 1ኛ ወ/ት ንሰሐ ወርቅህ 2ኛ ዳሽን ባንክ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው። የክሱ ይዘትም በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተከፋይ ያልሆነችው ወ/ሪት ንሰሐ ወርቅነህ ከአሁኑ ተጠሪ ሀዋሣ ዩኒቨርሰቲ ጋር በተፈራረሙት የበሰለ ምግም አቅርቦት ውል 1ኛ ተከሳሽ የነበረቸው ወ/ት ንሰሐ ቀርቅነህ ለመልከም አፈፃፀም ዋስትና 3ኛ ተከሳሽ ከነበረው የዳሽን ባንክ እንዲሰጣት ጠይቃ፤ 3ኛ ተከሳሽም ለዋሰትና የሚበቃ ንብራት እንድታቀርብ በመጠየቁ የአሁኑ 1ኛ አመልከች በስሙ ተመዝግቦ የሚገኝ የመኖሪያ ቤትና የሰሌዳ ቁጥር 3-42314 አይሱዙ የጭነት መኪና እንዲሁም 2ኛ አመልከች የመኖሪያ ቤት በመያዣ እንዲያዝ በመፍቀዳቸው ሦስቱም ንብረቶች በብር 658,568.00 ተገምተው ህዳር 15 ቀን 2007 ዓ/ም እ/ኤ/አ/ በተፈረመ የመያዣ ውል ለ3ኛ ተከሳሽ ሰጥቷል። 2ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ ተጠሪ) አቅርቦቱ የጥራት ደረጃውን አልጠበቀም በሚል የአቅርቦት ውሉን ከታህሳስ 13 ቀን 2000 ዓ/ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ አቋርጧል። ውሉ በተቋረጠ በ4ኛ ቀን 2ኛ ተከሳሽ ቀደም ሲል በጨረታው 2ኛ የወጣውን ተወዳዳሪ በ1ኛ ተከሳሽ ምትክ በመተካት ውል መፈጸሙ አቅርቦቱ በግለሰቡ አማካኝነት እየተከናወነ ይገኛል። የ1ኛ ተከሳሽ የአቅርቦት ውል በመቋረጡ በ2ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ላይ የደረሰ ኪሳራ ወይም ተጨማሪ ወጪ ከለ ለ1ኛ ተከሳሽ ተከፋይ ከሚሆን የአቅርቦት ሂሳብ ተቀናሽ ሆኖ ወጪው ከተካካ በኃላ 3ኛ ተከሳሽ ለሰጠው የብር 658,568 .00 ዋስትና በመያዣነት የተያዙ ንብረቶች እነዲለቀቅላቸው

www.abyssinialaw.com

ጥያቄ አቅርበው ኪሳራው አስልቶ ከአንደኛ ተከሳሽ ተከፋይ ሂሳብ ተቀነሽ በማድረግ ለራሱ ገቢ ካደረገ በኃላ ንብረቶችን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ የአቅርቦት ውሉ በ2ኛው ተጫራች አማከይነት ወዲያውኑ በመቀጠሉ ንብረቶቹ በመያዣነት እንደተያዙ ሊቀጥሉ ወይም የዋስትናውን ገንዘብ ሊወረስ የሚችልበት አግባብ ባለመኖሩ ዋስትናው ቀሪ ሆኖ ንብረቶቹ እንዲለቀቁ በ3ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኙት የበለቤትነት ሰነዶች ተመለሽ እንደሆኑ እንዲወስንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ የአሁኑ ተጠሪ ጨምሮ መልስ አቅርቦዋል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የነበረቸው የሚትከሰስበት ምክንያት እንደሌላ፤ ውሉ በ2ኛ ተከሳሽ ፍላጎትና ውሳኔ ተቋርጠዋል፤ በጨረታው አሸናፊ የሆነውን 2ኛ ተጫራች የነበረው ተተክቶ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር የውል ግዴታ ገብቶ ሥራን ቀጥሏል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የሚጠይቀው ዕዳ የለውም መያዣው ሊለቀቅ ይገባል የሚል ይዘት ያለው መልስ ያቀረበች ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ ተጠሪ) ደግሞ ከአመልካች ጋር የውል ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ተጣምሮ መከሰስ እንዳልነበረበት ክሱን ንብረቱን በያዘው አካል ላይ ብቻ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ በፍሬ ጉዳዩም የምግብ አቅርቦት ውሉ የተቋረጠው በ1ኛ ተከሳሽ ግዴታ ያለመወጣት ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ ለተጨማሪ ኪሳራ ተደርጓል፡፡ መያዣው ሊመሰስ አይገባም የሚል ክርክር አቅርቦዋል 3ኛ ተከሳሽ የነበረው የዳሽን ባንክ 1ኛ ተከሳሽ የውል ግዴታቸው ባለመወጣታቸውን በገባው ውል መሠረት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ብር 658,568.00 ለሐዋሳ ዩኒቨርሰቲ ገቢ አደርገዋል፡፡ መያዣው ሊለቅ አይችልም፡፡ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገበል የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡ መቃወሚያዎች ውድቅ አድርጓል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም 2ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) 1ኛ ተከሳሽ በውሉ መሠረት ግዴታዋን አልተወጣችም በሚል ያፈረሰው በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሁኔታ መመለስ የሚገበቸው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ውሉን ለመፈጸም የተሰራው ሁሉ ቀሪ ሆኖ ውጤት ስለማይኖረው በፍ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት አመልከቾች የገቡት ዋስትና ቀሪ ይሆናል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ (ተጠሪ) ውሉን እስከ ፈረሰ ድረስ ከ1ኛ ተከሳሽ አለኝ የሚለው ቀሪ ሂሣብ ከለው በህግ ከመጠየቅ ውጭ ለዋስትና ግዴታ የተገባው ንብረት ለ3ኛ ተከሳሽ ሊከለከል አይገበም፡፡ የምግብ አቅርቦት ውሉ ሲቋረጥ መያዣው ይቋረጣል፡፡ 3ኛ ተከሳሽ ገንዘቡን መክፈል አልነበረበትም፡፡ 3ኛ ተከሳሽ ለመልካም አፈፃፀም የከፈለው ገንዘብ የማስመለስ መብቱ ተጠብቆ ከአመልካቾች የተያዙ መኖሪያ ቤቶችና መኪና የባለቤትናት ማረጋገጫ ሰነዶች ጭምር ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ዳሽን ባንክ እንደቅደም ተከተላቸው በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 63309 እና 63860 ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ የነበረው

www.abyssinialaw.com

ዳሽን ባንክ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀበይነት በማግኘቱ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የሃዋሳ ዩኒቨርሰቲ በራሱ አነሰሽነት ውሉን ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ በሕግ መብት ያለው ቢሆንም እንደ ውሉ ያልፈጸመው ወገን ማን ነው? የሚለውን ክርክር ባስነሳ ጊዜ እና እንደውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰው የጉዳት ኪሣራ ምን ያህል ነው? የሚለው ሁሉ የመረጋገጥ ግዴታ ስላለበት በዚህ ጭብጥ መሰረት 1ኛ ተከሳሽ ባለችበት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቶ ሊወሰን እንደሚገባ፤ በዚህ ክርክር ውጤት መሠረት በማድረግ የዳሽን ባንክ ለዩኒቨርሲቲው የከፈለው የክፍያ መጠን አግባብ መሆኑና አለመሆኑን ታይቶ አሰፈላጊው ዳኝነት እንዲሰጥበት በጭብጥ የተያዙ ነጥቦች በክርክር እና በማስረጃ መሠረት ተለይቶ ከመታወቁ በፊት በመያዣ የተያዙ ንብረቶች ሊለቀቁ አይገበም በማለት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 (1) መሠረት ተጠርቶ እንዲወሰን ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የኮ/መ/ቁ. 67820 በማንቀሰቀስ ጉዳዩ በድጋሚ የተመለከተው ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ ባለመቅረቧ ክርክሩ በሌለችበት እንዲቀጥል አደርጓል፡፤ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋሪ በፈፀመችው የምግብ አቅርቦት ውል ከ11/2/2000 እስከ 11/12/2000 ዓ/ም ለ10 ወር ጊዜ ለማቅረብ የተስማማች ቢሆንም 2 ወር አቅርቦት ከፈጸመች በኃላ በማቋረጧ ተጠሪ ውሉን በ14/04/2000 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ማቋረጡን፤ ለውሉ ማቋረጥ ምክንያትም በጥራትና በጊዜ መቅረብ ባለመቻሉ ስለመሆኑ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ያሰያል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ቀርባ  አልተከራከረችም በመሆኑም 1ኛ ተከሳሽ ለውሉ መቋረጥ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ ተችሎአል፡፡ ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተ የጉዳት ከሳ ከደረሰው ጉዳት አንፃር መታየት ያለበት ስለመሆኑ ተጠሪ የገባው ሁለተኛ  ውል በመጀመሪያ ውል ከተቀመጠው ዋጋ በልዩነት 1,347,403.02 ተጨማሪ ወጭ የሚጠይቀው መሆኑ መከራከሩን፣ አቅርቦት በመጠን ሲያንስ ሂሳቡ ሲቀነስ እንደነበር ውሉ ከመቋረጡ በፊት የደረሰው ኪሳር ዝርዝር አለመያዙን ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ሲመዘንም ከ14/4/2000 እስከ 17/4/2000 ዓ/ም በለው ጊዜ የደረሰ ኪሳራ መሆኑን እንደሚያሳይ ለ8 ሺህ ተማሪዎች ለዳቦ ግዥ ለ3 ቀናት ያወጣው የኪሳራ ልክ 96,000 ብር መሆኑ እንዳረጋገጠ፤ 3ኛ ጭብጥ በተመለከተ 2ኛ ተከሳሽ የደረሰበት የጉደት መጠን አስልቶ ክስ ከሚያቀርብ በቀር አጠቃላይ ለውሉ አፈፃፀም የተያዘው መብት እንደሌለው፤ 3ኛ ተከሳሽ (ዳሽን ባንክ) የሚፈጸመው ክፍያም ውል ባለመፈፀሙ የደረሰ ጉዳት ታሳቢ የሚያደረግ እንጂ ጉዳት ቢደርስም በይደርስም ለመክፈል ይገደዳል ማለት አለመሆኑን፤ በዚሁም በሁለተኛ ጭብጥ በተረጋገጠው መሰረት 3ኛ ተከሳሽ ለ2ኛ ተከሳሽ ሊከፈል የሚገባው ብር 658,568 ሳይሆን ብር 96,000 መሆኑን፤

www.abyssinialaw.com

አራተኛው ጭብጥ መያዣው ከላይ በተመለከተው የካሣ ልክ ያረፈበት በመሆኑ ይህ ክፍያ ሳይፈፀም መያዣ ሊለቀቅ የሚችልበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ በመጀመሪያ እና ሁለተኛ አቅረቢ የዋጋ ልዩነት መኖሩን አልተከደም፡፡ በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩ አቅረቢ ለ8 ወራት ቢያቀርቡ ችግሩ አይከሰትም ነበር፡፡ 2ኛ ተጫራች የነበረው ሌላ ውድድር ሳይደረግ የአቅረቦት ውል እንዲቀጥል የተፈቀደው የ8,000 ተማሪዎች የምግብ አቅርቦት ማሟላት ፋታ የማይሰጥ ነው፡፡ የፌዴራል መንግስት የግዥ አዋጅ መመሪያ ይዘት መረዳት የሚችለው በአቅራቢ ችግር ምክንያት ውሉ በመቋረጡ ሊከሰት የሚችለው ተጨማሪ ውጭ /ጉዳት/ መሸፈን የሚገበው አቅረቢ መሆኑንና ለዚህም ለውሉ መልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለደረሰው ጉዳት መተኪያ ሊውል የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በውሉ መቋረጥ ምክንያት ደረሰብኝ የሚለው ጉዳት ብር 1,453,429.20 ነው፡፡ ይሁን እንጂ ክርክሩ ሲጀመረም ይሁን አሁን በይግባኝ ደረጃ ይህ ገንዘብ ሊከፈልኝ ይገበል የሚል ግልጽ ጥያቄ አላቀረበም፤ በግልጽ የጠየቀው ለመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ብር 658,568.00 ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ስለሆነ በይግባኝ ባይ (ተጠሪ) ለደረሰው ጉዳት ሊከፈል የሚገበው ብር 96,000 ሳይሆን ለውሉ መልካም አፈፃፀም የተያዘ ጠቅላላ ገንዘብ ብር 658,568 ነው፡፡ አመልከቾች ይህንን ገንዘብ ለሥር 3ኛ ተከሳሽ (ዳሽን ባንክ) ሲተኩ የዋስትና መያዝው ይለቀቅላቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልከቾች በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ጉዳዩን በሰበር ታይቶ እንዲመረመር እና እንዲለወጥ የሚጠይቅ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ክርክር አደርጓል፡፡ የአመልካቾች ቅሬታ መሠረታዊ ይዘትም ውሉ የተቋረጠው በዩኒቨርስቲው ድብቅ ምክንያት ነው፡፡ አቅርቦቱ የተቋረጠው ለ3 ቀን ብቻ በመሆኑ የጉዳት ከሳ ልክ መታየት ያለበት ከዚህ አንፃር መሆኑን እርግጠኛ ጉዳት መድረሱ ሳይረጋገጥ የጉዳት ከሳው ለመልከም አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው በሙሉ እንዲከፈል መውሰኑ በአግባቡ አይደለም፡፡ የግዥ አዋጅና መመሪያ አፈፃፀም በአግባቡ አልታየም፡፡ ጉዳዩ ሰበር በመለሰው መሰረት አልተጣራም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የአቅርቦት ውሉ የተቋረጠው በስር 1ኛ ተከሳሽ በነበረችው ምክንያት መሆኑን መረጋገጡን በመጀመሪያ እና ሁለተኛ አቅራቢ የዋጋ ልዩነት መኖሩን በተጠሪ ተቋም ላይ ጉዳት ማድረስን ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክራዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች እና ተጠሪ እያከራከሩ ያለው መሰረታዊ ነጥብ ለመልካም አፈጻጸም የተሰጠ ዋስትና ሙሉ በሙሉ ገቢ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ መኖር ያለመኖሩን ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዳጣራው የምግብ አቅረቦቱ ለ3 ቀን ብቻ ተቋረጦ የነበረ መሆኑን እየታወቀ የ8 ወር አቅርቦት መሰረት ተደርጎ የጉዳት ካሳው ሊሰላ አይገባም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የመጀመሪያ አቅርቢ በውሉ በሠረት ባለ መፈፀምዋ ውሉን እንደተቋረጠ 2ኛ አቅረቢ ሲመረጥ ያቀረበው ዋጋ ከመጀመሪያው የአቅርቦት ዋጋ በግልጽ ጭማሪ ያለው በመሆኑ የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን በማጣራት ለመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ገቢ እንዲሆን መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል ክርክር ማቅረቡን ተመልክተናል፡፡

በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ወ/ት ንሰሐ ወርቅነህ በገባችው ውል መሰረት የምግብ አቅርቦቱ በመጠን በጊዜ እና በጥራት ባለማከናወንዋ ተጠሪ ማስጠንቀቅያ በመስጠት ውሉን አቋርጦታል፡፡ በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ለውሉ መቋረጥ መነሻ አለመሆናን ያቀረበችው ክርክር ይሁን ማስተባበያ የለም ፡፡ በስር 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ዳሽን ባንክ የመልከም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ሊሰጥ የተቻለው ምናልባት በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው በውሉ ይዘትና መንፈስ አቅርቦቱን ከለከናወነች ተጠሪ ለሚደርስባት ጉዳት ለማከከሻ እንዲሆን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ለሁለት ወር ያህል ስታቀርብ በነበረችበት ጊዜ የነበረው ዋጋ እና ውሉ ከፈረሰ /ከተቋረጠ/ በኃላ በ2ኛ አቅራቢ የተጠየቀው ዋጋ ለወንዶ ገነት ዳን ኮሌጅ የ0.28 ሳንቲም ለሌሎች ከምፓሶች ደግሞ 0.39 ሳንቲም የዋጋ ልዩነት እንዳለው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ የዋጋ ልዩነቱ በ8 ወራት ሂሣብ ስሌቱ ሲሰራ በድምሩ ብር 1,453,429.20 ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መጀመሪያ ከነበረው የአቅርቦት ውል 2ኛ አቅራቢ ዋጋ በመጨመሩ በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ገንዘብ ወጭ ለማድረግ የሚገደድ ስለመሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ አመልካቾች አቅርቦቱ የተቋረጠው ለ3 ቀን ብቻ ነው የሚል ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ለ8 ወራት የሚዘልቅ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክር መረዳት ተችሏል፡፡ ምክንያቱም የአሁኑ ተጠሪ ከ2ኛ አቅራቢ ጋር ያደረገው ውል ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ ወጭ የጠየቀው በመሆኑ በስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው በውሉ መሰረት በጊዜ መጠን እና ጥራት የምግብ አቅረቦቱ ቢቀጥል ሌላ 2ኛ አቅራቢ በላሰፈለገ ነበር፡፡ በመሆኑም በተጠሪ ላይ ጉዳት አልደረሰም የሚለውን ክርክር በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠው አንጻር የህግ መሰረት ያለው ክርክር ሁኖ አላገኘነውም፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሰረቱ ለመልካም ስራ አፈፃፀም የሚሰጥ ዋስትና ዓይነተኛ ዓለማው በተሰራው ነገር ጉዳት የደረሰበት ተዋዋይ ወገን በገንዘብ ረገድ ለመካስ ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት የክርክር ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው አቅራቢ በውሉ መሠረት ማቅረብ ባለመቻሏ ውሉ ፈርሷል፡፡ ተጠሪ ከሌላ ተዋዋይ የአቅርቦት ውል የፈፀመ መሆኑ ባይካድም በመጀመሪያ እና ሁለተኛ አቅርቦት ላይ በዋጋ ረገድ ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን ግልጽ ነው፡፡ በአሁኑ ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረችው ግለሰብ ተፈፀሞ የነበረው የምግብ አቅርቦት ውሉ ለ10 ወራት የሚቆይ እንደነበር፤ ይሁንና በ1ኛ ተከሳሽ ውል አለመፈፀም ምክንያት በ2ኛ ወር ተቋርጧል፡፡ በአሁኑ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ የነበራችው እንደውሉ ባለመፈፀምዋ ከ2ኛ ተዋዋይ የአቅርቦት ውል ለማድረግ የተገደደ በመሆኑ ተጨማሪ ወጭ የጠየቀው ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ ከነበረው ዳሽን ባንክ የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ገቢ እንዲሆንለት መጠየቁ ውሉን መሰረት ያደረገ በደረሰው ጉዳት ልክ ሳይሆን በተሰጠው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ብር 658,568,00 የተገደደ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ጠቅለይ ፍርድ ቤት በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል መልካም የስራ አፈፃፀም ዋስትና ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ማለትም ብር 658,568.00 ገቢ እንዲሆን መወሰኑ ውሉን በህጉ አግባብ ተፈፃሚ አደረጓአል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሳይም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረሰ በተባለው ጉዳት ሊከፈል ይገባል በማለት የወሰነው 96,000 ብር በማሻሻል ለመልከም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘው ብር 658,568.00 ገቢ እንዲሆን መወሰኑ በህጉ አግባብ ሆኖ በመገኘቱ የሚታረም የህግ ስህተት የለውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 89493 በ30/03/2006 ዓ/ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 67820 በ 09/07/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. በተጠሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት ሊከፈል የሚገባው ብር 96,000 ሳይሆን ለውሉ መልከም ስራ አፈፃፀም የተያዘው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 658,568 /ስድስት መቶ ሃምሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ስምንት/ ተብሎ መወሰኑ በአግባብ ነው ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

3. አመልካቾች ይህንን ገንዘብ በስር 3ኛ ተከሳሽ ለነበረው ደሽን ባንክ ሲተኩ የዋስትና መያዣው ይለቀቅላቸው ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር በጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 101053

ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ጌታቸው መንትስኖት

ተጠሪ፡- አቶ የምሩ ነጋ - ጠበቃ አሳምነው አረጋ

**መዝገቡን መርምረን ተከታን ወስነናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በኪራይ የተያዘን ቤት ጥገና መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ታህሳስ 10 ቀን 2004 ዓ/ም ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡

የክሱ ይዘትም ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነ በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 20 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 695 የሆነ ቤት ተከራይቼ እንዳድሰውና ለዕድሳት የማወጣው ወጭ ከቤቱ ኪራይ እንዲታሰብልኝ ለመ/ቤቱ የቦርድ አመራር አመልክቼ ቦርዱ ህዳር 29/1998 ዓ/ም በፈቀደልኝ መሰረት የቤቱን ጥገና ለማካሄድ ከንኮማድ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግል ማህበር ጋር ተዋውዬ ለቤቱ ጥገና ብር 1,415,604.80 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስድስት መቶ አራት ከ80/100) ወጪ አድርጌ ሳስጠግን የቆየሁ ቢሆንም ተከሳሽ ሀምሌ 18/2000 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ ዋናውን የቤቱን አካል በማፍረስ በህገ-ወጥ መንገድ ግንባታ እያደረጉ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 555/2000 የተሰጠውን ስልጣን ያላግባብ ተጠቅሞ ሀምሌ 23/2000 ዓ.ም በፖሊስ ኃይል አስለቅቆ ቤቱን የወሰደው ስለሆነ ያላግባብ የወሰደውን ቤት መልሶ እንዲስረክበኝ፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ለቤቱ ጥገና ያወጣሁትን ወጪ እና በቤቱ ሳልጠቀም ጥገና ሲካሄድ ለነበረበት ጊዜ የከፈለኩት የኪራይ ገንዘብ ብር 232,891.50 ከወለድና ወጪና ኪሳራ ጋር እንደመልስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በክስ መቃወሚያነት ከሳሽ ከውል ውጭ ህገ ወጥ ግንባታ ስለገነቡና ህገ ወጥ ግንባታ የማስፈረስ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 555/2000 የተሰጠው በመሆኑና በዚሁ መሰረት ተከሳሽ ቤቱን የተረከበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ብሏል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በሰጠው መልስ ቤቱን ከሳሽ እንዲጠግኑ ፈቃድ ያልተሰጠ በመሆኑ የጥገና ወጪ ይከፈልኝ፤ በጥገና ለቆየበት ጊዜ የከፈልኩት የቤት ኪራይ ይመለስልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡ ከሳሽ ቦርዱ ቤቱን እንድጠግን ወስኖልኛል ካሉበት ከህዳር 29/1998 ዓ/ም በኃላ የኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ የካቲት 22 ቀን 1998 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ቤቱን ለማደስ በጣም አስቸጋሪና ወጪውም ከፍተኛ በመሆኑ በጠቅላላው ቤቱ ፈርሶ በአዲስ መልክ ቢሰራ የተሻለ መሆኑን ገልጿል፡፡ በዚሁ መነሻነት የተከሳሽ የማኔጅመንት ስራ አመራር ጥር 7/1999 ዓ/ም ባካሄደው ሰብሰባ ከሳሽ ቀደም ብሎ ባቀረቡት የማሻሻያ ስራ ጥያቄ ላይ ነባሩ የቤቱን ፕላን ተጠብቆ ስራው እንዲሰራ ይህንንም የቴክኒክና ምህንድስና መምሪያ በበላይነት እየተቆጣጠረ እንዲያሰራ የተወሰነ መሆኑን በማስታወስ የአሁን ከሳሽ ባቀረበው ጥናት መሰረት ቢሰራ የባለቤትነት ጥያቄ ሊያስነሳና የተከሳሽንም መብት ሊያሳጣ እንደሚችል በመረጋገጡ ከሳሽ ባቀረበው ጥናት መሰረት መፍቀድ ስለማይቻል ቤቱን እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ የተከሳሽ ስራ አመራር ቦርድ በወሰነው መሰረት ጥናት አካሂደ በኤጀንሲው ተቀባይነት ሳያገኙና ቤቱን እንዴት ማደስ እንዳለባቸው ሳይዋዋሉ በተከሳሽ ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በመሆኑም ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3) መሰረት ከውል ውጭ ህገወጥ ግንባታ በሚያካሄድ ተከራይ ላይ ማስጠንቀቂያ በመሰጠት ቤቱን እንዲረከብ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተረከባቸው በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም፡፡ ቤቱ እንደ አዲስ ፈርሶ እንዲሰራ አልፈቀደም ፤ የስራ አፈጻጸም ውልም አልገባም፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ እውቅና ውጭ ያወጡትን የጥገናና እድሳት ወጭ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸውም የህግ መሰረት የለውም፤ ተከሳሽ የመንግስት መ/ቤት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3250-3253 ድንጋጌዎች መሰረት የስራ ውል ከፈጸመ በኃላ በበላይነት የስራውን አካሄድ እንዲቆጣጠር ሊደረግ ይገባ ነበር፤ ከሳሽ ከንኮማድ ከተባለው የራሳቸው የኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር ያደረጉት የስራ ውል ተቀባይነት የለውም፤ በአጠቃላይ ከሳሽ ምንም ዓይነት የጥገና ዕድሳት ውል ሳይደረግ በማን አለብኝነት አፍረሰው በመሰራታቸው ለግንባታ አወጣሁ የሚሉትንም ሆነ በጥገና ለቆየበት ጊዜ የከፈልኩት ኪራይ ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃውን ተመልክቶ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ተከሳሽ መልሶ መውሰዱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የኪራይ ውሉ ሊቀጥል ይገባል? የሚሉትን ነጥቦች በተመለከተ በኪራይ ውሉ አንቀጽ 7(2) ተከራይ የአከራዩን

www.abyssinialaw.com

የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ የቤቱን ጣሪያ፣ ግድግዳ፣ ወለል አያፈርስም አይሰራም፣ በቤቱ ውስጥም ሆነ በቤቱ አጥር ክልል ውስጥ የኮንስትራክሽን ስራ አይሰራም ተብሎ የተከራዩ ግዴታ በግልጽ የተመለከት በመሆኑ፣ እንዲሁም በውሉ አንቀጽ 11(3) የቤት ኪራይ ውሉ ከሚፈርስባቸው መንገዶች መካከል አንደኛው አንዱ ወገን በውሉ ውስጥ የተመለከተውን ግዴታውን በትክክል ሳይወጣ መቅረቱ መሆኑ ስለተመለከተ፣ የተከሳሹ ድርጅት ስራ አመራር ቦርድ ቤቱን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ቢኖርም እድሳቱና ግንባታው በምን ያህል ወጪና ደረጃ እንደሚከናውን ከሳሽ ለተከሳሽ አሳውቆ ፈቃድ ሳያገኝ ግንባታውን ማከናወኑ በውል የተመለከተውን ግዴታ መጣስ ነው፣ ተከሳሹም በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቤቱን ከከሳሽ መረከቡ በህጉ አግባብ ነው፣ በውሉ መሰረት ከሳሽ ቤቱን እንዲጠቀሙበት ለመመለስ የሚገደድበት ምክንያት የለም ብሏል፡፡

ከሳሽ ቤቱን ለማደስ ያወጡትን ወጪና የከፈሉት የኪራይ ገንዘብ እንዲመለስ የተጠየቀውን ዳኝነት በተመለከተም ስለግንባታው የተደረገ ዝርዝር ስምምነት በሌለበት፣ ስለአፈጻጸሙም ሆነ ስለሚያስከትለው ወጪ ተከሳሽ እንዲያውቁትና በዚሁ መሰረት እንዲከታተሉ ሳይደረግ የቦርዱን መነሻ ውሳኔ በቻ መሰረት በማድረግ ግንባታ ማካሄዳቸው ተገቢ ባለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2912 አከራይ ሳይፈቅድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁኔታን መለወጥ እንደማቻል ስለሚደነግግ፣ የማደሻ ወጪን የሚችለው ተከራይ ባልሆነ ጊዜ ተከራዩ ይህን ሁኔታ ማሳወቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ3/ቁ.2917 የተደነገገ በመሆኑ፣ እንዲሁም ተከራይ ያላከራይ ፈቃድ በቤቱ ላይ ስላደረገው ማሻሻያ አንዳች ወጭ መጠየቅ መብት እንደሌለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2973(1) ስር የተደነገገ በመሆኑ፣ የቤቱን ዕድሳትና ጥገና ሁኔታ እና የሚያስከትለውን ወጪ ተከሳሽ አውቆ ስምምነቱን የሰጠና የፈቀደ ለመሆኑ ከሳሽ ባላስረዱበት ሁኔታ ቤቱን ለማደስና ለመገንባት ያወጡትን ወጪ ተከሳሽ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣ የኪራዩን ገንዘብ በተመለከተም ከተከራዩበት ጊዜ ጀምሮ የከፈሉትን ገንዘብም ተከሳሽ ሊመልስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝተው ይግባኙን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በመጨረሻ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ጥገናው ወዲያው እንደተጀመረ ተከታትሎ ማስቆምና ተጠሪን ከቤቱ ማስወጣት ሲገባው የቤቱ ዕድሳት ሲሰራ ዝም በማለት ለወጪ ከዳረጋቸው በኃላ እድሳቱን አቋርጠው እንዲወጡ ማድረጉ ቅንልቦናን የተከተለ ባለመሆኑ፣ የስር ፍ/ቤትም ጉዳይን ከግራ ቀኙ የቤት ኪራይ ውል እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2912፣ 2917፣ 2973(1) ድንጋጌዎች አንጻር ብቻ በመመልከት የአመልካች መ/ቤት ስራ አመራር ቦርድ ቤቱን እንዲጠግኑ ፈቃድ የሰጠበትን በተገቢው ሳያገናዝብ የቤቱ ዕድሳት ገንዘብ መክፈል የለበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፣ ነገር ግን የቤቱን ኪራይ በተመለከተ በቤቱ እንዳልተገለገሉ የሚያሳይ ማስረጃ ስላላቀረቡ ወይም ቤቱ እስኪጠገንና አገልግሎት እስኪሰጥ

www.abyssinialaw.com

ኪራይ እንዳይታሰብ የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ የኪራይ ገንዘብ ሊመለስ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የቤቱን ጥገና ወጭ በተመለከተ ክርክር ተደርጎ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበ በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 18/2006 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ አመልካች ሳልፈቅድለት በአከራየሁት የመኖሪያ ቤት ላይ ያካሄደው ግንባታ ከውል ስምምነታችን ውጭ በህገ ወጥ መንገድ የሰራው በመሆኑ ያወጣው ወጭ የመተካት ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ታይቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተጠሪ ጥያቄ በውሉም ሆነ በፍ/ብሔር ህጉ ድጋፍ የለውም ተብሎ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ ከአመልካች የተከራየውን ቤት ለማደስ ባያስፈቅድም ተጠሪ ግንባታ ሲያካሁድ እያወቀ ዝም ብሎ ቆይቶ እኔ ሳልፈቅድ ያወጣውን ወጭ አይከፍልም በማለት የስር ፍ/ቤት መወሰኑ የአመልካች ስራ አመራር ቦርድ ቤቱን ተጠሪ እንዲጠግኑ የሰጠውን ውሳኔ ያላገናዘብ ነው በማለት ሽሮ አመልካች ተጠሪ ለቤቱ ጥገና ያወጣውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን ተለዋወጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ካስነሳው የውሳኔ ክፍል እና አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ለእድሳት ያወጣው ገንዘብ እንዲተካለት ዳኝነት የጠየቀው የተከራየውን ቤት እንዲያድሰውና ለዕድሳት ያወጣው ወጭ ከቤቱ ኪራይ እንዲታሰብለት ለመ/ቤቱ የቦርድ አመራር አመልክቶ ተፈቅዶለት እያለ የቤቱን አካል በማፍረስ ህገ ወጥ ግንባታ እያደረጉ ነው በሚል አመልካች ቤቱን መልሶ ወስዷል በማለት ነው፡፡ አመልካች የኪራዩን ቤት ከተጠሪ መልሰው መውሰዳቸውን ሳይክዱ ከውሉ ወጭ ህገ ወጥ ግንባታ መደረጉን ከሳሽ ባቀረበው ጥናት መሰረት ቤቱን ለማደስ አስቸጋሪና ወጪውም ከፍተኛ በመሆኑ በጠቅላላ ቤቱ ፈርሶ በአዲስ መልክ ቢሰራ የተሻለ መሆኑ ስለተገለጸ በጥናቱ መሰረት መፍቀድ እንደማይቻልና ቤቱን እንዲያስረክቡ ከማድረጉ ውጭ የሰጠው ፈቃድ ስለሌለ ወጪውን ለመክፈል ኃላፊነት እንደማይኖርበት ተከራክሯል፡፡

በኪራይ ውሉ ተጠሪ በቤቱ ላይ የሚያከናውኑትን ግንባታ ለአመልካች በቅድሚያ የማሳወቅ እና ከአመልካቹ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኙ በቀር ግንባታ ያላመካሄድ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከህጉም አንጻር ሲታይ የማደሻውን ወጪ የሚችለው ተከራዩ ካልሆነ ይህን ሁኔታ

www.abyssinialaw.com

ላካራዩ ማስታወቅ ግዴታ ሲሆን ተከራዩ ያላከራዩ ፈቃድ በተከራየው ቤት ላይ ስላደረገው ማሻሻያ አንዳች ወጭ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት እንደማይኖረው፤ ነገር ግን ማሻሻያውን ያደረገው በአከራዩ ፈቃድ እንደ ሆነ ተከራዩ ያደረጋቸውን ወጭዎች ሁሉ እንዲከፍለው አከራዩን ከሶ ሊጠይቀው እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2973 እና 2917 እንዲሁም ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ ከተደነገጉ የፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

በኪራይ ውሉም ሆነ በህጉ ተጠሪ በኪራይ ቤቱ ላይ የሚያከናውነውን ግንባታ ለአመልካች ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን ለማሻሻያው ያወጣው ወጪ የሚተካለት ማሻሻያው በግልጽ በአከራዩ ተፈቅደ የተከናወነ ሲሆን ስለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አከራካሪ ሆነ የዘለቀው ለማሻሻያው የተደረገው ወጪን በተመለከ የሚሰጠው “ፈቃድ” ነው፡፡

ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍ/ቤቶች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር መረዳት እንዲሚቻለው የአመልካች ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ ህዳር 29/1998 ዓ/ም ባደረገው መደበኛ ስብሰባ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ውይይት አድርጎ ኤጀንሲው ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለጠያቂው (ለተጠሪ) በኪራይ እንዲሰጣቸውና ለጥገና የሚያወጡት ወጭም በኪራይ እንዲተካላቸው ወስኗል፡፡ ከቦርዶ ውሳኔ በኃላ የኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ ቤቱ ባለበት ሁኔታ ሊጠገን እንማይችል ባቀረበው አስተያየት መነሻነት ጥር 07 ቀን 1999 ዓ/ም በመ/ቤቱ የማኔጅመንት ስራ አመራር አካላት ዕድሳት ሊፈቀድ እንደማይችልና ተጠሪ ቤቱን ማስረከብ እንደሚገባቸው ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ቤቱ ፈርሶ መስራት ቢኖርበት እንኳ ስለሚደረገው መሻሻል እና ስለሚያስወጣው ወጭ የተደረገ ስምምነት እና የተሰጠ ፈቃድ በሌለበት ግንባታ በማድረጋቸው አመልካች ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ሀምሌ 23/2000 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 555/2000 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቤቱን መልሶ ተረክቧል፡፡ ይህ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር አመልካች በውሉና በህግ ከተመለከተው ውጭ ሰርቷል የሚያሰኝ ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ በኪራይ ቤቱ ላይ ጥገና (ማሻሻያ) ያደረጉት የሚጠበቀውን ፈቃድ ከአመልካች አግኝተው ነው የሚያሰኝ አይደለም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ለቤቱ ጥገና (ዕድሳት) ያወጡትን ወጪ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የወሰነው አመልካች ጥገናው እንደተጀመረ ተከታትሎ ማስቆምና ተጠሪን ከቤቱ ማስወጣት ነበረበት፤ ለወጭ ከዳረጋቸው በኃላ እድሳቱ አቋተጠው እንዲወጡ ማደረጉ ቀንልቦናን የተከተለ አይደለም እንዲሁም ጉዳዩ ከውሉ እና ከህጉ ድንጋጌዎች ብቻ ሳይሆን የአመልካች ስራ አመራር ቦርድ አስቀድሞ ካሳለፈው ውሳኔ አንጻር መታየት ነበረበት በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ከቀደመው የቦርድ ውሳኔ በኃላ የኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ ቤቱ ሊጠገን እንደማይችል ያቀረበውን አስተያየት ተከትሎ የአመልካች መ/ቤት ማኔጅመንት

www.abyssinialaw.com

እድሳት ሊፈቀድ እንደማይችል መወሰኑን እንደማያውቁ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይልቁንም ጉዳዩን በቅርበት እንደመከታተላቸው የቀደመውን የቦርድ ውሳኔ ሲያውቁ የኃለኛውን አያውቁም ለማለትም አይቻልም፡፡ ተከራይ የኪራይ ቤት ለማደስ ያወጣው ወጪ አከራዩ ሳይፈቀድ የተደረገ ከሆነ በህጉ መጠየቅ እንደማይቻል ከላይ ከተመለከተነው ድንጋጌ መረዳት እየተቻለ ከቅን ልቦና ውጭ የተሰራ ስለመሆኑ እንኳ ሳይረጋገጥ ይህን ምክንያት በማድረግ ተጠሪ ጥገናውን ወጭ የመክፈል ኃላፊነት አለበት መባሉ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ክርክሩም የግራ ቀኙ ካደረጉት የኪራይ ውል እና ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ በጠቅላላውና የቤትን ኪራይ በተለይ ከሚመለከቱ የህጉ ልዩ ደንቦች አንጻር ታይቶ የማይወሰንበት የህግ ምክንያትም የለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ለተጠሪ ባከራየው ቤት ላይ ስለተደረገው ጥገና (ማሻሻያ) የሰጠው ፈቃድ ስለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ለጥገና አወጣሁ ያሉትን ወጪ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1ኛ. በፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 91172 የካቲት 24/2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 111615 ሚያዝያ 21/2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

3ኛ. አመልካች ለጥገና የወጣውን ወጪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡

4ኛ. በዚህ ፍ/ቤት ፊት ስለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 111778

ጥር 16 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሪት ገንዘብ ስጦታው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት የክ/ዐ/ህግ ዘላለም ተስፋዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡንመርምረንተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለመንግስት መስሪያ ቤት ለሚፈጸም ቅጥር የተገባውን የዋስትና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞንራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤትየአሁን ተጠሪ ባሁኑ አመልካችና በአቶ ዘመኑ ይላቅ (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ በመሰረተው ክስ አቶ ዘመኑ ይላቅ በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በግዥና በፋይናንስ የሥራ ሂደት ተቀጥሮ እየሰራ እያለ በተሰጠው ውክልና መሰረት ከልዩ ልዩ ገቢ ደረሰኝ 2617.00 ብርና ከሞዴል 85 ብር 10,070.00 አጠቃላይ ብር 12,687 (አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት ብር) ያጎደለ ሲሆን አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ሐምሌ 2002 ዓ/ም በወጣው መመሪያ መሰረት ለስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ዘመኑ ይላቅ ዋስትና ስለገቡ የጎደለውን ብር 12,687.00 ከወለድ ጋር በዋስትና ግዴታቸው መሰረት ይክፈሉ ሲል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ የፍርድ ቤቱን የሥረ ነገር ስልጣን መሰረት አድርገው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የስር 1ኛ ተከሳሽ የተቀጠሩት በግዥ ኦፊሰርነት ሁኖ አመልካች ዋስ የሆኑትም ለዚሁ የስራ መደብ መሆኑን፣ ለክሱ መሰረት የሆነው ገንዘብ ሊጎድል የቻለው የሥር 1ኛ ተከሳሽ በእለት ገንዘብ ተቀባይነት የስራ መደብ ተጠሪ መድቦ ሲያሰራውና አመልካችም ስምምነት ሳይሰጡበት መሆኑን ጠቅሰው ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም 1ኛ ተከሳሽ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከሰጠ በኂላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳውን ክርክር መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን አመልካች እስከ ብር 60,000.00 የዋስትና ግዴታ የገቡ በመሆኑ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በገቡት ዋስትና መሰረት ከህጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ

www.abyssinialaw.com

ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር አመልካች ለስር 1ኛ ተከሳሽ ዋስ የሆኑት ሰራተኛው በግዥ ኦፊሰርነት የሥራ መደብ ተቀጥረው ለሚከሰት ጉዳት መሆኑን፣ ለክሱ መሰረት የሆነው ጉድለት የተከሰተው ደግሞ ሰራተኛው በውክልና በእለት ገንዘብ ያዥነት ተመድበው ሲሰሩና ተጠሪ ደግሞ ይህንኑ እንዲያውቁ ሳይደረግ መሆኑን፣ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ሐምሌ 2002 ዓ/ም የወጣው መመሪያም የሥራ መደብ ለውጥ ሲደረግ ዋሱ እንዲያውቅ መደረግ እንደአለበት የሚደነግግ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አመልካች ዋስትና የገቡበትን የስራ መደብና ለክሱ መስረት የሆነው ጉድለት የተከሰተው አመልካች በማያውቀት የስራ መደብ ላይ ሰራተኛው ተወክሎ ሲሰራ መሆኑን አግባብነት ያላቸውንየመመሪያ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው በማለት ሽሮታል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ቢሆንም የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን ግራ ቀኙን አከራክሮ አንድን የመንግስት ሰራተኛ ከተቀጠረበት የስራ መደብ ውጪ በሌላ የስራ መደብ ወክሎ ማስራት በክልሉ የመንግስት ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 171/2002 የተፈቀደ መሆኑን፣ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ወጣ የተባለው መመሪያም ተፈፃሚነት ያለው የስራ መደቡ ሲቀየር እንጂ በውክልና ለሚሰራ ስራ አለመሆኑን በምክንያነት ይዞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት አመልካችን ለጉድለቱ ኃላፊ አድርጎአል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን ለጉድለቱ ኃላፊ ያደረገው አመልካች ከገቡት የዋስትና አድማስ ውጪና በክልሉ ሲቭል ሰርቪስ ቢሮ የወጣውን መመሪያ እንዲሁም የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1928 ድንጋጌን ሳያገናዘብ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊስተካከል ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች የገቡት የመንግስት ስራ ቅጥር ዋስትና ውል ተቀጣሪው በመንግስት መስሪያ ቤት ባለበት ጊዜ ከተቀጠረበት የስራ መደብ በተጨማሪ በውክልና እንዲሰራ ቢደረግና በዚሁ በውክልና ደርቦ እንዲሰራ በተደረገበት የስራ መደብ ላይ ሁኖ ለሚያጠፋው ጥፋት ሁሉ ለዋናው የሥራ መደብ ዋስ በሆነው ሰው ላይ ኃላፊነትን የሚያስከትል ነው? ወይስ አይደለም?፣ የኃላፊነት መጠኑስ ምን ያህል ይሆናል? የሚሉትን ጭብጦች ምላሽ መስጠቱ ተገቢ ሁኖ አግኝቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካችን ለክሱ ገንዘብ ኃላፊ ያደረገው አሰሪው የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጣሪውን ሰራተኛ ከተቀጠረበት የስራ መደብ በተጨማሪ በውክልና በሌላ የሥራ መደብ ላይ መድቦ ማስራት በህግ የተፈቀደ ነው በሚል አቢይ ምክንያት ሲሆን የስራ መደብ ለውጥ ሳይደረግ በውክልና ይሰራ በነበረው የሥራ መደብ ሰራተኛው ተመድቦ ሲሰራ ለሰራተኛው ዋስ ለሆኑት ለአመልካች እንዲያውቁት ማድረግን የሚያስገድድ ሕግ የለም በማለት ነው፡፡ በመሆኑምአመልካች የዋስትና ግዴታቸውን የገቡት ሰራተኛው ለግዥ ኦፊሰርነት ስራ ሲቀጠሩ መሆኑና አሁን ክርክር ያስነሳው ደግሞ ይኼው ሰራተኛ በዚሁ አመልካች ግዴታ በገቡበት መስሪያ ቤት ውስጥ የስራ መደብ ለውጥ ሳይደረግ በውክልና ደርበው እንዲሰሩ በተደረገበት የእለት ገንዘብ ተቀባይ የሥራ መደብ ላይ በመስራት ላይ እያሉ በፈጸሙበት የእምነት ማጉደል ድርጊት የጎደለ ገንዘብ መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረና ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶችም የተቀበሉት የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ስለዚህ የሕግ ጥያቄው የሚሆነውና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት የተቀጠረ ሰራተኛ በውክልና ሲሰራላጎደለውገንዘብ ሰራተኛው ሲቀጠር ዋስ የሆነ ሰው የዋስትና ግዴታ አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ የዋስትና ግዴታ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በፍ/ሕ/ቁጥር 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዋስትና ግልፅ መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ከተደረገው ውል ወሰን ለማለፍ የማይችል እና ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘቡ ልክ በዋስትናው ውል መገለፅ አለበት፡፡ ዋስትና ይህን ፎርማሊቲ ከማሟላቱም በተጨማሪ ለዋስትናው መሰረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊና ግራ ቀኙ የተስማሙበትና የሚታወቅ መሆን አለበት፡፡

አመልካች አቶ ዘመኑ ይላቅ በግዥ ኦፊሰርነት የሥራ መደብ ሲቀጠሩ የዋስትና ውል ግዴታ መፈረማቸው እና የውሉ አይነት ዋስትና እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 እንደተመለከተው የዋስትና ግዴታውን በግልፅ ጠቅሶ አመልካቿ እስከ ብር 60,000.00 ግዴታ መግባታቸውም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ውሉ የዋስትና መጠኑን በግልፅ ከገለፀ አመልካች ሊገደዱ የሚገባው በዚሁ በውሉ በተገለፀው የገንዘብ መጠን ልክ ነው፡፡ አመልካች አቶ ዘመን ይላቅ የተቀጠሩት በመንግስት መስሪያ ቤት መሆኑን አውቀው እስከፈረሙ ድረስ ሰራተኛው በዚያው መስሪያ ቤት በተለያዩ ምክንያቶች ከተቀጠሩበት የስራ መደብ በተጨማሪ ሌላ የስራ መደብ ላይ ተወክለውየመንግስትን ስራ ሊሰሩ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን እንደሚያውቁ የሚታወቅ ነው፡፡ ሰራተኛው የሰራበት የስራ መደብ ባህርይ ለዋስትና ግዴታ ወሳኝነት ያለው መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን አመልካች መጀመሪያ ግዴታ የገቡበትየግዥ ኦፊሰርነት የሥራ መደብም ከመስሪያ ቤቱ አጠቃላይ ገንዘብና ንብረት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከእለት ገንዘብ ተቀባይነት የስራ መደብ የሥራ ባህርይ ያነሰ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ሰራተኛው ሲቀጥር የዋስትና ግዴታውን መግባታቸው ከተረጋገጠና ሰራተኛው በስራ መደቡ ላይ ተጨማሪ የሥራ ኃላፊነት

www.abyssinialaw.com

ሲሰጣቸውም ተከታትለው ግዴታቸውን እንዲወርድ ሳያደርጉ ሰራተኛው በዚያው በተቀጠረበት መስሪያ ቤት ክፍት በሆነው የሥራ መደብ ላይ በሕጉ አግባብ በውክልና እንዲሰሩ ተደርጎ ስራውን ሲሰራ ለተከሰተው ጉድለት የዋስትና ግዴታ ያልገባሁበትና ሰራተኛው ስራውን በውክልና እንዲሰራ ሲደረግ እንዳውቅ ያልተደረገ የስራ መደብ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም የሚሉት ክርክር የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731(1) ፣1922 እና 1928 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ሰራተኛው ከተቀጠረበት የስራ ባህርይ ጋር ያልተገናዘበ በመሆኑ የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ተጠሪ ሰራተኛውን ከተመደበበት የስራ መደብ ውጪ በውክልና ማሰራቱ የዋሱን ግዴታ የሚያባብስ/የሚያከብድ/ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1928(2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ከዋስትና ውል መፈጸም በኋላ በባለገንዘቡና ባለእዳው መካከል የዋሱን ግዴታዎች የሚያባብሱ አዲስ ስምምነቶች እንዳይደረጉና ዋሱን ለተጨማሪ ጉዳት እንዳይዳርጉት ለመጠበቅ ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17077 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከትምአመልካች ሰራተኛውን ተጨማሪ የስራ መደብ ላይ በውክልና ማስራቱ በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 አንቀጽ 61(3) የተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር በመሆኑ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት አለው የሚሉት የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች ዋስትና አፈፃጸም መመሪያም የስራ መደብ ለውጥ ሲደረግ ዋስ ይህንኑ እንዲያውቅ የሚደረግበትን አግባብ የሚመለከት እንጂ በውክልና ሰራተኛው ከተቀጠረበት ስራ ሌላ የሥራ መደብ ደርቦ እንዲሰራ ሲደረግ አሰሪው መስሪያ ቤት ይህንኑ ለዋስ እንዲያሳውቅ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌን ያልያዘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክርም ከመመሪያው ድንጋጌዎችና ከክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 አንቀጽ 61(3) ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ አንፃር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሣ ኔ**

1. በራያ ቆቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01017692 ጥር 26 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-08884 የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሠረት ለተጠሪ ኃላፊ ነው ተብለው ለክርክሩ ምክንያት እንዲከፍሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በዚህ ችሎት መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.106535

ቀን 17/05/2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** አቶ ረዲ ተፈራ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ አቶ አብሹ በቀለ } የቀረበ የለም

2ኛ አቶ ዳመሳ ኤርጳዛ

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አዳሚ ቱሉ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪዎች በመ/ቁ. 21265 በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሬ ሳይወሰደበት ዳለቻ በሬ ወሰደሃል በሚል ጥቁር ጋሬ የሆነ በሬ ግምቱ 8000 (ስምንት ሺህ) የሚያወጣ እንደወሰደበት የራሱ በሬ ከሌላ ሰው ጋር አግኝቶ የወሰደ ቢሆንም በሬውን አልመለስም በሽማግሌዎች አማካይነት በሬው ለመመለስ በ26/12/2005 በተፃፈ ውል በ03/13/2006 ዓ/ም በሬውን ለማቅረብ ተስማምተው እንደፈረሙ፤ 2ኛ ተጠሪም 1ኛ ተጠሪ በሬው የማይመለስ ከሆነ ዋስ እንደሆነ፣ በተጨማሪነትም 1ኛ ተጠሪ 27/08/2006 ዓ/ም በተፃፈው ውል ብር 6000.00 /ስድስት ሺህ/ ለመክፈል ፈርሞ የተቀበለ ቢሆንም ገንዘቡን ባለመክፈሉ ለመክሰስ እንደተገደደ በመሆኑም የበሬው ግምት 8,000.00 ብር ብድር 6,000.00 ከኪሰራና ወጪ ጭምር እንዲከፈለው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በቀረቡት የመከላከያ መልስ 1ኛ ተጠሪ በሬውን አለማግኘቱን በሽማግሌዎች ፊት ተስማምተናል በማለት ያቀረበው ውል በሕግ ተሟልቶ የቀረበ አይደለም፤ 03/13/2006 ዓ/ም የተባለው ቀን ስላልደረሰ አመልካች መክሰስ አይችሉም፤ የብድር ውሉ የተባለው በሐሰት

www.abyssinialaw.com

የተዘጋጀ ሰነድ ነው፤ በ2006 ዓ/ም ይበል እንጅ በየትኛው ቀን እንደሚከፈል ስለማይገልጽ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ይዘት ያለው መልስ አቅርበዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ክሱ የመክፍያ ጊዜ የተባለው ቀን ከመድረሱ በፊት እንደቀረበ ዋስ ተጠያቂ የሚሆነው ዋና ተበዳሪ አልከፈልም የሚል ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የገንዘብ ብድር ውል ስምምነት አለ ወይስ የለም? ተጠሪዎች የበሬውን ግምት መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በአመልካች የቀረበው የውል ሰነድ ሰርዝ ድልዝ ስላለው አመልካች ኦርጅናሉ እንዲያቀርብ የታዘዘ ሲሆን በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካች ኦርጅናል ነው ያለውን ውል ያቀረበ ሲሆን አመልካች መጀመሪያ ክስ ሲያቀርብ በ26/12/2005 ዓ/ም በተጻፈ ውል በማለት የተገለጸ ሲሆን እንደማስረጃ በቀረበው ውል ላይ ደግሞ በ2006 ዓ/ም የሚለውን በመሰረዝ 2005 ዓ/ም እንዳደረገ በችሎቱ ትዕዛዝ ከቀረበው ኦርጅናል ውል መረዳት እንደተቻለ፤ 2ኛ ተጠሪ በተመለከተውም 1ኛ ተጠሪ በሬው ስለ አገኘ የራሴ በሬ እንዲመስል ፈርሞልኛል የሚለው ከመነሻው የሰው ንብረት የወሰደ ሰው በሽማግሌ ታምኖበት ሳይገደድ ወሰደ የተባለው ንብረት ከከፈለ በኃላ እንዲመልስልኝ በማለት መስማማት የህግ መሠረት ያለው አለመሆኑን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ውል እንደኛው በምስክሮች የተፈረመ አለመሆኑን ውሉ ነው የተባለው በአመልካች ተሰርዞ የቀረበ ስለ መሆኑ በመረጋገጡ አመልካች በቀረበው ክስ ማስረጃ መስማት ሳያስልግ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች በነጻ አሰናብተዋል (ወስነዋል)፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከከራከረ በኃላ ኦርጅናል ውሉ የተሰረዘ ነገር እንዳለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማረጋገጡ ውሉ የተፃፈበትና የሚጠናቀቅበት ቀን ወደ ኃላ የሚቆጥር መሆኑ ሲታይ ውሉ የእውነት እንደልሆነ የሚያሳይ እና የህግ መሰረት የሌለው ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ ስህተት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ አመልካች በጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፀመዋል በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀበይነት አለገኘም፡፡ የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፀመ ያለውን ስህተት በመዘርዘር ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታው መስረታዊ ይዘትም በክሱ የጠቀሰቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ክሱ ውድቅ መደረጉ በሕጉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ጥሪ የተደረገላቸው ቢሆንም ባለመቅረበቸው መጋቢት 09 ቀን 2007 ዓ/ም መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

www.abyssinialaw.com

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ውሎች ላይ ስማቸው የተጠቀሱ እማኞች ቀርበው ስለ ውሎቹ መፈፀም አለመፈጸም መኖር ያለመኖር ምስክርነታቸው ሳይሰጡ ውሉ ስርዝ ድልዝ አለበት ተብሎ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፤

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች የተወሰደባቸው በሬ እንዲመለስላቸው በብሄረሰቡ ሽማግሌዎች የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ እና 1ኛ በብድር መልክ የወሰደው ገንዘብ እንዲከፍል፤ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ በሬ ከመመለስ ጋር በተያያዘ የተገበው ግዴታ ላይ ዋስ ስለመሆኑን ነው፡፡ ተጠሪዎች የቀረበባቸው ክስ ክደው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአመልካች እና ተጠሪዎች ተደረገ የተበለው ውል ስርዝ ድልዝ አለበት በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች ክሱን ለማስረዳት የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በመዘርዘር ያቀረበ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሳኔው ላይ እንዳስፈረው ውሉ የተሰረዘ በመሆኑ በምስክሮች ማረጋገጥ ወይም ማጣራት አይቻልም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱን መረዳት ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የስው ምስክሮች ለመስማት አልገደድም ለማለት እንደመነሻ የወሰደው የፍ/ሕ/ቁ. 2005 በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ቃላት በሰው ምስክር ለማስረዳት አይቻልም የሚል ይዘት ያለው ድንጋጌ ነው ከሚል እሰቤ ስለመሆኑ ተረድተናል፡፡ ይሁንና አመልካች እንዲሰሙለት እየጠየቀ ያለው በሁለቱም ውሎች ላይ እማኞች ናቸው ተብለው የፈረሙ ምስክሮች እንጅ በውሉ ላይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ምስክሮች አይደሉም፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ክልከላ የሚያደርገው አከራከሪ በሆነው ውል ላይ ይዘቱ ላይ ምስክሮች እንደይሰሙ እንጅ በጉዳዩ ላይ እማኞች በመሆን የፈረሙ ምስክሮች ካሉ ስለ ውሉ መኖር አለመኖር እንዳያስረዱ ክልከላ ስለማደረጉ ህጉ አያሳይም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ውል ላይ አልተማመኑም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክሱን ለማስረዳት የጠቀሳቸው የሰው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ ሊመረመርሉት ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቱ በአመልካች የቀረቡ ምስክሮች ከሰማ በኃላ የሰጡት ቃል በህጉ አግባብ መዝኖ ምክንያት በመስጠት ሊቀበለው ወይም ላይቀበለው ይችላል፡፡ ነገር ግን የአመልካች ምስክሮች አከራካሪ በሆነው የውል ጉዳይ ምን ዓይነት ምስክርነት እንደሚሰጡት ሳይታወቅ ከወዲሁ ሳይሰሙ በጽሁፍ ሰነድ ላይ ብቻ ተመስርቶ የአመልካች ክስ ውድቅ ማድረጉ በህጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአመልካች ምስክሮች እንዲሰሙ ካልተደረገ ያቀረበው ክስ ለማስረዳት የሚቸገር ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች እና ተጠሪዎች የሚከራከሩበት መሰረታዊ የውል ይፈጸምልኝ ክስ በተጠሪዎች የተከደ በመሆኑ ግራ ቀኙ በተካካዱበት ነጥብ ላይ አመልካች ማስረጃ የማቅረብ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ በአመልካች የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ያቀረበቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች በሕጉ አግባብ ተስምተው የሰጡት ቃል ይዘት ተመዝኖ በምክንያት የተደገፈ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ወረዳ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በየደረጃው በይግባኝ እና በሰበር የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክሱን የማስረዳት ማስረጃ የማስማት መብቱ አልፈው ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 238 (1) 255፣ 257፣259 እና 261 መሰረታዊ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገነዘበ ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ የአመልካች የመደመጥና ክሱን የማሳረዳት መብቱ ያለከበረ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በዚሁም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዳሚ ቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 21265 በ11/10/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/ቁ. 38245 በ14/01/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 187691 በ02/03/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአዳሚቱሉ ወረዳ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 21265 በመክፈት በፍርድ ይዘቱ በተገለጸው መንፈስ አመልካች በክሱ የጠቀሳቸው እና ለክርክሩ ምክንያት በሆኑ ውሎቹ ላይ እማኞች የነበሩ ግለሰቦች ቀርበው ግራ ቀኙ እያከራከሩ ያለው ውል መፈጸም ያለመፈጸሙን ውሉ መኖር ያለመኖሩን ምስክርነታቸው እንዲሰጡ ከተደረገ በኃላ የሰጡት ቃል በህጉ አግባብ ተመዝኖ ጉዳዩ ተገቢ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 343 (1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ

**መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር 112328

የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመለካች፡- ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይ - ኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ ዘለቀ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም አሸቱ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመኪና ሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም ባወጣው የመኪና ሽያጭ ጨረታ ላይ ተሳትፈው የታርጋ ቁጥር 3-18353 ኢት የሆነውን መኪና በብር 127,915.55 (አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ አምስት ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም) የገዙ ቢሆንም ለስም ዝውውሩ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሸከርካሪውን ማጣሪያ ክሊራንስ እንዲመጣ መጠየቃቸውንና ተጠሪ አመልካችን በዚህ አግባብ እንዲፈፀም ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም አመልካች ለማስጠንቀቂያው በሰጠው ምላሽ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስም ዝውውሩ እንዲፈጸም ቃል የገባ ቢሆንም አለመፈጸሙን፣ በዚህ መሰረት አመልካች መኪናውን ለገዛው ተጠሪ ስም ለማዛወር የሚረዱ ሰነዶችን ለተጠሪ የማስረከብ ግዴታውን ያልፈፀመ እና የመኪናው የኪራይ ገቢ ዋጋ በቀን ገቢ ተሰልቶ ብር 205,000.00(ሁለት መቶ አምስት ሺህ) ጥቅም የቀረባቸው መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ለተጠሪ መኪናው ከግብርና ታክስ እዳ ነፃ የሆነበትን የክሊራንስ ሰነዶች እንዲያስረክብ፣ በቀን የታጣ ገቢ ብር 205,000.00 እንዲከፍል፣ ሰነዶቹን እስከሚያስረክብ ድረስ ያለውን ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅላቸው ይወሰን ዘንድ

www.abyssinialaw.com

ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም፡- ተጠሪ አከራካሪውን መኪና ከአመልካች በጨረታ መግዛታቸውን ሳይክድ በመኪናው ላይ ምንም አይነት እዳና እገዳ የሌለበት መሆኑን፣ መኪናው ሲሸጥም የመኪናውን የባለቤትነት ደብተር/ሊብሬ/፣ ሌሎች ማስረጃዎችን በሙሉ ከነመለያው ለተጠሪ ማስረከቡን፣ ለሚመለከተው አካልም ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸው ነሀሴ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ደብዳቤ የፃፈላቸውና ተጠሪም ግልባጩን ተረክበው የወሰዱና ለፕሮክጀት ስራ ተቋራጭ ነፃ በገቡ ማስረጃዎች ጋር በተያያዘ ከኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በተፈጠረ ችግር ኃላፊነትት የለብንም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ አመልካች ለተጠሪ መኪናው ከግብርና ታክስ እዳ ነፃ የሆነበትን የክሊራንስ ሰነዶች እንዲያስረክብ፣ በቀን የታጣ ገቢ ብር 205,000.00 እንዲከፍል፣ ሰነዶቹ እስከሚያስረክብ ድረስ ያለውን ኪሳራ ደግሞ ተጠሪ የመጠየቅ መብት የተጠበቀ መሆኑን ገልፆ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት፡- ለክሱ መነሽ የሆነውን መኪና አመልካች በግልጽ ጨረታ ሽጦ የስም ዝውውር በተመለከተም በጨረታው መመሪያው መሰረት በሕግ የሚፈለገውን ተግባር ሁሉ አመልካች ድርጅት ፈጽሞ እያለ ንብረቱ ለስም ዝውውር ምንም አይነት እዳና እገዳ ሳይኖርበት የሕግና የፍሬ ነገር መሰረት በሌለበት አግባብ አመልካች ለክሱ ኃላፊ ተደርጎ የቀን ገቢ ብር 205,000.00 እና የጠበቃ አበል እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች አከራካሪውን መኪና ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ለተጠሪው አስረክቢያለሁ ብሎ ተከራክሮ ባለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያላስረከበ መሆኑን አመልካች አልካደም በሚል ምክንያት አመልካች ግዴታውን አልፈፀመም በማለት የተሠጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ባወጣው የመኪና ሽያጭ ጨረታ ላይ ተጠሪ ተወዳድረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ተሸከርካሪ መግዛታቸው ግራ ቀኙን ያላከራከረ ነጥብ

www.abyssinialaw.com

መሆኑን፣ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት ለስም ዝውውሩ አስፈላጊ ከሆኑት ሰነዶች መካከል መኪናው እዳና እገዳ የሌለበት መሆኑን የሚገለፅ የክሊራስን ሰነድ ለተጠሪ የመስጠት ግዴታ አመልካች ያለው መሆን ያለመሆኑን ላይ ስለመሆኑ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ ዋነኛ የዳኝነት ጥያቄ በውል ገዝቼዋለሁ የሚሉትን መኪና ስመሃብት በስማቸው እንዲመዘገብ መኪናው እዳና እገዳ የሌለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድ በአመልካች ይሰጠኝ ሲሆን በስሜ እንዲመዘገብ ለማድረግ አስፈላጊ ሰነዶች ከአመልካች አልተሰጠኝም የሚሉት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስለ መኪናው ከእዳና እገዳ ነፃ መሆን የሚያሳይ የክሊራንስ ሰነድን ነው፡፡ አመልካች የመኪናውን የባለቤትነት ደብተር/ሊብሬ/ እና ሌሎች ማስረጃዎችን በሙሉ ከእነመለያው ለተጠሪ ማስረከቡን ገልፆ ለአቀረበው ክርክር ተጠሪ ማስተባበያ ክርክርና ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ አሳያስም፡፡ አንድን ንብረት የሸጠ ሰው በፍትብሐር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሸጠውን ንብረት ባለሀብትነት ለገዥው የማዛወር ግዴታ ያለበት ሲሆን ይኸም የሻጭ የንብረቱን ባቤትነት ለገዥ የማዛወር ግዴታ በምን መልኩ መፈፀም እንደሚገባው ህግ አውጭው ‹‹ሻጩ የሸጠውን ነገር የማያስነካ መብት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ለመፈፀም ግዴታ አለበት›› በማለት በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2281 በግልጽ ከደነገገው የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ የመኪናን ሽያጭ በውሉ መሠረት እንዲፈጽሙና ስመንብረቱን ለተጠሪ ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን መፈጸን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም የስም ሃብት ዝውውሩን ለማድረግ አስፈላጊ ተግባራት አልተከናወኑም የሚለው ገዥ እነዚህን በሻጭ ያልተከናወኑትንና የስመ ሃብት ዝውውሩን የሚያከናውን አካል ኃላፊነቱንና ተግባር ለመፈፀም የማያስችለው አስፈላጊ ተግባር ምን እንደሆነ እና አስፈላጊነቱን ማስረዳት መቻል አለበት፡፡

ከዚህ ውጪ ተገቢው ሰነድና ለሽያጩ መሰረት የሆነው ንብረት ርክክብ ተፈጽሞ እያለ ስመ ሃብቱ አልተዛወረልኝም በሚል ምክንያት ብቻ በሻጩ ላይ ክስ ማቅረብ እና ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡

ከተዋዋዮቹ አንዱ ወገን የውል ግዴታውን ያልፈጸመ እንደሆነ ሌላው ወገን እንደነገሩ አጋጣሚ ሁኔታ ውሉ እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብት እንዳለው፣ ካልሆነም ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ እንደሚችል ወይም ውሉ መፍረሱን ለሌላው ወገን ሊገልጽ የሚችል መሆኑን የፍ/ህ/ቁ/1771(1) የሚደነግግ ሲሆን በውሉ አለመፈጸም የተነሳ ጉዳት የደረሰበት ከሆነም ኪሳራ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 ያመለክታል፡፡ ውሉ ተዋዋዮቹ በአንድነት የሚፈጽሙትን ግዴታ (simultaneous performance) የሚጥል ሆኖ ከተገኘም ተዋዋዩ የተዋዋለበትን ግዴታ በውሉ እንደተመለከተው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው

www.abyssinialaw.com

ወገን ከውሉ ስምምነት የተነሳ እሱም በበኩሉ ያለውን ግዴታ ወዲያውኑ መፈጸም ወይም ለመፈጸም የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባው መሆኑን የፍ/ህ/ቁ/1757 ያስገነዝባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ሊከሱ የቻሉት የስመ ሃብቱን ዝውውር በሚያደርጉት እለት በመኪናው ላይ የእዳና እገዳ ነፃ መሆኑን የሚያሳይ የክሊራንስ ሰነድ ከገቢዎችና ጉምሩክ ተጠይቀው ይኼው ሰነድ በአመልካች ሊቀርብላቸው ባለመቻሉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የክሊራንስ ሰነድ ማቅረብ የአመልካች ግዴታ ስለመሆኑ የሚያሳይ የውል ግዴታ የሌለ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ሰነዱን ራሳቸው ለመውሰድ ያላስቻላቸው ምክንያት ስለመኖሩ ወይም የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ክሊራንስ የከለከላቸው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ ስመ ሃብቱን ለማዛወር የሚያስችለው አስፈላጊ ተግባር በአመልካች መከናወን ያለበት ስለመሆኑ ባላስረዱበት ሁኔታና አመልካች ደግሞ መኪናውንና አስፈላጊ ሰነዶችን ለተጠሪ ማስረከቡን ገልፆ በተከራከረበት አግባብ የስር ፍርድ ቤት አመልካች አስፈላጊ ሰነዶችን ያላስረከበ መሆኑን አልካደም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ለጉዳዩ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ይዘት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 235 እና 83 ድንጋጌዎች ይዘት ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አመልካች ነሐሴ 03 ቀን 2003 ዓ/ም በፃፈለት ደብዳቤ መነሻ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሂደው መኪናው ከእዳና እገዳ ነጻ ስለመሆኑ የሚያሳይ የክሊራንስ ሰነድ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 258 እና 259 ድንጋጌዎች ይዘት መሰረት ባላስረዱበት ሁኔታ አመልካች ለክሱ ኃላፊ መደረጉ ከማስረዳት ሸክም አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሸጠውን መኪና ስመንብረት (ባለሀብትነት) ለተጠሪ ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታና ሀላፊነት ስላለመወጣቱ ተጠሪ ባለስረዱበት ሁኔታ አመልካች ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶች ያላስረከበ መሆኑን አልካደም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነውን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 197988 በ19/09/2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137860 በ06/08/2007 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች ለገዛው ተሽከርካሪ ስመ ሃብት ዝውውር ያልፈፀመው አስፈላጊ ተግባር ስለመኖሩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2273 እና 2281 ድንጋጌዎች አግባብ ተጠሪ ስላላስረዱ አመልካች ለክሱ ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡

www.abyssinialaw.com

3. ለክርክሩ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112168

የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የሺ ትራንስፖርት /የሺ ትራንስፖርት የጭነት ማመላለሺያ ባለንብረቶች ማህበር/ ደምሴ ገበየሁ

ተጠሪ፡- አቶ እስክንድር ዘርፉ - ዳዊት አባተ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205919 በቀን 13/02/07 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 162749 በቀን 09/07/0227 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት መድረስን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ ሲሆን አመልካች 2ኛ ተከሳሽ እንዲሁም የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ትራንዚት ሎጀስቲክ አገልግሎት 1ኛ ተከሳሽ ሲሆኑ ጣልቃ ገብ የነበሩት ደግሞ ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በተከሳሾች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ ቶዮታ ያሪስ 998 ሲሲ. የሻንሲ ቁጥር VNKKG96320A001372 የ2005 ምርት ዋጋ ብር 3000 ዩሮ የሆነ ከቤልጂየም ኢንትዌፕ ወደብ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ ለሚጓጓዝ እና ለማስረከብ በሰነድ ቁጥር LAU538 ከ1ኛ

www.abyssinialaw.com

ተከሳሽ ጋር ውል የገባ ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር የማጓጓዣ ውል የሌለው ንብረትነቱ የ2ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ የሆነ የሠሌዳ ቁጥር 3-51671 ኢት/3-17327 ኢት ተሳቢ በሆነ ተሸከርካሪ ከጅቡቲ ወደ ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲጓጓዝ በደረሰ የእሳት ቃጠሎ ሙሉ ለሙሉ ወድማል ስለዚህ በመኪናው የጉዞ ሰነድ ላይ የተቀነሰውን ብር 87148.50 /3000ዩሮ/፣ ለጭነት ብር 23546/1272.76 ዩ.ኤስ.ዲ/ እና ብር 3862.08፤ ለኢንሹራንስ ብር 235.60 እንዲሁም የተቀረጠ ጥቅም ብር 50000 በድምሩ ብር 164792.24 እንዲከፍሉኝ የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የኢትዮጵያ ባህር ትራንዚት ሎጀስቲክ አገልግሎት በሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኪና ከቤልጂየም ኢንትዋፕ ጅቡቲ ወደብ ለማድረስ በተሰማማው መሠረት ያደረሰ እና ከተጠሪ ጋር በነበረው ውል አጓጓዡ ሁሉንም ወይም ከፊሉን የሚጓጓዙ ሥራ በውሰታ ለሌላ ማስተላለፍ የምንችል መሆኑ ስለተገለፀ ለ2ተኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ያስተላለፈ መሆኑን አመልካች ተረክቦ በሚጓጓዝ ላይ እያለ በደረሰ ቃጠሎ መኪናዋ ሙሉ ለሙሉ መውደሚን መኪናው የተጓዘው በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል በመሆኑ በአዋጅ 348/44 መሠረት ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው ስለዚህ ክስ ሊያቀርብብን የሚያስችል መብት የለውም ኃላፊ ነው ከተባልንም ልንጠየቅ የሚገባው በዕቃው ክብደት ልክ በኤስ.ዲ.አር ወይም በጥቅል ሲሆን ይህም ብር 63900 ነው የሚሆነው እንዲሁም ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ የመድን ሽፋን የሰጡ በመሆኑ ወደ ክርክሩ ይግቡልኝ ብሏል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከከሳሽ ጋር ውል የገባው 1ኛ ተከሳሽ በመሆኑ ኃላፊነት የለብንም በከሳሽ መኪና ላይ ጉዳት አልደረሰም፣ መኪናው ጉዳት የደረሰበት በአመልካች መኪና ሳይሆን በደረሰ ቃጠሎ ምክንያት ነው ይህ ደግሞ ከአቅም በላይ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ የመኪናው ዋጋ የመድን ውል ሲገባ የተገለፀው ብር 76868.88 እያለ ተጠሪ ያቀረበው ያለአግባብ ነው፡፡ በማጓጓዝ የከፈለው ምንዛሬ መሠራት ያለበት መኪናውን ለመጫን በተከፈለ ቀን ነው ተጠሪ አጣሁ ያለውን ጥቅም በተመለከተም የቀረበ ማስረጃ የለም አለ ቢባልም መተካት ያለበት መድን ሠጪው ነው ብሏል፡፡ ፍርድ ቤቱም ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ እና አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አዞ መልሳቸውን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ጉዳት ደረሰበት ለተባለው መኪናም የመድን ሽፋን ያልሠጡ መሆናቸውን የገለጹ መሆኑን መዝግቧል፡፡ እንዲሁም የአሁን አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 256 መረት እንዲቀርብ ጠይቆ መኪናው የተቃጠለበትን ሁኔታ የሚገልይ የፌደራል ፖሊስ የምርመራ ዘርፍ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ለቃጠሎው መፈጠር ምክንያት የሆነው የተሸከርካሪው ተሳቢ የፊት የግራ ጉማዎች የውስጥ ጐማ በመፈንዳቱ ምክንያት ቸርኬው ከመሬት ጋር በመጋጨቱ የተፈጠረ እሳት ከተቀጣጣይ ነገሮች ጋር መያያዙ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ቀርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአዋጅ 547/99 አንቀጽ 36 ሊጋዥ የማጓጓዝን ሥራ በአንድ ውል የሚገዛ ሆኖ በተለያዩ አጓጓዦች በመቀባበል የሚፈጽሙ ከሆነ የመጀመሪያው

www.abyssinialaw.com

አጓጓዥ በገባው የመጓጓዣ ውል መሠረት 2ኛ አጓጓዥና ተከታዮች የመጓጓዥያ ሰነዱንና ውሉ የሚያስከትለውን ግዴታ በመቀበላቸው የተነሳ የማጓጓዥያ ውሉ ተዋዋይ ወገን ተደርገው በመቆጠሩ እያንዳንዱ አጓጓዥ በተናጠል ስለአጠቃላዩ የማጓጓዝ ስራ ኃላፊነት የሚኖርበት መሆኑ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የነበረው የማጓጓዥያ ውል ስምምነት መሠረት ከጅቡቲ ወደብ ሞጆ ደረቅ ወደብ ድረስ የማጓጓዝ ሥራ ለአመልካች መስጠቱን በግራ ቀኙ ወይም ውልም ሆነ በህጉ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ መኪናውን ለአመልካች ካስረከበ በኋላ የተፈጠረ አደጋ በመሆኑ የመጨረሻ ኃላፊነት የሚወድቀው በ2ኛ ተከሳሽ ነው፡፡ አመልካች የማጓጓዝ ሥራውን በሚረከብ ጊዜ እንደውሉ አካል የሚቆጠር እና ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ከተረከበ በኋላ ለተፈጠረው አደጋ አመልካች ኃላፊ ነው በማለት የኃላፊነት መጠን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 547/99 አንቀጽ 27/3/ እና 29 መሠረት መኪናው የተገዛበት ብር 87148.5፣ የመኪናውን ማስጫኛ እና የኢንሹራንስ ክፍያ በውላቸው አንቀጽ 5/2/ መሠረት ለጭነት ብር 23546 ለኢንሹራንስ ብር 235.60 በድምሩ ብር 107930.10 እንዲሁም መኪናው የተገዛበትን ዋጋ ክስ ከቀረበበት 12/04/2005 ዓ.ም ጀምሮ 9% ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል 1ኛ ተከሳሽ እና ጣልቃ ገቦች ከክሱ በነፃ ተሰናብተዋል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለመቀበል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም በክሱ ላይ የተገለፀሙ መኪና ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 አንቀጽ 10 እና 22 መሠረት ኃላፊነት የለብንም ጉዳት የደረሰበት መኪና ሙሉ በሙሉ ከነወለዱ የምንከፍል ከሆነ ጉዳት የደረሰበትን መኪና /ሰልባጁን/ እንዲመለስልን ሊወሰን ይገባ ነበር የሚል ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ እሳቱ የተፈጠረው የመኪናው የውስጥ ጐማ /ከመነዳሪ/ ፈንድቶ ቸርኬው ከመሬቱ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት መሆኑ በባለሙያ ከመረጋገጡ አንጻር ክስተቱ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሥር የሚሸፈን መሆን አለመሆን እና ጉዳት የደረሰበትን መኪና ሙሉ ዋጋ አከፋፈል የመኪናውን ቅሪት አካል /ሰልባጅ/ ተመላሽ እንዲሆን በቃል ክርክር ወቅት ጠይቀው መታለፉን ለመመርመር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ለሰጠው መልስ አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማስረጃ የለም ከፍ/ህ/ቁ 1793 ከተዘረዘረው ምክንያት ውስጥም የሚካተት አይደለም፡፡ የደረሰው ጉዳት ለጉዞ ከመሠማራት በፊትም ሆነ በጉዞ ላይ እያለ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ በተለይም የእሳት መከላከያና ማጥፊያ ቁሳቁስ በአጓጓዥ ተሽከርካሪ ውስጥ አለመኖር ወዲያውኑ እንዲጠፋ አላደረገም፡፡ ጐማው ሲፈነዳም በጥንቃቄ አቁሞ መቀየር ሲገባው መሄዱ ቸልተኝነቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል

www.abyssinialaw.com

የተሸከርካሪ አካልን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት አልተነሳም ዳኝነትም አልተከፈለበት፣ አመልካች ይህንን ቅሪትም አላስረከበኝም ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ይጽናልኝ ብሏል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ አጠቃላይ ሂደት ከለይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ፍርድ እና ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንፃር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የክርክሩ አጠቃላይ ሂደትም የሚያስገነዝበው ተጠሪ አንድ ቶዮታ ያሪስ 998 ሲሲ የሻንሲ ቁጥር VNKKG96320a001372 የ2005 ምርት የሆነች መኪና ከቤልጅየም ኢንትዊፕ ወደብ እስከ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝና ለመረከብ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው ከኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ትራንዚት ሎጅስቲክ አገልግሎት ጋር ውል ገብተዋል፡፡ ይህ 1ኛ ተከሳሽ በውላቸው ላይ ሁሉንም ወይም ከፊሉን የማጓጓዝ ሥራ በውል ለሌላ ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በተስማሙት መሠረት ከጅቡቲ ወደብ እስከ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ እንዲያጓጉዝ ለአሁን አመልካች ጅቡቲ ወደብ አስረክቧል፡፡ አመልካች በዚሁ መሠረት ሲያጓጉዝ የአጓዡ ተሸከርካሪ ተሳቢ የፊት የግራ ጐማዎች የውስጥ ጐማ በመፈንዳቱ ምክንያት ቸርኬው ከመሬት ጋር በመጋጨቱ በተፈጠረ እሳት መኪናው መቃጠሉ ሲሆን ይህም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ናቸው፡፡ አመልካች አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 547/1999 አንቀጽ 10 እና 22 ኃላፊነት የለብኝም የሚል ነው፡፡ በየብስ የዕቃ ማጓዝ ስራን ለመደንገግ ተሻሽሎ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 547/1999 ዓ.ም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ "በማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ወደ ጠቅላላ ህጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላ ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች መምራት የግድ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በፍ/ህ/ቁ 1792 ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ይህም ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለዕዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነበት አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመው ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለዕዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈጻጸም ከባድ የሆነ ወጪ በባለዕዳው የሚደርስ ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተልክቷል፡፡

ስለሆነም በእነዚህ የህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው በባለዕዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የሚያስችል

www.abyssinialaw.com

ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደርግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገት ደራሽ ቢሆንም እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይም የሥር ፍርድ ቤቱ አመልካችን ኃላፊ ያደረገው የክሱ ምክንያት የሆነው መኪና በእሳት ቃጠሎ ምክንያት ሊወድም የቻለው የመኪናው የውስጥ ጐማ /ከመነዳሪ/ በመፈንዳቱ እና ቸርኬው ከመሬቱ ጋር ሲጋጭ ለተፈጠረ እሳት ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ይህ አንዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው የማይችል በመሆኑ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጠረ ነው የሚል ነው፡፡ ይሁንና የተሽከርካሪው አንዥ የሆነው አመልካች ተሽከርካሪውን በዚህ አይነት ሥራ በሚያሠማራበት ወቅት ምንም አይነት ቴክኒካዊ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ተሽከርካሪው የሚጓዘውን ርቀት የአየር ሁኔታ ሌሎች በሚያረጋግጥበት ጊዜ ጐማውን ማየት እና ደረጃውን መገመት የሚቻለው ሲሆን በጉዞ ላይም ችግሩ በድንገት ደርሷል ቢባል እንኳን ሊቆጣጠረው የሚችል እና ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ነው ተብሎ ሊገመት የሚችል መሆኑ የፖሊስ ቴክኒካል ማስረጃን የስር ፍርድ ቤት የመዘነበት አግባብ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አደጋው የደረሰው የአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም የማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሠረታዊ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ጉዳት የደረሰበትን መኪና ሙሉ ለሙሉ ከነወለዱ የምከፍል ከሆነ ጉዳት የደረሰበትን መኪና /ስልባጁን/ እንዲመልስልኝ ሊወሰን ይገባ ነበር በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አመልካች ይህንን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤት አንስተው የተከራከሩበት ሁኔታ እንደሌለ ተጠሪ የገለፀ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት መዝገብም እንደሚያስገነዝበው አመልካች በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት ትራንዚት ሎጅስቲክ የተጠሪ ንብረት የሆነውንና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን ቶዮታ ያሪስ መኪና ጅቡቲ ወደብ መረከባቸውንና ወደ ኢትዮጵያ ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲያጓጉዙ በእሳት ሙሉ ለሙሉ መውደሙን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጉዳት ደረሰበት የተባለው መኪና በእሳት መውደሙን አሊያም በአመልካች እጅ መሆኑን የሚያመለክት ከመሆኑም ባሻገር በስር ፍ/ቤትም አልተነሳም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በህጉ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሠረት ሊያነሳቸው የሚገቡ እና ያላነሳቸውን መከራከሪያዎች በራሱ ምክንያት ሳያቀርብ እና ተጠሪም ባልተከራከረበትና ባልተነሳ ሁኔታ በይግባኝ ወይም በዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329/1/ እና 182/2 ድንጋጌዎች ዓላማ ጋር የማይጣጣም ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ያቀረቡት አቤቱታ ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ እና ትእዛዝ መሠረታዊ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 205919 በቀን 13/02/07 የሰጠው ፍርድ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 162749 በቀን 04/07/2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳት የደረሰበትን መኪና ለተጠሪ ስለማስረከባቸው እና የመኪናውን ቅሪት /ሰልባጅ/ አስመልክቶ ክስ ለማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ ትእዛዝ የስር ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 225335 የተጀመረው አፈጻጸም እንዲታገድ የተሠጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.99447

.ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች:-** አቶ ተፈራ ጣሰው - የቀረበ የለም

**ተጠሪ:-** ወ/ሮ ፈንታዬ በንቲ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ በተሽከርካሪ መገልበጥ ምክንያት ከደረሰ የሞት አደጋ ጋር ተያይዞ የተነሳ የጉዳት ካሳ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የምዕራብ ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ቤት ከሳሽ በመሆን ክሱን የመሰረቱት ተጠሪ ናቸው፡፡ ተጠሪ ክስ የመሰረቱት በአሁኑ አመልካችና አቶ አስማማው ደረጀ በተባሉ ግለሰብ ሲሆን ክሱም በ15/03/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ነው፡፡ የክሱ ይዘት ባጭሩ:- ንብረትነቱ የተከሳሾች የሆነና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-30038 ኢ.አ. የሆነ አይሱዚ ተሽከርካሪ በ04/05/2002 ዓ.ም. በደረሰ አደጋ በመገልበጡ ከጌዶ ወደ አዲስ አበባ ተሳፍረው ሲጓዙ በነበሩት የከሳሽ ባለቤት አቶ እንዳሉ ባይሳ ላይ የሞት አደጋ እንደደረሰ፣ ባለቤታቸው በንግድ ስራ ያገኙት ከነበረው ገቢ ከሳሽን እንዲሁም የ 4 እና የ 2 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ሁለት ልጆቹን ያስተዳድር እንደነበረ እና በሞቱ ምክንያት በመተዳደሪያ ረገድ ጉዳት እንደደረሰባቸውና በጉዳቱ ጊዜ ደግሞ ወጪ ያወጡ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ በድምሩ ብር 349,192.61(ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከስልሳ አንድ ሳንቲም)፣ የጠበቃ አበል 10% እና ለክሱ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ተከሳሾች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ 2ኛ ከሳሽ የነበረውን ግለሰብ ከተጠሪ ጋር በእርቅ በመጨረሳቸው ምክንያት ከክሱ ውጪ የሆኑ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ግን ወደ ክርክሩ ተጠርተው በሰጡት መልስ ጉዳዩ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ከነበሩት የመኪናው የጋራ ባለሃብት ጋር በእርቅ በማለቁ ክስ

www.abyssinialaw.com

ሊቀርብበት እንደማይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከአስቀደሙ በኋላ በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ ሟቹ ተሽከርካሪውን ባለው ግንኙነት ለምኖ በነጻ የተሳፈረና የሄደ በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊነት እንደሌለባቸው፣ የሟቹ ገቢ መጠንም ተቀባይነት እንደሌለውና የተቋረጠ ገቢ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአሁኑ አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙንና ማስረጃዎቻቸውን ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን የኃላፊነቱን መጠን በተመለከተም በትክክል ሟቹ ያስገኙ የነበረው የቀን ገቢ በተጠሪ ምስክሮች እንደተገለፀው ያለመሆኑን ደምድሞ መካከለኛ ያለውን የቀን ገቢ በብር 20.00 ፍርድ ቤቱ ይዞ እና ሟች ለ15 አመታት ሊሰሩ ይችሉ ነበር በማለት በድምሩ 100,800.00(አንድ መቶ ሺህ ስምንት መቶ ብር ) ለተቋረጠ ገቢ ወስዶና በአደጋው ምክንያት የወጣውን ወጪ ደግሞ ብር 6000.00(ስድስት ሺህ)፣የሞራል ካሳ ብር 1000.00 በመያዝ በድምሩ ብር 107,800.00(አንድ መቶ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ብር) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች ለክሱ ኃላፊ መባላቸው በአግባቡ መሆኑን፣የኃላፊነት መጠንን በተመለከተ ግን በተጨባጭ ይገኝ የነበረው ገቢ የሚያስቸገር መሆኑንና ተጠሪ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ከነበሩት የመኪናው የጋራ ባለሃብት ጋር ባደረጉት የእርቅ ስምምነትም ብር 14,000.00 የተከፈላቸው መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባትና በርትዕ መወሰን ተገቢ መሆኑን ገልጾ ብር 56,000.00 (ሃምሳ ስድስት ሺህ) እንዲከፈላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ግንኙነት የትራንስፖርት ግንኙነት መሆኑን፣ ግንኙነቱ የትራንስፖርት ቢሆንም በዚህ ረገድ ያለው ሕግ ስለ ካሳ የሚደነግገው ሁኔታ ያለመኖሩን ጠቅሶ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2095 ድንጋጌ መሰረት ካሳው መሰላት እንደአለበት፣ በዚህ አግባብ ሲሰላም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የካሳ መጠን ውሳኔ መኪናው የጋራ ባለሃብትነት የተቋቋመበት መሆኑን ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሰጠ መሆኑን መገንዘቡን ዘርዝሮ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የተጠሪ ባለቤት የሆኑት ሟች ከአመልካች ጋር የጥቅም ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ለሞት አደጋው ኃላፊ መደረጋቸው ያላግባብ መሆኑን፣የትራንስፖስርት ግንኙነት ነበር ከተባለም የካሳ መጠን በንግድ ሕጉ መወሰን ሲገባ ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት አድርጎ መወሰኑ ያላግባብ መሆኑን፣ እና አደጋውን አደረሰ የተባለን መኪና አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በጋራ

www.abyssinialaw.com

ያፈሩት መሆኑና ይኼው የጋራ ባለሃብት ደግሞ ከተጠሪ ጋር በአደረጉት እርቅ መሰረት ብር 14,000.00 ከፍለው እያለ ክሱ መቀጠሉ ያላግባብ መሆኑን፣ ክሱ መቀጠሉ ተገቢ ነው ከተባለም አመልካች ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉት በድርሻቸው መጠን መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍርድ ውሳኔ እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው ጭብጥ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካቹን ኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን ለመወሰን ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረጉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት የሆነው አይሱዙ ተሽከርካሪ ተገልብጦ በስር በተጠሪ ባለቤት ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ የጭነት ማመላለሻ መሆኑ እና ሟችም የእህል ነጋዴ ሁነው በተሽከርካሪው ሲጓዝ የነበሩት ከመኪናው የጋራ ባለሃብቶች ጋር የጥቅም ግንኙነት ሳይኖር ስለመሆኑ በአመልካች በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የተሽከርካሪው የጋራ ባለሃብት የሆኑት የአሁኑ አመልካች ሟቹ ከእህል ንግድ ጋር ተያይዞ በነበራቸው የመጓጓዣ ውል መግባታቸውን የሚያመለክት ሲሆን የማጓጓዝ ውል ማለት አጓዡ ዋጋ በመቀበል ሰውን፣ ጓዝን እና ዕቃዎችን ከተወሰነ ስፍራ ለማድረስ ግዴታ የገባበት ስምምነት ማለት መሆኑ በን.ሕ.ቁ. 561 ተመልክቷል፡፡ የዚህ ዓይነቱን ውል የገባ አጓዡ መንገደኛው በመንገድ ላይ ስለሚደርስበት መዘግየት፣ እንዲሁም በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሳፈርበትና ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም የሕይወት ማለፍ ኃላፊ መሆኑ በን.ሕ.ቁ.595 የተመለከተ ሲሆን በን.ሕ.ቁ. 599 በተመለከተው መሰረት ጉዳቱ የደረሰው አጓዡ በፈጸመው ተግባር ወይም ባደረገው ጉድለትና እንዲሁም ይህ ተግባርና አደጋ ጉዳት ሊያደርስ ወይም ሊፈጥር የሚችል መሆኑን እያወቀ በጥንቃቄ ጉድለት መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የተጎዳው ማንኛውም ዓይነት መንገደኛ ቢሆን አጓዡ በኃላፊነት ለአንድ መንገደኛ የሚከፍለው የካሳ መጠን ከብር 40,000 እንደማይበልጥ በዚሁ ሕግ በቁጥር 597(1) ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ተሽከርካሪው ተገልብጦ በባለቤታቸውን እና በልጆቻቸው አባት ላይ የሞት አደጋ ማድረሱን ከመግለጽ በስተቀር ለመገልበጡ በምክንያትነት የሚጠቀስ

www.abyssinialaw.com

በአሽከርካሪው ወይም በተሽከርካሪው ባለቤት የተከሰተ ጥፋት፣ ቸልተኝነት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት ስለመኖሩ የገለጹት ነገር ያለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ ለደረሰው አደጋ ካሳው በንግድ ሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ከፍ ብሎ ሊወሰንልኝ ይገባል የሚል ከሳሽ አደጋው የደረሰው በአንዣ ወይም የአንዙ ሰራተኛ በሆነ ሰው ጥፋት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ግን አደጋው የደረሰው በአንዣ ወይም በሰራተኛው ጥፋት ወይም ጉድለት ምክንያት ስለመሆኑ የተጠሪ የክስ ማመልከቻ አይገልጽም፡፡ ስለሆነም የአመልካችና የተጠሪ ባለቤት ግንኙነት የመጓጓዣ ውልን መሰረት ያደረገ ነው ከተባለና በን/ሕ/ቁጥር 599 አግባብ አደጋው መድረሱ እስካልተረጋገጠ ድረስ በዚህ አይነት ግንኙነት ለሚደደርሰው የሞት አደጋ የካሳ መጠን ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዛው የህግ ክፍል የተመለከቱት የካሳ አተማመን ድንጋጌዎች መሰረት ሊሆኑ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡፡

የካሳው መጠን መወሰን የሚገባው በንግድ ህጉ በተመለከተው ጣሪያ ነው፡፡ቀደም ሲል በውሳኔው ላይ እንደተገለጸው በንግድ ሕጉ በቁጥር 597 ድንጋጌ መሰረት የአመልካች የኃላፊነት ጣሪያ በብር 40,000 የተገደበ ሲሆን በስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ የመኪናው የጋራ ባለሃብት ነው፡፡ አመልካችና እኚህ ግለሰብ በመኪናው ላይ ያላቸው ድርሻ የሚበላለጥ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ ሃላፊነቱ እኩል ሊካፈሉት የሚገባ ነው፡፡ የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር ያደረጉት እርቅ አመልካች ስምምነታቸውን የሰጡ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለአመልካችም ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብም የለም፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የካሳ መጠን ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ) ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪ ከአደጋው ጋር ተያይዞ ያወጡት ወጪ በማስረጃ የተረጋገጠውን ገንዘብ ብር 6000.00 ግማሹን ብር 3000.00(ሶስት ሺህ) አመልካች ለተጠሪ ሊተኩላቸው የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካች በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የመጓጓዣ ውል ተብሎ ከተደመደመ በኂላ የካሳው መጠን ሊሰላ የሚገባው በንግድ ሕጉ መሰረት ሳይሆን ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ነው በማለት እና ከሳውንም በዚሁ መሰረት በማስላት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140813 በ13/03/05 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 158714 በ26/05/2006 ዓ.ም ምክንያቱ ተለውጦ የፀናው ውሳኔ በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተሽከርካሪው የጭነት ማመላለሻ ቢሆንም ሟች ከነበራቸው የንግድ ስራ ጋር በተያያዘ የመጓጓዣ ውል ግንኙነት ከአመልካች ጋር የነበራቸው በመሆኑና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበትም በአጓዡ ወይም በሰራተኛው ጥፋት ወይም የጥንቃቄ ጉድለት ስለመሆኑ ከሳሽ ወገን ክርክርም ሆነ ማስረጃ ያላቀረበበት በመሆኑ ለካሳ መጠን አወሳሰኑ አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ሳይሆን የንግድ ሕጉ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በተጠሪ ባለቤት እና የልጆች አባት ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ በጉዳት ካሳ ረገድ የአመልካቹና የስር 2ኛ ተከሳሽ የኃላፊነት መጠን ጣሪያ በንግድ ሕግ በቁጥር 597(1)ድንጋጌ መሰረት ብር 40,000 ነው በማለት ወስነናል፡፡በዚህም መሰረት አመልካች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ግማሹን ብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) ለሞት አደጋው ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ በአደጋው ምክንያት ተጠሪ ከአወጡት ወጪ ደግሞ ብር 3000.00 እንዲሁም ለሞራል ካሳ ብር 500.00 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 99124

የካቲት 28 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካቾች ፡- 1ኛ ወ/ሮ ስብለ ማሞ
2ኛ አቶ ዳዊት ግርማ } ጠበቃ እሌኒ አስራት ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ የ፲ አለቃ ተስፋየ በዛብህ ወራሾች

1. ወ/ሮ ትግስት ተስፋየ - ቀርቧል

2. ወ/ሮ አስራት ተስፋየ -ቀርቧል

2ኛ ወ/ሮ ጥሩነሽ ሀይሉ -ወኪል ወ/ሮ ትግስት ተስፋዬ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከሰሾች፤ የአሁኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሾች የካቲት 22 ቀን 2005ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ በግራ ቀኙ ጥቅምት 30/2005ዓ/ም በተደረገው የሽያጭ ውል በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወ/07 በተከሳሾች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የቦታው የስፋት መጠን 105ካ/ሜ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/154/12199/00 የሆነውን ቤት በ800,000/ስምንት መቶ ሺ ብር /ሊሸጡልን የተዋዋልን ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰነዶች ማረጋገጫ እና መዝገብ ጽ/ቤት እስከሚረጋገጥ ድረስ በቅድሚያ 50,000/ሀምሳ ሺ ብር/ በምስክር ፊት ቆጥረን ሰጠናል፡፡ ሆኖም ተከሳሾች ከዛሬ ነገ ሲሉ እስከ ሶስት ወር ውል ያልፈፀሙ ሲሆን እንዲያውም አንደኛ ተከሳሽ የአእምሮ በሽተኛ እንደሆነ እና ውሉን በምናደርግበት ሰዓት ሁለተኛ ተከሳሽ ይህኑን ያልነገሩን ሲሆን በዚሁም ምክንያት ውሉ ተፈፃሚ መሆን እንደማይችል

www.abyssinialaw.com

ስለተረዳን ውሉን ማፍረሳችን እና የሰጠውን ብር 50,000/ አምሳ ሺ ብር/ ቀብድ የሰጠናቸውን እንዲመልሱልን በቀን 11/06/2005 ዓ/ም በፅሁፍ ብንጠይቃቸው ፍቃደኛ ስላልሆኑ ፍ/ቤቱ አንደኛ ተከሳሽ የአእምሮ በሽተኛ ስለሆኑ ውሉ እንዲፈርስልን እንዲሁም ቀብድ የወሰዱትን 50,000 ብር እንዲመልሱልን እና በውሉ መሰረት ስላልፈፀሙ መቀጮ 20,000 ብር እንዲከፍሉ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እንዲተካላቸው ዳንኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በ29/08/2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ በፍ/በብስ/ስ/ህ/ቁ.1810 መሰረት ውሉን የማፍረስ ስልጣን የላቸውም፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የአእምሮ በሽተኛ አይደሉም እንጂ በሆኑ እንኳ እሳቸው ነበሩ ውሉ ይፍረስልን ብለው መጠየቅ የነበረባቸው፡፡ ከሳሾች ውሉን በፍቃዳቸው ካፈረሱት በውሉ ያስያዙት ቀብድና መቀጮ የጠየቁት ሕግን የተከተለ አይደለም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር ክሱን ውድቅ እንዲደረግ፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ግን በፍሬ ነገሩ ላይ የተሰጠ መልስ 1ኛ ተከሳሽ ውሉን ከተዋዋልን በኋላ ውልና ማስረጃ ሂደን ልናስመዘግብ ስንል በእድሜው የገፋ ሰው ስለሆኑ ፍ/ቤት ሄዳችሁ አጽድቁ እንዲህ አይነት ዕድሜ የገፋ ሰው ፍ/ቤት ነው የሚያፀድቀው በማለት እንዲመለስ አድርገኦናል፡፡ ነገር ግን ከሳሽ የባንክ ብድር ስለሚያመልጠኝ እና ቅናሽ ቤትም ስላገኘን ቀብዱን መልሱ ብለው ጠየቁን እኛ ግን ፍ/ቤት ሄደናል፡፡ አላፈረስንም እነሱ ናቸው ያፈረሱት ስለሆነም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1885/1/2/ መሰረት ከሳሾች በውሉ መሰረት 20,000 ብር ለተከሳሾች እና 20,000 ብር ለመንግሰት በአጠቃላይ 40,000 ብር መቀጮ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ በማስከፈል ክሱ ውድቅ ተብሎ እንዲወሰንላቸው በማለት መከላከያ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካከሄደ በኋላ ውሉ ያልተፈፀመው ተከሳሾች በውሉ መስረት ለመፈፀም ጥረት እያደረጉ እያለ በከሳሽ የባንክ ብድር ያመልጠናል በሚል እና ሌላ ቤት በማግኘት ውሉን በራሳቸው ፍቃድ ሰርዘው ሌላ ቤት የገዙ መሆናቸው ነው፡፡ ውሉ ያልተፈፀመው በከሳሾች ምክንያት ከሆነ ደግሞ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1885/1/ መሰረት ቀብድ የከፈለው ሰው በራሱ ፍቃድ ውል ከሰረዘ ቀብድውን መጠየቅ ስለማይችል ከሳሾች የከፈሉት ቀብድ ብር ተከሻሾች መክፈል የለባቸውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈፀመ ስሕተት የለበትም በማለት በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 19 ቀን 2006 ዓ/ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ከተጠሪዎች ያደረግነው ውል በ1ኛ ተከሳሽ ፍቃድ

ጉድለት ምክንያት ሊፈፀም አለመቻሉ በተጠሪዎች የታመነ ሁኖ እያለ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት ውሰኔ መስጠቱ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33 እና 244 ድንጋጌ የሚቃረን ውሳኔ በመሆኑ፤ 1ኛ መልስ ሰጪ የሰነዶች መረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በተደጋጋሚ ቀረበው ስለሚዋዋሉት ጉዳይ አውቀው ፍቃዳቸውን ለመስጠት ባለመቻላቸው ምክንያት የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 በሚደነግገው መሰረት ሊመዘገብና ሊፈፀም ያልቻለ መሆኑ፤ ጥቅማችን የጎዳ በመሆኑ ውሉ እንዲሰረዝ የመጠቅ መብት ያለን ሆኖ እያለ አትጠይቁም በማለት የተሰጠ ውሳኔ በመሻር በክሳቸው መሰረት እንዲወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 መሰረት በፍርድ ቤት ወይም በአዋዋይ ፊት ይላል እንጂ በአንዱ ብቻ እንዲደረግ አይልም፤ ውሉ ለመፈፀም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ውሉ አፍርሰናል የከፈልነው ቀብድ ይመለስልን ለማለት አይችሉም፤1ኛ ተዋዋይ የ፲ አለቃ ተስፋየ በዛብህ የእእምሮ በሽተኛ አይደሉም እንጂ ቢሆኑ እንኳን በእሳቸው የችሎታ አለመኖር አመልካቾች የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፤የስር ፍርድ ቤት ቀብድ አይመለስም ሲል የሰጠው ውሳኔ ህጉን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የሚነቀፍበት ምክንያት ስሌለ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማጽናት እንዲሰናበቱ በመጠየቅ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም ባንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለመቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በጽሁፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል የመዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን እንዳለባቸው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1) ተደንግጓል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ውል በተለየ ፎርም እንዲፈፀም ግድ ከሚሆንባቸው ሁኔታዎች አንዱ የሽያጭ ውል ነው፡፡ በአመልካቾችና ተጠሪዎች መካከል የሽያጭ ውል ለማድረግ ያሰቡት ይህንኑ የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሉ ለመዋዋል ስልጣን ባለው አካል ቀረበው ለመፈፀም መሆኑን በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን በመከተል ወደ ውልና ማስረጃ ማረጋገጫና ምዝገባ ሰነዶች ተመላልሰው 1ኛ ተከሳሽ ስለሚዋዋሉት ጉዳይ ሀሰባቸውን ለመግለፅ በላመቻለቸው ውሉ ለማድረግ ያለተቻለ መሆኑን ይህም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

በተጠሪዎች በፍርድ ቤት ሊነዋወል እየተቻለ አመልካቾች ፍቃደኛ አልሆኑም፤ፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 በአዋዋይ ፊት ብቻ አይልም በፍርድ ቤትም ሊደረግ የምችል ነው ከሁለቱ በአንዱ ሊደረግ ይችላል በማለት ያቀረቡት ተቀባይነት የለውም ምክንያቱ ህጉ ያስቀመጠው በአመራጭ ነው፡፡ በፍርድ ቤት ወይም በአዋዋይ ፊት ሊደረግ እንደሚቻል ሲገልፅ ከሁለቱ አንዱን የመምረጥ ለተዋዋዮች የተተወ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የተመረጠው በአዋዋይ ስልጣን በላው አካል እንዲደረግ ነው፡፡ ስለዚህ በተስማሙት መሰረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል በመቅረብ በታሰበው መሰረት ሊፈፀም በለመቻሉ ረቂቅ ውል ከመሆን አልፎ ውል ነበረ ለማለት አይቻልም፡፡ ረቂቅ ከሆነ ደግሞ በማናቸው ሁኔታ ያሰቡትን ለመተውና የተከፈለ ገንዘብ ካለ ለማስመለስ ከመጠየቅ የሚከለክሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከመሰረቱ ውል ከሌለ ከውል ጋር ተያይዥነት ያላቸው ውል እንዲሰረዝ የመጠየቅ መብት ያለው ማነው? የሚል እና ፍ/ብ/ህ/ቁ.1808 /1/2/፤1810፤1885/1/ የተመለከቱት ተያያዥ ጉዳች ሊነሱ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በረቂቅ ደረጃ በቀረ ጉደይ ላይ አግባብነት የሌላቸው የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የአመልካቾች ክስ ውድቅ በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረትም የሚከተለው ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.30711 ሐምሌ 2 ቀን 2005ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.140449 ታህሳስ 24 ቀን 2006ዓ/ም የተሰጠ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለአመልካቾች ብር 50,000 /አምሳ ሺ ብር/ በዚህ ችሎት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አስከሚያልቅ ድረስ ከ9% ወለድ ጋር ይክፈሉ፡፡
3. በፍርዱ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ቅጂ ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ይላክ፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
5. መዝገብ ተዘግተዋል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 100651

መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ወ/ሮ መንበረ ሰፈርህ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ብርሃኔ ጌቴ የኤርሚያስ ምህረት እና የትዕግስተ ምህረት ሞግዚት

2ኛ. ወ/ሮ ባንቻየሁ አዝመራ የሊዲያ ምህረት እና የውባለም ምህረት ሞግዚት

3ኛ. ወ/ሪት አዜብ ምህረት - አልቀረቡም

**መዝገቡ ለምርምራ የተቀጠረ ሲሆን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ከግራ ቀኙ የቀደመ ክርክር እና በሰበር መ/ቁ.78774 ጥር 29/2005 ዓ/ም ከተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ከሟች አቶ ምህረት ታዬ ጋር በተደረገ የጋብቻ ውል የክርክሩን ንብረት የጋራ አድርገናል ቢሉም የጋብቻ ውሉ በፍርድ ቤት ያልጸደቀ በመሆኑ ምክንያት ንብረቶቹ የውርስ ሀብቶች ናቸው በሚል ለወራሾች /ለተጠሪዎች/ እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው ጋር በጋብቻ አብረው ሲኖሩበት የነበረውን የመኖሪያ ቤት ተጠሪዎች የኪራይ ግምት አውጥተው ሟች ከሞቱበት ሚያዝያ 30/2000 ዓ/ም ጀምሮ እስካስረከቡበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ ኪራይ እንዲከፍሉ እና ንብረቱንም እንዲያስረክቡ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች ኪራይ አልከፍልም በማለት የሚከራከሩት ሚስት ነኝ በሚል ቢሆንም ሚስት የሆኑት እስከ ሟች እለተሞት ብቻ ነው ፤ ሟች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ በንብረቱ ምንም መብትና ጥቅም ሳይኖራቸው በቤቱ መቀመጣቸው የህግ ድጋፍ የለውም ፤ በቤቱ ኪራይ መጠን ላይ ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡ በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2162 መሰረት ያላግባብ በቤቱ ለተጠቀሙበት በወር 600 ብር ሂሳብ ለ 4

www.abyssinialaw.com

አመት ብር 28,800 (ሃያ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ) እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው አመልካች ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ኪራይ ሊታሰብ የሚገባ ተጠሪዎች ቤቱን ለመረከብ ከጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ ነው ፤ ሟች ምህረት ታዬ ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ አመት ተጠሪዎች ቤቱን ለመረከብ አልጠየቁም ፤ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ባልጠየቁበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች በቤቱ ለተጠቀሙበት ክፊሉ ሊባሉ የሚችሉበት ሁኔታ የለም በማለት የአንድ ዓመት ጊዜ ኪራይ ብር 7,200.00 ቀንሶ ብር 21,600 (ሃያ አንድ ሺ ስድስት መቶ) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 5/2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ከሟች ባለቤቴ ጋር በመሰረትነው ጋብቻ ምክንያት በጋራ ልንኖርበት በተስማማነው መሰረት የኖርኩበተን ቤት ፤ ቤቱን ለሌላ ሰው በማከረየት ያገኘሁት ጥቅም ስለመኖሩ ማረጋገጫ ሳይቀርብ መብቴን ለማስከበር በክርክር የቆየሁበት ጊዜ ተሰልቶ ኪራይ እንድከፍል መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2162 ድንጋጌ በአግባቡ ሳይተረጎም በመሆኑና በቤቱም የኖርኩት በአሳማኝና በቂ ምክንያት በመሆኑ ኪራይ እንድከፍል የቀረበው ጥያቄ እና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ ቤቱን እንዲያስረክቡና ለተገለገሉበት ኪራይ እንዲከፍሉ ለአሁኑ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ክስ ማቅረባቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ፤ በሟችና በአመልካች መካከል የነበረው ጋብቻ በሞት ምክንያት የፈረሰ በመሆኑ ሟች ከሞቱበት ከሚያዝያ 30/2000 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን ማስረከብ ሲኖርባቸው ክርክር በማቅረብ በተጠሪዎች የውርስ ሃብት ያላግባብ መጠቀም የሚገባቸው ባለመሆኑ ፤ ተገቢ ያልሆነ ክርክር በማቅረብ ፍርድ እስኪሰጥ ድረስ በውርስ ሃብት ያላግባብ መገልገል አለብኝ የሚለው ክርክርም የህግም ሆነ የፍትህ መሰረት የሌለው በመሆኑ የተገለገሉበትን ኪራይ እንዲከፍሉ እና ቤቱን እንዲያስረክቡ መወሰኑ ትክክል ነው ተብሎ የሰበር አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመ/መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ የተገለጸው የጉዳዩን አመጣጥ ለማመልከት ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር እና የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ለተገለገሉበት ጊዜ ኪራይ እንዲከፍሉ በተወሰነባቸው ቤት ውስጥ ከሟች ባለቤታቸው ምህረት ታዬ ጋር ተጋብተው ይኖሩበት እንደነበር ግራ ቀኙ አላከራከረም፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁን ተጠሪዎች የውርስ ሃብት ነው የተባለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት አመልካች በጋብቻ ውል የጋራ የተደረገ ነው የሚል ክርክር አቅርበውበት የነበረ ሲሆን ክርክሩን በቅድሚያ የተመለከተው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የጋራ ሃብት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በይግባኝ እና በሰበር ሲያከራክር ቆይቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥር 29/2005 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ የጋብቻ ውሉ በፍ/ቤት ያልጸደቀ በመሆኑ ምክንያት ንብረቱ የውርስ ሃብት ነው በሚል ተወስኗል፡፡

ግራ ቀኙ በክርክር መቆየታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ከባለቤታቸው ሞት በኋላ በቤቱ ለተጠቀሙበት ጊዜ አላግባብ ጥቅመ አግኝተዋል ተብሎ በንብረቱ በተገለገሉበት ልክ ኪራይ እንዲከፍሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2162 ተጠቅሶ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2162 እንደተደነገገው በሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ ሰው አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሃብቱ የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከባለቤታቸው ሞት በኃላ በቀደመው መልኩ በቤቱ መገልገል መቀጠላቸው እና ቤቱ የጋብቻ የጋራ ሃብት ነው በማለት ክርክር አቅርበው በክርከራቸው መሰረት ተወስኖላቸው የነበረ መሆኑ ሁሉ ሲታይ በቤቱ የተገለገሉት በቂ ምክንያት በሌለበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በህጉ መንፈስ አላግባብ ጥቅም አገኙ የሚሰኝ ሆኖ አይታይም፡፡ ከዚህም ሌላ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2178 ይዘት መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ንብረቱ ሊያፈራ የሚችለውን የገንዘብ ግምት እንዲመልሱ ሊወሰን የሚችለው በንብረቱ ላይ አንዳች መብት እንደሌላቸው እያወቁ በእጃቸው አድርገው እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተረጋገጡው ከላይ የተመለከተው ፍሬ ነገሮችን ይህን የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆም አመልካች ያላግባብ በልጽገዋል ተብሎ ገንዘብ እንዲመልሱ እና ተጠሪዎችን እንደ ክሱ የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

**ው ሳ ኔ**

1ኛ. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤተ በኮ/መ/ቁ. 135467 የካቲት 7/2006 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.25610 ሚያዝያ 7/2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. አመልካች በቤቱ ለተገለገሉበት እንዲከፍሉ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሸሯል፡፡

3ኛ. የስር ፍ/ቤቶች ያሳለፉት ቀሪው ፍርድ እና ውሳኔ የጸና ነው ብለናል፡፡

4ኛ. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 96548

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

**አመልካች**፡- የሐያት ሆስፒታል ባለቤት አቶ ኢብራሂም ናውድ ጠበቃ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን /የህፃን ሐምራዊ ቀለሙ ሞግዚት - ጠበቃ አሰፋ አሊ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በወሊድ ወቅት በተጠሪ ሕፃን ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት በተመለከተ የጉዳት ካሳ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የስር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ሆስፒታል የነፍሰጡር ምርመራ ክትትል ሳደርግ ቆይቼ፣ መጋቢት 4 ቀን 1992 ዓ/ም በ2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ይልማ አስረስ/ አዋላጅ ሀኪም አማካኝነት የወለድኩ ሲሆን የህፃን ሐምራዊ ቀለሙ እናት ከወሊድ በፊት በጥሩ ጤንነት ላይ የነበርኩኝ፤ በወሊድ ወቅት አዋላጅ ሐኪም በትክክለኛ የማዋለድ ሥርዓት የሙያ ግዴታቸውን መፈጸም ሲገባቸው ባለማድረጋቸው በቸልተኝነት ጉዳት የደረሰባት ልጅ እንድትወለድ አድርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ የጡንቻዎች መስነፍ፣ የብራካ መስለል፣ የቀኝ እጅ መስነፍ እና መዘርጋት ችግር አጋጥሟታል፣ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ላይ በወሊድ ወቅት የደረሰባት ከፍተኛ የጤና ጉዳት ችግር ለወደፊት የትምህርት እና እንቅስቃሴ ቀጣይ ሕይወቷ ላይ ቋሚ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት እና ተፅዕኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ስለዚህ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ወደ ውጭ አገር ሄዳ ቀዶ ጥገና ሕክምና ማድረግ እንዳለባት በባለሙያ ስለተረጋገጠ ለውጭ አገር ሕክምና እና ለልዩ ልዩ ወጪ የሚያስፈልገው ብር 410,050 ለረዳት

www.abyssinialaw.com

ሰራተኛ ለወደ ፊት ለ60 ዓመት የሚያስፈልገው በወር ብር 171.00 ለ60 ዓመት ሲደመር 5 ፐርሰንት ጭማሪ 799,923 ፀጉሯን ለማሰራት 406,511 ለተሽከርካሪ ሾፌር ደመወዝ ብር 811,391 ለወደ ፊት ለምትወልዳቸው ሶስት ልጆች ተንከባከቢ ሰራተኛ ብር 72,000 ጂምና ለፊዚዮቴራፒ እንቅስቃሴ ብር 1,611,811 በጠቅላለው ብር 4,111,686.00 /አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት/ ስለሆነ እና በርትእ የሚወሰን የሞራል ካሳ እና ከሕጋዊ ወለድ ጋር ተከሳሾች በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉኝ፣ የወጪ ዝርዝር መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት ከሳለች፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር 1ኛ ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ የጉዳት ካሳ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ጉዳቱ በደረሰ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለሆነ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የ1ኛ ተከሳሽ ሆስፒታል በቂ መሣሪያዎች እና አስፔሻሊስት ሀኪም በማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ ስለሆነ የራሱ ጥፋት የለበትም፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በስፔሻልስት ደረጃ የተመረቁ በሙያ ስነ ምግባራቸውና ጠንቃቀነታቸው መልካም ስም ያተረፉ ናቸው፣ ከሳሽ ቅድመ ውሊድ ክትትል ተከሳሹ ጋር ነው ያደረጉት፡፡ የከሳሽ እናት ለወሊድ ስትመጣና ከወሊድ በኃላ የጤና ችግር ነበረባት፡፡ ከሳሽ ሐኪሙ ቸልተኛ ነው ከማለት ውጭ ትክክለኛ የማዋለድ ስርዓት ምን እንደሆነ አልገለፁም፡፡ የሐኪሙ የኃላፊነት መስፈርት ምን እንደሆነ በመግለጽ አላስረዱም፡፡ የሕፀኗ ችግር ወይም ጉዳት ከሳሽን ተጠያቂ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ካሳውን ለመጠየቅ የሕክምና ቦርድ ውሳኔ አልቀረበም፡፡ ልጅቷ ሁሉንም ስራዎች መስራት የምትችል መሆኑን የከሳሽ ማስረጃ ያሳያል፡፡ የተጠየቀው ካሳም የተጋነነ እና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው፡፡ ሕፃኗ ወደ ውጭ ሄዳ የቀዶ ሕክምና ማድረግ አለባት የተባለው አይመለከተንም ከሆነም ደግሞ ህክምናውን በሕንድ አገር በአነስተኛ ወጪ ማግኘት ይቻላል በማለት ዘርዝሮ የካሳው ጥያቄ እንደማይመለከተው በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ /ዶ/ር ይልማ አስረስ መጥሪያ በጋዜጣ ተድርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ እሱ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የከሳሽን የሰው ምስክሮች ቃል በመስማት፣ የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በሰጠው ውሳኔ፣ የከሳሽ ህፃን በ1ኛ ተከሳሽ ሆስፒታል እና በ2ኛ ተከሳሽ አዋላጅነት ስትወለድ በወሊድ ወቅት የ"ፎርሲፕስ" መሳሪያ በመጠቀም እንዲወልዱ በማድረጉ በህፃኗ የቀኝ እጅ ጡንቻ ስንፈት እንደተከሰተ በሽታውም የብራቪያስ ነርቭ መጎዳት ሲሆን ይህ በሽታ ሊከሰት የቻለው በወሊድ ጊዜ በደረሰ ጉዳት እንደሆነ የቀረበው ማስረጃ ያስገነዝባል፡፡ ተከሳሽ ይህን ማስረጃ በማስተባበል በገባው የወሊድ ውል መሠረት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን አላስረዳም፡፡ 2ኛ ተከሳሽም ያለውን የሙያ ብቃት ተጠቅሞ ከሳሽ ያለ ምንም እንከን የማወለድ ስራቸውን የሰሩ መሆኑን አያመለክትም፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ የገባውን የማዋለድ ግዴታውን ሊወጣ ባለመቻሉ በከሳሽ ላይ ለደረሰው

www.abyssinialaw.com

ጉዳት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1790 /1/ መሰረት ኃላፊነት አለበት፡፡ 2ኛ ተከሳሽም ሥራቸውን ሲሰሩ የወሰዱትን እርምጃ የተከተሉትን ፕሮሲጀር ያልማዘገበ ሲሆን ከሕፃኗ ትልቅነት የተነሳ 2ኛ ተከሳሽ ከፎርሲፕስ የማዋለጃ መሳሪያ ይልቅ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም እንደነበረበት እንደሚያስገድዱ ያመለክታል፡፡ ይህን መሳሪያ ለመጠቀም የታካሚዋን ፍላጎት መጠየቅ ሲገባው የህን አላደረገም፡፡ ስለዚህ 2ኛ ተከሳሽ በሙያቸው ማድረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ማድረግ ባለመቻላቸው የደረሰ ጉዳት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2028 እና 2031 መሰረት ኃላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡ የካሳውን መጠን በተመለከተ የጥቁር አንበሳ እስፔሻሊሽት ሆስፒታል በሰጠው ማስረጃ ከጠቅላለ የሰውነት ክፍሉ 55 ፐርሰንት አከባቢ መሆኑን ስላራጋገጠ የመዕከላዊ ስታትስቲክስ በጻፈው ዳብዳቤ በአዲስ አበባ የተወለደች የአንድ ሴት ልጅ አማካይ ዕድሜ 68.9 ዓመት እንደሆነ ገልጿል፡፡ ሕፃኑ ለወደ ፊት የመኖር ዕድሜዋ 59.1 ዓመት ነው፡፡ ከሳሽ በሁለት እጅ የሚሰሩትን ስራዎች መሥራት እንደማትችል ተረጋግጧል፡፡ በርካታ ሥራዎች ራሷን ችላ መስራት አትችልም፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች በአንድነትና በነጣለ ከሳሽ ረዳት ሰራተኛ ለመቅጠር የሚያስፈልገውን ብር 689,049.32 ከሳሽ ውጭ አገር ሄዳ ለመታከም የሚያስፈልጋት ወጪ ብር 346,250፣ ከሳሽ ለጅምና ለፊዚዮትራፒ እና ለሰውነት እንቅስቃሴ የሚያሰልጋት ወጪ ብር 1,453,035.17 የሞራል ካሳ ብር 1000 በአጠቃላይ 2,489,334.49 የጉዳት ካሳ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ከታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9 ፐርሰንት ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍሏት በማለት ወስኗል፡፡ ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትም ጠብቋል፡፡ ከሳሽ ለፀጉር ማስሪያ ለሾፌር ደመወዝ ለወደፊት እወልዳለሁ ላለቻቸው ልጆች ለእንክብካቤ ያስፈልጋል በማለት የጠየቀችውን ወጪ በተመለከተ ፍ/ቤቱ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ምክንያቱን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን የሚያስለውጥ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት አላገኘንም በማለት አጽንቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በ06/05/2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ተጠሪ ሐኪሙ የፈፀመውን ቸልተኝነት የማስረዳት ኃላፊነት እያለባት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳቱ የመጣው በተፈጥሮ መሆኑን ሐኪሙ ስህተት አለመፈጸሙን አመልካችም ሆነ ሐኪሙ ኣላስረዳም በማለት የማስረዳት ሸክሙን ማዞሩ የህግ አግባብ የለውም ፡፡ የሕክምና ታሪክ አለመመዝገብ ለተጠሪ ወሊዱ ችግር ያለበት መሆኑን አለማስረዳት በፎርሲፐርስ ለመውለድ የተጠሪን ፈቃደኝነት አለመጠየቅ በሕይወት ማዳን ጥድፊያ ጊዜ ሊታለፍ የሚችሉ ሲሆን ስህተት የሚሆኑት ጥድፊያ የሌለ መሆኑን ማስረዳት ሲቻል ነው ፡፡ በአሁኑ ሁኔታ ተጠሪ የመውለድ ሁኔታ ጥድፊያ ውስጥ ስለገባች ሐኪሙ ተገቢውን ወስኖ የሙያ ግዴታውን መወጣቱ በቸልተኝነት /ስህተት/ መኖሩን አያመለክትም፡፡ አመልካች በበኩሉ

www.abyssinialaw.com

የጠራቸውን ሐኪሞች ምስክርነት የተወው የባለሙያ ምስክር በየትኛውም ወገን ቢቀርብ የሚመዘነው በመፅከላዊነት እና የባለሙያ ምስክር ለማስተባበል ሌላ የባለሙያ ምስክር አይቀርብም በሚል መርህ ነው፡፤ አመልካች ግን ተጨማሪ የባለሙያ ምስክር ከኢትዮጵያ የማህጸንና ፅንስ ባለሙያዎች ማህበር እንዲቀርብለት የጠየቀው ማስረጃ አለመቅረቡ አለአግባብ ስለሆነ ሊቀርብልን ይገባል ፡፡ ተጠሪ በእንግሊዝ ሀገር በግል ሆስፒታል ውስጥ ከሚሰሩት የሕክምና ባለሙያ የተገኘ የሕክምና ዋጋ ተመን የእንግሊዝ ፓውንድ 9625 ከኢንተርኔት የተወሰደ የላኪው ማንነት የማይታወቅ ስለሆነ እንደማስረጃ ሊወሰድ አይገባም በማለት አመልካች ቢከራከርም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ሰነድ የሰነድ ማስረጃ ከሚታወቅ ተቋም መቅረብ አለበት፡፡ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ገብቶ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት መመዝገብ አለበት፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም በመዝ.ቁ .32282 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ይህን የማይታወቅ የጉዳት ተመን እንደማስረጃ አድርጎ ወስዶ ውሳኔ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት መዝገቡን በመመርመር ህፃን ሐምራዊ ቀለሙ በወሊድ ጊዜ የደረሰባት ጉዳት በቸልተኝነት ለመፈጸሙ የቀረበ ሙያዊ ማስረጃ ሳይኖር የኃላፊነት ውሳኔ በስር ፍ/ቤቶች ተሰጥቷል፡፡ ይህ ቢታለፍ የካሳ መጠኑን በተመለከተ የቀረበ ተጨማሪ ማስረጃ ሳይኖር በኢንተርኔት የተገኘን መረጃ መሰረት በማድረግ ወሳኔ የመሰጠቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሠረት የካቲት 03 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ቀርቧል ፡፡ የመልሱም ይዘት ፡- የቀረበው ክርክር የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ጉዳይ ስለሆነ የዚህ ችሎት ስልጣን ስላልሆነ ሊስተናገድ አይገባም፡፡ የተጠሪን የማስረዳት ሸክምን በተመለከተ 1ኛ በሀኪሙ በኩል ግዴታ የነበረ መሆኑን፣ 2ኛ ሐኪሙ በውል ግንኙነት ሊፈጽም የሚገባውን ታካሚዋን የማዋለድ አገልግሎት ወይም እናት እና የልጅን በሰላምና በጤንነት የማለያየት ስራ አለመፈፀሙን 3ኛ የውል ግዴታውን ሙያው በሚጠይቀው ክህሎት ጥንቃቄና በተገቢው ሁኔታ ባለመፈፀሙ በህፃኗ ላይ የብራክያስ ነርቭ መጎዳት/የቀኝ ጡንቻ ሰንፈት /ጉዳት የደረሰባት መሆኑ ይህም በወሊድ ጊዜ ከውጭ በኃይል ጉተታ በደረሰ ጉዳት መሆኑን በተጠሪ በኩል በ12 ስፔሻሊስት ዶክተሮች ምስክርነት ፣በራሱ በአመልካች የተሰጡ የሰነድ ማስረጃዎች ፣ በአለርት ሆስፒታል፣ በቤተል ቲቺንግ ሆስፒታል በድንበሯ ሆስፒታል ፣ በኢንተርሜዲካል ዲያግኖስቲክ እና ኢሜጂንግ ማዕከል፣ በጥቁር አንበሳ የሐኪሞች ቦርድ፣ የተጎጂዋ የምስክርነት ቃል ጉዳቱንም ቀርባ ለፍ/ቤት አሳይታ በእናቷ እና በአባቷ የምስክርነት ቃል ያስረዳች ሲሆን በአመልካች በኩል አንዳችም የማስተባበያ መከላከያ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ከውጭ አገር የመጣውን አስፈላጊ የሆነውን የሕክምና ወጪን የሚያስረዳውን የሰነድ ማስረጃ በተመለከተ አመልካች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት አልተመዘገበም፣በማስረጃነት

www.abyssinialaw.com

ሊታይ አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤት ፈፅሞ ያልተነሳ ጉዳይ ስለ ሆነ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊነሳ አይችልም፡፡ ታካሚዋ በወሊድ ወቅት ችግር ያለበት ወሊድ ምልክቶች/ Risk factors/ መኖራቸው ከታወቀ ባለሙያ ሐኪሙ በፎርሴፕስ /የብረት መጎተቻ መሣሪያ/ ተጠቅሞ ፅንሱን በኃይል ከመጎተት ሌሎች ጥንቃቄ የሚፈልጉ የሙያ ወሳኔዎችን መስጠት ነበረባቸው ፣ በነበረው ሁኔታ ግፊ ማለት አልነበረባቸውም ፣ በፎርሲፕስ መጎተት አልነበረባቸውም፡፡ ፎርሴፕስና ምጥ የሚያፋፍም መድኃኒት መጠቀም አልነበረባቸውም ፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን መጠቀም ነበረበት፡፡ ይህ ደግሞ የሐኪሙ ጥፋት መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተጠሪ የባሙያ ምስክሮች ሁሉም እንዳስረዱት ሐኪሙ የታካሚዋ ካርድ ሪኮርድ አልተሞላም ፣ የተመዘገበ ነገር አልተገኘም፡፡ ይህ ደግሞ ስህተት መሆኑን መስክሯል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች ህፃኗ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት እንዳለባቸው በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠች ስለሆነ አመልካች በማስረጃ ያስተባበለው ነገር ስለሌለ የሥር ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሳውን እንዲከፍሉ የሰጡት ውሳኔ የማስረጃ ስህተትም ሆነ የሕግ መሰረት ስለሌለ የቀረበው አቤቱታ ፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር ስለሆነ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል እንዲወሰንበት በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች መጋቢት 01 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተ ሲሆን ፣ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ከወሊድ በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል አመልካች ሆስፒታል ዘንድ ስታደርግ እንደነበር ግራ ቀኙ አልተካካዱም ፡፡ይህ ማለት ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን የተሻለ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ሲባል አመልካች ዘንድ ቅድመ ወሊድ ክትትል ስታደርግ እንደነበር እና በወሊድ ወቅት ተገቢውን ሕክምና በማግኘት በሰላም ፣ጤናማ ልጅ ለመውለድ ሲባል እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አመልካች ደግሞ በሚያቀርበው ባለሙያዎች እና የሕክምና መሳሪያዎችን ተጠቅሞ በገባው ውል መሠረት ግዴታውን በሚገባ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አንፃር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2639፣2641፣2642 መመልከት ይቻላል፡፡ አመልካች ያለውን የሕክምና መሳሪያዎች እና ባለሙያዎችን አቀናጅቶ በወሊድ ወቅት እናትና ልጅን የመለያየት ስራ የሙያው ግዴታ በመወጣት እናትና ልጅን በሰላም እና በሙሉ ጤንነት ማለያየት አለበት፡፡ አመልካች ለሕክምና አገልገሎት የሚያስፈልገውን መሳሪያዎች ማቅረቡ ብቻ በቂ አይደለም ነገር ግን እንዚህን መሳሪያዎችን በመጠቀም ባለሙያው ያለውን እውቀትና ክህሎት ተጠቅሞ የማዋለድ ውሉ የሚጥልበትን ግዴታ መፈፀም አለበት፡፡ አመልካች ለሕክምናው የሚያስፈልገውን መሳሪያዎች ቢያቀርብም እንኳን የሥር 2ኛ ተከሳሽ እነዚህ መሳሪያዎችን

www.abyssinialaw.com

በመጠቀም የሕክምና ሙያው የሚጠይቀውን ሄደት በመጠበቅ ተጠሪን በሙሉ ጤንነት ካላዋለደ ከተጠያቂነት የሚያመልጥበት ሁኔታ የለም የአመልካች ተቀጣሪ ሰራተኛ የሆነው የሥር 2ኛ ተከሳሽ የሙያ ሰነ-ምግባሩ የሚጠይቀውን ሁሉ በመፈፀም እውቀቱን እና ክህሎቱን በመጠቀም ከአንድ አዋላጅ ሐኪም የሚጠበቀውን ሁሉ ያደረገ እንደሆነ እና ከዚህ ውጭ በሆነ ለምሳሌ በተፈጥሮ ችግር ምክንያት በእናትም ሆነ በተወለደች ሕፃን ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ አመልካችንም ሆነ የሥር 2ኛ ተከሳሽን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል ። አመልካችም ሆነ የሥር 2ኛ ተከሳሽ ከተጠያቂነት ነፃ ለለመሆን 2ኛ ተከሳሽ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ሙያው በሚጠይቀው መሰረት የፈፀመ መሆኑን አግባብነት ባለው ማስረጃ ያስረዱ እንደሆነ ብቻ ነው። አመልካች የሕክምና አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ሐኪሙ የሚጠበቅበትን ግዴታ መወጣቱን በቅድሚያ የማስረዳት ግዴታ/ሸክም የእርሱ ነው። አመልካች የሱ ተቀጣሪ ባለሙያ የሕክምና ሙያው በሚጠይቀው መሠረት ምንም ስህተት ፣ጥፋት፣ ቸልተኝነት ሳይኖር ስራውን መስራቱን በቅድሚያ የማስረዳት ግዴታ አለበት። ምክንያቱም የሕክምና አገልግሎት ውሉን በገባ ጊዜ በወሊድ ወቅት እናትና ልጅን በሰላምና በሙሉ ጤንነት ለመለያየት ግዴታ ስለገባ ነው ታካሚዋ በሕክምና ወቅት ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ የሕክምና አገልግሎት ሰጭውን ተቋም እና ሐኪሙ ለደረሰባት ጉዳት ተጠያቂ ናቸው በማለት በኃላፊነት የመጠየቅ መብት አላት። ይህን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2647 /2/ እና 2651 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል አመልካችም ሆነ ሐኪሙ ደግሞ በወሊድ ወቅት ምንም አይነት ስህተትም ሆነ ቸልተኝነት አለመፈፀሙን በተሻለ ማስረጃ የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው ። ከዚህ በኋላ ታካሚዋ የአመልካች ሐኪም ጥፋት የፈፀመ መሆኑን በማስረጃ የማስተባበል፣ በማስረጃ የማስረዳት ሸክም አለባት።

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘው ጉዳይ ሲታይ ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ተጠሪን በወለደች ወቅት ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ጉዳት እንደደረሰባት አመልካችም አልካደም። ከዚህም በላይ አመልካች የሰጠው ማስረጃን ጨምሮ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ በወሊድ ወቅት አካላዊ ጉዳት የደረሰባት መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው ።አመልካች በካርድ ው.12058 በ22/03/2000 ዓ.ም በፃፈው ሰነድ ሐምራዊ ቀለሙ ስትወለድ ክብደቷ 4.3 ኪ.ግ እንደሆነች፣የቀኝ እጅ ክንድ መስነፍ፣ የብራኪ መስለል የነበረባት እንደሆነ፣ የብራሺ.ጋያል ፓልሲ የሚባል የነርቭ በሽታ እንዳለባት እና ይህ በሽታ በወሊድ ጊዜ በደረሰ ጉዳት የተከሰተ መሆኑን ፣ሕፃኗ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለባት ያመለክታል ። ሌላው ከአለርት አገር አቀፍ ሪፈራል ማዕከል ፣ ኦፕሬሽናል ቴራፒ ምርመራ አገልግሎት ማስረጃ ድንበሯ የእናቶችን ሕፃናት ሆስፒታል ፣ኢንተርሜዲካ ዲያግኖስቲክ እና ኢሜጂንግ ማዕከል ፣ቤተል ቲቺንግ አጠቃላይ ሆስፒታል ፣ከፕሪንሰስ ግሬስ ሆስፒታል የቀረቡ ማስረጃዎች ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ በወሊድ ወቅት በደረሰባት ጉዳት በክሱ ላይ የተጠቀሰው የአካል ጉዳት የደረሰባት መሆኑን

www.abyssinialaw.com

እንዲሚያረጋግጥ የሥር ፍ/ቤቶች አመለክቷል፡፡ የተጠሪ የሰው ምስክሮችም በሰጡት የምስክርነት ቃል ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ የተባለው ጉዳት የደረሰባት እንደሆነ መመስከራቸውን የሥር ፍ/ቤቶች መዝገብ ያመለክታል፡፡

የሰው ምስክሮች እንዳመለከቱት 2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ይልማ አስረስ ወ/ሮ አስቴርን ሲያዋልዱ የተከተሉትን ፕሮሲጀር እና የወሰዱትን እርምጃዎችና አማራጮችን አለመመዝገቡን መመስከራቸው የሥር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ይህም በመንግስት ሆስፒታል ለምሳሌ እንደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እንኳን ሙሉ ለሙሉ እንደማይተገበር ምስክሮች ገልፀው፣ይህ ማለት ግን ይህን አለመመዝገብ ትክክል ነው ማለት እንዳሆነ አስረድተዋል ፡፡ ይህ ደግሞ የአመልካች ባለሙያ የነበረው አዋላጅ ሐኪም /የሥር 2ኛ ተከሳሽ / ሙያው በሚጠይቀው መሰረት ተጠሪን ሲያክም ለምን የተወሰደውን አማራጭ ሊወሰድ እንደቻለ አለመመዝገቡ በራሱ ጥፋት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሐኪሙ ይህን ባለመመዝገቡ የወሰዳቸው እርምጃዎች/ አማራጮች ልክ ነበሩ ለማለት የሚያስችል ነገር የለም ሐኪሙ /የሥር 2ኛ ተከሳሽ/ ለምን ምጥ የሚያፋፍም መድኃኒት እና ፎርሲፕስ መሳሪያ ተጠቅሞ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙን በመጎተት እንድትወለድ እንዳደረገ ምንም የሚያመላክት ነገር የለም ፡፡ የአመልካች ባለሙያ ይህን የታካሚዋን ታርክ በአግባቡ ባለመመዝገቡ አመልካች አሁን ላይ ቆሞ ባለሙያው ያን ጊዜ የወሰደውን እርምጃ ልክ ነው በማለት በማስረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ የክርክሩ ሄደት አያሳይም ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች በበኩሉ 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ አስቴር ሰለሞን ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙን በምትወልድበት ወቅት የወሰደው እርምጃ ትክክል እንደነበረ ህፃኗ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ከሐኪሙ ጥፋት ጋር የማይገናኝ እና ምንም አይነት ቸልተኝነት እንደሌለበት ለማስረዳት ምንም አይነት ማስረጃ አለመቀረቡን እሱም አይክድም የስር ፍ/ቤቶችም ይህንን በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች የሥር 2ኛ ተከሳሽ እናትና ልጅን በሙሉ ጤንነት እንዳለያየ ምንም አይነት ማስረጃ ባለቀረበበት በውሉ መሰረት ግዴታውን እንደተወጣ አስመስሎ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች ተቀጣሪ ሐኪሙ /የሥር 2ኛ ተከሳሽ/ ሙያው በሚያዘው መሰረት ታካሚዋን በሚያዋልድበት ወቅት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ሳይመዘግብ ሲቀር ተከታትሎ ማስተካከል ሲገባው አሁን ባለሙያው ይህን አለማድረጉ እንደጥፋት አይቆጠርም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበው መልስ የሰው ማስረጃ ዝርዝር ስር የኢትዮጵያ የማህጸንና የፅንስ ባለሙያዎች ማህበር እንደማስረጃ የጠቀሰ ሲሆን፣ የሰው ማስረጃ ማሰማት አልፈልግም በማለት የሥር ፍ/ቤት እንዲያልፍ ካደረገ በኋላ ፣ይህ ማስረጃ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክርም የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል መርህን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች እና ሐኪሙ ዶ/ር ይልማ አስረስ የሚጠበቅባቸውን የውል ግዴታ

www.abyssinialaw.com

ባለመወጣታቸው በሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ኃላፊነት ስላለበት የጉዳትካሳም ለመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1790፣2028፣2031፣2647 /2/ እና 2651/ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

የካሳውን መጠን አወሳሰን ስንመለከተም ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ሁለት እጆቿን በመጠቀም ሁሉንም ስራ መስራት እንደማትችል የተጠሪ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ማረጋገጣቸውን የሥር ፍ/ቤቶች መዝግቧል፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ለሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ አጋዥ ሰው እንደሚያስፈልጋት በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጦል ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ በተለያዩ ስራዎች ሕፃኗን የሚያግዝ ሰው በነጻ ያለ ክፍያ ማግኘት ይቻላል ተብሎ ስለማይገመት ክፍያ እንደሚያስፈልግ የሚያከራክር አይሆንም ፡፡ ነገር ግን ሕፃኗ ለመስራት ለማትችላቸው ስራዎች ስራተኛ ቀጥሮ ለማሰራት ለወደ ፊቱ በየወሩ እና በየአመቱ ይህን ያህል ገንዘብ ይከፈላል ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2102 መሰረት ዳኞች በርትዕ የካሳን መጠን የመወሰን ስለጣን እንዳለቸው ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ይህ ችሎት እንደተገነዘበው ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ለወደ ፊቱ ሕይወቷን ምቹ ለማድረግ መሥራት የማትችላቸውን ሥራዎች የሚያግዛትን ሰራተኛ ለመቅጠር ለረዳት ሰራተኛ በርትዕ ብር 300,000 /ስስት መቶ ሺህ ብር /ያስፈልጋታል ብለናል፡፡ ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ በደረሰባት ጉዳት ምክንያት ጤንነቷን በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅ የአካ እንቅስቃሴ፣ ጂምና ፊዚዮትራፒ እንደሚያስፈልጋት በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህም ደግሞ ለወደፊቱ በሳምንት ፣በወር ይህን ያህል ገንዘብ ያስፈልጋል ለማለት የሚያስቸግር ስለሆነ በርትዕ ግን ለመወሰን እንደሚቻል ሕጉ ይፈቅዳል፡፡ በዚህም መሠረት ሕፃኗ ለወደ ፊት ጂምና ፊዚዮትራፒ የሰውነት እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስፈልጋት ወጪ በርትዕ ብር 500,000/አምስት መቶ ሺህ/ ሊከፈላት ይገባል ብለናል፡፡

ሌላው ሕፃን ሐምዊ ቀለሙ ለደረሰባት የአካል ጉዳት ወደ ውጭ አገር ሄዳ ጥገና ሕክምና ማድረግ እንዳለባት እና ለዚህም ወደ እንግሊዝ አገር ሄዳ ለመታከም በአጠቃላይ ብር 346,250 /ሶስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ / ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ በተመለከተ አመልካች ባቀረበው ተቃውሞ ፣ይህ ማስረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ገብቶ በውልና ማስረጃ ስላልተመዘገበ እንደማስረጃ መወሰድ አልነበረበትም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን አመልካች ሚያዝያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው መልስ ይሀን ማስረጃ በተመለከተ ያቀረበው ክርክር ቢኖር ሕንድ አገር ተመሳሳይ አገልግሎት በአፖሎ ሆስፒታል በጣም አነስተኛ በሆነ ወጪ ለማግኘት እንደሚቻል ለመጠቆም እንወዳለን የሚል ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ከዚህ ውጭ የአቀረበው ማሰረጃ ተቀባይነት የለውም በማለት አሁን የሚያነሳውን ክርክር በሥር ፍ/ቤት በማንሳት የተከራከረው ነገር ባመኖሩ በዚህ ሰበር

www.abyssinialaw.com

ችሎት ይህን ማስረጃ በተመለከተ ያቀረበው አዲስ ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329 /1/ መሰረት ተቀባይነት የለውም ፡፡ ይህ በመሆኑ የሥ/ፍ/ቤቶች ሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ወደ ውጭ አገር ሄዳ ለመታከም የሚያስፈልጋት ወጪ የወሰኑት ገንዘብ በምንም መልኩ የተጋነነ አይደለም ብለናል፡፤ ስለዚህ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የካሳ መጠን በተመለከተ የሰጡትን ውሳኔ ብቻ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሰረት በማሻሻል በአብላጫ ድምፅ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.90681 መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.89303 በ30/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የካሳ መጠንን በተመለከተ ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት በድምፅ ብልጫ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች እና የሥር 2ኛ ተከሳሽ በሕፃን ሐምራዊ ቀለሙ ላይ በወሊድ ወቅት ለደረሰባት የአካል ጉዳት ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፣ በአንድነትና በነጠላ በፍርድ ሐተታው ውስጥ በዝርዝር እንደተመለከተው በአጠቃለይ ብር 1,147,250.00/አንድ ሚሊዬን አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ የጉዳት ካሳ ለተጠሪ ሊከፍሏት ይገባል ብለናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. የሥር ፍ/ቤት መዝገብ እንደመጣ ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

ህጻኗ የቀኝ እጅ የነርቭ መስነፍ ጉዳት የደረሰባት መሆኑ፤ ጉዳቱም የደረሰው በወሊድ ጊዜ መሆኑ እና የደረሰውም የስር 2ኛ ተከሳሽ ፎርሴፕስ (forceps) በተባለ የማወለጃ መሳሪያ ተጠቅመው የህፃኗን እናት ባዋለዱበት ጊዜ መሆኑ የልተካዱ እና የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ተጠሪዋ ካሰሚቸው ምስክሮች መካከል ከፊሎቹ በማወለድ የህክምና ሙያ ልዩ ዕውቀት ያላቸው የህክምና ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ሆስፒታል ውስጥ ይሰሩ የነበሩት የስር 2ኛ ተከሳሽ የማዋለድ ተግባሩን ባከናወኑበት ጊዜ ሆን ብለው ወይም በቸልተኝነት የሙያ ግድፈት ወይም ጥፋት በመፈጸማቸው ምክንያት ስለመሆኑ ከእነዚህ ባለሙያዎች መካከል አንዳቸውም

www.abyssinialaw.com

አረጋግጠው ያልመሰከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ በግልጽ ያመለክታል፡፡ የባለሙያዎች የምስክርነት ቃል ይዘት የማዋለድ ተግባሩ በፎርሴፕስ መሳሪያ በሚከናወንበት ጊዜ በሚወለዱት ህጻናት ላይ አሁን መከሰቱ የተረጋገጠው ዓይነት ጉዳት ሊደርስ የሚችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ከመሆኑ በቀር የስር 2ኛ ተከሳሽ የማዋለድ ተግባሩን በፎርሴፕስ ባከናወኑበት ጊዜ አሁን የተከሰተው ጉዳት እንዳይከሰት ማድረግ ይችሉ የነበረ ስለመሆኑ ወይም በሌላ አነጋገር ጉዳቱ የተከሰተው በሙያ ግድፈት ምክንያት ስለመሆኑ የሚያመለክት አይደለም፡፡ በፎርሴፕስ መሳሪያ ማዋለድ ያልተፈቀደ ተግባር ስለመሆኑም አልተገለጸም፡፡

በባለሙያዎች የተሰጠው ምስክርነት የማዋለጃ ስርዓቱን ወይም መሳሪያውን የመምረጥ እና የመወሰን ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ለአዋላጅ ሐኪሙ የተተወ መሆኑን እና የስር 2ኛ ተከሳሽ የተመሰከረላቸው ብቁ ባለሙያ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በርግጥ ምስክክሮቹ አዋላጅ ሐኪሙ በዘርፉ ከሚታወቁት የማዋለድ ስርዓቶች ወይም ዘዴዎች መካከል አንዱን ወይም ሌላኛውን የመረጠበትን ምክንያት በሕክምና ካርዱ ላይ ከተቻለ በማዋለዱ ሂደት የሁኔታዎች አጣዳፊነት ካላስቻለውም የማዋለዱ ተግባር ከተጠናቀቀ በኃላ መመዝገብ እንደሚገባው የሙያው ስነ ምግባር የሚያዝ መሆኑን ሐኪሙ እንደኛውን ወይም ሌላኛውን የማዋለድ ዘዴ የተጠቀመባቸውን ነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ እና ተገቢ ስለመሆን አለመሆኑ ሙያዊ አስያየት መስጠት የሚቻለው ከዚህ ዓይነቱ ምዝገባ መሆኑን እና በተያዘው ጉዳይ ግን ሐኪሙ ምዝገባውን ስላላከናወኑ በፎርሴፕስ የማዋለጃ መሳሪያ መጠቀማቸው ስህተት ነበር ወይስ አልነበረም የሚል አስተያየት ለመስጠት የማይችሉ መሆናቸውን ገልጸው መስክረዋል፡፡ የስር 2ኛ ተከሳሽ ምዝገባውን አላከናወኑም መባሉ በህጻኗ ላይ መድረሱ ከተረጋገጠው ጉዳት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ዓይነቱ የመመዝገብ ሁኔታ የመንግስት ትላልቅ ሆስፒታሎችን ጨምሮ በአገሪቱ ውስጥ ያልተለመደ እና የማይተገበር መሆኑን እና እራሳቸውም ቢሆኑ በሙያው ላይ በቆዩባቸው በበርካታ ዓመታት የሙያው ስነ ምግባር የሚጠይቀው ነው ያሉትን መረጃዎችን መዝግቦ የመያዝ ሁኔታ ተግባራዊ አድርገው የማያውቁ መሆኑን ጭምር እነዚሁ የተጠሪ ምስክሮች ገልጸዋል፡፡ በመሠረቱ የአንድን ሙያ ስነ ምግባር በሙያው ላይ የተሰማራ አንድ ሰው ሙያውን በቀሰመበት ቆይታ ሊያገኘው ይችላል፡፡ ይህ በትምህርት ቆይታ የተገኘ ነው የሚባለው የሙያ ስነ ምግባር የፍትሐብሔር ኃላፊነትን ለማስከተል በሚያስችል ሁኔታ ተጥሶአል ለማለት የሚቻለው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2031 (1) አነጋገር መሰረት **የሙያ ስራው የሚመራበት ደንብ** ወይም በፍትሕብሔር ሕግ ቁጥር 2647 (1) አነጋገር መሠረት **የሙያው የኪነ ጥበብ ደንብ** መሆኑ ሲረጋገጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የመመዝገቡ ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ያልተለመደ እና የማይተገበር መሆኑ በተጠሪዋ ምስክሮች የተገለጸ እስከሆነ ድረስ የምዝገባው ሁኔታ የሙያ ስራው የሚመራበት ደንብ ወይም የሙያው የኪነ ጥበብ ደንብ ነው

www.abyssinialaw.com

ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው ተሽሮ አንድ አዋላጅ ሐኪም በዘርፉ ከተፈቀዱት የማዋለድ ስርዓቶች ወይም ዘዴዎች መካከል አንዱን ወይም ሌላኛውን የመረጠበትን እና የተጠቀመበትን ምክንያት መዝገቦ የማስቀመጡ ጉዳይ በሚመለከተው የመንግስት አካል ታውቆ እና ተረጋግጦ የሙያ ስራው የሚመራበት ደንብ ነው በሚያሰኝ ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ዕውቅና እና ተቀባይነትን አግኝቶ በዘርፉ ባሉ ባለሙያዎች እየተተገበረ መሆን አለመሆኑ ወደ ስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመልሶ ተጨማሪ ማጣራት ሊደረግበት ይገባ ነበር በማለት ስሜ በተራ ቁጥር ሶስት የተመለከተውን ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬአለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 96041

ጥቅምት 26 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሴ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አልማዝ ግዛው ተወካይ ትዝታ አቡሌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ በፖስታ ቤት በኩል ወደ ኖርዌይ አገር እንዲላክ አመልከች የተረከበው እቃ አደራረስ ላይ በተነሳው ክርክር የግራቀኙ መብትና ግዴታ ምን እንደነበር ከመወሰን እንፃር የቀረበ ነው ። በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ። ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ በማድረግ የዕቃውን ዋጋ እንዲከፍል በመወሰናቸው ምክንያት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልከች ያቀረበው አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው።

የክሱ ይዘትም፡- አመልካች ወደ ኖርዌይ አገር ዕቃውን ለማድረስ ውል የገባ ቢሆንም ዕቃውን በውሉ መስረት ወደ ተባለው አገር ባለማድረሱ ነው የዕቃው ግምትና የማጓጓዣ ክፍያ በድምር ብር 9374.38 /ዘጠኝ ሺህሦስት መቶ ሰባ አራት 38/100) እንዲከፍላት ተጠሪ ዳኝነት መጠየቋን የሚያሳይ ነው ።

የአሁኑ አመልካች በሰጠው መልስም በግራቀኙ ስምምነት መስረት ዕቃው ወደ ኖርዌይ ተልኮ ተቀባይ ካላገኘ እንደሚመጣ መፈረማቸው ዕቃው ወደ ተባለው አገር ተልኮ ተቀባይ ያጣ በመሆኑ ወደ ሀገር ቤት እንደተመለሰ ፤የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካች ዕቃው ወደ ኖርዌይ አገር ልኮት ተቀባይነት ካጣ መመለስ አልነበረበትም ከስምምነታቸው ውጭ እንዲመለስ ዕቃው ወደ ኖርዌይ አገር ስለመላኩ እና ዕቃውን የሚቀበል ሰው ስለመጥፋቱ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካች ካሳ እንዲከፈል የካሳ መጠኑም ብር 5300 እንዲሁም ውጪና ኪሳራ ብር 750 እንዲሆን ፍርድ ሰጥቷል ፡፡ የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቤቱታው የቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር መላኩ አልተረጋገጠም በሥር ፍ/ቤት የተወሰነው የካሳ መጠን በማሻሻል ብር 5000 እና ወጪና ኪሳራ ብር 750 በድምር ብር 5750.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል ፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎላት ቀርባ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል ፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዕቃ ወደ ኖርዌይ አገር አድርሶ ተቀባይ በማጣቱ ንብረቱ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሰ ስለ ድርጅቱ አሠራር ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች ሳይደመጡ ጉዳዩ መወሰኑ የመደመጥ መብቱ እንደሚጋፋ በመግለጽ ውሳኔ እንዲሻር ጠይቋል ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አጣርተው የወሰኑት በመሆኑ የሚነቀፍ ነገር የለውም የሚል ክርክር አቅርበዋል ፡፡ አመልካች የመልስ መልስም አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነ ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዝብ እንዲሁም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል ፡፡

ከሥር የክርክር ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች እና ተጠሪ ዕቃን በፖስታ ቤት በኩል የመላክ ውል የተፈራረሙ ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

ግራቀኙ እያከራከረ ያለው መሠረታዊ ጭብጥ ለክርክር መነሻ የሆነውን ዕቃ በግራ ቀኙ ስምምነት መሠረት ወደ ኖርዌይ አገር ተልከዋል ወይስ አልተላከም ከተላከ በኃላ ተቀባይ በመጥፋቱ በእርግጥ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል ወይስ አልተመለሰም?የሚለው ነው፡፡ አመልካች በገባው

www.abyssinialaw.com

ውል መሰረት ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር እንደላከው እና ዕቃውን የሚቀበል ሰው በመታጣቱ የተላከው ንብረት ወደ አገር ቤት እንደተመለሰ ለዚህም የሰነድና የሰው ምስክሮች የቆጠረ ስለመሆኑ በአንድነት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ንብረቱ ወደ ኖርዌይ አገር አልተላከም ንብረቱ የተላከ ቢሆን እንኳ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ እንዳልነበረበት የበኩላቸውን ክርክር ማቅረባቸውን ተመልክተናል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር ስለመላኩ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች ካሣ እንዲከፍል ወስነዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ ግዴታ በአግባቡ መፈጸም ያለመፈጸሙን ለማጣራት የግራቀኙ ተዋዋይ ወገኖች የገቡት ግዴታ እና ያላቸውን መብት የሚገልጽ የሰነድና የሰው ምስክር እንዲሁም የግዴታው ልዩ ባሕሪ መሠረት በማድረግ አለም አቀፍ ልምዱ ጭምር መዳሰስ የሚጠይቅ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ዕቃውን ወደ ኖርዌይ አገር ለመላክ እንደተቀበለ የተካደ ባይሆንም ዕቃውን በእርግጥ ወደ ኖርዌይ አገር መላክ ያለመላኩን የሚያረጋግጠው በሚያቀርበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ እንዲሁም የድርጅቱ አሠራር አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከት ነው ፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዕቃ ወደ ኖርዌይ አገር ስለመላኩ ከዌብ ሳይት (ድሕረ ገጽ ) የተገኘው መረጃ አያያይዞ እንደቀረበ የሰው ምስክሮች እንደቆጠረ በሚከራከርበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች የቀረበው ሰነድ በዓለም አቀፍ የፖስታ አገልግሎት አሰጣጥ ልምድ ያለው ተቀባይነት እና ምስክሮች የሚሰጡት ቃል ይዘት ምን እንደሆነ ሳይቀበል ቀረበ በተባለው የሰነድ ማስረጃ ብቻ ተመርኩዞ ከድምዳሜ ላይ መድረሱ ጉዳዩን በአግባቡ በማጣራት ውሳኔ አለመስጠቱን የሚያሳይ ነው ፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ዕቃውን ለፖስታ ቤት (አመልካች )ካስረከቡ በኃላ ዕቃውን በስምምነቱ መስረት አለመላኩን እቃው ተቀባይ አለማጣቱን የሚያስረዳ ነገር ስለማቅረበቀቸውም በሥር ፍ/ቤት የተመዘገበ ነገር የለም፡፡ ተጠሪ ዕቃውን በውላቸው መሠረት አለመላኩን መነሻ በማድረግ ክስ ማቅረባቸው ሲታይ የቀረበው ክስ በማስረጃ አስደግፈው የማስረዳት ግዴታቸው ሳይወጡ ወይም ፍ/ቤቱ ዕቃው መላኩን የማስረዳት ግዴታው የአመልካች ነው ለማለት የሚያስችለው ሕጋዊ ምክንያት መኖሩን በውሳኔው ሳይገልጽ በደፈናው ዕቃውን በግራቀኙ ውል መሰረት አልተላከም ከሚል ድምዳሜ ላይ መደረሱ በሕጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘውም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ እያከራከረ ያለው የውል አፈፃፀም ክርክር በተገቢ ሁኔታ ለመወሰን በሕጉ አግባብ የሚያከራክረው ጭብጥ ተለይቶ የግራቀኙ ማስረጃ ተመዝኖ መሆን ሲገባው የአመልካች የሰው ምስክሮች ቃል ሲያዳምጥ ቀረበ የተባለው የሰነድ ማስረጃም ከዓለም አቀፍ ልምድ ያለው ተያያዥነት በባለሙያ አስተያየት ተደግፎ ማብራሪያ ሳይሰጥበት ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ ውድቅ ማድረጉ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 ፣247፣248 እና 249 የተመለከቱት መሠረታዊ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 136 እና 264(1) እና (2) ድንጋጌዎች በሚያዙት አግባብ ተገቢ ነው

www.abyssinialaw.com

ያለው ማስረጃ በማስቀረብ እና ጉዳዩን በማጣራት መወሰን እየቻለ ከዚህ በተቃራኒ ቀረበ የተባለው የሰነድ ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ አመልካች ግዴታውን አልተወጣም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በሕጉ አግባብ አይደለም ብለናል ። በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በአግባቡ ሳያጣሩ ውሳኔ ላይ መድሳቸውን የተረዳን በመሆኑ ውሳኔውን ተሽሮ በድጋሚ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ነው ። በመሆኑም የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፈጸመውን ስህተት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳያርም ውሳኔው ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የባሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ16237 በ 23/11/2005 የሰጠው ፍርድ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 168408 በ 15/04/2006 የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ይዘቱ እንደተገለፀው ግራቀኙ የሚከራከሩበት ዕቃ ወደ ኖርዌይ አገር ተልኳል ወይስ አልተላከም ? ወደ ኖርዌይ አገር መላኩ ከተረጋገጠ ወደ ኢትዮጲያ የተመለሰው ተቀባይ በመጥፋቱ ነው ወይስ አይደለም ? በአመልካች የቀረበውና ከዓለም አቀፍ ዌብይት ተገኘ የተባለው የሰነድ ማስረጃ ይዘት እና በዓለም አቀፍ ስለፖስታ አላላክ ያለው ልምድ ምን ይመስላል ?በግራቀኙ የውል ስምምነት ዓለም አቀፍ ልምድ ዕቃው የሚላክበት ሥርዓትና አፈፃፀሙ ምን ይመስላል?የሚሉና ተያያዥ ነጥቦች አመልካች የቆጠራቸው ምስክሮች እና በተጠሪ በኩል የሚቀርብ ማስረጃም ካለ አንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የሚጠቅም ከሆነ በፍ/ቤቱ አነሳሽነት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ተገቢ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ወደ መዝብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 108251

ቀን ጥር 5/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን የጎዴ ደናን መንገድ ፕሮጀክት

-ነ/ፈ አብርሃም አሰፋ ቀረቡ።

ተጠሪ፡- አቶ አመካክ ከሊፋ -አልቀረቡም።

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል።

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሸበሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. M/S/Sh — 60/2006 ግንቦት 26 ቀን 2007ዓ.ም እንዲሁም የኢትዮጵያ ሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05-1-185/06 ህዳር 5ቀን 2007ዓ.ም ያሳለፉትን ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአሁን ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ድርጅት በቆፈረው የውሃ መሄጃ ጉድጓድ ልጃቸው መሃመድ አመካክ ከሊፋ ህዳር 12/2006ዓ.ም ጉድጓዱ ውሃ ሞልቶ በቸልተኝነት ሳይሸፈን በመቅረቱ ምክንያት ገብቶ ስለሞተ ለደረሰባቸው ጉዳት አመልካች ሃላፊ እንዲባልና ልጁ የ4ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ከትምህርት ሰዓት በኋላ በአህያ ውሃ እየቀዳ ለሰፈር ነዋሪዎች በበርሚል 25ብር በመሸጥ በቀን የስምንት በርሚል ብር 200.00 በወር ብር 6000.00 ለቤተሰቡ ገቢ በማስገባት ደረጃ ስለነበር ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ታስቦ በጠቅላላ ብር 564,000.00፤ እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 1,000.00 እና የቀብር ማስፈጸሚያ ብር 25,000.00 እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል።

www.abyssinialaw.com

የአሁኑ አመልካች ለክሱ መቃወሚያ እና በሃላፊነት ሆነ በጉዳቱ መጠን ላይ የበኩሉን ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ክርክሩን እና ማስጃዎችን ሰምቶ አመልካች ለጉዳቱ ሀላፊነት አለበት በማለት ካሳውን በርትዕ አስተያየት በመወሰን ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ/ እንዲከፈል ፈርዷል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ለማከራከር ስልጣን የለውም በማለት የሚያቀርቡትን መከራከሪያ በተመለከተ አስቀድሞ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ክሱን የስር ፍ/ቤት ተመልክቶ እንዲወስን በመለሰለት መሰረት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ ተቀባይነት እንደሌለው፣ ለጉዳቱ ሃላፊ መደረጉ በአግባቡ መሆኑን፣ እንዲሁም የካሳውን መጠን በተመለከተ የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ /የጎዴ አካባቢ/ በሙሉ ልጆቹን ውሃ በአህያ እያስቀዳ የሚያሰራቸውና የኑሮ መሰረታቸው ስለመሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ፍርዱ እንዲጸና ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 21,2007ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ ሟች የ8 ዓመት ልጅ የነበረ ከመሆኑ አኳያ ውሃ በመሸጥ በየወሩ ያለማቋረጥ ብር 6000 ያስገኝ ነበር ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች በእርግጠኝነት ተቀባይነት ማግኘቱ ከህግም ሆነ ከልማዳዊ አሰራር አንጻር ተገናዝቦ የተሰጠ መሆን አለሞኑን ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ግራቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ እንዲለዋወጡ ትእዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው እንዳልቀረቡ አመልካች በቃለ መሃላ የተደገፈ አቤቱታ ስላቀረቡ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ መዝገቡ ለምርመራ ቀጠሮ ይዟል፡፡

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ቅሬታ ያስነሳውን ውሳኔ ከተያዘው ጭብጥ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

አመልካች የስር ፍ/ቤት በህግ ከተሰጠው በገንዘብ መጠን የተወሰነ የዳኝነት ስልጣን በላይ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዳልተሰጠ እንዲቆጠር በሰበር ቅሬታቸው ያመለከቱ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተመለከተው ይኸው መከራከሪያቸው ታልፎ ጉዳዩ በስር ፍ/ቤት ታይቶ እንዲወሰን ሲመለስ በወቅቱ ጉዳዩን በሰበር አቅርበው እንዲታረም ያላደረጉ በመሆኑ ቅሬታው ክርክሩ አሁን በደረሰበት ደረጃ የሚቀርብ አይደለም ብለናል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የካሳውን መጠን በርትዕ የወሰነ ሲሆን አመልካች የካሳው መጠን እጅግ የተጋነነ እና ካሳው ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት በህጉ

www.abyssinialaw.com

ከተደነገገው ውጭ የተወሰነ መሆኑን በመጥቀስ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው እንዲባል ጠይቀዋል፡፡

በመሰረቱ ጉዳት መድረሱ ምክንያታዊ የሆነ እርግጠኝነት ሲኖር እና የካሳውን መጠን ለመወሰን አስቸጋሪ ሲሆን ዳኞች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 መሰረት የካሳውን መጠን በርትዕ እንዲወስኑ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጎጂው የ4ኛ ክፍል ተማሪ የነበረና እንደ አካባቢው ህጻናት ውሃ በአሕያ በመቅዳት ቤተሰቡን ይረዳ እንደነበር ቢታወቅም በህጻኑ ሞት ምክንያት የቀረው ጥቅም መጠን በትክክል ለማስላት ስለሚያዳግት በርትዕ መወሰን ተገቢ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የካሳ መጠኑ ያላግባብ እንዳይጋነንም ሆነ ያላግባብ እንዳይቀንስ በተቻለ መጠን የጉዳት ካሳው መጠን ከደረሰው ወይም ወደፊት ሊደርስ ከሚችለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግና ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ውሳኔ መስጠት ይገባል፡፡ ስለሆነም በርትዕ በሚወሰንበት ጊዜም ቢሆን የጉዳት ካሳው መጠን ከጉዳቱ ተመጣጣኝ ይሆን ዘንድ ሚዛን ላይ ሊቀመጡ የሚገባቸው መለኪያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2153 እንደተደነገገው ዳኞች ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ በአግባቡ በመያዝ፣ ሊገምቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ በመያዝ፤ ከአእምሮ ግምት ውጭ ያልሆነ፤ ከዝንባሌ የጸዳ ውሳኔ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡

የካሳውን መጠን በርትዕ ለመወሰን የሚያስገድድ ሁኔታ በገጠመ ጊዜ መጠኑን ለመወሰን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ሁኔታዎች ወይም መለኪያዎች ካልተመለከቱ የሚሰጠው ውሳኔ ስሜትን መሰረት የሚያደርግ እና የሕጉን አላማ የሚስት በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በተያዘውም ጉዳይ የካሳው መጠን የተሰላበት ሁኔታ እና ለስሌቱ ግምት ውስጥ የገቡ ሁኔታዎች (መለኪያዎች) በግልጽ ሳይመለከቱ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1ኛ. የሸበሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. m/s/sh/60/2006 ግንቦት 26/2006ዓ.ም ያሳለፈው እና በሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05-1-185/06 ህዳር 5/2007ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. አመልካች ለጉዳቱ ሃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ በመሆኑ ይኸው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

3ኛ. የካሳውን መጠን በተመለከተ በርትዕ መወሰኑ የሚነቀፍ ባይሆንም መጠኑን ለመወሰን ያስቻለው ሁኔታ ወይም መለኪያዎች ባልተመለከቱበት እና ይህ ነው የሚባል መነሻ ምክንያት ሳይሰጥ አመልካች ለተጠሪ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺ.ህ/ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ተሽሯል፡፡

4ኛ. የከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ የካሳውን መጠን በህጉ አግባብ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

5ኛ. ጉዳዩ በሰበር ሲታይ ስላስከተለው ወጪ አመልካች የራሱን ይቻል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ወንጀል

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 117383

ቀን 6/03/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፍ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸመሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሠለ

አመልካች፡- አቶ አዲስ ዋለልኝ በላይ

ተጠሪ፡- የፌ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በወንጀል የዋስትና ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች አብረዋቸው ከተከሰሱ ሌሎች ተከሳሽ ጋር በመሆን ተከሰንበት የነበረው የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁ. 881/2007 የተሻረ በመሆኑ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ዋስትና መብት ስለማይከላከል የዋስትና መብት ይፈቀድልን ብለው ያመለከቱ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በአዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 37 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ስር ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተያዘው የሙስና ወንጀሎች የሚታዮት በወንጀል ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ይሆናል ስለሊልና የወ/ህ/አ/676/1/ የዋስትና መብት ስለማያሰጥ ዋስትና ሊፈቀድ አይገባም፡፡ የሚሰጥ ከሆነም የዐ/ሕግ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ ማስረጃ ተመዝኖ መሆን አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካለው ህግ ጋር መርምሮ የወንጀል ህግ አንቀጽ 6 እና የህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 መሠረት ቅጣት ሲወሰን ለተከሳሽ ጠቀሜታ ካለው ሕግ አኳያ ሊታይ ይገባል፡፡ የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ስለሚወድቅ እና ቅጣቱ ከ10 ዓመት በታች በሆነ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ በፌ/ሥ/ፀ/ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ቁ.434/97 መሠረት በብር 10,000 ዋስትና ከእስር ሊፈቱ ይገባል በማለት ብይን የሰጠ መሆኑን ከስር መዝገብ ለመረዳት ተችሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ብይን ቅሬታውን ለማሳረም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ካከራከረ በኃላ መልስ ሰጪዎች የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ ከ 5 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ቅጣት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ተከሳሽ (መ/ሰጪዎች) የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31 የተካተተ ቢሆንም፡፡ ቀደም ሲል በመ/ሰጪዎች ላይ የቀረበው የከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ ባለበት የቀጠለ እንጂ እንደገና ተሻሽሎ በአዲስ መልክ የቀረበ አይደለም፡፡ መሸጋገሪያ ድንጋጌው ቀደም ሲል የተፈፀሙ ወንጀሎች ባሉበት ሁኔታ መታየታቸው እንደሚቀጥል የሚጠቁም ነው አዲሱ አዋጅ ቁጥር 881/2007 መውጣቱ አስቀድሞ የተከላከሉትን የዋስትና መብት በአዲስ መልክ ለማቅረብ የሚያስችላቸው አይደለም፡፡ መ/ሰጪዎች የተከሰሱበት የወ/ህ/ቁ. 676/1/ በአዲሱ አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ሥር የማሸፍን መሆን አለመሆኑ ማስረጃ ተሰምቶ ከሚረጋግጠው ፍሬ ነገር አንፃር ታይቶ የሚወሰን እንጂ ማስረጃ ተሰምቶ ባልተጠናቀቀበት ጉዳዩና የተረጋገጠውም ፍሬ ነገር ምን እንደሆነ ባልታወቀበት ሁኔታ እንደገና በቀረበ የዋስትና ጥያቄ መነሻ ከወዲሁ ወደ ፍሬ ነገር ምዘና በመግባት ከአስር ዓመት በታች በሚያስቀጣው በአዋጅ አንቀጽ 31/1/ ሥር የሚሸፍን ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የህጉን ስርዓት የሚንድ ነው አደሱ አዋጅ መውጣቱ እና መ/ሰጬዎች የተከሰሱበት ወንጀል የአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 31 መተካቱ እንደገና የዋስትና ጥያቄ ለማቅረብም ሆነ በዋስትና መልቀቅን ለመፍቀድ የሚያስችል ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት መልስ ሰጭዎች በዋስትና ይፈቱ በማለት የሰጠው ብይን ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ በመዘርዝር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለው በአመልካች ላይ ተጠሪ ጠቅሶ ያቀረበው የወ/ህ/አ/676/1/ በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስርዓት እና ማስረጃ ህግ አ. 434/97 አንቀጽ 4 መሠረት ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በመሆኑ የዋስ መብት የተከላከለ ሲሆን የሙስና ወንጀሎችን አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ስር የወ/ህ/ቁ. 676/1/ የሚወድቅ በመሆኑ የዋስትና መብት አይከላከልም በማለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ለብር 10,000 ለሚበቃ ዋስትና የፈቀደውን በይግባኝ ደረጃ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አመልካች ዋስትና የተከለከለበት ጉዳይ የወ/ህግ አንቀጽ 676/1/ በአዋጅ ቁ 881/2007 አንቀጽ 31/1/ ስር የሚወድቅ መሆን ያለመሆኑ ወደ ፊት ማስረጃ ተሰምቶ የሚረጋገጥ እንጂ ከወዲሁ መተበይ የማይቻል ስለሆነ የዋስትና ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤትን ብይን የሻረበትን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ነው፡፡

ግራ ቀኙ በፅሑፍ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ይህ ሰበር ችሎት የአመልካችና የተጠሪን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ምክንያት ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና አግባብነት አለው የህግ ድንጋጌ ጋር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት የተከሰሰበት ወንጀል የወ/ህግ አንቀጽ 27፣32/1/ሀ/ እና 676/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የእምነት መጉደል ወንጀል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ የወ/ህ/ቁ. 676/1/ ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን ከ5 ዓመት እስከ 25 ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት እና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስቀጣ የተመለከተ ሲሆን የሙስና ወንጀሎቹን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 እምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ተክቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 ሥር 4 ንዐስ አንቀጽ ያሉ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው የቅጣት መጠን ከ3 ዓመት እስከ 7 ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ የተመለከተ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 2 የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የጥፍተኛው የስልጣን ወይም የኃላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት በህዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ያደረሰ ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተፈፀመውን ወንጀል ከባድ አድራጉት እንደሆነ ቅጣቱ ከ7 ዓመት እስከ 25 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሀምሳ ሺህ እስከ መቶ ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በፌ/ከፍ/ቤት የተከሰሰበት ወንጀል የሙስና ወጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 በአንቀጽ 31 የተደነገገ ሲሆን፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር 4 ንዑስ አንቀጾች ተመልክተዋል በንዕስ ቁጥር 1 የተመለከተው የቅጣት መጠን ከ3 ዓመት እስከ 7 ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል በንዑስ ቁ. 2 የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የጥፋተኛው የሥልጣን ወይም የኃላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት፣ በሕዝባዊ ድርጅት በሕዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተፈፀመውን ወንጀል ከባድ አድራጉት እንደሆነና ቅጣቱ ከ7 ዓመት እስከ 25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ እስከ መቶ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል ክስ ማመልከቻ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር ከሚቀርበው የዐ/ሕግ /የተጠሪ/ ማስረጃ ጋር መዝኖ አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ስር በየትኛም ንዑስ አንቀጽ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ክሱ እየታየ ባለበት ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ብይን የሚሰጥበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመልካች ላይ በተመሰረተው ወንጀል ክስ በወንጀሉ ዝርዝር ከተመለከተው አንፃር የአመልካች በዋስትና የመለቀቅ ጥያቄ በስር

www.abyssinialaw.com

ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተቀባይነት ማጣቱ ወይም የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አመልካች በዋስትና ይፈቱ በማለት የሰጠውን ብይን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሳ ኔ**

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሐምሌ 24 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ. 113580 የሰጠውን ውሳኔ አፅንተናል፡፡

መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 107166

ቀን ጥቅምት 4/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብራሃ መለሰ

አመልካች ፡- መኳንንት ማሞ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(1) ተላልፎ እድሜዋ 8 ዓመት የሆናት የግል ተበዳይ ሕፃን ያብስራ አብይ ላይ የግብረሥጋ ግንኙነት ፈፅሟል ተብሎ የቀረበበት ክስ የሥር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የ16 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖበት በየደረጃው ያሉት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ስለፀኑበት ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልኝ ሲል አመልካች ስለጠየቀ ነው፡፡

የአመልካች የቅሬታ ነጥብ የግል ተበዳይ ክብረ ንፅህና ያልተገረሰሰ ስለሆነ በሙከራ ደረጃ የቀረ ስለሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ ቅጣቱ እንዲሻሻል የሚል ነው፡፡

ይህንኑ ጉዳይ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ዐቃቤ ሕግ መልስ ሰጥቷል ፡፡ ዐቃቤ ሕግም የአመልካች ድርጊት በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ተበዳይን ጨምሮ የተረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶ በሥር ፍርድ ቤት የተላለፈው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ተብሎ እንዲፀና ተከራክሯል ፡፡በእኛ መኩል ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል አመልካች የሚከራከረው የሕፃኗ ክብረ ንፅህና አለመገርሰሱ በህክምና ማስረጃ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት

www.abyssinialaw.com

ድርጊቱ በሙከራ ቀርቷል በማለት ነው፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ተግባር (ድርጊት) ስለመፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ፍሬ ነገር የመመርመርና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋጡት ጉዳይ ነው ፡፡ የድርጊቱ አፈፃፀም ሲታይ አመልካች የወንድ ብልቱን በሕፃኗ የሴት ብልት ውስጥ ማስገባቱ በግል ተበዳይ የተመሰከረ ሲሆን በዚህም ምክንያት ማህፀኗ ላይ የመቅላት ምልክት የታዬ ስለመሆኑ በህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ክብረንፅህና አለመገርሰሱ ድርጊቱን በሙከራ የቀረ ነው የሚያሰኝ ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 627(1) ድንጋጌም ክብረ ንፅህና መኖር አለመኖር ወይም መገርሰስ አለመገርሰስ እንደ መስፈርት ያስቀመጠው ጉዳይ ባለመሆኑ ክርክሩ የሕግ መሠረት የለውም ብለናል፡፡

በቅጣት ረገድ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት አንቀጽ 627(1) ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት (15-25) በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት በማድረግ በሕግ ተቀባይነት ያለው እና በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ተቀብሎ የድንጋጌው መነሻ የሆነ ቅጣት አሥራ ስድስት ዓመት (16) ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው የሚያስኝ የሕግ ምክንያት አልተገኘም ፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 186777 በ 20/01/07 የሰጠው ትዕዛዝ ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 122177 በ 22/11/06 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11654 በ 08/09/06 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2-.ለ-.2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112725

ቀን 22/02/2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ስርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች፡-** አቶ ሀሰን አብዳል ጠበቃ ገበዮሀ ይርደው ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ማዕከል ዐቃቤ ህግ የቀረ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከተዩ ፍርድ ተሰትቷል

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ አመልካች የፀና ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ ሰርቷል በሚል በአዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 2(3) 31(1) እና 60(1) የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል በሚል የወንጀል ክስ የቀረበበት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ እየተመለከተ የነበረው ፍርድ ቤትም የአመልካቾችን ዋስትና መብት በብር 50,000 ወይም ለዚሁ ብቁ የሆነ ዋስትና ከቀረበ በኃላ ከእስር እንዲለቀቅ በሚል የዋስትና መብቱን ጠብቆለታል፡፡ ተጠሪ ቅሬታ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረቡ ግራ ቀኙን አስቀርቦ በዋስትና ጉዳይ ላይ እነዲከረከሩ ከዳረገ በኃላ የስር ፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ በመሻር የአመልካችን ዋስትና መብት ጥያቄ ከወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 67(ሀ) አንፃር በመካልከል አመልካች ማረሚያ ቤት ሆኖ ጉዳዩን ይከታተል ስል ወስነዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስላወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በዋስትና መፍቀድ ላይ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ ለማለት ስልጣን አለው የሚል አንቀጽ በወ/መ/ስ/ስ/ህጉ ላይም ሳይኖር ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተቀብሎ አከራክሮ ዋስትናውን መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፤ ዐቃቤ ህግ አመልካች በዋስትና ቢወጣ የዋስትና ግዴታውን አክብሮ አይመጣም ለማለት የቀረበው ምክንያት አድራሻ የለውም ቢፈረድበት ብዙ ዓመት ስለሚቀጣ የሚል ሲሆን አድራሻ የለውም የሚለው አመልካች አድራሻ እንዳለው የተረጋገጠና ሊረጋገጥ የሚችል በመሆኑ የዋስትና መብት

www.abyssinialaw.com

የሚያስከለክል ሁኔታ ስለሌላ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለለበት በመሆኑ ነው ተብሎ ተሽሮ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ፀንቶ አመልካች በዋስ ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል የሚል ትዕዛዝ እንደሰጠው የመለከተው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ መልሱን በፅሑፍ ሰጥቶአል፡፡

ይህ ችሎትም አመልካችና አቃቤ ህግ ያቀረቡትን የፅሑፍ ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመልክቶታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀረብ እንዲታይ የተደረገው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች በዋስትና መለቀቅ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችል መሆኑ ያለመሆኑን ይህ ቢታለፍ ከሆነም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝን መሻሩ ከወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 67(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 686 (2002 አንቀጽ 60(1) ድንጋጌ አንፃር በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

አቃቤ ህግ በዋስትና መለቀቅ ውሳኔ ላይ አቃቤ ህግ ይግባኝ ለመጠየቅ የሚችል መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ፡- በመሠረቱ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 75 ርዕሱ ሲታይ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ያልተፈቀዳ ሲሆን ለይግባኝ ፍርድ ቤት ማመልካቻ ስለማቅረብ በሚል የተቀመጠ ሆኖ ዝርዝር ይዘቱ በዋስትና ወረቀት እንዲለቀቅ ያልተፈቀደለት ተካሳሽ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማመልካቸውን ማቅረብ የሚችል መሆኑንና የጊዜ ገደቡን የሚያስቀምጥ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ድንጋጌው አቃቤ ህግ የዋስትና መብት ሲፈቀድ ይግባኝ ማቅረብ የማይችል መሆኑን አይደነግግም፡፡ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ በስነ ስርዓት ህጉ ስለ ይግባኝ አቅራረብ ከተመለከቱት ድንጋጌዎችና ከወንጀል ሕጉ መሰረታዊ አላማ ሲታይ የዋስትና መብት ጠይቆ ሊከለከል የሚችለው ተከሳሽ በመሆኑ ተከሳሹ በህጉ ሊኖረው የሚችለውን የመብት ማስከበሪያ መንጋድ ለመጠቆም ተብሎ የተቀመጠ ከመሆኑ ውጭ ህጉ በማይፈቅደው አግባብ የዋስትና መብት የተከበረለት ተካሳሽ ሁሉ ዋስትና መብቱ ተከብሮለት በዋስትና ወረቀት ሲለቀቅ የወንጀል ሕጉን የሚያስፈፅመው አቃቤ ህግ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ለማለት አይችልም በሚል ሊተረጎም የማይገባው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው የአቀቤ ሕግን ይግባኝ የማቅረብ መብት የማይከለክል በመሆኑ በዚህ ረግድ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፈፀመው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡

አመልካች ወደ ፊት ቀጠሮ አክብረው ሊቀርቡ አይችሉም ተብሎ ግምት መወሰዱን በተመለከተ፡- የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካች ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ በረሱ ዋስትና የሚከለክል አለመሆኑን የተቀባሉት ጉዳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ለዋስትና መከለካል ምክንያት ያደረገው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ ቁጥር 67(ሀ) ሲሆን ፍረድ ቤቱ ይህንኑ ድንጋጌ ተግባራዊ

www.abyssinialaw.com

ሲያደርግ ግምትን መነሻ ለማድረግ የሚችለው ሕጋዊ ስልጣን ያለው መሆኑን ነው፡፡ የዋስትና መብት መሠረታዊ የሆነ ህግ መንግስታዊ መብት ቢሆንም ፍፁም መብት ሳይሆን በሕጉ አግባብ ሊከለከል የሚችል ነው፡፡ ፍርድ ቤት አግባብነት የለውን ልዩ ህግ መሠረት አድርጎ ጉዳዩን ሊመዝነውና ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳዩ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካቾች የዋስትና ጥያቄ ያልተቀበለው በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 67(ሀ) መሠረት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በዋስትና ወረቀት የመልቀቅ ማመልካቻ ለመቀበል የማይቻልባቸውን ሁኔታዎችን አስቀምጧል፡፡ ፍርድ ቤቱ ዋስትናውን ለመከለከል ግምቱን መነሻ የሚያደርግባቸው ሁኔታዎች በተጠቀሰው ድንጋጌ በግልፅ አልተመለከቱም እንዲህ ከሆነ አንድ ተካሳሽ የዋስትና መብት ቢከባርለት ግዴታውን የሚፈፅም፣ የማይመስል ነው ተብሎ ግምት የሚወስዳው በቂና እና ህጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይግባል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ምክንያቶቹ በቂና ህጋዊ ናቸው የሚለው ጉዳዩ ከተለያዩ ከባባዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህሪይ አንፃር እየተየ በፍርድ ቤቱ ግንዘቤ ሊወስድባቸው የሚችላቸው ነጥቦች ናቸው ተብሎ የሚታሰብ እንጂ ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ ለማለት የማይችልበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 67 በጠቅላላው ሲታይ ፍርድ ቤት የወስትና መብትን የሚከለከልበቻው ሁኔታዎች የሚያሰይ ሲሆን ምክንያቶችን ፍርድ ቤቱ ከተለየዩ ሁኔታዎች በመመልከት ሊመዝናቸው የሚገባቸው ሲሆን የድንጋጌው ቅርፅ ይዘትና መንፋስ ሲታይ በሁኔታዎቹ ግምት የመውሰድ የለመውሰድ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን (Discretion) መሆኑን ያሰያል በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 59304 በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ቢወጣ የዋስትናውን ግዴታ አክብሮ ይገኛል ለማለት የሚችል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ይህ ግምት መሠረቱ በአመልካች ቋዋሚ አድራሻ አለመኖር ሳይሆን ትኩረት የተሰጠው በአመልካች ላይ የተመሰረተው ክስ ሊያስከትል ከሚችለው የእስራት ቅጣት ከፍተኛነትና ከወንጀሉ ልዩ ባህሪይ መሆኑ መገመቱን ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ ገልፀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ዋስትናውን ከልክለዋል፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ለግምቱ መነሻ እንዲያደርግ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው በህጉ የተከለከለ ካለመሆኑንም በላይ ግምት የመውሰድ ጉዳይ በህጉ ለፍርድ ቤቱ ስልጣን የተሰጠው ነው፡፡ ግምቱ በቂ ነው ወይም አይደለም የሚለው ክርክር ደግሞ የጠቅላላ ሁኔታዎች ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሰበር

www.abyssinialaw.com

ችሎት ደግሞ በኢ.ፌ/ዲ/ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) ሀ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትን ማንኛውንም የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ የማስረጃና የሌሎች ክባቢያዊ ነገሮችን ምዘና ጉዳይ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን ፍሬ ነገሩን የማጠረትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ስላለው ይህ ችሎት የክርክር አጠቃላይ በህሪይ መሰረት በማድረግ የሚዘው ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው ሊባል የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ይጋባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ ህገ መንግስት አንቀጽ 19(6) እና የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 67(ሀ) መሠረት የሰጠው መሳኔ ሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት ያደረገ እና በሕጉ አተረጋጓም አተገባበር ረገድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 110478 መጋቢት 21 ቀን 2007 ዓ/ም መተሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 75(2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ጉዳያቸውን በማረሚያ ቤት ሆኖው እንዲከታተሉ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 109441

ቀን 17/05/2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጢታ

አመልካች፡- ፌይሳ ማም ማሩ የቀረበ የለም ከተበለ በኃላ አዲስ መሀመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች ቁምቢ በዳሳን የመግደል ወንጀል ፈጽሟል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በህግ አግባብ የተሰጠነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ሰዓቱ በውል ተለይቶ በውል ባልታወቀ ጊዜ በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 ሃያት ኮንደሚኒያም ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ አብሮት ከኦሮሚያ ክልል ሰንደፈ ወረዳ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ወደ አዲስ አበባ የመጣውን ሟች ቁንቢ በዳሳ ምንነቱ ባልታወቀ ነገር ጭንቅላቱን በመምታት በደርሰበት ጉዳት ህክምና ሲከታተል ቅይቶ ሀምሌ 18 ቀን 2003 ዓ/ም ህወይቱ እንደያልፍ በማድረጉ ተራ የሰው መግደል ወንጅ ፈጽሟል በማለት የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያስረዳልኛል በማለት የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የተጠሪ የሰው ምስክሮች ቃል በተመለከተ ፤ አንደኛ የተጠሪ ምስክር ሟች አጎቷ መሆኑን ገልጾ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ከቀኑ 6:00 ሰዓት አከባቢ ሟች እና ተከሳሽ ከሰንደፋ ወደ አዲስ አበባ ስሄዱ አግኝቻቸው የት ልትሄድ ብየ ሟችን ስጠየቀው ልጄን ለመጠየቅ ወደ አዲስ አበባ እሄዳለሁ አለኝ፡፡ ሟች አዲስ አበባ ከተከሳሽ ጋር ከሄደ በኃላ በዚያው ሳያመለስ ቀረ፡፡ ከዚያ ሟች ወድቋል ተብሎ እንደተነገራቸውና ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ሄደን ስናየው ጭንቅላቱ ቅስሎና ተፈንክቶ ነበር፡፡ በመጨረሻም ወደ ቤት የመጣና ያስታመመችው መሆኑን ሟች ወደ ቤት በመጣ ጊዜ መናገር ማይችል እንደነበር፣ ይህንን የፈጸመብህ ተከሳሽ ነወይ ብየ ሰጠይቀው በሟች በምልክት በአዎት መልስ ሰጥትኛል ምስክር ተከሳሹን የጠረጠረችው በመጀመሪያ ከሟች ጋር አዲስ አበባ አብሮ በመሄደና ተከሳሽም ሲሞት ለቀበር ያልመጣ በመሆኑ ምክንያት መሆኑን፤ ሟች በምልክት ለምስክር ምላሽ ከሰጠ ከአምስት ቀን በኃላ ህይወቱ ያለፈ መሆኑን የመሰከረች መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

3. ሁለተኛ የተጠሪ ምስክር የሟች እህት መሆኗን ገልጻ፣ ተከሳሽ ሟችን አዲስ አበባ ልጅህንና ሚስትህን ያሉበት ቦታ አሳይለሁ ብሎ ከቤት ይዞት እንደወጣ አብረው እንደሄዱ የሰማች መሆኑን፤ ሟች ከቤት ከወጣ በኃላ ሳይመለስ እንደቀረና ከሁለት ሳንምንት በኃላ ዳግማዊ ሚኒሊክ የተኛ መሆኑ አንደወቁ ሟች እግሩ፣ አንገቱና ጭንቅላቱ ተጎድቶ እንደነበር፤ ሟች ወደ ቤት ከመጣ በኃላ መልስ መስጠትና ከሰው ጋር መግባባት የማይችል መሆኑንና የሚገባባውም በምልክት እነደነበርና ሟች እሺ የሚል መልስ ብቻ ይሰጥ እንደነበር ተከሳሽን የጠረጠሩት አብርው ከቤት ወጥተው የት ጣለው በሚልና ሟች ከጠፋና ከታመመ ጊዜ ጀምሮ ተከሳሽ ፍለጋ አለማድረጉ ሟችንም አለመጠየቁን ሟችና ተከሳሽ ጠብ የሌላቸው መሆኑንና አንደኛ ምስክር ሟችን ድርጊቱ የፈጸመብህ ተከሳሽ ነዎይ ብያ ስጠይቀው በምልክት አዎ ብሎ መልሶልኛል ብላ እንደነገራቻትና ነግራኛለች፣ እኔ ሟች በምልክት ተከሳሽ ነው ብሎ መልስ ሲሰጥ አልሰማሁም፡፡ ሟች ብር 5000 (አምስት ሺ ብር) ይዞ ስለነበር ለብሩ ስል ገድሎታል ብላ እንደምታሰብ የመሰከረች መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

4. ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር ሀምሌ 23 ቀን 2003 ዓ/ም ተከሳሽን ሲይዘው ተከሳሽ ለማምለጥ መከራ ያለማድረጉን እንደመሰከር በስር ፍርድ ቤት በውሳኔው አስፍሯል፡፡ በችሎት ያልቀረበው የተጠሪ ምስክር በበኩሉ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል አከባቢ በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም አከባቢ ሰው ተሰብስቦና ሟችን ውድቆ እንዳየና ከሟች አጠገብ ሁለት ዱላዎች እንደነበሩና

www.abyssinialaw.com

ሟችን ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የተወሰደ መሆኑን ገልጾ ለፖሊስ ቃሉን ያስመዘገበ መሆኑን እንደተረዳ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ገልጿል፡፡ ተጠሪ ስለ ሟች አሞሞት የሚገልጽ የአስክሬን ምርምራ ውጤት የቀረበ መሆኑና ማስረጃው ሟች የሞተው በድብደባ ምክንያት ሁለቱም ሳንባዎቹና ጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት መሆኑን የሚገልጽ እንደሆነ ተረድተናል፡፡

5. የስር ፍርድ ቤት አመልካች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን ሰጥቶ ሟች በምልክት ፈይሳ ነው ብሏል በተባለው መሰረት ሌለ ፈይሳ የተባለ ሰው ተይዞ እንደነበርና ግንቦት 3 ቀን ስራ ስሰራ ወየ ማታ አስራ አንድ ሰዓት አከባቢ ባለቤቴ ስራ ቦታ መጥታ ተያይዘን ከአበልጃችን ጋር ሄደን እዚያ አድርን ግንቦት 4 ቀን 2030 ዓ/ም ወደ ቤታችን መመለሳችን ያስረደልናል በማለት ጭብጥ አስይዞ አራት መከላከያ ምስክሮችን ቃል አስምቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተከሳሽ በጉዳዩ ተጠርጥሮ ሲያዝ ጳግሜ 3 ቀን 2003 ዓ/ም ለፖሊስ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ከሟቸው ጋር ቀርስ ምላስ ሰንበር በልተን ማወራረጃ አንድ አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጥተው እንደተለያዩና ፤ ከሟች ጋር ከተለያዩ በኃላ ተከሳሽ በኮንትራት ጭቃ የመለጠፍ ስራ ሲስራበት ወደ ነበረው ጠጅቱ ቤት በመሄድ ጭቃ ሲለጥፍ ወሎ፣ ስራው ስላለቀለት ወ/ሮ ጠጀቱ ቤት አድሮ በማግስቱ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም አምስት ሰዓት አከባቢ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ በመግልጽ ከሰጠው ተከሳሽነት ቃል ጋር የሚቃረንና ታዓማኒነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የአመልካችን የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ አድርጎታል፡፡

6. የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ማስረጃ አመልካች በወንጀል ክሱ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ መተላለፍ ሟችን የገደለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ ያቀረባቸው የመከላከያ ምስክሮች ቃል ተዓማኒነት የሌለውና የዐ/ህግን ማስረጃ የሚያስተባብል አይደለም በማለት አመልካች (ተከሳሽ) በወንጀል ህግ አንቀጽ 540 የተመለከተውን በመተላለፍ ሟችን በመደብደብ ህይወቱ እንደያልፍ ያደረገና ተራ የሰው መግደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው ብሎ ፤ አመልካች በአሰር አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም፤ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት አጽንቶታል፡፡

7. አመልካች ጥር 20 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈጸምኩ ስለመሆኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አቅርቦ የሰማቸው ምስክሮች አላስርዱም፡፡ የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት ቃልም ሰፊ ልዩነት ያለበት የተጠሪ ምስክሮች በአከባቢው ከእኔ ሌላ ፈይሳ ቡሻ የሚባል ሰው እንዳለና ሟች ከሟች ፈይሳ ቡሻና ከአንድ

www.abyssinialaw.com

ልጅ ጋር ቁማር ስጫወት እንደነበር መስክረዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ወንጀሉን የፈጸምኩ ስለመሆኑ የቀረበብኝ በቂ ማስረጃ ሳይኖር፣ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽመሀል ተብሎዬ የ ተወሰነብኝ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 21 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ አመልካችና ሚች አንድ ላይ ወደ አዲስ አበባ የመጡ መሆኑንና ሚች ወደ ቤቱ ሳይመለስ መቅረቱና ሚች ህይወቱ ያለፈው በደብደባ በደረሰበት ጉዳት መሆኑ የተጠሪ ማስረጃ ተደጋጋፊ በሆነ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 1 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

8. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ አመልካች ሚችን ሆነ ብሎ ባደረሰበት ድብደባ ህይወቱ እንዲያልፍ ያደረገ መሆኑን የማስረዳት ግደታውን (Burdon of proof) የተወጣ መሆኑን መርምረናል፡፡ አመልካች የተከሰሰበትን ተራ የሰው መግደል ወንጀል እንዳለፈጸመ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የሚገመት በመሆኑ አመልካች በህገ መንግስቱ የፀና ነው ተብሎ የመገመተ መብት ጠቃሚ ከማስረጃ የማፍረስና አመልካች ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የማስረዳት ህጋዊ ግደታ (Legal Burdon of proof) ያለበት አመልካችን በወንጀል የከሰሰው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ይህንን የተጠሪን ጥፋተኝነት ማለትም ተጠሪ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን የማስረዳት በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ግደታውን የሚወጣው፣ አመልካች ወንጀሉን የፈጸመ መሆኑን በምን ደረጃ ማስረጃ በማቅርብ (Standard of proof) ሲያስረዳ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 149 ተደንግጓል፡፡

9. ከላይ ከተጠቀሱት የህገ መንግስቱና የወንጀል መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት የሚቻለው፣ አመልካች ሚችን ሆነ ብሎ የገደል ስለመሆኑ ተጠሪ በበቂና አሳማኝ ማስረጃ የማስረዳትና የማረጋገጥ ግደታ አለበት፡፡ ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግደታውን በአግባቡ ካልተወጣ፣ መልካች የተጠሪን ማስረጃ የመከለካልም ሆነ የማስተባበል ግደታ እንደሌለበት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ ተጠሪ ሚች ቁንቢ በዳሳ፣ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ልዩ ቦታው አያት ኮንደሚኒየም አካባቢ፣ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ከጧቱ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን ለጊዜው ማንነቱ ባልታወቀ ሰው ጭንቅላቱንና ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ተደብደቦ ወድቆ መገኘቱ፣ ሚችን ወድቆ ያገኙት ሰዎች የህክምና እርዳታ እንደያገኝ

ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የወሰዱት መሆኑን፣ ሟች ከሆስፒታል እርዳታ ስደርግለት ከቆየ በኃላ ወጥቶ ወደ ቤቱ መሄዱን፣ ሟች ቤቱ ውስጥ በህመም ላይ ቆይቶ፣ ሀምሌ 18 ቀን 2003 ዓ/ም ከዚህ አለም ህይወቱ ያለፈ መሆኑን፤ ሟች የሞተው በድብደባው ምክንያት በጭንቅላቱና በሁለት ሳንባዎቹ ላይ በደረሰበት ጉዳት መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧለው፡፡

10. ይህም ሟች ቁንቢ በዳሳ ህይወት ማለፍ ምክንያት የሆነው ማንነቱ ባልታወቀ ወይም ባልታወቁ ሰዎች ትክክለኛ ሰዓቱ ተለይቶ ባልታወቀበት ሰዓት በተፈጸመበት ደብዳብ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት መሆኑን የወንጀል ህግ አንቀጽ ት 24 በሚደነግገው መሰረት ተጠሪ የማስረዳት ግደታውን የተወጣ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተርድተናል፡፡ ተጠሪ በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ የተወጣ መሆኑ አከራካሪ የሚሆነው ሟችን ደብዱቦ በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም ከሚባለው ልዩ ቦታ የጠለው ተከሳሽ (አመልካች) መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ነው፡፡

11. ተጠሪ አመልካች ሟችን ስደበድብ አይቻለሁ የሚል ቁጥተኛ ማስረጃ (direct evidence) አላቀረበም፡፡ ተጠሪ ሟችን የገደለው አመልካች ነው በማለት ያቀረበውን የወንጀል ክስ ለማስረዳት የሞከረው ሟች ተደብድቦ ወድቆ ከመገኘቱ በፊትና ሟች ተደበድቦ ወድቆ ከተገኘ በኂላ የነበሩትን የአካባቢ ሁኔታ ነገሮች በማስረዳት፣ ፍርድ ቤቱ ሟችን የገደለው ተከሳሽ (አመልካች) ነው ወይም አይደለም ከሚለው ሎጅካል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃዎችን ከማቅረብ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው አንደኛ የተጠሪ ምስክር አመልካችና ሟች ግንቦትን 3 ቀን 2003 ዓ/ም አንድላይ ወደ አዲስ አበባ ስሄዱ ማየቷን፣ አመልካች ሟች ጠፍቶ ስፈለግም ሆነ ታሞ እቤት በነበረበት ሰዓት ያልጠየቁ መሆኑን፣ አንደኛ ተጠሪ ሟች በምልክት የደበደበህ ተከሳሽ ነወይ? ብየ ስጠይቀው ተከሳሹ መሆኑን በምልክት መልስ ሰጥቶኛል በማለት የሰጠችውን የምስክርነት ቃል እና የስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት ባስቀርበው የፖሊስ መርመራ መዝገብ ውስጥ አመልካች በወንጀለኛ መቀጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለፖሊስ 3-13-2003 በሰጠው የተከሳሽነት ቃል "ተከሳሽ ከሟች ጋር ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ አብረው መጥተው አዲስ አበባ ከደርሱ በኃላ ቁርሳቸውን ምሳስ ሰንበር በልተው ማወራረጃ አንድ አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጥተው የተለያዩ መሆኑን ተከሳሽ ከሟች ጋር ከተለያየ በኃላ ኮንትራት ጭቃ የመለጠፍ ስራ ይሰራበት ወደነበረው ወ/ሮ ጠጅቱ ቤት የሄደ መሆኑንና ከሳሽ የጭቃ ልጠፋው ስራ ያላለቀለት በመሆኑ ከወ/ሮ ጠጅቱ ቤት አድሮ በማግስቱ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ከቀኑ አምስት ሰዓት ወደ ቤቱ የተመለስ

www.abyssinialaw.com

መሆኑን በመግለጽ የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል፤ እንድዚሁም የሟች እህት የሆነቸው ሁለተኛ ተጠሪ ምስክር ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አመልካች ከሟች ጋር ወደ አዲስ አበባ መሄዱን ሰዎች እንደነገሯት፣ ሟች ተከሳሽ ነው የደበደበኝ ብሎ በምልክት ነግሮኛል ብላ አንደኛ ተጠሪ የነገረቻት መሆኑን ሟች በምልክት ይህንን ሲናገር እንዳላየች የሰጠችውን የምስክርነት ቃልና አንደኛ ሁለተኛ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪዎችን ታሞ በነበረበት ጊዜ ያልጠየቀው መሆኑንና በሟች ቀብር ስነ ስርዓት ላይ አመልካች ያልተገኛ መሆኑን በመግልጽ የሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች ሟችን የገደለ መሆኑን የሚያረጋግጡ የአካባቢ ሁኔታ ማስረጃዎች ናቸው በማለት እንደሆነ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

12. የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃ ወንጀሉን የፈጸመው ተከሳሽ መሆኑንና ከተከሳሽ ውጭ ሌላ ሰው ወንጀሉን ሊፈጽመው አይችልም በሚል መደምደሚያ ላይ ለማድረስ በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የሚያስርዳ ሆኖ ሲገኝ የአስረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንደሚወስድ የማስረጃ ብቃት መስፈርትና የማስረጃ አመዛዘን መርሆች ያሳያሉ፡፡ የአከባቢ ሁኔታ አንድን የተፈጸመ ወንጀል ለማስረዳት የአሰረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ የሚሆነው ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ወንጀሉ ከተፈጸመ በኃላ ስላላው ሁኔታ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች (የአከባቢ ሁኔታዎች) ተከሳሽ ወንጀሉን ፈጽሞታል ከሚል እርግጠኛ መደምደሚያ ለመድረስ የሚያስችል ይዘትና ባህሪ ያላቸው ሲሆን፣ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎቹ ተያያዥነት ያላቸውና ክፍተት የሌለባቸው ሲሆኑ፤ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎቹ የተከሳሹ ጥፋተኝነት ወንጀል መምራት የሚያረጋግጡ አንጅ በተቃራኒው ተከሳሹ ንጹህ ነው ወንጀሉን አልፈጸመም ወደሚለው ሎጅካል መደምደሚያ የማይወሰደ ሲሆኑና የቀረቡት የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎች በማናቸውም የሞራልና የህሊና መመዘኛ ወንጀሉ በተከሳሹ ሳይሆን በሌላ ሰው የመፈጸም እድልና አግጣሚ የሌለ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት የሚችሉ ሆነው ሲገኙ እንደሆነ ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ህግ መርሆች ያሳያሉ፡፡

13. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች ሟች አዲስ አበባ አብረው ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም የወጡ መሆኑን፣ አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ወደ ቤቱ መመለሱና ሟች ሳይመለስ መቅረቱ፣ ሟች በአዲስ አበባ የካ ከተማ አያት ኮንደሚኑየም ከተባለው አከባቢ ደብደባ ተፈጽሞበት ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም አንድ ሰዓት ተኩል አከባቢ ውድቆ መገኘቱ ሟች ላይ የሞት ጉዳት የደረሰበትን ድበዳቤ የፈጸመው አመልካች ስለመሆኑና ከአመልካች ውጭ ሟችን ሌላ ማን ሰው ሊደበድበው የማይችል ስለመሆኑ ሎጅካል መደምደሚያ ላይ የሚያድረሱ፣ ተያያዥነት ያላቸውና ክፍተቶ የማይፈጥሩ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃዎች ናቸው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡

www.abyssinialaw.com

14. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ዕወነትነት ያለው ማስረጃ እንደሆነ በመውሰድ የአመልካችን የመከላከያ ምስክሮች ቃል ውድቅ ለማድረግ አመልካች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 27 ንዑስ አንቀጽ 2 የሰጠው የተከሳሽነት ቃል፣ አመልካችና ሟች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አዱስ አበባ አብረው ከመጡ በኃላ ከሟች ጋር ምላስ ሰንበር ቀርሳቸውን በልተውና ማወራረጃ አንድ አንድ ብርሌ ጠጅ ጠጥተው የተለያዩ መሆኑን፣ አመልካች ከሟች ጋር ቀርስ በልተው ከተለያዩ በኃላ ኮንትራት ሲሰራው ጭቃ የመልጠፍ ስራ ሲሰራበት ወ/ሮ ጠጁቱ ቤት መሄዱን ከዚያ በኃላ ጭቃ የመለጥፌ ስራው ስላልተጠናቀቀለት ከወ/ሮ ጠጅቱ ቤት አድሮ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ብቻውን ወደ ቤት መመለሱን የሚገለጽ ማስረጃ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት የቀር በትዕዛዝ ያስቀረበው ይህ አመልካች ለፖሊስ የሰጠው የተከሳሽነት ቃል፣ የአስርጅነት ብቃት እና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በማረጋገጥ ለፍርድ ግበዕት አድርጎ ተጠቀሞበታል፡፡ ይህ ከሆነ የስር ፍርድ ቤት ለፖሊስ ከሰጠው የተከሳሽነት ቃል ውስጥ አመልካቹን የሚግዳውን ማለትም ከሟች ጋር ወደ አዲስ አበባ አብረው መምጣታቸውንና ቁርስ አብረው መብላታቸውን የሚገልጸውን የማስረጃነት ክፍል ለማስረጃነት ከያዘ በኃላ አመልካች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ ከደርስንና ቁርስ ከባለን በኃላ እኔና ሟች ተለያይተናል፡፡ ከዚያ በኃላ እኔ በኮንትራት ጭቃ ወደምለጥፍበት ወ/ሮ ጠጅቱ ቤት ሄጄ፣ ወ/ሮ ጠጅቱ አድሬ በማግስቱ ብቻየን ወደ ቤት ተመልሻለሁ በማለት አመልካችን የሚጠቅመውን የማስረጃ ክፍል በማስረጃነት አልያዘለትም፡፡ ይህም የስር ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ባስቀርበው የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ውስጥ ተይይዞ ያገኘውንና አመልካች በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 27(2) የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል ከነሙሉ ይዘቱ ሳይሆን አመልካች ጥፋተኛነው ለማለት የሚጠቅመውን የማስረጃውን ክፍል ብቻ ለፍርድ ግብዓት ያዋለና መሰረታዊ የማስረጃ አመዛዘን መርህ በመጣስ መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

15. እንደዚሁም ከላይ በተገለጸው በተጨማሪ አንደኛ ተጠሪ ሟች በምልክት ተከሳሽ እንደደበደበው ገልጾልኛል በማለት የምስክርነት ቃል የሰጠች ቢሆንም ሟች በምልክት ይህንን ሲገልጽ ከምስክር ውጭ ሌሎች ሰዎች ያላዩ መሆኑና የሟች የምልክት ቋንቋ ትክክለኛ መልዕክት ለመረዳት አስቸጋሪ በመሆኑ፣ የተጠሪ አንደኛ ምስክር ሟች በምልክት ቋንቋው ስለገለጸው ትክክለኛ መልዕክት ሳይሆን እሷ ይህንን ማለቱ ነው ብላ የገመተችውን የመሰከረች መሆኑን ስለሚያሳይ፣ አመልካች በቁጥጥር ሲወል ለማምለጥ አለመምከሩና ሌሎች ባህሪያቶችን አለማሳያቱን የተጠሪ ሶስተኛ ምስክር የመሰከር በመሆኑና ሁለተኛ ተጠሪ የሰጠችው የምስክርነት ቃል የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በመሆኑ ማስረጃው በወ/መ/ስ/ህግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ

www.abyssinialaw.com

ቢሆንም አመልካች ሟችን ስለመግደሉ ለማረጋገጥ የሚያስችል ይዘት የሌለው በመሆኑ፣ የተጠሪ የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃም ሟች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም ከአመልካች ጋር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ፣ አዲስ አበባ ከአመልካች ጋር ቁርስ ከበሉ በኃላ አመልካችና ተጠሪ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ሄደዋል ወይስ አብረው አንድ ላይ ዉለዋል፣ አመልካች ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ ከደረሰ በኃላ ወደየት ቦታ እንደ ሄደ፣ ምን ሲሰራና እነ ማን ጋር እንደዋል፣ የማያስረዳና ክፍተት ያለበት በመሆኑ፣ ሌላው ቀርቶ ሟች ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም ወድቆ ከተገኘበት የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም ከተባለው ቦታ ላይ ሟች ከወደቀበት ጎን ወድቀው ከተገኙት ሁለት ብትሮች አንደኛው የአመልካች ስለመሆኑ ተጠሪ በሰው ምስክር ወይም በሳይንስ ምርመራ ያላረጋገጠ በመሆኑ፣ ተጠሪ ሟች ሰዓቱ በውል ባልተወቀበት ጊዜ ማንነቱ ወይም ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ተደብድቦ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ አያት ኮንደሚኒየም ከተባለው ቦታ ወድቆ መገኘቱንና በድበደባው በደረሰበትን ጉዳት ህይወቱ ያለፈ መሆኑን ከማስረዳት ውጭ ሟችን የደበደብ አመልካች ስለመሆኑ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 በሚደነግገው መሰረት በቂና አሳመኝ የሆነ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ግደታውን አልተወጣም፡፡ ተጠሪ የማስረዳት ግደታውን ባልተወጣበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን በወ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 141 መሰረት በነጻ ማሰናበት ሲገባው ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንደያቀርብ የሰጠው ብይንና በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የማስረጃ ህግ መርሆች የሚጥስ ነው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ስህተት ሳያርም ፍርዱን ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሽረነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 113102 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101772 የሰጠውን ፍርድ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ-1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል በነጻ የተሰናበት በመሆኑ ከእስር እንዲለቀቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር 113464

ህዳር 22 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- 1. እናት ሁናቸው
2. ባለው እንደወቅቱ
3. ሃብታሙ ሁነኛው
4. በልስቲ ሁነኛው
} የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካቾች እና ስንሻው አለሙ በተባለው ግለሰብ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱም ይዘት፡- ተከሳሾች በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ወንጀል አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 671(2) ስር የተደነገገውን መተላለፍ የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት አስበው ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 4፡00 እስከ 6፡00 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ጎዛመን ወረዳ ማይ አንገታም ቀበሌ ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ውስጥ አቶ

www.abyssinialaw.com

ውባለም ግዛቸው ይባል የነበረውን በአሰቃቂ ሁኔታ ደብድበው ገለው እሬሳውን ከሻይ ቤት ራቅ አድርገው ጥለውት ይዞት የነበደርን ባለሰደፍ ክላሽ ጠመንጃ የወሰዱበት መሆኑን ዘርዝሮ ተከሳሾች ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾችም ሆነ የሥር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ስንሻው አለሙ ፍርድ ቤት ቀርበው የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በሁዋላ እምነት ክህደት ቃላቸውን ሲጠየቁ የወንጀል ድርጊቱን አለመፈፀማቸውን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን አራት ምስክሮቸ ቆጥሮ ሶስቱን ፍርድ ቤት አስቀርቦ አስምቷል፡፡ ከዚህም በሁዋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የማጣሪያ ምስክሮችን መስማት አስፈላጊ ነው ብሎ ትዕዛዝ ሰጥቶ የ1ኛ አመልካች ጎረቤት ናቸው የተባሉትን ግለሰብ የምስክርነት ቃል በመቀበልና የፖሊስ የምርምራ መዝገብ ሁሉ አስቀርቦ አይቶ አመልካቾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎች ቀርበው ተሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ስንሻው አለሙ በመከላከያ ማስረጃዎቹ የአቃቤ ሕግን ማስረጃዎችን አስተባብሎአል በማለት ከክሱ በነጻ ያሰናበተ ሲሆን የአሁኑን አመልካቾች ግን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው የአቃቤ ሕግ ማስጃዎችን አላስተባበሉም በማለት በአቃቤ በኩል ተጠቅሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ እና የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል የቅጣት አወሳሰኑን ከተሻሻለው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንፃር በማየት የወንጀሉ ደረጃ በእርከን 38 ስር እንደሚወድቅ ከለየና ለሁሉም አመልካቾች ሁለት ሁለት የቅጣት ማቅለያ በመያዝ ወደ እርከን 36 አውርዶ በዚሁ እርከን ስር አመልካቾች እያንዳንዳቸውን በ18 አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በመወሰን በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ ተያዘ ተብሎ በኢግዚቢትነት የተያዘው የጦር መሳሪያም የዚሁ ሰው መሆኑ ተረጋግጦ እንዲመለስላቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኋላ የሰበር ኤቱታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኘት ውሳኔ አፅንቶ የቅጣት ውሳኔውን ብቻ ከመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንጻር መታየት እንደነበረበት በምክንያትነት ይዞ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተያዘላቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በእያንዳንዱ ሶስት ሶስት እርከን መቀነስ እንዳለበትና በዚህም ስሌት መሰረት ቅጣቱ ወደ እርከን 32 እንደሚወርድ ገልፆ በዚሁ እርከን ለፍርድ ቤቱ በተተወው ፍቅድ ስልጣን መሰረት እያንዳንዳቸው በአስራ አራት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዚያ 29 ቀን 2007 ዓ/ም በጻፉት ሶስት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለን እንድንቀጣ የተወሰነው አቃቤ ሕግ

www.abyssinialaw.com

ምስክሮች በአይን ባላዩትና የስሚ ስሚ ምስክርነት ነው፣ በመከለካከያ ማስረጃዎችም የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል አስተባብለናል በማለት ዘርዝረው የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪ ቀርቦ በቁጥር ወየሂ/4173/መ/ቁ95/908 በቀን 21/01/2008 ዓ/ም በተፃፈ አራት ገፅ ማመልከቻ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው በሚታመን የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል መሆኑን ዘርዝሮና ውሳኔው ተገቢነት ያለው መሆኑን በመግለፅ ውሳኔው ሊጸና የሚገባው መሆኑን ጠቅሶ የጹሑፍ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ ፣ ከድርጊቱ አፈፃጸም ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካቾች ጥፋተኛ ተብለው በስር ፍርድ ቤቶች የመቀጣታቸውን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 671 (2) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከባድ የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል፣ ውባለም ግዛች ይባል የነበርን ግለሰብ ደብድበው ገድለው ሬሳውን ከሻይ ቤት ራቅ አድርገው ጥለው ይዞት የነበረውን ባለሰደፍ ክላሽ ጠመንጃ ወስደዋል በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካቾች ድርጊቱን መፈጸማቸውን ክደው ተከራክረውም አቃቤ ሕግ ሶስት የሰው ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ለትክክለኛ ፍትህ ሲል ማጣሪያ ምስክሮችን ከመስማቱም በላይ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ሁሉ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ እነዚህ የሕግ ማስረጃዎች ታይተውም አቃቤ ሕግ እንደክሱ አስረድቷል የሚል እምነት የበታች ፍርድ ቤቶች ደርሰዋል፡፡ ለጉዳዩ በማስረጃነት የተሰሙት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ይዘትም የሚከለተው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ያሳያል፡፡

አቶ ታዬ ብርሃን የተባል የአቃቤ 1ኛ ምስክር በሰጠው የምስክርነት ቃል በክሱ በተገለፀው ቀንና ቦታ ማታ ተከሳሾችና ሟች ሻይ ቤት ከምስክሩ ጋር ገብተው እንደነበር፣ ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት እንተኛ ተባብለው ይኼው ምስክርና አሊ የተባለው የአቃቤ ሕግ ምስክር ለሽንት ወጥተው ወደ አሁኗ 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ሲመለሱ የኩራዝ መብራት ጠብቶ የሽመልና የብርጭቆ ኳኳታ ድምጽ ሰምተው አሊ የተባለው ምስክር ምንድን ነው ሲል ምን ሰማህ ብሎ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አቶ ስንሻው አመራ መሳሪያ ሲያቀባብል ደንግጠው በመሮጥ ይኼው ምስክሩና አሊ የተባለው ምስክር ተበታትነው ከውጭ አድረው ከዚያ በነጋታው ውባለም ሞተ ተብለው ምስክሩ ከሟች ጋር የጋብቻ ዝድምና እንዳለው፣ ከበረሃው በእዛው እለት ድርጊቱ ተፈጸመ ወደ ተባለበት ሐሙሲት ከተማ ምስክሩ ሲሄድ

www.abyssinialaw.com

የቻለውም ሟች ዱቄት ይሰጣችኃል ተብሎ መሆኑንና በዚህ ምክንያት ድርጊቱ ሲፈፀም ማየቱን እንዲሁም ከ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ የገቡ መሆኑን ገልጾ መስክሯል፡፡

አቶ አሊ መኮንን የተባለው የአቃቤ ሕግ ምስክር በበኩሉ እንደ አቶ ታዬ ብርሃን በተመሳሳይ መመስከሩን ፍርድ ቤቱ ገልፆ የምስክርነቱን ቃል ዝርዝሩን በውሳኔው ላይ አላሰፈረውም፡፡ ቄስ ማማሩ ደመወዝ የተባለው የአቃቤ ሕግ ሶስተኛ ምስክር ደግሞ በክሱ በተገለጸው ቀን በነጋታው ጥዋት ከአገራቸው ወደ ሃሙሲት ከተማ ሞባይል ካርድ ሊሞሉ መጥተው ሳለ ሟች ሞተ ተብሎ ፖሊስ እንደአስጠራቸው፣ የሟች አስክሬን ከወደቀበት ቦታ ሂደው ሲመለከቱም የሟችን መታወቂያ፣ዱላ፣ ሽመልም ያገኙ መሆኑን፣ ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ቤት እስከ ሟች አስክሬን የደም ነጠብጣብ መመልከታቸውን እንዲሁም አልኮል የተቀባ የቁስል ማሸጊያ/ፋሻ/ ማግኘታቸውን፣ የአሁኑ 4ኛ አመልካች በስለት ተቆርጦ ታሽጎ ማየቱንና የሟችን አስክሬን ወደ አገሩ መውሰዳቸውን እንዲሁም ምስክሩም ራሱ ተጠርጥሮ ታስሮ እንደነበር፣ ነገር ግን ድርጊቱን እንዳልፈፀሙ፣ ድርጊቱን የፈጸመው ማን ነው የሚለውን ያጣራ መሆኑንና ከሟች ጋር በገንዘብ ተጣልተው በሽማግሌ የታረቁ መሆኑን፣ የሙሉ ቢተው ሚስት አቃቤ ሕግ በክሱ በገለፀው እለት አህያ ከውጭ ታስሮ ነበር፣ ድምፅ የአህያው ሳይሆን ሰው ሲያጓጉርና ሲንፈራገጥ ሰማሁ በማለት ለአለኸን ሚስት ተናግራ አለኸኝ ደግሞ ለምስክሩ የነገራቸው መሆኑን፣ አቃቤ ሕግ በክሱ በገለጸው እለት ሟች መሳሪያ ይዞ ከሟች አበጀ መንግስቴ ያስፈጨውን ዱቄት ከፋንታ ምስጋናው ማስቀመጡን መስማቱን፣ ሟች ልደር ብሏት ወንድ የለም ብዬ መልሼዋለሁ ብላ የነገረቻቸው መሆኑንና የሟችን አስክሬን መጀመሪያ ያገኘው ልጃለም ስንታየሁ ነው በማለት መስክሯል፡፡ ከዚኀም በኃላ ፍርድ ቤቱ የአሁኗ አመልካች ጎረቤት ሰው ሲያጓጉር ሰምቻለሁ ብላ ተናግራለች ተብሎ በሶስተኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር በመገለፁ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ያመች ዘንድ ምስክሯ ቀርባ እንድትሰማ ትዕዛዝ ሰጥቶ ምስክሯ ቀርባ የተሰማች ሲሆንን ምስክሯ በሰጠችው የምስክርነት ቃልም የአሁኗ 1ኛ አመልካች ጎረቤታቸው መሆናቸውን ገልፀው ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም ምሽት የሰሙት ድምጽ የለም፣ አህያም ከውጭ አልታሰረም በማለት የመሰከረችና ምስክርነቱ በዚሁ ያበቃ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በማየት ድምጽ መሰማቱን፣ አህያ መስሎኝ ነው እንጂ በማለት መገለጹን አገንዝቦ አልፎታል፡፡ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በመመርመር ዱቄት 1ኛ እና 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እንዲያመጡ ላካቸው የተባለውን ስንሻው ጎሹ የተባለውን ግለሰብ ቀርቦ እንዲሰማ ትዕዛዝ ሰጥቶ የክፍሉ ፖሊስ ሰንሻው ጎሹ የተባለ ግለሰብ እንደሌለና ሊያገኘው ያለመቻሉን ለፍርድ ቤቱ በመግለፁ ምክንያት ይኼው ግለሰብ በተጨማሪ ማስረጃነት ሳይሰማ ታልፎአል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወ.ሕ.አ. 23 (1)

www.abyssinialaw.com

እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በሙሉ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በወ.ሕ.አ. 32(1) ስር ተደንግጎአል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወ.ሕ.አ. 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል መማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቶአል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 142 መሰረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከአንድ በላይ ሰዎች በተከሰሱበት የወንጀል ጉዳይም የእያንዳንዱ ተከሳሽ ሚና እና የተሳትፎ ደረጃው በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ በከሳሽ ወገን በኩል በሚቀርበው ማስረጃ ነጥሮ ሊወጣ የሚገባ መሆኑን ስለመወንጀል አፈፃጸም ተካፋይ መሆን የሚመለከቱ የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች በተለይም አንቀፅ 32 እና 40 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በዐ/ሕግ በኩል በቀረበው የአካባቢ ማስረጃ የተረጋገጡት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ሟች ከ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ገብተው እንደነበርና በሻይ ቤቱ ከሟች ጋር ነበርን ያሉት 1ኛ እና 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ከሻይ ቤቱ ለሽንት ወጥተው ሲመለሱ በቤቱ የነበረው የኩራዝ መብራት ጠፍቶ የሽመልና የብርጭቆ ኳኳታ ሰምተው ምንድነው የሚለውን ጥያቄ 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ሲያቀርብ በስር 1ኛ ተከሳሽ ተከሳሽ የነበረውና በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል አስተባብሎአል ተብሎ በነጻ የተሰናበተው አቶ ስንሻው አመራ የጦር መሳሪያ ሲያቀባብሉ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ደንግጠው የራሳቸውን ሕይወት ለማትረፍ ተበታነው ሸሽተው አድረው በበነጋው ሟች ሞተ ተብሎ እንደተነገራቸውና የሟች አስክሬንም ከአሁኗ 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ራቅ ብሎ ተጥሎ መገኘቱን ነው፡፡

በመሰረቱ እነዚህ ፍሬ ነገሮች ደግሞ ብቻቸውን በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 ስር በግልጽ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ ነው

www.abyssinialaw.com

ለማለት የሚያስችሉ አይደሉም። ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ሟቹ በአመልካቾቹ ተገድሏል ለማለት የማያስደፍር ስለመሆኑ የምስክሮች ዝርዝር የምስክርነት ቃሉ አያሳይም፡ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በተለይ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ሟችን ከእነማን ጋር እንደነበር ከማየታቸው ውጪ አመልካቾቹ በወንጀሉ ድርጊት የነበራቸውን ሚና፣ ተሳትፎና ደረጃውን ገልጸው የመሰከሩ አይደሉም። አመልካቾች በጊዜና በቦታው ነበሩ ስለተባለ ብቻ ግን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያስችል የወንጀል ጉዳይ ማስረጃ ምዘና መርህ የለም። እያንዳንዱ አመልካች በወንጀሉ የነበረው ተሳትፎና ደረጃው በቂ በሆነ ሁኔታ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ይህ ካልሆነ ግንሞ ፍ/ቤቱ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 141 መሰረት ተከሳሽን ማሰናበት የግድ የሚል እንጂ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ መስጠት የሕግ መሰረት አይኖረውም። ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾች በሟች ሕይወት ማለፍ የነበራቸው ተሳትፎ ተለይቶ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ከሟቹ ጋር ነበሩ ስለተባሉ ብቻ ድርጊቱን እንደፈጸሙ በአቃቤ ሕግ ምስክሮች ተረጋግጦባቸዋል ተብሎና በመጨረሻም የዐ/ሕግን ማስረጃ አላስተባበለም በማለት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠታቸው ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የሆኑ የወንጀል ሕግ እና የወንጀል ስነስርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን የጣሰ መሆኑን ተገንዝበናል። የተጠሪ ምስክሮች በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /circumstantial Evidence/ የሠጡ ናቸው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተገለጸው የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ስለ አከባቢ ማስረጃ ምዘና መርህ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ አይደለም። ለአንድ የአከባቢ ማስረጃ ክብደት ለመስጠት ማስረጃው ጠንከራ መሆንን ይጠይቃል። የአከባቢ ማስረጃ ስለጉዳዩ በቀጥታ የማይነግረን በመሆኑ የተወሰኑ ፍሬ ነገሮች መኖራቸው ወይም ያለመኖራቸው ሲረጋገጥ ወደ አንድ ድምዳሜ የምንደርስበት የማስረጃ አይነት ነው። ስለመሆኑም ፍሬ ጉዳዮቹ ተያያዥነት ያላቸውና ጠንከራ ሊሆኑ ይገባል። ከዚህ ውጪ ተያያዥነት የሌላቸው ፍሬ ነገሮች መሰረት ተደርጎና የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ያለመኖር ሳይረጋገጥ ለአከባቢ ማስረጃ ክብደት መስጠት የማስረጃው አይነት የምዘና መርህን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም። በአገራችን የህግ ሥርዓት ምስክሩ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች በአይኑ የታዘበውን በጆሮው የሰማውንና የሚያውቀውን ፍሬ ጉዳይ ሊስመሰክር እንደሚችልና የምስክሩም ቃል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል። በተያዘው ጉዳይ ግን የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ቃል የአከባቢ ማስረጃ ከሚመዝንበት እና የስሚ ስሚ ማስረጃውም ለጉዳዩ በማስረጃነት ከሚሰድበት አግባብ ወጪ የመሰከሩ ናቸው ከሚባል በስተቀር በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የአመልካቾችን የወንጀሉን ተሳታፊነት ያረጋገጡ ናቸው ተብሎ የሚወሰዱ ሁነው አልተገኘም። በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረው ግለሰብ በ1ኛ እና 2ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ሟች ሞተ በተባለበት ሻይ ቤት በመሳሪያ ያስፈራራቸው ስለመሆኑ የተነገረ ቢሆንም ይህ ግለሰብ ከወንጀሉ ነፃ ከመውጣቱም በላይ ከሟች ተወሰደ የተባለው

www.abyssinialaw.com

መሳሪያም በኢግዚቪትነት የተያዘ ስለመሆኑ ያለመረጋገጡም የአመልካቾችን የወንጀል ተሳታፊነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚከተው ሁኖ አግኝተናል፡፡ አቃቤ ሕግ በዚህ ሰበር ችሎት አመልካቾች ተጠያቂነት የለባቸውም ተብሎ ቢወሰን በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅጽኖ ገልፆ መከራከሩ አመልካቾች በወንጀሉ የነበራቸውን ተሳትፎና በወንጀል ጉዳይ ማስረጃ የሚመዘንበትን መርህ መሰረት ያላደረገና የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለል ከሳሽ ዐ/ሕግ በአመልካቹ ላይ ባቀረበው የግፍ ግድያ የወንጀል ክስ መሰረት ለማስረዳት በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባልወጣበት ሁኔታ ክሱን የተመለከተው የዞን አንድ ከ/ፍ/ቤት ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ በመጨረሻ የሰጠውና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ በአብላጫ ድምጽ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0206782 ጥር 26 እና የካቲት 06 ቀን 2006 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ./ቁጥር 09870 መጋቢት 23 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናውና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 39613 በ12/06/2007 ዓ.ም. የተሻሻለው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሰረት በድምጽ ብልጫ ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ አመልካቾች ወንጀሉን ማድረጋቸውን ያላስረዳ እና በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ ያልተወጣ በመሆኑ አመልካቾች ከተከሰሱበት የከባድ ውንብድና የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. በአመልካቾች ላይ ተጥሎ የነበረው የአስራ አራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተሻረ በመሆኑ የሚፈለጉበት ሌላ ጉዳይ አለመኖሩን አረጋግጦ አመልካቾችን ዛሬውኑ ከእስር እንዲለቃቸው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ትዕዛዝ ይተላለፍ፡፡ ይፃፍ፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች እና ለአውሲረሱ ማረሚያ ቤት ይላክ፡፡ ለአመልካቹም በዚያው በኩል ይድረስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

www.abyssinialaw.com

## የልዩነት ሐሳብ

ሰሜ በ5ኛ ላይ የተጠቀሰው ዳኛ የአብላጫ ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ እንደሚከተለው በመለየት ሐሳቤን አስቀምጣለሁ፡፡ ከዚህ መዝገብ ውስጥ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ያቀረበው ክስ የስር 1ኛ ተከሳሽ እና የአሁን አመልካቾች የወ/ህ/ቁ.32/1፣ሀ/ እና 671(2) በመተላለፍ ጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ/ም በግምት ከምሽቱ 4:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት ባለው ጊዜ የግል ተበዳይ ዉባለም ግዛቸው የሚባለውን በአሰቃቂ ሁኔታ ደብድበው ገድለው አሬሳውን ጥለው ይዞት የነበረውን ጠመንጃ የወሰዱ በመሆኑ ከባድ የውንበድና ወንጀል ፈጽመዋል ተከሷል፡፡ አመልካቾች ፍ/ቤት ቀርበው በሰጡት የእምነት ክህደት ቃላቸው ወንጀሉን አልፈጸምንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቶች የግራ ቀኝ የሰው ምስክሮች በመስማት ተጨማሪ የሰው ማስረጃ መስማት፣ የፖሊስ ማስረጃ በማስቀረብ በማየት በሰጡት ውሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ስንሻው አለሙ ከክሱ በነጻ በማሰናበት፣ የአሁን አመልካቾችን በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው በማለት የእስራት ቅጣት የወሰኑ መወሰናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካቾችን ወንጀሉን አልፈጸምንም፣ በመከላከያ ምስክሮቻችን ተከላክለናል፣ የስር ፍ/ቤት የጥፋተኝነትም ሆነ የእስራት ውሳኔ ተሽሮ በነጻ እንዲንሰናበት የሚል አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች የተከሰሱበተን ወንጀል ስለመፈጸማቸው የዐ/ህግ ምስክሮች በሚገባ ስላረጋገጡ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናልን በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ካረጋገጡት ነገሮች አንጻር ማይት አስፈላጊ ነው፡፡ የዐ/ህግ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች የወንጀል ድረጊቱ ተፈጸመ በተባለ ቀን ምሽት በሚች ጋር 1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ከቀኑ 11:00 ሰዓት ጀምሮ እንደነበሩ፣ ሚችን እዛው ትተው ለሽንት ወጥተው ስመለሱ የሻይ ቤቱ መብራት ጠፍቶ የሻይ ብርጭቆና የአረቂ መለኪከ ኳኳ የሚል ድምጽ እንደሰሙ፣ ዓሊ የተባለው ምስክር ምንደነው ብሎ ሲጠይቅ የስር 1ኛ ተከሳሽ ምን ሰማህ በማለት መሳሪያ ሲያቀባብል ለህይወታቸው ፈርተው ሸሽተው እንደሄዱ መስክሯል፡፡ 3ኛ ምስክር ደግሞ በሰጠው ቃል ጠዋት ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ ሚች ወድቆ ሞቶ እንደገኘ ሚች ከወደቀበት እስከ ከ1ኛ አመልካች ቤት የደም ነጠብጣብ መኖሩን መስክሯል፡፡

ስለዚህ እነዚህ የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይ የአከባቢ ማስረጃ ይሁኑ እንጂ ከሚች ጋር የ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት እንደነበሩ እና ሌሎች አመልካቾች እዛው እንደነበሩ ሚችን ሻይ ቤቱ ውስጥ ትተው ለሽንት ወጥቶ ስመለሱ የሻይ ቤቱ መብራት ጠፍቶ የሻይ ብርጨቆ እና የአርቂ መለኪያ ኳኳታ ድምጽ እንደሰሙ እና 1ኛ ተከሳሽ ወደ ቤት

www.abyssinialaw.com

እንዳይገቡ አድርጓቸው ለሕይወታቸው ሲሉ ሸሽቶ ከቦታው መሄዳቸው ሲታይ ሟች ከዚህ ሻይ ቤት እንደነበር ያመለክታል፡፡ ሟች በዚህ ሻይ ቤት ውስጥ ከምስክሮች ጋር እንደነበረ በመረጋገጡ፣ ሟች ከምስክሮቹ ጋር አብሮ ወጥቶ መሄዱ እስካልተረጋገጠ ድረስ፣ ምስክሮቹ ከሄዱ በኋላ እንኳን ወጥቶ መሄዱ እስካልተረጋገጠ ድረስ፣ ሟች በ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት እያለ የተገደለ መሆኑን ያመልክታል፡፡ በዚህ ሻይ ቤት ውስጥ በዛን ሰዓት ከአመልካቾች በቀር ሌላ ሰው መኖሩን የሚያረጋግጥ ነገር የለም፡፡ አመልካቾች በ1ኛ አመልካች ሻይ ቤት ውስጥ እያሉ ሟችም እዚያው ሻይ ቤት ውሳጥ እያለ የግዱያ ወንጀል የተፈጸመበት በመሆኑ አመልካቾች ውጭ ሌላ ሰው ይህን የግድያ ወንጀል ፈጸሟል ለማለት የሚያስችል ነገር የለም፡፡ ከዚህም በላይ የስር ፍ/ቤቶች የፖሊስ ምርምራ መዝገብ ማስቀረበ ያዩ መሆናቸውን መዝገቡን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ እነዚህ የዐ/ህግ ምስክሮች የአከባቢ ምስክሮች ቢሆኑም አመልካቾቹ ሟች ዉባለም ግዛቸው የሚባለውን ሰው ገድለው ይዞ የነበረውን ጠመንጃ መውሰዳቸውን ለማስረዳት በቂ ማስረጃ (sufficient evidence) ሊሆን የማይችሉበት ምንም ተጨባጭ ምክንያት የለም፡፡ ይህ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት አመልካቾች በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.142(1) መሰረት መከላከያ ምስክሮቻቸውን አቅርበው እንዲከላከሉ ብይን መስጠታቸውን በአግባቡ ነው፡፡

በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካቾች ባቀረቡት የሰው ምስክሮች የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ጥርጣሬ ላይ እንዲወድቅ አድርገዋል ወይ? የሚለውን ነጥብ መልስ ማግኘት ያለበት ነገር ነው፡፡ አመልካቾች መከላከያ ምስክሮቻችው ቃል ሲታይ 1ኛ አመልካች ቤት መጥተው ቆይተው የሄዱ ጊዜ፣ እሮንድ መጠበቃቸው፣ ሌሎች ተከሳሾች 1ኛ አመልካች ቤት ስለመግባታቸው ጋር ተያይዞ የሰጡት ቃል የዐ/ህግ ምስክሮችን ጥርጣሪ ውስጥ አስገብቷል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ የመከላከያ ምስክሮች በተጠቀሰው ምሽት 1ኛ አመልካች ቤት ሻይ ወይም አረቂ ለመጠጣት ሟች እና የዐ/ህግ ምስክሮች በእርግጠኝነት አለመምጣታቸውን ያመሰከሱት ነገር የለም፡፡ እነዚህ ምስክሮች በእርግጠኝነት ሟች እና የዐ/ህግ ምስክሮች አለማምጣታቸውን ካላረጋገጡ ደግሞ የዐ/ህግ ምስክሮች የሰጡትን ቃል ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱበት አቅም አይኖራቸውም፡፡ ይህ በመሆኑን የስር ፍ/ቤቶች አመልካቾች የዐ/ህግ ምስክሮችን የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ጥርጣሬ ላይ በመጣል አመልካቾች ተከላክለዋል የሚያስብላቸው ነገር ባለመኖሩ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ሲታይ የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡትን እውነታ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መቀበል ይገበዋል፡፡ በመሆኑም የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና አማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም እላለ፡፡

www.abyssinialaw.com

ቅጣትን በተመለከተ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የጽኑ እስራት ቅጣት ሊጸና ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል እንጂ አመልካቾች ነጻ እንዲሰናበቱ የሚያበቃቸው ምክንያት የለም በማለት የልዩነት ሐሰቤን አስቀምጣለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 118252

ቀን 24/05/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንደሻው አዳነ

ቀንዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ሀብታሙ አያሌው - ጠበቃ አመሃ መኮንን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ዐ/ህግ ብርሃኑ ወንድምአገኘሁ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ በሽብር ወንጀል የተከሰሰ ሰው ከክሱ ምንም መከላከል ሳያስፈልገው በነጻ ሲሰነበት በዚሁ ብይን አቃቤ ህግ ይግባኝ ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የስር ፍርድ ቤት የነጻ መለቀቅ ብይን እንዲታገድለት ሲያመልክት ተቀባይነት የሚያገኝበትን የህግ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሌሎች ዘጠኝ ግልሰቦች ጋር የተከሰሱበት የጸረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ከሽብር ቡድን ጋር የተለያዩ ግንኙነቶች በመፍጥር የሽብር ቡድኑ በኢትዮጵያ ሊያደርግ ያሰበውን የሽብር እንቅስቃሴ በመምራት በስሩም አባላትን በመመልመል፣ ከሽብር ድርጅቱ አባልና አመራሮች ጋር ግንኙነት በማድረግ፣ የሽብር ቡድኑን ዓላማ፣ ተግባር እና ተልእኮ ለመፈጸም በመንቀሳቀሳቸው በፈጸሙት የሽብርተኝነት ድርጊት ማቀድ፣ መዘጋጀት፣ ማሴር፣ ማነሳሳት እና ሙከራ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው፡፡ አመልካቹ የወንጀል ድርጊቱን ክደው በመከራከራቸው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸው ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቶአል፡፡ ከዚህም በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አቃቤ ሕግ አመልካቹ የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ስለመፈፀማቸው እንደ ክሱ አላስረዳም በማለት አመልካቹን ምንም መከላከል ሳያስፈልጋቸው ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱና ማረሚያ ቤቱም ከእስር

www.abyssinialaw.com

ወዲያውኑ እንዲፈታቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ብይን የአሁን ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑን አመልካች እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሳይሰጥ አመልካቹ በነፃ እንዲሰናበቱ በተሰጠው ብይን መሰረት ከእስር እንዲለቀቁ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲታገድ የአሁኑ ተጠሪ አመልክቶ ፍርድ ቤቱም የተጠሪን ጥያቄ መነሻ በማድረግ የአመልካችን የነፃ መለቀቅ ትዕዛዝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188(5) ድንጋጌ መሰረት ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤተታ የቀረበውም ይህንኑ የእግድ ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ የተሰጠው ትዕዛዝ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የታገደው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ መሆኑን የሚዘረዝር ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ትዕዛዝ እና ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት እንዲታይ በሰበር አጣሪ የተያዘው ጭብጥ አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188(5) ተጠቅሶ መታገዱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ፍርድ ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርጎ ዳኝነት በመስጠት ሂደት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መለየትና ተፈጻሚ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ የፀረ ሽብር አዋጅ ተጠቅሶ ክስ የቀረበበት ሰው ክርክሩ የሚመራበት አግባብ በአዋጁ አንቀጽ 36 የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጸረ ሽብር አዋጁን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ ክርክሮች በአዋጁ በራሱ በተጠቀሱት የስነ ስርዓት ደንቦች እንዲሁም ከአዋጁ ጋር ተቃርኖ ከሌለ ደግሞ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግና በ1954ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ሰርዓት ሕግ የሚመሩ መሆኑን ተጠቃሹ የአዋጁ ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የጸረ ሽብር አዋጅ መሰረት ክስ ቀርቦበት የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ከተሰሙ በኋላ አንድ ሰው በነፃ ቢሰናበት አቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ብሎ የስር ፍርድ ቤት የነፃ መለቀቅ ብይንን ማሳገድ የሚችልበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን የአዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች አያሳዩም፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 36 መሰረት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 188/5/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳም ይህ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ አርዕስቱ ፍርድ እንዳይፈፀም ስለማገድ የሚል ያለው ሁኖ ዘርዝሮ ይዘቱ በተለይም የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር አምስት ሲታይ ይግባኙ ከመሰማቱ በፊት

www.abyssinialaw.com

በማንኛውም ጊዜ ወይም ይግባኙ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ፍርዱ እንዲታገድ ለይግባኝ ፍርድ ቤት ማመልከት እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ የዚህ ንዑስ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ በአንቀፁ ንዑስ አንድ ድንጋጌ ስር ያለውን ድንጋጌ ዉጤታማ ለማድረግ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን የወንጀል ጉዳይ ከሰው ልጅ ነፃነት፣ ሕይወትና ክብር ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ፍርድ ቢፈፀም በእነዚህ መብቶች ላይ ሊመለስ የማይችል ጉዳት ሊደርስ ስለሚችል ከወዲሁ ለመከላከል ነው ተብሎ መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ፍርዱ በተከሳሹ ከተሰጠ ተከሳሹ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብሎ ሲቀርብ የበታች ፍርድ ቤትን ውሳኔ የበላይ ፍርድ ቤቱ ማገድ የሚችልበትን አግባብ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 188/5/ ድንጋጌ የሚያስገነዝብ ከመሆኑ ውጪ ከሳሽ ወገን በነፃ መለቀቅ ላይ ይግባኝ ብሎ ሲሄድ ፍርዱ እንዳይፈፀም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለመስጠት መነሻ የሚያደርገው ድንጋጌ ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሆኖም አንድ ተከሳሽ በነፃ ሲሰናበት አቃቤ ሕግ ይግባኝ ብሎ ፍርዱን ለማሳገድ የሚችልበት የሕግ መሰረት የለም ማለት ግን አይደለም፡፡ የፀረ ሙስና ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎችና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 63 እና 67 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌወችን መሰረት በማደረግ በነፃ የተለቀቀ ተከሳሽ በማረሚያ ቤት ሁኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ማድረግ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ግን ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በነፃ እንዲሰናበቱ የተሰጠውን የስር ፍርድ ቤትን ብይን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 188/5/ መሰረት ያገደው ድንጋጌው ለጉዳዩ አግባብነት ሳይኖረው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው የፍርድ ቤቶች መደበኛ የስራ ጊዜ በተዘጋበት ተረኛ ችሎት በተመደበበት አግባብ ሲሆን ዋናውን ጉዳይ ሳይመረምር የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንደሚመጣ ብሎ ከአዘዘ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ ከትዕዛዙ ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ቀርቦ መ/ሰጪን የሚያስቀርብ የህግና የፍሬ ነገር ነጥብ ስለመኖሩ የሚያሳይ ትዕዛዙ በተረኛው ችሎት አልተሰጠም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ከቀረበ በኂላ በዋናው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙን ለማከራከር የሚያስችል የህግና የፍሬ ነገር ነጥብ መኖሩ ላይ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው መደበናው ችሎት መሆኑን ተረኛው ችሎት በ15/12/2007 ዓ/ም ከሰጠው ትዕዛዝ በኃላ ያሉት ጊዚያትና የክርክር ሂደቶች የሚያስገነዝቡት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዋናውን ጉዳይ ማየት የቀጠለው መደበኛ ችሎት አመልካች ጉዳዩን በውጪ ሁነው የማይከታተሉበት ህጋዊ አግባብ መኖር ያለመኖሩ ላይ አግባብነት ያለውን ህግና ድንጋጌ በመለየት ብይን ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

www.abyssinialaw.com

በ15/12/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 117340 በ15/12/2007 ዓ/መ የተሰጠው እግድ የህግ መሰረት የለውም በማለት በድምጽ ብልጫ ሽረናል፡፡ በሌላ በኩል መደበኛው ችሎት በዋናው ጉዳይ ክርክር ቀጥሎ ከሆነ አመልካች ከእስር ውጪ ሁነው ጉዳዩን መከታተል የማይችሉበት የህግ መሰረት መኖር ያለመኖሩን ተመልክቶ ተገቢውን ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር ሶስት የተመዘገብኩት ዳኛ የስራ ባልደረቦቼ በሰጡት ፍርድ ባለመስማማት የልዩነት ሐሳቤዩን እንደሚከተለው አስፍሬአለሁ፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 117340 ነሀሴ 15 ቀን 2007 ዓ/ም ችሎቱ የሰጠው ትዕዛዝ ሲሆን በትዕዛዝ ክፍሉም የቀረበውን ይግባኝ ቅሬታ መርምሮ ተገቢ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 158194 በ14/12/2007 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ከመፈጸም ታግዶ እንዲቆይ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 188(5) መሰረት ትዕዛዝ መስጠቱን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ የውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡

የአሁኑ አመልካች አቶ ሀብታሙ አያሌው ከሌሎች ዘጠኝ ግለሰቦች ጋር ከተከሰሱበት የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 የተመለከተውን በመተላለፍ የሽብር ወንጀል በማቀድ፣ በመዘጋጀት፣ ማሴር እና መነሳሳት ወንጀል ዐቃቤ ህግ እንደክሱ አላስረዳም ተብሎ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበቱና ማረሚያ ቤቱም ከእስር ወዲያውኑ እንዲፈታቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመወሰኑ ምክንያት የአሁኑ ተጠሪ በጉዳዩ ይግባኝ በመጠየቅ ፍርዱ እንዳይፈጸም ዕግድ አሰጥቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሰረታዊ የክርክር ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሰረቱ አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ ሁኖ ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(2) በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ የሚሆነው አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ (Final court decision) ያገኘ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊ ነጥብ ስለመሆኑ የድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝቡናል፡፡ በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ ባለገኙ ጉዳዮች ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ለሰበር ብቁ ያልሆኑ የመጨረሻ ፍርድ ያላገኙ ጉዳዮች በሰበር ሰሚ ችሎት ሊስተናገዱ የሚችሉበት ስርዓት አይኖርም፡፡

አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆን ያለመሆኑን ለመለየት በመመዘኛነት መታየት ያለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች ምን ምን ናቸው? የሚለው አንኳር ነጥብ አገሪቷ ከምትከተለው የህግ ስርዓት ጋር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል፡፡ አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው አከራካሪ ጭብጥ ለመፍታት እንደመነሻ ከሚወሰዱ ነገሮች በፍርድ ቤቶቻችን የዳበረው አሰራር፤ የምንከተለው የህግ ስርዓት እና ሰበር ሰሚ ችሎቱ የራሱ የሆነ የስነ ስርዓት ህግ ያልተቀረጸለት በመሆኑ በህገ መንግስቱ የተጠቀሰው “የመጨረሻ ውሳኔ” የሚለው ቃል ይዘት ከህግ አወጭው ሐሳብ በተጣጣመ መልኩ በመተርጎም እና በመደበኛ እንደሁም ከስነ ስርዓት ህጎቻችን መሰረታዊ ድንጋጌዎች አንጻር መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተያያዘ በስነ ህግ (jurisprudence) የዳበረው የአተራጓጎም ስርዓት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ሲባል መሰረታዊ ህጋዊ መስፈረቱ ምንድነው? የሚለው እንደአግባብነቱ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆንበት ስርዓት ይኖራል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው መሰረታዊ ነጥብ ሊመዘን የሚችለው በተያዘው ጉዳይ ምንም የተንጠለጠለ ነገር የሌለው፤ የይግባኝ ሂደቱ አግጦ የጨረሸ፣ በጉዳዩ በተያዙ አከራካሪ ነጥቦች መልሶ ማየት በማያስችል መንገድ ዕልባት የተሰጠበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በስነ ህግ በዳበረው የአተረጓጎም ስርዓትም አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘነው የሚለው ሲታይ፡- final decision generally is one which ends the litigation on the merit and leaves nothing for the court to do but execute the judgment በማለት ትርጉም የተሰጠው ሲሆን ይህ ትርጎም በግርድፍ ወደ አማርኛ ስንመለሰው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ አገኝቷል ለማለት የሚቻለው በሚያከራክረው ጭብጥ ላይ የመጨረሻ መቋጫ ያገኘ ሲሆን እና ጉዳዩ እንደ ፍርዱ ከመፈጸም ወጭ ሌላ አማራጭ የሌለው የውሳኔ ዓይነት መሆኑን ሲርጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተያየዘ በመጀመሪያ መቃወሚያ ወይም ጊዜያዊ  አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ ላይ የሰበር አቤቱታ መቅረብ እንደማይችል በዚህ

www.abyssinialaw.com

ረገድ የዳበረው የሰነ ህግ ትርጉም ያመልከታል፡፡ (preliminary ruling and temporary injunctions may not qualify a case to be reviewed by way of cassation) ከዚህ የምንገነዘበው ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ትዕዛዙን በሰጠው ችሎት በራሱ ጊዜ መልሶ ሊያስተካክለው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው የሚችል ነው፡፡ የመጀመሪያ መቃወሚያ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ትዕዛዞች በተከራካሪ ወገን መብት እና ነፃነት ላይ ለጊዜው ገደብ አይጥሉም ባይባልም በዚህ አግባብ የሚሰጥ ትዕዛዝ ግን የመጨረሻ ውሳኔ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከእስር እንዲፈቱ የተሰጠው ትዕዛዝ ለጊዜው መታገዱን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዕግድ የሰጠበት የህግ ድንጋጌ ተገቢ ባይሆንም የትዕዛዙ ይዘት ሲታይ ግን አመልካች ከእስር እንዲፈቱ ገደብ የተደረገው ጉዳዩ በይግባኝ እስከሚታይ እንጂ ሊታረም የማይችል በፍሬ ጉዳዩ (merit of the case) የመጨረሻ ውሳኔ መስጠቱን አያሳይም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ለሰበር ብቁ የሚሆነው የተሰጠው ትዕዛዝ (ውሳኔ) ፍርድ ይዘትና መንፈስ ሲታይ የመጨረሻ እና ጉዳዩ በያዘው ፍ/ቤት መልሶ የማይታርም ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በአመልካች ላይ የቀረበው የዐቃቤ ህግ ይግባኝ ፍርድ ቤቱ ሊቀበለው ወይም ላይቀበለው ይችላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች በእስር ይቆይ ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረበው ይግባኝ አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ እና የዐቃቤ ህግ ክስና ማስረጃ እንዲከላከል የሚታዘዝ ከሆነ አመልካች የተጠረጠሩበት ወንጀል ዓይነትና ክብደት መሰረት ተደርጎ የዋስትና ጉዳይ የሚታይ ይሆናል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን የሚያጸና ከሆነም ስርዓቱን ጠብቆ ለሰበር የሚቀርብ አቤቱታ ቢኖርም ባይኖርም ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ የሚገኝ በመሆኑ የአመልካች በእስር ይቆይ ትዕዛዝ ህጋዊ ውጤት በተሰጠው ውሳኔ ምክንያት የሚያበቃ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ችሎት አመልካች ከእስር እንዳይለቀቁ የሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው በአመልካች ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ ይዘት እና ባህሪ ችሎቱ በራሱ ጊዜ መልሶ የሚያርመው ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ያልቀረበ ጊዜያዊ ዕገዳ (temporary injuction) መሆኑ እየታወቀ ለሰበር ብቁ ነው መባሉ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንኡስ አንቀጽ (3) (ሀ) እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት አይነተኛ ዓላማ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ በማረም የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የሰበር

www.abyssinialaw.com

ጽንስ ሐሳብና ዓላማ የምንረዳው ነው፡፡ የሰበር ስርዓት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ውሳኔዎች በማረም በአንድ አገር በተቻለ መጠን ወጥ የሆነ የህግ አተርጓጎም እና አፈጻጸም (in order to attain uniform application and interpretation of laws throughout the nation) እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አንድ ጉዳይ በሰበር እንዲታይ እንደመሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ የሚወሰድ አስገዳጅ ህጋዊ መስፈርት ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆን ያለመሆኑን ህገ መንግስቱና ተከታይ አዋጆች መሰረት በማድረግ መመዘን ነው፡፡ ህግ አወጪው የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የሚፈጸም መስረታዊ የህግ ስህተት ካለ እና ይህ ስህተት ሳይታረም እንደረጋ ወይም እንደጸና የሚቆይ ከሆነ በአንድ አገር ህዝብ፤ መንግስት እና ዜጎች መብትና ጥቅም ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ የህግ የበላይነትን (rule of law) ከማረጋገጥ አንጻር ያለው ዓይነተኛ ትርጉም እና ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ታሳቢ በማደረጉ ስለመሆኑ ከህገ መንግስቱ እና ተከታይ ድንጋጌዎች (አዋጆች) የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ሰበር ሰሚ ችሎቱ መሰረታዊ ያልሆኑ የህግ ስህተቶች የማረም ስልጣን ይሁን ኃላፊነት አልተሰጠውም፡፡ የፍሬ ነገር ክርክር እና የማስረጃ ምዘና ስርዓትም ከሰበር ስልጣን ውጭ መሆኖቸው ልብ ይሏል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪ ሁኖ የቀረበው የፍርዱ ለጊዜው እንዳይፈጸም የማገድ ጉዳይ በአመልካች ላይ ለጊዜው በእርስር መቆየትን ማስከተሉ ግልጽ ቢሆንም የተረኛ ችሎቱ ትዕዛዝ የማይታረም የመጨረሻ ውሳኔ (ትዕዛዝ) ነው ለማለት የሚያስችል አንዳችም የህግ መሰረት የለውም፡፡

አከራካሪው ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በክርክር ጊዜ ሊያረመው የሚችል ወይም የይግባኝ ሂደቱ ካበቃ በኃላ ህጋዊ ውጤቱ የሚያበቃ ትዕዛዝ መሆኑ እየታወቀ እንደ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ መወሰዱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በእነዚህ ሁሉም ምክንያቶች የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረኛ ችሎት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙ እስከሚታይ (እስከሚሰማ) ማገዱ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዘዝ ሰጥቷል ከሚባል በስተቀር የመጨረሻ ውሳኔ እንደሰጠ መቆጠሩ በህጉ አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ በጊዜያዊ ዕግድ ላይ የተመሰረት እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆኑን ግንዘቤ በመወሰድ ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት መዝገቡ መዝጋት ሲገባው በፍሬ ጉዳዩ ውሳኔ እንደተሰጠ ግምት በመወሰድ ውሳኔ መስጠቱ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተመለከተው “የመጨረሻ ውሳኔ” (Final decision) መስፈርት የማያሟላ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ለሰበር ብቁ አይደለም በማለት በልዩነት ሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 111498

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አቃቤ ሕግ

- የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ ሃብታሙ ካርሎ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በሀድያ ዞን የሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱም ይዘትም፡- ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2)(ሐ) ስር በመተላለፍ ተጠሪ በሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት ለማድረስ አስቦ በቀን 14/05/2006 ዓ/ም ከቀኑ በግምት 6፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በሆሳዕና ከተማ ሜእእል አምባ ቀበሌ ልዩ ስሙ ውሃዋና ፊት ለፊት ባሉ መጋዘኖች አከባቢ ወ/ሮ ነፃነት አለሙ የተባለችውን ሚስቱን አንገቱን አንቆ በመያዝ አንድ ጊዜ በቀኝ እጁ በጥፊ ፊቷን ሲመታት በአፏና በጥርሷ ላይ ደም ከመፍሰሱም በላይ በግንባሯ ላይ በቦክስ አንድ ጊዜ ሲደግማት ወዲያውኑ መሬት ላይ እንደወደቀች ፖሊሶች ደርሰው ያስጣሉት በመሆኑ በሰው አካል ላይ ቀላል የአካል ጉዳት አድርሷል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ክሱ ድርሶት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ሲጠየቅ ወንጀሉን አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ሁለት የሰው ምስክሮችን ከሰማና ማስረጃዎቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ከመረመረ በኃላ በግል ተበዳይ ላይ ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ተግባር ስለመፈፀሙ የተመለከተ ምስክር የሌለ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ ተጠሪን

www.abyssinialaw.com

ከክሱ ምንም መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ ያሰናበተው ሲሆን አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን፣ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ሳይጠራ ቅሬታው ተሰርዞበታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በግል ተበዳይ ላይ በተጠሪ የአካል ጉዳት ስለመድረሱ በተረጋገጠበትና ማን እንደአደረሰው ደግሞ ለፍርድ ቤት ቀርበው የምስክርነት ቃል የሰጡት ፖሊሶች በምርመራ ጊዜ መስክረው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ መቀየራቸው እየታወቀ የሥር ፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል ሲቀበል ተገቢውን ጥያቄ ሳይጠይቅና የግል ተበዳይ ቀርባ እንድትመሰክር ያለማድረጉና፣ ፖሊሶች በምርመራ ጊዜ የሰጡትን ቃል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 145(1) አስርቀቦ ሳይመለከት ተጠሪን በነፃ ማሰናበቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

ከሥር የክርክሩ አምጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አልተመሰከረበትም በሚል ምክንያት በነፃ እንዲሰናበት ማድረጋቸው ህግን መሰረት ያደረገ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአካል ጉዳት አድርሷል ተብሎ የተከሰሰው በሚስቱ ላይ ሲሆን ይህ አድራጎት ሲፈፀም በጊዜውና በቦታው ደርሰው የግል ተበዳይን ከድብደባው ተግባር ያስቀሯት ሁለት ፖሊሶች መሆናቸው በአመልካች ክስ ተጠቅሶ እነዚህ ፖሊሶች ለምስክርነት ተቆጥረው ፍርድ ቤት ቀርበው የመሰከሩ መሆኑን፣ ፖሊሶቹ ፍርድ ቤት ቀርበው በተመሳሳይ የሰጡት ምስክርነት ቃል ደግሞ በጊዜው በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በጥበቃ ስራ ላይ የነበሩ መሆኑን፣ ተጠሪ ቀደም ሲል ፖሊስ ጣቢያ ገብቶ እንደነበር፣ የግል ተበዳይ ከቀኑ 6፡00 ላይ መጥታ ከተጠሪ ጋር ጭቅጭቅ ስትፈጥር ጊዜ በዚያ ግቢ ውስጥ እንዲህ አይነት ጭቅጭቅ መፍጠር አግባብ ያለመሆኑን አስረድተዋት የግል ተበዳይን ያረጋጉ መሆኑን፣ ሆኖም የግል ተበዳይ በግንባር ላይ እብጠት ይታይባት እንደነበርና አፏ ላይም ደም ይታይባት የነበረ ቢሆንም ማን እንደመታትና እንዳቆሰላት የማያውቁ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፣ ፖሊሶቹ በጥበቃ ስራ ላይ የነበሩና የግል ተበዳይ ጉዳት ደረሰባት የተባለው በሜፅላባ ቀበሌ ልዩ ስሙ ውሃ ዋና ፊት ለፊት ሁኖ በዚህ ቦታ ላይ የነበረውን ክስተት ምስክሮቹ እንደማያውቁና በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ስለነበረው ሂደት የመሰከሩ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹን መዝኖ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጣቸው ነጥቦች መሆናቸውንና በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ስልጣን ያለው የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ የደረሰ መሆኑን ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች በዚህ የክርክር ደረጃ አጥብቆ የሚከራከረው የስር ፍርድ ቤት ምስክሮቹ መጠየቅ ይገባቸው የነበራቸውን ማጣሪያ ጥያቄዎችን አልጠየቀም፣ ፖሊሶቹ በምርመራ ጊዜ የሰጡት የምስክርነት ቃል ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ ለውጠው በወንጀልም የተቀጡ በመሆኑ በምርመራ ጊዜ የሰጡት የምስክርነት ቃላቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 145(1) ቀርቦ መታየት ነበረበት፣ የግል ተበዳይም ለምስክርነት የተቆጠረች በመሆኑ መሰማት ነበረባት በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ክርክር ሂደት ምስክሮች ሲጠየቁ በተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በፍርድ ቤት የሚጠየቁ ጥያቄዎች አይነታቸው የትኞቹ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር ጥር 137፣ 138 እና 140 ስር የተመለከተ ሲሆን የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ስርዓትም በዚሁ ሕግ ተመልክቶአል፡፡ አቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዱልኛል ብሎ የቆጣራቸው ምስክሮችን ሲያሰማ በዋና ጥያቄ ስር ተገቢ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ፍርድ ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ሊጠየቅ የሚችለውም ያልተብራራለት የምስክርነት ቃል ሲኖር መሆኑን ስለፍርድ ቤቱ ሚና የሚያመላክተው የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 136 (4) እና 143 (1) ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው በመሰረቱ ማስረጃ ማቅረብና ምስክሮችን መመርመር የዓቃቤ ህግና የተከሳሹ ኃላፊነት ቢሆንም ፍርድ ቤቱም ውስን ሚናዎች የአሉት መሆኑን ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎችና በሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ምስክሮችን መመርመር የባለ ጉዳዮች ሚና ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ትክክኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ምስክሮቹን የማብራሪያ ጥያቄ መጠየቅ እንደሚችል በወ/መ/ህ/ቁ 136/4/ የተመለከተ ሲሆን በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ 143/1/ መሰረት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ምስክርነቱ አስፈላጊ ከመሰለው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ምስክር /አስቀድሞ ቃሉን የሰጠም ሆነ ያልሰጠ/ መጥራት የሚችል ሲሆን እንዲሁም አቃቤ ህጉ ወይም ተከሳሹ በምስክር ዝርዝር ላይ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡላቸው በጠየቁ ጊዜም ምስክሮቹ ነገሩን ለማዘግየት ሳይሆን ለትክክለኛ ፍትህ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሮቹ እንዲጠሩ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተጨማሪ ማስረጃ ሊሰማ የሚችለው ተጨማሪ መስማት የሚያስፈልግ መስሎ ሲታየው ስለመሆኑ በወ/መ/ህ/ቁጥር 194/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ በማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ሂደቶች ፍርድ ቤቱ ስለሚኖረው ሚና ከሚደነግጉት ሕጋዊ ስርዓቶች መረዳት የሚቻለው በሕጉ ተለይቶ የተሰጠውን ሚና ፍርድ ቤቱ ሊያከናውን የሚችለው የፍርድ ቤቱን ገለልተኛነቱን በማይነካ መልኩ በጥንቃቄ መሆን የአለበት መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 136/4/ እና 143 እንዲሁም 194/1/ ድንጋጎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ፍርድ ቤት ወይም ዳኛው የቀረበለትን ጉዳይ በተመለከተ ማስረጃ ለመፈለግ የግሉን ምርመራና የምርመራ ስራ ለማድረግ የሚችልበት የዳኝነት አሰጣጥ ስርአት የለም፡፡ እንዲሁም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 ላይ አንድ ምስክር በፖሊስ

www.abyssinialaw.com

ምርመራ ወቅት የሰጠው ቃል ዓቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሹ ባመለከተ ጊዜ የተሰጠውን ምስክርነት ፍርድ ቤቱ ሊመለከተው እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማም በምርምራ ጊዜ ተሰጠ የተባለውን የምስክርነት ቃል በፍርድ ቤት ምስክሩ ቀርቦ ቢለውጠው ይኼው ምስክርነት እንዲቃናና ፍርድ ቤት ለያዘው ክስ ሁልጊዜ ከብደት እንዲሰጠው ለማድረግ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡

ከላይ ከተመለከቱት በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ስርዓቶች አንጻር የተያዘውን ጉዳይን ስንመለከትም አመልካች ድርጊቱ ሲፈጸም በቦታው ተገኝተው ተመልክተዋል የተባሉት ፖሊሶች ቃላቸውን ስለቀየሩና በወንጀል ስለተቀጡ በምርመራ ጊዜ የሰጡት የምስክርነት ቃል ለማስረጃነት መቅረብ ነበረበት፣ ፍርድ ቤቱም ማጣሪያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ነበረበት በማለት የሚያቀርበው የሰበር ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ እንዲሁም የግል ተበዳይ የሆኑት ወ/ሮ ነጻነት አለሙ በስር ፍርድ ቤት መሰማት ነበረባቸው የሚለው ቅሬታውም ምስክሯ በጉዳዩ ምስክር ሁነው እስከተቆጠሩ ድረስ በስር ፍርድ ቤት እንዲሰሙ ማድረግ የአቃቤ ሕግ ግዴታ ሁኖ እያለና ምስክሯ ሳይሰሙ የታለፈበት ሂደት በፍርድ ቤቱ ግድፈት ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት አግባብ በሰበር ቅሬታነት ሊነሳ የሚችልና ተቀባይነት የሚያገኝ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ አቃቤ በሕጉ የተጣለበትን የማስረጃ ማቅረብና ጉዳዩን በበቂና በአሳማኝ የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ በማስረጃ አቀራረብናና አቀባበል ረገድ ለፍርድ ቤቱ በሕጉ በግልጽ ተለይተው የተሰጡት ሚናዎችን ባላገናዘበ መልኩ ፍርድ ቤቱ የምርመራና የምርመር ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል በሚል ይዘትና መንፈስ የቀረበው የአቃቤ ሕግ የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ደግሞ ፍሬ ነገሩን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ተጠሪ በግል ተበዳይ ላይ በክሱ ላይ የተገለፀውን አድራጎት ስለመፈጸሙ እንደክሱ አልተነገረበትም በማለት በነፃ እንዲሰናበት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሆሳእና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15/99 በ06/06/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13598 ታህሳስ 09 ቀን 2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63871 በ29/05/2007 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡ ፡፡
2. ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም ተብሎ በነፃ እንዲሰናበት በተሠጠው ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/120762

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-**የፌደራል ዐቃቤ ሕግ - ሮዛ በላቸው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ዱባይ አውቶ ጋለሪ-ኤል.ኤል.ሲ.

2. ወርልድ ኢንተርናሽናል ፍሪዞን ካምፓኒ } ጠበቃ አበበ አስማረ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155568 ታህሳስ 28 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 111863 ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት መዝገቡን በመዝጋቱ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ክስ በቀረበበት ጊዜ በጠበቃ የመወከል ላይ የተሰጠ ትእዛዝ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ሲሆን ተከሳሾች እነአሽረፋ አወል አብዩ /17 ሰዎች/ ሲሆን ተጠሪዎች 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች በተከሳሾች ላይ 6 የተለያዩ ክሶችን ያቀረበ ሲሆን በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ 3ኛ ክስ የወ/ህ/ቁ 32/1/ /ለ/፣ 34/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 የተመለከተውን በመተላለፍ የንግድ ትርፍ ግብር ባለመክፈል፣ 4ኛ ክስ የወ/ህ/ቁ 32/1/ /ለ/፣ 34/1/ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 በመተላለፍ

www.abyssinialaw.com

ግብይት ባካሄዱባቸው ሥራዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ አሳውቆ ባለመክፈል፣ 5ኛ ክስ የወ/ህ ቁጥር 32/1/ /ለ/34/1/ እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 37/1/ /ሀ/፣/ለ/ እና 3/ለ/ በመተላለፍ ለባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት መካተት የሚገባውን ነጥብ በማስቀረትና ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማስረጃ በማቅረብ 6ኛ ክስ የወ/ህ/ቁ 32/1/ /ሀ/ /ለ/፣ 34/1/ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 50/1/1ሀ/ /ለ/ እና /3/ በመተላለፍ ለግብር ሰብሳቢ ባለሥለጣን መሥሪያ ቤት መካተት የሚገባውን ነጥብ በማስቀረት እና ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ማስረጃ በማቅረብ የሚሉ ሲሆኑ 12ኛ ተከሳሽ የነበረው 1ኛ ተጠሪ በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት 13ኛ ተከሳሽ የነበረው 2ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ መሠረት ጠበቃው ቀርበው የክሱ ማመልከቻ የደረሳቸው ሲሆን ፍርድ ቤቱ በጋዜጣ ተጠርተው ባልቀረቡት ላይ በሌሉበት ክርክሩ እንዲቀጥል አዞ በክሱ ላይ የተጠሪዎች ጠበቃን መቃወሚያ መቀበል ሲጀምር አመልካች የተጠሪዎች ሥ/አስኪያጅ እና ባለቤት የሆኑት በክሱ በተራ ቁጥር 14፣15 እና 16 የተጠቀሱት ከህግ ተሰውረዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህን የወከሉ ጠበቃ ለድርድቶቹም መከራከር አይችሉም፡፡ ድርጅቶቹ የሚከሰሱት ሥ/አስኪያጅ ወይም ሠራተኞች በፈፀሙት ድርጊት ነው፡፡ ሥ/አስኪያጅ በሌለበት እንዲታይ ከታዘዘ የድርጅቶቹም ጉዳይ በሌሉበት መታየት አለበት በማለት ያቀረበው ከአቤቱታ በመመርመር አመልካች ያቀረበው ክስ የድርጅቶቹ ከሥራ አስኪያጆች የተለያየ ነው፡፡ በጠበቃ የመወከል መብት ደግሞ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል መብት ነው፡፡ አንድ ድርጅት በወንጀል ህግ ድንጋጌ ተከሳሽ ለመሆን የሚያበቃ ሁኔታ አለ ተብሎ ክስ ከቀረበ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 20/5/ መሠረት በጠበቃ የመወከል መብት አለው ይህንን የሚጻረር አሠራርም ሆነ ሌላ ህግ ተፈጻሚነትየሌለው መሆኑን ይደነግጋል ስለዚህ የአሁን ተጠሪዎች በጠበቃ መወከል ይችላሉ አለ፡፡

አመልካች ይህንን ትእዛዝ በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ ዳኘነተት የሚታየው በህጉ በተመለከተው መሠረት ነው፡፡ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 184 እና 185 በግል ይግባኝ የሚባልባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር የተቀመጠ በመሆኑ አሁን ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ ወደፊት በክርክር መጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ተጠቃልሎ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል እንጂ አሁን በዚህ ደረጃ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ዘግቶታል፡፡ የአመልካች 8 ገጽ የሰበር አቤቱታ መሠረት ያደረገውም በዚሁ ውሳኔ ሲሆን ይዘቱም የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 184 ይግባኝ የማይባልባቸውን ትእዛዞች የሚዘረዝረው ሆኖ በስር ፍ/ቤት ይህንኑ በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ መሠታዊ ስህተት ነው፡፡ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 185 የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ላይ የሚቀርብ እንጂ ከዚህ ውጭ በሆኑ ጉዳዮች ይግባኝ ማለት ይቻላል አይልም፡፡ ከቁጥር 184 ጋር ተጣጥሞ ሊተረጐም የሚገባና ከሰበር መ/ቁ 93234 ከተሰጠው ትርጉም ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ የወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 127/1/ በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ጠበቃ ብቻውን ሊቀርብ እንደማይችል የሚያሳይ ነው፡፡ የተከሳሽ በጠበቃ የመወከል መብት የተቀመጠው ተከሳሹ በቀረበ ጊዜ ተፈጻሚነት

www.abyssinialaw.com

ያለው እንጂ ለመቅረብ ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ አይደለም፡፡ የወ/ህ/ አንቀጽ 34/1/ እንደተመለከተው ድርጅት በወንጀል የሚጠየቀው የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በሰራው ወንጀል በመሆኑና ለጠበቃው ውክልና የሰጠው 15ኛ ተከሳሽ የሆነው የ12ኛ እና 13ኛ ተከሳሽ ድርጅቶች ባለቤትና ሥራ መሪ ከቀረበባቸው ክስ ተሰውረው በሌሉበት እየታየ በጠበቃ ተወክለው መከራከር የህግ መሠረት የለውም፣ በወንጀል ጉዳይ ህጋዊ ሠውነት ያላቸው ድርጅቶት ከድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጆችና ሠራተኞች ተነጥለው የሚታይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች በ15ኛ ተከሳሽ በተሰጠ ውክልና እንዲከራከሩ መፍቀድ በሌሉበት እንዲታይ ብይን የተሰጣቸውን ተከሳሾች በጠበቃ እንዲከራከሩ የመፍቀድ ውጤት አለው፡፡ ስለዚህ በወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ ላይም ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱም የስር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184 እና 185 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በጠበቃ መወከል አይችሉም በማለት አመልካች ያቀረበው ተቃውሞ የመሰረታዊ ህግም ሆነ የስነ-ሥርዓት ህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ፍ/ቤቱ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 184 ውጭ በመሆኑ ሊያልፈው ይገባ ነበር፣ በጠበቃ የመወከል መብት ሕገ-መንግስታዊ ሆኖ በአንቀጽ 20/5/ የተደነገገ ሲሆን አመልካችም በውጤት ደረጃ በወንጀል ፍትህ ሥርህቱ የሚያስገኘው አሉታዊ ተጽዕኖ አንጻር አክብሮ ሊቀበለው የሚገባ ነው፣ ሰበር መ/ቁ 93234 የሰጠው ውሳኔ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 185 /2/ የይግባኝ መብቱ የተገደበውን አመልካችን የሚመለከት አይደለም፡፡ ከአመልካችና ከተጠሪ ክርክር ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፣ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በመልስ ሰጪዎችላይ የወንጀል ዳኝነት ሥልጣን የላቸውም፣ የወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 127/1/ እና 197 ተፈጻሚ የሚሆነው ለተፈጥሮ ሠዎች እንጂ የህግ የሰውነት ባላቸው ሰዎች አይደለም፣ አንድ ሠው በግሉ የተከሰሰበት ጉዳይ በሥ/አስኪያጅነት ከሚመራው የህግ ሠውነት ካለው ድርጅት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ ውክልና ለመስጠት መብት ያለው የተፈጥሮ ሠው ስለድርጅቱ በመሆን ጠበቃ መወከል የተፈቀደ ተግባር ነው፡፡ ተጠሪዎች ከ14፣15 እና 16ኛ ተከሳሾች ጋር ፈፀሙ ያለው ተግባር ምንም ግንኙነት የለውም ተጣምረው ወይም በግብረ አበርነት የቀረበባቸው ክስ የለም፣ የወ/ህ/ቁ 34/1/ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ለተመዘገቡ ድርጅቶች ሲሆን ተጠሪዎች ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገቡ ዓለምዓቀፋ የንግድ ድርጅቶች ናቸው ስለዚህ በተጠሪዎች ላይ ተፈጻሚነት የለውም፣ የድርጅት የወንጀል ኃላፊነት የሥ/አስኪያጅ የወንጀል ኃላፊነት አያስከትልም 15ኛ ተከሳሽ የተከሰሰው በራሱ በግሉ ሲሆን ከተጠሪዎች ጋር ክስ አልቀረበበትም፣ ሌሎች በአመልካች ተነስተዋል ባሉት ነጥብም በዝርዝር መልስ ሠጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የክርክሩ አጠቃላይ ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የተነሱትን ክርክሮች ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

አመልካች በእነ አሸረፍ አወል /17 ሰዎች/ ላይ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ የአሁን ተጠሪዎች 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች በመሆን በጠበቃቸው አማካኝነት በችሎት የተገኙ ቢሆንም አመልካች ተከሳሾች ያልቀረቡና ሥራ አስኪያጆችም በሌሉበት ክርክሩ እንዲሰማ ትእዛዝ ተሰጥቶ ባለበት እነዚህ ተከሳሾች በጠበቃ ተወክለው መከራከር አይችሉም በማለት የቀረበውን ተቃውሞ ፍርድ ቤቱ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ የሠጠ ሲሆን በዚህ ትእዛዝ ላይ የቀረበውን ይግባኝ ሠሚው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደፊት በክርክሩ መጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥበት ይግባኝ ሊባልበት የሚችል እንጂ በዚህ ደረጃ ይግባኝ የሚቀርብበት አይደለም በማለት በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 184 እና 185 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ ሰበር ችሎት በቅድሚያ መታየት ያለበት ተጠሪዎች በጠበቃ ሊወከሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጭብጥ እና አመልካችና ተጠሪ በሰፊው ያደረጋቸውን ክርክሮች ሳይሆን ተጠሪዎች በጠበቃ ሊወከሉ ይገባል በማለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ አይገባም በማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠታዊ ስህተት መኖር አለመኖሩን ነው፡፡

የፌደራሉ ጠቅላይ ፍድ ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 የትእዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ እና የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 185 የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ወይም በቅጣቱ ይግባኝ ስለማለት የሚደነግገውን ነው፡፡

ይግባኝን በተመለከተ መሠረቱ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግስት ሲሆን የተከሰሱ ሰዎችን መብት በሚደነግገው አንቀጽ 20/6/ ላይ ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም ፍርድ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ አንድ የበታች ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ ወይም በፍርዱ ቅር የተሰኘና ፍትህ ተዛባብኝ የሚል ተከራካሪ ወገን ቅሬታውን ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርዱ እንዲመረመር እና ተፈፀመ ያለው ሥህተት እንዲታረምለት ይግባኝ የማለት መብት ተሠጥቶታል፡፡

የሥነ-ሥርዓት ህጐች ዋናው ዓላማ ፍትሐዊ ኢኰኖሚያዊና አፋጣኝ በሆነ መንገድ ክርክሮች እንዲያልቁ ማስቻል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የሥነ-ሥርዓት ህጉን አስመልክቶ ክርክሮች ሲቀርቡ ከተከራካሪ ወገኖች መብት አልፎም የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅና የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ መተርጐም ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም አንጻር በወንጀል ክስ ጉ ዳይ ይግባኝ የሚባልባቸውን የፍርድ ቤት ውሳኔዎች የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 ስለ ይግባኝ መሠረቱ

www.abyssinialaw.com

ሊዘረዝር የሥረ-ነገር ክርክሩን የሚያቋርጡ መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን ይኸውም የጥፋተኝነት ውሳኔ፣ የቅጣት ውሳኔ፣ ለጊዜው የመለቀቅ /Discharge/ እና በነፃ የመለቀቅ ውሳኔ /aquittal/ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን የሥረ-ነገር ክርክር የሚያቋርጡ እንደቀጠሮ መስጠት አለመስጠት እንደማስረጃ መቀበል አለመቀበል የመሳሰሉት የብይን /ትእዛዝ/ ሁኔታዎች ወዲያውኑ ይግባኝ የማይባልባቸው ናቸው ሆኖም ግን በእነዚህ ብይን/ትእዛዞች ላይ ወዲያውኑ ይግባኝ ለማለት ባይቻልም ፍርድ ቤቱ ነገሩን ሠምቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ፍርዱን በመቃወም ይግባኝ ሲቀርብ እነዚህን በክርክሩ ሂደት የተሰጡ እትዛዞች የቅሬታው ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 መደንገጉ የተፋጠነ ፍትህ የማይገኝት ህገ-መንግስትዊ መብት ያለውን ተከራካሪ ተጠቃለው መታየት በሚችሉ ሁኔታዎች ምክንያት ክርክሩ እንዳይዘገይ የማድረግ ዓላማ ያለው መሆኑን የማያስገነዝብ ነው፡፡

በዚህ በያዝነው ጉዳይም የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባልበት የሚገባ አይደለም ያለው በወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 181 እንደተመለከተው የሥረ-ነገር ክርክሩን የማያቋርጥ እና ፍርድ ቤቱ ነገሩን ሠምቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት የቅሬታ ምክንያት ሆነ ተጠቃሎ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል መሆኑን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች የሰበር መ/ቁ 93234 የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ያቀረቡት መከራከሪያም ቢሆን ጉዳዩ የክስ ማሻሻልን የሚመለከት ሆኖ የተሰጠው ትእዛዝ በቀጣይ የወንጀል ክርክር ሂደት ጋር የሚያስተሳስረው ነገር ባለመኖሩ ድጋሚ ክርክር የሚቀርብበት ዕድል የሌለ በመሆኑ ትእዛዙ የመጨረሻ በመሆኑ ከዋናው ክርክር ጋር ተጠቃልሉ ይግባኝ ሊባልበት የማይችል መሆኑን መሠረት በማድረግ የተሰጠ በመሆኑ ጠበቃ በመወከል ላይ በተሰጠው ትእዛዝ ጋር ተመሳሳይነት የላቸውም፡፡

በአጠቃላይ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ በጠበቃ መወከልን አስመልክቶ በተሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181, 184 እና 185 አንጻር መሠረታዊ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155568 በቀን ታህሳስ 28/2004 በሰጠው ትእዛዝ ላይ የቀረበው ይግባኝ ላይ የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 111863 በቀን ጥቅምት 1/2008 የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

<u>ት እ ዛ ዝ</u>

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 155568 የቀጠለው ክርክር ለጊዜው እንዲታገድ በ 12/05/08 የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፡፡* የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 103940

ቀን 24/05/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

.እንደሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ አመለወርቅ ጌታነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የአሁኗ አመልካች ጨምሮ በ17 ተከሳሾች ላይ ክስ ማቅረቡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት 9ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ አመልካች ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡- በንፋስ ስልክ ከተማ ቀበሌ 12/13 የቤት ቁጥር የማይታወቅ ንግድ ቤት ውስጥ ስልክ የማስደወል ፈቃድ ሳይኖራት ከቴሌ ኮሚንኬሽን ሲስተም በመደበቅ ስልክ ማስደወል የሚያስችል ራስ አዲስ ፒሲቶከር እና ራስ ዳሽን የተባሉ ሶፍትዌሮችና የካርድ ቁጥሮች (Accounts numbers) ከ3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በመግዛት እንዱሁም ለጊዜው ማን እንዳስመጣው የማይታወቅ ኔት 2ፎን ዲያለር የተባለ ሶፍትዌር በመጠቀም 3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በስውር በመመሳጠር ባዘጋጁት ህገወጥ ተግባር በመታገዝ ወደ ወጭ አገር ስልክ በማስደወል እ.ኤ.አ ከ01/11/2004 እስከ 06/10/2010 ለ5 አመታት ከ339 ቀናት 779,040 ደቂቃዎች ወደ ተለያየ አገራት ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ሲስተም መደበቅ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመጠቀም በህገወጥ መንገድ በማስደወል ብር 7,70,400 (ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሺህ አራት መቶ ብር)

www.abyssinialaw.com

በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲዳረስ በማደርገና በህገወጥ መንገድ ብር 3895200.00 (ሶስት ሚሊዮን ዘጠና አምስት ሺህ ሁለት መቶ ብር) ተጠቃሚ በመሆኗ እንዲሁም በሽያጭ የተዘጋጁ ግምታቸው USD 17500 የሚያወጡ የካርድ ቁጥሮች በህገ ወጥ ሱቋ ውስጥ በመገኘታቸው የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፤ 33፣ 411(1) ሐ የተመለከተው በመተላለፍ በህዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሳለች የሚል ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ የቀረበባት ክስ ክዳ በመከራከሯ የስር ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ካደመጠ በኃላ እንድትከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ የአሁኗ አመልካች የበኩሏን የመከላከያ ማስረጃ በማስቀረብ አስምታለች፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የአሁኗ አመልካች እና ሌሎች ተከሳሾች በክሱ በተገለጸው አግባብ ከቴሌኮሚኒኬሽን እውቅናና ፈቃድ ውጭ ሶፍትዌሮችን በመገልግል በኢንተርኔት ስልኮች በማስደወል ከፍተኛ ገንዘብ መሰብሰባቸውንና መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ የቴሌኮሙኒኬሽንን መስርያቤት ማስጣታቸውን ተረጋግጦባቸው አልተከላከሉም፡፡ በክሱ ላይ የተገለጹት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች መከላከላቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ጉዳዩ የሙስና ወንጀል መሆኑ ይቀራል ይህ በመሆኑም በ1ኛ ክስ የቀረበባቸው ዘጠኝ ተከሳሾች (3ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛ፣ 9ኛ፣ 11ኛ፣ 12ኛ እና 13ኛ ተከሳሾች) በህገወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ስልክ ለማስደወል ሶፍትዌሮች ማስደወያ ካርድ ቁጥሮችን በማከፋፈል ለአገኙት ህገወጥ ጥቅምና ለአሳጡት ጥቅም ተጠያቂና ጥፋተኛ የሚሆኑት በሙስና ወንጀል መሆኑ ቀርቶ ተከሳሾች ሊጠየቁ የሚገባቸው በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 11(4) ድንጋጌ ኢንተርኔት በመጠቀም የድምጽ መልእክትን ማስተላለፍ ወይም የማስተላለፍ አገልግሎት መስጠት ድንጋጌ ተላልፎ መገኘት በመሆኑ የተከሰሱበትን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1) (ሀ)፣ 33፣ 411(1) (ሐ) እና (2) ድንጋጌዎች በወ/መ/ስ/ስ/ቁ. 113(2) በመለወጥ ከላይ በተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 13 ድንጋጌ ጥፋተኛ ናቸው በማለት በአብላጫ ድምጽ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመረመረ ሲሆን ወንጀሉ በከፍተኛ ደረጃ መድቦ ቅጣቱ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማስላት ወስኗል፡፡ ድንጋጌው ከ3 እስከ ከ5 አመት የሚያስቀጣ በመሆኑ ለከባድ ወንጀል የቅጣት መነሻና መድረሻ ከ4 ዓመት አስከ 4 ዓመት ከ6 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ በእርከን 18 የሚውድቅ ነው፡፡ በአሁኗ አመልካች የቀረበው አንድ የቅጣት ማቅለያ ተቀብሎ በእርከን 17 ስር በ3 አመት እንዲትቀጣ፤ የገንዘብ መቀጮ በተመለከተ ከኢፌዴሪ የኢንፎርመሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በ11/04/2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት በአሁኗ አመልካች ተሰበሰበ የተባለው የገንዘብ መጠን 3,895,200 (ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ) ያለፈቃድ በሰሩበት ጊዜ ውስጥ

www.abyssinialaw.com

አግኝተውታል ተብሎ የቀረበባቸውንና በመከላከያቸው ያላስተባበሉት ገንዘብ እጥፍ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያደረጉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኗ አመልካች የስር ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበገውም የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የወንጀል ድርጊቱ እንዳልፈጸሙ፤ በማስደወል አገኙት የተበለው ገንዘብም ሆነ በመንግስት ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት አልተረጋገጠም፤ የተወሰነው የእስራት ቅጣት ይሁን የገንዘብም መቀጮ የግህ መሰረት የለውም በማለት መከራከራቸውን ያሳያል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ያገናዘበ ስለመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርባዋል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ግራ ቀኝ በጽሁፍ ያደርጉት ክርክር ፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንዲሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የእስራት ቅጣት በአግባቡ ሆኖ በወንጀል ስራ ምክንያት አመልካች አግኝታለች የተባለው የገንዘብ መጠን የተወሰነበት ስርዓት በህጉ አግባብ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡

ጉዳዩ እንደመረመረነውም አመልካች ፈቃድ ሳያወጡ ወይም የፀና ፈቃድ ሳይኖራቸው ስልክ በማስደወላቸው ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት የአሁኗ አመልካች ምንም ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ስልክ በማስደወል ብር 3895200.00 እንደሰበሰቡ ቴሌኮሚንኬሽን ደግሞ ብር 7790400.00 ማጣቱን ከኢፌዴሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ማስረጃ መቅረቡን በውሳኔው አስፍሯል፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም፣ ስልክ በማስደወል ገንዘብ አላገኘሁም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለጸው የቀረበው ማስረጃ የሚያስተባብል ነገር አለማቅረባቸውን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገር በማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ረገድ የሚደርስበት ድምዳሜ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው እንጂ በድጋሚ የሚያጣራበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው የአሁኗ አመልካች (የስር 9ኛ ተከሳሽ የነበሩ) ያለ ፈቃድ ስልክ በማስደወል ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሁለት መቶ ብር ጥቅም እንዳገኙ ነው፡፡ ይህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ይዘን

www.abyssinialaw.com

የአዋጅ ቁጥር 49/1989 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ስር የተመለከተው መቀጮ ዓይነትና ባህሪ መርምረናል፡፡

በዚህ አዋጅ ክልከላ የተደረገባቸው ድርጊቶች ፈጸሞ ጥፋተኛ የተበለው ግለሰብ በእስራትና በመቀጮ እንደሚቀጣ ተመልክቷል፡፡ የድንጋጌው የአማራኛ እንግልዝኛ ይዘት፡- "በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች አግባብ ባለቸው ህጎች መሰረት ፈቃድ ሳያወጣ ወይም የጸና ፈቃድ ሳይኖረው አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ በሰራበት ጊዜ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ተብሎ የሚወሰነውን ገቢ እጥፍ የገንዘብ መቀጮና ከ3 አመት እስከ አምስት አመት በሚደረስ እስራት ይቀጣል በማለት የተደነገገ ሲሆን የእንግልዝኛው ትርጉም "any person who engages in tele communication service without having license or a valid license as per this proclamation or any other relevant laws shall be punished with fine equal to double the revenue estimated to have been earned by the person during the period of time he operated the service and with imprison mint from 3 up to 5 years" በማለት ተደንግጓአል፡፡ በዚህ ድንጋገ የመቀጮው መሰረት ወንጀል ፈጻሚው ካገኘው ጥቅም ወይም ሊያገኘው ይችላል ተብሎ የሚገመት የገንዘብ መጠን መሰረት የሚያደረግ ስለመሆኑ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በህገ ወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ያገኙት የገንዘብ መጠንና መንግስት ያጣው ገቢ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ እና ተረጋግጦ መቅረቡን የስር ፍ/ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 281/1994 አንቀጽ 13 ላይ እንደተገለጸው የመቀጮው መጠን እጥፍ እንደሚሆን ነው፡፡ ድንጋጌው ተቀጪው እጥፍ እንደሚከፈል በግልጽ ካስቀመጠ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በህገ ወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል ያገኙው ጥቅም እጥፍ እንዲከፍሉ መወሰናቸው ሲታይ በህጉ አተረጓጉም ረገድ የፈጸሙት ስህተት መኖሩን አያሳይም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በአዋጅ ቁጥር 281/94 አንቀጽ 13 ድንጋጌዎች መሰረታዊ የመቀጮ አወሳሰን ስርዓት ተቀጪው ወንጀል በመስራቱ ያገኘው ጥቅም ታሳቢ ያደረጉ በመሆኑ ወንጀል በመስራቱ ብቻ ጥቅም ሲያገኝ የሚወሰንበት ስርዓት መሆኑን ተረደተናል፡፡ ከዚህ አንጻር በአመልካች ላይ የተወሰነው መቀጮ ተገኘ የተባለው ጥቅም በማስረጃ መረጋገጡን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 281/94 አንቀጽ 13 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ፍርድና ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. አመልካች በህገወጥ መንገድ ስልክ በማስደወል አገኙት የተባለው የገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍሉ መወሰኑ በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.94913

ህዳር 24 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት - ዓ/ሕግ አቤል ገ/እግዚአብሔር - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ጆሳምቢን ትሬዲንግ ኃ/የግ/ማህበር
2. አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ አርጋዉ } ከጠበቃ አለማየሁ ታደሰ ጋር - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ ከጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ጋር በተያያዘ ተፈጸመ የተባለዉን የማጭበርበር ወንጀል የሚመለከት ክርክር መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የሥር ከሳሽ /የአሁን አመልካች/ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ተከሳሾች የጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 93 /1/ (ሀ) እና 93 /2/ በመፈተላለፍ ቻይና አገር የተመረቱን ዕቃዎች ከዉጭ አገር ለማስገባት የንግድ ፈቃድ አዉጥቶ፣ ዕቃዎቹ ሞጆ ደረቅ ወደብ ገብቶ ሲፈተሽ በዲክላራስዮን ቁጥር C-10951 በ20/12/2012 እ.አ.አ. እና ይህን በሚደግፍ ሰነድ ላይ ያልተሞለዉን መለያ ያለዉ ቬትናም አገር የተመረተ እና የጫማ ሳጥን በማስገባት ቀረጥ እና ታክስ ብር 3,328,524.38 መከፈል ያለበትን ብር 931,799.33 በመክፈል በልዩነት ብር 2,396,725.05 ሳይከፍል ዝቅተኛ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ዕቃዉ ወደ አገር ወስጥ እንዲገባ ስላደረገ በማጭበርበር ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

የሥር 2ኛ ተከሳሽ /የአሁን 2ኛ ተጠሪ/ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት በሰጠዉ ቃል በዚህ የወንጀል ድርጊት ምንም ዓይነት ተሰትፎ የለኝም ምክንያቱ በዲክላራስዮኑ ሰነድ ላይ ከተጠቀሱት ዕቃዎች ዉጭ የላከዉ ከዉጭ አገር ዕቃዎቹን የላከዉ ካመፓኒ የፈጸመዉ ስህተት ነዉ እንጂ የተከሳሽ ተሳትፎ የለም በማለት ገልጿል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮችን በመስማት፣ 2ኛ ተከሳሽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.142 /3/ መሰረት የሰጠዉን ቃል በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ከዉጭ የመጠዉን ዕቃዎች ያወቀዉ

www.abyssinialaw.com

በሞጆ ደረቅ ጣቢያ ሲፈተሽ እንደሆነ የዐ/ሕግ ምስክሮች ገልጸዋል፤ ዕቃዉ የመጣዉ ከተከሳሽ ጥያቄ ዉጭ በመሆኑ፣ ላኪዉ ካመፓኒ የራሱ ስህተት እንደሆነ እና ተከሳሹ በሰጠዉ ቃል የላኪዉ ካምፓኒ ስህተት እና ከእርሱ እዉቅና ዉጭ እንደሆነ በመግለጹ በወ/ሕ/ቁ.23 /2/ መሰረት ወንጀል ለመፈጸም የሐሰብ ክፍል ስላልተሟላ፣ ተከሳሽ ሊጠየቅ አይገባም በማለት በወ/ሕ/ቁ.149 /2/ መሰረት ነጻ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምስራቅ ችሎት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሾች ይህን ለመፈጸም የሀሳብ ክፍል የለም በማለት ከክሱ ነጻ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፣ በዕቃዎቹ ላይ መከፈል ያለበትን ቀረጥና ታክስን በተመለከተ ዕቃዎቹ ላይ መከፈል ባለበት ላይ በተከፈለዉ መካከል በቅናሽ የሚፈለግ ክፍያ ካለ ተከሳሾች በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊዉን ክፍያ ከከፈሉ በኃላ ዕቃዎቹ እንዲለቀቁ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች በ07/03/2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 93 /1/ (ሀ) የተጠቀሱ የወንጀል ድርጊቶችን መፈጸሙ በአዋጁ አንቀጽ 93 /2/ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን፣ ተጠሪ ድርጅት በመሆኑ  የሐሳብ ክፍል እንዲያሟላ የሚጠበቅ ሳይሆን ተጠሪዉ በከፈለዉ ታክስ እና ቀረጥ መካከል በልዩነት ብር 2,396,725.05 ሳይከፍልበት ወደ አገር ዉስጥ አስገብቶ መገኘቱ ነዉ፡፡ ይህን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙ ተረጋግጧል፡፡ በዲክላራሲዮን ቁጥር C-10951 በቻይና አገር የተመረተዉን ዕቃ አቅራቢ ከሆነዉ ከSHEZHENE XINGCHEN በአደራ ተቀብሎ ተጠሪዎችን ወክሎ ተረክቦ የላካ ሆፕ ኢንተርናሽናል /HOPE INTERNATIONAL/ በአዋጁ አንቀጽ 2/23/ መሰረት ወኪልንም ስለሚጨምር አቅራቢ ያልሆነዉ ሆፕ ኢንተርናሽናል የጻፈዉን ደብድቤ በመዉሰድ ተጠሪዎችን ነጻ መልቀቁ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ሆፕ ኢንተርናሽናል ድርጅት የጻፈዉ ደብዳቤ በአዋጅ ቁ.334/1995 አንቀጽ 26 /1/ እና 27 /1/ መሰረት ስላልተረጋገጠ፣ የደብዳቤዉም ይዘት ሲታይ በልዩነት የታየዉን ገንዘብ ትተንልሃል የሚል ስለሆነ ከዘመናዊ ግብይት አንጽር ከንግድ መርህ ዉጭ ነዉ፤ ደብዳቤዉም የተጻፈዉ ተጠሪዎች ከተከሰሱ በኃላ ነዉ፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤቶች በሕግ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ያልሆነን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን ከክስ ነጻ ማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለዉ በመሆኑ ተጠሪዎቹ ላይ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እንዲሰጥ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን በመመርመር ፣ተጠሪዎች ይህን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም የሐሳብ ክፍል እንደአስፈላጊ ሁኔታ ተቆጥሮ የተሰጠዉን ዳኝነት አግባብነት፣ ለማየት ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ በታዘዙት መሰረት መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ቀርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡ 1ኛ ተጠሪ ሆፕ ኢንተርናሽናል ቻይና አገር ከሚገኝ ዕቃዎችን ለመግዘት ይህ ድርጅት የዕቃዎቹን ከዋጋ ዝርዝር ጋር በላከዉ መሰረት የዉጭ ምንዛሬ እንዲፈቀድለት ጠይቆ ሲፈቀድለት በዳሻን ባንክ በኩል አል.ሲ /letter of credit/ ከፍቶ ግዥዉን

www.abyssinialaw.com

አከናዉኗል፡፡ ይህ ኩባንያ የዕቃዉን ዝርዝር እና የዋጋዉን መጠን በኮሚርሻል ኢንቮይስ በባንክ በኩል ለተጠሪዎች ልኮ ክፍያም በዳሽን ባንክ በኩል በኤል.ሲ አድቫይዝ ተፈጽሟል፡፡ ዕቃዎቹ በኢትዮጵያ መርከብ ተልከዉ ሞጆ ደረቅ ወደብ የደረሱ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ኤልሲ፣ ኮሚርሻል ኢንቮይስ፣ የዕቃዎች ዝርዝር ፓክንግ ሊስት፣ ቢል ኦፍ ሎድንግ፣ እና ሌሎች አስፈላጊ ዶክመንቶችን በአግባቡ ተልከዉለት በሰጠዉ ትዕዛዝና በከፈለዉ ዋጋ መጠን መሆናቸዉን አረጋግጦ ሰነዶቹ በሙሉ ትክክል ስለሆኑ ሰነዶቹን ከባንክ አዉጥቶ ለትራዚተር አስተላልፏል፡፡ በዚህ መሰረት ዲክላራሲዮን ተሞልቶ ተገቢዉ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ዕቃዎቹ በፍተሻ ሲታይ ቻይና አገር የሚገኘዉ አቅራቢ የአላላክ ስህተት በመፈጸሙ ዕቃዎቹ ጫማ መሆናቸዉ እና ብዛታቸዉ በሠነዱ በተገለጸዉ ልክ ቢሆንም ስሪታቸዉና አዲዳስ የሚል ቢራንድ ስም ስለተለጠፈባቸዉ በመሆኑ በቀረጥና ታክስ አከፋፈል ላይ ለብራንድ የሚከፈለዉ ቀረጥና ታክስ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ የአቅራቢዉ ስህተት መሆኑን ኩባንያዉ ገልጿል፡፡ በተጠሪዎች በኩል የተፈጸመ ሕገ ወጥ ድርጊት የለም፤ በተጠሪዎች እዉቅና ወይም ቸልተኝነት የተፈጸመ ነገር የለም፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 መሰረት የፈጸምነው የወንጀል ድርጊት የለም፡፡ ወንጀል ለመፈጸማችን የሐሳብ ክፍል የተሟላ ነገር የለም፡፡ የሥር ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በልዩነት የታየዉን ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ስላደረገ የመንግስት ጥቅም ያስጠበቀ ዉሳኔ ነዉ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ክርክራቸዉን አቅርበዋል፡፡ አመልካች በ23/07/2006 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተ ሲሆን፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እና መዝገቡ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪዎች ከዉጭ አገር ለማስገባት ፈቃድ ከወሰዱት ዕቃዎች ዉጭ ሌላ አገር የተመረተ ዕቃዎች በማስገባት ሊከፈል ከሚገባ ቀረጥ እና ታክስ አናስተኛ በመክፈል የማጭበርበር ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ የፈጸምናዉ የወንጀል ድርጊት የለም፣ ዕቃዎቹን ከዉጭ አገር የላከዉ ኩባንያ የፈጸመዉ ስህተት ስለሆነ ሊንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ሥራ አስኪያጅነት በቻይና አገር የተመረተ የእስፖርት ጫማዎችን ወይም ዕቃዎችን ወደ አገር ዉስጥ ለማስገባት ፈቃድ የወሰዳ ሲሆን፣ እነዚህ ዕቃዎች ከዉጭ አገር ወደ አገር ዉስጥ ገብቶ ሞጆ ደረቀ ወደብ ከደረሳ በኃላ በተደረገ ፍተሻ ቻይና አገር የተመረተ ሳይሆን መለያ ያለዉ ቬትናም አገር የተመረቱ ዕቃዎች እንደሆኑ፣ በዚህ ምክንያት ለመንግስት መከፈል ካለበት ቀረጥና ታክስ ዉስጥ በልዩነት ብር 2,396,725.05

www.abyssinialaw.com

ሳይከፍልበት ወደ አገር ዉስጥ እንደገቡ ግራ ቀኙ ያልተካካዱ ከመሆኑም በላይ በማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ የአመልካች ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ይህ ድርጊት መደረጉን በዲክላራሲዮን ላይ ከተገለጹት ዕቃዎች ዉጭ ወደ አገር ዉስጥ መግባታቸዉን አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ያቀረባቸዉ የሰነድም ሆነ የሰዉ ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ ወደ አገር ዉስጥ እንዲያስገባ ከተፈቀደለት ዕቃዎች ዉጭ ሌሎች ዕቃዎችን ወደ አገር ዉስጥ በእሱ ምክንያት እንደገባ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች በተጠሪዎች ምክንያት ወደ አገር እንዲገባ ከተፈቀዱ ዕቃዎች ዉጭ ወደ አገር ዉስጥ ገብቶ መገኘታቸዉ እና በዚህ ምክንያት መከፈል ከነበረበት ቀረጥና ታክስ በክሱ ላይ የተጠቀሰዉ ገንዘብ በልዩነት መገኘቱን የማስረዳት ሸክሙን መወጣቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች እንዳረጋገጡት በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ ማስረጃ ዕቃዎቹን ከዉጭ አገር የላከዉ ሆፕ ኢንተርናሽናል ኩባንያ በኩል የተፈጠረ ስህተት መሆኑን የሚያመለክት እንደሆነ ገልጸዋል፤ 2ኛ ተጠሪም በሰጠዉ ቃል ዲክላራሲዮን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ሰነዶች በአግባቡ ተሞልቶ በባንክ በኩል ተገቢዉ ክፍያ ተፈጽሞ የተላካ ሲሆን፣ ከዉጭ አገር ዕቃዎቹን ወደ አገር ዉስጥ የላካዉ ኩባንያ በፈጠረዉ ስህተት በሰነዱ ላይ ያልተጠቀሱ ዕቃዎች ወደ አገር ዉስጥ ገብቶ ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲፈተሽ እንዳወቀ እና አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ተብሎ ምንም ነገር እንዳላደረገ እና በዚህ ድርጊት ዉስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ እንደሌለዉ ገልጻል፡፡ በጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 93 (1)(ሀ) እና 93 /2/ በመፈተላለፍ የማጭበርበር የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም እያወቁ የተፈጸመ ድርጊት መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይደለም፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 /2/ መሰረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለዉ ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሞልተዉ ሲገኙ ብቻ ነዉ በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ ሲታይ 2ኛ ተጠሪ ይህን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም ምንም ዓይነት ሚና እንዳልነበረዉ እና ድርጊቱን ለመፈጸም ሐሳብ እንዳልነበረዉ የቀረበዉ ማስረጃ እንደሚያረጋግጥ የሥር ፍ/ቤቶች አረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ይህን የወንጀል ድርጊት አዉቆ መፈጸም ይቅርና ያልተጠየቁ ዕቃዎች ወደ አገር ዉስጥ መግባታቸዉን ያወቀዉ ሞጆ ደረቅ ወደብ እንደሆነ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ 2ኛ ተጠሪ በዚህ ድርጊት ምክንያት የወንጀል ተጠያቂነት አለበት ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 (3) የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በዚህ ሕግ በአንቀጽ 34 በተደነገጉ ሁኔታዎች መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ሲሆን እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በአንቀጽ 34 (1) መሰረት አንድ ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣዉም ከኃላፊዎቹ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ

www.abyssinialaw.com

የድርጅቱን ጥቅም በሕገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ፣ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ፣ ወይም ድርጅቱን በመሳሪየነት ያለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ነዉ በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ ማስረጃ የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ድርጅቱን ተገን በማድረግ ወንጀሉን ያልፈጸመ መሆኑን ባቀረበዉ ማስረጃ ያረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ አግባብ 1ኛ ተጠሪ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙን በማረጋገጡ፣ የሥር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተጠሪን ከክሱ ነፃ እንዲወጣ የሰጡት ዉሳኔ የህግና የማስረጃ ድጋፍ ያለዉ ነዉ፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች በዚህ የወንጀል ድርጊት ዉስጥ ምንም ተሳትፎ እንደሌላቸዉ በመከላከያ ማሰረጃ በማረጋገጥ እና በመከላከላቸዉ ከክሱ ነጻ እንዲወጡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.33613 በ02/08/2005 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የምስራቅ ችሎት በመ.ቁ.161271 በ16/12/2005 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.195 /2/ /ለ/፣/ 2/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ዉሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 101618

ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/መ/ፀረ- ሙስና ኮሚሽን - ዐ/ህግ የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** መስከረም ፋንታዬ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀትና ወደ ሐሰት መለወጥ የሙስና ወንጀል ድርጊትን የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የሥር ከሳሽ /የአሁን አመልካች / ለጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ ቁ. 379/1/ሀ በመተላለፍ ተከሳሽ በ26/03/2001 ዓ.ም የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር የተጠቀሰ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ የሥራ ሂደት በሚል የሚጀምር እና በሀሮ ወላቦ ክ/ከተማ ንግድ ምዝገባና ፍቃድ ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ የስራ ሂደት የተዘጋጀ በማስመሰል በስሙ የተዘጋጀ የቡና አቅራቢነት ሀሰተኛ ንግድ ፈቃድ በሀሰተኛ ክብ ማህተም፣ ሀሰተኛ ስምና ስልጣን ቲተሮች የተዘጋጀውን ሰነድ በመያዝ በቀን 18/08/2005 ዓ.ም 9፡30 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሀሮ ወላቡ ክ/ከተማ ንግድ ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ወደ ጌድኦ ዞን ንግድ ማስፋፊያ ይዛወርልኝ በማለት ሲገለገል ሊያዝ ችሏል ፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ የሕዝብ ጥቅም የሚሰራበት ሰነድ ላይ በሀሰት የተዘጋጀ ስለመሆኑ እያወቀ በመገልገሉ በፈጸመው መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ በማዘጋጀት ወይም ወደ ሀሰት መለወጥ የሙስና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

የሥር ተከሳሽ/ የአሁን ተጠሪ/ ፍ/ቤት ቀርቦ ይህ ክስ ተነቦለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ሳይቀበለው በመቅረቱ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል ፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮችን በመስማት ተከሳሽ እንዲከላከል ባዘዘው መሰረት ተከሳሽ ራሱ ቃሉን በመስጠት የመከላከያ ምስክር አንድ ሰው ያቀረበውን ሰምቷል ፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ የተከሰሰበት ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት የሚል ሲሆን ተከሳሹ የፈጸመው ድርጊት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 379/1ሀ/ ሥር የሚሸፈን አይሆንም ፣ ተከሳሽ የፈጸመው ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 378 ሥር የሚሸፈን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የዐ/ሕግ ምስክሮችም በሰጡት የምስክርነት ቃል ይህ የሀሰት ሰነድ በተከሳሹ መዘጋጀቱን አናውቅም በማለት መስክሯል ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በሐሰት የተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት በወ/ሕ/ቁ. 375 መሰረት ቅጣት ይጣልበታል፡፡ ነገር ግን የዐ/ሕግ ምስክሮች ተከሳሹ ይህ የሐሰት ሰነድ ይዞ ከመገኘት ውጭ በሰነዱ መገልገሉን አልመሰከሩም፡፡ የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች ተከሳሽ የሐሰት ሰነዱን አለማዘጋጀቱንና አለመገልግሉን፣ ይህንንም የሀሰት ሰነድ አምጥቶ ለሚስቱ የተሰጠው ተከሳሽ ለትምህርት ወደ ጎንደር ዩኒቨርስቲ በሄደበት ወቅት ጉዳይ አስፈጻሚ እንደሆነ የመሰከሩ ሲሆን እና በተባለ ጊዜ ተከሳሹ ዩኒቨርስቲ እንደነበር በዩኒቨርስቲ የተጻፈ ደብዳቤ ያመለክታል፡፡ ተከሳሹ በተጠቀሰው የሐሰት ሰነድ ምንም አይነት የቡና ንግድ ያላካሄደ መሆኑን የዲላ ዙሪያ ወረዳ ግብይትና ኀ/ሥራ ማህበር ጽ/ቤት መግለጹ እንዲሁም የሚፈለገው ምንም እዳ የሌለ መሆኑን ከገቢዎች ጽ/ቤት የተጻፉ ደብዳቤዎች ያስረዳሉ፡፡ ተከሳሹ በሀሰት ሰነድ አለመገልገሉ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ተከሳሹ ይህ ሰነድ ይዞ መገኘቱ እንደወንጀል ሊቆጠር ስለማይገባ ተከሳሹ ከተከሰሰበት የወንጀል ክስ በነጻ እንዲለቀቅ ወስኗል ፡፡ የሥር ከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ቅሬታውን ባለመቀበል ውድቅ በማድረግ የሥር ውሳኔ በማጽናት ወስኗል ፡፡ የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በ27/09/2006 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ የሥር ፍ/ቤት ለወ/ሕ/ቁ. 379/1፣ሀ/ የሰጠው የሕግ ትርጉም አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የዐ/ህግ ምስክሮች ተጠሪው በሐሰተኛ የንግድ ፈቃዱ እያወቀ መገልገሉን አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንዲታረምልን ተጠሪ ላይ ተገቢው የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ እንዲወሰንበት በማለት አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ ተጠሪ ሐሰተኛ የንግድ ፈቃድ ተጠቅሞ ማህደሩ ከአንዱ የመንግስት መ/ቤት ወደ ሌላ እንዲዛወርለት ጠይቆ ይህንኑ ሂደት በማስፈጸም ላይ እያለ

www.abyssinialaw.com

የተደረሰበት ሆኖ ሳለ ድርጊቱ የወንጀል ሃላፊነትን አያስከትልም ተብሎ በነጻ የመሰናበቱ፣ አግባብነት ለመመርመር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 06 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የመልሱም ይዘት ተጠሪ ሀሰተኛ ሰነድ መሆኑን እያወቅሁ ማህደር ከአንዱ የመንግስት መ/ቤት ወደ ሌላ የመንግስት መ/ቤት እንዲዛወር ያላደረግኩ ስለመሆኑ በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ለወ/ሕ/ቁ. 379/1ሀ/ የሰጡት ትርጉም አግባብነት ያለው ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ሰነዱ ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ መሆኑን እያወቅኩ ስለመገልገሌ በማስረጃ ያላረጋገጠ ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያቀረበው ወንጀል ክስ በማስረጃ ባለመረጋገጡ ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ ውሳኔው እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በ04/05/2007 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን፤ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እና መዝገቡ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል ፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ባቀረበው ክስ መሰረት የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል መንግስታዊ ወይም ወታደራዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት ወይም ወደ ሀሰት መለወጥ ያረጋገጡት ነገር እንደሌለ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ያመለክታል፡፡

እንዲያውም የዐ/ሕግ ምስክሮች እንደገለጹት ተጠሪን ከየት አመጥተህ ነው ብሎ ሲጠይቁት እሱ ለትምህርት በሄደ ጊዜ የተወከለ ሰው እንዳወጣለት እና ተጠሪው ሰነዱን ማዘጋጀቱን እና መገልገል አመለገልገሉን እንደማያውቁ መስክረዋል ፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ ከምስክሮች ቃል አንጻር ሲታይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት የተባለውን ድርጊት እንደማይሸፍን በመግለጽ ወደ ወ/ሕ/ቁ. 378 መለወጡ በአግባቡ ነው እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል የሚያስብል ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጡት ዐ/ሕግ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተጠሪው ይህን ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ አዘጋጅቶ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ የሚያረጋግጡት አይደለም፡፡ በወ/ሕ/ቁ. 378 መሰረት የወንጀል ሃላፊነት ሊያስከትል የሚችለው በሀሰት የተዘጋጀ ወይም የተለወጠ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ተጠሪ እና ያቀረበው መከላከያ ምስክር በሰጡት ቃል ተጠሪ ይህን ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ እንዳላዘጋጀ እና ሐሰተኛ መሆኑን አውቆ እንዳልተገለገለበት ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል በስር ፍ/ቤት የቀረበው የሠነድ ማስረጃ ተጠሪ በዚህ ሀሰተኛ የንግድ ፈቃፈድ በመገልገል ያካሄደው የቡና ንግድ እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪው ይህ ሀሰተኛ የንግድ ፈቃድ በማዘጋጀት እያወቀ የተገለገለበት መሆኑን በማስረጃ አላረጋገጠም በማለት ተጠሪ ከተከሰሰበት ወንጀል በነጻ

www.abyssinialaw.com

እንዲሰናበት የሠጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጿሚል በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ . 09459 በ30/05/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61255 በ26/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 61563 በ14/08/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 195/2፣ለ፣2 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ወ/ከ**

www.abyssinialaw.com

# ጉምሩክ/ታክስ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 95941

ታህሳስ 7 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ሔስ ትራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ረታ አለማየሁ - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዓ/ህግ ኃይለመለኮት አበበ - ቀርበዋል

2. የኢትዮጵያ ግዮን ሆቴሎች ድርጅት - ነ/ፈ ሙላት ማሞ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡ ተከታዩን

## ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች ሔስ ትራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ታህሣስ 15 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 92474፣ ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ቅሬታውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ሲከራከር የነበረው ለአመልካች የገበሩት ታክስ ቅናሽ እንዲደረግለት ግብሩን ሲያሳውቅ አብሮ ሕጋዊ ደረሰኝ (የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ) ማቅረብ አለበት፡፡ አመልካች ግን ደረሰኝ ብያቀርብም ህጋዊ አይደለም የሚል ሲሆን፤ ከአሁን በፊት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በጣልቃ ገቢነት የኢትዮጲያ ግዮን ሆቴሎች ድርጅት ገብቶ እንዲከራከር ወስኖ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመለሰው መሠረት የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት በጣልቃ ገቢነት የሰጠው መልስ በግብር ዘመኑ ገቢ ያደረገ መሆኑን ከአሁን አመልካች ብር 533,951.97 የሰበሰበና የተ.ኡ.ታ. ብር 80,089.97 ብቻ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ይህ የጣልቃ ገቢ (የኢትዮ.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት) የሰበሰው የተ.እ.ታ. ብር 80,089.97 ብቻ ያለው ስህተት መሆኑና ብር 408,619.47 እንደሆነ ይጣራልኝ ብዬ ፍ/ቤቱን ብጠይቅም አልተቀበለኝም፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሆኑም የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት የተ.እ.ታ ሲሰበሰብ የነበረው በአንደኛ ተጠሪ የታወቁ ደረሰኞች እንደሆኑና 2ኛ ተጠሪ (የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት) ታክሱን አልከፈሉም ሳይባል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ የሥር ፍ/ቤት መሻሩ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ ይላል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ ክርክር የተነሳበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሥር ጣልቃ ገብ የሆነው የአሁን 2ኛ ተጠሪ መክፈሉ ተረጋግጦ እያለና የሂሳብ ስሌት ስህተት ካለም በሂሳብ አጣሪ እንዲታይ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት ይህን ባለማገናዘብ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ነው የሚለውን የአመልካች ቅሬታ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡

1ኛ ተጠሪ መጋቢት 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በትክክል የዚህን ዘመን የተ.እ.ታ በስሙ የከፈለ ለመሆኑ የሚያስረዳ ተጨባጭ ደረሰኝ ማቅረብ ሲገባው ያላቀረበ በመሆኑና 2ኛ ተጠሪ በስሙ ለተጠሪ ገቢ ያደረገው ታክስ በስሜ እንደተከፈለ ተቆጥሮ ይቀነስልኝ በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑና የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከላክሏል 2ኛ ተጠሪም የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በተ.እ.ታ. አዋጅና በደንቡ ላይ ተመስርቶ ህጉን ተከትሎ በመሆኑ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ያፅናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በዚሁ መሠረት መዝገቡን እንደመረመርነው ከፌ/ከ/ፍ/ቤት ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ውሳኔ የሰጠበት በመጀመሪያ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 115 መሠረት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም በሰጠው መሠረት በቀረበው ላይ ነው፡፡ የአሁን አመልካች (ይግባኝ ባይ) ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረበው ይግባኝ የግብር ዓላማ በሕጎቹና በደንቦቹ ላይ እንደተጠቀሰው ከሚሰጡ አገልግሎች ላይ ግብሩ ተሰብስቦ በጊዜው ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ገቢ መደረጉ ሲሆን፤ ይሄውም ገቢ መደረጉ ግብሩን የሰበሰበው በጊዜው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከከፈሉት ድርጅቶች ማረጋገጫ ለተገኘበት ሂሳብ በእኛ በኩል እንዳልተከፈለ ተደርጎ ተቀባይነት ማጣቱ ተገቢ ባለመሆኑ የቀረቡትን ማስረጃ በተገቢው ሁኔታ ዝርዝሩ ታይቶ ይስተካከልልኝ የሚል ሲሆን መልስ ሰጪ የኢት/ገ/ጉ/ባለሥልጣንም የሰጠው መልስ በተጨማሪ እሴት ታክስ አ.ቁ 285/94 አንቀጽ 21 የተ.እ.ታ ከፋይነት ታክስ ተመዝጋቢ ሰው ከቫት በተቀበለው የተ.እ.ታ ደረሰኝ መሆን አለበት፡፡ ይግባኝ ባይ ታክስ የከፈለበትን የተ.እ.ታ ደረሰኝ ሳያቀርብ ታክሱ እንዲቀነስለት መጠየቁ ተቀባይነት የለውም ይግባኝ ባይ ከ1995 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም የግብአት ታክስ ከፍያለሁ ቢልም የተ.እ.ታ የከፈለበትን ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ይግባኛቸው ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከላክሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባይ ለተጠየቁት ግብር ከ1995 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም የግብር ዘመን የተ.እ.ታ የግዮን ሆቴሎች ድርጅት በጊዜው በትክክለኛ ፎርማት መሠረት ደረሰኞቹን እንዳላሳተመና በኢንቮይስ እንዲጠቀም የፈቀደለት መሆኑን ገልፆ የግዮን ሆቴሎች ድርጅት በይግባኝ ባይ ስም የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ለመልስ ሰጪ ገቢ ያደረገበት ማስረጃ እና ይህንኑ የሚያስረዳ ባለሙያ ቀርበው ገቢ ማድረጋቸውን አስረድተዋል፡፡ ይግባኝ ባይ በመልስ ሰጪ መሥሪያ ቤት የተጠየቀውን የተ.እ.ታ.መክፈሉን የጊዮን ሆቴሎች ያረጋገጠ ሲሆን መልስ ሰጪ ገቢው በትክክል አልደረሰም የሚል ከሆነ የጊዮን ሆቴሎች ድርጅት መጠየቅ እንጂ በይግባኝ ባይ ላይ የወሰነው ግብር አለአግባብ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ይህን ውሳኔ መልስ ሰጪ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ የፌ/ከፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ብሎ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በጣልቃ ገቢነት የኢትዮ. ግዮን ሆቴሎች ድርጅት አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ወደ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመመለሱ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤ በመ.ቁጥር 94730 ይግባኝ ባይ የኢት.ገ/ጉ ባለሥልጣን መልስ ሰጪ ሔስ ትራቭል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጣልቃ ገቢ የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅትን አከራክሮ ሐምሌ 3 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባይ አጥብቆ የሚከራከረው መልስ ሰጭ (ሔስ ትራቭል ኃ/ተ/የግ/ማ) የግብአት ታክስ እንዲቀነስለት ግብር ሲያስታውቅ አብሮ የተጨማሪ እሴት ደረሰኞችን ማቅረብ አለበት፡፡ መልስ ሰጪ ደግሞ ግብሩን የከፈለው መሆኑን ህጋዊ ደረሰኝ ያልቀረበና በጣልቃ ገቢ በኩል ያልተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ መልስ ሰጭ ግብሩን በጣልቃ ገቢ በኩል ከፍያለው ቢልም በስሙ የተከፈለ መሆኑን ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪን የግብር ክፍያ የጠየቀው ጣልቃ ገቢ በግብር ዘመኑም የሰበሰበው ታክስ እንደከፈለ ግን በመልስ ሰጪ ስም ለይቶ ያልከፈለ መሆኑን የገለፀ ስለሆነ በመልስ ሰጪ ላይ የሚፈለገው ታክስ በራሱ ስም ገቢ ሆኗል ለማለት አይቻልም በማለት የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ.ቁ. 625/1/02 የሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የአሁን አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢልም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 92474 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ..337 መሠረት የስር ፍ/ቤት ፍርድ ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተናል ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ (የኢት/ገ/ጉ/ባለሥልጣን) በሥር ፍ/ቤት ሲከራከር የነበረው ለአመልካች የግብአት ታክስ ቅናሽ እንዲደረግለት ግብሩን ሲያሣውቅ አብሮ ሕጋዊ ደረሰኝ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤ አመልካች ግን ደረሰኝ ቢያቀርቡም ህጋዊ አይደለም በሚል ሲሆን 2ኛ ተጠሪ የኢት.ግዮን ሆቴሎች ድርጅት የወቅቱን የግብር ታክስ አልከፈለም ሣይባል በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጣራ የተያዘው ጭብጥ ክርክር

www.abyssinialaw.com

የተነሣበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በሥር ጣልቃ ገቢ የሆነው 2ኛ ተጠሪ የወቅቱ ግብር መከፈሉ ተረጋግጦ እያለና የሂሣብ ስሌት ስህተት ካለም በሂሣብ አጣሪ እንዲታይ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤት በማለፍ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ነው የሚለውን የአመልካች ቅሬታ ለማጣራት ነው፡፡ በዚሁ በተያዘው ጭብጥ መሠረት እንደመረመርነው የአሁን አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ ለ2ኛ ተጠሪ የከፈልኩት ተቀናሽ ያደረግልኝ ሲል ለ1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ደረሰኞች አሉ፡፡ 1ኛ ተጠሪ እነዚህን ደረሰኞች ህጋዊ ደረሰኞች ባለመሆናቸው ተቀናሽ ማድረግ አልችልም በማለት ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ያቀረባቸው ደረሰኞች ህጋዊነትን ለመለየት 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተወስኖ 2ኛ ተጠሪም ጣልቃ ገብቶ ሲከራከር በወቅቱ የሰበሰባቸውን ግብር ለ1ኛ ተጠሪ ገቢ ያደረጋቸው መሆኑን፣ ከአሁን አመልካች የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 80,089.97 በስሙ ገቢ ያደረገ መሆኑን ገልጿል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በዘመኑ ግብር ሲሰበስብ የነበረው በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሣይሆን 1ኛ ተጠሪ በፈቀደለት ደረሰኝ በመሆኑ የአሁን አመልካች ተቀናሽ እንዲደረግለት ለ1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ደረሰኞች ሁሉም ከ2ኛ ተጠሪ የተሰጡ ለመሆኑ ሊረጋገጥ የሚችለው በ2ኛ ተጠሪ (ደረሰኙን በሰጠውና) በ1ኛ ተጠሪ የደረሰኙን በፈቀደው ስለሆነ ከ2ኛ ተጠሪ የተሰጡ ደረሰኞች ስለመኖራቸው 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች የሰበሰበውን ግብር ከራሱ ሰነዶች እና ደረሰኞች ላይ በማመሣከር የተገኘውን የግብር መጠን አሳውቋል፡፡ የ2ኛ ተጠሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል አለመክፈል ለመመርመር ሥልጣኑ የተሰጠው ለ1ኛ ተጠሪ ነው፡፡ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪን ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ካደረገ በኃላ የአሁን አመልካች ተቀናሽ እንዲደረግለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ደረሰኞች ህጋዊ ደረሰኝ ያለመሆናቸውን፣ 2ኛ ተጠሪም በጣልቃ ገብ የሰጠው መልስ ይህንኑ የሚያረጋግጥ መሆኑን በማረጋገጥ የግብር ይግባኝ ጉባኤን ውሳኔ የሻረውና፣ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤትም የከፍ/ፍ/ቤትን ውሳኔ ያፀናው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94730 ሐምሌ 3 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 92474 ጥቅምት 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሣራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.114043

የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አቃቤ ሕግ ዐ/ህግ መብት አየሁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አባዲ ሞገስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በአቶ ንጉሴ ገ/ሕይወት ላይ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ) እና(ለ) እንዲሁም የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 166 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ሆነ ብለው ሕገ ወጥ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ወይም ማወቅ ሲገባቸው ንብረትነቱ የ2ኛ ተከሳሽ(ንጉሴ ገ/ሕይወት) የሰሌዳ ቁጥር 2-A01474 አ.አ የሆነች የቤት መኪና የቀረጥና ታክስ ስሌቱ ብር 170,958.10(አንድ መቶ ሰባ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከአስር ሳንቲም) የሚያወጣ የኮንትሮባንድ እቃ በ2ኛ ተከሳሽ እና በሌሎች ግብረአበሮች አማካኝነት ጭኖ በመያዟ እና 2ኛ ተከሳሽም የመኪናው ባለቤት በመሆኑ እና የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ ተመስርቶበት ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታዬ ባለበት ሁኔታ እና ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያስገኝ ድረስ ተከሳሽ በዋስ ሁኖ ጉዳዩን እንዲከታተል የተሰጠውን መብት በመጠቀም ልትወርስ የምትችለውን መኪና በቀን 27/04/07 ዓ/ም የመኪና ሽያጭ ውል በመፈራረም ሽያጩን ከቅን ልቦና ውጪ ከመደበኛ የገበያ ዋጋ በታች በ35,000.00(ሰላሳ አምስት ሺህ) በመሸጥ እና መኪናዋንም በጉምሩክ ወንጀል መተላለፍ ምክንያት በጉምሩክ ቁጥጥር ስር መሆኗን እያወቁ የባለቤትነት መብት /ሊብሬ/ 2ኛ ተከሳሽ ለ1ኛ ተከሰሽ (አባዲ ሞገስ) ስም ንብረቱ

www.abyssinialaw.com

እንዲተላለፍ በማድረግ በቁጥጥር ስር የነበረችውን መኪና በ1ኛ ተከሳሽ አማካኝነት በቀን 01/05/07 ዓ/ም ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ መኪናዋን ለማውጣት ሲሞክር በቁጥጥር ስር በመዋሉ የጉምሩክ ቁጥጥር በማሰናከል ወንጀል ተከሶአል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃልም ስለወንጀሉ የሚያውቁት ነገር የሌለ መሆኑን፣ መኪናውን በቅን ልቦና የገዙት መሆኑን ጠቅሰው መብታቸውን ጠብቀው የተከራከሩ ሲሆን የስር 2ኛ ተከሳሽ ግን ሊቀርብ ባለመቻሉ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ ትእዛዝ ተሰጥቶአል፡፡ በአመልካችና በአሁኑ ተጠሪ መካከል ያለው ጉዳይ ግን ክርክሩ ለብቻው እንዲቀጥል ተደርጎ አመልካች አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ያቀረበ ሲሆን ተጠሪም የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ መኪናውን የገዙት የፍርድ ቤት እግድ በሌለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ መኪናው እንዲለቀቅለት ጉምሩክ ቀርቦ መኪናው ኮንትሮባንድ በመጫኑ ምክንያት ለመንግስት ሊከፈል የሚገባውን ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ) መክፈሉ ግዥውን የፈፀመው በቅን ልቦና መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ተጠሪን ከወንጀሉ ክስ ነፃ ያሰናበታቸው ሲሆን የተያዘውም ንብረት ተገቢውን የአስተዳደር ቅጣት መክፍሉ ተረጋግጦ እንዲለቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪ ከቅን ልቦና ውጭ በመንቀሳቀስ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 198(1) በወቅቱ የመኪናው ባለቤት የነበረው ግለሰብ በመተላለፍ በሕግ ጥላ ስር ውላ እና የውርስ ውሳኔ ተላለፎባት የምትገኘውን መኪና በሕገ ወጥ መልኩ በመግዛት እና ባለቤት ነኝ በማለት የጉምሩክ ቁጥጥር ስራን ሆነ ብሎ ለማሰናከል ጥረት ያደረገ እና በእጅ በማስገባት ሲል እጅ ከፍንጅ የተያዘ መሆኑ መረጋገጡን ገልፆ ተጠሪ በዚሁ አድራጎታቸው ጥፋተኛ ሊባሉ እንደሚገባ፣ የሥር ፍርድ ቤቶች ከስልጣናቸው ውጪ መኪናው እንዲለቀቅ የሰጡት ውሳኔም ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና ለተጠሪ እንዲለቀቅ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማጋዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኪና በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት ግለሰብ ስም የሚታወቅ ሁኖ የኮንትሮባንድ ወንጀል ተፈጽሞበታል ተብሎ በ09/04/2007 ዓ/ም በአመልካች ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ በ13/08/2007 ዓ/ም በውልና ማስረጃ በተደረገ የሽያጭ ውል ከስር 2ኛ ተከሳሽ በብር 35,000.00 የገዙ መሆኑን፣ግዥው ሲፈጸም በመኪናው ላይ የተላለፈ እገዳ የሌለ መሆኑ የተረጋገጠና ተጠሪ መኪናው መያዙን አውቀው ለማስለቀቅ በሄዱበት ጊዜም ብር 40,000.00(አርባ ሺህ) እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ይህንኑ ክፍያ ከፈፀሙ በኃላ የጉምሩክ ቁጥጥር ስራ በማሰናከል ወንጀል የተከሰሱ መሆኑን ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ የጠቀሰባቸው አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 166 ሙሉ ይዘቱ ሲታይ የጉምሩክ ቁጥጥርን ስለማሰናከል የሚል አርእስት ያለው ሁኖ ዝርዝሩ ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ሹም ሰነዶችን እንዳይመረምር ወይም ማጓጓዣዎችን ወይም ዕቃዎችን እንዳይፈትሽ ወይም ወደ መጋዘን፣ የንግድ መደብር ወይም መኖሪያ ቤት እንዳይገባ ያደረገ ወይም ሁከት የፈጠረ ወይም ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያልሰጠ ወይም ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም መንገድ ሥራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 5,000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ እንደሚቀጣ በንኡስ ቁጥር አንድ ስር ያሰፈረ ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ፅኑ እስራት ከፍ ይደረጋል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ ከድንጋጌው ለተጠሪ አድራጎት አግባብነት ያለው የወንጀሉ ማቋቋሚያ "በማናኛውም መንገድ ስራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ" የሚለው ሐረግ ሲሆን አድራጎቱ ሆነ ተብሎ የሚፈጸም መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የጉምሩክ ቁጥጥርን የማሰናከል ተግባር ሆነ ተብሎ የሚፈፀም ስለመሆኑ የተጠቃሹ አዋጅ ድንጋጌ ይዘቱን መንፈሱ የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ተጠሪ አድራጎቱን ሆነ ብለው ስለመፈፀማቸው የሚያስገነዝቡትን የድርጊት አፈፃጸም ተግባር የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፣ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተጠሪ አከራካሪው መኪና የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ከተያዘ በኋላ መግዛታቸውን ያስረዱ ቢሆንም ተጠሪ በመኪናው ላይ የእግድ ትዕዛዝ ባለመሰጠቱ ምክንያት ተገቢው ማጣራት ተደርጎ በውልና ማስረጃ ቀርበው ግዥውን ፈጽመው መኪናው በጉምሩክ ቁጥጥር ስር የዋለ መሆኑን ከአወቁ በኋላም በመኪናው ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ብር 40,000.00 ለአመልካች ገቢ ከአደረጉ በኋላ በወንጀል የተከሰሱ መሆኑን በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አረጋግጠው አመልካች ይህንኑ ማስረጃ ሊያፈርስ የሚያስችል ማስረጃ ሊያቀርብ ያለመቻሉን ፍሬ ነገሩን የማጣራቱና

www.abyssinialaw.com

ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የግዥ ተግባር በቅን ልቦና የተፈጸመ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ደግሞ ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 166 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይ በዚህ ችሎት ሊሊወጥ የሚችል ሁኖ አልተኘም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የፈፀሙት ተግባር በቅን ልቦና የተከናወነ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ ይህ ችሎት የሚቀበልበት አግባብ የሌለ ሁኖ ተገኝቶአል፡፡ እንዲሁም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ባቀረበው የወንጀል ክስ መነሻ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው መኪና አስተዳደራዊ ቅጣት ተከፍሎ እንዲለቀቅ ያሰፈሩት ምክንያት ክፍልም በውጤቱ ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ለአመልካች መስሪያ ቤት የተሰጠውን አስተዳደራዊ ስልጣን የገደበ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም የበታች ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን አስተዳደራዊ ስልጣን ተፈጻሚ እንዲሆን በሚያስገነዝብ መልኩ በውሳኔአቸው ላይ ከማስፈራቸው ውጪ ይህንኑ ስልጣኑን ተግባራዊ እንዳያደርግ በግልጽ አልገለፁምና፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በጉዳዩ ለይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3867 ግንቦት 06 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3997 ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 192(2(ሀ)) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ የቅን ልቦና ገዥ ነው ተብሎ ከወንጀሉ በነፃ እንዲሰናበት በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ሆኖም አመልካች በሕጉ በተሰጠው ስልጣን አግባብ በመኪናው ላይ የሚወስደውን አስተዳደራዊ ውሳኔ ይህ ውሳኔ አያስቀረውም ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 111086

የካቲት 25 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጠታ

**አመልካች፡-** የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ህግ ማትሪያሲን

**ተጠሪ፡-** አሚኮ/ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ፍርድ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በአፋር ክልል የገቢርሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው ክስ አጭር ይዘትም የአሁኑ ተጠሪ የኢፌደሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 34/1/ እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ለ/ የተመለከተውን በመተላለፍ ለሱማሌ ክልል ህዝብ የሚያገለግል የምግብ ሸቀጥ የለውም ምንዛሪ /ፈራኮ ቫሎታ/ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ እንዲገባ የተደረገው 400 ኩንታል ስኳር የመመሪያ ቁጥር 25/2002 አንቀጽ 6 እና 7/2/ የተመለከተውን በመተላለፍ ተጠሪ ሆነ ብሎ ህገወጥ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ መመሪያው መሰረት ባለስልጣኑ ባዘዘው መሰረትና ቀን ማጓጓዝ ሲገባው ከተመለከት አላማው ውጭ በመገልገል መብቱን ሽፋን በማድረግ በሌላ ሰው ይዞታ ስር ለማዋዋል በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር በአዋሽ ጉምሩክ ኬላ በመያዙ በፈጸመው ከቀረጥ ነፃ በገባ እቃ አላግባብ መገልገል ወንጀል መከሰሱን የሚያሳይ ነው፡፡

የተጠሪ ድርጅት ወኪል ቀርቦ በሰጠው መልስ ድርጅቱ ወንጀል አለመፈጸሙን፤ በንብረቱ አጓጓዥ ላይ አመልካች ያቀረበው ክስ በብይን ውድቅ ተደርጓል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ አመልካች ባቀረበው ክስ ስኳሩን ጭነው ሲሄዱ የተያዙ ሹፌሮች በፍ/መ/ቁ/ 03544 ተከሰው በነፃ እንደተሰናበቱ፤ የአሁኑ ተጠሪ አብሮ ተከሰው የወጣ

www.abyssinialaw.com

ባይሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ አንቀጽ በመሆኑ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የዓቃቤ ህግ /አመልችች ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁን አመልች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይቅባኝ ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር እንዲታይ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርጓል፡፡ ዐቃቤ ህግ በሰበር አቤቱታው የአሁኑ ተጠሪ ከአሁን በፊት ተከሶ በነፃ አለመሰናበቱን፣ በሹፌሮች ላይ የቀረበው ክስ የኮንትሮ ባንድ ወንጀል ስለመሆኑ በመዘርዘር የስ ር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻር የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ ከሰ/መ/ቁ/111087 አንፃር እንዲታይ የቀረበ ሲሆን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት  ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽመዋል የተባሉት ሹፌሮች በአመልካች የቀረበባችው ክስና ማስረጃ እንዲከላከሉ ትእዛዝ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ በዚህም ክርክሩ በስር በገቢርሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲቀጥል መደረጉን የውሳኔው ግልባጭ ያመላክታል፡፡

የአሁኑ አመልች መዝገቡ በቀጠሮ ላይ በነበረበት ጊዜ ነሀሴ 22 ቀን 2007 ዓ/ም በፃፈው አቤቱታ በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ለ/ እንደወንጀል ድርጊት የሚቆጠር ቢሆንም በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት ድርጊቱ አስተዳደራዊ ጥፋት ሆኖ ወንጀልነቱ ቀሪ የተደረገ በመሆኑ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5፣3 መሰረት በሰ/መ/ቁ/ 111086 የተጀመረው የወንጀል ክርክር ተቋርጦ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት ጉዳዩ በባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁኑ ተጠሪ የተከሰሰበት አዋጅ ቁ/ 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ እና /ለ/ በአዲሱ  አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት ወንጀልነቱ ቀሪ ሆነዋል ወይስ አል ሆነም? አመልካች በጉዳዩ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ያቀረበው ጥያቄ በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦች ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ሁነው አግኝተናቸዋል፡፡

የመጀመሪያ ጭብጥ በተመለከተ፡- በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98/1/ሀ/ እና /ለ/ ስር እንደተመለከተው ከቀረጥ ነፃ በገባ እቃ አላአግባብ መገልገል የወንጀል ተጠያቂነት እንደሚያስከትል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት ሰው የእቃው መወረስ

www.abyssinialaw.com

እንደተጠበቀ ሆኖ እቃው በገባ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር የሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮና ከሶስት አመት እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት እንደሚያስቀጣ ተመልክቷል፡፡ በአዲሱ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163/1/ሀ/ እና /ለ/ ከቀረጥ ነፃ በገባ እቃ ያለአግባብ መገልገል ያለው ተጠያቂነት ቀረጥና ታክስ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱ በመቶ /50%/ የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተደርጓል፡፡ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል ሰባት የጉምሩክ ጥፋቶች እና ቅጣቶች በሚል በምእራፍ አንድ "የጉምሩክ ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች" በሚል ከአንቀጽ 156 እስከ 165 የተዘረዘሩትን ድርጊቶች በአስተዳደራዊ ቅጣት የሚታዩ ስለመሆናቸው ከድንጋጌዎቹ ይዞት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በአቤቱታው እንዳስረዳው ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ አስተዳደራዊ ጥፋት ሆኖ ወንጀልነቱ ቀሪ መሆኑ ተረድተናል፡፡ በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5/3/ መሰረት በቀደሞ ህግ እንደወንጀል የሚቆጠር ድርጊት በአዲሱ ህግ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ቀሪ ከሆነ ጉዳይ በሚታይበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በዚህም ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚታይ እንጂ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም ብለናል፡፡

ሁለተኛ ጭብጥ በተመለከተ፡- በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 163 መሰረት የተያዘው ጉዳይ በአስተዳደራዊ ውሳኔ የሚታይ ስለመሆኑና የአሁኑ አመልካችም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የማስተላለፍ ስልጣን በዚህ አዋጅ የተሰጠው በመሆኑ የመወሰን ስልጣኑ የተጠበቀ ነው፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአፋር ክልል የገቢረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 03559 በ30/03/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ/ 3106 ጥር 28 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በተለወጠ ምክንያት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ ወንጀልነቱ ቀሪ የተደረገ፤ በአስተዳደራዊ ቅጣት የሚታይ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች በተጠሪ ላይ ህጉ በዘረጋው ስርዓት አስተዳደራዊ ቅጣት የመወሰን ስልጣኑ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 117065

የካቲት 30 ቀን 2008ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሺርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዓቃቤ ህግ ምህረቱ ቁምላቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሚፍታ ካሚል ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ክሱ የኮንትሮባንድ ወንጀል ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ከስር ክስ ሶስት ተከሳሾች ከነበሩት ጋር የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ በቀን 10/10/2006 ዓ.ም ከቀኑ 7፡15 አከባቢ ምንም ዓይነት የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈፀባቸው እና ጠቅላላ ቀረጥና ታክሳቸው ብር 15,425.23 /አስራ አምስት ሺህ አራት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ ለመንግስት ያልተከፈለባቸው መሆናቸውን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው የተለያዩ ንብረቶች በ1ኛው ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ረዳትነትና የመኪናው ባለቤትነት እና 2ኛ ተከሳሽ አሽከርካሪነት ከጊዘን ወደ አሶሳ ለመሄድ በኮድ3-00277 ቤጉ በሆነ ሚኒባስ ጭነው በመጓጓዝ ላይ እያሉ ሽርቆሌ ፌዴራል ፖሊስ ካምፕ አካባቢ በፌዴራል ፖሊስ አባላት በቁጥጥር ስር በማዋላቸው የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ክስ ቀርበውበታል፡፡ ከ2ኛ-4ኛ ተከሳሾች ባለመቅረባቸው በሌሉበት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን ከስር መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የቀረበውን የወንጀል ክስ በመካዱ ፍርድ ቤቱም የዐ/ህግ ምስክሮች በመስማት ከመረመረ በኋላ ተጠሪ እንዲከላከል ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ መከላከያ ምስክር ያቀረበ ቢሆንም ባለመከላከሉ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ካለ በኋላ ቅጣት በተመለከተም በሁለት ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 50,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣና የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ ገደብ እና በተከሳሾች እጅ የተያዘው የኮንትሮባንድ ወንጀል ንብረቶች ለመንግስት ገቢ እንዲደረጉ፡፡ በተጠሪ

ስም የተመዘገበውን ንብረት ኮድ 3-00277 ቤት ሚኒባስ መኪና ለባለ ንብረቱ እንዲመለስ በማለት ወስኗል ፡፡

አመልካች በዚሁ የእስራት ቅጣቱ በገደብ መለቀቁና መኪናው ይመለስ በማለት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታው ቢያቀርብም በውሳኔ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የስር ፍርድ ቤቶች ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረም በማለት የቀረበ ነው፡፡ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የአሁኑ ተጠሪ የተሽከርካሪው ባለቤት እና በወቅቱ በተሽከርካሪው ላይ በረዳትነት ሲሰራ የኮንትሮባንድ እቃዎች ጭኖ በመያዙ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የተከሰሰ እና በዚሁ አዋጅ ስር ጥፋተኛ የተባለ እንደመሆኑ በወንጀል የተፈፀመበትን ማጓጓዣ መወረስ እንዳለበት ህጉ በግልፅ ደንግጎ ይገኛል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን የህግ ድንጋጌ በጥልቀጥት ሳይመለከት እና ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ማጓጓዣውን በተመለከተ ያለምንም ምክንያት ለባለንብረቱ ይመለስ በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ማጓጓዣ ላይ የተሰጠውን ትእዛዝ አግባብነት ከጉምሩክ ህግ አንፃር በጥልቀት መመርመር ሲገባው ተጠሪ በወቅቱ በመኪናው ላይ በረዳትነት ሲሰራ እንደነበረ የስር ፍርድ ቤት በማረጋገጥ የሰጠው ጥፋተኝነት ውሳኔ ባልተሸረበት እና የመከራከሪያ ነጥብ ያለሆነውን የአሁን ተጠሪ መኪናው ኮንትሮባንድ እቃ ሲጫን በቦታው አልነበረም በማለት የወ/መ/ስ/ስ/ህግን እና የሙግት ስነስረአት በሚቃረን መልኩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማፅናቱ የህግ ስህተት የተፈፀመ መሆኑን፤ እንዲሁም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192፤196 እና 197 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት የቅጣቱን አፈፃፀም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 196/2/ መሰረት መገደቡ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ተጠሪ ላይ የተጣለውን የቅጣት አፈፃፀም ገደብ እንዲያነሳልን እና የአሁኑ ተጠሪ የሆነውን ኮድ 3-00277 ቤት ተሽከርካሪ እንዲመለስ የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሮ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ መሰረት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ትእዛዝ እንድሰጥላቸው አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር ንብረትነቱ የተጠሪ ከሆነ ኮድ 3-00277 ቤት ሚኒባስ የኮንትሮባንድ ዕቃ ተጭኖ በመገኘቱ በአዋጅ ቁ.622/2001/ አንቀጽ 91/2/ መሰረት ተጠሪ ጥፋተኛ መባሉ ተረጋግጦ እያለ ዕቃው የተጫነበት መኪና ለተጠሪ ይመለስ የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁ. 622/2001/ አንቀጽ 91/2/ እና 104 ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረትም ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በታዘዘው መሰረት በቀን 21/01/2008ዓ/ም የተፃፈ 2 ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡  ይዘቱም ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ

www.abyssinialaw.com

የገደበው ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ስለሆነ የህግ ስህተት የሚያነሳና ለክርክር የሚቀርብ አይደለም። በወቅቱ ነዳጅ አልቆብናል አምጣልን ብለውን ከአሶሳ ይዘናቸው በሄድኩበት የእርዳታ ዘይቱ ጫነ መሆኑን በመገንዘብና ከፍተኛው የገንዘብ ቅጣት 50,000 የተቀጣሁ በመሆኑ በኢግዚቢትነት የተያዘው ተሽከርካሪ ለተከሳሽ ይመለስለት መባሉአግባብነት ያለውነው። ስለዚ የስር ፍርድ ቤቶች ወሳኔ በማፅናት የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ በነፃ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልሱን አቅርበዋል።

አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2008ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል ተጠሪ በጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ምንም ቅሬታ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አላቀረበም:: የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሻር መኪናው ሲያዛ በቦታው አልነበርኩም የመከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም:: በሌላ በኩል 50,000 ብር ከፈልኩ በማለት ያቀረበው ጥፋተኛ በተባለበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ ስር በተነገገው መሰረት የተጣለበት የገንዘብ መቀጮ እንጂ የተያዘው መኪና ላማስለቀቅ የተከፈለ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንዲገነዘብልን በማለት አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመርነውም ታክስና ቀረጥ ሳይከፈለበት የኮንትሮባንድ ዕቃ ስታጓጉዝ የተያዘችው የተጠሪ መኪና ይመለስ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከግምሩክ አዋጅ ህጉ አግባብነት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን የሚለውን ጭብጥ መልስ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባው ታክስ እና ቀረጥ ብር 15,425.23/አስራአምስት ሺህ አራት መቶ ሃያ አምስት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም/ያልተከፈለበት ሲያጓጉዝ በተያዘበት ወቅት ተጠሪ የመኪነው በረዳትነት እንደነበረ እንዲሁም የመኪናው ባለቤት መሆኑን በማረጋገጥ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ የጥፋተኝነት ውሳኔ በመስጠት የፅኑ እስራትና የገንዘብ መቀጮ ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን ተረጋግጠዋል። በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ በይግባኝ ቀርቦ የተለወጠ አይደለም። ተጠሪ ጥፋተኛ ከተባለና ለኮንትሮባንድ ዕቃ መጓጓዣ የዋለው የተጠሪ መኪና መሆኑን ከተረጋገጠ መኪናው የማይወረስበት ሁኔታ አለ ወይ የሚለውን ከሕጉ አንፃር መታየት አለበት።

አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91/2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ/1/ ላይ በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ የተገኙ እቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው እቃዎቹ ያጓጓዘ፣

www.abyssinialaw.com

ያከማቸ፤ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው በቅን ልቦና ለወንወጀሉ ባዕድ የሆኑት ሰዎች መብት ሳይነካ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃና መሳሪያ እና የወንጀሉ ፍሬ እንደሚወረሱ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ የኮንትሮባንድ ዕቃ መሆኑን እያወቀ ያጓጓዘ በመሆኑ በመረጋገጥ ጥፋተኛ ስለተባለ በቅንልቦና ወይም ለወንጀሉ ባዕድ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ እንዲሁ በሆነበት ከጉምሩክ አዋጅ ቁ.622/2001 አንቀጽ 104/1/ ማንኛውንም እቃ ወይም ማጓጓዣ ሊወረስ በሚችል ወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ተጨማሪ ትእዛዝ መስጠት ሳይስፈልግ እቃው ወይም ማጓጓዣው እንዲወረስ ይደረጋል ሲል ተደንግጓል፡፡

የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ለማፅናት እንደምክንያት ያደረገው ተጠሪ ዕቃው ሲያዝ በቦታው አልነበረም ዕቃው ሲጫን አያውቅም የሚለውን በማስረጃ የተረጋገጠው ረዳት ሆኖ ዕቃው የመኪናው ሽፌር የነበረው 2ኛ ተከሳሽ የኮንትሮባንድ ነው እንዳይጫን እየተባለ የጫነ መሆኑን በአመልካች ምስክሮችበመረጋገጥ በተጠሪ ላይ የጥፋተኘነት ከተሰጠበት ውሳኔ በሚቃረን እና የሰ/መ/ቁ.76976 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመጥቀስ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ለዚህ ጉዳይ ተመሳሳይ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64819 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥተቦታል፡፡ በመሆኑ ይህ የህጉ መንፈስ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት ሆኖ በወንጀሉ ተሳተፊነት በማረጋገጥ የጥፋተኝነት ከተሰጠ ሌላ ተጨማሪ ትእዛዝ ሳያስፈልግ የኮንትሮባንድ ዕቃ ለመጓጓዣ የዋለው መኪና ምንም ህጋዊ ምክንያት በሌለው ለተጠሪ ይመለስ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ከጉምሩክ አዋጁ አንቀጽ 91/2/ እና 104/1/ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝተዋል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የቤ/ጉ/ክ/መ/ ጠ/ፍ/ቤትበመ/ቁ.06590ሐምሌ 23 ቀን 2007ዓ/ም፤ የተሰጠ ውሳኔ እና የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.09092ግንቦት 28 ቀን 2007ዓ/ም የተጠሪ መኪና ይመለስለት በማለት የተሰጠ ቅጣት ውሳኔ ክፍል ብቻ በወ/መ/ስ/ስ/ቁ.195/2/መ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ ላይ የሁለት ዓመት የፅኑ እስራት በመገደብ የተወሰነ ቅጣትና የገንዘብ መቀጮ ፀንተዋል፡፡
3. በተጠሪ ስመንብረቱ ተመዝግቦ የሚገኘው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-00277 ቤጉ የህዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ ለመንግስት በውርስ ገቢ እንዲደረግ በማለት ታዟል፡፡

**መዝገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡** የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# አዕምሯዊ ንብረት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 99082

ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍሬ ህይወት ደመቀ (የመካኒኩ ፊልም ኘሬዲውሰር)- ጠበቃ ሙሉጌታ ዘመነ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ት ቤሩት ዳዊት - ጠበቃ መንግስቴ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቅጅና ተዛማጅ መብት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡

የተጠሪ የክስ ይዘትም፡- ዕውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውን በመሰዋት በነጠላ ዜማ የለቀቁትን "በትዝታ አቅርቤ" የተሰኘውን የዘፈን ሥራቸውን ያለፈቃዳቸውና ያለ ስምምነታቸው የአሁኗ አመልካች ኘሮዲውስ ላደረጉት "መካኒኩ" ለተባለው ፊልም በማጀቢያነት (ሳውንድትራክ) በመጠቀም ያለአግባብ ቁሳዊ ጥቅም ያገኙበት መሆኑን፣በአመልካች አድራጎትም 164,000.00 የሚገመት የኢኮኖሚ ጥቅም ማጣታቸውንና የብር 100,000.00 የሞራል ጉዳት እንደደረሰባቸው ጠቅሰው በድምሩ ብር 264,000.00 (ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ብር) ከነወለድ ወጪና ኪሣራ ጨምረው እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ ክስ በሰጡት መልስም፡- የተጠሪ የሙዚቃ ሥራ ለመካኒኩ ፊልም ማጀቢያነት የተጠቀሙት መሆኑን ሳይክዱ የሙዚቃው ሥራ ለፊልሙ መጠቀም ይችሉ እንደሆነ በአቶ ዮናስ ብርሃነ መዋ በኩል ተጠሪን ጠይቀውና ተገናኝተንው የተጠሪን ስራ

www.abyssinialaw.com

እንዲያስተዋውቁላቸው ተነጋግረው ሰኔ 8 ቀን 2003 ዓ.ም በአቀነባባሪያቸው የእጅ ጽሑፍ የተፃፈ ሲዲ ተጠሪ አምጥተው የሠጧቸው መሆኑን፣ በዚህም ተጠሪ ወደውና ፈቅደው በማጀብያነት አመልካች እንዲጠቀሙበት ሰጥተዋቸው እያለ ያለፍቃዴ ነው ማለታቸው ሐሰት መሆኑን ጠቅሰው ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያስችላቸው ምክንያት የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭም እንደተጠሪ ያለ ጀማሪ ዘፋኝ የዘፈነው ዘፈን ከብር 3000.00(ሶስት ሺህ) ባለይ እንደማይሸጥ እየታወቀ ተጠሪ ብር 164,000.00 የኢኮኖሚ ጉዳት ደርሶብኛል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸው ያላግባብ መሆኑንና በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ግምት እንደሚቃወሙ፣አዲስ ዘፈን እንደመሆኑ መጠን ለዘፈኑ ገንዘብ ከሚከፈላቸው ክሊፕ እንዲሰራላትና ዘፈኑ የፊልም ማጀቢያ እንዲሆን የምረቃ ቀን ቀርበው ምስጋናና ሰርቲፊኬት እንዲሰጣት፣ዘፈኑ በተለያዩ ሚዲያዎች ተሰራጭቶ እንዲተዋወቅላት በዝርዝር ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ሰኔ 08 ቀን 2003 ዓ/ም ተፈራርመው ከስምምነቱ በኋላ ሰኔ 14 ቀን 2003 ዓ/ም በአቀናባሪያቸው የእጅ ፅሑፍ የተፃፈ ሲዲ እራሷ አምጥታ የሰጠቻቸው መሆኑን፣በዚህም መሰረት የሙዚቃ ሲዲዋን በላይ ላይ ድምፃዊት እራሷ መሆኗን አቀናባሪያቸው ሮቤል ዳኜ መሆኑን፣ ስራቸው በቅርብ ቀን በአልበም እንደሚወጣ፣ሲዲውም ላይ በመግለፅ የተለያዩ ሚዲያዎች በፕሮግራማቸው በማስተላለፍ እንዲያስተዋወቁላቸው ያደረጉ መሆኑን፣ፊልሙ በሚመረቅበት ጊዜም ለፊልሙ ማጀቢያነት የተጠቀሙት ሙዚቃ የተጠሪ መሆኑን በማስተዋወቅ በመድረክ ላይ ተጠርተው ሰርቲፊኬት እንዲሰጣቸው ማድረጋቸውንና በስምምነቱ መሰረት በአመልካች በኩል ሳይፈፀም የቀረው የዘፈኑን ክሊፕ ማዘጋጀት ብቻ ሲሆን ይህን በተመለከተም ስራው ያልተሰራው ተጠሪ የዘፈኑን ታሪክ አዘጋጅተው ባለማቅረብና ለክሊፑ የሚሆነውን አልባሳትና ቦታ አዘጋጅተው ባለመቅረባቸው ጥፋት መሆኑን፣ ክሊፑ የሚሰራበት ዋጋ ከብር 4000.00 እንደማይበልጥና ተጠሪ ዜማቸውን በመሸጥ ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አመልካች ያለማስቀረታቸውንና በፈቃዳቸው መሰረት ለተከናወነ ተግባርም የሞራል ካሳ የሚከፈልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና የአመልካችን የሰው ምስክሮችን ከሰማ በኋዋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ከተጠሪ ዕውቅና ውጭ ማጀቢያ ዘፈኑን ለፊልሙ ያለመጠቀማቸውን ያስረዱ ስለሆነ ከሳሽ የደረሰባቸው ኢኮኖሚያዊም ሆነ የሞራል ጉዳት የለም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያነት የተጠቀሙት በተጠሪ ሙሉ ፍቃድ ስለመሆኑ ተረጋግጦአል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ ባግባቡ ነው በማለት

www.abyssinialaw.com

የተቀበለው ሲሆን ተጠሪ ዘፈናቸውን ለአመልካች ፊልም ማጀቢያ በፍቃዳቸው ሲሰጡ ተጠሪ በአመልካች በኩል የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰራላቸው፣በገንዘብ መልክ ከሚሰጣቸው ይልቅ የዘፈኑ ክሊፕ እንዲሰራላቸው አመልካች መዋዋላቸውን አልካዱም፣አመልካች እንደውሉ ያልፈጸምኩት ተጠሪ የዘፈኑ ታሪክ፣ አልባሳት እና ክሊፑ የሚሰራበት ቦታ ባለመምረጣቸው ነው ቢሉም አመልካች ክሊፑን ለመስራት የጠቀሷቸው ነገሮች ተጠሪ ሚሟላት እንደሚገባቸው የሚያመላክት ስምምነት ስለመኖሩ አላስረዱም በሚል ድምዳሜ ተጠሪ እነዚህ ነገሮች ባይሟሉኳ በክሊፑ ፈንታ ገንዘብ ሊከፈላቸው ይችል እንደነበረ፣ አመልካች በክሊፑ ፋንታ ለተጠሪ ክፍያ ሊፈጽሙ እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ አምኖበታል በማለት የካሳውን መጠንም በርትዕ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) አድርጎ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም፡- ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያነት የተጠቀሙት በተጠሪ እውቅና እና ፈቃድ ስለመሆኑ ከአረጋገጠ በኂላ በክሊፑ ፋንታ ተጠሪ ገንዘብ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ባልተወጡበት አግባብ ከመሆኑም በላይ የካሳው መጠንም ማስረጃ ቀርቦ እያለ በርትዕ መወሰኑ ከሕጉ ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም

1. አመልካች ለተጠሪ በክሊፑ ፈንታ ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ የግራ ቀኙን ተነፃፃሪ ግዴታ ያገናዘበ ነው? ወይስ አይደለም?
2. የካሳው መጠን በርትዕ መወሰኑን ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታይ የሚገባ ሁነው አግኝተናል፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ ውል መኖሩን በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ አመልካች በጽሑፍ የተደረገው ውል ጠፍቶአል በማለት በሰው ምስክሮች ማረጋገጥ እንደሚችሉ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢነት የሌለውና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2003 ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ለዚህ ችሎት በጽሑፍ ከአቀረቡት መልሳቸው የተገነዘብን ቢሆንም ይህ የተጠሪ ክርክር በዚህ አመልካች

www.abyssinialaw.com

ባስከፈቱት የሰበር መዝገብ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ ራሱን የቻለ የሠበር አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን የጠቀሱ ሲሆን በዚህ ረገድ አለ የተባለውን የሰ/መ/ቁጥር 100338 አስቀርበውን ስንመለከተውም መዝገቡ በሰበር አጣሪ ችሎት በ03/10/2006 ዓ/ም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ መዘጋቱን መረዳትን ችለናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በግራ ቀኙ መካከል በፅሑፍ የተደረገ ውል የለም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተኘም፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ሕጋዊ ውል መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ የግራ ቀኙ ተነፃፃሪ

ግዴታ የሚለየው በዚሁ ውል በመሆኑ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን የሚቀርበው ክርክር በዚሁ የውል ሰነድ ይዘት መደገፍ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2001 እና 2005 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡

በመሠረቱ ውል ሕጋዊ ውጤት ያለው ተግባር እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በውሉ የተጣለበትን ግዴታ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ተዋዋዮች በውሉ በተገለጸው ስምምነት መሰረት ግዴታቸውን ከተወጡ ውለታው በታሰበው ዓላማ መሰረት ተፈፅሟል ለማለት የሚቻል ሲሆን ይህም ማለት የውሉ ግዴታ ያለበት ሰው በውሉ ላይ የተገለጸውን የመስጠት፣ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ተግባር በተገቢው መንገድና በብቃት ማከናወኑን ማረጋገጥ መሆኑ ይታመናል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በምን አይነት አኳኋን፣ ጊዜና ቦታ የውል ግዴታቸውን መፈጸም እንዳለባቸው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ከቁጥር 1740 እስከ 1762 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ አንድ ተዋዋይ ወገን በውሉ የገባውን ግዴታ በውላቸውና በሕጉ ውስጥ በተደነገገው አኳኋን ያልፈፀመ እንደሆነ የውል ግዴታውን እንደጣሰ የሚቆጥር ሲሆን የውሉ ተጠቃሚ የሆነ ተዋዋይ ወገን ደግሞ እንደውሉ እንዲፈጸምለት ወይም ውሉ እንዲፈርስለት የመጠየቅ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1771(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1757 ድንጋጌ እንደሚየሳየው ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወገን ጥያቄውን ማቅረብ ያለበትና ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው በውሉ መሠረት አስቀድሞ ሊወጣው የሚገባ ግዴታ የተወጣ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሊፕ ለማሰራት ግዴታ መግባቸውን ሳይክዱ የክሊፑ ስራ እንደውሉ ያልተፈፀመው በተጠሪ ጥፋት ነው፣ተጠሪ የዘፈኑን ታሪክ፣አልባሳት ባላማቅረባቸውና ክሊፑ የሚሰራበትን ቦታ ባለመምረጣቸው ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በዚህ ረገድ ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ውሉ መኖሩን አምነው የተጠሪ ግዴታ ነው እስካሉ ድረስ ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ መወጣት የነበረባቸው መሆኑን ከክርክራቸው አቀራረብ መረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በውሉ የገቡትን ግዴታ ያልተወጡበት መንገድ ስለመኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር

www.abyssinialaw.com

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 258 እና 259፣ እንዲሁም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1757፣ 2001 እና 2005 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ዘፈኑ ለፊልም ማጀብያ እንዲውል ፈቅደው ከሰጡ የሞራል ጉዳት ደርሶብኛል፣ የሞራል ጉዳት ካሣ ይከፈል ሊሉ አይችሉም በማለት መወሰናቸውን፣ግራ ቀኙን እስከዚህ ችሎት የሚያከራክራቸው ነጥብ ግን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በክሊፑ ፈንታ አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ ሊከፍሉ የሚገባ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አምኖአል በማለት አመልካችን ኃላፊ አድርጎ የኃላፊነቱን መጠንም በርትዕ ብር 100,000.00 ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መሆኑን ነው፡፡

የተጠሪ ስራ በአዋጅ ቁጥር 410/96 አግባብ ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑና አመልካች ለፊልማቸው ማጀቢያነት የተጠቀሙበት መሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊማቸው ማጀቢያነት ሲጠቀሙ ግን ለተጠሪ የከፈሉት ገንዘብ ስለመኖሩ በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ለተጠሪ ገንዘብ ከሚከፈላቸው የክሊፑን ወጪ አመልካች ሸፍነው ክሊፑን ሊሰሩላቸው መስማማቸውን፣ ሆኖም ይህ ስምምነት ተፈፃሚነት ሳያገኝ የቀረው ተጠሪ በራሳቸው በኩል የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ባለመወጣታቸው ነው በማለት አመልካች ተከራክረው ይህ የአመልካች ክርክር በማስረጃ ያለመደገፉን ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማረጋገጡን ይህ ችሎት ተገንዝቦአል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 410/96 ጥበቃ ያገኘውን የተጠሪን ዘፈን አመልካች መጠቀማቸው እስከተረጋገጠ ድረስ አንድ ዘፈን ለፊልም ማጀቢያነት ሲውል ለዘፈኑ ባለቤት ሊከፈል የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያህል ተጠሪ የማያገኙበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ አመልካችን ኃላፊ ማድረጉ ከአዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 7፣ 8 እና 34 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንጻር የሚነቀፍ ሁኖ ስላልተገኘ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ረገድ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው አቢይ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ካሳውን የወሰነበት አግባብ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡ በቅጅ ወይም በተዛማጅ መብቶች መጣስ ምክንያት ለፍ/ቤት የቀረቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የካሣ አከፋፈል ባለመብቱ የደረሠበት የገንዘብ ጉዳት እና በመብቱ መጣስ ምክንያት የተገኘ ትርፍን መሰረት ያደረገ መሆን እንደአለበት የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ የካሳ አከፋፈሉ ባለመብቱ መብቱ ለተጣሰበት ሥራ ያወጣውን ወጪና ተከሣሹ ያገኘው ትርፍን ኢኮኖሚያዊ መብቱን ለማስከበርና የሞራል ካሣ የመክፈል ኃላፊነትን የሚያጠቃልል መሆኑ ይታወቃል፡፡ አዋጁ ለሞራል ጉዳት የሚከፈል ካሣ በጣም አነሰ ቢባል ከ100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የማያንስ ሆኖ እንደ ጉዳቱ መጠን ከ100 ሺህ ብር በላይ

www.abyssinialaw.com

ሊወሠን እንደሚችል የአንቀፅ 34(4) ድንጋጌ በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን የቅጂና ተዛማጅ መብቶችን በመጣስ የሚኖር የፍትሐብሔር ኃላፊነት የጉዳት ካሣና የሞራል ካሣ ከመክፈል በተጨማሪ ለካሣ አከፋፈሉ ምክንያት የሆነው ሥራ በባለመብቱ ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ ከንግዱ እንቅስቃሴ ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዲወገዱ ወይም በሌላ ተገቢ አኳኋን እንዲጣሉ ለማዘዝ እንደሚቻልም ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ ውሳኔ ሲሰጥ የተከራካሪ ወገኖችን የማስረዳት ግዴታ ግንዛቤ ባስገባ መልኩ ማስረጃን መሰረት ማድረግ እንዳለበት የሚታወቅ ሲሆን በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ቀርቦ በማስረጃው መወሰን አስቸጋሪ ሁኔታ ካለም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 በተመለከተው አግባብ ካሳውን መወሰን እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1790(2) ድንጋጌን በምንመለከትበት ጊዜ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ካሳ በርትዕ ከሚወሰንባቸው ምክንያቶች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ስር የተመለከቱት ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የነገሮች ተራ ሁኔታዎች የሚለው ሐረግ ይገኝበታል፡፡ ይህ የድንጋጌው ይዘት ነባራዊ አለምን መሰረት በማድረግ የነገሮች ተራ ሁኔታዎች ተመዛዝነው የካሳ መጠኑ ሊወሰን እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያ በመጠቀማቸው ምክንያት በተጠሪ የደረሰ የኢኮኖሚ ጉዳት አልያም አመልች የተጠሪን ዘፈን በፊልም ማጅብያ ሲጠቀሙበት በገንዘብ ምን ያህል ይከፈላቸዋል ለሚለው ጥያቄ ተጠሪ 164,000.00 (አንድ መቶ ስድሳ አራት ሺህ ብር) የኢኮኖሚ ጉዳት ደርሶብኛል ከማለታቸው በቀር ይህንኑ የኢኮኖሚ ጉዳት የደረሰባቸው ለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረቡ፣ አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልም ማጀብያ ሲያውሉ ሊከፍላቸው ያሰቡት አልያም ለዘፈኑ ክሊኘ ምን ያህል እንደሚያወጡ ተዋውለናል ከማለታቸው ውጪ በጽሑፍ ውስጥ አስፍረው የነበረ ስለመሆኑ ያስረዱት ነገር የለም የሚሉትን ምክንያቶችን ጠቅሶ በተጠሪ ላይ የደረሰው ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ወይም የቀረ ጥቅም ለመገመት አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱን መደምደሙን በዚህም ምክንያት አመልካች በርትዕ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት መወሰኑን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በውል ሰነዱ ላይ የሰፈረውን ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ባያስረዱም ለአንድ ፊልም ማጀቢያነት የሚውል ዘፈን ሊከፈልበት የሚገባው ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ገበያውን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ዘፋኞች ለተያዩ ፊልሞች የተከፈላቸውን ዋጋ ለይተው በመግለፅ፣ በዚህ ረገድም የሰነድ ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪም አመልካች የጠቀሷቸው ዘፈኖችና ዋጋቸው በስር ፍርድ ቤት በክርክር ደረጃ አልተነሱም ሳይሉ አመልካች ሊከፈል ይገባል የሚሉት ዋጋ የወቅቱን የፊልም ማጀቢያ ዘፈን ዋጋ ያላገናዘበ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ለዚህ ችሎት ከሰጡት የፅሑፍ መልስ ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ማስረጃ ቆጥረው እያሉና ማስረጃዎቹ ለጉዳዩ ያላቸውን አግባብነት ሳይመረምር በውል

www.abyssinialaw.com

ሰነዱ ላይ ሰፍሮ የተገኘ ዋጋ አልተገኘም በሚል ምክንያት ብቻ ወደ ርትዕ መሄዱ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ድንጋጌን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን ማስረጃ የመስማት መብት እና ፍርድ ቤቱ እውነትን መሰረት ያደረገ ዳኝነት ለመስጠት ይቻለው ዘንድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 ድንጋጌን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባበትን አግባብ ያላገናዘበ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

አንድ ዘፈን ለአንድ ፊልም ማጀቢያ ሲውል ዋጋው በተዋዋይ ወገኖች ሊቆረጥለት የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም ዋጋው በውሉ መታወቅ ካልተቻለ ግን ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቧቸው አግባብነት ባላቸው ሌሎች ማስረጃዎች ወይም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 መሰረት መድቦ በሚያጣራው ባለሙያ ሊታወቅ የሚችል መሆኑን የነገሮች ተራ ሁኔታዎች የሚያስረዱ መሆኑን ነባራዊው አለም ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪ ዘፈን ለፊልም ማጀቢያነት ሲውል ሊከፈል ይችል የነበረውን ዋጋ አመልካች በዚህ ረገድ ማስረጃዎቼ ናቸው በማለት ከአቀረቧቸው የሠነድ ማስረጃዎች ወይም ከሚመለከተው የሙያ ማህበር አግባብነት ያለውን ባለሙያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 መሰረት እንዲመደብ አድርጎ ትክክለኛውን የወቅቱን ዋጋ አጣርቶ መወሰን ሲገባ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጪ በርትዕ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 117093 ሐምሌ 16 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 93456 ጥር 30 ቀን 2006 ዓ/ም በከፊል የተሻረው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የተጠሪን ዘፈን ለፊልሙ ማጀቢያ በመጠቀማቸው ዋጋውን ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ሆኖም አመልካች ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ በርትዕ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2102 ትክክለኛ አፈፃጸም ያላገናዘበ በመሆኑ ተሽሯል፡፡በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ኃላፊ የተባሉ መሆኑን በመገንዘብ የኃላፊነት መጠኑን ግን በፍርድ ሀተታው ላይ በተገለጸው አግባብ አግባብነት ባላቸው የአመልካች ማስረጃዎች እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 መሰረት ከሚመለከተው የሙያ ማህበር ተጣርቶ በሚቀርበው ማስረጃ መሰረት በመመርመር ሊወሰን ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡

www.abyssinialaw.com

4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡ **መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡** የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

# የዳኝነት ስልጣን

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 105211

ጥቅምት 1/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካቾች፡- 1. አቶ እንዳለ ደንቦባ
2. አቶ ንጉሴ ደንቦባ
3. ወ/ሪት ውቢት ደንቦባ
4. ወ/ሮ ሽቶ ደንቦባ
} ጠበቃ አብዮት አበበ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አልማዝ ደንቦባ
2. ወ/ሮ ዘውዲቱ ደንቦባ
3. ወ/ሮ እታፈራሁ ደንቦባ
4. አቶ ጌታቸው ደንቦባ
5. ወ/ሮ ወይንሐረግ ደንቦባ
} ጠበቃ ሰለሞን ስዩም ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ የቀደመ ውሳኔውን በመሻሩ እና ይግባኝ ሰሚውና የሰበር ችሎቱም

www.abyssinialaw.com

ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የቀረበላቸውን አቤቱታ ባለመቀበል መዝገቡ በመዝጋታቸው የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ባላንባራስ ደንቦባ ውፍዬ ህዳር 1996 ዓ.ም ኑዛዜ አድርገዋል ተብሎ ለፍ/ቤቱ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ኑዛዜውን በማፅደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በኑዛዜው ላይ የተጠቀሱት ምስክሮች ኑዛዜው በተደረገበት ዕለት በቦታው ያልነበሩ ኑዛዜው ላይ የፈረሙት ኑዛዜው ከተደረገ በኂላ ቢሮዋቸው ድረስ በሄደላቸው መሰረት በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881/3/ የተመለከተውን የሚያሟላ አይደለም፤ በኑዛዜው ተራ ቁጥር 5 የተመለከተው የንግድ ድርጅት ሟች ከባለቤታቸው ጋር ያፈሩት በመሆኑ የራሳቸው ብቻ ባልሆነ ንብረት ላይ ኑዛዜ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፤ ለመቃወም አመልካቾች የተናዘዙትም ሊደርሳቸው ከሚገባው ድርሻ በታች ነው፤ ስለሆነም ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት የመቃወም አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች ለአቤቱታው በሰጡት መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት የሚቀርብ አቤቱታን ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ጉዳይም ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት የተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 881 እና 882 የተመለከተውን የተከተለ ነው፤ ሟች በኑዛዜው የገለፁት ድርሻዬን በማለት ነው፤ ሊደርሰን ከሚገባው ድርሻ በታች ነው ለሚሉትም በህይወት የሌሉትን ወ/ሮ አለምፀሐይ ደንቦባን በመቀላቀል የንብረቱን ግምት በማካፈል በመሆኑ መቃወሚያው የሕግ መሰረት የለውም ብለዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በተመለከተ የኑዛዜውን ሰነድ መርምሮ የኑዛዜ ወራሽነት ውሳኔ የሰጠ ራሱ ፍ/ቤቱ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት በውሳኔው ላይ በዚያው መዝገብ ላይ የሚቀርበውን መቃወሚያ ተቀብሎ ለማየት ስልጣን አለው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በፍሬ ጉዳዩም የግራ ቀኙን ክርክር እና በኑዛዜው ላይ የተመለከቱ ምስክሮችን ቃል ከሰማ በኂላ ከአራቱ ምስክሮች መካከል ሁለቱ ኑዛዜው በማን እንደተፃፈ የት እንደተፃፈ አለማወቃቸውን ገልፀው ኑዛዜው ላይም የፈረሙት ሁሉም ምስክሮች በሌሉበት መሆኑን ተናዛዡ ሲፈርም ያላዩ መሆኑን ገለፀዋል፤ የቀሩት ሁለቱ ምስክሮች ደግሞ ኑዛዜው የት እንደተፃፈና ማን እንደፃፈው ያላዩ መሆኑን ገልፀው ነገር ግን ተፅፎ የቀረበው ኑዛዜ በአራቱ ምስክሮች ፊት ተነቦ ተፈርሞ ነበር በማለት መስክረዋል፡፡ ስለሆነም ኑዛዜው የፍ/ብ/ህ/ቁ 881 ስር የሰፈረው ያሟላ ካለመሆኑም በላይ የምስክሮች ቃል ተመሳሳይ አይደለም በማለት ቀሪዎችን መከራከሪያዎች መመልከት ሳያስፈልግ አስቀድሞ የተሰጠው የኑዛዜ ወራሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 360/2/ መሰረት በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

ይግባኙ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት የሰረዘ ሲሆን የከተማው የሰበር ችሎትም ውሳኔው መሰረታዊ ሊባል የሚችል የሕግ ስህተት ስላልተገኘበት ለሰበር አያስቀርብም ብሏል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ፍ/ቤት መስከረም 13/2007 ዓ.ም የተፃፈ 4 ገፅ ዝርዝር የሰበር ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ይኸው ተመርመሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሰረት የቀረበለትን የመቃወም አቤቱታ አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና ከአዋጅ ቁጥር 408/1996 እንዲሁም በሰበር መ/ቁ 75560 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም በፅሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41/1//ሸ/ በአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 2/1/ እንደተሻሻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡ ተቃውሞ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠውም በሕጉ በተደረገው የዳኝነት ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በሌላም በኩል የተቃውሞ አቤቱታው ያስከተለው የሕግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ይዘት ሲታይ ከኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀቱ የዘለለ እንድምታ የለውም፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች አስቀድመው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በቀረበ አቤቱታ ላይ ባሳለፉት ውሳኔ የሚነሳን የተቃውሞ አቤቱታ ተቀብለው ለማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የላቸውም ተብሎ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም፡፡

የሰ/መ/ቁ/ 75560 ሐምሌ 26/2004 ዓ.ም በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የባልና ሚስትነትን ማስረጃን የሚመለከት ሲሆን በእጃችን ካለው የወራሽነት ማስረጃ ጥያቄ ጋር አንድ ናቸው ወይም ተመሳሳይነት አላቸው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የስረ ነገር ስልጣን ጥያቄን ለመወሰን መርህ የሆነው የክሱን ምክንያት ይዘት መመልከት ነው፡፡ ከይዘቱ ውጭ የሆኑ ሌሎች የማያመሳስሉ ሁኔታዎች መኖር ጉዳዮች በተመሳሳይ የስረ ነገር ስልጣን ስር ያርፋሉ የሚል መደምደሚያ ላይ አይደርስም፡፡ የባል ወይም የሚስትነት ማስረጃ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በቀረበ አቤቱታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት ተቃውሞ ሲቀርብበት ተቃውሞውን ተከትሎ ፍ/ቤቶች የምስክር ወቀረቱን ትክክለኛነት ከማረጋገጥ ባለፈ ስለ ጋብቻ መኖር አለመኖር እና

www.abyssinialaw.com

በጋብቻ ውጤት ላይ ሁሉ እንድምታ ያለው ሌሎችን ሕጎች የሚነካ የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ይመለከታሉ፡፡ በአንፃሩ የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ የሚቀርብ የተቃውሞ አቤቱታ የማስረጃውን ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ከማረጋገጥ ያለፈ እንድምታ የለውም፡፡

በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሚሰጠው ትርጉም አስገዳጅነት የሚኖረው ተመሳሳይ የሕግ ክርክር በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ ድንጋጌ እና ከአስገዳጅ ውሳኔዎች ፅንስ ሃሳብ መረዳት የሚቻል ሲሆን በሰ/መ/ቁ. 75560 በተሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበው የሕግ ክርክር በእጃችን ካለው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተው በስር ፍ/ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መረዳት እንደሚቻለው ኑዛዜው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 የተመለከተውን ፎርም ተከትሎ የተደረገ ባለመሆኑ አስቀድሞ የተሰጠው የኑዛዜ የወራሽነት ምስክር ወረቀት በመሻሩ የተፈፀሙ የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 1038/2005 ግንቦት 28/2006 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የአ/አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22371 ሐምሌ 22 ቀን 2006 ዓ.ም እና የአ/አበባ ከተማ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 22404 ነሐሴ 8/2006 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 92991

ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ተፈራ ተሰማ አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የአርሲ ዞን አስተደደር ጽ/ቤት አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንቨስትመንት ውልን መሠረት አድርጐ ለአመልካች ተሠጥቶ የነበረ የገጠር መሬትን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ ውሉን አፍርሶ መሬቱ እንዲለቀቅ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ለክሱ ምክንያት በማድረግ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በተጠሪ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩ የኢንቨስትመንት ጉዳዩችን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የተቋቋመው የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስልጣን መሆኑን በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶችም ውሳኔው ጉድለት የለበትም እንዲሁም የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት አሰናብተዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በሊዝ የወሰደውን መሬት በማልማት የተለያዩ አትክልት አይነቶች እያመረተ መሆኑን በሚከራከርበት ሁኔታና የአርሲ ዞን አስተዳደር የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ከአዋጅ ውጭ መሬቱን የነጠቀው መሆኑን እየተከራከረ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በዳኝነት አካል የሚታዮ አይደለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ የማድረጋቸው አግባብነት የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር እንደገና ለመወሰን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 115/1998 አንፃር ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፅሑፍ አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

በበኩላቸን ቅሬታ ያነሳውን ውሳኔ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው ጉዳዩ በፍርድ ሊታይ የሚችል መሆን አለመሆኑ እና የሥር ፍ/ቤት የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ ህጉን የተከተለ መሆኑን መመልከት ይጠይቃል፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37/1/ ማንኛውንም ሰው በፍ/ቤት ወይም የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል ጉዳዮን አቅርቦ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 4 ሥር እንደተመለከተውም ፍርድ ቤቶች በሌላ ህግ በግልፅ ለሌላ አካል ከተሰጡ ጉዳዮች ውጭ አከራክሮ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው ስለሆነም ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው በማከራከር ውሳኔ መሰጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በግለፅ ህግ ለሌላ አካል እስካልተወጣ ድረስ ነው፡፡ በህግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቋጩ በተባሉት ጉዳዩች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኛት የስረ ነገር ሥልጣን ስለሌለው በህጉ መሠረት ሥልጣን ለተሰጠው የአስተዳደር አካል ቀርቦ በየደረጀው አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥበትን ጉዳይ ፍ/ቤት አስተናግዶ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም፡፡

በተያዘው ጉዳይ የኢንቨስትመንት ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን በሚመልከት በኮሚሽኑና በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ ድርሻ ባላቸው አካላት የሚወሰኑትን ጉዳዩች አስመልክቶ በሚቀርቡ ይግባኞች ላይ ውሳኔ የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ቦርዱ ስለመሆኑ እና ብርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደርን እንደገና ለመወሰን የመጣውን አዋጅ ቁጥር 115/1998 ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 138/2000 አንቀጽ 6/5/ ይደነግጋል፡፡ የተሻሻለው አዋጅ አንቀጽ 9/4/ ላይ እንደተመለከተውም ካሳ አነሠኝ ወይም ካሳ ተከሰከስኩ ወይም መሠረታዊ የህግ ሥህተት ተፈፀመብኝ በሚሉ ክርክሮች ላይ ካልሆነ በቀር በኢንቨስትመንት የሚቀርቡ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ይግባኞች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሠጠው ቦርዱ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የቀጥታ ክስ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣንን አስመልክቶ የቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/2/ሀ/ እና 245/2/ መሠረት ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት መወሰኑ እና ይግባኝ መባሉም ሆነ የሰበር ችሎቱ አቤቱታውን በመሰረዛቸው የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩን ወስነናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1ኛ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38932 ህዳር 14/2005 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 152805 ታህሳስ 23/2005 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.158804 ሰኔ 18/2005 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2ኛ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 107805

ጥቅምት 04 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- ጄዳው አማካሪ አርክተክቶችና መሐንዲሶች ባለቤት አቶ ዳንኤል አሰፋ ጠበቃ

አለሙ ገበየሁ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ. የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ነገረ ፈጅ አቶ ፋሲል ተሰማ - ቀረቡ

2ኛ. የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በአስተዳደር አካል የተወሰነ ጉዳይ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችልበትን የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓትና ቅሬታውን ተቀብሎ የማየትና የመወሰን ሥልጣን ያለው በየትኛው ደረጃ የተዋቀረው ፍ/ቤት ነው? የሚለውን አስመልክቶ ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት ጉዳይና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ ለይቶ ለመወሰን በሚል የቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀጥታ ያቀረበው ክስ ሲሆን የክሱም ይዘት ተከሳሹ ለብሔራዊ ስታድየም ግንባታ የሚሆን የዲዛይን ሥራ ፈልጎ ባወጣው የጨረታ ውድድር መሠረት ተወዳዳሪ አሸናፊ ሆኛለሁ በጨረታ ሰነዱ (በዝክር ተግባሩ) መሠረት ሥራው ለ2ኛው ዕጩ ተወዳዳሪ ሊሰጥ የሚችለው አሸናፊው በእርሱ ምክንያት ሥራውን ለማከናወን አለመቻሉ የተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ መሆኑ ተገልፆ እያለ ተከሳሹ በህገ-ወጥ መንገድ ጨረታ እንደገና እንዲደረግ የሚያስችል ተግባር በሚከናወን በሁለተኛ ደረጃ ለተሰየመው ተወዳዳሪ ሰጥቶ በዚሁ መሠረት እያከናወነ ስለሚገኝ ይህንኑ ተግባሩን አቁሞ በአሸናፊነቴ ቴክኒካል ፕሮፖዛል እንዲቀርብ እና የቴክኒካል ፕሮፖዛል ድርድር እንዲያደርግ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ተከሳሽ የነበረውም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ በጨረታው የአሸናፊነት ደረጃ አልደረሰም የሚልበትን ዝርዝር የክርክር ነጥብ በመጥቀስ በውድድሩ ሂደት ከሳሽ ለዲዛይን ሥራው ብቁ የሚያደርገውን መስፈርት አላሟላም፤

እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 75(1) መሠረት የመንግሥት ግዥን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች ሥልጣን ባለው የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ ቀርበው እንዲታዩ በማድረግ ሥልጣኑን የቦርዱ እንጂ የፍ/ቤቱ አይደለም ስለሆነም ክሱ ሊዘጋ ይገባል የሚለውንም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር አቅርቧል፡፡

ከሳሽም ጉዳዩን ለዚሁ ቦርድ አቅርቦ ማስወሰኑን ይህ ቦርድ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ ነው ተብሎ በአዋጅ አልተደነገገም ይልቁንም አዋጁን ተከትሎ በወጣው መመሪያ አንቀደጽ 49 (1) መሠረት በቦርዱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው አቤቱታውን አግባብ ባለው ፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚቻል ስለተደነገገ ፍ/ቤቱ የቀረበለት ክስ ተቀብሎ ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ በቀጥታ ተቀብሎ በማስተናገድ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በሚመለከት አግባብነት ያለወን የአዋጁንና የመመሪያውን ድንጋጌዎች በመጥቀስ የጉዳዩ አቀራረብ ሥርዓቱን ጠብቆ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት የቀረበ ነው የሚል ዳኝነት የሰጠበት ሲሆን፤

ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ጉዳዩ በይግባኝ ደረጃ የይግባኙን ጉዳዩ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ከማቅረብ በቀር የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን የሚያስችል የህግ የመነጨ ሥልጣን የለውም ሲል ሽሮ ወስኗል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይግባኝ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በየደረጃው የተሰጡትን ውሳኔዎች ተመልክቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆኑን አትቶ በመወሰን የአሁን አመልካችን አሰናብቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ትርጉም የሚያስፈልገው ሆኖ ከተያዘው አከራካሪ ነጥብ አንፃር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ግራ ቀኙ የተከራከሩበትን ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 649 /2001 አንቀጽ 75 (1) መሠረት አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል አይደለም በሚል ያቀረበው ክርክር

www.abyssinialaw.com

ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በሠጠው መመሪያ አንቀጽ 49 (1) ድንጋጌ ሥር በግልፅ እንደተመለከተው ይኸው ቅሬታ ሰሚ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ያለው ወገን አግባብ ላለው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ የሚቻል በመሆኑ ጉዳዩ በማናቸውም ምክንያት ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል አይደለም የሚለው ክርክሩ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

አከራካሪ ሆኖ የተገኘው በዚሁ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን "አግባብ ባለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ ተብሎ ከተደነገገው ይህ አግባብ ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው? የመጀመሪያ ደረጃ ክስን በጉዳዩ ዓይነት ወይም በገንዘቡ መጠን መሠረት ተቀብሎ ጉዳዩን በቀጥታ የክስ ደረጃ የሚያየው ፍ/ቤት ወይስ የቦርዱን ውሳኔ አግባብነት እንደገና ተመልክቶና ክስ በይግባኝ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት? የሚለው ነው፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 79 የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው በሚል የተደነገገውን በዚሁ ህገ-መንግስት የፍ/ቤቶችን የሥልጣን ወሰን ለሚያመለክተው ከአንቀጽ 37 ጋር አጣቅሶ ማየት እንደሚቻለው ማንኛውም ጉዳይ ያለገደብ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ሊታይ የማይችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይልቁንም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 የተቀመጠው የሥልጣን ክፍፍል ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል እና ጉዳዩንም አይቶ ለመወሰን ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጭ በሌላ የዳኝነት ሰጭ አካል ያልተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህንኑ በፍርድ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ ለማየትና ለመወሰን ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው (exclusive Jurisdiction jurisdiction ) ያላቸው ፍ/ቤቶች መሆናቸውን ለማስገንዘብ ሲባል በአንቀጽ 79 መደንገጉን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም መደበኛ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ በፍርድ ሊያልቅ የሚችል መሆኑን በማረጋገጥ ላይ ብቻ ላይወሰኑ በህገ- መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ይኸው ጉዳይ ከመደበኛ ፍ/ቤት ውጭ ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ቀርቦ የሚታይ መሆኑንና አለመሆኑን በቀጥታ የመመርመር ግዴታ አለባቸው፡፡

ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት በፍሬ ነገር ደረጃ እንደተረጋገጠውና ግራ ቀኙም እንደተማመነበት ሁለቱም ወገኖች ያለያያቸው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 75(1) መሠረት ጉዳዩ ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ከመታየቱ በፊት በመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ መቅረብ እንዳለበትና በዚሁ የቅሬታ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማግኘት አለበት በዚህም መሠረት ጉዳዩ በዚሁ አካል ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ነው በዚህም አኳኃን በዚሁ የአስተዳደር አካልም (ከፊል የዳኝነት ሰጭ አካል) ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ሆኖ የሚቀር ሳይሆን በውሳኔው ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን አግባብ ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ

www.abyssinialaw.com

አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ አንቀጽ 49(1) ተደንግጓል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 75(1) በህገ-መንግስት አንቀጽ 37 እንደተደነገገው ይህንኑ ጉዳይ በቀዳሚ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን ያለውን የዳኝነት አካል (ከፊል የዳኝነት አካል) ለይቶ ካስቀመጠ በኃላ እንደገና ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ለማቅረብ የጉዳዩን አሰማምሮ አወሳሰን በሚመለከት በአስተዳደራዊ ክፍል የዳኝነት ሰጭ አካል እና በመደበኛ ፍ/ቤት መካከል ያለውን ቁርኝት በሚመለከት ይህንኑ በአዋጅ አንቀጽ 75(1) የተቀመጠውን ድንጋጌ ለማስፈፀም በሠጠው መሠረት አንቀጽ 49(1) በግልፅ ተመልክቷል፡፡ እንግዲህ በከፊል የዳኝነት ሰጭው አካልና በመደበኛው ፍ/ቤት መካከል ያለውን ቁርኝነት በተገለፀበት መመሪያ አንቀጽ 49(1) "በቦርዱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው አግባብ ላለው ፍ/ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡" በሚል ከተገለፀው ቅሬታው አስቀድሞ በተሰጡ የቦርድ ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ከመሆኑ፤ ቅሬታ የሚለውም ቀጥተኛ ትርጉም በአንድ አካል በተሰጠ ውሳኔ ላይ ያልተስማማ ወገን አለመስማማቱን የሚገልፁበት ቃል መሆኑን በዚህም ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ቅጂ "Review of complaint by the coyrt" በሚል ከተገለጸው "Review" የሚለው አስቀድሞ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ተመርኩዞ በዚሁ ውሳኔ ላይ ቅር ተሰኝቶ ከቀረበው ቅሬታ ጋር በማዛመድ ጉዳዩን እንደገና በዳኝነት ሰጭ አካል የሚታይ መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ በህገ -መንግስቱ አንቀጽ 37 ሆነ በአዋጅ አንቀጽ 75(1) የመደበኛ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ወሰን ካስቀመጠ በኃላ በማስፈፀሚያው መመሪያ አንቀጽ 49(1) የተቀመጠው ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ጋር ያለው ቁርኝት መገለጫው በይግባኝ ሥርዓቱ አማካኝነት ውሳኔውን በይግባኝ ሰሚነቱ ሥልጣን መሠረት በቦርዱ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግና መመሪያ አንፃር በማየት መመርመር እንዲቻል እንጂ ጉዳዩን እንደ አዲስ በመቀጠር ተከራካሪ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ክርክር በአዲስ መልክ የሚያከናውኑበትን ሥርዓት የሚመለክት አይደለም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አግባብ ያለው ፍ/ቤት ጉዳዩን ከህግ አንፃር ብቻ መመልከት እንዲቻል ሆኖ አልተቀረፀም ይባል እንጂ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠበትና በዚህም ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል በመመሪያ የተፈቀደ በመሆኑ ጉዳዩን በክለሳ "Review" መልክ የሚያየው ፍ/ቤት የህግም ጥያቄ ሁሉ መመልከት የሚችል መሆኑ በውስጠ ታዋቂነት ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባ ነበር እንጂ ጉዳዩ በቀጥታ ክስ አማካኝነት ሊቀርብ ይገባል የሚለው ወደሚለው በቂ የውሳኔ መነሻ ትችትና ሊያደገውም አይገባም ነበር፡፡

በሀገራችን የህግ ሥርዓቱ በልዩ ልዩ ህጎች እንደተመለከተው በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37 በአስተዳደርና፣ በከፊል የዳኝነት ሰጭ አካል እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤቱ አስቀድመው ሊታዩ የማይችሉን ጉዳዮች ከተመለከቱ በኃላ ፍትህ የማግኘት መብትን ይበልጥ ለማረጋገጥ ሲባል ከፍ/ቤቱ ጋር ቁርኝት ሊኖራቸው እንደሚገባና ቁርኝቱም ለይግባኝ ሥርዓቱ አማካኝነት ጉዳዩ

www.abyssinialaw.com

በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አማካኝነት እንዲታዩ በማድረግ የተደነገጉ እንጂ እንደገና እንደ አዲስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ (of first instance ) አቅርቦ አዲስ ክርክርን በሚጋብዝ ደረጃ የተቀረፀ አይደለም፡፡

በዚሁ ሁሉ ምክንያት በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ ሥልጣን ላይ መ/ቁ 103961 ህዳር 17/2007 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ በትዕዛዝ የሰጠው የመጨረሻ ዳኝነት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ ቅሬታ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን በይግባኝ አቤቱታ አቀራረብ ደንብን ሥርዓት መሠረት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው አግባብ ላለው ፍ/ቤት ከሚያቀርብ በቀር በቀጥታ ክስ አቀራረብ ሥርዓት የጉዳዩን ዓይነትም ሆነ የገንዘብ መጠኑን መሠረት በማድረግ ጉዳዮች በቀጥታ ደረጃ በሚታዩበት ሥርዓተ መሠረት ማቅረቡ ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ደረጃ ግራቀኙ ባደረጉት ክርክር ሳቢያ ለወጣው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.117390

ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ አለማየሁ መኮንን ጠበቃ ሞላ ዘገየ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የምስራቅ አፍሪካ የበርሃ አንበጣ መከላከያ ድርጅት ጠበቃ አድምጠው በለጠ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ላይ ያቀረብኩትን ክስ የማየትና አጣርተው የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ገልፆ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች የተጠሪ ሰራተኛ የነበሩ መሆናቸውን ገልፀው ተከሳሽ ሊከፍለኝ ይገባል የሚሏቸውን ክፍያዎች ዘርዝረው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ አለም አቀፍ ድርጅት መሆኑን ገልፆ፣ የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በኢትዮጵያ አቆጣጠር ግንቦት 30 ቀን 1969 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ሰኔ 7 ቀን 1977 ዓ.ም በተዋዋለው ውል መሰረት በፍትሐብሔር ጉዳይ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ያለመክሰስ መብት ያለኝ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪ ዋና መስሪያ ቤት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያደረገው ስምምነት ያለመሆኑንና ስምምነቱም እስካሁን ድረስ የፀናና ያልተሻረ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በፅሁፍ ያረጋገጠለት መሆኑን ገልፆ፣ ስምምነቱ በይዘቱ የኢትዮጵያ መንግስት በድርጅቱ ላይ ክስ እንዳያቀርብ የሚገደብ

www.abyssinialaw.com

እንጅ ዜጎች በድርጅቱ ላይ ክስ እንዳያቀርቡ የሚከለክል አይደለም በማለት አመልካች በክሱ የጠቀሰውን ገንዘብ ተጠሪ ክዶ የቀረበው ክርክር ስለሌለ እንዳመነ ይቆጠራል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ስምምነቱ በተጠሪ /ይግባኝ ባይ/ ላይ የማቀረብ የፍትሐብሔር ክስ የኢትዮጵያ መንግስት የመዳኘት ስልጣን የሌለው መሆኑን የሚገልፁ ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን የለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሯታል፡፡

3. አመልካች ስምምነቱ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብት በማያጣብብ ሁኔታ መተርጎም ይገባዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አገሪቱ የገባችውን አለም አቀፍ ግዴታና ስምምነት መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት ከተጠሪ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትን ውል አለን፡፡ አሰሪው በስር ውሉ መሰረት ለመወጣት የሚገባውን ግዴታ ያልተወጣና መክፈል የሚገባውን ክፍያ ያልከፈለኝ ስለሆነ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ አለም አቀፍ ድርጅት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ባሉ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ለማስተዳደር የወጣ ልዩ የሕግ ክፍል ቢሆንም ይኸ አዋጅ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ልዩ ሁኔታዎች በአዋጅ ተደንግጓል፡፡ አዋጅ ተፈፃሚ የማይሆንበት ልዩ ሁኔታ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ስራቸውን የሚያከናውኑ አለማቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያዊን ጋር በሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት ላየ ተፈፃሚ እንዳይሆን በአለም አቀፍ ስምምነት የተወሰነ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በአዋጅ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3/ሀ/ ተደንግጓል፡፡ ይኸ ድንጋጌ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረገና ፀንተው የቆዩ አለም አቀፍ ስምምነቶችንም የሚያካትት ድንጋጌ ነው፡፡
5. የኢትዮጵያ መንግስትና የተጠሪ ዋና መሰሪያ ቤት ያደረጉት ስምምነት አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1 በተፃፈበት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ቃል በቃል ሲነበብ “The organization shall, enjoy immunity from the criminal junsdiction of the government. If shall also enjoy immunity from its civil and administrative Jurisdiction except in so far as the counsel of the organization has unvalued the immunity”

www.abyssinialaw.com

የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይኽ ስምምነት እስካሁን ድረስ የፀናና ሕጋዊ ውጤት ያለው ስምምነት መሆኑን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለስር ፍ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡

6. ይኽ የስምምነቱ ሃይለ ቃል፣ የኢትዮጵያ መንግስት ተጠሪ ከሚቀጥራቸው ሰራተኞች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚወስን ሕግ የማውጣት፣ በዳኝነት አይቶ የመወሰንና ውሳኔውን በፍርድ ቤትም ሆነ በአስተዳደራዊ መንገድ የማስፈፀም ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ ከተጠሪ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ያላቸው ኢትዮጵያውያንም ሆነ የሌሎች አገሮች ዜጎች መብታቸውንና ጥቅማቸውን በተጠሪ መተዳደሪያ ደንብና አግባብነት ባላቸው አለማቀፍ ስምምነቶች አለም አቀፍ ልምዶችና ሕግጋት መሰረት ጉዳዩን አይተው ውሳኔ ለሚሰጡ አካላት በማቅረብ እንዲወሰንላቸው ከሚጠይቁ ውጭ በኢትዮጵያ ሕግና መሰረት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ የማይችሉና የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም የዚህ አይነት ጉዳይ በዳኝነት አይተው የመወሰን ስልጣን የሌላቸው መሆኑን ግልፅ የሚያደርግ ነው፡፡ የስምምነቱ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2 ይዘትም ከላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ መልዕክት የሚያጠናክር ይዘት ያለው ነው፡፡

7. የአንድ አለም አቀፍ ድርጅት በግዛት ክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ወይም ዋና ፅ/ቤት እንዲከፍት የፈቀደች ወይም አለም አቀፍ ድርጅቱ በግዛት ክልል እያንቀሳቀሰ የተቋቋመበትን መሰረታዊ ዓላማና ተግባር እንዲፈፅም የፈቀደች አገር፣ ከአለም አቀፍ ድርጅቱ ጋር ያደረገችውን ስምምነት የማክበር ግዴታ ያለበት መሆኑን ከቬና የአለም አቀፍ ስምምነቶች ሕግ እና በልምድ ከዳበረው የግል ማዕቀፍ ሕግ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም መሆኑ አገሪቱ ለተጠሪ ድርጅት የሰጠችው በፍትሐብሔር ያለመከሰስ ጥበቃ እስካሁን ድረስ የፀናና አገሪቱ ልታከብረው የሚገባው ቃል ኪዳን በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን የሌለ መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረበውን ክስ አይቶ የመወሰን ስልጣን የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 104858

ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ካሣ - ጠበቃ እንዳልካቸው ይሳቅ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር
2ኛ. ቦሌ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር } አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት ከከተማ ቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ምትክ ቦታን በተመለከተ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የለኝም በማለት ያሳለፈውን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ነሀሴ 27/2006 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተመርምሮ የአዲስ አበባ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ከአዋጅ ቁጥር 721/2003 አንቀጽ 29 እና 30 ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ መሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸውና መልስ ለመስጠትም ቀጠሮ እንዲለወጥላቸው ጠይቀው ነገር ግን መልስ ስላላቀረቡ በፅሑፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ መዝገቡ ለምርምራ ተቀጥሯል፡፡ በበኩላችን የከተማው ሰበር ችሎት ያሳለፈውን ትዕዛዝ አመልካች ካቀረቡት ቅሬታ እና ተገቢነት ካላቸው ህጎች ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አስተዳደር ውስጥ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በ200 ካ.ሜ ቦታ ላይ ቤት ገንብተው እየኖሩ ከተጠሪዎች ቦታው ለልማት ይፈለጋል በሚል እንዲለቁ ማስጠንቀቂያ በፅሑፍ ስለተሠጣቸው የቤት ካሣ እና ምትክ ቦታ እንዲሠጣቸው ጠይቀው አስተዳደሩ በህግ ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎብኛል በሚል ይግባኙን ለመስማት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሠን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 455/1997፣ ስለ ካሣው አወሳሰን ከወጣው የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/1999 እንዲሁም አዋጅና ደንቡን ለማስፈፀም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ከወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2002 አንፃር በመመርመር በህጎቹ እንዲቀርብ የሚጠበቀው የንብረት ካሣ እና ምትክ ቦታ ለማግኘት የሚያበቁ ማስረጃዎ አልቀረቡም ስለሆነም ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የምትክ ቦታ ጥያቄውን በተመለከተ የጉባኤው ውሳኔ የመጨረሻ ነው በማለት የሰበር አቤቱታ ለከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሚኖረው የአ/አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ነው፣ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም ሥልጣን ያለው የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ነው በመሆኑም ጉዳዩ በከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችል ነው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

እንደመረመርነው የከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ምትክ ቦታን በሚመለከት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በሰበር አይቶ ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው የህግ ጭብጥ ውሳኔ የሚሻ ነው፡፡

የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(3) መሠረት በካሣ ክርክር ላይ ካልሆነ በቀር ምትክ ቦታን ጨምሮ በሌሎች  በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ላይ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡ በሌላ በኩል በካሳው ላይ የከተማው  ይግባኝ  ሰሚ ፍ/ቤት  ይግባኝ  ሊቀርብ እንደሚችል በአንቀጽ 29 (4) ሥር ተመልክቷል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በከተማው ቻርተር  አዋጅ  ቁጥር 361/95 አንቀጽ 43(5) እና አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 29(6) ድንጋጌዎች መሠረት የመጨረሻ በመሆኑ በዚህ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በሰበር ስርዓት ለከተማው ፍ/ቤት የሰበር ችሎት ስለመሆኑ በቻርተሩ አንቀጽ 42(2) ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

የከተማ ቦታ ማስለቀቅ እና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም በቻርተሩ አንቀጽ 40 ከተዘረዘሩ በህግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት የሚመደብ ነው፡፡

በመሆኑም ጉባኤው ምትክ ቦታን በተመለከተ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑና ጉባኤውም በህግ የመዳኘት ስልጣን ተሰጥቶት የተቋቋመ የአስተዳደሩ አካል መሆኑ እየታወቀ በዚህ ውሳኔ ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የከተማው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የመመለስ ሥልጣን የለውም ተብሎ የተሰጠው ትዕዛዝ ህጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ. 104857 ህዳር 24/2008 ዓ.ም በዋለ ችሎት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በምትክ ቦታ ይሰጠኝ ጥያቄ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ የሠበር አቤቱታ ለከተማው ፍ/ቤት ሳይቀርብ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት የህግ አግባብ እንደሌለም ተወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔም በተያዘው ጉዳይ በተመሳሳይ ተፈፃሚ ነው፡፡

በመሆኑም የከተማው ሰበር ችሎት ያሳለፈው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1ኛ. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22374 ነሀሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን ያለው በመሆኑ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሰናል ይፃፍ፡፡

3ኛ. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.112575

30/06/2008 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሠለ

አመልካች፡- አቶ አፈወርቅ መኩሪያ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ማዳሊና ፍራንሲኔቲ ጠበቃ ኤልያና ጥላሁን

መዝገቡን መርምረን ተከታዮን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዮ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል ከዚህ ፍ/ቤት የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝ አመልካች ያቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ይዘት የመቃ/ተጠሪ/የአሁኗ ተጠሪ/ የሟች ወ/ሮ ፈንታዮ መተኪያ ልጅ ሳይሆኑ በተፈጥሮ ሟች እንደወለዱዋቸው ልጅ ነኝ ብለው የወሰድት የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት የመጀ/ደ/መቃወሚያ ፍ/ቤቱ የልጅነትን ክርክር ጭብጥ ይዞ ለማየት ስልጣን የለውም፣የመቃ/አመልካች የሟች ልጅ /ተወላጅ/ ሳይሆኑ ያቀረቡት መቃወሚያ አቤቱታ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ፣የመቃ/አመልካች ወላጅ እናት ወ/ሮ አፀደ ንዋይ የሞቱት ከ 30 ዓመት በፊት ስለሆነ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መቃወሚያ እና በአማራጭም መልስ ማቅረባቸው ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመልክቷል፡፡

ፍ/ቤቱ የቀረበውን የመጀመሪያ መቃወሚያ መርምሮ የመቃ/አመልካች እንደሚሉት እና በመቃ/ተጠሪም የግራ ቀኙን የልጅነት ክርክርን ፍ/ቤቱ ጭብጥ ይዞ ሲመረምረው በተገቢው ፍ/ቤት አጠናቀው እና ማስረጃ ይዘው እስከ ቀረቡ የወራሽነት ክርክሩ መዝገብ ለጊዜው ተዘግቶ ይቆይ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ሌሎች መቃወሚያዎች ላይ መቃወሚያዎቹን ባለመቀበል በብይን አልፋል፡፡ ተጠሪ በዚህ ብይን ላይ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት

www.abyssinialaw.com

አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሠረት ይግባኙ የተሰረዘ ሲሆን የሰበር አበቱታ ለይ/ሰሚው ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ብይን በመሻር አመልካች /የስር የመቃ/ተጠሪ/ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፍቻ ልጅ መሆን አለመሆኑን የቀረበውን ማስረጃ እና እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ በማስቀረብ መርምሮ የመሰለውን እንዲወሰን ለስር ፍ/ቤት በመመለስ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ቅሬታቸውን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን አለመሆናቸውን የማጣራት የሥር ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው ሲል ጉዳዮ ተጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.343/1/ መሠረት የመለሰበትን አግባብ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁ.361/1996 አንቀፅ 41 መሠረት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ ከዚህ በላይ አጠር ተደርጐ የተመዘገበዉ ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ከስር ፍ/ቤት ጀምረው የሚከራከሩት ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ አይደለም በማለት ሳይሆን ተጠሪ ከሚች በተፈጥሮ የተወለዱ ልጅ ሳይሆኑ የተፈጥሮ ልጅነኝ ብለው የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው ተጠሪ በበኩላቸው የሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ መሆናቸውንና ለዚህም ማስረጃ ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ የተመለተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ተጠሪ ከሚች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ በተፈጥሮ የተወለዱ መሆኑን ገልፀው ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት የወራሽነት ማስረጃ ወስደዋል ወይስ አልወለዱም የሚለውን ጭብጥ ለማጣራት ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ወስደዋል የተባለበትን መዝገብ አሰቀርቦ አልተመለከተምደ ግራ ቀኙንም በዚህ ነጥብ ላይ አላከራከረም ፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በአንቀጽ 182 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቀው ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ የሚቆጠር መሆኑን ደንግጓል፡፡ የጉዲፈቻ ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል የሚደረግ መሆኑ በዚሁ ሕግ አንቀፅ 190 የተመለከተ ሲሆን የጉዲፈቻ ስምምነትን አስመልክቶ

www.abyssinialaw.com

ስለ ፍ/ቤት ስልጣን በአንቀጽ 194 ተደንግጓል፡፡ የጉዲፈቻ ስምምነትን በተመለከተ የፍ/ቤት ሚና ስምመነቱን ከማፅደቁ በፊት በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 2 እስከ 4 የተመለከቱ መመዘኛዎችን የማጣራትና የማረጋገጥ መሆኑን ከድንጋጌው መረዳት ይቻላል፡፡ የጉዲፈቻ ስምምነቱ የሚሰረዝበትን የሕግ አግባብ በተመለከተም በአንቀፅ 196 ተመልክቷል ፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ አጥብቀው የሚከራከሩት የሟች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያላቸው መሆኑ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.145 መሠት በፍ/ቤቱ ትህዛዙ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት እና እንዲቀርብ የጠየቁ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጐ የሟች ወ/ሮ ፋንታዬ መተኪያ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን አለመሆናቸውን ማስረጃን በመመርመር ወራሽ ናቸው ወይም ወራሽ አይደሉም ብሎ ውሣኔ መስጠት፣የተፈጥሮ ልጅነት ከሚረጋገጥበት በህጉ ከተመለከተው ስርዓት የተለየ ነው ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣንን የደነገገው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ.361/1995 አንቀጽ 41/ሸ/ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታን ለማየት የዳኝነት ሥለጣን ያላቸው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የቤተሰብ ሕግ በተመለከተው መሠረት የተደረገ የጉዲፈቻ ስምምነት ማስረጃን ተመልክቶ ወራሽነት ማስረጃን በስተት የአ/ከተማ ፍ/ቤት ስልጣን ሆኖ እያለ ክርክሩ የጀመረበት የአ.አ.ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የክርክር ይዘት በውል ባለማጤን የልጅነት ክርክርን ለማየት ስልጣን የለኝም በተገቢው ፍ/ቤት ተጣርቶ ይቅረብ ብሎ የሰጠው ብይን ተገቢ አለመሆኑን እና የተጠሪን የጉዲፈቻ ልጅ ማስረጃን ተመልክቶ የመሰለውን እንዲወሰን የአ.አ.ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአ.አ. ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.22960 በቀን 30/07/2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348/1/ መሠረት ፀንቷል ፡፡
2. በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ላደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡
3. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

# ንብረት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.ጥር 108335
የካቲት 4 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

አመልካቾች፡-

1. አቶ ዓለሙ ስሜ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ታደሱ ስሜ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ብዙነሽ ስሜ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ፀዳሉ ስሜ - ቀረቡ
3. አቶ ተሾመ ሽሜ
4. ወ/ሮ ሰላማዊት ስሜ } ወኪል 1ኛ ተጠሪ ቀረቡ
5. ወ/ሮ ወርቅነሽ ስሜ
6. አቶ ብርሃኑ ስሜ } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ የተነሳ የውርስ ይገባኛል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሾች የነበሩት የአሁኖቹ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡የአሁኗ 2ኛ አመልካች በዋናው ክርክር ጊዜ በጉዳዩ በጣልቃ ገብነት የተከራከሩ ሲሆኑ የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በጉዳዩ ላይ የወረዳ ፍርድ ቤቱ በ27/07/2006 ዓ.ም. ውሳኔ ከሰጠ በኃላ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት ወደ ጉዳዩ የገቡ ናቸው፡፡

ፍርድ ቤቱ በከሳሾች እና በተከሳሽ፣እንደሁም በጣልቃ ገቧ የአሁኗ 2ኛ አመልካች መካከል የነበረውን ክርክር መርምሮ ክርክር ያስነሳውን የእርሻ መሬት፣ እንዲሁም የእንስሳት ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች እና ተከሳሽ እኩል ይካፈሉ በማለት በመዝገብ ቁጥር 12083 በ27/07/2006 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ከዚህ በኃላ የእርሻ ይዞታው እና የከብቶቹ ግምት በውርስ

www.abyssinialaw.com

ሊተላለፍ የሚገባው ለከሳሾች እና ለተከሳሹ ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር በመሆኑ ውሳኔው ሊሻሻል ይገባል በማለት የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት በ24/10/2006 ዓ.ም. የተጻፈ የመቃወም አቤቱታ በማቅረባቸው መዝገቡ ተንቀሳቅሶ የስር ከሳሾች ውሳኔው መቃወሚያ አቅራቢዎቹ በጠየቁት አግባብ ቢሻሻል ተቃውሞ እንደሌላቸው በመግለጽ መልስ የሰጡ ሲሆን የስር ተከሳሽ በበኩላቸው በሰጡት መልስ መቃወሚያ አቅራቢዎቹ ከሟች ስሜ ደገፋ የሚወለዱ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ እና በደመወዝ የሚተዳደሩ በመሆናቸው እና የሟች የቤተሰብ አባል ከሳሽ ብቻ በመሆናቸው ጥያቄአቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርመሮ መቃወሚ አቅራቢዎቹ የሟች ስሜ ደገፋ ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው አልተካደም በማለት የቀድሞውን ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360 (2) መሰረት አሻሽሎ ክርክር ያስነሳውን የእርሻ መሬት፣እንዲሁም የእንስሳት ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት በ09/11/2006 ዓ.ም.ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበለትን አቤቱታ ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን ለዚህ ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ እና በደመወዝ የሚተዳደሩ በመሆናቸው የገጠር የእርሻ ይዞታን የመውረስ መብት የላቸውም በማለት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. 2ኛ ተጠሪ በዚህ መዝገብ በአመልካችነት የመከራከር መብት አላቸው ወይስ የላቸውም?
2. 1ኛ አመልካች በ27/07/2006 ዓ.ም. በወረዳው ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ መዝገብ ያቀረቡት የክርክር ነጥብ በዚህ መዝገብ ሊስተናገድ የሚችል ነው ወይስ አይደለም?

www.abyssinialaw.com

3. የቀድሞውን ውሳኔ በማሻሻል በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ የተሰጠው ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ፍሬ ነገሮች በአግባቡ እንዲጣሩ ከተደረገ በኃላ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ 2ኛ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት የክርክሩ ተካፋይ የነበሩት የመቃወም አቤቱታ ከመቅረቡ በፊት በነበረው ሂደት ነው፡፡የመቃወም አቤቱታው ከቀረበ በኃላ 2ኛ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የነበሩ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የመቃወም አቤቱታው ከመቅረቡ በፊት ውሳኔ የተሰጠው በ27/07/2006 ዓ.ም. ሲሆን የመቃወም አቤቱታ ከቀረበ በኃላ ውሳኔ የተሰጠው ደግሞ በ09/11/2006 ዓ.ም. ነው፡፡2ኛ አመልካች በ27/07/2006 ዓ.ም. በተሰጠባቸው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው በውሳኔው ላይ ያላቸውን ይግባኝ እና አቤቱታ ስርዓቱን ጠብቀው ማቅረብ ይችሉ የነበረ ከመሆኑ ውጪ ተካፋይ ባልተደረጉበት ክርክር በ09/11/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እና አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ በዚህ መዝገብ በአመልካችነት የመከራከር መብት አላቸው ማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የመቃወም አቤቱታ ከቀረበ በኃላ በ09/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በመሆኑ 1ኛ አመልካች ይግባኝ እና አቤቱታ ማቅረብ የሚገባቸው ይህንኑ በ09/11/2006 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ከሚሆን በቀር የኃለኛውን ውሳኔ አስታከው የመቃወም አቤቱታ ከመቅረቡ አስቀድሞ በ27/07/2006 ዓ.ም.በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እና አቤቱታ ሊያቀርቡ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡በመሆኑም 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጭምር የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመሆናቸው የእርሻ መሬት የመውረስ መብት የላቸውም፣በ3ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኝ የውርስ ንብረት ጭምር መኖሩን በመጥቀስ ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የታለፈብኝ አላግባብ ነው በማለት 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በዚህ መዝገብ ሊስተናገድ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ 1ኛ አመልካችም ሆኑ ተጠሪዎቹ የሟች ስሜ ደገፋ ልጆች እና ወራሾች መሆናቸው በግራ ቀኙ ያልተካደ ሲሆን የአንድ አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት በውርስ የሚተላለፈው በውርስ ሕግ መሰረት በይዞታው የመጠቀም መብቱን የመውረስ መብት ላለው የቤተሰብ አባል ስለመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 9 (1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅድሚያ የውርስ መብት የሚሰጠው ከመሬቱ በሚያገኙት ገቢ ለሚተዳደሩ ወይም ሌላ መተዳደሪያ ገቢ ለሌላቸው ወራሾች እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 9 (2) ስር

www.abyssinialaw.com

ተመልክቶአል፡፡አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 10 (1) ስር ያለው ድንጋጌም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡ የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ እና በደመወዝ የሚተዳደሩ በመሆናቸው የገጠር የእርሻ ይዞታን የመውረስ ቀዳሚ መብት ያላቸው የሟች ቤተሰብ አባል ሆነው ከእርሻ መሬቱ በሚገኘው ገቢ የሚተዳደሩ የአሁኑ 1ኛ አመልካች መሆናቸውን በመግለጽ የአሁኑ 1ኛ አመልካች መከራከራቸውን እና 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሳይሆኑ የእርሻ መሬቱ የሚገኝበት ቀበሌ ነዋሪዎች መሆናቸውን በመግለጽ የተከራከሩ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን መከራከሪያ ሳይቀበሉ የቀሩት ሁሉም ወራሾች በእርሻ መሬት አወራረስ ላይ እኩል መብት እንዳላቸው በመቁጠር እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በመሆኑም በአንድ በኩል በ1ኛ አመልካች እና በሌላ በኩል ደግሞ በ5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች መካከል የተነሳውን ክርክር በማስረጃ ሳያጣራ ሁሉም ወራሾች በእርሻ መሬት ላይ እኩል መብት እንዳላቸው በመቁጠር መሬቱን እኩል እንዲካፈሉ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡ከእርሻ ይዞታው ውርስ ጋር ተያይዞ በተነሳው ክርክር ከሟች የተላለፉት እንስሳት ውርስ ጉዳይ የሚገዛው ውርስን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት በመሆኑ የእንስሳቱን ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. 2ኛ አመልካች ተከራካሪ ወገን ባልነበሩበት በ09/11/2006 ዓ.ም. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እና አቤቱታ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
2. በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12083 በ09/11/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 47817 በ28/12/2006 ዓ.ም. በፍርድ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 187287 በ09/04/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. የእንስሳቱን ግምት ብር 7,000 (ሰባት ሺህ) ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

4. ክርክር ያስነሳውን የእርሻ ይዞታ ከሳሾች፣ተከሳሽ እና መቃወሚያ አቅራቢዎቹ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
5. የአሁኖቹ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች የመኖሪያ አድራሻ እንደ 1ኛ አመልካች አባባል በአዲስ አበባ ከተማ ነው ወይስ እንደ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች አባባል ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት በሚገኝበት ወረዳ እና ቀበሌ ነው? 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ከደመወዝ በሚገኝ የሚተዳደሩ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚሉትን እና ተያያዥ ነጥቦችን በግራ ቀኙ ማስረጃ፣እንደሁም ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ሁሉ በፍርድ ቤት በትዕዛዝ በሚቀርብ የማጣሪያ ማስረጃ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 9 (2) እና በደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 10 (1) ድንጋጌዎች አነጋገር መሰረት ክርክር የተነሳበትን የእርሻ ይዞታ ውርስ የመካፈል መብት ያላቸው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ለደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ሰለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 110549

የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ደመቀች ንርአ ጠበቃ ኪሮስ አቢዲ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጋለመ ረብሶ ተወካይ አለ ረብሶ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት የሚመለከት ሆኖ በአሁኑ ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በአላማጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከከሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ፡- አዋሳኙ በክስ ማመልከቻቸው የጠቀሱትና በአላማጣ ወረዳ፣ ኩልግዘ ለምለም ጣብያ፣ በጆሃን ጎጥ ውስጥ የሚገኘውንና ስፋቱ 33ሜትር በ50 ሜትር የሆነውን የእርሻ መሬት በሕግ አግባብ ከአያታቸው ከሟች ወ/ሮ ሙሽራ አራርሶ ወርሰው የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡበት መሆኑን፣ ይዞታውን ለአመልካች በኪራይ እያከራዩ የነበሩ መሆኑን፣ ቦታው ወደ አላማጣ ከተማ ሲገባ ግን ተጠሪ የታመሙበትን አጋጣሚ በመጠቀም የጎጆ መውጫ የነበረ ቦታ በማስመሰል አመልካች ይዞታውን በስማቸው እንዲሆን ማድረጋቸውን ዘርዝረው አመልካች ቦታውን እንዲያስረክቡ ወይም የአስር አመት አላባ፤ የመሬቱን ቋሚ ማሻሻያ ብር 126,500.00(አንድ መቶ ሃያ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም በይዞታቸው ስር ያለው በተጠሪ ክስ ውስጥ አዋሳኙ የተጠቀሰው ይዞታ ያለመሆኑን፣ በይዞታቸው ስር ያለው መሬት የሚታረስ ሳይሆን የጎጆ መውጫ ሁኖ ባለቤታች ሟች አቶ አድሃና አስፋው በቀን 10/10/1994 ዓ/ም ከወ/ሮ ሙሽራ ልጆች ከሆኑት ወ/ሮ ቡልቡላ ብርዋን በሽማግሌ ፊት በብር 1500.00 የገዙት መሆኑን፣ ይህ መሬት ታራሽ መሬት ነው፣ ይገባኛል በማለት ወ/ሮ ቡልቡላ ብርዋን በተወካያቸው አቶ መሃመድ ጎሳ በ2000 ዓ/ም ክስ መስርተውባቸው ቦታው ጎጆ መውጫ ነው በኩሉግዘ ለምለም ቀበሌ የመሬት ዳኝነት በ12/5/2000 ዓ/ም የተወሰነ መሆኑንና በፍርድ ያለቀ ጉዳይ መሆኑን፣ ጎጆ መውጫ ሁኖ ባለቤታቸው በ1994

www.abyssinialaw.com

ዓ/ም የገዙት ከመሆኑም በላይ በ2001 ዓ/ም ወደ ስማቸው ዙሮ የሚጠቀሙበትና ቦታው ታራሽ ነው በሚል የአላባ ጥያቄ መቅረቡ ያላግባብ ነው የሚሉ ነጥቦችን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ከሚመለከተው አካል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ያደረገውን ማስረጃ በመመርመር የአሁኑ ተጠሪ በውርስ ያገኙት ታራሽ መሬት መሆኑን፣ክርክሩ በመታየት ላይ ባለበት ጊዜ ግን ይዞታው ወደ አላማጣ ከተማ ስለገባ በስም የተጠሪ ሁኖ እንዲመዘገብ፣ የአንድ አመት አላባ ብር 5238.65 ደግሞ ለተጠሪ እንዲከፈላቸው፣ በአመልካች ባለቤት ስም ያለው ሳይት ፕላንም እንዲሰረዝ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለአላማጣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት እስከ 2005 ዓ/ም ድረስ ከከተማ ውጪ ሁኖ በገጠር መሬት አስተዳደር ቁጥጥር የነበረ ሁኖ አመልካች ከ12 አመታት በላይ ይዘው በቁጥጥራቸው ስር አድርገው ቤት ስርተውና የተለያዩ ተክሎችን ተክለው የሚኖሩበት የነበረ ጎጆ መውጫ በ2001 ዓ/ም ወራሽነት ማስረጃ አውጥቼአለሁ በሚሉ ተጠሪ በ2006 ዓ/ም ክስ ሊመሰርትባቸው አይገባም እንደማይገባ፣ የሽያጭ ውሉም የይርፍረስልኝ ጥያቄ ሳይቀርብበት ክርክር ሊነሳበት የማይገባ መሆኑን እና በክፍሉ ማዘጋጃ ቤት አመልካች የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር ያገኙ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊመክን የማይችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች ለተጠሪ የሚያስረክቡት መሬትና የሚከፍሉት አላባ ግምት የለም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ይዞታው ወደ ከተማ ክልል ከመግባቱ በፊት የሚታረስ የነበረ መሆኑ መረጋገጡን፣ አመልካች ይዞታውን አገኘሁ የሚሉት ደግሞ በሽያጭ በመሆኑና የገጠር እርሻ መሬት የሚሸጥበት ወይም የሚለወጥበት አግባብ በሕግ የተከለከለ ተግባር መሆኑን፣ ከሕግ ውጪ የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ደግሞ በፍርድ ቤት ውሳኔ የማይመክንበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በምክንያት ይዞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ይዞታው በተጠሪ ስም እንዲመዘገብ፣በአድሃና አስፋው ስም የተመዘገበው ሳይት ፕላን ሕገ ወጥ በመሆኑ እንዲሰረዝ፣ አላባውን ግን ያልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፈላቸው የማይገባ መሆኑን ገልጾ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ይዞታው የጎጆ መውጫ ሁኖ በሽያጭ ለአመልካች ባለቤት በ1994 ዓ/ም ተላልፎ ቆይቶ

www.abyssinialaw.com

ይዞታው ወደ አላማጣ ከተማ ክልል ከገባ በኂላም በ2001 ዓ/ም በአመልካች ስም የይዞታ ማረጋገጫ ከአላማጣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ተሰጥቶአቸው ይዞታው ላይ ቤት ሰርተውና የተለያዩ ተክሎችን አልምተው የሚገኙ መሆኑን ዘርዝረው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አከራካሪው ይዞታ ወደ አመልካች የተላለፈው በሽያጭ ውል ነው ተብሎ ሽያጩ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብነትና ተያያዥ ነጥቦችን በጭብጥነት መያዙ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአመልካች ባለቤት የነበሩት ሟች አቶ አድሃና አስፋው 10/10/1994 ዓ/ም ከወ/ሮ ሙሽራ ልጆች ከሆኑት ወ/ሮ ቡልቡላ ብርዋን በሽማግሌ ፊት በብር 1500.00 የገዙት መሆኑና አከራካሪው መሬት ወደ አላማጣ ከተማ አስተዳደር ከመግባቱ በፊት ታራሽ መሬት እንጂ ጎጆ መውጫ ያልነበረ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጧቸው ነጥቦች መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ግዥው ሲደረግ ይዞታው ላይ የጎጆ መውጫ ነው፣ ቤት ተሰርቶና ተክሎችን በመትከል ይዞታውን አልምተን ለብዙ አመታት በመጠቀም ላይ ቆይተን ይዞታ ወደ ከተማ ክልል ገብቶ ከሚመለከት አስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያገኘሁበት ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሕጋዊነት ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ እና ስለጠቅላላ ውል በፍትሓብሔር ሕጋችን የተመለከቱትን የውል አመሰራረት መርሆች ጋር ተዛምዶ መታየት ያለበት መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ውል በሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ወይም እንዲጸና በሕጉ ተለይተው የተቀመጡት ሁኔታዎችን አሟልቶ ሊገኝ ይገባል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም ውሉ ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፣በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ መሆንና የውሉ አጻጻፍ ፎርም በህግ በታዘዘ ጊዜ ይህኑ ልዩ ፎርም አሟልቶ መገኘት የሚሉትን ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ድንጋጌው- ከሀ-ሐ ፊደላት ስር በዝርዝር አስቀምጧቸዋል፡፡ የአንቀጹ ፊደል "ለ" ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ውሉ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንደሚገባው የሚያስገነዝበው ሲሆን በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ፤የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ደግሞ ህገ

www.abyssinialaw.com

ወጥ ውል ( unlawful contract )ይሆናል፡፡ አንድ ውል የተደረገበት መሰረታዊ ጉዳይ (object of contract) በህግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜም ውሉ በህግ ፊት ምንም ዓይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትል (void contract) መሆኑ ይታመናል፡፡
ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪው ይዞታ ወደ አመልካች እጅ ሊገባ የቻለው ሟች ባለቤታቸው አቶ አድሃና አስፋው በ10/10/1994 ዓ/ም አደረጉ በተባለው የገጠር እርሻ መሬት ይዞታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና ህዝብ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የክልሉ ሕገ መንግስትም በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ድንጋጌ አስቀምጦአል፡፡ በሌሎች ዝርዝር ህጎችም ማለትም፡- በአዋጅ ቁጥር 456/97"ም" ቢሆን ባለይዞታ አርሶ አደር የመሬት ይዞታውን ለመሸጥ መብት አልተሰጠውም፡፡ አሁን በስራ ላይ ባለው  የክልሉ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006ም ሆነ በ1994 ዓ/ም ስራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 55/1994  የገጠር መሬትን በሽያጭ ማስተላለፍ በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም በአመልካች ባለቤት በ1994 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ውል በገጠር መሬት ላይ በግልጽ በሕግ ክልከላ ተደርጎ እያለ የተደረገ በመሆኑ ሕገወጥ ነው ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ ህገ ወጥ ውል ደግሞ በፍ/ህ/ቁ/1716 መሰረት በህግ ፊት ውጤት የማይኖረው ፈራሽ ውል ነው፡፡

ይህ ብቻም ሳይሆን ሕገ ወጥ ውል በማናቸውም ጊዜ ሊፈርስ የሚችል እንጂ የይርጋ ገደብ የሌለው መሆኑን ይህ ችሎት የፍ/ህ/ቁ/1678፣1716 እና 1718 ድንጋጌዎችን በጣምራ በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 43226፣79394 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ወስኗል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነውን ውል (unlawful contract) በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብም መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል ችሎቱ በግልጽ አስፍሯል፡፡

ስለሆነም አመልካች ለብዙ አመታት ይዞታውን ይዘው መጠቀማቸውን ጠቅሰውና እና ተክል አልምተው ይዞታው ወደ ከተማ ሲከለል ከማዘጋጃ ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር  አግኝቼአለሁ የሚለውን ምክንያት መሰረት አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የተጠሪን አውራሽ ልጆች የሆኑት ከአመልካች ባለቤት ጋር የገጠር እርሻ መሬት ሲሸጡ ሙሉ ፍላጎትና እውቅና የነበራቸው መሆኑም በሕግ በግልጽ የተደረገውን የገጠር እርሻ መሬት ሽያጭ

www.abyssinialaw.com

ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል ካለመሆኑም በላይ የሕገ መንግስቱንና ይህንኑ ተከትሎ የወጡትን የክልሉን የገጠር እርሻ መሬት አስተዳደር ሕግጋትን መሰረት ያላደረገ ነው፡፡

አመልካች ይዞታው ወደ ከተማ ክልል ከገባ በኂላ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋጋጫ ደብተር መውሰዳቸው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም ይዞታው ወደ አመልካች የገባበት መንገድ ከመነሻው ሕጋዊ ባለመሆኑና በሕግ አግባብ ባልተገኘ የይዞታ መብት ላይ የሚሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስልጣን ባለው አካል በመሰጠቱ ብቻ ሕጋዊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከፍ//ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እንዲሁም ሕገ መንግስቱ ስለንብረት መብት ከሚሠጠው ጥበቃና የመሬት ሽያጭ ውል ሕገ ወጥ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ውድቅ በማድረግ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች በተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መሰረት የሽያጭ ውሉ ህገ ወጥ ነው በሚል ይዞታውን አመልካች ለተጠሪ እንዲለቁ፣ በአመልካች ባለቤት ስም የተሰራው ሳይት ፕላን እንዲሰረዝ በማለት መወሰናቸው ስለገጠር መሬት ይዞታ በፌዴደራሉም ሆነ በክልሉ ሕግጋተ-መንግስታት፣ሽያጩ ተደረገ በተባለው ጊዜ ስራ ላይ በነበረው የክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 55/94፣ እንዲሁም ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ተፈጻሚነት ባለው አዋጅ ቁጥር 236/2006 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ባገናዘበ መልኩ የሰጡት ውሳኔ ሁኖ ስለአገኘን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 682220 በ11/02/2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 70901 በ18/05/2007 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ ፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አከራካሪው ይዞታ የሚታረስ መሬት ነው ሁኖ በሽያጭ ወደ አመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ዙሮአል ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ሆኖም በይዞታው ላይ በአመልካች የተፈሩትን ንብረቶችን አመልካች በሕግ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

በ25/06/2007 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 112906

ቀን የካቲት 16 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ማንአህሎህ አንተነህ ተወካይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የማቻካል ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተወካይ የክልሉ ዓ/ሕግ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ እና የሰብል ግምት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በአብኪመ የማቻኮል ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በዓቃቤ ህግ በኩል በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ባጭሩ ፡- አመልካች ከማንም ሕጋዊ መብት ካለው አካል ሳይሰጠው በመቻከል ወረዳ በሽይ ቀበሌ ልዩ ስሙ ገለቦ በተባለው ቦታ በምስራቅ መንገድ በምዕራብ ተምጫ ወንዝ፣ በሰሜን የኔወርቅ ለቀው በደቡብ አሚጋ የሚያዋስነው የህዝብ ግጦሽ መሬት በወርድ 50 ሜትር በቁመት 80 ሜትር የሆነውን የመስኖ መሬት በመያዝ በ2004፣2005 እና 2006 እህል በመዝራት፤ አትክልት በማፍራት ገቢ በማግኘቱ የሰብል ግምት በመክፈል የህዝብና የመንግስት ይዞት ለቆ እንዲያሰረክብ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሰይ ነው፡፤

የአሁኑ አመልካች የመከለከያ መልስ ያቀረበ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ የሰብል ግምት መቅረብ ያለበት በመሬት ይዞታው ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ መሆን እንዳለበት፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት በ1994 ዓ/ም የቀበሌ አመራር ኮሚቴዎች ለወፍጮ መትክያ የተሰጠው ስለመሆኑ በመግለጽ መልስ አቅርበዋል፡፤

የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ የአሁን አመልካች መሬቱ ከ1994 ዓ/ም የያዙኩት ስለሆነ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረበው ክርክር በተመለከተ በዚህ ጉዳይ በ1999 ዓ/ም በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ የተበለ በመሆኑ በይርጋ የሚቋረጥ አይደለም ፡፡ አመልካች መሬቱን በቀበሌ የአመራር አካላት የተሰጠኝ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም መሬት የማስተዳደር ስልጣን የወረዳው መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ጽ/ቤት

www.abyssinialaw.com

እንጅ የቀበሌ አመራር አይደለም፡፡ አመልካች በመሬቱ ላይ የዘራው ሰብል ግምት በድምሩ 11,474/ አስራ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር ይክፈል ይዞታውም ይልቀቅ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች የስር ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ከከራከረ በኃላ አመልከች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት ለወፍጮ ተጠቃሚ ህብረተሰብ አህያ እንዲያስርበት በቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው መሆኑ በወቅቱ የቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች የነበሩ ቀርበው የመስከሩ ቢሆንም መሬት የመስጠት ስልጣን የወረዳ አስተዳደር መሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 133/98 ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች መሬቱን ያገኘው ህጋዊ ሥልጣን ከሌለው የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሆኑ ይልቀቅ መባሉ በአግባብ ነው፡፡ የሰብል ግምት በተመለከተ አመልካች መሬቱን ያረሰው መብት ያለው መስሎት በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ/1173 (2) መስራት ሊሻሽል እንደሚገባው የጤፍ ሰብል ግምት ዳኝነት ያልተጠየቀበት በመሆኑ የዚህን ግምት መጠን ተቀንሶ ብር 7,726.5 ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አደርጓል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት መሬቱ በ1994 ዓ/ም የተሰጠው በመሆኑ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንንደሚሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት የሰጡት የቀበሌ አስተዳደር በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር መጠየቁን የሚያሰይ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የህዝብና የመንግስት ንብረት በህገወጥ የያዘ በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ ህግ ቀሪ የሚሆን አይደለም መሬቱም ሥልጣን በሌለው የቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው በመሆኑ ይልቀቅ መባሉ በህጉ አግባብ ነው የሚል መልስ አቅርበዋል፡፤ አመልካች የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም ያለመፈፀሙን መርምረዋል፡፡ እንደመረመርናውም የአሁኑ አመልካች አጥብቆ የሚከራከራው የመሬት ይዞታው በቀበሌ አስተዳደር እንደተሰጠው እና ለረጅም ዓመት ሲጠቀምበት እንደነበር ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የቀበሌ አስተዳደር መሬት የመስጠት ስልጣን እንደሌለው እና ሰብል በማምረት ያገኘው ህገወጥ ጥቅም ገቢ እንዲያደርግ መወሰኑ በአግባቡ ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው አመልካች ከዚህ መሬት ጋር በተያየዘ በ1999 ዓ/ም በወንጀል ተከሶ እንደተቀጣ መሬት የመስጠት ስልጣን በሌለው የቀበሌ አስተዳደር የተመራው ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካች የመሬት ይዞታው በቀበሌ አስተዳደር ተሰጠኝ ይበል እንጂ የቀበሌ አስተዳደር መሬት የመስጠት ኃላፊነት እንደነበራቸው በህግ የተደገፈ ክርክር አላቀረበም፡፤ በህጉ አግባብ ሥልጣን ባለው አካል የመሬት ይዞታው ማግኘቱ ካልተረጋገጠ ደግሞ የህዝብና የመንግስት ይዞታ ሊለቅ ይገባል መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ያቀረበው የይርጋ ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም ብለናል፡፡

አመልካች በህገ ወጥ መንገድ በያዘው መሬት ላይ ሰብል ዘርቶ ገዚ በማግኘቱ ምክንያት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በማሻሸል 7,726 ብር የሰብል ግምት እንዲከፍል ወስኗል፡፡ አመልካች ሰብሉን የዘራበት አግባብ ሲታይ የመሬት ይዞታው በቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው ስለመሆኑ እምነት በመያዝ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙ የቀበሌ የስራ ኃላፊዎች የነበሩ ግለሰቦች መሬት ሰጥተው እንደነበረ አስረድቷል፡፡ ይህ ሲታይ አመልካች መሬቱ ስልጣን ባለው አካል ተሰጥቶኛል ከሚል እምነት በመነጨ በቅን ልቦና ሰብል ያመረተ መሆኑን መረዳት ይቻላል ተጠሪም መሬቱ ሥልጣን ባለው አካል አልተሰጠውም በማለት ተከራከረ እንጅ የቀበሌ አስተዳደር ያልሰጠው ስለመሆኑ ክዶ አልተከራከረም፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ሰብል በመዝራት አገኘው የተበለው ግምት 7,726 ብር ይክፈል መባሉ በህጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም አመልካች መሬቱ እንዲለቅ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ የሰብል ግምት ይክፈል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን ሊሻሻል የሚገባው ነው፡፤ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፤

## ው ሳ ኔ

1. የምስራቅ ስደሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 011806 በ 24/06/2007 ዓ/ም የመቻከል ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11475 በ2/08/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በማሻሸል የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፤
2. አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን መሬቶች እንዲያስረክብ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች የሰብል ግምት 7726 /ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ሰድስት ብር 50/100 የሆነውን ለመልስ ሰጭው ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል
4. የወጪና ኪሰራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሩ/ለ

www.abyssinialaw.com

# ንግድ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 99900

መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሣለኝ

አመልካች፡- አቶ ኃይሉ መንግስቱ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሬገን መሐመድ - አልቀረቡም

2. አቶ ጌታሁን ገሰሰ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የሽርክና ማህበር በማቋቋም የተዋጣው ገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው የአሁኑ አመልካች በአፋር ክልል ገቢረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም በአጭሩ ከተጠሪዎች ጋር በነበራቸው የሽርክና ውል መሰረት የእርሻ ስራ መጀመራቸውን ገልፆ በመካከሉ ግን አመልካች ከማህበሩ መውጣት መፈለጉን ተከትሎ ያዋጣው ገንዘብ ብር 38,900 አመልካች እንዲመለስለት በጠየቀው መሰረት ተጠሪዎች ገንዘቡን በሁለት ዙር ክፍያ ሊከፍሉ ከተስማሙ በኃላ ያለመከፈላቸውን ጠቅሶ በውሉ መሰረት ሊከፍሉ የተስማሙበትን ብር 38,900ና ብሩ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም በውሉ መሰረት ባለመፈፀማቸው ቅጣት/ ገደብ ብር 5000 እና ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፈልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ሲሆን የስር 1ኛ ተከሳሽ የሆነው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ ፡- ከአመልካች ጋር በሽርክና በጋራ ስራ ለመስራት ገንዘብ ማዋጣቸውን አምኖ ሆኖም ግን አመልካች የዋጣውን ገንዘብ ለመመለስ አለመስማማቱን ወይም ውል አለመፈረሙንና አመልካች የውል ስምምነት ነው ብሎ ያቀረበው ሰነድም 2ኛ ተጠሪን ብቻ በሽማግሌዎች አማካኝነት በመደለልና

www.abyssinialaw.com

አታሎ ያስፈረመው ውል እንጂ እኔን ጭምር ያካተተ ባለመሆኑ ውሉ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ ይልቁንም በሽርክና ውላችን መሰረት የከዚህ ቀደሙን ኪሳራ አመልካች ከእኛ ጋር ከተጋራ በኃላ በቀጣዩም አብረን እንድንሰራ ተብሎ ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም በበኩሉ የግራ ቀኙን ቃል ክርክር ካአዳመጠ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አስቀድሞ ያዋጣው የገንዘብ ይመለስለት በሚለው ሰነድ ላይ 1ኛ ተከሳሽ (የስር 1ኛ ተጠሪ ) ባይፈርምም በሁለቱ ተከሳሾች መካከል የወካይና ተወካይ ግንኙነት መኖሩንና እንዲሁም የስር 1ኛ ተከሳሽም በራሱ በውሉ ላይ ባይፈርምም በውሉ መስማማቱን ግን ከቀረበው ክርክር ለመረዳት መቻሉን ካሰፈረ በኃላ ተከሳሾች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1675 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በገቡት ውል መሰረት ዋናውን ገንዘብ ብር 38,900 ክስ ከተመሰረተበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ 9%ወለድ ጋርና እንዲሁም ብር 5000 ገደብ ጭምር በአንድነትና በነጠላ ለስር ከሳሽ ይከፈሉ ሲል ወስኗል ፡፡ በአሁኑ ተጠሪዎች የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን ተከራከሪ ወገኖች አስቀርቦ እንዲከራከሩ ካደረገ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች መካከል የሽርክና ውል መኖሩን መረጋገጡን ከገለፀ በኃላ ከዚኅ ውል ለመውጣትም ሆነ የሽርክና ውሉን ለማፍረስ የፈለገ አባል ካለ ጥያቄውን ማቅረብ ያለበትም ሆነ ጉዳዩ ታይቶ ተገቢው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳዩን በተለይ በሚገዛው ንግድ ህጉ መሰረት መሆን አለበት እንጂ ስለ ውሎች በጠቅላላው የሚመለከተው የፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት ባለመሆኑ የህንኑን ተከትሎ ተፈጸሟል የተባለው የውል ሰነድም በዚሁ ምክንያት ተፈፃሚነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ከተቸ በኃላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ሽሮታል ፡፡አሁን የቀረበው በሰበር አቤቱታም ይህንኑ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አቤቱታውም ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል መዝገቡን እንደተመለከትነውም በአመልካችና ተጠሪዎች መካከል አስቀድሞ የተቋቋመ የሽርክና ማህበር ውል መኖሩን ፤በዚህ ውል መነሻነትም አመልካች የበኩላቸውን ድርሻ ብር 38,900 ገንዘብ ማዋጣቱን በሽርክና ውሉ መሠረትም የእርሻ ስራ በጋራ መስራት መጀመራቸውም ፤ይህ በእንዲህ እንዳለ 2ኛ ተጠሪ በ23/11/2004 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት መሰረት አመልካች በማህበር አባልነቱ አስቀድሞ ያዋጣውን ገንዘብ በሁለት ዙር የክፍያ አፈጻጸም ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለመክፈል በራሱና 1ኛ ተጠሪን በመወከል ውል መፈረሙን አመልካችም ይሄው ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ በተጠሪዎች እንዲከፈለው የጠየቀው ይህንኑን

www.abyssinialaw.com

ውል መሰረት በማድረግ መሆኑን ፣ነገር ግን 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ውክልና ስልጣን አለመኖሩን ፣1ኛ ተጠሪም በዚሁ መሰረት በአመልካች ጥያቄ አለመስማማቱንና እንዲሁም ካለ 1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ውጭ ሁለቱ አባላት ብቻቸውን ይህንኑ አመልካች አስቀድሞ ያዋጣውን መዋጮ ይዞ ከማህበሩ ይውጣ በማለት መወሰንም የማይችሉ መሆኑን ገልፆ የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

እንግዲህ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች መካከል በውል መሰረት የተቋቋመ የሽርክና ማህበር አለ ከተባለ ከዚህ ማህበር ለመውጣት የፈለገ አባል እንዴት እና በምን አግባብ መውጣት እንደሚችል በንግድ ህጉ አንቀጽ 227 እና ተከታዮቹ ጠቅላላ ድንግጌዎች በሚመለከተው መሰረት ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል ፡፡ በእርግጥ አመልካች የራሱን መዋጮ ይዞ ከማህበሩ ይውጣ በሚለው ሀሳብ ላይ ሁሉም የማህበሩ አባላት ቢስማሙበት ኖሮ አመልካች ይህንኑ በውሉ መሰረት እንዲሰጠው መጠየቅ እንደሚችል ከንግድ ህጉ አንቀጽ 233(1) ድንጋጌ ይዘትና ሌሎችም ተከታይ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል ፡፡ይሁንና ከማህበሩ አባላት አንዱ የሆነው 1ኛ ተጠሪ በዚህ ነጥብ ላይ መስማማቱን አመልካች አላስረዳም ፡፡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪም ቢሆን ከ1ኛ ተጠሪ የተሰጠውን ውክልና ስልጣን መሠረት በማድረግ ለአመልካች መዋጮው እንዲመለስለት የሚለውንና በ 23/11/2004 ዓ.ም ተደርጓል የተባለውን የውል ስምምነቱ ስለመፈረሙም በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ አልተረጋገጠም እንዲህ ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው የውክልና ስልጣን ከሌለና 1ኛ ተጠሪም በራሱ በ 23/11/2004 ዓ.ም ተደርጓል በተባለው ስምምነት ሰነድ ላይ አለመፈረሙ ከተረጋገጠ አመልካች ይህንን ውል በሰነድ መሠረት በማድረግ አስቀድሞ የዋጣው መዋጮ እንዲከፈለው /እንዲመለስለት /መጠየቅ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም ፡፡ ስለሆነም አመልካች ሁሉም የማህበሩ አባላት ያልተስማሙበትን የውል ስምምነት ሰነድ( በ23/11/2004 ዓ.ም ተደርጓል የተባለውን) መሠረት በማድረግ አስቀድሞ ለማህበሩ አዋጥቶ የነበረውን መዋጮ ብር 38,900 እንዲመለስለት መጠየቁ ለጉዳዩ በተለይ አግባብነት ያለው የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች መሠረት ያላደረገ በመሆኑ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሆኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን መሻሩ በውጤት ደረጃ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ው ሳ ኔ

1. የአፋር ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 2752 በ 14/5/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም
3. አመልካች በንግድ ህጉ መሰረት መብቱን ከማስከበር ይህ ውሳኔ አይከለከለውም ፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.97760

ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- ወ/ሮ ንግስቲ አትክልቲ -ጠበቃ ሙሉዓለም ፈጠነ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አበባው ሽፈራው -የቀረበ የለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአካል ጉዳት ካሳ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች እና አቶ በረከት ተስፋዬ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነውና በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ በረከት ተስፋዬ ይሽከረከር በነበረው ኮድ 3-58098 አ.አ ተሽከርካሪ ከአለታ ወንዶ ከተማ ወደ ሐዋሳ ከተማ ብር 22.00 ከፍለው በመጓጓዝ ላይ እንዳሉ መኪናው በከፍተኛ ፍጥነት ይሽከረከርና ሹፌሩም ሞይባል ያናገር ስለነበር ከተራራው ጋር ተጋጭተው በአካላቸው ላይ 50% የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን፣በዚህም ምክንያት ገቢ ያጡና ለሕክምና ወጪ ያወጡ መሆኑንና ሹፌሩም በወንጀል የተቀጡ መሆኑን ዘርዝረው በድምሩ ብር 497,105.97(አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ አምስት ብር ከዘጠና ሳንቲም) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የመኪናው ባለቤትና ሹፌሩ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳቱ የጥቅም ግንኙነት በሌለው ሁኔታ ስለመሆኑ፣ ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ገቢ ወይም ጥቅም የሌለ መሆኑንና የጉዳት ካሳ መጠኑም የተጋነነ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎአል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካችን ኃላፊ በማድረግ ብር 376,226.00 (ሶስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ስድስት ብር) በአንድነትና በነጣላ እንዲከፈላቸው ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን እንዲከራከሩ እና አማካይ እድሜን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ እንዲቀርብ ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ላይ የተሰጠውን የኃላፊነት ውሳኔ ተቀብሎ የጉዳት ከሳ መጠኑን ግን ከአማካይ እድሜ ጋር በማመጣጣን አስልቶ በድምሩ ብር 284,280.00( ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ ከዚኅም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ የካቲት 04 ቀን 2006 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት አራት ገፅ የሰበር አቤቱታ በታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2081፣2086(2) እና 2089 ድንጋጌዎች ጋር እና የጥቅም ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ የተሽከርካሪው ባለቤት ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ ከተወሰነው የዚህ ሰበር ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ ጋር ያልተጣጣመ መሆኑን፣ ተጠሪ ክሱን ከውል ውጪ ሃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች መሰረት ማቅረባቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑንና የካሳ መጠኑንም በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠ የተጠሪ ጥቅም በሌለበትና የተጠሪ ገቢ በአግባቡ ባልተጣራበት ሁኔታ በተጋነነና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 ይዘትና መንፈስ ውጪ የተወሰኑ መሆኑን ዘርዝረው ውሳኔው ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ የፁሑፍ ክርክር አድርገዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድነጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዙት ጭብጦች አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዙት ጭብጦች፡-

1. በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2089 ድንጋጌ እና ከሰ/መ/ቁጥር 38457 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን፣
2. የአንቾ ተጓዥ ውል መኖሩ ሳይካድ ከውል ውጪ ሃላፊነት ተብሎ የቀረበው ክስ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን እና

www.abyssinialaw.com

3. ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት ያጡት ጥቅም እንደተቋረጠባቸው ባላስረዱበት ለተጠሪ ካሳ እንዲከፈላቸው የተወሰነው የካሳ መጠን ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር የጥቅም ግንኙነት የለኝም በማለት የሚከራከሩት ጉዳት አደረሰ የተባለውን ተሽከርካሪ በወቅቱ Populationa Service International(PSI) ለተባለ ድርጅት አከራይቼ ከመኪናው ጥቅም ሲያገኝ የነበረው ይኼው ድርጅት ነው በሚል አቢይ ምክንያት መሆኑን ተገንዝናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጎ የኪራይ ውል ሊቀርብ ባለመቻሉ መኪናው ተከራይቶ የነበረ ነው ለማለት እንዳልቻለ ግልጾ ያለፈው ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዘብናል፡፡ በመሆኑም አመልካች መኪናውን አከራይተው ያልነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን ፍሬ ነገሩን ለማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ ፍሬ ነገር የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ስናው ይህ ችሎት አመልካች መኪናውን አከራይተው ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለውን የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ነጥብ የሚመረምርበት አግባብ የለም፡፡ ምክንቱም ለዚህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን ፍሬ ነገርን ለማጣራት ወይም ማስረጃን ለመመዘን ሳይሆን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም ብቻ ነውና፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በአመልካች በኩል የቀረበው ቅሬታም ሆነ በሰበር አጣሪ ችሎቱ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና የዚህን ችሎት ስልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- </u>ተጠሪ በአመልካች መኪና ክፍያ ፈጽመው ሲጓጓዙ የነበሩ መሆኑ ያልተካደና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ግንኙነቱ ውልን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ውልን መሰረት ያደረገ የመጓጓዣ ግንኙነት በን/ሕ/ቁጥር 588 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ ሊታይ የሚገባ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በን/ሕ/ቁጥር 588 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ አጓዡ መንገደኛውን በመልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ስለ ምቾቱና ስለ ጉዞው በውሉ የተወሰነውን ጊዜ አክብሮ እንደተወሰነው እመድረሻ ስፍራ የማድረስ ግዴታ እንዳለበት በሓይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት የአጓዡን የትራንስፖርት መኪና በሀላፊነት ተረክቦ መኪናውን ደህንነትና ብቃት አረጋግጦ የትራፊክ ደንብና ሥርዓትን አክብሮ የማሽከርከር ሀላፊነት ያለበት አሽከርካሪ /ሹፌር/ ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች መንገደኛውን መልካም ይዞታና ጥበቃ እንደዚሁም ምቾት በመጠበቅ በሰላም ወደሚፈለግበት ቦታ የማድረስ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ማስቻል ሲሆን ይህንኑ በሕግ የተጣላባቸውን ግዴታ ካልተወጡ ደግሞ

www.abyssinialaw.com

መንገደኛው በጉዞው ላይ ስለሚደርስበት መዘግየትና በጉዞው ጊዜ ወይም በሚሣፈርበት ወይም በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል ማጉደል ወይም የህይወት ማለፍ አጓዡ ሀላፊ እንደሚሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡የዚህ ድንጋጌ አጓዡ መንገደኛው በጉዞ ጊዜ በሚሣፈርበትና በሚወርድበት ጊዜ በአደጋ ምክንያት ለሚደርስበት መቁሰል ወይም የአካል መጉደል ወይም ህይወት ማለፍ አጓዡ በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በመሠረታዊ መርህነት የሚያስቀምጥ ሲሆን ፣ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ የሚሆንባቸዉን ልዩ ሁኔታዎች የሀላፊነቱን መጠንና አጓዡ በህግ ከተደነገገው መጠን በላይ በሀላፊነት ሊጠይቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል፡፡ በንግድ ህግ አንቀጽ 595 ከተደነገገው ሀላፊነት አጓዡ ነጻ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግገው የንግድ ህጉ አንቀጽ 596 ሲሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 596 አጓዡ በመንገደኛው ላይ የአካል መጐዳት ወይም የሞት አደጋ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ከፍተኛ ሀይል መሆኑን ፣ ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሶስተኛ ሰው ጥፋት መሆኑን ወይም በመንገደኛው ጥፋት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አጓዡ ከሀላፊነት ነጻ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ የካሳ መጠኑን በተመለከተ የቀረበውን ቅሬታ ስንመለከተውም አጓዡ በንግድ ህግ ቁጥር 596 መሠረት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ በመንገደኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት በሀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 597 ድንጋጌ ያሳያል፡፡ የሀላፊነት መጠን በተመለከተ ደግሞ ለአንድ መንገደኛ ከብር 40,000 /አርባ ሺ ብር/ እንደማይበልጥ የንግድ ህግ አንቀጽ 597 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በንግድ ህግ አንቀጽ 597 የተደነገገው የሀላፊነት መጠን አጓዡ በንግድ ህግ አንቀጽ 596 የተደነገጉትና ከሀላፊነት ነጻ የሚያደርጉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት ባልቻለበት ሁኔታና መንገደኛው በንግድ ህግ አንቀጽ 599 በሚደነገገው መሠረት አጓዡ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እያወቀ በፈጸመው ተግባር ወይም ጉድለት ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን ለማስረዳት ባልቻለበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን ድንጋጌ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን የአመልካች ንብረት የሆነውን ተሽከርካሪ ያሽከረክር የነበረው የአመልካች ሰራተኛና የመኪናው ሹፌር የሆነው ለአደጋው ምክንያት ስለመሆኑ ተረጋግጦ በወንጀልም ክስ ተመስርቶበት ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ግልጽ የሆነ ክርክርና ማስተባበያም የለም፡፡ በንግድ ህግ ቁጥር 588 በሚደነግገው መሠረት የመንገደኛውን መልካም ይዞታ ደህንነትና ምቾት በመጠበቅ መንገደኛውን የማጓጓዝ ሀላፊነቱን ሊወጡ የሚገባቸውን ወገኖች የመኪና ባለቤት፣ ሹፌር፣ረዳቱና ሌሎች ሰራተኞች ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ መኖሩን፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 599 "አጓዡ የተፈፀመው ተግባር ወይም ጉድለት" የሚለው ሀረግ አጓዡ በግሉ የፈጸመውን ተግባር ወይም ጉድለት የሚመለከት ሣይሆን የአጓዡ ሰራተኞች አደጋ ሊያደርስ ወይም ሊፈጠር እንደሚችል እያወቁ የፈጸሙትን

www.abyssinialaw.com

ተግባር ወይም ጉድለት የሚያካትት ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 67973 በሆነው መዝገብ ላይ በቀረበው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በማናቸውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተያዘው ጉዳዩ ሲታይም አደጋው የደረሰው የ2ኛ አመልካች መኪና ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር ባጠፋው ጥፋት ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች የክርክር ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የን/ሕ/ቁጥር 599 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች በተጠሪው ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በግንድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው በላይ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች በንግድ ህግ አንቀጽ 597 ከተደነገገው የሀላፊነት መጠን በላይ ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት እንደአለባቸው የንግድ ህግ አንቀጽ 599 ድንጋጌ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በን/ሕ/ቁ 599 ድንጋጌ መሠረት ለመንገደኛው ካሣ የመክፈለ ሀላፊነት ያለበት አጓዥ ለመንገደኛው የሚከፍለው የካሣ መጠን ለመወሰን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 የተደነገጉት የካሳ አከፋፈል መርሆች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸውም ይህ ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ጉዳዩ ሲታይም ክሱ መቅረብ ያለበት ከውል ውጪ ሃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች በመሆኑ ተጠሪ በዚህ አግባብ ክስ ማቅረባቸውና የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ክስ ተቀብለው ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች መሰረት መወሰናቸው የሚንቀፍበትን ሕጋዊ ምክንየት አላገኘንም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ተጠሪ በመኪናው ግጭት ምክንያት በአካላቸው ላይ 50% ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ፣ ከጉዳቱ የተነሳ ለተለያዩ ወጪዎች የተዳረጉ መሆኑንና ከጉዳቱ በፊት በሲዳማ ቡና አብቃይ ገብሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ይሰሩ እንደነበርና በጉዳቱ ምክንያትም የስራ ብቃታቸው እና ሲያገኙ የነበረው የገቢ መጠንን ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት ተጠሪ የሚቀርባቸውን ገቢና ከጉዳቱ ጋር ተያይዘው የወጡትን ወጪዎች በመለየት የካሣ መጠኑን ወስነዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተለይ ካሳውን ሊወሰን የቻለው የተጠሪን እድሜና በአከባቢው በጊዜው የታወቀውን አማካይ እድሜ ስንት እንደሆነ በመለየት ስለመሆኑ ውሳኔው በግልጽ ያሳያል፡፡
በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092 ፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው

www.abyssinialaw.com

ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጸዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታ መሰረት ስናደረግ በካሳ አተማመኑ ላይ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ሳይገቡ በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ስለመሠጠቱ የሚያሳይ ነገር ያለ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ አካላቸው በሕገ መንግስቱም ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን ካሳው ሲወሰንም ይህንኑና ጉዳቱ በአመልካች የወደፊት ኑሮ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አጠቃላይ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል ነው፡፡ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያሊዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራሊዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመሥራት አቅም /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሓዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ከማጋነንና ከመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣዳሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ለዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍርድ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2101 እና 2102 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው

www.abyssinialaw.com

አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማጣት ከአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አላማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ አይሆንም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ  በአመልካች መኪና ተሳፍረው ሲሄዱ በደረሰው ከተራራ ጋር የመጋጨት አደጋ በአካላቸው ላይ ጉዳት መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፉ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም  በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበው ቅሬታም ሆነ በአጣሪ ችሎቱ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2141 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር ያላገናዘበ ሁኖ አግኝትናል፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ስላለገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1656 ሚያዚያ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 594440 በ10/01/2006 ዓ/ም የተሻሻለውና ይህንኑ የተሻሻለውን ውሳኔ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ያፀናው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 94784 በ30/04/2006 የሠጠው ትዕዛዝ  በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 105628

ጥቅምት 24/2008 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡……… ዩኒቨርሳል ሜታልስና ሚኒራል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ ማርሻል ፍ/ማርቆስ ቀረቡ

ተጠሪ፡………….. ባሰፋ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይሄ ጉዳይ የሕንጻ ኪራይ ውል ካለቀ በኂላ ያልተከፈለውን ከሕንጻው የታጣ ገቢን ለማስከፈል የቀረበ ክስን መሰረት ያደረገ ክርክር ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የሥር ከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የባለ ሁለት ፎቅ ህንጻ ተከሳሽ ህዳር 15 ቀን 2003 ዓ.ም በተሻሻለው የኪራይ ውል ስምምነት የኪራይ እና የተለያዩ ክፍያዎችን ጨምሮ በየወሩ በብር 51,750.00 ተከራይቶ ከህዳር 9 ቀን 2003 ዓ.ም እስከ ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም ሲገለገልበት ቆይቶ የውሉ ዘመን እስከሚያልቅ በዚህ አልገደድም በማለት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ ተከሳሽ ያለበትን የቤቱን ኪራይ ከፍሎ ቤቱን እንዲያስረክበን ከሰን በ20/03/2005 ዓ.ም ፍርድ ተፈርዶበት ፣ በአፈጻጸም በ30/08/2005 ዓ.ም ሕንጻውን ሊያስረክበን ችሏል ፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ በአዲስ የኪራይ ታሪፍ መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ በቀን በብር 3,333.33 ወይም በወር ብር 100,000.00 ሂሳብ የ172 ቀናት ጊዜ ማግኘት የነበረብንን ገቢ በድምሩ ብር 573,333.28 ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለን በማለት ጠይቋል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር ተከሳሽ /የአሁን አመልካች/ ባቀረበው መልስ ተከሳሽ ቤቱን ለቆ የወጣው ታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ.ም ቢሆንም ከሳሽ ቤቱን ለመረከብ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ከሳሽ

www.abyssinialaw.com

በውሳኔው መሰረት ቤቱን ያስረክበኝ በማለት አፈጻጸም ቢያቀርብም ተከሳሽ ቤቱን አስተካክሎ ሊያስረክበኝ ይገባል በሚል ምክንያት ሳይረከብ ቀርቶ በተከሳሽ ተደጋጋሚ ልመና በ30/08/2005 ዓ.ም የቤቱ ርክክብ ሊፈጸም ችሏል ። ከሳሽ ቤቱን ተረክቦ የጎደለ ነገር መጠየቅ ይገባው ነበር እንጂ በዚህ ምክንያት አልረከብም ማለቱ ተገቢ አይደለም ለጨመረው ኪሳራ ሃላፊ እሱ ነው፡፡ የቤቱ ርክክብ የዘገየውን በተመለከተ ከታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ.ም በኋላ ያለው የኪራይ ገንዘብ ተከሳሽን አይመለከትም፡፡ የኪራይ መጠን መታሰብ ያለበት በብር 51,750.00 እንጂ በብር 100,000.00 ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ የከሳሽ ክስ ተሰርዞ ከ9/03/2005 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ1 ወር ከ16 ቀን ብቻ ብር 79,350.00 ብቻ ተብሎ እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል ።

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ የቤት የኪራይ ውል እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን ተከሳሽ በ20/03/2005 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ህንጻውን ያስረክበው ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በኪራይ ውሉ አንቀጽ 5 መሰረት የኪራይ ውሉ ዘመን ሳያልቅ ቤቱን አስተካክሎ በነበረበት ሁኔታ ለከሳሽ ማስረከብ እንዳለበት ያሳያል፡፡ ከሳሽ በ03/04/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማስጠንቀቂያ የቤቱ የኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 ሆኖ መወሰኑን ለተከሳሽ አሳውቆ ተከሳሽም በሰጠው መልስ ይህን እንደማይቀበል ገልጿል፡፡ ይህ ማለት ተከሳሽ የቤቱ የኪራይ ዋጋ ተመን ብር 100,0000.00 እንደሚሆን አውቋል ። ስለዚህ ተከሳሽ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ብር 573,333.28 የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ከግንቦት 5 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍለው በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ ይህን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻውን ለፌደራል ጠቅላጠይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ምክንያቱን በመጥቀስ የሥር ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መስከረም 03 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የተስማበት የኪራይ ዋጋ ብር 51,750.00 ሲሆን ይህ የኪራይ ዋጋ በስምምነት ካላሻሻሉት አከራይ የሆነው ወገን ብቻ በራሱ ዋጋ ሊተመን የሚችልበት የሕግ ስርዓት የለም፡፡ ተጠሪ የውሉ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት ኪራዩን ብር 100,000.00 አድርጌያለሁ በማለት የሰጠው ማስታወቂያ በወቅቱ በአመልካች ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ቀሪ ሆኗል፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ የኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 /መቶ ሺህ/ ሂሳብ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ቤቱን እንዲያስረክበኝ በማለት ክስ ሲመሰርት እስኪያስረክበኝ ድረስ የቤቱን ኪራይ በወር 51,750.00 ይክፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ይህ ማለት የኪራይ ጭማሪ ተቀባይነት እንደሌለው ተረድቶ የተወ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች የሚጠይቀው ዳኝነት የሥር ፍ/ቤቶች ኪራዩ በብር 100,000.00 ይከፈል በማለት የተሰጠበት ውሳኔ ተሽሮ ስምምነት

www.abyssinialaw.com

በተደረገበት በብር 51,750.00 እንዲወሰንና የደረሰውን ወጪና ኪሳራ ተጠሪ እንዲተካ እንዲወሰን በማለት አመልክቷል ፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን በመመርመር የሚጣራ ጉዳይ ስላለ አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የካቲት 05 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ፡- ይህ ክስ የጉዳት ካሳና ኪሳራ ይከፈለን የሚል ነው እንጂ የቤት ኪራይ ይከፈለን የሚል አይደለም፡፡ አመልካች የሕንጻው የኪራይ ውሉ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ የቤቱ ኪራይ ታሪፍ ከነታክስ ብር 51,750.00 ወደ ብር 100,000.00 ማደጉን በጽሑፍ የተገለጸለትና የአወቀው ሆኖ ሳለ ቤቱን እንዲለቅ ተወስኖበት የውሉ ዘመን ካበቃም በኋላ ከተጠሪ እውቅናና ፈቃድ ውጭ ለ172 ቀናት ከህግ ውጭ ቤቱን ይዞ እየተገለገለበት ማግኘት የነበረብንን እና የቀረብንን ገቢ አመልካች በአዲሱ የኪራይ ታሪፍ የጉዳት ካሳና ኪሳራ እንዲከፍለን ጠይቀን ተፈረደበት እንጂ የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍል አልተፈረደበትም፡፡ አመልካች የኪራይ ውሉ ካበቃ በኋላ ቤቱን እንዲያስረክበን በተደጋጋሚ ጊዜ በጽሁፍ እየጠየቅነውና ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው ከተጠሪ እውቅና ፈቃድ ውጭ ቤታችንን ከ6 ወራት በላይ ያለአግባብ ተገልግሎበታል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የኪራይ ውሉ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት የኪራይ ታሪፉን ተጠሪ ባሳወቀው መሰረት የጉዳት ካሳ እንዲከፍለን መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ እንዲሆንልን ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲተካልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ09/07/2007 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አመልካች የሕንጻው ኪራይ ዘመን ካለቀ በኋላ ሕንጻውን በፍርድ እስካስረከበበት ጊዜ ተጠሪ ያጣውን ገቢ በምን ልክ መክፈል አለበት? የሚለውን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ እና አመልካች መካከል በነበረው በተሻሻለው የሕንጻ ኪራይ ውል መሰረት የኪራይ ዋጋ እና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ በብር 51,750.00 ከህዳር 9 ቀን 2003 ዓ.ም እስከ ህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም አመልካች ተከራይቶ ሲገለገልበት እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በግራ ቀኙ መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ተጠሪ ባቀረበው ክስ አመልካች ያለበትን የኪራይ ገንዘብ ከፍሎ ሕንጻውን እንዲያስረክበው ክስ አቅርቦ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 196631 በ20/03/2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች ያለበትን የሕንጻውን ኪራይ ዋጋ ከፍሎ ሕንጻውን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በማለት ወስኗል፡፡

www.abyssinialaw.com

አመልካች ግን በዚህ ውሳኔ መሰረት የሕንጻው ኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ በፍርድ አፈጻጸም መምሪያ በኩል ሲካሄድ በነበረው የፍርድ አፈጻጸም ሂደት ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ሕንጻውን ለተጠሪ ያስረከበው መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገር በማስረጃ አጣርቶ በደረሱበት መደምደሚያ በኪራይ ውሉ መሰረት የኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በሕንጻው ላይ የተገኙትን ጉድለቶች አስተካክሎ ሕንጻውን በነበረ ሁኔታ ነው የመለሰ በሚያስብል መልኩ ለተጠሪ ማስረከብ እንዳለበት አረጋግጧል፡፡ አመልካች የሕንጻው ኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መስተካከል ያለበትን አስተካክሎ በህዳር 8 ቀን 2005 ዓ.ም ሕንጻውን ለተጠሪ ማስረከብ አለበት እንጂ የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ ሕንጻውን ለማደስ መነሳቱ አግባብነት የለውም፡፡ የሕንጻው የኪራይ ውል ዘመን ካለቀ በኋላ አመልካች በጊዜ ሕንጻውን ማስተካከል ያለበትን ነገር አስተካክሎ ባለማስረከቡ የሕንጻው ርክክብ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም የዘገየ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሕንጻው ርክክብ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም የዘገየ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ያረጋገጡት ጉዳይ ነው ስለዚህ የህንጻው ርክክብ የዘገየው በተጠሪ ምክንያት መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች የቀረበውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ይህን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ከመቀበል በቀር ተመልሶ የሚያጣራበት የሕግ አግባብ የለውም፡፡

ይህ በመሆኑ አመልካች የሕንጻው የኪራይ ዘመን ካለቀ በኋላ ያለአግባብ ሕንጻውን ይዞ ለቆየበት ጊዜ ተጠሪው ያጣውን ገቢ በምን ስሌት መክፈል አለበት የሚለው ጭብጥ እልባት ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ሲታይ በ03/04/2004 ዓ.ም ለአመልካች በተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሕንጻው ኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 መሆኑን ያሳወቅን በመሆኑ፣ አመልካች ሕንጻውን ያለአግባብ ይዞ በቆየባቸው ጊዜያት በዚህ ገንዘብ ልክ ኪራዩን ሊከፍለን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ባቀረበው ክርክር የኪራዩን ዋጋ በስምምነት እስካላሻሻልነው ድረስ ተጠሪው ብቻውን ሊወስን አይችልም፣ የተሰጠውም ማስጠንቀቂያ ቀሪ ስለሆነ በብር 100,000.00 የኪራይ ዋጋ ተመን አልገደድም በማለት ተከራክሯል ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪን ክርክር በመቀበል ከሕንጻው አጥቷል ያሉትን ገቢ አስልቶ መወሰናቸውን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በ03/04/2004 ዓ.ም የሕንጻው ኪራይ ዋጋ ብር 100,000.00 እንዲሆን ተወስኗል በማለት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ በሰጠ ጊዜ የኪራይ ውሉ ዘመን እንዳላለቀ ያመለክታል፡፡ ከዛ በኋላ ተጠሪ አመልካች በኪራይ ውሉ ላይ በተጠቀሰው የኪራይ ዋጋ ታሪፍ ብር 51,750.00 መሰረት ያልከፈለውን ክፍያ ፈጽሞ ሕንጻውን እንዲያስረክበው የተወሰነ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ የኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት ማስጠንቀቂያ የሰጠ ቢሆንም በክርክር ሂደት ውስጥ ይህ ማስጠንቀቂያ ታልፎ እስከ ኪራይ ዘመኑ ያለውን በነበረው የኪራይ

www.abyssinialaw.com

ዋጋ ፍ/ቤቶቹ ያሰሉት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም ተጠሪ የኪራይ ውሉ ዘመን ሳያልቅ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ መሰረት በማድረግ ዳኝነት የጠየቀው እና የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ሲታይ አግባብነት የሌለው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪ የኪራይ ዘመኑ ካለቀ በኋላ የአካባቢውን የሕንጻ ኪራይ ዋጋ ተመን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ የሆነ የኪራይ ዋጋ በማስቀመጥ ለአመልካች ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆን አለመሆኑ ሳይጣራ እንዳለ መውሰድ የሚቻል ሆኖ አይታይም ፡፡ ነገር ግን የአካባቢው የሕንጻ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ሚዛነዊነቱ፣ ተመጣጣኝነቱ እና ፍትሐዊነቱ ባልተጣራበት ሁኔታ ተጠሪ የቀድሞውን የኪራይ ዋጋ በዕጥፍ በመጨመር በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት ያጣሁት ገቢ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን፣ የሥር ፍ/ቤቶች ምንም ማጣሪያ ሳያደርጉ በመቀበል የሰጠበት ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የኪራይ ውል ዘመን ካለቀ በኋላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ውልን መሰረት ያደረገ የኪራይ ዋጋ ተመን እንደሌለ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ተጠሪ ከሕንጻው ያጣውን ገቢ ለመተመን የኪራይ ልክ መወሰን ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2950/2/ መሰረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት "የኪራይ ልክ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስጣኖች በወሰኑት ታሪፍ መሰረት ወይም የተወሰነ ታሪፍ የሌለ እንደሆነ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል ይወሰናል" በማለት ደንግጓል፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ ድንጋጌ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ መሆኑን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ለክርክር ምክንያት የሆነው ሕንጻ ያለበት አካባቢ የዚህ ሕንጻ ኪራይ ዋጋ ልክ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ተጣርቶ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሕንጻ የሚገኝበት አካባቢ ባለው የገበያ ዋጋ ልማድ መሰረት ሚዛናዊነት እና ፍትሐዊነትን በጠበቀ መልኩ የኪራይ ልክ ተተምኖ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የተጠሪን ሕንጻ በፍርድ ተገዶ እስካስረከበ ጊዜ ድረስ ሊከፍል የሚገባው ተጠሪ ያጣውን ገቢ በሚመለከተው ባለሙያ ሳያጣሩ አመልካች እንዲከፍል የወሰኑት የገንዘብ ልክ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የሚከተለከው ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 138322 በጥር 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 99152 በሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. አመልካች የሕንጻው የከራይ ውል ዘመን ካለቀ በኂላ በፍርድ ሕንጻውን እስካስረከበ ጊዜ ድረስ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ተጠሪ ያገኝ የነበረውን ግን ያሳጣውን ገቢ ለተጠሪ የመክፈል ሃላፊነት አለበት ብለናል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ሕንጻውን ሳያስረክብ ለዘገየበት ጊዜ ተጠሪ ሰጠ በተባለ ማስጠንቀቂያ ላይ የተጠቀሰውን የገንዘብ ልክ ብር 100000.00/መቶ ሺህ/ መሰረት በማድረግ የኪራይ ልክ በመተመን ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህ ጉዳይ በድጋሚ በማየት በፍርድ ሐተታው ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት ተጠሪ ለአመልካች አከራይቶት የነበረው ሕንጻ ባለበት አካባቢ የገበያ ዋጋና ልማድ መሰረት ይህ ሕንጻ ከህዳር 9 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ.ም ባለው ጊዜ በቀን ወይም ወር የኪራይ ልክ ምን ያህል እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ ተመልሶለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ የሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

www.abyssinialaw.com

# አፈፃፀም

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 101631

ጥቅምት 2 ቀን 2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ በየነ አሸናፊ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ያሳለፈው የአፈጻጸም ትእዛዝ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር የአፈጻጸም ተከሳሽ እንዲሁም የአሁኑ ተጠሪ የአፈጻጸም ከሳሽ ነበሩ፡፡

ግራ ቀኙ በአፈጻጸም ያደረጉት ክርክር ታይቶ በመጨረሻ በተሰጠው ትእዛዝ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በሐምሌ 2002 ዓ.ም በወጣው በኃላፊነት የሚነሱ የመንግስት ተሿሚዎች ምደባ አሰጣጥ እና ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ምደባ እንዲደረግ እና በመመሪያው ቁጥር 2.1 አግባብ እንዲፈጸም የተወሰነ በመሆኑ፤ በዚህ መመሪያ መሰረትም ከ3 ዓመት በላይ በሹመት አገልግሎት ከኃላፊነት የተነሳ ከሆነ ይዞት የነበረው ደመወዝ ይዞ ሊቀጥል እንደሚገባ የተደነገገ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፤ በመሆኑም የአፈ/ከሳሽ ይዞት የነበረውን 3348.00 ውሳኔ ከተሰጠበት የካቲት 26/2005 ዓ.ም ጀምሮ ሊከፈለው ይገባል በማለት የአፈጻጸም ተከሳሽ እንዲከፍል ታዟል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ትእዛዝ ላይ አቤቱታ የቀረበበት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር አፈፃፀም ችሎት የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታውን ሰርዟል፡፡

አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በዋናው ፍርድ እና በመመሪያው መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ፤ የስር ፍ/ቤት ያሳለፈው የአፈጻጸም ትእዛዝ ዋናውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ እና ትእዛዙ የመመሪያውን አንቀጽ 2.1 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 375(1) ሥር የተደነገገውን የስልጣን ወሰን የተላለፈ በመሆኑ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ በሰጡት መልስ በአፈጻጸም የተላለፈው ትእዛዝ ውሳኔውን እና መመሪያውን መሰረት ያደረገና ተገቢነት ያለው በመሆኑ ቅሬታው ውድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡ አመልካቹም ክርክራቸውን በማጠናከር የመ/መልስ ሰጥተዋል፡፡

በበኩላችን እንደፍርዱ አልተፈጸመም ተብሎ አመልካች እንዲፈጽም በተሰጠው ትእዛዝ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለአፈጻጸሙ ምክንያት በሆነው ፍርድ እና ውሳኔ የክልሉ የአቅም ግንባታ እና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በሐምሌ 2002 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ ክፍል ሁለት በቁጥር 2.1 በተመለከተው መሰረት ለአሁን ተጠሪ ባላቸው የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ በሚመጥናቸው መደብ ሊመደቡ እንደሚገባ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞም ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊያገኙ የሚገባው ጥቅማ ጥቅም ሊያገኙ እንደሚገባ ተወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች መ/ቤት የሰው ሀይል ስራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት የምደባ እና መረጣ ክፍል የፍርድ ውሳኔውን በተመለከተ መጋቢት 18/2005ዓ.ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ ተጠሪን በጽ/ቤቱም ሆነ በወረዳው በሚገኙ ጽ/ቤቶች ለመመደብ በትምህርት ዝግጅታቸው የስራ መደብ የጠፋ መሆኑን፤ የሚያሟሉት የስራ ደረጃ በማይገኝበት ጊዜ በመመሪያው ቁጥር 2-2-1 መሰረት ከሚያሟሉት የስራ ደረጃ አንድ ደረጃ ያነሰውን ደመወዝ እየተከፈላቸው በተገኘው ክፍት የስራ ደረጃ እንዲመደቡ እንደሚደረግ፤ በዚህም መሰረት ለተጠሪ የምደባ ቦታ ባለመኖሩ መመደብ እና ጥቅማ ጥቅም ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ ከዚህ በፊት በተመደቡበት የስራ መደብ ተመድበው እንዲሰሩ ብሏል፡፡

ይህን ተከትሎ ተጠሪ እንደፍርዱ አልተፈጸመም በማለት አመልካች ደግሞ ተፈጽሟል በማለት ተከራክረው ከላይ የተገለጸው ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

በመሰረቱ አፈጻጸምን ከሚመሩት የስነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው በውሳኔ ባለመብት የሆነ ሰው ፍርዱ ባስገኘለት መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ስለሚገባ ሊፈጸም

www.abyssinialaw.com

የሚችል ውሳኔ እስከቀረበ ድረስ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በተለይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392(1) እንደተደነገገው ፍርዱ የማይፈጸምበት ምክንያት ያለመኖሩ ሲረጋገጥ ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ አፈጻጸሙ መመራት ያለበት በዚህ ስርዓት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለስር ፍርዱ መሰረት የሆነው የመመሪያው ቁጥር 2.1 በተከታታይ ሶስት ዓመት እና በላይ በሹመት ላይ ቆይተው በተለያየ ምክንያት ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች ምደባ የሚደረግላቸው ያላቸው የት/ዝግጅት እና የስራ ልምድ ከግምት ውስጥ ገብቶ በሚያሟሉበት የስራ ደረጃ ላይ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ፍርዱም የተሰጠ በዚህ መሰረት ነው፡፡ ከዚህ በቀር ቅሬታ ባስነሳው የስር ፍ/ቤት ባሳለፈው ትእዛዝ እንደተገለጸው ከ 3 ዓመት በላይ በሹመት አገልግሎት ከኃላፊነት የተነሳ ከሆነ ይዞት የነበረውን ደመወዝ ይዞ ሊቀጥል እንደሚገባ በመመሪያው አልተደነገገም፡፡ ስሆነም በአፈጻጸም የተሰጠው ትእዛዝ የሥር ፍርዱንም ሆነ ፍርዱ የተመሰረተበትን የመመሪያውን ድንጋጌ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ትእዛዙ ከላይ የተመለከተውን አፈጻጸምን የሚመሩትን የስነ-ሥርዓት ህጉን ድንጋጌዎች የተከተለ ባለመሆኑም የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1ኛ. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 35184 ሚያዚያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ትእዛዝ፤ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ. 39465 ግንቦት 4/2006 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የፍርዱን አፈጻጸም በተመለከተ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከስር ፍርዱ፤ ለፍርዱ መሰረት ከሆነው መመሪያ፤ አፈጻጸሙ ከሚመራበት ስነ-ሥርዓት እና ተገቢነት ካላቸው ህጎች ጋር በመመርመር ተገቢውን ይወስን ብለናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

3ኛ. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.95537

ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሸሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- ክራውን ቴክስታይል ዊቪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ቸርነት

ወርደፍ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. ሚድሮክ ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ መከተ ዳኘው ቀረቡ
2. ሠመራ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ የሽጥላ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር ክርክር መነሻ የሆኑትም የፍርድ ባለመብት በነበረው የአሁነ 2ኛ ተጠሪ፣የፍርድ ባለዕዳ በነበረው የአሁነ አመልካች እና በአፈጻጸም መዝገቡ ላይ "ተጠሪ" ተብሎ በተሰየመው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረውን የፍርድ አፈጻጸም ክርክር የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 107477 በ10/09/2003 ዓ.ም.እና በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጣቸው ትዕዛዞች፣እንዲሁም በትዕዛዞቹ ቅር በመሰኘት የስር የፍርድ ባለዕዳ ያቀረበው ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁኖቹን ተጠሪዎች ተቃውሞ በመቀበል በመዝገብ ቁጥር 71612 በ30/03/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን ናቸው፡፡

በ10/09/2003ዓ.ም. የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ፡-

1. የፍርድ ባለዕዳ ለተጠሪ አክሲዮን ድርሻውን /ለሚድሮክ / በውልና ማስረጃ አቅርበው በስምምነቱ መሰረት ፈጽመው እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. የፍርድ ባለዕዳ መጋቢት 20/2002 በተደረገው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት የአክሲዮን ማህበሩን እንዲያስረክቡ ታዟል።
3. የአክሲዮን እና የኩባንያው ርክክብ እንደተፈጸመ ተጠሪ በስምምነቱ የተገለጸውን 12 ሚሊዮን ብር ለፍርድ ባለመብቱ እንዲከፍሉ ታዟል።ቀጠሮ ውጤት ለመጠባበቅ ቀጠሮ 29/09/2003 በ3፡00 ሰዓት ተቀጠረ።
4. ዳኛ እንዲነሳ በ10/09/2003 በአቶ ምኒልክ ሙሉዓለም በቀረበው አቤቱታ ላይ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ 12/09/2003 በ8፡00 ሰዓት ተቀጠረ።

የሚል ሲሆን በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ ይዘት ደግሞ ጉዳዩ በዚህ ቀን ለተሰየመው ችሎት የተመራው ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሰጡት ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ በመደረጉ መሆኑን፣ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ላይ የፍርድ ባለዕዳው ቅሬታ ካለው ለበላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ማሳረም የነበረበት ከመሆኑ በቀር ጉዳዩ የተመራለት በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኝ ችሎት የቀድሞውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ለመቀየር የሚያስችል ስልጣን የሌለው መሆኑን የሚገልጽ እና ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም ጉዳዩ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት እንዲተላለፍ መደረጉን የሚያመለክት ነው።

የስር የፍርድ ባለዕዳ ያቀረበው ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአሁኖቹን ተጠሪዎች ተቃውሞ በመቀበል በመዝገብ ቁጥር 71612 በ30/03/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን መዝገቡን የዘጋው ይግባኙ ያስቀርባል ተብሎ የነበረው በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢነት ለማጣራት ተብሎ መሆኑን፣የፍርድ ባለዕዳው በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠበት የአፈጻጸም ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የጠየቀው በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠበትን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በማስታከክ መሆኑን፣ይሁን እና በ29/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቀደም ሲል በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም የሚል እንጂ ከቀድሞው ትዕዛዝ የተለየ ባለመሆኑ ምክንያት በ29/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ራሱን ችሎ የይግባኝ ምክንያት ሊሆን የማይችል መሆኑን፣ይግባኝ ባዩ ያቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አለመኖሩን እና የይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ሊስተናገድ የሚችልበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ነው።

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ10/09/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ዳኝነት ከመስጠቱ በፊት ዳኛው ከችሎት ይነሱልኝ የሚል አቤቱታ የአሁን አመልካች አቅርቦ እንደነበረ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ

www.abyssinialaw.com

የሚያስገነዝብ ሆኖ እያለ ዳኛው ከችሎት ሊነሱ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ጉዳይ ላይ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ዳኛው በዋናው ጉዳይ ላይ ትዕዛዝ መስጠታቸው እስከታወቀ ድረስ ለይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው መነሻ ተደርጎ መያዝ የሚገባው ጉዳዩን ቀደም ሲል ባዩት ዳኛ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠውን ትዕዛዝ ለመለወጥ የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት በኃላ ላይ ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት በ29/11/2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ትዕዛዝ የሰጠበት ቀን ሳይሆን የመጀመሪያው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሰጠበት ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. ነው በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በ30/03/2006 ዓ.ም. የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ከመሆኑም በላይ በ02/10/2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ይግባኙ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ካለፈ በኃላ የቀረበ በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልች አጥብቆ የሚከራከረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሰጠው ትዕዛዙን የሰጡት ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ ጥያቄ ካቀረብን በኃላ አመልካች የትዕዛዙን መሰጠት ማወቅ በማይችልበት ሁኔታ በመሆኑ የትዕዛዙን መሰጠት ያወቅነው በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፈጽመን እንድንቀርብ በ14/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ከደረሰን በኃላ ነው፣በ10/09/2003 ዓ.ም. ትዕዛዝ የተሰጠው የፍርድ ባለዕዳው እንደፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት በወከላቸው የሕግ ባለሙያዎች አማካይነት ቀርቦ ተገቢውን መከራከሪያ እንዲያቀርብ ሳይደረግ ከስረ ነገሩ ስምምነት ይዘት ውጪ በመሆኑ ይኸው የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲታረምልን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 ድንጋጌ መሰረት ያቀረብነው ጥያቄ በ29/11/2003 ዓ.ም. ተቀባይነት ያጣውም አላግባብ ነው፣ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የይግባኝ ጊዜው አልፎበታል በማለት የያዘው አቋምም የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207  እና 320 (2) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው በማለት ሲሆን ተጠሪዎቹ በበኩላቸው በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዙ የተሰጠው የፍርድ ባለዕዳው ተወካዮች ጭምር ባሉበት እና ክርክራቸውንም ካሰሙ በኃላ ነው፣ ዳኛው ከችሎት እንዲነሱ የፍርድ ባለዕዳው በ10/09/2003 ዓ.ም. ጥያቄ ያቀረበውም በዕለቱ የተሰጠበትን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ዳኛው በችሎት ከገለጹ በኃላ ነው፣ትዕዛዙም ሊለወጥ ወይም ሊታረም የሚገባው በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንጂ በዚያው ትዕዛዙን በሰጠው ፍርድ ቤት ባለመሆኑ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ አልፎአል

www.abyssinialaw.com

በሚል በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ሊነቀፍ አይገባውም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ዳኛው ከችሎት እንዲነሱ በ10/09/2003 ዓ.ም. አቤቱታ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እስከ 14/11/2003 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ በመዝገቡ ላይ የተለያዩ ትዕዛዞች ሲሰጡ የቆዩት ዳኛው ከችሎት እንዲነሱ ከቀረበው ጥያቄ ጋር በተያያዘ ጉዳይ መሆኑን የከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡አመልካች በ10/09/2003 ዓ.ም. የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሰጠብኝ መሆኑን ያወቅሁት በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፈጽሜ እንድንቀርብ በ14/11/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ከደረሰኝ በኃላ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካቹ ጉዳዩን በማየት ላይ የነበሩት ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ በ10/09/2003 ዓ.ም. ጥያቄ ያቀረበው ዳኛው የአፈጻጸም ትዕዛዙን ከሰጡ በኃላ እና የትዕዛዙን መሰጠትም እያወቀ ስለመሆኑ ዳኛው ከችሎት እንዲነሱ በ10/09/2003 ዓ.ም. አዘጋጅቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 8ኛ የፍትሐብሔር ቀጥታ ክስ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ በግልጽ እና በማያሻማ ሁኔታ የሚያረጋግጥ በመሆኑ ዳኛው ከችሎት እንዲነሱ ጥያቄ ያቀረብኩት የአፈጻጸም ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት እና የትዕዛዙን መሰጠት ሳላውቅ ነው በማለት አመልካቹ ያቀረበው የክርክር ነጥብ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተደረገውን የክርክር ሂደት መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የፍርድ ባለዕዳው እንደ ዕርቅ ስምምነቱ የማይፈጽምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ተጠርቶ በቀረበበት ቀን የፍርድ ባለዕዳውን ወክለው የቀረቡት ስራ አስኪያጅ ናቸው የተባሉት አቶ ምኒልክ ሙሉዓለም እና ሁለት ጠበቆች መሆናቸው አላከራከረም፡፡በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው የቃል ክርክር እንደ ስምምነቱ የማይፈጽምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ የፍርድ ባለዕዳው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠርቶ ምክንያቱን በጠበቆቹ አማካይነት እያስረዳ በነበረበት ሂደት ከፍርድ ባለዕዳው ጠበቆች አንዱ ከችሎት እንዲወጡ በችሎቱ ታዘው መውጣታቸውን እና ሌላኛው ጠበቃም እንዲቀመጡ ታዘው መቀመጣቸውን በመግለጽ የአመልካቹ ጠበቆች እና ተወካዮች የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎቹ በበኩላቸው አንዱ ጠበቃ ከችሎት የወጡት በራሳቸው አነሳሽነት እንጂ በችሎቱ ትዕዛዝ እንዳልሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡የፍርድ ባለዕዳው ሁለቱ ጠበቆች ረዥም ንግግር በማድረግ ንግግር ሊያቆሙ ባለመቻላቸው እንዲቀመጡ እና ስራ አስኪያጁ አቶ ምኒልክ ሙሉዓለም ባለዕዳው እንደፍርዱ የማይፈጽምበትን ምክንያት እንዲያስረዱ የተደረገ ስለመሆኑ ዳኛው ከችሎት የሚያስነሳቸው በቂ ምክንያት አለመኖሩን ገልጸው በ12/09/2002 ዓ.ም. በሰጡት ትዕዛዝ ላይ ገልጸዋል፡፡

በመሰረቱ የአፈጻጸም ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርድ እንዲፈጸም ትዕዛዝ የሚሰጠው የፍርድ ባለዕዳውን ጠርቶ ከመረመረው በኃላ እንደፍርዱ

www.abyssinialaw.com

የማይፈጸምበት ምክንያት አለመኖሩን ካረጋገጠ በኃላ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 392 (1) ላይ ተመልክቶአል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ለሚደረግ ምርመራ የሚሰጠው ምላሽ ደግሞ የፍሬ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሕግ ጭምር ሊሆን እንደሚችል የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁኔታዎች ተገናዝበው ሲታዩ በሕግ ጠበቆቹ ሳልወከል በቁጥር 392 (1) የተደረገው ምርመራ መሰረት ተደርጎ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠብኝ ትዕዛዝ ከስነ ስርዓት ውጪ በመሆኑ በቁጥር 320 (2) ድንጋጌዎች 207 ድንጋጌ መሰረት ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት በዚያው ፍርድ ቤት ሊታረም የሚገባው ነው የሚል በፍርድ ባለዕዳው ላይ እምነት ሊያሳድሩበት የሚችሉ አይደሉም ከሚል የተረጋገጠ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ ሆነው አልተገኙም፡፡ጉዳዩም የስረ ነገር ሳይሆን የአፈጻጸም ክርክር ነው፡፡አመልካቹ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲታረምለት የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 207 ድንጋጌን ጠቅሶ በጽሁፍ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው አቤቱታ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክተው ነገር ባይኖርም በ28/11/2003 ዓ.ም. ግራ ቀኙ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስመዘገቡት ክርክር ይዘት ሲታይ አመልካች በዚህ ረገድ በቃል ክርክሩም ቢሆን ጥያቄ አቅርቦ የነበረ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ፍርድ ቤቱ በ29/11/2003 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በ10/09/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ትዕዛዝ ሊታረም የሚችለው በበላይ ፍርድ ቤት እንጂ በራሱ በዚህ ፍርድ ቤት አይደለም የሚል ይዘት ያለው ትችት ማስፈሩም አመልካቹ የእርማት ጥያቄ ማቅረቡን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ የነበረ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ በ10/09/2003 ዓ.ም. በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው መቆጠር መጀመር የሚገባው ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በዚያው ፍርድ ቤት ሊታረም የማይችል መሆኑን ገልጾ በቀድሞው ትዕዛዝ መሰረት እንዲፈጸም ትዕዛዝ ከሰጠበት ከ29/11/2003 ዓ.ም. ነው፡፡ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ይግባኙ የቀረበው በሕግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ነው፡፡

ሲጠቃለል ይግባኙ የቀረበው የይገባኝ ማቅረቢያው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. ይግባኙ የቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኃላ በመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 71612 በ30/03/2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ከላይ በውሳኔው ዝርዝር ውስጥ በተገለጸው መሰረት የይግባኝ ጊዜው ያላለፈ መሆኑን በመገንዘብ የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ጉዳዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 110681

ቀን 08/04/2008 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሀዋ ጀሬ ተወካይ ታጁ ጀሬ

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ ቀንጨራ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ሰጥተናል**

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን ቀደም ሲል በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረውን የባልና ሚስት ክርክር ተከትሎ የተሰጠውን የፍቺ እና የንብረት ክፍፍል ውሳኔ መሰረት በማድረግ ተጠሪ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ሞያሌ ወ/ፍ/ቤት የንብረት ክፍፍል ውሳኔን ለማስፈጸም የአፈጻጸም አቤቱታ አቅርበው የአፈጻጸም መዝገብ አስከፈተዋለው፡፡ የአፈጻጸም ችሎቱ የቤቱን ደርሻ ክፍፍል በተመለከተ ግራ ቀኙ ስላልተሰማሙ ቤቱ በግልጽ ጨረታ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ በሚፈቅድው መሰረት ተገቢው ማስታወቂያ ተደርጎ በጨረታ ተሸጦ እኩል እንዲካፈሉ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የጨረታውን ውጤት ለመጠባበቅ በተያዘው ቀጠሮ በቀን 21/01/2007 ዓ/ም ጨረታውን እንዲያስፈጽም የታዘዘው የከተማው አስተዳደር መሐንዲስ ፍ/ቤት በአካል ቀርቦ ለጨረታ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ብዙ ተወዳዳሪዎች ስላልቀረቡ እና በስህተት የጨረታ መነሻ ዋጋ ስላላወጣን ሌላ ቀጠሮ ይሰጠን በማለት ለአፈጻጸም ችሎቱ ሲያመለከት ችሎቱ የቤቱን የጨረታ መነሻ ዋጋ ብር 140,500 (አንድ መቶ አርባ አምስት መቶ ብር) ሆኖ ግልጽ ጨረታ በማወጣት ለ10 ቀን ማስታወቂያ አየር ላይ አቆይቶ ቤቱን በጨረታ በመሸጥ ውጤቱ በቀን 21/01/2007 ዓ/ም እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ቤቱ በጨረታ በብር 210,000 (ሁለት መቶ አስር ሺህ

www.abyssinialaw.com

ብር) አሸናፊ ለሆኑት አቶ መሐመድ ጀሎ መሸጡን የጨረታ ኮሚቴም በቀን 16/3/07 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ ጉባኤ ለፍ/ቤቱ አስታወቋል፡፡ በቃለ ጉባኤው ላይ የአሁኑ አመልካችን ጨምሮ 3 ተወዳዳሪዎች ቀርበው አቶ መሐመድ ጀሎ በብር 210,000 ያሸነፉ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን ተጠሪ ደርሻቸውን ብር 105,000 በማመልከቻ ላይ ፈርሞ መወሰዱን እና የአሁኑ አመልካች ድርሻ ገንዘባቸው ሌሎች እኩል ተከፈሉ የተባሉ ዕቃዎች ግምት እስከከፈለኝ ድረስ ይህን ገንዘብ አልወሰደም ማለታቸው ስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ ቤቱን በጨረታ በአሸናፊው አቶ መሐመድ ጀሎ ስም እንዲዛወር ችሎቱ ተዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች (የስር የአፈጻጸም ከሳሽ) በዚህ አፈጻጸም ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለማሳረም ለቦረና ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራካረ በኂላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን በመዘርዘር አቤቱታ አቅርበዋል የአቤቱታው ይዘት በጨረታው ለማስተፍ ለስር ፍ/ቤት አመልካች ፍ/ቤቱ ፈቅደልኝ ተሳትፈያላው የሞያሌ ወ/ፍ/ቤት የጨረታ ማስታወቂያ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ቆይቶ የጨረታው ሽያጭ እንዲካሄድ ማዘዝ ሲገባው ለ10 ቀን ብቻ አየር ላይ ማሲታወቂያው እንዲቆይ የሰጠው ትእዛዝ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.426 ውሳኔ ነው አመልካች ከጨረታ መነሻ ዋጋ ላይ በመጨመር 300,000 ብር ግምት የተጠሪን ድርሻ ብር 150,000 ካፍዬ ቤቱን እንዳሰቀር ለሐራጀ ሻጩ የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ከማወጣቱ በፊት አስቀደሜ አስወቂው እያለ ያለ ምንም የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ በጨረታ ተወዳዳር ለአሸነፈው ሰው በብር 210,000 መሸጡ የጨረታ ሽያጭ ሂደቱ ስነ ስርዓቱን ያልተከተለ እና የተጭበረበረ በመሆኑ መብቴን የሚጎዳ ነው፡፡ የተጠሪን ድርሻ ብር 150,000 ከፍዬ ብር 300,000 ግምት ቤቱን ለማስቀርት ጨረታው ይፍረስልኝ ብዬ ያቀረብኩትን መቃወሚያ ያለበቂ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የማይነቀሳቀስ ንብረት የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ለ30 ቀናት አየር ላይ እንዲቆ መደረግ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.426 አስገዳጅ ደንጋጌ እያለ የስር ፍ/ቤት ማስታወቂያው ለ 10 ቀን አየር ላይ እንዲቆይ ማደረጉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት የቤቱ የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ከአንድ ወር በላይ አየር ላይ ቆይቷል፡፡ አመልካች በጨረታው ለመወዳደር ያቀረበችው ብር 150,000 ብቻ ነው የሚል ሲሆን አመልካች በመልስ መልሳቸው አመልካች ብር 150,000 በጨረታው ላይ የጠቀሰኩት የተጠሪን ድርሻ እንጂ

www.abyssinialaw.com

ሙሉውን የጨረታ ዋጋ አይደለም፡፡ የመጀመሪያው ጨረታ ማስታወቂያ የቆየው ለ15 ቀን ሲሆን የሞያሌ ከተማ መሀንዲስ ተለዋጭ ትእዛዝ እንዲሰጠው ለስር ፍ/ቤት በጠየቀው መሰረት የጨረታ ማስታወቂያው ለ10 ቀን አየር ላይ እንደወል ትእዛዝ የሰጠ መሆኑን የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የሰር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ እንዲጣራ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክር ምክንያት በሆነው የቤት ሽያጭ ጨረታ ላይ አመልካች ፍ/ቤቱን አስፈቅደው በጨረታው የተሳተፉ ሲሆን በጨረታው ከተሳተፉ ተጨርቶች መካከል አቶ መሐመድ ጅሎ የተባሉ ተጨራች በብር 210,000 ጨረታውን ያሸነፉ መሆኑን እና አመልካቿ በጨረታው ሲሰተፉ ቤቱን በጨረታ ለመግዛት የገለጹት ዋጋ ብር 300,000 ሳይሆን ብር 150,000 ብር ነው ብር 150,000 የጠቀሱት የተጠረን ድርሻ እንደሆነ በመልስ መልሳቸው የገለጹ ቢሆንም በእርግጥም ቤቱን በ300,000 ብር በጨረታ አሸንፈው የተጠሪን ድርሻ ብር 150,000 ለመከፈል አሰበው ቢሆን በጨረታው ለመወዳደር መጥቀሰ የነበረባቸው ብር እንጂ 150,000 ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ያነሱት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የአፈጻጸም ሂደቱ በተካሄደበት የስር ፍ/ቤት ከጨረታው ውጤት በኂላ አመልካች ከቤቱ ሽያጭ ድርሻቸውም ብር 105,000 ለመወሰድ ፈቃደኛ ያልሆኑ በሰበር አቤቱታቸው ላይ እንደገለጹት ሳይሆን ሌሎች ከተጠሪ ጋር እንዲከፍሉ ውሳኔ የተሰጠባቸው ዕቃዎች ግምት እንዲከፍላቸው ድርስ ገንዘቡን አልቀበልም ማለታቸው በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተመልክቷል አመልካች ለቦረና ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የጨረታ ማስታወቂያ ለአንድ ወር አየር ላይ ሳይቆይ መሸጡን በመቃወም ሳይሆነ በጨረታው እና ብር 300,000 አቅርቤ እያለ በብር 210,000 መሸጡ ተገቢ አይደለም የተጠሪን (የመልስ ሰጪን) ድርሻ ብር 150,000 ካፍዬ ቤቱን እንድወሰድ የወሰንልኝ የሚል መሆኑን ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተመልክቷል፡፡

አመልካች አፈጻጸሙ በተጀመረበት ቦረና ዞን የሞያሌ ወረዳ ፍ/ቤት የጨረታ ማስታወቂያው ለአንደ ወር አየር ላይ አልቆየም በማለት የተቃወመ መሆኑን በይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት ይህን መቃወመያ ያነሱ መሆኑ በውሳኔው ላይ አልተመለከተም፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በጨረታው እንዲሳተፉ ተፈቀደላቸው በጨረታው በብር 150,000 ተወዳደረው ከአመልካች ጋር ተወዳደርው አሸናፊ ለሆነው ተጨራች በብር 210,000 መሸጡን አረጋግጠናል አመልካች በስር ፍ/ቤቶች በነበራቸው ክርክር የጨረታ ማስታወቂያ ለአንድ ወር አየር ላይ አልቆየም በማለት ያነሱት መቃወሚያ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተመለከተ ባይሆንም

www.abyssinialaw.com

አንስተወት እንኳ ቢሆን በአመልካቿ መብት ላይ ቀጥታ ጉዳት ያደረሰ ወይም የሚያደርስ መሆኑ አልተረጋገጠም በመሆኑም በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.445 መሰረት ጨረታ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን የሞያሌ ወ/ፍ/ቤት በፋ/ቁ. 04295 ከፍ/ፍ/ቤት በፋ/ቁ.10915 በቀን 25/04/2007 ዓ/ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፋ/ቁጥር 199719 በቀን 17/06/07 በዋለ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ላደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጪ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገብ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ በቀን 8/07/2007 ዓ/ም በዋለ ችሎት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል ይጻፍ ብለናል መዝገቡ ዕልባት ያገኘ በመሆኑ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

›

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ. 103787

ቀን ታህሳስ 21/2008ዓ.ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- የኢት/ያ ገ/ጉ/ባለስልጣን ሚሌ ቅ/ጽ/ቤት -ዓ/ሕግ መለስ ማእከል

ተጠሪ፡- ፉአድ ደኑር ሁሴን -ወኪል ጠይብ አህመድ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፤ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ በግራቀኙ መካከል በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ምክንያት ያቀረቡትን ክርክር የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ አመራርም ሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ዳኝነት አፈጻጸም ፍርድን መሰረት ሊያደርግ እንደሚገባ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ በአፋር ብ/ክ/መንግስት የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም እንደሆነ ግራቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡

በዚህም ውሳኔ የአሁን ተጠሪን ባለመብት፤ የአሁን አመልካችን ባለዕዳ ለማድረግ የሚያስችለው በዚሁ በፍ/መ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠው የፍርድ ክፍል የአሁን ተጠሪ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባቸው ፈቃድ አግኝቶ በዲክላራሲዮን ለተዘረዘሩት 9አይነት እቃዎች 5አይነት እቃዎች ካርታ ከተፈቀደ እቃዎች ውጭ በመሆናቸው ወደ ሃገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ አይደለም፡፡ ስለሆነም አሁን አመልካች በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጠቅሞ ተገቢ የሆነውን አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ይህንን የማይፈጽም ከሆነ ደግሞ ቀደም ሲል ለእቃዎቹ ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ 5% ተቀጥቶ እቃዎች ወደ መጡበት ሃገር እንዲመለሱ የአሁን ተጠሪ

www.abyssinialaw.com

በዲክላራሲዮኑ መሰረት ያስገባቸው በዲክላራሲዮኑ የተዘረዘሩት ህጋዊ እቃዎች ደግሞ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ በሚል የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

ይህ ውሳኔ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ያልተለወጠ ስለመሆኑም ግራቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ ነው፡፡

እንግዲህ ለዚህ ሰበር መነሻ ለሆነው በአፈጻጸም መ/ቁ. 4043 ለሆነው የአፈጻጸም ጉዳይ ምክንያት የሆነው ይህንኑ ከላይ የተመለከተውን ፍርድ ለማፈጸም እስከሆነ ድረስ በዚሁ ፍርድ የፍርድ ባለመብት የሆነው የአሁን ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ሆኖ በተሰየመው በአሁን አመልካች ላይ ሊያቀርብ የሚገባው የፍርድ ማስፈጸሚያ አቤቱታ ይዘት ይህንኑ ከላይ የተጠቀሰውን ፍርድ ለማስፈጸም የፍርዱን ይዘት በአፈጻጸም ማመልከቻው ላይ በመግለጽና የፍርዱንም ግልባጭ በማስረጃነት በማያያዝ ሊሆን እንደሚገባው የአፈጻጸም ክስ አዘጋጀጀት እና የአፈጻጸም ክስ ጉዳይ አጀማመርን አስመልቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 የተመለከተው ድንጋጌ አስረጂ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአፈጻ/መ/ቁ. 4043 ተሰይሞ ለቀረበው የአፈጻጸም ጉዳይ መነሻ ይሆን ዘንድ የአሁን ተጠሪ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 በሚያዘው መሰረት ታህሳስ 04ቀን 2006ዓ.ም በተጻፈ የአፈጻጸም ክስ ማመልከቻ ያቀረበው የአፈጻጸም ክስ አቤቱታ ይዘት ወይም ፍሬ ቃሉ በአፈጻጸም ክሱ ምክንያት የሆነውን ፍርድ ይዘት የሚጠቅስ፤ በማስረጃነትም ይህንኑ የፍርድ ግልባጭ አባሪ በማድረግ መሆን ሲገባው በዚሁ ታህሳስ 04ቀን 2006ዓ.ም በተጻፈው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ የተገለጸው ከፍርዱ ውጭ በፍርድ ያልተካተተውን ሁሉ በመጨመር <<በስህተት ወደ አገር ውስጥ ለገቡት እቃዎች የተከፈለው 5% ቀረጥና ታክስ የፍርድ ባለመብት ተቀጥቶ እቃዎቹ ወደመጡበት አገር እንዲመለሱ እንዲሁም የአሁን አመልካች በሰጠው ፈቃድ (declaration) መሰረት ቀሪ ህጋዊ እቃዎችን ወደ ሃገር ውስጥ እንዲያስገባ የተወሰነልን ቢሆንም በስህተት ወደ ሃገር ውስጥ የገቡት እቃዎች በተከሳሽ እምቢተኛነት በአፋጣኝ ወደ መጡበት ሃገር ባለመመለሳቸው፡፡ በፍርድ ባለዕዳ እጅ የሚገኙት እቃዎች የተበላሹ በመሆኑ የወቅቱ የእቃዎች ዋጋ ተገምቶ ገንዘቡን እንዲከፍል ይታዘዝልኝ>> በማለት የቀረበ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በፍርድ ባለመብት አማካኝነት የተፈረደን ፍርድ ለማስፈጸም የቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ ይፈጸም የተባለውን ፍርድ መሰረት ሊያደርግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይኸው ፍርዱን መሰረት ያላደረገ የአፈጻጸም ማመልከቻ መቅረቡን እንደተረዳ የአፈጻጸም ችሎቱ የፍርድ ባለእዳን ከመጥራቱ በፊት ይህንኑ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ የአፈጻጸም ማመልከቻ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ማድረግ ይገባው ነበር፡፡

ይህም ታልፎ የአሁን አመልካች በፍርድ ባለእዳነቱ መልስ እንዲሰጥ እንደተጣራ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 386 እንደተመለከተው እቃዎቹ ያልተበላሹ፣ እንዲሁም እቃዎች ወደ

መጡበት ሃገር አንዲመልሱ እንጂ በፍርድ ባለመብት እንዲወሰዱ በሚል ባልተወሰነበት ሁኔታ የእቃዎችን ግምት መጠየቃቸው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ማሰባቸውን የሚያመለክት ነው የሚለውን ሁሉ ጨምሮ መልሱን በይዘቱ የአፈጻጸም ማመልከቻው ፍርዱን መሰረት ያደረገ ስላልሆነ እንደጥያቄው እንዲፈጸም አልገደድም በማለት መልሱን የሰጠ መሆኑንም የስር ፍ/ቤቱ እንደተረዳ የአፈጻጸም ማመልከቻውን፤ ለማመልከቻው በፍርድ ባለእዳው የተሰጠውን መልስ፣ በአፈጻጸሙ ጉዳይ ምክንያት ከሆነው በመ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም ከተሰጠው የፍርድ ይዘት ጋር በማገናዘብ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃም ቢሆን የፍርድ ባለመብት በአፈጻጸም ችሎቱ እገዛ እንዲፈጸምላቸው በክስ ማመልከቻው ያቀረቡት ዝርዝር እና የጠየቁት ዳኝነት ለፍርዱ አፈጻጸም መነሻ የሆነውን ፍርድ ምርኩዝ ያላደረገ መሆኑን ገልጾ ዳኝነት መስጠት ሲገባው ከፍርዱ አድማስ ውጭ በመውጣት እቃዎች ተበላሽተው የተገኙ ከሆነ የፍርድ ባለእዳ በምትኩ የእቃዎችን ግምት ዋጋ ሊከፍል ይገባል በሚል በአማራጭ ፍርድ ያረፈበት በማስመሰል አሁን የአሁን አመልካች የእቃዎችን ግምት ዋጋ ብር 4,732,278.64 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ከ64%/ እና በዚሁ የገንዘብ ግምት ልክ 10% የጠበቃ አበል የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ ስለፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ አመራር ከተዘረጉት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378,386,391 አንጻር ሲታይ ህጋዊ መሰረት ያለው ዳኝነት ሆኖ አላገኘነውም።

ምናልባት የአሁን ተጠሪ በመ/ቁ. 4043 ታህሳስ 28ቀን 2006ዓ.ም በተወሰነበት ውሳኔ መሰረት እቃዎችን ወደመጡበት ሃገር ለማስመለስ በፍርድ አፈጻጸም ችሎት እገዛ ጥያቄ አቅርቦ እንደፍርዱ ለማስፈጸም ጥረት ሲደረግ ወደ መጡበት ሃገር ይመለሱ የተባሉት እቃዎች ተበላሽተዋል ካለ፤ የፍርድ ባለእዳም ለአፈጻጸም ክሱ በሰጠው መልስ ላይ አልተበላሹም በማለቱ እቃዎች ተበላሽተዋል ወይስ አልተበላሹም? የሚለውን ጭብጥ የስር ፍ/ቤት በአፈጻጸም ጉዳዩ እንደሰጠው ዳኝነት እቃዎችን በማስፈተሽ እምቢተኛ እስከሆነ ድረስ እቃዎቹ እንደተበላሹ ይቆጠራሉ እንኳ ቢባል እቃዎቹ ተበላሽተው የተገኙ እንደሆነ የሚለውን ታሳቢ በማድረግ አማራጭ ክስ ያልቀረበበት፤ በዋናው ፍርድም እቃዎቹ ተበላሽተው የተገኙ እንደሆነ የአሁን አመልካች የእቃዎችን ዋጋ ግምት እንዲከፍል ይገደዳል በሚል ፍርድ ያላረፈበት በመሆኑ ፍርድ ያላረፈበትን ጉዳይ በአፈጻጸም ክስ አስታኮ በአፈጻጸም ጉዳይ ላይ እንደአዲስ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል የህግ መሰረት የለም።

ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ለአሁን አመልካች እንደፍርዱ እቃዎችን ወደ መጣበት ሃገር እንዲመለሱ ለማድረግ እምቢተኛ በመሆኑ የተነሳ እቃዎቹ ተበላሽተው ከሆነ ይኸው ስህተት የአሁን አመልካች ከህግ ወይም ከውል በመነጨ ለመክሰስ የሚያስችል ግዴታ

www.abyssinialaw.com

ያለበት ከሆነ እራሱን ከቻለ ክስ የክስ ምክንያት ሊሆን ከሚቻል በቀር ከቶውንም ቢሆን እንደአሁን ተጠሪ አቀራረብ በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ለመወሰን የሚቻል አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን ተጠሪ ታህሳስ 04 ቀን 2006ዓ.ም አዘጋጅቶ በቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ መሰረት የስር ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸምን የጉዳይ ሂደት ለፍርድ አፈጻጸም አንኳር እና መሰረት የሆነውን አፈጻጸም እንደፍርዱ ሊፈጸም እንደሚገባ በፍርድ አፈጻጸም ስርዓት የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጥሰው ለአፈጻጸም ክሱ መነሻ ከሆነው ፍርድ ይዘት በመውጣት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአፋር ብ/ክ/መንግስት የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአፈ/መ/ቁ. 4043 መጋቢት 12ቀን 2007ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአፈጻጸሙ 4,732,278.64 /አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ሰላሳ ሁለት ሺ. ሁለት መቶ ከሰባ ስምንት ከ64%/ ሳንቲም እና በዚሁ ልክ የጠበቃ አበል 10% ጨምሮ በድምሩ ብር 5,205,504.00 /አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ አምስት መቶ አራት ብር/ የመክፈል ግዴታ ስለመሆኑ ለተጠሪ እንዲከፍል አይገደድም ብለናል፡፡
2. ወደ መጡበት ሃገር ይመለሱ የተባሉት እቃዎች በመበላሸታቸው ምክንያት እንደፍርዱ ለመፈጸም የሚቻል አይደለም ከሚል መነሻ የአሁን ተጠሪ መብቱን በማረጋገጥ ረገድ ወደ ፊት ክስ የሚያቀርብ ቢሆን ይህ ፍርድ የሚያግደው አይሆንም ብለናል፡፡
3. በዚሁ የሰበር ጉዳይ ምክንያት ግራቀኙ ባደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

www.abyssinialaw.com

# ልዩ ልዩ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁጥር 103826

ቀን 25/01/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

አመልካች፡- አንዋር አህመድ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የቤ/ጉ/ክ/መ/ፍትህ ቢሮ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአፈፃፀም ክስ ሂደትን የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ከፓዊ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የፓዊ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የፍርድ ባለመብት በመሆን በአመልካች ላይ ያቀረበው የአፈፃፀም ክስ ሲሆን ዝርዝሩም አመልካች ያለፈቃድ በማሽከርከር በቀን 12/6/2005 - 13/06/2005 ዓ.ም የትራፊክ ደንብ በመጣስ 5000 ብር የተቀጣ ስለሆነ በቅጣቱ መሰረት ይፈጽምልኝ በማለት አቅርቧል፡፡ አመልካችም ያለአግባብ ስለተቀጣሁ ልፈፅም አይገባም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የፓዊ ወረዳ ፍ/ቤት አመልካች በውሳኔው መሰረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ስለአልሆነ በስድስት /6/ ወር/ እስራት እንዲቀጣ ገንዘቡን የሚከፍል ከሆነ ደግሞ ከእስራት እንዲፈታ በማለት ይወስናል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት የስነ ስርዓት መቆጣጠሪያ መመሪያ ስራ ጥፋት ሪኮርድ አያያዝና ስለቅጣት ደረጃ በዝርዝር የሚገልፅ እንጅ ይህ ቅጣት ባልተፈፀመ ጊዜ ምን መደረግ እንዳለበት በሕጉ የተገለጸ ነገር ስለሌለ በፍ/ቤት የተሰጠ ምንም ውሳኔ ሳይኖር አመልካች እንዲፈፅም መደረጉ ትክክል አይደለም በማለት ወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለክልሉ /የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 377 መሰረት ይግባኙን በመሰረዝ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ ሲቀርብ ሰበር ችሎቱም የፓዊ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የመንገድ ትራንስፖርት መመሪያን ደንብን በመተላለፍ የቀረበበትን የአፈፃፀም ክስ ማስፈፀሙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፓዊ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኖአል፡፡

አመልካችም ለዚህ ሰበር ችሎት በቀረቡት የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለአለበት ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ምክንያት በአመልካች ላይ የተጣለውን ቅጣት በፍርድ ቤት የአፈፃፀም ክስ ሊቀርብበት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጎአል አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርመረናል፡፡ አመልካች ላይ የቀረበው የአፈፃፀም መዝገብ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ምክንያት ስራን የትራፊክ ደንብን መተላለፍ የሚገዛው ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 ነው፡፡

በዚህ ደንብ አንቀፅ 85 ስለ ቅጣቱ እና አፈፃፀሙን የደነገገ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 85/2/ መሰረት የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ ያገኘው አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን እንዲሰጠው በመጠየቅ ቅጣት እንዲፈፅም በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት በማለት ደንግጎአል፡፡ በዚህ ደንብ መሰረት ይህን አዋጅ የተላለፈ አሽከርካሪ ቅጣት ከተጣለበት አፈፃፀሙ የትራፊክ ተቆጣጣሪው በፅሁፍ በማሳወቅ የተቀጣው አሽከርካሪ እንዲፈፅም ማድረግ ነው እንጅ ለአፈፃፀም ፍ/ቤት የሚቀርብ ስለመሆኑ በደንቡ አልተቀመጠም፡፡ ከደንቡ እንደምንረዳው በትራፊክ ተቆጣጣሪው በዛ ሂደት እንዲቀጥል እንጂ ፍ/ቤት ለአፈፃፀም እንዲቀርብ አይደለም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378/1/ የተደነገገው በፍ/ቤት አፈፃፀም የሚፈፀመው ውሳኔው በፍ/ቤት የተወሰነ መሆኑን ታሳቢ የደረገ ነው፡፡ በመሆኑም የትራፊክ ፍሰትን ለመቆጣጠር ሲባል በደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 85 መሰረት የሚጣስ ቅጣት አፈፃፀሙ በፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችል መሆኑን የሚደነግግ ሕግ የለም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ በተጠሪ በኩል የቀረበውን የአፈፃፀም ማመልከቻ ውሳኔው በፍ/ቤት ባልተሰጠበት ሁኔታ እንዲሁም በደንብ ቁጥር 208/2003 አፈፃፀሙ ለፍ/ቤት መቅረብ እንደአለበት ሳይደነግግ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ

www.abyssinialaw.com

ቤት ሰበር ችሎት በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተጣለው ቅጣት በፍ/ቤት ሊፈፀም ይገባል በማለት የወሰነው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብለን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 05033 ሚያዝያ 27/2006 በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የፓዊ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06041 በቀን 22/09/2005 በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በማፅናት የወሰነውን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመከተል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09 በቀን 28/10/2005 በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ /በአብላጫ ድምፅ/ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. እዚህ ፍ/ቤት ለተካሄደው ክርክር ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊረማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ 103458

ቀን 27/01/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ተፈሪ ገብሩ

ሹምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ጋረድ ለበሰ

ተጠሪ፡- የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጡረታ መብትን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በተለየዩ መ/ቤቶች ለ17 ዓመት እና በአ/ብ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊ ሆነው ለ10 አመት አገልግለው በራሳቸው ጥያቄ ከሹመት የተነሱ መሆኑን በአዋጅ ቁ 714/2003 አንቀፅ 19/5/ መሰረት ከአንድ የምርጫ ዘመን ያገለገሉና ዕድሜያቸው ከ50 አመት በላይ በመሆኑ የጡረታ መብታቸው እንዲከበርላቸው አሰሪ መ/ቤታቸውን ጠይቀው የተሰጣቸው ምላሽ ፍትሐዊ አለመሆኑን ገልፀው ቅሬታቸውን ለሰሜን/ምዕ/ሪጅን ማ/ዋ/ኤጀንሲ አቅርበው ኤጀንሲው አመልካች ስራቸውን የለቀቁት በራስ ፈቃድ በመሆኑ በአ/ቁ 714/2003 አንቀፅ 19/3/ መሰረት ዕድሜያቸው 55 አመት ሲሞላ ከየካቲት 1/2010 ጀምሮ የጡረታ አበል የሚወሰንላቸው መሆኑን ኮሚቴው የወሰነ ሲሆን፡-

በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅሬታቸውን ለማህበራዊ ዋሰትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ አቀርበው የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋሰትና ኤጀንሲ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት ያፀናው መሆኑን ከቀረበው የአመልካች አቤቱታ እና ውሳኔዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አቀርበው ይግባኝ የተባለበት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁጥር 337 የዘጋው ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ተፈፀመ ያሉትን ስህተት በመዘርዘር በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታረምላቸው አቅርበዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለው ከአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 172/2002 አንቀፅ 3/1//ሀ/ አንፃር አመልካች የጡረታ ይከበርልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በሰበር ለመመርመር ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት የስር ፍ/ቤቶች ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 19/3/ ለመንግስት ተሿሚዎች የሚያገለግል ሣይሆን ከሹመት ውጭ በመንግስት ሰራተኞች ሲያገለግሉ ለነበሩ ሰራተኞች ነው የተጠቀሰው አንቀፅ በፌዴራል ልዩ የተሿሚዎች አዋጅ ቁጥር 653/2001 እና በአማራ ክልል ዝክረ ሕግ አዋጅ ቁጥር 172/2002 በተለየ ሁኔታ መብት የተሰጣቸውን የመንግስት ኃላፊዎች የማይመለከት በመሆኑ ይህ ድንጋጌ ከዝክረ ሕግ አዋጅ ቁጥር 172/2 አንቀፅ 3/1//ሀ/ ጋር ተጣምሮ ሊተረጎም የማይገባው ሆኖ ሣለ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት የሕግ ትርጉም መሰረታዊ ስህተት ስላለበት ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 172/2002 አንቀፅ 3/1//ሀ/ ከመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀፅ 62/2/ መሰረት የሚቃረን ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በአዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀፅ 2/1/ የመንግስት ሰራተኛ ማለት የመንግስት ተሿሚዎችንም የሚያካትት መሆኑ ተመልክቷል የጡረታ መብትና ጥቅምን በተመለከተ የክልሉ አዋጅ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁ. 714/2003 ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የመንግስት ሰራተኞች ጡረታን በተመለከተ ስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 714/2003 ሲሆን በዚህ አዋጅ ትርጓሜ አንቀፅ 2/1/ ላይ የመንግስት ሰራተኛ በመንግስት መ/ቤት በቋሚነት በመቀጠር ደመወዝ እየተከፈለው የሚሰራ ሰው ሲሆን የመንግስት ተሿሚዎች፣ የምክር ቤት አባላትንና የመከላከያ ሰራዊት አባላትን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡ በአንቀፅ 2/2/ "ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ" ማለት ሚኒስቴር፣ሚኒስቴር ዲኤታ ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የመንግስት ኃላፊ ነው በሚል የተመለከተ ሲሆን በአንቀፅ 2/6/ "መንግስት" ማለት በኢፌዴሪ መንግስት እና የክልል መንግስታትን እንደሚያጠቃልል በአንቀፅ 2/7/ ደግሞ "ክልል" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብትና ጥቅም ለመጠበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀፅ 12 እና 21 የጡረታ መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአዋጅ 714/2003 አንቀፅ 62/1//ሐ/ የተሻሩ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች ወይም የአሰራር

www.abyssinialaw.com

ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም በማለት ተመልክቷል፡፡ የአ/ብ/ክ/መ/አዋጅ ቁጥር 172/2002 ቀደም ብሎ የወጣ ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች የጡረታ መብት ጥያቄ መታየት ያለበት የጡረታ መብትን አስመልክቶ በወጣው ልዩ ሕግ በመንግስት ሰራተኞች  የጡረታ ሕግ አዋጅ ቁ. 714/2003 እንጅ በአ/ብ/ክ/መ/በወጣው ዝክረ ሕግ አዋጅ ቁጥር 172/2002 አይደለም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 19/5/ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊን ወይም የምክር ቤት አባልን የሚመለከት ሲሆን ለከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በአዋጅ ትርጓሜ ክፍል ከተሰጠው ትርጉም አንፃር አመልካች ይህን የሚያሟሉ ባለመሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 19/3/ መሰረት በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ የሰበር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅሟል የሚባል አይደለም ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሰሜን ምዕ/ሪጅን ማ/ዋ/ኤጀንሲ በቀን 8/6/2005፣ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በቁጥር ጡ/ይ/1/1/92/2006 በቀን 17/08/2006 የሰጡት ውሳኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 100266 በቀን 11/09/2006 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ላደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ/104512

መስከረም 24 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

**አመልካች፡-** አቶ አባስ ኢብራሂም ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የሐረር ቢራ አ/ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንብረት ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የጀመረው ያሁን አመልካች በሀረሪ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በሰበር ተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፡- ተጠሪ ኮስቲክ ሶዳና ሃይድሮሊክ አሲድ የተባለ መርዛማነት ያለው ተረፈ ምርት በእርሻ ማሳዬ ላይ አፍስሶ የተለያዩ ቋሚ ተክሎችና ሰብሎቹን በማድረቅ ስላወደመብኝ በዚህ ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት በድምሩ ብር 1,526,700 ካሳ ይከፈለኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ፡- በክሱ የተጠቀሰውን መርዛማ ኬሚካል በአመልካች ማሳ ላይ አለማፍሰሱን፣ ያም ሆኖ ግን የድርጅቱን ፍሳሽ ወይም ተረፈ ምርት የክልሉ አርሶ አደሮች ለእርሻ ማሳቸው በማዳባሪያነት ጠቃሚነቱን ተረድተው እንዲደፋላቸው በጠየቁት መሰረት የተደፋላቸው መሆኑን፣ ተረፈ ምርቱም ለእርሻ ማሳ ማዳበሪያነት ጠቃሚ መሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ በሐሮሚያ ዩኒቨርስቲ እየተካሄደ ያለው ጥናትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ መሆኑንና የጉዳት ካሳ መጠኑም የተጋነነ ነው የሚልና የመሳሰሉትን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ቃል ከሰማ በኃላ በተጨማሪነትም ከክልሉ አካባቢና ጥበቃ ባለስልጣን ጽ/ቤትም ባለሙያ አስቀርቦ በጉዳዩ ላይ ሙያዊ አስተያየቱን ከተቀበለ በኃላ ጉዳዩን መርምሮና ማስረጃውንም ከመዘነ በኃላ የተጠሪ ተረፈ ምርት በአመልካች ማሳ ላይ መፍሰሱን፣ይህንን ተከትሎም ተክሎችና ሰብሎቹ በመድረቅ ጉዳት የደረሰባቸው

www.abyssinialaw.com

መሆኑን፣ ለዚህም ጉዳት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 300/95 አንቀጽ 4 /1/ ና ፍ/ብ/ህግ/ቁ/2035 መሰረት ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና የደረሰውን ጉዳት መጠንም ብር 145,840 መሆኑን መረጋገጡን ከገለጸ በኃላ በሌላ በኩል ደግሞ ተረፈ ምርቱንም አመልካች እራሱ እንዲደፋለት በጠየቀው ጥያቄ መሰረት በማሳው ላይ እንዲደፋ መደረጉንና እንዲሁም አመልካችም ሌሎች አርሶ አደሮች እንደሚያደርጉት ተረፈ ምርቱ የሚያመጣውን ጉዳት ለማስቀረት ፍሳሹን በየጊዜው በመጥረግ የበኩሉን አስተዋፅዖ ማድረግ ሲገባው ይሄንን አለማድረጉም በምስክሮች ቃል መረጋገጡን ገልፆና ይህም በአንድ ላይ ተገናዝቦ ሲታይ ክፊሉ ጉዳት ራሱ በአመልካች ጥፋት መድረሱን መገንዘቡን በውሳኔው በማስፈርና ይህንኑም በካሳ ክፋያ አሰላሉ ሂደት ከግምት ውስጥ ማስገባቱን ጭምር ከገለጸ በኂላ ተጠሪ ከብር 145,845 ውስጥ የበኩሉን የኃላፊነት ድርሻ 100,00፣ የጠበቃ አበል10% /10,000/ እና የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ብር 3,350 ጋር ለአመልካች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አሁን ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የተጠሪ ተረፈ ምርት በእርሻው ማሳው ላይ እንዲደፋ መፍቀዱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለደረሰው ጉዳት እሱም አስተዋፆ አለበት ተብሎ ሊከፈለው ከሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ውስጥ ብር 45,840 ተቀንሶ እንዲከፈለው የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎና ለተጠሪም በህጉ መሰረት መጥሪያ እንዲደርሰው ቢደረግም ባለማቅረቡ በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ ጉዳዩ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 300/95 አንቀጽ 4/1/ ስር በግልጽ ተደንግጎ እናገኛለን ፡፡ ከዚህም መገንዘብ እንደሚቻለው አስቀድሞ የአካባቢው ጥበቃ መስሪያ ቤት ሳያስፈቅዱ የፋብሪካ ውጤት የሆነውን መርዛማነት ያለው ተረፈ ምርት ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ማጓጓዝ ወይም ማስወገድ በህጉ የተከለከለ ተግባር መሆኑን ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ቆሻሻ ውሃ የተቀላቀለበትና መርዛማነት ያለው ተረፈ ምርት በአመልካች ማሳ ላይ ማፍሰሱና ይህንንም ያደረገው ያለ አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፍቃድ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ፍሳሹም በአመልካች ሰብሎችና አትክልቶች ላይ ጉዳት በማድረሱ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 300/95

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 4/1/ እና ፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2035 መሰረት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት እንዳለበት በስር ፍ/ቤት ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ግን የስር ፍ/ቤት ተረፈ ምርቱ እንዲደፋ አመልካችም በመፈቀዱና እንዲሁም ተረፈ ምርቱ በእርሻ ውጤቶች ምርት ላይ የሚያመጣውን ጉዳት ለማስቀረት አመልካችም ያደረገው ጥረት ባለመኖሩ እሱም ከዚህ አንፃር ላደረሰው ጉዳት አስተዋፅዖ አድርጓል በሚል ምክንያት ሊከፈለው የሚገባውን የካሳ መጠን በፍ/ብ/ህ/ቁ/2098 መሰረት ቀንሶበታል፡፡ ይሁንና ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የፋብሪካ ተረፈ ምርት የሚደፋበትን ቦታ ለመፍቀድ በህግ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው ለአካባው ጥበቃ መስሪያ ቤት እንጂ ለግለሰቦች አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ተረፈ ምርቱን በማሳ ላይ የደፉሁት አመልካችን ጨምሮ ሌሎች የክልሉ አርሶ አደሮች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ከዚህ አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፋብሪካው ተረፈ ምርት በሰብል ምርቱ ላይም ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ጉዳትም አመልካች እንደ አርሶ አደርነቱ ያውቃል ወይም ሊያውቅ ይገባ ነበር በሚል ደምዳሚ ግምት መውሰድም የሚችል አይሆንም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የጉዳቱን ውጤት እንዴት እንዲቀንስ ማድረግ ይችል እንደነበርም በዚህ ረገድ ክርክሩ በግልጽ በተጠሪ ቀርቦና በማስረጃም ባልተረጋገጠበትና እንዲሁም አመልካችም በዚህ ረገድ ከቅን ልቦና ውጪ እንቅስቃሴ ማድረጉም ተጠሪ ባላስረዳበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህ/ቁ/2098/1/ ድንጋጌ መሰረት እሱም ለጉዳቱ አስተዋፅዖ አድረርጓል ተብሎ በዚህ ምክንያት ሊከፈለው ከሚገባው የካሳ ክፍያ መቀነሱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ከዚህ አንፃር የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሐ/ሕ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 02554 በ 6-8-2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማጽናት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኮ/መ/ቁ/101454 በ17/10/2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካች ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ሙሉ ሐላፊነት አለበት ብለናል፡፡ ስለሆነም በስር ፍ/ቤቶች ከተወሰነው በተጨማሪ ብር 45,840 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ተብሏል፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

www.abyssinialaw.com

የሰ/መ/ቁ.109535

የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

**አመልካች፡-** ሳልቫቶሪ ዴበታኮምፕሌክስ ጠበቃ ንጉሸ በልሁ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሀብታሙ አባዲ ጠበቃ ታየ ወጂ ቀረቡ

**መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰትተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የደለላ አበል ክፍያ የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ቀራንዮ ምድብ ችሎት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁነ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በነበረው የቆየ የኮሚሽን ስራ ግንኙነት በቃል በደረጉት ስምምነት የአመልካች ንብረት የሆነው አንድ ቪላ መኖርያ ቤት ተከራይ ፈልገው እንዲያካራዩላቸው በተለመደው የኮሚሽን ክፍያ አሰራር መሰረት የአንድ ወር የኪራይ ገቢ በኮሚሽን መልክ ለተጠሪ እንደሚከፈሉ በዚህም በተደጋጋሚ በተደረገው ጥራት ቤቱ ጳጉሜ 02 ቀን 2005 ዓ/ም የሮያል ኖረዊጂን ኤምበሲ ቤቱን ለጽ/ቤቱ አገልግሎት በወር 20,000 ዶላር ሂሳብ ኪራይ በመስማማት መስከረም 23 ቀን 2006 ዓ/ም የ10 ዓመት ኪራይ ውል ስምምነት በመፈራረም ተከራዩ የአንደኛ ኣመት ቅደመ ክፍያ 4,540,800 ብር ለአመልካች የከፈለ ሲሆን አመልካች ግን በስምምነቱ መሰረት መክፈል የሚጠበቅባቸው የአንድ ወር ኪራይ ሒሳብ ለመክፈል ፈቃደኛ በለመሆኑ የኮሚሽን ክፍያ 378,400.00 ብር ከመስከረም 2006 ዓ/ም ከሚተሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍላቸው ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሰይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚ እና በፍሬ ነገሩ መልስ አቅርበዋል፡፡ የመጀመሪያ መቃወሚያ በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የግዘት ስልጣን እንደሌለው ቤቱም የራሰቸው አለመሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ከኖርዋይ ኤምበሲ በተደረገው የኪራይ ውል ስምምነት ተጠሪ ሳይሆን እንግልዝኛው ዴቪድ ዊልስ የተበሉ የረዱዋቸው ስለ መሆኑ የቆየ ግንኙነት እንደልነበራቸው በመካከላቸው ውል የለም እንጅ ውል አለ ከተባለ መክፈል ያላበቸው በመቶ ሁለት ፐርሰንት (2%) ስለመሆኑ የሚገልጽ መልስ አቅርቦዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ለመመልከት ሥልጣን እንደለው ቤቱም በአመልካች የሚታወቅ የራሳቸው ስለመሆኑ በሰነድ የተረጋገጠ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ

www.abyssinialaw.com

መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ከያዘ በኃላ የተጠሪ ምስክሮች በአመልከች እና ተጠሪ መካከል የድለላ ስራ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጣቸው የአመልከች ምስክሮች በአንፃሩ የራሱ ልጆች በመሆናቸው በተሸለ አግባብ አስረድቷል ለማለት እንደማይቻል የተጠሪ 2ኛ ምስክር የኖርዋ ኤምባሲ ሰራተኛ በመሆኑ ወገንተኝነት እንደሌለው እና ኤምባሲው እና አመልካች ያገናኛቸው ተጠሪ ስለመሆኑ ማስረዳቱን ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 686/2002 በ20/02/2006 ዓ/ም የታደሰ የድላለ ስራ ፈቃድ ያለቸው መሆኑ መረጋገጡ ክፍያ በተመለከተም በቃል ባደረጉት ስምምነት የአንድ ወር የቤት ኪራይ ክፍያ እንደሆነ ቤቱም በወር 20,000 ዶላር በመስማማት ለ20 ዓመት እንደተከራየ ኤምባሲው በበኩሉ 57,000 ብር መክፈሉ ሲታይ ከአመልከች ጋር ያገናኙዋቸው ተጠሪ መሆናቸውን እንደሚያሳይ በመግለጽ በግራ ቀኙ የቃል ውል ስምምነት መሰረት የአንድ ወር ኪራይ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር 378,400 ብር ይህ ክስ ከተመሰረተበት ከታህሳስ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከ9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልከች በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አለገኘም፡፡ የህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ይቅረብ በመባሉ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር አደርጓአል፡፡ አመልካች ሰፊ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን እንኳን ይዘቱ ከተጠሪ ጋር የድለላ ስምምነት እንዳልነበረ ይከፈል የተበለው የገንዘብ መጠንም ከፍተኛ በመሆኑ ሊቀንስ እንደሚገባ የሚጠይቅ ነው፡፡ ተጠሪ በበኩለቸው በአመልካች ጋር ስምምነት የነበራቸው ስለ መሆኑ ማስረዳታቸው የክፍያ መጠኑም አመልካች በ20 ዓመት ያገኙታል ተብሎ ከሚጠበቀው የኪራይ ገቢ አንጻር እና ተጠሪ ከሰጡት የድለላ አገልግሎት ሲታይ ተመጣጠኝ ነው በዝቷል ሊባል አይገባም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የደላለ አበል ክፍያ መጠን በተመለከተ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 59(3) አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ነው የሚል ነው፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የድለላ ስራ ግንኙነት መኖሩን ማረጋገጣቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአመልከች እና ተጠሪ ምስክሮች ቃል የሰነድ ማስረጃ መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች ክሱን በተሸለ አግባብ ማስረዳታቸውን ከድምዳሜ ላይ መደረሱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ባደረጉት ጥረት አመልካች አንድ ቪላ ቤት ለኖርዌይ ኤምባሲ ለ20 ዓመት ማከራየታቸው እና ክፍያም በወር

www.abyssinialaw.com

20,000 ዶላር ስለመሆኑ የከራከረ ጉዳይ አይደለም። የአሁኑ አመልካች ከተጠሪ ጋር የድለላ ስራ ግንኙነት የለንም በሚል በአጽንኦት የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ግንኙነት መኖሩን ነው። የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጠራት እና ማስረጃ ምዘና እና ድምዳሜ በዚህ ችሎት በድጋሚ የሚመዘን ሆኖ አልተገኘም። ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ሥልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 መሠረታዊ ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስ የምንገነዘበው ነው። በመሆኑም አመልከች በፍሬ ነገር ክርክር እና ማስረጃ ምዘና ላይ ያቀረቡት ክርክር በአጠሪ ችሎት በጭብጥ ከለመያዙ በተጨማሪ ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ውጪ በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር የህግ መሠረት የለውም ብለናል።

አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል የተወሰነው የአንድ ወር የቤት ኪራይ ሒሣብ ብር 378,400.00 ከ9% ወለድ ጋር በዝቷል የሚል ክርክር አቅርበዋል። አመልካች አከራከሪው ቤት ለ20 ዓመት በወር 20,000 ዶለር ለኖርዌይ ኤምባሲ ማከራየታቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም። የድለላ ኣባል ክፍያ መጠን በግራ ቀኑ ስምምነት የሚወሰን ሲሆን ፍርድ ቤቱ የድለላ አበል በዝቷል የሚል እምነት ከያዘ ሊቀንስ እንደሚችል በንግድ ህግ አንቀጽ 59 (3) ሥር ተመልክቷል። በመሰረቱ የድለላ አበል ክፍያ መጠን ከተሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን እንደሚገባ የሚታመን ቢሆንም ግራ ቀኙ የአበል ክፍያ መጠን ሲወሰኑ ታሰቢ ያደርጓቸው ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለበቸው። በተያዛው ጉዳዩ አከራካሪ የሆነው ጭብጥ ለተጠሪ የሚከፈለው የደለላ አበል ክፍያ መጠን በዝቷል? ወይስ አልበዛም? የሚል ነው። ከላይ እንተመለከተው ግራ ቀኙ ፈቅደው ያደረጉት ስምምነት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧዋል። አመልከች የድለላ አበል መጠን 2% መሆን አለበት በማለት የተከራከሩ ቢሆንከም የዚህ ክርክር ሕጋዊ መሰረት ማሳየት አልቻሉም። የቤት ኪራይ ውሉ ለ20 ዓመት የሚቆይ መሆኑ ሲታይ የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ በስምምነታቸው መሰረት የአንድ ወር ኪራይ ሒሳብ እንዲከፈል መወሰኑ የግራ ቀኑ ስምምነትና አጠቃላይ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የወሰነው መሆኑን ከመቀበል ውጭ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለመሆኑ የሚያሰይ ነገር አልቀረበም። የቤት ኪራይ ውል ለ20 ዓመት መደረጉን በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ በአመልከች እና ተጠሪም የድላለ ስራ ስምምነት መኖሩን የስር ፍ/ቤት በተቀበለበት ሁኔታ የድለላ አበል ክፍያ መጠን በዝቷል ወይም አንሰዋል በሚል በመጠኑ ላይ የሚደረገው ክርክር አጠቃላይ ሁኔታዎች መመልከት የሚጠይቅ እንጂ አንድ ወጥ መስፈርት መሰረት ተደረጎ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም። ይህ ከሆነ ደግሞ በድለላ አበል መጠን ላይ በሚደረገው ክርክር እንደጉዳዩ ዓይነት እና የተሰጠው አገልግሎት እየተገናዘበ የሚወስን ከመሆኑ አንፃር የስር ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም። በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የድለላ ስምምነት

www.abyssinialaw.com

መኖሩን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጦ ተጠሪ ለሰጡት አገልግሎት የአንድ ወር ኪራይ ሒሰብ 378,4000.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፈለቸው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን አያሰይም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 35650 በ21/02/2007 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 162863 በ15/05/2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች እና ተጠሪ የድለላ ስራ ስምምነት መኖሩን ተረጋግጦ የቤቱ የአንድ ወር ኪራይ ብር 378,400.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፈል መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ፍ/ቤት መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡